

# ያኮረፉ ምድሮች

## (ወለጋ እና ጎጃም)

ተስፋዬ ደመላሽ ሲሳይ /MSC/

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ያኮረፉ ምድሮች

(ወለጋ እና ጎጃም)

ተስፋዬ ደመላሽ ሲሳይ /Msc/

ሸወርቅባ ማተሚያ ቤት
2009 ዓ.ም

- ጎጃምና ጎንደር ኢትዮጵያን የተቀላቀሉት መጨረሻ ላይ ከሐረር በኋላ ነው (ሁሉም ብሄረሰቦች ይቀድሟቸዋል) ፡፡
- እስከ አሁን ድረስ ቤተመንግስት የገባ (የነገሰ) ብቸኛ የጎንደር ሰው አፄ ቴዎድሮስ ሲሆን እሱም የጁዎችን ተጠግቶ ነው (ጎንደር ቤተመንግስት ውስጥ የነገሰ የጎንደር ሰው አፄ ቴዎድሮስ ብቻ ነው) ፡፡ እስከ አሁን ድረስ ቤተመንግስት የገባ የጎጃም ሰው የለም ፡፡
- ጎንደር ለዋና መቀመጫነት የተመረጠችበት ምክንያት ምንድን ነበር? (ሸዋዎች ቤተመንግስታቸውን ከደብረ ብረሃን ወደ ጎንደር የቀየሩበት ምክንያት ምንድን ነበር?) ፡፡
- ሰሜን ሸዋ ምንድን ነው? /በስተ ሰሜን የከሚሴ ኦሮሞዎች የሚያዋስኑት ሲሆን በስተደቡብ የሸዋ ኦሮሞዎች ያዋስኑታል/ ፡፡
- ወሎ፣ ጎንደርና ጎጃም እንደት አማርኛ (አረብኛ) ተናጋሪ ሆኑ? /ሸዋ፣ ላስታና የጁ/ ፡፡
- የላስታ ላሊበላ አካባቢ ህዝቦች አገዎች ናቸው ፡፡ በላስታ (ላሊበላ)ና በደብረ ታቦር መካከል ያለው እርቀት ከ 350 ኪ.ሜ በላይ ሲሆን በላስታ (ላሊበላ)ና በወልዲያ መካከል ያለው እርቀት ግን 100 ኪ.ሜ አይሞላም ፡፡
- ግማሹ የወሎ ህዝብ ሙስሊም የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? /ግሸን/ ፡፡
- አባ ኮስትር በላይ ዘለቀ ማን ነው? /ልጅ እያሱ/ ፡፡
- የኢትዮጵያ ህዝቦች የዘር ግንድ አንድ ነው ወይስ ይለያያል?
- ወሎ የሁሉም ብሄረሰቦች ድብልቅ (collection)ነው፣ ሰ/ሸዋ የወሎ አካል ነው (ሰ/ሸዋ ከደብረ ብረሃን ጫጫ ከተማ እስከ ከሚሴ ያለውን ቦታ ይሸፍናል) ፡፡

የኢትዮጵያ አፈጣጠር (የአፄ ሚኒሊክ ዘመቻዎች ቅደም ተከተል)

- 1ኛ. የሸዋና የደቡብ ዘመቻ
- 2ኛ. የኦሮምያ (የጊቤና የከፋ) ዘመቻ
- 3ኛ. የአሩሲ ዘመቻ
- 4ኛ. የሐረር ዘመቻ
- 5ኛ. የጎንደር፣ የጎጃምና የትግራይ ዘመቻ
  /በትግሬው አፄ ዮሃንስ ስር ነበሩ/
- 6ኛ. የወላይታ ዘመቻ.

ከላይ እንደምናየው፣ የኢትዮጵያ አፈጣጠር ማለት የሸዋ የመስፋፋት ሂደት ማለት ነው ፡፡

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ማዉጫ

መግቢያ 8

ምዕራፍ አንድ 13

የኢትዮጵያ ወሳኝ ታሪካዊ ሚስጥሮች 13

ሰንጠረዣዊ የውርስ ማሳያ 16

ወሎ የሚባሉት እነማን ናቸዉ? 46

የወፋ ዉጊያ 58

የውሀ ሽያጭ ስራ 64

ምዕራፍ ሁለት 74

ዛግዌ በላስታ/መስራች ወሎ ላስታ/ 74

የአፄ ላሊበላ ዘመነ መንግስትስት (ከ1157-1197ዓ.ም) 77

የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት አመሰራረት የአፄ ነአኩቶለአብ ዘመነ መንግስት (ከ1197-1237 ዓ.ም) 80

ምዕራፍ ሦስት 85

ሰለሞናዊ በሸዋ /መስራች ወሎ ሸዋ/ 85

ምዕራፍ አራት 100

ሰለሞናዊ በጎንደር /መስራች ወሎ ሸዋ/ 100

ምዕራፍ አምስት 108

ዘመነ መሣፍንት (ዘመነ የጁ) በጎንደር፣ ከትልቁ ራስ አሊ እስከ ትንሹ ራስ አሊ ልጅ እቴጌ ተዋበች (ከ1777-1860) 108

እቴጌ ተዋበችና ካሳ ሀይሉ /አጼ ቴዎድሮስ 2ኛ/ 116

አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ዋግሹም ጎበዜ/ ከ1860-1863 ዓ.ም 134

ምዕራፍ ስድስት 139
አፄ ምኒሊክ 2ኛ (ከ1882-1906) 139
የኢትዮጵያ አፈጣጠር (የወሎ የመስፋፋት ሂደት) 143
የሸዋና የደቡብ ዘመቻ፡ - 143
የኦሮሚያ ዘመቻ፡ - 143
የአሩሲ ዘመቻ ፡ - 149
የንጉስ ሚኒሊክ እና የእቴጌ ጣይቱ መገናኘት 158
የአዲስ አበባ ከተማ መቆርቆር 160
የሐረር ዘመቻ ፡ - 160
የጎንደር፣ የጎጃምና የትግራይ ዘመቻ ፡ - 163
የትግራይ ዘመቻ ፡ - 165
የወላይታ ዘመቻ ፡ - 165
የአድዋ ዘመቻ 167
የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ 192
1. ነገደ ኦሪት 192
2. ነገደ ካም /ኩሽ/ 193
3. ነገደ ሴም /አጋዚያን/ 195
4. ነገደ እስራኤል/ቤተ እስራኤል/ 206
ብሔረ ትግሬ 208
ብሔረ ኦሮሞ 208
ብሔረ ወላይታ /እናሪያ/ 211
ብሔረ ጉራጌ 212
ብሔረ አማራ 212

ያኮረፉ ምድሮች /ወለጋና ጎጃም/ 214
ምዕራፍ ሰባት 222
ልጅ እያሱ (ከ1906-1909) 222
ንግስት ዘዉዲቱ (ከ1909-1922 ዓ.ም) 233
ምዕራፍ ስምንት 235
አፄ ኃይለስላሴ (ከ1923-1966) 235
ማኑፋክቸሪንግ 251
ዋና ዋና ዋቢ መጻህፍት 270

# መግቢያ

የሰዉ ልጆች በተለይ ነጮች በተፈጥሯቸዉ ታሪካቸዉን ማወቅ ይፈልጋሉ ። ታሪክ ማለት ማንነት ማለት ነዉ ። የሰዉ ልጆች አመጋገባቸዉ፣ አለባበሳቸዉ፣ ቋንቋቸዉ /አነጋገራቸዉ/፣ እምነታቸዉ፣ ኪነጥበባቸዉ /አዘፋፈናቸዉ/ …ወዘተ ከፊተኛዉ ትዉልድ /ከታሪክ/ የመጣ ነዉ ። ትዉልድ ከታሪኩ መማር ይችላል፤ የፊተኛዉን ትዉልድ ስኬትና ስህተት ገምግሞ የአሁኑን ያስተካክላል፣ አስደናቂና ሳቢ ታሪክ ካለም ከታሪክ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል ።

በአለም ላይ የራሳቸዉ የሆነ ታሪክ ያላቸዉ ሀገሮች እጅግ ዉስን ናቸዉ ። ከነዚህም ዉስጥ አንዷ ኢትዮጵያ(ወሎ) ናት /ሸዋ፣ የጁ፣ አገውና ወረሂመኖ/ ። ወሎ የጥቁሮች ምድር ከመሆኗ አንፃር ታሪኮቿም ከአዉሮፓዊያኑም የበለጠ አስደናቂና ሳቢ ናቸዉ ። የወሎ ታሪክ በቴክኖሎጂ /በጦር መሳሪያ ብልጫ/ የመጣ ሳይሆን የወሎ ጀግኖች ህይወት /ነፍስ/ ተከፍሎ የተገኘ ነዉ ። ስለሆነም ከአስደናቂነቱ አንፃር በአለም የመጀመሪያዉን ደረጃ ይይዛል ።

የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የወሎ ታሪክ ማለት ነው /ሸዋ፣ አገው፣ የጁ፣ ወረሂመኖ /፤ ኢትዮጵያና አማራ ራሳቸዉ የወሎ ስሪት ናቸዉ ። ወሎ ኢትዮጵያን ሲፈጥር /ሀገር ሲያሰፋ/ ጎጃምና ጎንደር በትግሬው አጼ ዮሃንስ ስር ስለነበሩ አገር የማቅናት /የማስፋት/ ጦርነት ላይ አልተሳተፉም ነበር ። ጎጃምና ጎንደር ኢትዮጵያን የተቀላቀሉት መጨረሻ ላይ ነው /ከሁሉም ብሄረሰቦች በኋላ ነው/ ። የጎንደር ቤተመንግስትም ውስጥ መንገስ የቻለ የጎንደር ሰው አፄ ቴዎድሮስ ብቻ ነው /አጎቱ ቤተመንግስት ውስጥ ስላስቀጠረው፣ ጥሩ አገልጋይ በመሆን እየተሾመ፣ እየተሾመ መጥቶ ነው፣ የጦር አዛዥ ሆኖ እስከ መንገስ ድረስ የደረሰው / ። በአድዋ ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያ ካሰለፈችዉ 73 ሺ ሰራዊት ዉስጥ ከ67 ሺ በላይ የሚሆነዉን ሰራዊት ያመጡት የወሎ ባላባቶች ነበሩ፣ ሌሎቹ ባላባቶች ቅርብ ጊዜ የተቀላቀሉ ስለነበሩ በአጠቃላይ 6ሺ ሰራዊት ብቻ ነበር ያዋጡት ። በአምባላጌዉና በመቀሌዉ ጦርነት ጊዜ በኢትዮጵያ በኩል የተሰለፉት የወሎ ባላባቶች ብቻ ነበሩ /መረጃ ከመስጠት አንጻር ብቻ የትግሬዉ ራስ መንገሻ ተሳትፏል/ ። አማራም የወሎ ፍጡር ነዉ ። አማርኛ ቋንቋ ከዛግዌ /ዘ-አገው/ በፊት ያልነበረና ዛግዌ ከሁሉም ብሄረሰቦች

አውጣጥቶ የሰበሰባቸው ወታደሮች የፈጠሩት የአራዳ ቋንቋ ነው ። ስለሆነም የአማራ ብሄር እድሜ ከላስታ ገዳማት እድሜ ያንሳል ማለት ነው /የላስታ ገዳማትንም የገነባቸው ዛግዌ ነው/ ። ከአፄ ዮሃንስ /ትግራይ/፣ ከግራኝ አህመድ /ሐረር/ና ከመለስ ዜናዊ /ትግራይ/ ዉጭ ያሉት የኢትዮጵያ ነገስታት በሙሉ የወሎ ሰዎች ናቸዉ /የአፄ ቴዎድሮን ጉዳይ እናየዋለን/ ። ሰሜን ሸዋ የወሎ አካል ነዉ፣ ሰሜን ሸዋ ማለት ከደብረብርሃን ጫጫ ከተማ ጀምሮ እስከ ከሚሴ ያለዉ ቦታ ነዉ፤ በአንድ አቅጣጫ /በሳይንት አቅጣጫ/ ከከሚሴም ያልፋል ።

እናም አፍሪካዊያን ሁሉም ታሪካቸዉ ያለዉ እዚሁ ወሎ ዉስጥ ነዉ ። የአድዋ ድል፣ የጥቁሮች ቁጥር አንድ ቅርስ ላሊበላ፣ የአለማችን ትልቁ ሰርግ /የወረኢሉዉ ሰርግ/፣ የአለማችን ምቹ እስር ቤት /የግሸን አምባ እስር ቤት/፣ የአፍሪካ ትልቁ የሐይማኖት ጉባኤ /የቦሩ ሜዳዉ የሐይማኖት ጉባኤ፣ የጎንደር ቤተመንግስት /አፄ ፋሲል የወሎ ሰው ነው/ … ወዘተ ሁሉም የወሎ ታሪኮች ናቸዉ ።

ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ይህን የወሎ ጀግኖች ነፍስ እየተከፈለ የተገኘ እጅግ ዉድ የታሪክ ሀብቷን መጠቀም አልቻለችም ። አፍሪካዊያን ወደ ታሪካቸዉ ሀገር ኢትዮጵያ ሲመጡ የህዝቡ ትኩረት ፍፁም ያልጠበቁት ሆኖ ያገኙታል ። ስለአድዋ፣ ስለ ላሊበላ ቅርስ፣ ስለ አፄ ምኒሊክ፣ ስለ እቴጌ ጣይቱ ወዘተ ሰምተዉ ይመጡና ኢትዮጵያ ሲደርሱ ግን ዘፋኞቹ /የሙዚቃ አርቲስቶቹ/ አብዛኞቹ የሚንጫጩት ስለ በላይ ዘለቀና ስለ አፄ ቴዎድሮስ ነዉ፤ እናም ግራ ታጋብተው ይመለሳሉ ። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ ሁሉም የምንሰማቸው ዘፈኖችና የምናነባቸው መፀሀፍቶች በጎጃምና በጎንደር ሰዎች የተሰሩ ስለሆኑ ነው ። ወሎዎቹ ቁጥራቸው ትንሽ ነው (ሰ/ሸዋ እንጂ የጁና ላስታ ወረዳዎች ናቸው) ፤ እናም ቁጥራቸው ትንሽ ስለሆነ በጎጃምና በጎንደር የኪነጥበብ ስራዎች ይዋጣሉ /dominate ይደረጋሉ/ ። በመሆኑም ጎብኝዎቹ ኢትዮጵያ ከደረሱ በኋላ በሚሰሙት ዘፈንና በሚያነቡት ነገር ሁሉ ግራ ተጋብተዉ ይመለሳሉ ። በነገራችን ላይ ጎብኚዎች የትም ሀገር ሲሄዱ መጀመሪያ የሚዩት የህዝቡን ትኩረት ነዉ ። ህዝቡ የጣለዉ ነገር የግድ ይወድቃል፤ እናም አፍሪካዉያን ኢትዮጵያ ከደረሱ በኋላ የታሪካቸዉን ጉዳይ እርግፍ አድርገዉ ይታዉታል ።

የበላይ ዘለቀን ያህል ስለአድዋ፣ ስለላሊበላ፣ ስለአፄ ምኒሊክ …ወዘተ ተዘፍኖ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ድረስ እኛን ተከትለዉ የአፍሪካ ታዋቂ ዘፋኞች /የሙዚቃ አርቲስቶች/ ለነዚህ ታሪኮቻቸዉ ማዜማቸዉ አይቀርም ነበር ፡፡ አንድ የአፍሪካ ታዋቂ ዘፋኝ ስለነዚህ ታሪኮች አዜመ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የቱሪዝም መዕከል ሆነች ማለት ነዉ ፡፡ አዲስ አበባ ዉስጥ “ሰባ ደረጃዉ” የሚባለዉን ቦታ የዚያዉ የሰፈሩ ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር ማንም አያዉቀዉም ነበር፤ አሁን ግን ቴድ አፍሮ አንድ ዜማ በመስራቱ ምክንያት “ሰባ ደረጃዉን” የማያዉቅ የአዲስ አበባ ነዋሪ የለም ፡፡ የአውራምባ ማህበረሰቦችም ታዋቂ የሆኑት አንድ ዜማ ከተሰራላቸው በኋላ ነው /የኪነጥበብ ተፅዕኖ ይህን ያህል ነዉ/ ፡፡

እናም ወሎ የሁሉም ብሄረሰቦች ድብልቅ /collection/ ከመሆኑ አንፃር የኢትዮጵያ ዘፋኞች /የሙዚቃ አርቲስቶች/ ስለታሪኮቻቸዉ ቢያዜሙ ኖሮ ኢትዮጵያም ከታሪኮቿ ተጠቃሚ መሆን ትችል ነበር ፡፡ ከብሄረሰቦቹ መፍዘዝም በተጨማሪ የወሎ ዘፋኞች ትኩረት ቁንጅና ላይ መሆኑ የኢትዮጵያን ታሪክ ከነአካቴው ተቀብሮ እንዲቀር አድርጎታል ፡፡ ጎጃምና ጎንደር ደግሞ እነኝህን አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢትዮጵያን ታሪክ ቆራርጠውና አድበስብሰው በመፃፍና ዜማዎችን በመስራት በላይ ዘለቀንና አፄ ቴዎድሮስን አጉልተው ማሳየት ችለዋል ፡፡ /ኢትዮጵያ ውስጥ፣ በተለይ አማራ ክልል ውስጥ ያለው ጥበት እጅግ አሳፋሪ ነው፤ ለምሳሌ ያህል ነጮችን እንዲናሸንፍ ያደረጉን አፄ ሚኒሊክ ናቸው /አድዋ/፣ ኢትዮጵያንም በዚህ መልኩ የፈጠሯት አፄ ሚኒሊክ ናቸው ወዘተ፤ ነገር ግን ሥማቸው እጅግ ገኖ ሰማይ ጥግ የደረሰው በላይ ዘለቀና አፄ ቴዎድሮስ ናቸው ፡፡ ይህ ሁኔታ ለጎጥ እንጂ ለሀገሪቱ የሚቆረቆር እንደሌለና ሀገሪቱ ባለቤት እንደሌላት ያሳያል /ከጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ታሪክ በሙሉ ጠፍቶ የበላይ ዘለቀና የአፄ ቴዎድሮስ መሆኑ አይቀርም/ ፡፡

ሌሎቹ ብሄረሰቦች ደግሞ ታሪካቸውን አያውቁም፤ ታሪክን አለማወቅ እጅግ አደገኛ ነገር ነው /ታሪኩን የማያውቅ ህዝብ እጅግ ብዙ ነገሮችን ያበላሻል/ ፡፡ ለምሳሌ ያህል ኦነግ፣ ኢትዮጵያን ማን እንደፈጠራት፣ ጎጃምና ጎንደር ወደ ኢትዮጵያ መቼ እንደመጡ፣ ጎጃምንና ጎንደርን ማን ዘምቶ ወደ ኢትዮጵያ እንዳመጣቸው /በነ ንጉስ ተክለሐይማኖት ላይ/፣ የጎንደር

ቤተመንግስት የማን እንደሆነ... ወዘተ አውቆ ቢሆን ኖሮ ኦሮሚያን የመገንጠልን ሀሳብ ፈፅሞ አያስበውም ነበር ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሁሉም ችግሮች የሚመነጩት ህዝቡ ታሪኩን ባለማወቁ ነው ማለት ነው /ታሪኩን የማያውቅ ህዝብ የያዘች ሀገር ጤነኛ አይደለችም ማለት ነው/ ። ስለሆነም ህዝቡ ታሪኩን እንዲያውቅ ማድረግ ማለት የሀገሪቱን በሽታ ከስሩ ነቅሎ መጣል ማለት ነው ። ከዚህ አንጻር ከኢትዮጵያ በተለይ ከወሎ ደራሲያን ብዙ ስራ ይጠበቃል ። ዘፋኞቹ ለመዝፈን የተፃፈ ምንጭ ያስፈልጋቸዋል ። የኢትዮጵያ ታሪክ በግልፅ ባለመቀመጡ ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይ ታሪኩን አያዉቅም ። እስከ አሁን ድረስ ተፅፎ የሚገኘዉ የኢትዮጵያ ታሪክ የተድበሰበሰና እየተቆረጠ የወጣለት ስለሆነ ታሪኩን አገጣጥሞ ለመረዳት በጣም ከባድ ነዉ፤ እናም ዘፋኞቹ ስለታሪኮቻቸው ለማዜም በጣም ይቸገራሉ ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ደራሲያን፣ የኢትዮጵያን ያልተድበሰበሰና ወጥ ታሪክ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል ።

እናም ይህን ችግር ለመቅረፍ የበኩሌን አስተዋፆ ማድረግ ስላለብኝ፣ ከብዙ ድካም በኋላ የኢትዮጵያን ወጥ ታሪክ በግልፅና እጅግ ባጭሩ ለማስቀመጥ ሞክሬለሁ ። ይች መፀሀፍ የኢትዮጵያን ታሪክ አጠቃላይ ሚስጥር ከማዉጣት አንፃር የመጀመሪዋ ስለሆነች፣ የኢትዮጵያ ህዝብም ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያን ያውቃታል ። መጸሀፍቷ ዉስጥ ስለተጻፉት ነገሮች፣ ቀድመን ምንጫቸዉን ስለምናስቀምጥ ማመሳከር ይቻላል ።

እናም ይች መፀሀፍ ቢያንስ አንድ እጅግ ትልቅ ስራ ትሰራለች፤ እሱም ይችን መፀሀፍ ያነበበ አንድ ሰዉ፣ ሌላ ማንኛዉንም መፀሀፍ ቢያነብ ልብ እያለና እያስተዋለ ስለሚያነብ ሁሉንም ነገር እራሱ በቀላሉ ይደርስበታል ። እደግመዋለሁ ይችን መፀሀፍ ያነበበ አንድ ሰዉ ሌላ ማንኛዉንም መፀሀፍ ቢያነብ ልብ እያለና እያስተዋለ ስለሚያነብ ሁሉንም ነገር እራሱ በቀላሉ ይደርስበታል ። እናም ኢትዮጵያን በማቅናትም ሆነ በንግስና ላይ ተሳትፎ ባልነበራቸው ሰዎች ኪነጥበብ /አርት/ ተታሎ /ተሸዶ/ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብም ለመጀመሪያ ጊዜ ሀገሩን ያውቃታል ።

እኛም ይችን መፀሀፍ ለመፃፍ በምንጎረጉርበትና መፀሀፍቶችን በምናገላብጥበት ወቅት ስለሀገራችን የነበረን መንፈስ /አመለካከት/ ተቀይሮ ሀገራችንን ፈፅሞ የማናውቃት ሌላ ሀገር ሆና አግኝተናታል ። ለወሎ /ሸዋ፣ የጁ፣ ላስታና ወረሂመኖ/ ያለኝ አድናቆትና አክብሮትም እየጨመረ ሄዶ ሰማይ

ጥግ ደረሶ አሁን የወሎ አድናቂ ከመሆን አልፎ የወሎ አምላኪ ሆኛለሁ ። ወደ ሰሜን በምሄድበት ወቅት እጅግ ያስጠሉኝ የነበሩት የደብረ ሲና ቁልቁለትና የኮምቦልቻ አቀበት አሁን የእኔ የአምልኮ ጣኦቶቼ ሆነዋል ። ወደ ሰሜን ስሄድ እጅግ ያስጠሉኝ የነበሩት የወሎ ገደሎችም አሁን ቤተክርስቲያን እየመሰሉ ይታዩኝ ጀምረዋል ። በአጠቃላይ አሁን አሁን ወደ ወሎ ስገባ ወደ ቤተመቅደስ የገባሁ አይነት የሚያስፈራ ስሜት ይሰማኝ ጀምሯል ። አባቢያን፤ መፀሀፍቷን አንብባችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ከእኔ ይልቅ እናንተ ይብስባባችሁና አብረን የወሎ አምላኪዎች እንሆናለን /ሸዋ፣ ላስታ፣ የጁ፣ ወረሂመኖ/ ።

ሌላዉ ነገር እዚች መፀሀፍ ላይ አይባልም የሚባል ነገር የለም ። አይባልም እያልን፣ መጥፎ መጥፎውን ታሪክ እየቆረጥን እየጣልን ጥሩ ጥሩዉን ብቻ የምንፅፍ ከሆነ፣ የጥሩ ታሪክ ባለቤቶችን ለይቶ ለማወቅ ያስቸግራል ። ይህ ደግሞ ታሪክ የሰራው ሌላ ተሸላሚዉ ሌላ እንዲሆን ያደርጋል /እምዬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፣ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ አይነት ዘፈኖችን ያስከትላል/ ። መጥፎ ታሪክ እየተቆረጠ የሚጣል ከሆነ ጥሩ ታሪክ ለመስራት የሚጨነቅ አይኖርም፤ የአሁኑም ትዉልድ ከመጀመሪያዉ ትዉልድ ስህተት ሊማር አይችልም ። ስለዚህ የአንድ የታሪክ ፀሀፊ ስነምግባር እንደሚያዘዉ፣ በእዚች መፀሀፍ ዉስጥ ታሪኩን እንደ ወረደ ፍርጥ እያደረግነዉ ነዉ የምናልፈዉ፤ ታሪኩን ከነ ጠማማዉ እያስቀመጥነዉ እናልፋለን ።

በተጨማሪም ደራሲዉ በብሄር አያምንም፤ ምክንያቱም በብሄር የምትዋደደዉ ሌሎች ብሄሮች ጋር አብረህ እስከ ኖርከባት ደቂቃ ድረስ ብቻ ነዉ ። የዉጮቹ ሱማሌዎች አንድ ብሄር ብቻ ናቸዉ፤ ነገር ግን ይኸዉ በጎሳ እየገጠሙ ሊያልቁ ነዉ ። የሩዋንዳ ጎሳዎች እልቂትም በዘግናኝነቱ በአለም የሚቀድመዉ የለም ። ደቡብና ሰሜን ኮሪያም አንድ ብሄር ብቻ ናቸዉ፤ ነገር ግን ይኸዉ ኢትዮጵያ ሳይቀር ሰላም አስከባሪ የላከችዉ ኮሪያ ነበር ። ስለዚህ አንድ ብሄር ብቻውን ሀገር አይሆንም ማለት ነው ። ከብሄር አንፃር ሲታይ በጎሳ /በጎጥ/ የሚፈጠረዉ ቡድን እጅግ አደገኛ ነዉ፤ ፈጥኖ ወደ እልቂት ይቀየራል ። ብሄር ሰፊ ስለሆነ በቀላሉ ለመዶለትና ለመምራት አይቻልም ። ብሄርን አቀናጅቶ መምራት የሚችል ቡድን ከተፈጠረም እጅግ ትልቅ ቡድን ስለሚሆን ወደ መንግስትነት ይቀየራል ። እናም ሁሉንም ነገር ስለሚቆጣጠረዉ እልቂት ሊከሰት አይችልም ። ብዙ ብሄሮች አብረው በሚኖሩባቸው ሀገሮች ውስጥ የእርስበርስ እልቂት ተከስቶ አያውቅም

/ናይጀሪያ/ ። ሌሎች ብሄሮች ጋር አብረህ ስትኖር እጅግ አደገኛ የሆነዉን ጎሳን /ጎጥን/ ብሄር ተጭኖ ይይዘዋል /እጅግ በርካታ ትንንሽ ቡድኖች እንዳይፈጠሩ ያደርጋቸዋል/ ። እናም በብሄር የምትዋደድ ስለሚመስልህ የጎጥ ፀብ /የጎጥ መቀሳሰር/ አይኖርም ።

ነገር ግን ሌላ ብሄር ከሌለና ስለብሄር የማይወራ ከሆነ ወሬዎች ሁሉ ስለጎጥ ይሆናሉ /የዚያኛው ጎጥ ሰዎች ስልጣን እየያዙብን ነው፣ የዚህኛው ጎጥ ሰዎች ስልጣን ይዘው አያውቁም ወዘተ አይነት ወሬዎችና ሎሎችም ቅሬታዎች እጅግ በርካታ በሆኑ ትንንሽ ጎጦች ውስጥ የዘወትር ወሬ ይሆናሉ/ ። ብሄር የሚባል ነገር ጠፉ ማለት ጎጥን ተጭኖ የዞት የነበረው ትልቅ ድንጋይ ተነሳለት ማለት ነዉ፤ እናም ወዳውኑ ይህ ጎጥ የሚባለዉ አደገኛ ነገር አፈሩን አራግፎ ይነሳና በጠባብ ቀለበት ውስጥ /በጠባብ ቦታ ውስጥ/ በርካታ ትንንሽ ጎጦች ይፋጠጣሉ ። ይህ ጠባብ ቀለበት /ጠባብ ቦታ/ ውስጥ ያለ ፍጥጫ አይቆይም በፍጥነት ወደ እልቂት ይቀየራል ። ስለዚህ በብሄር የምትዋደደዉ በሀገር መኖር /በሌሎች ብሄሮች አብሮ መኖር/ ላይ ነው ማለት ነው ። ሀገር ከሌለች /ሌሎች ብሔረሰቦች አብረው ከሌሉ/ በብሔር መዋደዱም የለም ማለት ነው /ሁሉም ነገር በሀገር መኖር ላይ የተመሰረተ ነው ማለት ነው/ ። እናም ከሌሎች ብሄሮች መለየት ይህን ያህል አደገኛ ነገር ከሆነ ብሄርተኝነት ያልገባቸዉ ሰዎች ጨዋታ ነዉ ማለት ነዉ ። ስለሆነም ደራሲዉ ከዚህ ብሄርተኝነት ከሚባለው ድንቁርና ነፃ ነው ።

አንባቢያን፣ አንዳንድ ከአንባቢው ጭንቅላት ውስጥ እንዳይጠፉ /save ለማድረግ/ የተፈለጉ ነገሮች ሊደገሙ ይችላሉ፤ ሆኖም ተጨማሪ ሀሳብ ሊኖራቸው ስለሚችል ሳትዘሉ ደግማችሁ ማንበብ ይኖርባችኋል ።

# ምዕራፍ አንድ

## የኢትዮጵያ ወሳኝ ታሪካዊ ሚስጥሮች

የአክሱም ታሪክ የትግሬዎች ታሪክ መሆኑ በሁሉም መፀሀፍቶች ላይ በግልፅ ስለተቀመጠ ቀስ ብለን ከአፄ ሚኒሊክ በኋላ የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ በሚለው ርዕስ የሴም ነገድ በሚለው ስር እናየዋለን ። አሁን

ከአክሱም ቀጥለው ስልጣን ከያዙት ከአገው ህዝቦች ማለትም ከዛግዌ /ዘ-አገው/ ስረወ መንግስት እንጀምራለን ። አገዎች በወሎ ከ/ሀገር፣ በላስታና ሰቆጣ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው ። ወደ ዘ-አገው /ዛግዌ/ ስረወ መንግስት ከመግባታችን በፊት ግን የኢትዮጵያን አጠቃላይ ታሪክ ከቀጣዩ ሰንጠረዥ እንመልከት ። ከቀጣዩ ሰኝጠረዥ እንደምናየው ከአፄ ዮሃንስ /ትግራይ/፣ ከግራኝ አህመድ /ሐረር/ና ከመለስ ዜናዊ /ትግራይ/ ዉጭ ያሉት የኢትዮጵያ ነገስታት በሙሉ የወሎ ሰዎች ናቸዉ፤ የአፄ ቴዎድሮስን ጉዳይ ከሰንጠረዡ በኋላ እናየዋለን ። ሰሜን ሸዋ የወሎ አካል ነዉ፣ ሰሜን ሸዋ ማለት ከደብረ ብርሃን ጫጫ ከተማ ጀምሮ እስከ ከሚሴ ያለዉ ቦታ ማለት ነዉ፣ በአንድ በኩል ከከሚሴም ያልፋል /ወደ ሳይንት አቅጣጫ ከከሚሴም ያልፋል/ ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ያልተዘፈነለትና የተረሳ ጀግና ካለ፣ እሱ ወሎ ነዉ /ሸዋ፣ የጁ፣ አገውና ወረሂመኖ ታሪክና ጀግና የረከሰባቸው የአፍሪካ ልዩ ቦታዎች ናቸው/ ።

ከቀጣዩ ሰንጠረዥ እንደምናየው፣ የኢትዩጵያ ታሪክ ማለት የሸዋ፣ የአገው /የላስታ/ና የየጁ ታሪክ ማለት ነዉ ። በሌላ አገላለፅ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የዛግዌ ስረወ መንግስት /አገው/፣ የሰለሞናዊ ስረዎ መንግስት /ሸዋ/ና የዘመነ መሳፍንት /የጁ/ ታሪክ ማለት ነው ። አሁንም በሌላ አገላለፅ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የመራተክለሐይማኖት ቤተሰቦች፣ የይኩኖ አምላክ ቤተሰቦች፣ የትልቁ ራስ አሊ ቤተሰቦችና የአፄ ሚኒሊክ ቤተሰቦች ታሪክ ማለት ነው ። በርካታ ህዝብ ስለ ዛግዌ እንጂ ስለ ሰለሞናዊ ስርወ መንግስትና ስለ ዘመነ መሳፍንት አያዉቅም ።

ስለ ሰለሞናዊ ስረወ መንግስት አመሰራረት፣ አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴል-ኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ያሰፈሩትና በዓለማየሁ አበበ የተተረጎመዉ መጸሀፍ ውስጥ ያለው ፅሁፍ ባጭሩ ሲቀመጥ "አባ ተክለሐይማኖትን /ተክልዬን/ ሁላችንም እናዉቃቸዋለን፤ በአካባቤችንም የተክለሐይማኖት ቤተክርስቲያን አይጠፋም ። እናም በአባ ተክለሐይማኖት አማላጅነት ምክንያት የላስታዉ አፄ ነአኩቶለአብ ስልጣናቸዉን አሸከራቸዉ ለነበረው፣ ለሸዋው ይኩኖአምላክ በማዉረሳቸዉ ምክንያት ሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ሰ/ ሸዋ ላይ ተመሰረተ ። አፄ ነአኩቶለዓብ ስልጣናቸዉን ለሸዋው ይኩኖአምላክ ያወረሱት በዉል ነበር

። ዉሉ ደግሞ የመጨረሻዉን የዛግዌ ንጉስ አፄ ይትባረክን በላስታ ዙፋን ላይ እንዲቀመጡ የሚያስችል ነበር” ። ስንደርስበት በአጼ ነአኩቶለአብ ስር በዝርዝር እናየዋለን ።

እናም ሸዋና ጎንደር ላይ በተከታታይ ስልጣናቸዉን ለልጆቻቸዉ እያወረሱ የነገሱት የዚሁ የሸዋው የይኩኖአምላክ ቤተሰቦችና የየጁው የትልቁ ራስ አሊ ቤተሰቦች ብቻ ናቸዉ፤ ብቻ ናቸዉ ። ሸዋዎች ዋና መቀመጫቸውን ከደብረ ብረሃን ወደ ጎንደር የቀየሩበት ምክንያት ደግሞ በዚያን ዘመን ጎንደር የረጅሙ ከምፅዋ እስከ ሱዳን የተዘረጋዉ የንግድ መስመር ማዕከል /center/ በመሆኗ ነበር /ከሸዋ በታች ያለው አገር የኢትዮጵያ አካል አልነበረም/ ። በወቅቱ በተለይ የባሪያ፣ የወርቅና የቡና ንግድ እያደገ ስለነበር ጎንደር ዉስጥ የሚኖረዉና የሚንቀሳቀሰዉ ህዝብ እየበዛ መጣ ። እናም ነገስታቱ ሁሉንም የንግድ እንቅስቃሴ በቅርበት ለመቆጣጠር ሲሉ ቤተመንግስታቸዉን ከሸዋ /ከደብረ ብረሃን/ ወደ ጎንደር መቀየር ግድ ሆነባቸዉ ። እናም ‘’የጎንደር ነገስታት’’ የሚባል ነገር የለም ማለት ነው ። አዲስ አበባ፣ ኦሮምያ ዉስጥ ስለተገኘች አዲስ አበባ ላይ የነገሱትን ነገስታት “የኦሮሞ ነገስታት” ማለት አይቻልም ። በተመሳሳይ ጎንደርም ላይ የነገሱትን ነገስታት ‘’የጎንደር ነገስታት’’ ማለት አይቻልም ። ጎንደር ቤተመንግስት ዉስጥ ነግሶ የሚያዎቅ የጎንደር ሰዉ የለም፣ የአፄ ቴዎድሮስንም ጉዳይ ከሰንጠረዡ ቀጥለን እናየዋለን ።

የጎንደር ቤተመንግስት ለ308 ዓመት ያህል መናገሻ ሆኖ ሲያገለግል፣ ለ234 ዓመት ያህል ጎንደር ቤ/ትን ነገሱበት ከሸዋ የሄዱት የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ነገስታት ሲሆኑ ቀሪዉን 74 ዓመት ያህል ደግሞ ጎንደር ቤ/ትን የነገሱበት የየጁ መሳፍንቶች ናቸው ። ከዚህ የላስታ፣ የሸዋና የየጁ /የኢትዮጵያ/ ታሪክ ውስጥ ጣልቃ የገቡት የትግሬው አፄ ዮሃንስና የሐረሩ ግራኝ አህመድ ብቻ ናቸው ። እንግዴህ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት ይኸው ነው፤ ቀጣዩ ሰንጠረዥ በጣም ግልፅ ያደርገዋል ።

/ሰንጠረዡ ውስጥ ከመራ ተክለሐይማኖት፣ ከትልቁ ራስ አሊ፣ ከአፄ ዮሃንስ፣ ከአፄ ተከተለጊዮርጊስ 2ኛ /ዋግሹም ጎበዜ/፣ ከአፄ ምኒሊክና ከአፄ ኃይለስላሴ ውጭ ያሉት ነገስታት በሙሉ የነገሱት ያለምንም ጦርነት በውርስ ብቻ ነው /ከአባት የሚወርደውን የንግስና ውርስ መቀበል ብቻ ነው/ ።

# ሰንጠረዣዊ የውርስ ማሳያ

እንግዴህ ከሰንጠረዡ እንደምናየው የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የ 4 ሰዎች ቤተሰቦች ታሪክ ብቻ ማለት ነዉ /አራቱም የወሎ ሰዎች ናቸው/ ። አራቱ ሰዎች ማለት መራ ተክለሐይማኖት፣ ይኩኖአምላክ፣ ትልቁ ራስ አሊና አፄ ሚኒሊክ ናቸው ።

የዛግዌ ስርወ መንግስት የነገስታት ዝርዝር፣ መስራች ወሎ ላስታ

| ተ.ቁ | የነገስታት ሥም | የአዉራሹ ሥም | ዝምድና | ዋና መቀመጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መራ ተክለሐይማኖት | በኃይል | በኃይል | ላስታ |
| 2 | ጠጠዉድም | መራ ተክለሐይማኖት | ልጅ | ላስታ |
| 3 | ጃን ስዩም | ጠጠዉድም | ልጅ | ላስታ |
| 4 | ግርማ ስዩም | ጃን ስዩም | ወንድም | ላስታ |
| 5 | መይራራ | ግርማ ስዩም | ልጅ | ላስታ |
| 6 | ሐርቤ 1ኛ | መይራራ | ወንድም | ላስታ |
| 7 | ይምርሐነ ክርስቶስ | ሐርቤ 1ኛ | ወንድም | ላስታ |
| 8 | ቅዱስ ሐርቤ 2ኛ | ይምርሐነ ክርስቶስ (ወንድ ልጅ የለዉም) | የወንድም ልጅ | ላስታ |
| 9 | ቅዱስ ላሊበላ | ቅዱስ ሐርቤ 2ኛ | ወንድም | ላስታ |
| 10 | ቅዱስ ነአኩቶለአብ | ቅዱስ ላሊበላ | የወንድም ልጅ | ላስታ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 11 | ይትባረክ | በስምምነቱ ዉል መሰረት | በዉሉ መሰረት | ላስታ |

| የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ነገስታት ዝርዝር፣መስራች ወሎ ሸዋ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ. ቁ | የነገስታት ሥም | አውራሽ | ዝምድና | ዋና መቀመጫ |
| 1 | ይኩኖአምላክ | ነአኩቶለአብ /ዛግዌ/ | አሽከር | ሸዋ |
| 2 | አግብአ ፅዮን | ይኩኖ አምላክ | ልጅ | ሸዋ |
| 3 | ፅንፈ አርእድ | አግብአ ፅዮን /ለ5ቱ ልጆቹ ተራበተራ/ | ልጅ | ሸዋ |
| 4 | ህዝበ አሰግድ | ፅንፈ አርእድ | ወንድም | ሸዋ |
| 5 | ቅድመ አሰግድ | ህዝበ አሰግድ | ወንድም | ሸዋ |
| 6 | ጃን አሰግድ | ቅድመ አሰግድ | ወንድም | ሸዋ |
| 7 | ሰብዓ አሰግድ | ጃን አሰግድ | ወንድም | ሸዋ |
| 8 | ዉድም አርዕድ | ሰብዓ አሰግድ/ልጅ አልነበረዉም/ | አጎት | ሸዋ |
| 9 | ዓምደ ፅዮን 1ኛ | ዉድም አርዕድ | ልጅ | ሸዋ |
| 10 | ሰይፈ አርዕድ | ዓምደ ፅዮን 1ኛ | ልጅ | ሸዋ |
| 11 | ዉድም አስፈሬ | ሰይፈ አርዕድ | ልጅ | ሸዋ |
| 12 | ዳዊት | ዉድም አስፈሬ | ወንድም | ሸዋ |
| 13 | ቴዎድሮስ 1ኛ | ዳዊት | ልጅ | ሸዋ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 14 | ይስሐቅ | ቴዎድሮስ 1ኛ | ወንድም | ሸዋ |
| 15 | እንድርያስ | ይስሐቅ | ልጅ | ሸዋ |
| 16 | ህዝበናኝ | እንድርያስ | ወድም | ሸዋ |
| 17 | በድልናኝ | ህዝበናኝ | ወንድም | ሸዋ |
| 18 | አምደእያሱ | በድልናኝ | ወንድም | ሸዋ |
| 19 | ዘርዓ ያዕቆብ | አምደእያሱ/ዳዊት/ | ወንድም | ሸዋ |
| 20 | በእደማርያም | ዘርዓ ያዕቆብ | ልጅ | ሸዋ |
| 21 | እስክንድር | በአደማርያም | ልጅ | ሸዋ |
| 22 | አምደ ፅዮን2ኛ | እስክንድር | ልጅ | ሸዋ |
| 23 | ናኦድ | አምደ ፅዮን 2ኛ | ወንድም | ሸዋ |
| 24 | ልብነድንግል ና ግራኝ አህመድ | ናኦድና ግራኝ በኃይል | ልጅና ግራኝ በኃይል | ልብነድንግል ሸዋና ግራኝ ጎጃም |
| 25 | ገላዉደወስና ግራኝ አህመድ | ልብነ ድንግልና ግራኝ በኃይል | ልጅና ግራኝ በኃይል | ገላውዲዎስ ሸዋና ግራኝ ጎጃም |
| 26 | ሚናስ | ገላዉድዎስ | ወንድም | ሸዋ |
| 27 | ሠርፀ ድንግል | ሚናስ | ልጅ | ጎንደር |
| 28 | ያዕቆብ | ሠርፀ ድንግል | ልጅ | ጎንደር |
| 29 | ዘድንግል | ያዕቆብ | ወንድም | ጎንደር |
| 30 | ሱስኒዮስ | ዘድንግል | ወንድም | ጎንደር |
| 31 | ፋሲል /የጎንደር ቤ/ን የገነባዉ/ | ሱስኒዮስ | ልጅ | ጎንደር |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 32 | ዮሐንስ 1ኛ | ፋሲል | ልጅ | ጎንደር |
| 33 | እያሱ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ልጅ | ጎንደር |
| 34 | ተ/ሐይማኖት | እያሱ 1ኛ | ልጅ | ጎንደር |
| 35 | ቴዎፍሎስ | ተክለሐይማኖት | ወንድም | ጎንደር |
| 36 | ዮስጦስ | ቴዎፍሎስ | ወንድም | ጎንደር |
| 37 | ዳዊት 3ኛ | ዮስጦስ | አጎት | ጎንደር |
| 38 | በካፋ | ዳዊት 3ኛ | ወንድም | ጎንደር |
| 39 | እያሱ 2ኛ | በካፋ | ልጅ | ጎንደር |
| 40 | ኢዮአስ | እያሱ 2ኛ | ልጅ | ጎንደር |
| 41 | ዮሐንስ 2ኛ | ኢዮአስ | ወንድም | ጎንደር |
| 42 | ተክለሐይማኖት 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ልጅ | ጎንደር |
| 43 | ሠለሞን | ተክለሐይማኖት 2ኛ | ወንድም | ጎንደር |
| 44 | ተክለጊዮርጊስ 1ኛ | ሠለሞን | ወንድም | ጎንደር |

ዘመነ መሳፍንት/ዘመነ የጁ/፣ መስራች ወሎ የጁ /ወልዲያ/

| ተ. ቁ | የነገስታት ሥም | አውራሽ | ዝምድና | ዋና መቀመጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ትልቁ ራስ አሊ /ከክርስቲያን ቤተሰብ ነው የተወለዱት/ | በኃይል | በኃል | ጎንደር |
| 2 | የትልቁ ራስ አሊ ወንድም ራስ አሊጋዝ | ትልቁ ራስ አሊ | ወንድ ም | ጎንደር |
| 3 | የትልቁ ራስ አሊ የእናቱ ወንድሞች ራስ አስራትና ራስ ወ/ገብርኤል | ራስ አሊጋዝ | ወንድ ም | ጎንደር |
| 4 | የትልቁ ራስ አሊ ሌላ ወንድም ራስ ጉግሳ /የደብረታቦር ከተማ መስራች/ | በከፊል ራስ ወ/ገብርኤል እና በከፊል በኃይል | አጎት | ጎንደር |
| 5 | የራስ ጉግሳ ልጅ ራስ ይማም | ራስ ጉግሳ | ልጅ | ጎንደር |
| 6 | የራስ ጉግሳ ሌላ ልጅ ራስ ማርዬና ራስ ዱሪ | ራስ ይማም | ወንድ ም | ጎንደር |
| 7 | የእቴጌ መነንና የራስ ማርዬ ልጅ ትንሹ ራስ አሊ | ራስ ማርዬ | ልጅ | ጎንደር |
| 8 | የትንሹ ራስ አሊ ልጅ እቴጌ ተዋበች /የአጼ ቴዎድሮስ ሚስት/ | ትንሹ ራስ አሊ /እቴጌ መነን/ | ልጅ | ጎንደር |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ /ዋግ ሹም ስዩም ጎበዜ/፣ ወሎ ሰቆጣ | በኃይል /ተዋበች ከሞተች በኋላ ቴድን ቤተመንግስቱንና ግዛቱን ያስለቀቀዉ/ | በኃይል | ጎንደር |
| 1 | አፄ ዮሃንስ | በኃይል | በኃይል | አድዋ በኋ ላ መቀሌ |

| በየጁዎች ስልጣን ተነጥቆ የነበረው ሰለሞናዊ ስርወ መንግስት እንደገና በአፄ ሚኒሊክ አማካኝነት ስልጣን ያዘ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ ቁ | የነገስታት ሥም | አውራሽ | ዝምድና | ዋና መቀመጫ |
| 1 | አፄ ምኒሊክ | ልዕልት ወርቂት የመነሻ ሰራዊት በመስጠት | በኃይል | አዲስ አበባ |
| 2 | ልጅ እያሱ | አፄ ሚኒሊክ | የልጅ ልጅ | አዲስ አበባ |
| 3 | ንግስት ዘውዲቱ | አፄ ሚኒሊክ | ልጅ | አዲስ አበባ |
| 4 | አፄ ኃይለስላሴ | አፄ ሚኒሊክ /በጥቆማ ምርጫ/ | አጎት | አዲስ አበባ |

የአፄ ቴዎድሮስና የበላይ ዘለቀ ታሪኮችም ሳይቀር የወሎ ታሪኮች ናቸዉ፤ ከዚህ ቀጥለን እናያቸዋለን ።

እንግዴህ ከሰንጠረዡ እንዳየነው ከአፄ ዮሃንስ /ትግራይ/ና ከግራኝ አህመድ /ሐረር/ ዉጭ ያሉት ነገስታት በሙሉ የወሎ ሰዎች ናቸዉ ። ቀደም ሲል እንደጠቀስነዉ፣ ኢትዮጵያና አማራ ራሳቸዉ የወሎ ስሪት ናቸዉ ። አንዳንዶች ኢትዮጵያን የፈጠሯት /ኢትዮጵያን ያቀኗት/ ጎንደርና ጎጃም

ይመስሏቸዋል ፤ እጅግ ስህተት ነው /የሉበትም/ ። ጎጃምና ጎንደር ኢትዮጵያን የተቀላቀሉት መጨረሻ ላይ ነው /ከሁሉም ብሄረሰቦች በኋላ ነው/ ። ወሎ ኢትዮጵያን ሲፈጥር /ሀገር ሲያቀና/ ጎጃምና ጎንደር በትግሬው አጼ ዮሃንስ ስር ስለነበሩ አገር የማቅናት ጦርነት ላይ አልተሳተፉም /በአፄ ዮሃንስ ሹመኞች ስር ነበሩ/ ። እንዳዉም ጎጃሞች ለሀገር ፈጠራዉ እጅግ ትልቅ እንቅፋት ነበሩ፤ በአፄ ዮሐንስ እየተገፉ ከወሎ ጋር ሦስት ጦርነቶችን አድርገዉ ነበር ። ሁለቱ ጦርነቶች በተለይ እጅግ ዘግናኝና አያሌ /እጅግ ብዙ/ ጎጃሜዎች ያለቁባቸው ነበሩ፤ በአፄ ምኒሊክ ስር ያለውን አንብበን ስንጨርስ በጣም ግልፅ ይሆናል ። በአድዋ ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያ ካሰለፈችዉ 73 ሺ ሰራዊት ዉስጥ ከ67 ሺ በላይ የሚሆነዉ ሰራዊት የወሎ ሰራዊት ነበር /የወሎ ባላባቶች ያመጡት ሰራዊት ነበር/፣ ሌሎቹ ባላባቶች ቅርብ ጊዜ ኢትዮጵያን የተቀላቀሉ ስለነበሩ በድምሩ 6ሺ ሰራዊት ብቻ ነበር ያዋጡት ። በአምባላጌዉና በመቀሌዉ ጦርነት ጊዜ በኢትዮጵያ በኩል የተሰለፉት የወሎ ባላባቶች ብቻ ነበሩ /መረጃ ከመስጠት አንጻር ብቻ የትግሬዉ ራስ መንገሻ ተሳትፏል/ ፤ በአፄ ምኒሊክ ስር በዝርዝር ተቀምጠዋል ።

ከአፄ ሚኒሊክ በኋላ፣ የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ በሚለው ርዕስ ስር እንደምናየው፣ አማራ ብሔርም የወሎ ፍጡር ነው /ሸዋ፣ የጁ፣ አገው፣ ወረሂመኖ/ ። ከመነሻውም ጎጃምንና ጎንደርን ይህንን የአሁኑን ተፈጥሯቸውን ያስያዛቸው ማለትም አማርኛ ተናጋሪና ክርስቲያን እንዲሆኑ ያደረጋቸው አገው /ዛግዌ/ መሆኑን ቀጥለን ከአፄ ሚኒሊክ በኋላ የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ በሚለው ርዕስ ስር እናየዋለን ። እናም ለምሳሌ ያህል ወሎ ሙሉ በሙሉ ሙስሊም ሆኖ ቢሆን ኖሮ አገው ሙስሊም ነበር ማለት ነው፤ ስለዚህ ጎንደርና ጎጃም ከመነሻውም ሙሉ በሙሉ ሙስሊም ነበሩ ማለት ነው ። ከአገው ቀጥለው ስልጣን የያዙትም ሸዋዎች ናቸው፤ ወሎ ሙሉ በሙሉ ሙስሊም ሆኖ ቢሆን ኖሮ ሰ/ሸዋም ሙስሊም ነበር ማለት ነው ። ሰ/ሸዋ ሙስሊም ሆነ ማለት

ደግሞ ጎጃምና ጎንደር አገው /ዛግዌ/ ያስያዛቸውን ተፈጥሯቸውን ይዘው አይቀጥሉም ነበር ማለት ነው ። ከሸዋም ቀጥለው ለ74 አመት ያህል ስልጣን የያዙት የጁዎች ናቸው፤ የየጁ ህዝብ አብዛኛው ክርስቲያን ባይሆን ኖሮ ጎጃምና ጎንደር ሸዋ ያስያዛቸውን ተፈጥሯቸውን ይዘው አይቀጥሉም ነበር ማለት ነው ። ስለዚህ ጎጃምንና ጎንደርን ይህንን የአሁኑን ተፈጥሯቸውን ያስያዟቸው

የወሎ ክርስቲያኖች ናቸው ማለት ነው ። በሌላ መልኩም ብናየው ጎጃምና ጎንደር ወደ ንግስና መጥተው የማያውቁ ከሆነና አፄ ቴዎድሮስም የነገሰው የጁን ተጠግቶ /ከራስ አሊ ጋር ተጋብቶ/ ከሆነ፣ አማራን ይህንን የአሁኑን ተፈጥሮውን እንዲይዝ ያደረገው ወሎ ነው ማለት ነው ። አሁንም በሌላ አገላለፅ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የአገው /ዛግዌ/፣ የሸዋ /ሰለሞናዊ/ና የየጁ /ዘመነ መሳፍንት/ ታሪክ ማለት ከሆነ አማራን ይህንን የአሁኑን ተፈጥሮውን እንድይዝ ያደረገው ወሎ ነው ማለት ነው ። አሁንም በሌላ አገላለፅ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የመራተክለሐይማኖት ቤተሰቦች፣ የይኩኖአምላክ ቤተሰቦች፣ የትልቁ ራስ አሊ ቤተሰቦችና የአፄ ሚኒሊክ ቤተሰቦች ታሪክ ማለት ከሆነ አማራን ይህን ያሁኑን ተፈጥሮውን ያሲያዘው ወሎ ነው ማለት ነው / ሸዋ፣ የጁና አገው /ላስታ/ ናቸው ማለት ነው ።

/ሸዋ፣ የጁ፣ አገው፣ ወረሂመኖ/ ወሎ ባይኖርም ኢትዮጵያ አንዳንድ የሀገር ዉስጥ ታሪኮችን አታጣም /አፄ ዮሃንስና ግራኝ አህመድ/፤ ነገር ግን ወሎ ባይኖር ኖሮ አማራና አፍሪካ ታሪክ አይኖራቸዉም ነበር ። አማራ ክልል ዉስጥ ወሎ ተቦጭቃ ብትወጣ ኦሮምያም ሆነ ደቡብ ክልሎች ከአማራ የተሻለ ታሪክ ይኖራቸዋል ። ኦሮምያ የአባ ጅፋርን ታሪክ ሊጠቅስ ይችላል፣ ደቡብም የጦናን ታሪክ ሊጠቅስ ይችላል ። አማራ ዉስጥ ግን ወሎ ተቦጭቃ ከወጣች የሚጠቀስ ታሪክ አይኖርም ። የበላይ ዘለቀና የአፄ ቴዎድሮስ ታሪኮችም ሳይቀር የወሎ ታሪኮች ናቸዉ ።

ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ፡ - አባቱ ባሻ ዘለቀ ላቀዉ ይባላሉ፤ ባሻ ዘለቀ ላቀዉ የልጅ እያሱ አንጋች ነበሩ ። እናቱ እመት ጣይቱ ሐሰኔ ይባላሉ ። የበላይ ዘለቀ አባትና እናት የወሎ ቦረና ሳይንት አዉራጃ ሰዎች ናቸዉ ። በላይ ዘለቀ በወሎ ክ/ሀገር፣ ቦረና ሣይንት አዉራጃ፣ በጫቃታ ወረዳ፣ በጅሩ ቀበሌ፣ ጎጣ በተባለ መንደር፣ ነዉ ተወልደዉ ያደጉት ።

ልጅ እያሱ ከስልጣን ከወረዱ በኋላ ባሻ ዘለቀ ላቀዉ ወደ ተወለዱበት ቦረና ሳይንት ተመልሰዉ ቤተሰቦቻቸዉ ጋር እየኖሩ ሳለ በእጃቸዉ የሰዉ ህይወት አለፈባቸዉ ። እናም በቀል እንዳይደርስባቸዉና በመንግስትም እንዳይያዙ፣ በሌሊት ጨረቃ ሁለቱን ልጆቻቸዉን /በላይንና እጅጉን/ ይዘዉ ወደ አባይ ሸለቆ ጫካ ሸፈቱ ። አባይ ሸለቆም ዉስጥ በሽፍቶች ይዘወተር ወደ ነበረዉ “የለምጨን” ጫካ ዉስጥ ገቡ ።

“የለምጨን” ጫካ በጎጃም ክ/ሀገር፣ በብቸና አዉራጃ፣ በእነማይ ወረዳ፣ በአባይ ሸለቆ ዉስጥ የሚገኝ፣ ከላይ ዳገት ከታች ገደል ሆኖ፣ በቀይትና ጢጋ ወንዞች የተከበበ፣ በረሀና ሰዋራ ሥፍራ ነዉ ፡፡ ባሻ ዘለቀም በዚሁ በለምጨን ጫካ ውስጥ ተደብቀው ልጆቻቸዉንና እራሳቸዉን በሽፍትነት ስራ ማስተዳደር ጀመሩ ፡፡ ሆኖም ግን የአካባቢዉ ሰዎች አይተዋቸዉ ኖሮ፣ አዳዲስ ዘራፊ ሌቦች ከወሎ መጥተዋል ብለዉ በወቅቱ “ሌባ አዲን” እየተባሉ ይጠሩ ለነበሩት ሹመኞች ጠቆሙ ፡፡ የአካባቢዉ የሌባ አዲን ሹም የነበሩት ፊታዉራሪ እንዳለም፣ ሚኒሻዎቻቸዉን በማዘዝ፣ በድንገት ባሻ ዘለቀን አስከብበዉ፣ እጅ እንዲሰጡ ጠየቋቸዉ ፡፡ ባሻ ዘለቀም እጅ አልሰጥም በሚል፣ ተኩስ ከፍተዉ፣ ብዙ ሰዉ ካለቀ በኋላ እሳቸዉም ተገደሉ ፡፡

ከዚህ በኋላ በላይ ወንድሙን ይዞ እየተጠነቀቀ አንደዬ ቦረና ሌላ ጊዜ አባይ ሸለቆ እያለ እየኖረ ሳለ፣ የጣሊያንን መምጣት ሰማ ፡፡ የጣሊያንን መምጣት እንደሰማ ቦረና ሳይንት እየሄደ አብሮ አደጎቹን እየሰበሰበ “መሳሪያችሁን ለጣሊያን ማስረከብ የለባችሁም፣ የጣሊያን ባሪያ መሆን የለብንም” እያለ ማሳመን ጀመረ ፡ በመጨረሻም ቁጥራቸዉ ወደ 30 የሚደርሱ የአንድ አያት ልጆች ማለትም የእናቱ አባት የሐሰኔ ወዳጆ ተወላጆችና ሌሎችም ለመጀመሪያ ጊዜ ከበላይ ዘለቀ ጋር ተቀላቅለዉ ለምጨን ጫካ ዉስጥ ገቡ ፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላም አጎቱ ለገሠ ሐሰኔ ቦረና ሣይንት

አካባቢ የሰበሰባቸዉን ወደ 100 የሚሆኑ ልጆች ይዞ በላይን ተቀላቀለ ፡፡ እናም የበላይ ዘለቀ ትግል ወደ 130 በሚሆኑ የወሎ ልጆች ተጀመረ ፡፡

የጎጃም ዘፋኞች/የሙዚቃ አርቲስቶች/ በላይ አባይ ሸለቆ ለምጨን ጫካ ዉስጥ ነበር በሚል፣ በዘፈን ጎጃሜ አድርገዉታል ፡፡ እንደዚያ ከሆነ አፄ ቴዎድሮስም፣ ከእንግሊዞች መምጣት በፊት ዋግሹም ጎበዜ /አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ጎንደር ቤተመንግስትንና መላውን ግዛቱን ሲያስለቅቀው ወደ ደቡብ ወሎ መቅደላ ሸሽቶ፣ የእንግሊዞች መምጣት ድረስ እዚያው ወሎ መቅደላ ውስጥ ነበር ለ4 ዓመት ያህል መሽጎ የኖረው፣ የሞተውም እዚያው ወሎ መቅደላ ውስጥ ነው ፡፡ በላይ ዘለቀና ሌሎች ሽፍቶች ሁሉ ግን ወደ አባይ ሸለቆ ይገቡ የነበረው ከአባይ ሸለቆ የተሻለ፣ ሽፍቶ ለመኖር የሚሆን ሌላ ቦታ ስላልነበር ነዉ ፡፡ የበላይ ዘለቀ መደበኛ ወታደሮች ግን በሙሉ በሚባል ደረጃ በተለያዬ ጊዜ በፍላጎት የገቡ የወሎ ሰዎች ነበሩ ፡፡ ምክንያቱም በላይ ለሰራዊቱ የሚሆን

በቂ ራሽን /ምግብ/ ስላልነበረዉ፣ በተቆጣጠራቸዉ የአባይ ሸለቆ ወረዳዎች የተመለመሉት ወታደሮች እዚያዉ ቤታቸ እየኖሩ፤ የከትት ጦርነት ሲታወጅ ብቻ ከያሉበት በመምጣት መደበኛዉን የወሎ ወታደር ያግዛሉ፤ ጦርነቱ እንዳለቀ ወደ ቤታቸዉ ይመለሳሉ፤ ከተት ታዉጆ ከቀሩ ግን ማታ እየተለቀሙ ከፍተኛ ቅጣት ይደርስባቸዋል ።

እናም እራሽን ይቀርብ የነበረዉ 500 አባላት ላሉትና “ጋሜ” በመባል ለሚታወቀዉ ልዮ ጦር እና “ዙሪያ ሰፋሪ” በመባል ለሚታወቀዉ መትረየስ ተኳሽ ጦር ብቻ ነበር ፡ እነዚህ ደግሞ በላይ ከማይቆጣጠራቸዉ የወሎ አካባቢዎች በየጊዜዉ በፍላጎት የመጡ ወታደሮች ስለሆኑ ከተበተኑ በኋላ በከትት አዋጅ ተገደዉ ሊመጡ አይችሉም ። እናም ከሞላ ጎደል በሙሉ የበላይ መደበኛ ወታደሮች የወሎ ሰዎች ነበሩ /አባይ ጎጃምን ይዞራል የበላይ ምሽግም የአባይን ወንዝ የተከተለ ነበር/ ።

ስለ ጣሊያን ዳግም ወረራ/ሁለተኛ ወረራ/፤ በእኛና በነጭ ታሪክ ፀሀፊዎች መካከል ትልቅ ልዩነት አለ ። እኛ ኢትዮጵያዊያን፣ በጣሊያን ዳግም ወረራ ጊዜ ኢትዮጵያ የተሸነፈችዉ በጦር በሳሪያ ብልጫ ነዉ እንላለን ። እንደ ነጭ ፀሀፊዎች ግን ኢትዮጵያ የጦር መሳሪያ ብልጫዉን መቋቋም ትችል ነበር /አትሸነፍም ነበር/ ። ኢትዮጵያን እንዲትሸነፍ ያደረጋት የጎጃሞች ክህደት ነዉ፣ ጎጃሞች የጣሊያንን መምጣት ከሸዋ አገዛዝ ለመገላገል የተፈጠረ ልዩ አጋጣሚ አድርገዉ ነበር የወሰዱት ። የጎጃሞች አመፅ አጠቃላ የሰራዊቱን የአንድነት ስሜት ገድሎታል፣ የወታደሩን ኢትዮጵያዊነት ስሜቱንና የእርስ በርስ መተማመኑን አዳከሞታል፣ የወታደሩን ሀገራዊ አቋም ሰብሮታል…ወዘተ ይላሉ ።

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴልኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች “የኢትዮጵያ ታሪክ” በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ያሰፈሩትና በዓለማየሁ አበበ የተተረጎመዉ መጸሀፍ ዉስጥ የሰፈረዉ ፅሁፍ ቃል በቃል ሲቀመጥ ፡ -

“ከረጅም ጊዜ አንስቶ ሲብላላ የቆየዉ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ላይ የተቃጣዉ የጎጃሞች አመፅ፣ በጦርነቱ ዋዜማ ላይ የንጉሰ ነገስቱን ሰራዊት አቋም አዳከሞታል ። ጎጃሞች፣ ጦርነቱ ከአፄ ኃይለስላሴ አገዛዝ ለመላቀቅ ጥሩ አጋጣሚ ነዉ የሚል እምነት ነበራቸዉ ። ጎጃሞች፣ ይህ “የሸዋ ንጉስ” ይላሉ እንጂ “ንጉሰ ነገስት” የሚለዉ ቃል ከአፋቸዉ አይወጣም ነበር ይልና፣

ጦርነቱ እንደተጀመረ የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ዉስጥ አንዳንድ የጎጃም መኳንንት ንጉሰ ነገስቱን እየተዉ ከየዕርስታቸዉ እየሄዱ ይቀመጡ ጀመር ። በራስ ኃይሉ ተከተለሐይማኖት ቀስቃሽነት ግልፅ አመፅ ጀመሩ ። በዚህም ምክንያት ታህሳስ 8 ቀን 1928 ዓ.ም ንጉሰ ነገስቱ ለጎጃም ህዝብ አዋጅ አስነገሩ ። በዚህ አዋጅ ዉስጥ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ከብዙዉ በጥቂቱ እንዲህ ብለዋል ፡ - የጎጃም ህዝብ ሆይ፣ ጠላት ሲመጣ ያለርህራሄ በጭካኔ ሐይማኖትህን ያስለዉጥሀል፣ ሚስትህንና ሴት ልጆችህን ይነጥቅሀል፣ ከአባቶችህ የወረስከዉን መሬት ይቀማሀል ። ለሀገርህ ለኢትዮጵያ ነፃነት፣ ለኦርቶዶክስ እምነትህ ደምህን ታፈሳለህ እንጂ ትከዳኛለህ የሚል እምነት አልነበረኝም ። ደጃች ገሡ፣ ፊታዉራሪ ታምራት፣ ፊታዉራሪ ገሡ ንጉሴ፣ ፊታዉራሪ ዘለቀ ካሳ፣ ፊታዉራሪ ዘለቀ ወሌ፣ ቀኛዝማች አየለ ኃይሉ፣ ቀኛዝማች መርዕድ ዋሴ፣ ቀኛዝማች ዘለቀ አሰጌ ወዘተ የተባሉት ባላባቶች አገራቸዉን ኢትዮጵያንና እኔን ንጉሰ ነገስቷን ከድተዋል" ብለዉ አዋጅ አስነገሩ ይልና፣

ሆኖም ግን የታህሳሱ፣ የንጉሰ ነገስቱ አዋጅ ምንም አድማጭ አላገኘም ። ጎጃም ዉስጥ ንጉሰ ነገስቱ፣ በአዋጁ፣ በሥም በጠቀሷቸዉ መኳንንት መሪነት ግልፅ ጦርነት ተቀጣጠለ ። ከዚህ በኋላ አንድ ታማኝ ጦር ከግምባር ቀንሶ ወደ ጎጃም ማዝመት ግድ ሆነ ። ይህ ጎጃሞች ያቀጣጠሉት የክህደት ጦርነት የኢትዮጵያን ሰራዊት አቋም /የአንድነት አቋም/ አዳክሞታል ፡ ይህ በጎጃም የተቀሰቀሰዉ ሁከት በተለይ በሰሜኑ ግምባር ወሳኝ በነበረዉ የማይጨዉ ጦርነት ላይ የኢትዮጵያን ጦር ኃይል አቋም አዳክሞታል" ይላል ።

ጎጃምና ጎንደር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ታማኝ ተቆጥረው ጦርነት ላይ የተሰለፉት በዚህ ጦርነትና ደርግ ከኢህአዴግ ጋር ባደረገው ጦርነት ላይ ብቻ መሆኑ መፅሀፉን አንብበን ስንጨርስ በጣም ግልፅ ይሆናል ። ይህ የሆነበትም ምክንያት ጎጃሞች የበፊቱን የአፄ ሚኒሊክን ቂም ይረሱታል ተብሎ ስለተገመተ ነበር ጥርጣሬው የቀረላቸው ። ነገር ግን ጎጃሜዎች የበፊቱን በአፄ ሚኒሊክ የደረሰባቸውን ቂም አረሱትም ነበርና በአፄ ኃይለስለሴ ጊዜ የጣሊያንን መምጣት እንደ ልዩ አጋጣሚ ተጠቅመው በሸዋና በየጁ ላይ ቂማቸውን ለመወጣት ሞከሩ ። በአድዋ ጦርነት ጊዜ ግን እራሳቸው አፄ ሚኒሊክ ስለነበሩና የቂማቸውንም መጠን ስለሚያውቁት በጥርጣሬ ጎጃሜዎችን ለብቻቸው ነበር ያሰለፏቸው፤ ስለሆነም ጦርነቱን ጥሩ በሆነ

ሀገራዊ አቋም ማሸነፍ ተቻለ /ጦርነቱ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ነደመደመ/ ። ነገር ግን ጎጃሞች ለመጀመሪያ ጊዜ ታማኝ ተደርገው በተሰለፉበት በዚህ የጣሊያን ዳግሞ ወረራ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሀገራዊ አቋም ባየነው መልኩ ስለተበላሸ ጦርነቱ በኢትዮጵያ ተሸናፊነት ተጠናቀቀ /የውስጥ ባንዳ ካለ የውጭ ጠላትን በርትቶ መዋጋት አይቻልም/ ። እናም ጎጃሚዎች ወሎን /ሸዋና የጁን/ የተበቀሉ መስሏቸው ለውጭ ጠላት በባንዳነት በማገልገልና የውስጥ ውጋት በመሆን ሀገራቸውን እንድትደፈር አደረጉ ። የዚህ የጎጃሞች ጉዳይ መነሻዉ አፄ ሚኒሊክ ናቸዉ፤ በአፄ ምኒሊክ ስር ያለዉን አንብበን ስንጨርስ በጣም ግልፅ ይሆናል ።

ስለዚህ የበላይ ዘለቀ ታሪክ የጎጃሞች ታሪክ ሊሆን አይችልም ማለት ነዉ ። የበላይ ዘለቀ ታሪክ በዘፈን ብቻ ወደ ጎጥ ታሪክነት ከተቀየሩ የኢትየጵያ /የወሎ/ ታሪኮች መካከል አንዱ ነዉ ማለት ነው /ወሎ የብሄረሰቦች ድብልቅ ነው/ ። ይህ በርግጥ የጎጃሞች ስህተት ብቻ አይደለም የአሁኑ የኢትዮጵያና የወሎ ትዉልድ በቁንጅና ዘፈኖች ተጠምዶ ለታሪኮቹ ቦታ ባለመስጠቱ የመጣ ነዉ ። ወሎ የሁሉም ብሄረሰቦች ድብልቅ /collection/ ከመሆኑ አንፃር ሁሉም የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ታሪካቸውን የመጠበቅ የዜግነት ግደታ አለባቸው ። እናም ኢትዮጵያዊያን በየጊዜው ወደ ጎጥ ታሪክነት ሲቀየሩ የኖሩ የሀገሪቱን ታሪኮች በዘፈንና በፅሁፍ እንደገና ማስተካከል ይኖርባቸዋል ማለት ነው ። ዘፈን በዘላቂነት ታሪክን ከማስተካከል አንፃር ዋናውን ድርሻ ይወስዳል፤ መፀሀፍ ጊዜዊ ነው /በፋሽን ነው የሚነበበው/፣ በዚያ ላይ አንባቢው ለራሱ ብቻ ነው የሚያነበው፤ ዘፈን ግን ለዘለዓለም ዘላቂ ነው /የአሁኑ ትውልድ የዱሮዎቹን የእነ ጥላሁን ገሰሰን ዜማዎች እንደሚደምጠው ማለት ነው/፣ በዚያ ላይ አንድ ሰው ዘፈን ሲከፍት ሁሉም ሰው ይሰማል፣ አንድ ሙዚቃ ቤት ዘፈን ሲከፍት ሰፈሩ ሁሉ ይሰማል ወዘተ ። እናም ወሎ የብሄረሰቦች ስብስብ /collection/ ስለሆነ ሁሉም ብሄረሰቦች የሀገራቸውን የኢትዮጵያን ታሪክ መጠበቅ የዜግነት ግደታቸው ነው ማለት ነው ።

በነገራችን ላይ በላይ ዘለቀ በርካታ የጎጃም ዘፋኞች ስላዜሙለትና ታዋቂ ስላደረጉት እንጂ ከአርበኝነት አንፃር ሲታይ በላይን የሚበልጡ በርካታ ስማቸዉ ተነስቶ የማያዉቅ አርበኞች አሉ ። እናም ስለእነሱ ሳንፅፍ ስለ በላይ መፃፋችን ከአንባቢያን ጋር ከማስተዛዘቡም ባሻገር ለህሌናም ጥሩ ስለማይሆን የበላይ ዘለቀን ጉዳይ እዚህ ላይ እናቆማለን ።

አፄ ቴዎድሮስ ፡ - ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ፣ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፍሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ ፡ - “ልጅ ካሳ /በኋላ አጼ ቴዎድሮስ/ ጥር 6 ቀን 1811 ዓ.ም ከቋራዉ ተወላጅ ከሀይሉ ወልደጊዮርጊስና ከእንፍራዟ እመቤት ከወ/ሮ አትጠገብ ነበር የተወለዱት ።

በተወለዱ በ1 ዓመታቸዉ አባታቸዉ ስለሞቱ እናታቸዉ ወ/ሮ አትጠገብ ተምረዉ ለወግ ለማዕረግ ይበቁ ዘንድ ወደ አንድ ገዳም ወስደዉ ለመነኮሳቱ አደራ ሰጧቸዉ ። በመጀመሪያ በማህበረ ስላሴ ገዳም፣ ቀጥለዉ በቸንክር ተክለሐይማኖት ገዳም መንፈሳዊ ትምህርትና ዓለማዊ ትምህርታቸዉን ሲከታተሉ አደጉ ።

ወደ ወጣትነት ሲሸጋገሩም ከደንቢያዉ ባላባት ከናታቸዉ ወንድም ከደጃች ክንፉ ጋር ሆነዉ እየኖሩ ሳለ ገሰሰች እንግዳ የተባለች ልጃገረድ ጋር ተጋብተዉ መሸሻንና አልጣሽን ወለዱ ። ትዳራቸዉ ግን ብዙ አልቆየም ። ትዳራቸዉ ስኬታማ ስላልነበረ ከአጎታቸዉ ጋር ወደ ጎንደር ቤተመንግስት መጡ ። ቤተመንግስቱ ዉስጥም ማገልገል ጀመሩ ይልና፣ በአጭር ጊዜ ዉስጥም በሚፈፅሟቸዉ የድፍረትና የጀግንነት ሥራዎች በእቴጌ መነን ዘንድ ተወዳጅ እየሆኑ ሄዱ ። በልዩ ልዩ ግዛቶች ለዘመቻ ሲሄዱም በታላቅ ጀብድ ድል እያደረጉ ምርኮም እያመጡ ለትንሹ ራስ አሊና ለእናቱ ለእቴጌ መነን በማስረከብ ታማኝ አገልጋይ ሆኑ ይልና፣ በ1840 አካባቢ የግብፅ ጦር በሱዳን በኩል ኢትዮጵያን ለማጥቃትና ለመዉረር ከመቸዉም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ የመጣበት ወቅት ነበር ። ካሳም ጦሩን በከፍተኛ ጀግንነት በመምራት ስናር ድረስ ዘልቀዉ ገብተዉ የግብፅን ወራሪ ሀይል ድምጥማጡን አጥፍተዉ ተመለሱ ። እጅግ ጀግና መሆናቸዉ በሁሉም የቤተመንግስት ሰዎች ዘንድ ታየላቸዉ ። ራስ አሊና እቴጌ መነንም ከሁሉም መኳንንቶቻቸዉ የበለጠ ካሳን ወደዷቸዉ ።

ነገር ግን የካሳ ጀግንነት ለራሳቸዉም ስጋት ሆናቸዉ ። ስለዚህ በዘዴ መያዙን መረጡና በጋብቻ ገመድ ጠፍረዉ ለማሰር ሲሉ የራስ አሊን ልጅ፣ የእቴጌ መነንን የልጅ ልጅ ተዋበችን በሚስትነት ሰጥተዉ አጋቧቸዉና 40 ቀን የቆዬ ድግስና ግብዣ ተካሄደ ።

የደጃዝማችነት ማዕረጉንም ያገኙት በዚሁ በሰርጉ ጊዜ ነበር” ይላል ።

/እዚህ ላይ ማለትም “በዘዴ መያዙን መረጡና በጋብቻ ገመድ ጠፍረዉ ለማሰር ሲሉ” የሚለዉ ሀረግ ታሪኩ ተቀጥቅጦ የተጣመመበት ቦታ ነዉ ። ካሳ ቤተመንግስት የገባዉ ባዶ እጁን መሆኑን አይተናል ። አንዳንዶች ካሳ ባዶ እጁን አልነበረም፣ ሰራዊት ነበረው እያሉ ይከራከራሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ ሽፍታ ያደርጉታል ። ሁለቱም እጅግ ስህተት ናቸው፤ ምክንያቱም ካሳ የራስ አሊ ሎሌ እንደነበር፣ በዚያው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን በህይወት የነበሩት እነ ጸሐፌ ትዛዝ ፅፈዋል (ጸሐፌ ትእዛዝ በአፄ ቴዎድሮስም በአፄ ሚኒልክም ጊዜ በህይወት ነበሩ፣ አፄ ሚኒሊክ በአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ ታስረው ነበር) ። ካሳ ሎሌ ከሆነ በኋላ ሽፍቶ ቢሆን ኖሮ ደግሞ እንደገና ተመልሶ ታዛዥ ሆኖ ቀጥለን እንደምናየው አንድ እግር ወርቾ ስጋ አይላክለትም ነበር ። እናም የእቴጌይቱ ውለታ ገደል የገባበትና የየጁ ወታደሮች ታሪክ ተጣሞ ለቴድ የተሰጠበት ቦታ ይህ ነዉ /በጋብቻ ገመድ ጠፍረው ለማሰር የሚለው ሀረግ/ ። እስኪ እንደዉ ማን ይሙት? ሴት ልጅ እንጂ ወንድ ልጅ እንደት ተገዶ ሊያገባ ይችላል ። በዚያ ላይ ማስገደድ ከተቻለና ሰውየው ስጋት ከሆነ አስገድዶ ከማጋባት ይልቅ መግደል ይቀላል ። ቀጥለን እንደምናየው ቴድ ተዋበችን ከሞት መንጋጋ /ከግብፆች እስር ቤት/ አውጥቶ ነው ያገባት ። እናም የኢትዮጵያን /የወሎን/ ታሪክ አጣሞና አድበስብሶ ለመውሰድ ሲባል የወሎን ውለታ መካድና የአባቶቻችንን መዋደድ ማበላሸት ተገቢ አይመስለንም ። ጎጃሜዎች የበላይ ዘለቀን ታሪክ በዘፈን አማካኝነት ብቻ ከወሎ መውሰዳቸው ይታወቃል ። ይህ ለሀገራችንም ጥሩ አይሆንም፣ ታሪክ ሰሪዉ ሌላ ተሸላሚዉ ሌላ ከሆነ ታሪክ ሰሪ አይገኝም ። የወሎ ታሪክ የሁላችንም ታሪክ ሆኖ እያለ ታሪክ ሰሪዎቹን ማበረታታት ሲገባን ታሪካቸዉን ለመዝረፍ ስንል የኢትዮጵያን /የወሎን/ ታሪክ በማጣመም ለሌላ ሰዉ እየሸለምን ሀገሪቱ ጀግና እንዳይኖራት ማድረግ ጥሩ አይመስለንም/ ። ታሪኩ ተስተካክሎ ሲፃፍ እንዲህ ይሆናል ።

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴልኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች “የኢትዮጵያ ታሪክ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትና በዓለማየሁ አበበ ከተተረጎመዉ መፀሀፍ ውስጥ የሰፈረዉ ፅሁፍ ቃል በቃል ሲቀመጥ “ከግብፅ ጋር በተካሄደዉ ጦርነት የመነን ሰራዊት ጠንክሮ እንዲዋጋ እንዲታደፋፍር ተብሎ፣ የልጅ ልጇ ልዕልት ተዋበች ሰራዊቱን እንዲታጅብ ተደርጎ ነበር ። ነገር ግን ግብፆች ያሏቸዉ መድፎች ለድል አበቋቸዉ፣ ኢትዮጵያዊያኑ ተሸነፉ፣ ልዕልት ተዋበችም ተማረከች ይልና፣

በዚህ ጊዜ ካሳ ከእቅዶቹ ዉስጥ ብዙዉን ክፍል እዉን የሚያደርግበት ጊዜ እንደ ደረሰ ተገነዘበ ። ይኸዉም በመጀመሪያ ደረጃ በኢትዮጵያ ዉስጥ ለማዕከላዊዉ ስልጣን ለሚደረገዉ ትግል አመች መቆናጠጫ ማግኘት፤ ቀጥሎም የራስን አቋም ማሻሻል ነዉ ፡ እነዚህንም በሁለት መንገዶች ለማከናወን ወሰነ ፡ - አንደኛ ግብፆችን ድል ማድረግና በጠላት ኃይል ላይ በተገኘዉ ድል አማካኝነት የራሱን ወታደራዊ ተደማጭነት ማጠናከር ። ሁለተኛ ከቤተመንግስቱ ጋር መጋባትና በባላባታዊዉ የደረጃ ርብራብ ዉስጥ ተቀባይነት የሚያስገኝ የኅላ ስፍራ መያዝ ። ምናልባትም ይህን ታላቅ ምኞትና የመሪነት ተሰጥኦ የታደለዉ ካሳ፣ ይህን ሁለተኛዉን ሀሳብ መተግበሩ ወደ ፊት ለንጉሳዊዉ ዙፋን ለሚደረገዉ ትግል ጥሩ መቆናጠጫ እንደሚሆንለት ሳይገነዘብ አልቀረም ይልና፣

ካሳ ሰራዊቱን እየመራ የግብፅን ጦር ወግቶ በመበታተን፤ ከተማረከች በኋላ፣ ለሙላ ፓሻ ሐሬም የመዝናኛ ጫጉላ ታጭታ የነበረችዉን ልዕልት ተዋበችን፣ ከግብፆች እስር ቤት መንጥቆ አወጣት ። ያን ጊዜ ገና የ15 ዓመት ጉብል የነበረችዉ ተዋበች እጅግ የምታምር ቆንጆ ነበረች ። ከጎንደሩ ቤተመንግስት ጋር በጋብቻ የመተሳሰሩ የካሳ ምኞት እዉን ወደ መሆኑ የተቃረበበት ዋናዉ ምክንያት ይህ ነዉ ፡ ለጊዜዉ ግን ተዋበች ወደ ወላጆቿ ቤተመንግስት ጎንደር እንድትሄድ አደረገ" ይላል ።

/በነገራችን ላይ ይህ ተርጓሚ አፄ ቴዎድሮስ ላይ ሲደርስ በርካታ የአደባባይ ሚስጥሮችን ዘሎቸዋል፤ ለምሳሌ ያህል ካሳ የራስ አሊ ሎሌ እንደነበር፣ በዚያው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን በህይወት የነበሩት እነ ጸሐፌ ትእዛዝ ፅፈዋል፣ እንዲሁም ተርጓሚው ካሳና እቴጌ መነን የተከዳዱበትን የወይፈንና የአንድ እግር ወርች ስጋ ጉዳይንም ዘሎታ፤ እነኝህን የመሳሰሉ የአደባባይ ሚስጥሮችን ቆርጦ መጣል ተገቢ አይመስለንም ። ሆኖም ግን እስከ አሁን ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፃፉ የታሪክ መፀሀፎች ውስጥ ይህ መፀሀፍ እጅግ የተሟላና እጅግ የተሻለ ሚዛናዊነት ስለሚታይበት እኛም ልንጠቀምበት በአንደኛ ደረጃ መርጠነዋል ። የፀሐፊ ትእዛዝ መፀሀፍ ደግሞ አፄ ሚኒሊክ በጆት በጆተው ከራሳቸው ከአፄ ሚኒሊክ አፍና ከእቴጌ ጣይቱ አፍ ላይ እየተወሰደ የተፃፈ ትክክለኛ (original) መፀሀፍ ስለሆነ ስለ አፄ ሚኒሊክ ዘመን ይህንን መፀሀፍ ልንጠቀምበት በአንደኛ ደረጃ መርጠነዋል ። የጋዜጠኛ ፍሰሐ መፀሀፍ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ እጅግ

በተሟላ ሁኔታ የያዘና እጅግ የተሻለ ሚዛናዊነት ስለሚታይበት ይህንንም መፀሀፍ ልክ እንደላይኞቹ በፅሀፎች በአንደኛ ደረጃ ልንጠቀምበት መርጠነዋል/ ።

እናም ከላይ ካየነው የትርጉም መፅሀፍ እንደተረዳነው ካሳ ተዋበችን ከሞት መንጋጋ /ከግብፆች እስር ቤት/ ነበር ያወጣት ማለት ነዉ ፡ ስለዚህ ለተዋበች ከካሳ የበለጠ ሰዉ አይኖርም ማለት ነዉ ።

ወደ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ፅሁፍ ስንመለስ "በዚህ ድርጊታቸዉ /ታዘው ልጅቱን ከግብፆች እስር ቤት በማውጣታቸው/ ካሳ እጅግ ጀግና መሆናቸዉ በሁሉም የቤተመንግስት ሰዎች ዘንድ ታየላቸዉ ።ራስ አሊና እቴጌ መነንም ከሁሉም መኳንንቶቻቸዉ የበለጠ ካሳን ወደዷቸዉ ። ነገር ግን የካሳ ጀግንነት ለራሳቸዉም ስጋት ሆናቸዉ ። ስለዚህ በዘዴ መያዙን መረጡና በጋብቻ ገመድ ጠፍረዉ ለማሰር ሲሉ የራስ አሊን ልጅ፣ የቴጌ መነንን የልጅ ልጅ፣ ተዋበችን በሚስትነት ሰጥተዉ አጋቧቸዉና 40 ቀን የቆዬ ድግስና ግብዣ ተካሄደ ። የደጃዝማችነት ማዕረጉንም ያገኘዉ በዚሁ በሰርጉ ጊዜ ነበር ይልና፣

በመሐመድ አሊ በተመራዉ የግብፅ ጦርና በእቴጌ መነን ጦር መካከል በተካሄደዉ ከባድ ዉጊያ በርካታ ሰራዊት ከማለቁም በላይ እራሳቸዉ የጦር መሪዎቹም ቆስለዉ ነበር ። በዚህ ጦርነት ደጃዝማች ካሳ ሀይሉና አብሯቸዉ ዘምቶ የነበረዉ የባለቤታቸዉ የተዋበች ወንድም፣ ቆስለዉ ነበርና ሁለቱም እንዲያገግሙ በማሰብ እቴጌ መነን ለልጅ ልጃቸዉ /ለተዋበች ወንድም/ ጥሩ ወይፈን ሲልኩ ለደጃዝማች ካሳ ግን አንድ እግር ወርች ሥጋ ብቻ ላኩላቸዉ ይልና፣

እቴጌዋ ደጃዝማች ካሳን ዝቅ አድርገዉ በማየታቸዉ ያዘኑት ጀግናም ባለቤታቸዉን ተዋበችን "ተመልከች የእናትሽን ግፍ" አሏት በምሬት ። ተዋበችም በእናቷ እጅግ አዘነች ። በተለይም በበርካቶች ዘንድ "ከደሐ ጋር የተጋባች" እየተባለች ትወቀስ ነበርና በንዴት ተዉጣ ዝም ባለች ጊዜ "ምን ትያለሽ ተዋበች" ብለዉ ሲጠይቋት "ተነሳ ነዋ የምልህ! ታጠቅ ነዉ የምልህ" የሚል መልስ ሰጠች" ይላል ።

/እንግዲህ ካሳ ወይፈን እንኳ ማረድ አይችልም ነበር ማለት ነው ። ካሳ ቤተመንግስት ባዶ እጁን ሄዶ የተቀጠረ መሆኑንም አይተናል ። አንዳንዶች ካሳ

ባዶ እጁን አልነበረም፣ ሰራዊት ነበረው እያሉ ይከራከራሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ ሽፍታ ያደርጉታል ። ሁለቱም እጅግ ስህተት ናቸው፤ ምክንያቱም ካሳ የራስ አሊ ሎሌ እንደነበር፣ በዚያው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን በህይወት የነበሩት እነ ጸሐፊ ትዛዝ ፅፈዋል፤ ካሳ ሎሌ ከሆነ በኋላ ሽፍቶ ቢሆን ኖሮ ደግሞ እንደገና ተመልሶ ታዛዥ ሆኖ አንድ እግር ወርች ስጋ አይላክለትም ነበር ።

እናም ካሳ በራስ አሊ ቤተመንግስት ውስጥ ከሎሌነት ጀምሮ እየተሾመ፣ እየተሾ መጥቶ የእቴጌ መነን ጦር ዋና አዛዥ እስከመሆንና ደጃዝማች እስከመባል ደረሰ ። ካሳና ተዋበች በተጋቡበት የስርግ ስነስረዓት ላይም ካሳ የደጃዝማች ማዕረግ ተሰጥቶት የመንግስት ጦር አዛዥ ተደርጎ ተሾመ ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ካሳ የሚያዘውን የመንግስትን ሰራዊት ይዞ ለመክዳት ተዋበችን የሚያሳምንበት ነገር ብቻ ነበር የሚፈልገዉ ። ተዋበች ደግሞ ከሞት መንጋጋ ያወጣትን ካሳን ትወደው ስለነበርና በዘመኑ የነገስታት ልጆች የእናት-የአባትን ስልጣን ቀድመው ለመውረስ ይሽቀዳደሙ ስለነበር የአባቷን ስልጣን ቀድማ ለመውረስ ፈልጋለች ። ተዋበች ካሳ ሸፈተም አልሸፈተም ከእቴጌ መነን እጅ እንደማይወጣ እርግጠኛ ነበረች ። ምክንያቱም የያዘዉ ሰራዊት የሱ ሰራዊት አይደለም፤ የየጁዉ የእቴጌ መነን ሰራዊት ነዉ ። በዚያ ላይ ቴድ ባላባት አይደለም /ተዋበች ከሌለች መንገስ አይችልም፣ አይቻልም፣ እዚያ ዘመን ላይ ሆነን ማሰብ አለብን ጭሰኛ መንገስ አይችልም፣ ስለዚህ እሷ ነች የምትነግሰው ማለት ነው፣ ቴድ ከተዋበች እጅ ሊወጣ አይችልም ማለት ነው፤ መጨረሻ ላይ ተዋበች ስትሞትም የታየዉ ይኸዉ ነዉ ።

እናም ተዋበች ለወንድሟ ወይፈን ተልኮ ለእሷ አንድ እግር ወርች ሥጋ ብቻ መላኩ አስቆጥቷታል፤ ካሳን ሳይሆን እሷን ነው ማየት ያለባቸው፤ ካሳን ከናቁት አለማጋባት ነበር፣ ከሞት መንጋጋ ካወጣት ከካሳ የበለጠ ሰዉ ደግሞ የላትም ። እናም ምን ትያለሽ ተዋበች ሲላት፣ በሁኔታው ተናዳ ስለነበርና በዘመኑም የነገስታት ልጆች የእናት-የአባትን ስልጣን ቀድመው ለመውረስ ይሽቀዳደሙ ስለነበር ፈቀደችለት፣ ተነስ ታጠቅ አለችዉ ።

እናም ካሳ ተዋበች ሀሳቧን ትቀይራለች ብሎ የፈራ ይመስላል፤ ወዳው በፈቀደችለት ሌሊት ተዋበችንና የሚመራውን ሰራዊት ሁሉ ጠራርጎ ይዞ ወደ ቋራ ሲጓዝ አድሮ በአካባቢው በረሀ ሰፈረ ። ከሸፈቱም በኋላ ተዋበች ብዙም ፖለቲካዊ ብቃት ስላልነበራት፤ ሁሉንም የፖለቲካ ስራዎች የሚያስፈፅመዉ ወትሮዉንም የተሻለ ፖሊቲካዊ ተሰጦ የነበረዉ ካሳ ሀይሉ ነበር ። እቴጌ

ተዋበችም ልክ እንደ እናቷ ካሳ በሚሰራቸዉ ስራዎች እምነት እያደረባት ስለመጣ የፖለቲካዉን ስራ ሙሉ በሙሉ ለቀቀችለት ። ከዚህ በኋላ ካሳ ያለማንም ከልካይ በየጁዉ የእቴጌ መነን ሰራዊትና መሣሪያ መሣፍንቱን ሁሉ ያጭደዉ ጀመር ። በሸፈተ በአመቱ በደረስጌ ማሪያም ቤ/ን በጳጳሱ ተቀብቶ ነገሰ ።

ወደ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ስንመለስ "ምን ትያለሽ ተዋበች" ብለዉ ሲጠይቋት "ተነሳ ነዋ የምልህ! ታጠቅ ነዉ የምልህ" የሚል መልስ ሰጠች ። ይህ አጋጣሚ በዉስጣቸዉ የተጸነሰዉን ሀገር አንድ የማድረግ ፍላጎትና አላማ የማሳኪያ የመጀመሪያዉ መንገድ ስለሆነላቸዉ እየተደሰቱ የዚያኑ ዕለት ሌሊት የሚመሩትን ጦር አስከትለዉ ተዋበችንም ይዘዉ ሸፈቱ፤ ወደ ቋራ አቅንተዉም በአካባቢዉ ባለዉ በረሀ ሰፈሩ ይልና፣

ወዳዉም ከእቴጌ መነን ጋር ተጣልቶ የሸፈተዉን ይልማ ወሰንን አገኙትና በከፍተኛ ደስታ ተቀብሎ ከጎኑ አደረጋቸዉ ። የመሪነቱን ቦታም ለደጃዝማች ካሳ ሀይሉ ለቀቀላቸዉ ። ህብረት ፈጥረዉም የአካባቢዉን ግዛት ሹማምንት ድል እያደረጉ በርካታ ቦታዎችን ተቆጣጠሩ" ይላል ።

እንግዴህ በርካታ ፀሀፍት የካሳን ታሪክ መፃፍ የሚጀምሩት ከዚህ በኋላ ያለውን ነው፣ እስካሁን ድረስ ያየነው የካሳ ታሪክ ይዘለላል /ተቆርጦ ይጣላል/ ወይ ተድበስብሶ ይታለፋል ።

እናም በወቅቱ በኢትዮጵያ ተወዳዳሪ የሌለዉንና የግብፅን ጦር እንደ እሳት የበላዉን፣ የእቴጌ መነንን ጦር ይዞ የሸፈተዉ፣ ደጃዝማች ካሳ ሀይሉ መሳፍንቱን ሁሉ ይጠራርገዉ ጀመር ። ሁሉም መሳፍንቶች የቴጌ መነን ገባር ስለነበሩ ጦራቸዉም በትጥቅም ሆነ በብዛት ከእቴጌ መነን ጦር እንደሚያንስ ግልፅ ነዉ ። እናም የበርካታ መድፎችና የተሻለ ትጥቅ ባለቤት የሆነዉን የቴጌ መነንን ጦር ይዞ የሸፈተዉን ደጃዝማች ካሳ ሀይሉን የሚቋቋመዉ መሳፍንት አልተገኘም ። እናም ደጃች ካሳ በሸፈተ በአመቱ በጳጳሱ ተቀብቶ ነገሰ ።

ጸሓፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ "ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒሊክ" በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ያሰፈሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ "ደጃች ካሳ የራስ አሊ ሎሌ ነበር /ራስ አሊ የእቴጌ መነን ልጅ ነዉ/ ። ጌታ አክዓብን በተጣላዉ ጊዜ መንግስቱን ለሎሌዉ ለኢዩ አሳልፎ እንደሰጠዉ ሁሉ የነዚህንም ትዕቢታቸዉንና

ጥጋባቸዉን እግዚአብሔር አይቶባቸዉ መንግስታቸዉን አሳልፎ ለሎሌቸዉ ለደጃች ካሳ ሰጠባቸዉ ይሉና፣

ደጃች ካሳም ደግሞ በሸፈተ በአመቱ ደጃች ዉቤን ድል አድርጎ፤ ደጃች ዉቤ እነግሳለሁ ብሎ ባሰራዉ ምንጣፍ፣ ባሰራዉ ዘዉድ፣ ባሰራዉ ቤተክርስቲያን ደረስጌ ማሪያም ላይ ስሜም ቴዎድሮስ ነዉ ብሎ ነገሰ” ይላል ። /ስለዚህ በዓለም ላይ በሸፈተ በአመቱ የነገሰ ሽፍታ ካሳ ሀይሉ ይሆናል ማለት ነው፤ አንዳንድ ፀሀፍት አንድ አመት ተኩል ያደርጉታል፣ ጋዜጠኛ ፍሰሀ መፀሀፍ ላይም ስናቀናንሰው እንዲሁ አንድ አመት ተኩል አካባቢ ነው/ ።

ቀጥሎም የሚከተሉትን ህጎች በአዋጅ አስነገረ ።/እዚህ ላይ ለካህናቱ የወጣዉን ህግ፣ ቁጥር 3ን፣ ልብ እንበል፤ ተዋበች ከሞተች በኋላ ይቀየራል/ ።

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ቃል በቃል አስነብባችኋለሁ ።

1. ‘‘ክርስትያን በክርስትያንነቱ፣እስላም በእስላምነቱ ጸንቶ ይቀጥል ።ነገር ግን እምነቱን ከአንዱ ወደ ሌላ የቀየረ እንደሆነ ሰባኪዉም ተሰባኪዉም አንገቱ በሰይፍ ይቆረጣል ። ደረቱ በጦር ይወጋል ።
2. ክርስትያን የሆነ ሆሉ ከአንድት ሴት ዉጭ ሌላ አግብቶ ቢገኝ ሀብቱን ሁሉ እንዳለ ለመጀመሪያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣና እርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠዉ/ተዋበችንና የየጁን ሰራዊት ለማስደሰት የታሰበ ይመስላል/ ።
3. ከጥንት ጀምሮ የነበረዉ የቄስና የደብተራ የመሬት ግብር እንደነበረ ሆኖ ይቀጥል /ይህን ህግ ተዋበች ከሞተች በኋላ መሳፍንቱ ሁሉ ስላመፁበት፣ ካህናቱ አመፁን ማስቆም አለባቸዉ በሚል ቀይሮታል/ ።
4. የቤተመንግስቱ ባለስልጣኖች በእለት ተግባራቸዉ በደመወዝ እንዲሰሩ እንጂ ባሪያ መግዛትና መሸጥ እንዳይፈጽሙ ።
5. የቤት ሰራተኞች ገረድና አሽከሮች በደመወዝ እንዲያገለግሉና ከአሰሪያቸዉ ጋር ተጣልተዉ ቢወጡ
6. በዉላቸዉ መሰረት ነገሩ የጸናል ።

7. ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በሙያዉ እንድሰለፍ፣ገበሬዉም በግብርናዉ ነጋደዉም በንግዱ እንድተዳደር ፡፡
8. ገበሬዉ ከጥንድ በሬ በላይ የሚያርስ ከሆነና ነጋደዉ ከአጋሰስ ጭነት በላይ የሚነግድ ከሆነ ግብር እንዲከፍል’’ ይላል ፡፡

ከነገሰበት ጊዜ ጀምሮ ያለ ምንም አመፅና ተቃወሞ ሀገሪቱን በሰላም እየመራ ጎንደር ቤተመንግስት ውስጥ ተቀምጦ ነበር ፡፡ ነገር ግን በ1852 ዓ.ም ተወዳጇ ሚስቱ ተዋበች ሞተች፤ ከዚህ በኋላ ሁሉ ነገር ተቀያየረ ፡፡ ቴድ ተዋበች ከሞተች በኋላ ሰላምና ስልጣን አልነበረዉም ፡፡

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴልኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች “የኢትዮጵያ ታሪክ” በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ካሳፈሩትና በዓለማየሁ አበበ ከተተረጎመዉ በፅሀፍ ዉስጥ ያለው ፅሁፍ ባጭሩ ሲቀመጥ “ቴዎድሮስ ከተዋበች ጋርና እሷም ከሞተች በኋላ ከጥሩወርቅ ጋር የፈፀማቸዉ ጋብቻዎች ፖለቲካዊ ፀባይ ያላቸዉ ነበሩ ፡፡ ተዋበች ከሞተች በኋላ ባላባታዊ ተቃወሞ ተቀሰቀሰ ፡፡ ሰራዊቱም /የየጁዉ ሰራዊት/ ከ150ሺ ወደ 10ሺ አሽቆለቆለ ፡፡ በዚህ ምክንያት አፄ ቴዎድሮስ ከሚሰነዘርበት የግድያ ሙከራ የተነሳ ጭንቀት ዉስጥ ወድቆ ነበር ፡፡ የተወዳጇ ሚስቱ የተዋበች በ1852 ዓ.ም መሞት ለዚህ የግድያ ሙከራና ጭንቀቱ ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል ፡ ወዳዉም የወሎዉ መስፍን ዋግሹም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ተዋበች ከሞተች በኋላ አፄ ቴዎድሮስ ባላባት አይደለም በሚል የአፄ ቴዎድሮስን መሪነት አልቀበልም ብሎ ግዛቱን ዙሪያዉን አጥሮ በመቆጣጠር ቴድን በመቅደላ ብቻ እንዲወሰን አደረገዉ /መቅደላ ደቡብ ወሎ ውስጥ የሚገኝ ወረዳ ነው/ ፡፡ በ1856 ዓ.ም የአፄ ቴዎድሮስ ግዛት ከሁለቱ ማለትም ከበጌምድርና ከዋድላ ደላንታ አዉራጃዎች የሚያልፍ አልነበረም” ይላል ፡፡ /ስለዚህ የቴድ ንግስና የቆየው ተዋበች እስከ ሞተችበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር ማለት ነው/ ፡፡

ተዋበች ከሞተች በኋላ ቴድ ባላባት ስላልሆነና የየጁ ሰራዊትን በፍጥነት እየሟሸሸ መምጣትን ተከትሎ በየቦታዉ ያሉ መሳፍንቶች አመፁ፣ አንገብርም አሉ ፡፡ መሳፍንቶቹ ቴድን እየተዉ ግዙፍ ሰራዊት ለነበረዉ ለወሎዉ ለሰቆጣዉ መስፍን ለዋግሹም ስዩም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ መግባት ጀመሩ፡፡

መሣፍንቶቹ በቴድ ሰራዊት መመናመን ብቻ አይደለም ያመፁት ። የህልውና ጉዳይ ስለሆነባቸው ነው፤ ምክንያቱም መሳንቶቹ በዉስጣቸዉ ያለዉን ጭሰኛ የሚያስገብሩት “እኛ ባላባት ነን፣ እንበልጥሀለን፣ የተሻልን ዘሮች ነን ወዘተ” እያሉ ነዉ ። ጭሰኛዉም በዚሁ የባላባትነት ስርዓት አምኖ ነዉ የሚገብረዉ ። ተዋበች እስካለች ድረስ መሳፍንቶቹ ችግር አልነበረባቸዉም ። ምክንያቱም እየገበሩ ያሉት ለራስ ዓሊ ልጅ፣ ለእቴጌ መነን የልጅ ልጅ፣ ለእቴጌ ተዋበች ነዉ ፡ እቴጌ ተዋበች ደግሞ በባላባትነት ሁሉንም ሀገሪቱ ዉስጥ ያሉትን መሳፍንቶች ትበልጣቸዋለች፣ የምትኖርበት ጎንደር ቤተመንግስትም የአባቷ የራስ አሊና የአያቷ የእቴጌ መነን ቤተመንግስት ነዉ፤ ይህን ደግሞ የሀገሪቱ ጭሰኛ ሁሉ አሳምሮ ያዉቀዋል ። ስለዚህ ተዋበች እስካለች ድረስ የባላባትነት ስረዓት አልፈረሰም ማለት ነው ። እናም መሳፍንቶቹ በሰላም ለእቴጌ ተዋበች ሲገብሩ ኖሩ ። ቴድም ያለምንም ተቃዉሞ ንጉሰነገስት ሆኖ ጎንደር ቤተመንግስት ውስጥ ተቀምጦ ነበር ።

አሁን ግን እቴጌ ተዋበች ሞተዋል ። እቴጌ መነንና ራስ አሊም የሉም ። ቴድን ደግሞ በባላባትነት ሀገሪቱ ዉስጥ ያሉት ሁሉም መሳፍንቶች ይበልጡታል ። ስለዚህ ከአሁን በኋላ መሣፍንቶቹ ለቴድ ገበሩ ማለት አንገታቸዉ ላይ ገመድ አስገቡ ማለት ነዉ፤ በዉስጣቸዉ ያለዉ ጭሰኛ “የባላባትነት ስረዓት ፈረሰ” እያለ እየጨፈረ ወጣ ማለት ነዉ /የህልዉና ጉዳይ ነዉ ማለት ነው/ ። መሳፍንቶቹ እንደለመዱት እኛ ባላባት ነን፣ እንበልጥሀለን፣ አርፈህ ተቀመጥ ብለዉ ጭሰኛዉን መናገር አይችሉም ማለት ነዉ ። ስለዚህ ወይ ቴድ ወይ መሳፍንቶቹ መጥፋት ነበረባቸዉ ።

ቴድም አማራጭ አልነበረዉም ።እንደ ትልቁ ራስ አሊ አሻንጉሊት ንጉስ እንዳያስቀምጥ ቸኩሎ እራሱ ንጉስ ሆኗል ። ትልቁ ራስ አሊ አሻንጉሊት ንጉስ ያስቀመጠዉ ወዶ አይደለም ። የህዝቡን ኋላ ቀር አመለካከት በስልት ለመያዝ ስለፈለገ ነበር ። ከላይ የባላባትነትን ስርዓት አፍርሶ ከታች ህዝቡን በባላባት ስርዓት መቆጣጠር ፈፅሞ አይቻልም ። አማራጮቹ 3 ብቻ ነበሩ ።1ኛ የባላባትነት ስረዓትን ከነአካቴዉ ከላይ እስከ ታች አጥፍቶ ህዝቡን በሹመኞች መምራት፣ 2ኛ የዘር መበላለጥን ከላይ እስከ ታች ጠበቆ የባላባትነት ስርዓትን ማስቀጠልና 3ኛ እንደ ትልቁ ራስ ዓሊ የነጋሲ ዘር ያለዉ መጋረጃ /ኮፍያ/ ማስቀመጥ ነበሩ ። 3ኛዉ ምርጫ ለቴድ አይሆንም፤ እራሱ ሮጦ ንጉስ ስለሆነ አሻንጉሊት ንጉስ ማስቀመጥ አይችልም ፡ 2ኛዉ ምርጫ ደግሞ እራሱ ስልጣን

ካለቀቀ በስተቀር አይሆንም ። 1ኛዉ ምርጫ ይቻላል፤ ነገር ግን 1ኛዉን ምርጫ ለማስፈፀም መጀመሪያ የባላባቶችን አመፅ መቆጣጠር ያስፈልጋል፤ ይህ ነበር ችግሩ ። እናም ቴድ አማራጭ ስላልነበረው እየተመናመነ ላለዉ ጦሩ የእቴጌ መነንን መሳሪያ እያስታጠቀ ወደ አንድ ቦታ ዘምቶ ለመቀጣጫ እያለ እጃቸዉን ቆርጦ ሲመጣ ሌላ ቦታ ያምጻሉ ። ሰራዊቱም እጅጉን እየተመናመነ መጣ ።

ቴድ የመሣፍንቶቹ አመፅ ከአቅሙ በላይ ሲሆን ከካህናቱ ጋር ተጋጠመ ። ካህናቱ አመፁን ማረጋጋት አለባቸዉ፣ አመፁን ለማቆም እየሞከሩ አይደለም በሚል ግምት የሚከተለዉን ህግ አወጣ ።

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ቃል በቃል አስነብባችኋለሁ ።

1. ‘‘በመጀመሪያ ከጥንት ጀምሮ ከ24 እስከ 500 የሚደርሱ ካህናት ለየአድባራቱ አገልግሎት ይመደቡ የነበረዉን በመሻር ለአንድ ቤተክርስትያን 2 ቄስና 3 ድያቆን ብቻ እንዲያገለግል ሲያደርጉ፤ የቀረዉ አገልጋይ በምርት ተግባር ላይ ተሰማርቶ እራሱ ሰርቶ እንዲተዳደር አደረጉ ።
2. ለየአድባራቱ በርስትነት የተሰጠዉ መሬት ተነጥቆ ለወታደሩ እንዲከፋፈል አደረጉ’’ ይላል ።

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ቀጥለውም፣ ‘‘በተለይ የቤተክህነት ሰዎች እብድ ሆኑ ። ከጳጳሱ ከአቡነ ሰላማ ጋርም ሀይለኛ ግጭት ዉስጥ ገቡ ። የቃላት ምልልሱ ከጳጳሱ ጋር እየተካረረ በመሄዱም ተሰዳደቡ ። አፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተቆጥተዉ “ጳጳሱን ከሴቶች ጋር በስዉር ሲወሰልት አይቸዋለሁ” በማለት ራሳቸዉን ምስክር አድርገዉ አቀረቡ ። በዚህ ጊዜ ጳጳሱ እጅግ ተበሳጭተዉ ‘’ልዑል እግዚያብሄር በሚያመጣዉ መቅሰፍት ይቅሰፍህ፣ ከከዳተኛዉ ይሁዳ ጋር እድል ፋንታህ ይሁን” ብለዉ ተራገሙ ። አፄ ቴዎድሮስ በእርግማኑ /በተለይ ከከዳተኛዉ ጋር በምትለዉ ቃል/ እጅግ ተናደዉ አቡነ ሰላማን አሰሩና አድባራቱንና ገዳማቱን ማፍረስ ጀመሩ’’ይላል ።

ቴድ አመፁን አስቁሙልኝ ብሎ ለካህናቱ አልነገራቸውም ። ቴድ አመፁን አስቁሙልኝ ብሎ ለካህናቱ ግልፅ መሆንን እንደ ሽንፈት ነበር የቆጠረዉ ።

እናም ካህናቱን ሳሰቃያቸዉ አመፁን ያስቆሙታል በሚል፤ ግልጽነት የሌለዉና እልህ የሚያጋባ አካሄድን ተከተለ ። ካህናቱን ግልጽ ሆኖ አመፁን አረጋጉልኝ ቢላቸዉ ኖሮ፣ እንደማይሳካ ቢያዉቁትም መሞከራቸዉ አይቀርም ነበር ።

ቴድ ጳጳሱን ካሰሯቸዉ በኋላ ካህናቱም አመጹን ያቀጣጥሉት ጀመር ። በየግዛቱ አምጻዉ ላሉ የወሎ መሳፍንቶች በተለይ ለዋግሹም ስዩም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ምቹ አጋጣሚ ተፈጠረላቸዉ፤ በቴድ ቅዠትም መሳቅ ጀመሩ /ካህናቱ ምንም አላደረጉትም ነበር/ ።

ወደ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ስንመለስ ‘‘ቴድም ነገሩ ሁሉ ከቁጥጥራቸው ዉጭ እየሆነ ሲመጣ ቁጣቸዉ ገንፍሎ አሁንም ካህናቱን እጣን ጠባሽ፣ ሬሳ መሪ፣ ራሱን ታጣቂ፣ ወገቡን ሰባቂ… እያሉ ይዘልፏቸዉ ጀመር ። በርካቶችን ወደ ገደል አስወረወሯቸዉ ። ብዙዎችንም እሳት አንዲደዉ ወደ እሳት ጨመሯቸዉ ። የቀሩትንም በጦር አስወጓቸዉ ይልና፣

ይህን ሁሉ ግፍ በካህናቱ ላይ ቢፈፅሙም የመሳፍንቱ አመፅ እንኳን ሊቆም እየባሰበት ሄደ ። አፄ ቴዎድሮስም አመፁን መቋቋም ተሳናቸዉና የጎንደር ቤተመንግስትን ለመልቀቅ ተገደዱ ።እቃቸዉን ጠቅልለዉ ይዘዉ ሄደዉ መቀመጫቸዉን ደብረ ታቦር አደረጉ’’ ይላል ።

ከዚህ በኋላ የሀገሪቱ የፖለቲካ ቁልፍ የሰቆጣዉ ዋግሹም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ እጅ ዉስጥ ገባ ። ቴድ ወደ ደብረ ታቦር ሲያፈገፍግ ሁሉንም የጦር መሳሪያና እስረኞቹን ይዞ ነበር ። ዋግሹም ጎበዜም /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛም/ ቴድን ዙሪያውን ከቦ እየተከታተለ ግዛቶቹን ሁሉ ነጥቆ በደቡብ ወሎዋ መቅደላ ብቻ እንዲወሰን አደረገው /ዋግሹም የሰቆጣ አካባቢ የማዕረግ ስም ነው/ ።

ለዚህም ነዉ እንግዴህ እቴጌ ተዋበችን እንደ ዋና ቴድን እንደ ተጨማሪ /አጋዥ/ ለማድረግ የምንገደደው ። በእርግጥ የፖለቲካውን ስራ ሙሉ በሙሉ ለቴድ ለቃለት ስለነበር እሱ ነበር አድራጊ ፈጣሪው ። ነገር ግን ተዋበች ባልኖረች ጊዜ ቴድ ንጉስ ሆኖ መቀጠል አልቻለም፤ መጀመሪያም ዝም ያሉት እሷ ስላስጠጋችው ነበር ማለት ነው ። ምክንያቱም እሷ ከሞተች በኋላ ወዳውኑ በሚሰነዘሩበት የግድያ ሙከራዎች ምክንያት ጭንቀት ውስጥ ገባ፣ ቤተመንግስቱንና መላውን ግዛቱንም አስለቀቁት ። ስለዚህ ቴድን ያነገሰችው

እሷ ነበረች ማለት ነው ። እናም የቴድ መንግስት የቆመዉ እሷ እስካለችበት ጊዜ ድረስ ብቻ ከሆነ ዋናዋ እሷ ነበረች ማለት ነዉ ። ልክ በዘመነ መሳፍስት ጊዜ መንግስቱ የሚቆመዉ በተቀባው በአሻንጉሊቱ ንጉሱ ላይ ሳይሆን ባነገሰው መስፍን ላይ ነበር ። አሻንጉሊት ንጉሱ ኖረም አልኖረም ችግር የለዉም፤ ካስፈለገ አሻንጉሊት ንጉሱ ሊቀየር ይችላል ። አሻንጉሊት ንጉሱ እንደተቀባ ነግሶ የሚኖረው ደግሞ ያነገሰው መስፍን እስካለ ድረስ ብቻ ነበር ።

የእነ ቴድንም ጉዳይ ስናየዉ ከተዋበች ይልቅ ቴድ ባይኖር ይሻል ነበር ። ቴድ ባይኖርም ሰራዊቱ አይበተንም ነበር ። መሳፍንቶቹም ለእቴጌ ተዋበች መገበራቸዉን ይቀጥሉ ነበር ። ስለዚህ ምን ይሻላል? አሻንጉሊቱ ማን ይሁን? እርግጥ ነዉ ቴድ አሻንጉሊት መሆንም አይችልም /የነጋሲ ዘር የለዉም/ ። ተዋበች ከሞት ስላዳናትና በዘመኑ የነገስታት ልጆች የእናትየአባትን ስልጣን ለመውረስ ይሽቀዳደሙ ስለነበር ነው ቴድን እዚህ ደረጃ ላይ ያደረሰችው ። እናም ቴድ እቴጌ ተዋበችን ተጠግቶ ነበር ነግሶ የኖረዉ ማለት ነው /ልክ አሻንጉሊቱ ንጉስ ወራሹን መስፍን ተጠግቶ ነግሶ እንደሚኖረዉ/ ። አሻንጉሊቱ ንጉስ ነግሶ /ተቀብቶ/ የሚቆየዉ ደግሞ ያነገሰዉ መስፍን እስካለ ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር ። ቴድም ነግሶ /ተቀብቶ/ የኖረዉ ተዋበች እስካለች ጊዜ ድረስ ብቻ ነዉ ። ስለዚህ ከመስፈርቱ አንፃር መሳፍንቱን /ገባሩን/ መከተል ስላለብን፣ የግድ ቴድን ሙሉ በሙሉ አሻንጉሊት ንጉስ ለማለት ባይቻልም የእቴጌዋ ረዳት /ኢጋዥ/ ለማድረግ እንገደዳለን ። ለዚህም ነዉ ቴድ ከእቴጌ መነን እጅ ወጥቶ አያዉቅም የሚባለዉ ።

እንግዲህ ከላይ እዳየነው ተዋበች ከሞተች በኋላ የየጁዉ ጦር እየሟሸሸ መጥቶ ከ150ሺ ወደ 10ሺ በመዉረዱና ቴድ ባላባት ስላልሆነ ሁሉም መሳፍንቶች መገበር አቁመዉ ቴድን ቤተመንግስቱን አስለቅቀዉ ለዋግሹም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ መገዛት ጀመሩ ። ቴድም የእንግሊዞች መምጣት ድረስ ወሎ መቅደላ ላይ መሽጎ ነበር የሚኖረዉ ። ግዛቱም ከሁለት አዉራጃዎች ማለትም ከበጌምድርና ከዋድላ ደላንታ አይበልጥም ነበር ።

ሁለት ንጉስ ተቀብቶ ንጉሰ ነገስት መባል ስለማይቻል ነዉ እንጂ ተዋበች ከሞተች በኋላ አገሪቱን ያሽከረከራት የነበረዉ ዋግሹም ጎበዜ ነበር /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ። ዋግ ሹም ጎበዜ፣ ወሎ መቅደላ ላይ መሽጎ የሚኖረውን አፄ ቴዎድሮስን በትንሽ መስዋእትነት ለመያዝ፣ መሳሪያውን እስከሚጨርስ

ድረስ ብቻ ነበር የሚጠብቀው፤ ለዚያም ነበር ቴድ መሳሪያ የማሰራት ትንቅንቅ ውስጥ የገባው ። እንግሊዞች ደግሞ ሁሉም መረጃ /information/ ነበራቸው ። ቴድ አሁን መንግስት አይደለም፤ ቤተመንግስቱንና መላውን ግዛቱን ለቆ ወሎ መቅደላ አምባ ላይ መሽጎ ነዉ የሚኖረዉ ። በፊት መንግስት በነበረበት ሰዓት ባለሙያ ጠይቋቸው ቢሆን ኖሮ ምናልባት ሊልኩለት ይችሉ ነበር፤ እሱ ግን በፊት ሰላም በነበረበት ሰዓት ይህን መሳሪያ የማሰራት ጉዳይ አስቦት አያውቅም፤ አሁን ግን መንግስት ላልሆነና ገና እንግሊዞችን የጦር መሳሪያ አሰርቼ ወደ ቤተመንግስቴ እመለሳለሁ ብሎ ተስፋ ላደረገ ቡድን ባለሙያ ሊልኩ አይችሉም ማለት ነው ። አሁን ሀገሪቱን እያሽከረከረ ያለዉ ዋግሹም ጎበዜ የሚባል ነዉ ። ንጉሰ ነገስቱ /ቴድ/ ትግሉን እስካላቆመ ድረስ ሁለተኛ ሰዉ ተቀብቶ ንጉሰ ነገስት መባል ስለማይቻል ነዉ እንጂ ሀገሪቱን በበላይነት እያስተዳደረ ያለዉ ዋግሹም ጎበዜ ነዉ ። እናም እንግሊዞች ይህን ስለሚያውቁ ለአንድ መንግስት ላልሆነና ገና እንግሊዞችን የጦር መሳሪያ አሰርቼ ወደ ቤተመንግስቴ እመለሳለሁ ብሎ ተስፋ ላደረገ ቡድን ባለሙያ ሊልኩ ስለማይችሉ ነበር፣ ዜጎቻቸውን በማታለል ለማስፈታት ሲሞክሩ የነበረው ። እንግሊዞች ዜጎቻቸውን ለማስፈታት እንደት ሲያታልሉት እንደነበር ስንደርስበት በአፄ ቴዎድሮስ ስር እናየዋለን ።

የእንግሊዝን ጦር እየመሩ የመጡት ጀኔራሎች እዚሁ መንግስት ሆነው የመቀጠል ፍላጎት ነበራቸው ። ነገር ግን ሀገሪቱ ከገመቱትም በላይ ጠንካራና ከአቅማቸው በላይ ሆና ነው ያገኟት ። ሁሉም መሳፍንቶች በወሎው ዋግሹም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ዙሪያ እንደተሰለፉና ሀገሪቱ ጠንካራ መንግስት እንዳላት በአይናቸው አረጋገጡ ።

እንግሊዞች ወሎ መቅደላ ላይ መሽጎ የሚኖረውን የነቴድን ቡድን በመምታት እስረኞቻቸውን ካስፈቱና ቴድም ከሞተ በኋላ ለተወሰኑ ቀናት የሀገሪቱን ሁኔታ ማስተዋል ጀመሩ፤ ነገር ግን የቴድ መሞት ምንም ለውጥ አላመጣም፤ መጀመሪያ የነበራቸዉ መረጃ /information/ ትክክል እንደነበር በአይናቸው አረጋገጡ ። ወሎ መቅደላ አምባ መሽገዉ ይኖሩ የነበሩት ቴድ፣ ምንም አይነት ሀገራዊ ሚና እንዳልነበራቸዉና ስልጣናቸዉም ከሚመሩት ቡድን የሚያልፍ እንዳልነበር አረጋገጡ ። በተቃራኒው ዋግሹም ጎበዜ የሚባል ከአቅማቸው በላይ የሆነ ጠንካራ መንግስት እንዳለ አስተዋሉ ።

የእንግሊዝ ጀኔራሎች ቀጥለውም የአፄ ቴዎድሮስ የነበረውን ግዛት ስፋት ማጥናት ጀመሩ፤ ነገር ግን የአጼ ቴዎድሮስ ግዛት እጅግ ጠባብ ሆነባቸው /እዚሁ መንግስት ሆነው የሚቀጥሉ ከሆነ ዋግሹም ጎበዜን መዋጋትና ግዛታቸውን ማስፋት የግድ ሆነባቸው/ ። እንግሊዞች ቀጥለውም የራሳቸዉንና የዋግሹም ጎበዜን ሁኔታ ማመዛዘን ጀመሩ ። በስንቅ ስለሆነ የመጡት በማያዉቁት አገር ዉስጥ ተከበዉ ከ60ሺ በላይ በሚሆነዉ የዋግሹም ጎበዜ ጦር መሀል ላይ ነበር የሚገኙት ። እናም ምንም ሌላ ነገር ሳይፈልጉ በፍጥነት ሀገሪቱን ለቀዉ ወጡ /የቴድ ግዛት እጅግ ጠባብ ስለሆነባቸው ትተውት ወጡ እንጂ በቴድ እጅ ያገኟቸውን ቅርሶች ግን ጠራርገው ወስደዋል/ ። በዚህ ምክንያት እንግሊዞች ዋግሹም ጎበዜን በጣም ስለጠሉት አንድት እንኳን የጦር መሳሪያ አልሰጡትም፤ እንግሊዞች ከጎበዜ ጋር በቃላትም ሆነ በአካል ተገናኝተው አያውቁም ። ቴድም የተሻለ የጦር መሳሪያ አስመጥቶ፣ ካልተቻለ ደግሞ አሰርቶ ዋግሹም ጎበዜን ለማንበርከክና ወደ ቤተመንግስቱ ለመመለስ ያደረገዉ ጥረት ሳይሳካ ቀረ ።

ስለዚህ ዋግሹም ጎበዜ ሀገሪቱን ከእንግሊዝ ጀኔራሎች ቅኝ ግዛት አድነዋታል ማለት ነው ። ነገር ግን ስማቸው ተነስቶ አያውቅም ምክንያቱም ወሎ ነዋ! ወሎ ገራገሩ ስለሆነ ነው /ጀግና ሰው ገር ነው የሚለው አባባል ታሪክ ከመጠበቅ ጋር አይገናኝም/ ። የጎንደርና የጎጃም የኪነጥበብ ሰዎች ደግሞ ጎበዜ ከተነሳ ቴድ ትርጉም አይኖረውም፤ ስለዚህ ጎበዜ መረሳት አለበት ነው ። ምክንያቱም ዋግሹም ጎበዜ /አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ካልተረሳ፣ ቴድን ከስልጣኑ ያወረደው /ቤተመንግስቱንና መላዋን ሀገሪቱን ያስለቀቀው/ ዋግሹም ጎበዜ እንጂ እንግሊዞች እንዳልሆኑ ይታወቃል ማለት ነው ፡ ፡ እናም የእንግሊዝ ጀኔራሎች አዝነውልን እንደወጡ ይቆጠር እንጂ ቴድ በጎበዜ ተሸንፎ እንደነበርና እንግሊዞችም ጎበዜን ፈርተው እንደወጡ መታወቅ የለበትም ነው /የእንግሊዝ ጀኔራሎች ሌሎች የአፍሪካ አገሮችን አሳራቸውን እያበሉ እኛን ሊያዝኑልን አይችሉም፣ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ሁኔታ ስለነበር ነው/ ። በእርግጥ እስከ አሁን ድረስ የእንግሊዝ ጀኔራሎች አዝነውልን ነው የወጡት ተብሎ የተፃፈ የለም /አዝነውልን እንደማይወጡ ይታወቃል/ ። ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ እንግሊዞች በፍጥነት የወጡበት ምክንያት ተፅፎ አያውቅም ። የኢትዮጵያ ህዝብም እስከ አሁን ድረስ እንግሊዞች ለምን በፍጥነት እንደወጡ አያውቅም፣ ምክንያቱ ደግሞ ዋግሹም ጎበዜ /አፄ

ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ካልተረሳ፣ ቴድን ቀድሞ ከስልጣኑ ያወረደው /ቤተመንግስቱንና መላዋን ሀገሪቱን ያስለቀቀው/ ዋግሹም ጎበዜ እንጂ እንግሊዞች እንዳልሆኑ ይታወቃል ማለት ነው ። እናም የአፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ ታሪክ፣ እንዲጠፉ ከተደረጉ የሀገራችን ታሪኮች መካከል አንዱ ነው ማለት ነው /ከጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ታሪክ በሙሉ ጠፍቶ የበላይ ዘለቀና የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ብቻ መሆኑ አይቀርም/ ።

በጀኔራል ሮቤርቶ ናፒየር የተመራዉ የእንግሊዝ ጦር ሰራዊት ይህ ቡድን በመሸገባት የመቅደላ ተራራ ላይ ተከማችተዉ ያገኟቸዉን የየጁና የሸዋ ነገስታት የወርቅ ዘዉድ፣ የወርቅ ፅዋ፣ የእቴጌ መነንን የወርቅ አክሊል፣ በሳጥን የተሞሉ ወርቆችን፣ በወርቅ የተለበጡ ጋሻዎችን፣ በወርቅ የተለበጡ ጸናጽሎችንና የበርካታ አድባራትን ዉድ ቅርሶች በደላንታ ሜዳ ለእንግሊዝ ዜጎች ጨረታ አቅርበዉ ከተቀራመቷቸዉ በኋላ በፍጥንት ኢትዮጵያን ለቀዉ ወጡ ። የነቴድን ጉዳይ ስንደርስበት እንደገና በጥልቀት እናየዋለን ።

እናም የአማራ ታሪክ ሙሉ በሙሉ የወሎ ታሪክ ነው ማለት ነው ። ከላይ እንዳስቀመጥነው፣ ወሎ ባይኖርም ኢትዮጵያ አንዳንድ የአገር ዉስጥ ታሪኮችን አታጣም /አፄ ዮሃንስና ግራኝ አህመድ/፤ ነገር ግን ወሎ ባይኖር ኖሮ አማራና አፍሪካ ታሪክ አይኖራቸዉም ነበር ። የአድዋ ድል፣ የላሊበላ ገዳማትና የጎንደር ቤተመንግስትን የመሳሰሉ የአፍሪካ ቅርሶችና የአለማችን ትልቁ ሰርግ፣ የአለማችን ምቹ እስር ቤት፣ የአፍሪካ ትልቁ የሐይማኖት ጉባኤ … ወዘተ ሁሉም የወሎ ታሪኮች ናቸዉ ። በአጼ ምኒሊክ ስር በዝርዝር ተቀምጠዋል ። ለአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያ ካሰለፈችዉ 73 ሺ ሰራዊት ዉስጥ ከ67 ሺ በላይ የሚሆነዉ ሰራዊት ከወሎ የተሰበሰበ ነበር /የወሎ ባላባቶች ያመጡት ነበር፣ ከሌሎች ባላባቶች የተገኘው 6ሺ ሰራዊት ብቻ ነበር/ ። የአድዋ ድል የሁሉም ብሔረሰቦች ድል የሚሆነዉ ወሎ የሁሉም ብሄረሰቦች ድብልቅ/collection/ ስለሆነ ብቻ ነዉ ። በአፄ ምኒሊክ ስር እናየዋለን ።

አማራ ከየት መጣ? ኢትዮጵያን ማን ፈጠራት?

ስለ አማራ ብሄር አመጣጥ ከአፄ ሚኒሊክ በኋላ የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ በሚለው ርዕስ ስር ያለውን ስታነቡ ይጋችኋል /አሁን ላይገባችሁ ይችላል/፤ ሆኖም ለጊዜው እንድሆነን ቅንጭብጭቡን እንየው ። አማራን ማን

ፈጠረዉ? አማራ ከየት መጣ? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ አለቃ ታዬ "የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ "አማራ ከወዴትም አልመጣም፤ ጥሩ የላስታ ወታደር፣ ከያይነቱ /ከየብሄሩ/ የተጠራቀመ፣ ኃይለኛ፣ ግፈኛ፣ አድመኛ፣ እዉቀት ያለዉ፣ ጨካኝ፣ ጭፍራ ነዉ" ብለዉታል /በላስታና አካባቢው የሚኖሩ ህዝቦች አገዎች ናቸው/ ። ቀጥለዉም አማርኛ ላስታ ዉስጥ የተፈጠረና ከዕብራይስጥ፣ ከሳባ ከአረብ፣ ከግዕዝ፣ ከትግርኛ የመጣ መሆኑን ገልፀዋል /አማርኛ ከአረብኛ የመጣ መሆኑን ላማሳየት ያህል ፡ - ሀምሲ-ሀምሳ፣ አርባ-አርባ፣ አሽራ ዋህድ-አስራ አንድ፣ ዋህድ- አንድ፣ ጀነትገነት፣ አከቡር- አክብር፣ መዲና-መዲና፣ ተወከል-ወኪል …ወዘተ/ ። እዚሁ መፀሀፍ ላይ "በንጉስ ላሊበላ ዘመን አማራ የተባለ ወታደር በዋድላ ደላንታ፣ በበጌምድርና በሣይንት ተመሰረተ" ይላል ። ስለዚህ አማራ ማለት የአንድ ክፍለ ጦር መጠሪያ ሥም ነበር ማለት ነዉ /ባሩድ ክፍለ ጦር እንደሚባለው ማለት ነው፣ አማርኛ፣ ባሩድኛ/ ።

ስለ አማራ አፈጣጠር ሌሎች ፀሀፍት የፃፉትን አንድ ላይ ጨምቀን ስናየዉ ፡ - አማራ የሚባል ብሔር ከዛግዌ በፊት አልነበረም፣ አማርኛ ቋንቋን የፈጠሩት የዛግዌ /ዘአገው/ ወታደሮች ናቸው ። አሮጌዉ አማርኛ /ትግርኛ/ና አዲሱ አማርኛ/ላስታኛ/ የመጡት ከሳባ፣ ከአረብኛና ከግዕዝ ነዉ ። አረብኛ የግዕዝ አባት ነው ። አዲሱ አማርኛ /አማርኛ/ ላስታ ዉስጥ "አራዳነን" በሚሉ የእነ ንጉስ ላሊበላ ወታደሮች አማካኝነት የተፈጠረ ነዉ ። በዘመኑ ከወታደር የበለጠ አራዳ ነኝ የሚል ሰው ስላልነበር አማርኛ አራዳነን የሚሉ ሰዎች ሁሉ መነጋገሪያ እየሆነ መጣ ። ይህ ላስታኛ /አማርኛ/ ቋንቋ ቀስ በቀስ ከላስታ እስከ መራቤቴ ዶባ ድረስ ተስፋፋ ።

ለረጅም ዘመናት /333 ዓመት/ ያህል የቆየዉ የዛግዌ ስርወ መንግስት ግዛቶች የነበሩት በሙሉ ግዕዝ /አረብኛ/ ተናጋሪ ሆነዋል /አዲስ አበባ ገና 135 አመቷ ነው/ ። የዛግዌ ግዛት የነበሩት በአሁኑ አጠራር አማራና ትግራይ ናቸዉ ። በአሁኑ ወቅት ትግሬዎች የአሮጌዉ አማርኛ /ትግርኛ/ ተናጋሪ ሲሆኑ አማራዎች ላስታኛ /አማርኛ/ ተናጋሪዎች ናቸዉ ። ይህ አማርኛ ቋንቋ ከላስታ እስከ መራቢቴ ዶባ ድረስ ተስፋፋ ። ከወሎ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ አማራ የሆነዉ የጎንደር ህዝብ ነው፤ ከአፄ ሚኒሊክ በኋላ የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ

በሚለው ርዕስ ስር እንደምናየው የጎንደር ህዝብ የጥንት ቋንቋ ጋፋትኛ፣ ኳረኛና ቅማንትኛ ነበር ። በሦስተኛ ጀረጃ አማራ የሆነዉ ደግሞ የጎጃም ህዝብ ነዉ ።

ስለ ጎጃም ህዝብ ዘር እዚያዉ የአለቃ ታዬ መፀሀፍ ላይ “.... የሜጫ ልጆች ከኦሮሞ ቤት ሜጫ ተነስተዉ ለኢትዮጵያ ንጉስ ለጌታ አደሩ፤ ንጉሱም አፄ አምደፅዮን ነበር ። እሱም በመልካም ተቀብሎ በጣና ባህርና በዳሞት መካከል አገር ሰጣቸዉ ። እነርሳቸዉ ያን አገር ተቀብለዉ ያዙና ስሙን ባባታቸዉ ስም ሜጫ አሉት ። ከዚህ በኋላ ክርስትና ተነስተዉ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በተቀበሉት አገር ሁሉ ሰርተዉ ክርስቲያኖች ሆነዉ ተቀመጡ ። በአማራ ህዝብ መሀከል /በላስታዎች መካከል/ ኦሮሞኛን ፈፅመዉ አጥፍተዉ ባማርኛ ቋንቋ ብቻ ይናገራሉ” ይላል ። ከአፄ ሚኒሊክ በኋላ የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ በሚለው ርዕስ ስር እንደምናየው የጎጃም ህዝብ የጥንት ቋንቋ ኦሮምኛ፣ ሽናሽኛ፣ ወይጦኛና ጋፋትኛ ነበር ።

ጎጃም ዉስጥ ሜጫና ዳሞት የሚባሉ ወረዳዎች አሉ፣ ሜጫና ዳሞት የኦሮሞ ሰዎች ስሞች ናቸዉ ። ጂማ፣ ወለጋ፣ ወሎ፣ ጎጃም፣ ሰላሌ፣ ጉለሌ ... ወዘተ ቃላቶችም የኦሮሞ ሰው ስሞች መሆናቸው ይታወቃል፤ ከአፄ ሚኒሊክ በኋላ የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ በሚለው ርዕስ ስር እናየዋለን ። እናም አማርኛ ቋንቋ ከላስታ /ከዛግዌ/ ወታደሮች በፊት ካልነበረና የዛግዌ ወታደሮች ደግሞ ከሁሉም ብሄረሰቦች የተውጣጡ ከነበሩ አማራ የብሄረሰቦች ውህድ እንጂ ዘር አይደለም ማለት ነው ።

እናም ከዛግዌ በፊት አማራ የሚባል ብሔር አልነበረም ማለት ነው ። አማራ ማለት የላስታን ቋንቋ /አማርኛ ቋንቋን/ ቀድሞ የተቀበለና ከሁሉም ብሄረሰቦች የተውጣጣ የዛግዌ ፍጡር ነው ማለት ነው ። በሌላ አገላለፅ አማራ ማለት የላስታ ወታደሮችን ቋንቋ ቀድሞ የተቀበለ የትግሬና የኦሮሞ /የሜጫ ኦሮሞ/ ስብስብ ነው ማለት ነው ። ስለዚህ ጉዳዩ የወታደሮቹን /የላስታን/ ቋንቋ ቀድሞ የመቀበልና ያለመቀበል ጉዳይ ነው ማለት ነው ፡ ስለሆነም የአማራ ብሄር የበቀለው /ስሩ ያለው/ ወሎ ላስታ ውስጥ ነው ማለት ነው ። አሁን አማራ የሚባሉትና በአማራ ክልል ውስጥ የሚኖሩት ህዝቦች በሙሉ አማርኛ ተናጋሪና ክርስትያን የሆኑት የዚሁ የወሎ /የላስታ/ ቋንቋና እምነት እየተስፋፋ

መጥቶ ነው /በኋላ በግሸን ምክንያት ግራኝ ግማሹን የወሎ ህዝብ ወደ እስልምና ቀይሮታል/ ።

ስለዚህ አማራን ይህንን የአሁኑን ተፈጥሮውን እንዲይዝ ያደረጉት /አማርኛ ተናጋሪና ክርስቲያን እንዲሆን ያደረጉት/ ወሎዎች ናቸው ማለት ነው /በተከታታይ ስልጣን የያዙት አገው፣ ሸዋና የጁ ናቸው ማለት ነው/ ። በሌላ መልኩ ብናየውም፣ ጎጃምና ጎንደር ወደ ንግስና መጥተው የማያውቁ ከሆነና አፄ ቴዎድሮስም የነገሰው የጁን ተጠግቶ /ከራስ አሊ ጋር ተጋብቶ/ ከሆነ፣ አማራን ይህንን የአሁኑን ተፈጥሮውን ያስያዘው ወሎ ነው ማለት ነው /አገው፣ ሸዋና የጁ/ ። አሁንም በሌላ አገላለፅ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የአገው /ዛግዌ/፣ የሸዋ /ሰለሞናዊ/ና የየጁ /ዘመነ መሳፍንት/ ታሪክ ማለት ከሆነ አማራን ይህንን የአሁኑን ተፈጥሮውን ያስያዘው ወሎ ነው ማለት ነው /አገው፣ ሸዋና የጁ/ ። አሁንም በሌላ አገላለፅ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የመራተክለሐይማኖት ቤተሰቦች፣ የይኩኖአምላክ ቤተሰቦች፣ የትልቁ ራስ አሊ ቤተሰቦችና የአፄ ሚኒሊክ ቤተሰቦች ታሪክ ማለት ከሆነ አማራን ይህንን የአሁኑን ተፈጥሮውን ያስያዘው ወሎ ነው ማለት ነው /አገው፣ ሸዋና የጁ/ ። ስለዚህ አማራ የወሎ ፍጡር ነው ማለት ነዉ ። የአማራ ብሔር እድሜ ከላስታ ገዳማት እድሜ ያንሳል /አማረኛን የፈጠሩት የንጉስ ላሊበላ ወታደሮች ከሆኑና የላስታ ገዳማትንም የገነባቸው ንጉስ ላሊበላ ከሆነ የአማራ ብሄር እድሜ ከላስታ ገዳማት እድሜ ያንሳል ወይ እኩል ይሆናል ማለት ነው/ ።

ኢትዮጵያም የወሎ ፍጡር ናት፤ አንዳንዶች ኢትዮጵያን የፈጠሯት /ያቀኗት/ ጎንደርና ጎጃም ይመስሏቸዋል፤ እጅግ ስህተት ነው /የሉበትም/ ። ጎጃምና ጎንደር ኢትዮጵያን የተቀላቀሉት ከሁሉም ብሄረሰቦች በኋላ ነው /ከሐረር በኋላ ነው/ ። ወሎ ኢትዮጵያን በሚያስፋበት ወቅት ጎጃምና ጎንደር በትግሬው አፄ ዮሃንስ ስር ስለነበሩ በሀገር ማቅናቱ /ማስፋቱ/ ጦርነት ላይ አልተሳተፉም ነበር ። እንዳውም ጎጃሞች የሀገር ማቅናቱ ዋና እንቅፋት ነበሩ፤ በአፄ ዮሐንስ ግፊት ከወሎ ጋር ሦስት ጊዜ ጦርነት አድርገዋል፤ በተለይ ሁለቱ ጦርነቶች እጅግ ዘግናኝና አያሌ ጎጃሜዎች ያለቁባቸው ነበሩ ። ወሎ ኢትዮጵያን እንደት እንዳቀናት በአፄ ምኒሊክ ስር የሸዋ መስፋፋት በሚለው ርዕስ ስር በግልፅና በዝርዝር እናየዋለን ።

ወደ ርዕሳችን ስንመለስ፣ በአራተኛ ደረጃ አማራ እየሆነ የመጣዉ የአዲስ አበባ ዙሪያ ህዝብ ነዉ ። እናም የኢትዮጵያ ህዝብ ቀስ በቀስ ቋንቋዉ ብቻም ሳይሆን አዘፋፈኑም ጭምር ላስታና ሰቆጣ መሆኑ አይቀርም ።

በእርግጥ ላስታኛ ቋንቋ ከቦታ ቦት ልዩነት እያመጣ ነዉ ። ለምሳሌ የወሎና የጎጃም አማርኛ የተወሰኑ ልዩነቶች አሉት ።

ለምሳሌ ያህል ፡ -

<u>የወሎ አማርኛ</u> ፣ ምንድን ነዉ የምትለዉ?

<u>የጎጃም አማርኛ</u>፣ ምንድን ነዉ የምትል?

<u>የወሎ አማርኛ</u>፣ሰክረሀል ልበል? ።

<u>የጎጃም አማርኛ</u>፣ ሰክረሀል ልበል ይሆን? ።

<u>የወሎ አማርኛ</u>፣ ዛሬ አበበ ወደ አንተይመጣል፣ ከዚያ… ።

የ<u>ጎጃም አማርኛ</u>፣ ዛሬ አበበ ወደ አንተ ይመጣልኝ፣ ከዚያ... ።

ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ወሎ ዉስጥ “ደ” ና “ረ” ን የሚያጠብቁ ሲሆን፤ ጎጃም ዉስጥ “አልበልቶም” ና “አልጠጥቶም” ይላሉ ።

እንግዲህ ከላይ እንደምናስተዉለዉ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚነገረዉ የወሎዉ አማርኛ ቢሆንም እንደነ “ደ” ና “ረ” የመሳሰሉ ፊደሎች ላይ ልዩነት አለ ። እነኝህን ፊደሎች ወሎዎቹ እያጠበቁ የሚናገሩ ሲሆን አዲስ አበቤዎቹ ግን አያጠብቁም፤ በዘመነና በተሻለ መልኩ ያጣፍጧቸዋል ።

## <u>ወሎ የሚባሉት እነማን ናቸዉ?</u>

ወሎ በ5 ዞኖች የተከፈለ ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን የሚገኝ ቦታ ነዉ ። እነዚህም የወሎ ዞኖች ሰ/ሸዋ ዞን፣ ደ/ወሎ ዞን፣ ኦሮምያ ልዩ ዞን፣ ሰ/ወሎ ዞንና ዋግምራ ዞን ናቸዉ ።

ሰ/ሸዋ ዞን ፡ - ከደብረ ብረሃን ጫጫ ከተማ ጀምሮ እስከ ከሚሴ ያለዉን ቦታ ይሸፍናል፣ በአንድ በኩል ከከሚሴም ያልፋል /ወደ ሳይንት አቅጣጫ

ከከሚሴም ያልፋል/ ። ይህ ዞን ካፈራቸው እጅግ በርካታ ጀግኖች መካከል ፡ -

- አባ ተክለሐይማኖት /ተክልዬ/
- አፄ ሚኒሊክ /ኢትዮጵያን የፈጠሯት/
- አፄ ኃይለስላሴ /በአባቱ/
- አፄ ይኩኖ አምላክ /የሰለሞናዊ መስራች/
- አፄ ዘርያዕቆብ /የደብረ ብርሃን ቤተመንግስትን የገነባው/
- አፄ ፋሲል /የጎንደር ቤተመንግስትን የገነባው/
- ንግስት ዘውዲቱ /በአባቷ/
- ንጉስ ኃይለመለኮት /የአፄ ምኒሊክ አባት/
- ራስ መኮንን /የኃይለስላሴ አባት/
- ራስ ተሰማ ናደዉ /የልጅ እያሱ እንደራሴ/ … ወዘተ ይገኙበታል ።

ደ/ወሎ ዞን ፡ - ከከሚሴ ጀምሮ እስከ ደሴና በደሴ ዙሪያ ያሉ ወረዳዎችን ይይዛል ። ይህም ዞን እንደሌሎቹ የወሎ ዞኖች በርካታ ጀግኖችን አፍርቷል ። ይህ ዞን ካፈራቸዉ ዋና ዋና ጀግኖች መካከል ፡ -

- አቡነ ጴጥሮስ /በጣሊያን የተገደሉ /የተወለዱት ኦሮምያ ሰላሌ ነዉ
- አፄ ኃይለስላሴ /በእናቱ/
- ወ/ሮ የሺእመቤት ዓሊ/ የአፄ ኃይለስላሴ እናት/
- እቴጌ መነን 2ኛ /የአፄ ኃይለስላሴ ሚስት፣ የንጉስ ሚካኤል የልጅ ልጅ/
- ልጅ እያሱ
- ልዕልት ወርቂት /አፄ ምኒሊክን የመነሻ ሰራዊት ሰጥተዉ ያነገሱት/
- ንግስት ዘውዲቱ /በእናቷ/
- አብቸዉ በያን /የንግስት ዘዉዲቱ እናት/

- ንጉስ ሚካኤል
- አባኮስትር በላይ ዘለቀ … ወዘተ ይገኙበታል ፡፡

**ኦሮምያ ልዩ ዞን** ፡ - ይህ ዞን በከሚሴ ዙሪያ የሚገኙ ኦሮምኛ ተናጋሪ ወረዳዎችን ይይዛል ፡፡ በስተ ደቡብ ከሰ/ሸዋ ዞን ጋር ሲዋሰን በስተ ሰሜን ከደ/ወሎ ዞን ጋር ይዋሰናል ፡፡ ኦሮምያ ልዩ ዞን ጀግና አፍርቷል አላፈራም ለማለት ያስቸግራል፤ ምክንያቱም ስንነረጉረዉ ሁሉም ኦሮሞ እየሆነ ተቸግረናልና ፡፡ ከሚሴ ዉስጥ ንጉስ ነግሶም ቢሆን ኖሮ የከሚሴ ህዝብ አማራ መሆኑ አይቀርም ነበር ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ላስታኛ የዘመኑ የአራዳ ቋንቋ ስለነበር ነው /ላስታኛ አሁንም ድረስ የአራዳ ቋንቋ ሆኖ ቀጥሏል/ ፡፡

ሰ/ወሎ ዞን ፡ - ይህ ዞን በወልዲያ ዙሪያ ያሉ ወረዳዎችን ይይዛል ፡፡ ይህ ዞን የኢትዮጵያን አብዘሀኛውን ታሪክ የሚሸፍኑትን ሁለት ወረዳዎች ማለትም ላስታና የጁን ይዟል ፡፡

ላስታ

ይህ ወረዳ የዛግዌ ስረዎ መንግስት መስራች ነዉ ፡፡ የዛግዌ ስረወ መንግስት ለ 333 ዓመታት ያህል ቆይቷል፣ አዲስ አበባ ገና 134 ዓመቷ ነው ፡፡የተለዩ ስራ ከሰሩት ጀግኖች መካከልም ፡ -

- አፄ ላሊበላ /የቅዱስ ላሊበላ ገዳማትን የገነቡ/
- አፄ መራ ተክለሐይማኖት /የዛግዌ ስርወ መንግስት መስራች/
- አፄ ነአኩቶለአብ … ወዘተ ይገኙበታል ፡፡ <u>የጁ</u>

ይህ ወረዳ መንግስትን እጅግ ከባድ በሆነ ጦርነት ገርስሶ ዘመነ መሣፍንትን /ዘመነ የጁን/ በመመስረት የጎንደር ቤተመንግስትን ለ74 ዓመታት ያህል ተቆጣጥሮ ሀገሪቱን መርቷል /ቴድ ከራስ አሊ ጋር ተጋብቶ እስከከዳበት ጊዜ ድረስ ማለት ነው/ ፡፡ የጁዎች ሰለሞናዊ ስረወ መንግስትን ስልጣን መንጠቅ የቻሉ ብቸኛ ህዝቦች ናቸው /ላስታዎች ከሰለሞናዊ ጋር ጋብቻ ነበራቸው/ ፡፡ አንዳንዶች ዘመነ መሳፍንትን መጥፎና የማያስፈልግ አድርገዉ ፅፈዋል ፡፡ እጅግ ስህተት ነዉ፤ የህዝቡን ኋላቀር አመለካከት በመስበር የሸዋና የላስታ ንጉስዊ ዘር የሌለዉ ሰዉ ሀገር መምራት እንደሚችል አሳይቷል ፡፡ አሻንጉሊት ንጉስ ከላይ እንደ መጋረጃ /ኮፍያ/ ለህዝቡ እንዲታይ አድርጎ

በማስቀመጥ መግዛት ማለት ነዉ፤ በወቅቱ የነበረዉ አመራጭም ይህ ብቻ ነበር ። ይህን ያገዛዝ ስልት እንግሊዞች እስከአሁንም ድረስ እንደ ቅርስ ጠብቀውት ይገኛሉ /ከጠቅላይ ሚንስትሩ በተጨማሪ ምንም አይነት ፖለቲካዊ ሚና የሌላት ንግስት ያስቀምጣሉ/ ።

ይህ ወረዳ ካፈራቸዉ ዋና ዋና ጀግኖች መካከል ፡ -

- እቴጌ ጣይቱ ብጡል /የአፄ ምኒሊክ ሚስት/
- እቴጌ መነን 1ኛ /አፄ ቴዎድሮስ ተጋብቶ የከዳቸዉ፣ የራስ አሊ እናት/
- ትልቁ ራስ ዓሊ /የዘመነ መሳፍንት መስራች ጀግና፣ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለደ ነው/
- የትልቁ ራስ አሊ ወንወድም ራስ አሊጋዝ
- የትልቁ ራስ አሊ የእናቱ ወንድሞች ራስ አስራትና ራስ ወ/ገብርኤል
- የትልቁ ራስ አሊ ሌላ ወንድም ራስ ጉግሳ /የጎንደሯ ደብረ ታቦር ከተማ መስራች/
- የራስ ጉግሳ ልጅ ራስ ይማም
- የራስ ጉግሳ ሌሎች ልጆች ራስ ማርዬና ራስ ዱሪ
- የራስ ማራዬ ልጅ ትንሹ ራስ ዓሊ /የእቴጌ መነን ልጅ/
- ራስ ወሌ /የንግስት ዘዉዲቱ ባል/
- እቴጌ ተዋበች /የአፄ ቴዎድሮስ ሚስትና የትንሹ ራስ አሊ ልጅ፣ የእቴጌ መነን የልጅ ልጅ/ …ወዘተ ይገኙበታል ።

**ዋግህምራ ዞን፤** ይህ ዞን በሰቆጣ ዙሪያ ያሉ ወረዳዎችን ይይዛል ። በስተ ደቡብ የሰ/ወሎ ዞን ሲያዋስነዉ በስተ ሰሜን የትግራይ ክልል ያዋስነዋል ። ይህ ዞን ካፈራቸዉ ዋና ዋና ጀግኖች መካከል ፡ -

- አፄ ተክለጊርጊስ 2ኛ (ዋግ ሹም ጎበዜ) /ተዋበች ከሞተች በኋላ አጼ ቴዎድሮስን ቤተመንግስቱንና መላውን ግዛቱን ያስለቀቀዉና እንግሊዞችን ከሀገር በፍጥነት ያስወጣቸው/

- ዋግ ስዩም ጓንጉል ወዘተ ይገኙበታል።

ያዉ ከላይ የዘረዘርናቸዉ ጀግኖች በጣም ታዋቂዎቹን ብቻ ነዉ እንጂ ከአፄ ዮሃንስ፣ ከግራኝ አህመድና ከመለስ ዜናዊ ዉጭ ያሉት ነገስታት በሙሉ የወሎ ሰዎች ናቸዉ ።

ያ ወሎ የሚባል ገደል ዉስጥ ያልተፈፀመ ነገር የለም፤ የወሎ ሰዎች ያላሳለፉት ነገር የለም ። በአድዋ ጦርነት ጊዜ ከ10ሺ በላይ ኢትዮጵያዊያን ያለቁ ሲሆን ከሞላጎደል ሁሉም የወሎ ሰዎች ናቸው ። ግራኝ ባደረገዉ ጭፍጨፋ ሁሉንም መሰዋዕትነት የከፈሉት የወሎ፣ የትግራይና የሸዋ ኦሮሞ ወጣቶች ብቻ ናቸዉ፣ የከሚሴ ኦሮሞዎች ወሎ ስለሆኑ ነው /ወሎ ከግራኝ በፊት በሙሉ ክርስቲያን እንደነበር ይታወቃል/ ። በወሎ ሰራዊት እልህ ምክንያት ግራኝ በወሎ ህዝብ ላይ ወደር የሌለዉ ጭካኔ ፈፅሞባቸዋል ። ግራኝ ግሸን አምባን እይዛለሁ አትይዝም ትንቅንቅ ዉስጥም አያሌ የወሎ ሰዎች አልቀዋል /ከግራኝ ጋር የተካሄደውን ጦርነት የእርስ በርስ ጦርነት አድርጎ መውሰድ አይቻልም፣ ምክንያቱም

ሐረር የዛኔ የኢትዮጵያ አካል አልነበረችም/ ። ግራኝ ቤተመንግስቱን ጎጃም ጣና ሐይቅ አካባቢ ‘’ደምቢያ’’ ላይ አድርጎ ኢትዮጵያን ለ15 አመት ያህል ሲገዛ፣ 12ቱን አመት ሙሉ የግራኝ ሰራዊት ወሎ ዉስጥ ተከማችቶ የአለማችን ቁጥር አንድ ምቹ እስር ቤትና የነገስታቱ ንብረት ማከማቻ /ግምጃ ቤት/ የነበረችውን ግሸን አምባን ለመያዝ የማያቋርጥ ትንቅንቅ ሲያደርግ ነበር የኖረዉ፤ በዚህ ምክንያት አንዳንድ የወሎ ቦታዎችም ሳይቀር ስማቸውን ቀይረዋል /ኮምቦልቻ ሐረር አለ ወሎም አለ፣ ቆቦ ሐረር አለ ወሎም አለ ወዘተ/ ።

ወሎዎች ለኢትዮጵያ ያልሆኑት ነገር የለም፤ በአፄ ምኒሊክ፣ ሀገር በሚፈጠርበት ጊዜ /በሀገር ማስፋፋት ጊዜ/ ይብዛም ይነስም ኢትዮጵያ ዉስጥ የወሎ ሰዎች ደም ያልፈሰሰበት ተራራ፣ ሜዳና ኮረብታ አይገኝም ። ወሎዎች ብቻቸውን ያለማንም ረዳት ይችን የምታክል እጅግ ሰፊ ሀገር ፈጥረውና ተከላክለው እዚህ ማድረስ ችለዋል ። ከደርጎ- ኢህዴግ ጦርነት ውጭ ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱ ጦርነቶች በሙሉ የወሎ ህዝቦች ያካሄዷቸው ጦርነቶች ብቻ ናቸው ። ጎጃምና ጎንደር በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ተሳትፎ

አድርገው አያውቁም፤ መፅሀፉን አንብበን ስንጨርስ በጣም ግልፅ ይሆናል /ሸዋ፣ የጁ፣ ላስታ፣ ወረሂመኖ/ ።

ስለሆነም ወሎ ማለት የሀገር ግንድ፣ የአማራና የኢትዮጵያ ፈጣሪ ፣ የሀገሪቱ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባህልና የኪነጥበብ መነሻ፣ የሁሉም ቤሔረሰቦች መኖሪያ (collection)

….ወዘተ ማለት ነዉ ።

በተለይ የክርስትና እምነት መነሻዉና መሰረቱ ያለዉ እዚሁ ወሎ ዉስጥ ነዉ ። ኢትዮጵያ ዉስጥ 4 እጅግ ታላላቅ ገዳማት አሉ ። እነሱም ግሸን ደብረ ከርቤ፣ ቅዱስ ላሊበላ፣ አክሱም ፂዮንና ቁልቢ ገብርኤል ናቸዉ ። በአስደናቂነቱና በአሰራር ጥበቡ ቅዱስ ላሊበላ በጥቁር አፍሪካ ተወዳዳሪ የለዉም ። አፍሪካ ዉስጥ በጥቁሮች የተሰራ ላሊበላን የሚወዳደር ቅርስ የለም ። ነገር ግን በያዘችዉ ሀይማኖታዊ ቁም ነገር፣ ግሸን ደብረ ከርቤ ከእየሩሳሌም ቀጥላ በዓለም በሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች ። ምክንያቱም እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትና ደሙ የፈሰሰበት እዉነተኛዉ መስቀል ግማሹ እየሩሳሌም የሚገኝ ሲሆን ቀሪዉ ግማሹ ደግሞ ግሸን ደብረ ከርቤ ዉስጥ ይገኛል ። እነዚህ ሁለቱም ማለትም ግሸን ደብረ ከርቤና ቅዱስ ላሊበላ ገዳማት የሚገኙት እዚሁ ወሎ ዉስጥ ነዉ ። ስለግሸን ስንደርስበት በግራኝ ስር በዝርዝር እናየዋለን ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ 3 ሐይማኖታዊ ጀግኖች አሉ ። እነሱም ቅዱስ ያሬድ፣ አባ ተክለሐይማኖትና አቡነ ጴጥሮስ ናቸዉ ። ሁለቱ ማለትም አባ ተክለሐይማኖትና አቡነ ጴጥሮስ የወሎ ሰዎች ናቸዉ /ቅዱስ ያሬድ የትግራይ ሰው ነው/ ። ስለዚህ የክርስትና እምነት መሰረቱ ያለዉ እዚሁ ወሎ ዉስጥ ነዉ ማለት ነዉ ።

እናም ኢትዮጵያን ክርስቲያናዊት ያደረጓት የወሎ ክርስቲያኖች ናቸው ማለት ነው /ሸዋ፣ አገውና የጁ/ ። ወሎዎች ቅልቅል ባይሆኑ ኖሮ ኢትዮጵያን ሙስሊም ከመሆን ማንም አያድናትም ነበር ። ይህ ሁኔታ ከሸዋና ከላስታ በተጨማሪ በድጋሜ በዘመነ መሳፍንት /በዘመነ የጁ/ ጊዜ በግልፅ ታይቷል ።

ስለ ዘመነ መሳፍንት ጋዜጠኛ ፍስሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ፣ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፅሀፋቸዉ ካሰፈሩት ውስጥ ፡ -

"በዚህ ዘመን አካባቢ በመላ ሀገሪቱ እጅግ ግዙፍ ሰራዊት ያላቸዉ መሳፍንቶች የተፈጠሩበት ዘመን ነበር ። በተለይ የየጁዉ ትልቁ ራስ አሊ በሀገሪቱ ሁሉ ስሙ ከንጉሱ በላይ እየገነነ መጣ ። የጎጃም፣ የጎንደርና የሌሎችም አካባቢ ሴቶች በግጥም እየዘፈኑ "አሊና አሊና አሊና በሞቴ፣ የአማራ ማተብ ሰለቸዉ አንገቴ" እያሉ ያዜሙ ነበር ።

የትልቁ ራሰ አሊ ሰራዊት ወሎንና ጎንደርን ሙሉ በሙሉ እየወረረ ወደ ቤተመንግስቱ ተጠጋ ። በዚህ ጊዜ በየግዛቱ ያሉ የንጉሱ መሣፍንቶች ከያሉበት ተሰባስበዉ ራስ አሊን ለመዉጋት ተስማሙ ።

በዚህም የጎጃሙ ራስ ሀይሉ፣ የሰሜኑ ራስ ገብሬ፣ የላስታዉ ዋግ ራስ ስዩም፣ የትግሬዉ ደ/ች ወልደ ገብርኤል፣ የቆማዉ ራስ ደመ ክርስቶስ፣ የአለፋ ጣቁሳዉ ደ/ች ዘክርስቶስ፣ የቋራዉ መስፍን አዛዥ ልደት...ወዘተ ሁሉም የንጉሱ መሣፍንቶች ህብረት ፈጠሩና ጦራቸዉን ይዘዉ ወደ በለሳ ተጉዘዉ 'መደብ" ተብላ በምትጠራዉ ቦታ ሰፈሩ ።

በአጠቃላይ በመላ ሀገሪቱ ያሉት የንጉሱ መኳንንት ሁሉ ተጣምረዉ በምድረ "መደብ" ያገራችንን ትልቁን ዉጊያ አካሄዱ ። እስከ አሁን ድረስ ባገራችን ዉስጥ በርካታ ከባባድ ጦርነቶች ቢካሄዱም ሁሉም የዉጭ ድጋፍ ያለባቸዉና አሸናፊነታቸዉም በዉጪ ድጋፍ መጠንና ጥራት ላይ የተመሰረተ ነዉ ። ባገራችን ዉስጥ የዉጭ ድጋፍ የሌለበት ይህን የሚያህል ከባድ ጦርነት እስከ አሁን ድረስ ተካሂዶ አያዉቅም ። የጁዎች መሀል አገር ዉስጥ ስለሚገኙ ምንም አይነት የዉጭ ድጋፍ ያልነበራቸዉና እጅግ ኋላ ቀር መሣሪያ የታጠቁ ነበሩ ። በአንፃሩ በንጉሱ በኩል ያለዉ ሀይል ከግራኝ ጀምሮ ሲማረክ የኖረ፣ ፖርቹጋሎች ሲመጡ ያመጡትና በየጊዜው ሲገዛ የኖረ በርካታ የዘመኑ መድፎችንና ሌሎች የተሻሉ መሣሪያዎችን የታጠቀ ነበር ። ሆኖም የመንግስት ጦር የታጠቀዉን መሳሪያ ለመጠቀም አስቸጋሪ ሆነበት ። ምክንያቱም የጁዎች የሚተኩሱት ነገር ስለሌላቸዉ፣ የጦርነት ስልታቸዉ ፈጥኖ መቀላቀልና የጨበጣ ጦርነት መጀመር ነበር ። ስለሚቀላቀሉባቸዉ የንጉሱ ወታደሮች ወደ የትም አቅጣጫ መተኮስ አልቻሉም ነበር ። እናም የየጁዉ ጦር የሞተዉ እየሞተ እጅግ በፍጥነት ስለሚቀላቀል የመንግስት ተኳሾች

ጠላትን ከወገን ለይተዉ ለመምታት ይቸገሩ

ነበር ።

እናም በአካባቢው ቀጥቃጮች የተሰራ ጦርና ጎራደ ብቻ የታጠቀው በየጁ ሰዎች የተዋቀረዉ /የሚመራው/ የራስ አሊ ጦር ክፉኛ አጠቃ ። የተጣመረዉ የንጉሱ ሀይልም የሞት ሽረት መከላከል አደረገ ። ነገር ግን የየጁዉን ሰራዊት እጅግ ፈጣን ማጥቃት የሚቋቋመዉ አልተገኘም ። እናም የንጉሱ ጦር ያለቀዉ አልቆና የተማረከዉ ተማርኮ የተረፈዉ ተበታተነ ። ራስ ደመ ክርስቶስ በዉጊያዉ ላይ ሲሞት ሌሎቹ መኳንንቶች ወታደሮቻቸዉን አስፈጅተዉ በየቦታዉ ሸሹ ። ሁሉም የሀገሪቱ መሳፍንቶች ተሰባስበዉ አንድ ቦታ ላይ ስለተመቱ፤ ትልቁ ራስ አሊ ያለማንም ከልካይ መላዋን ሀገሪቱንና የጎንደር ቤተመንግስትን ተቆጣጠሩ’’ ይላል ። /በነገራችን ላይ ይህን ጦርነት የወሎ የእርስ በርስ ጦርነት አድርጎ መዉሰድ አይቻልም ። ምክንያቱም በንጉሱ በኩል /በሸዋዎች በኩል/ ሌሎች የሀገሪቱ መሳፍንቶች ሁሉ አብረዉ ተሳትፈዋልና/ ። ስንደርስበት በዝርዝር እናየዋለን ።

እዚህ ላይ ቢያንስ አንድ ትልቅ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም ። ትልቁ ራስ አሊ እንደት ክርስቲያን እንደሆኑ ቀጠሉ? /ትልቁ ራስ አሊ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለዱ በሆኑን ማለትም የትልቁ ራስ አሊ አባትና እናትም ክርስቲያን እንደነበሩና አያቶቹም፣ ቅድመ አያቶቹም ሁሉ ክርስቲያን እንደነበሩ አለቃ ታዬ ‘’የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ’’ በሚለው መፀሀፋቸው ውስጥ አስፍረውታል ። ወሎ ውስጥ እስከ አሁንም ድረስ አሊ የሚባል ክርስቲያን የተለመደ ነው/ ። እናም አንዳንድ ሰዎች የየጁ ህዝብ አብዛኛዉ ሙስሊም ይመስላቸዋል፤ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ትልቁ ራስ አሊ የአብዛኛውን ሰራዊታቸውን ስሜት ለመጠበቅ ሲሉ እምነታቸውን ወደ እስልምና ቀይረው እስልምናን ማወጃቸው አይቀርም ነበር ። ትልቁ ራስ አሊ መላዋን ሀገሪቱንና የጎንደር ቤተመንግስትን ሲቆጣጠሩ ሁሉም የክርስቲያን ባላባቶች “መደብ” በሚባለዉ ቦታ ላይ ተሰባስበዉ አንድ ላይ ስለተመቱ በሀገሪቱ ዉስጥ አንድም የክርስቲያን ሀይል አልነበረም ፡ ስለዚህ ያለማንም ከልካይ እስልምናን ማወጅ ይችሉ ነበር ማለት ነው ። ስለሆነም ትልቁ ራስ አሊ ክርስቲያን ሆነዉ የቀጠሉበት ምክንያት አብዛኛው የሰራዊታቸው አባላት ክርስትያን ነበሩ ማለት ነው ። ከዚህ በመነሳት ብቻ የጁ ዉስጥ ክርስቲያኑ እንደሚበዛ ማወቅ ይቻላል ።

የጁ አብዛኛዉ ሙስሊም ሆኖ ቢሆን ኖሮ ትልቁ ራስ አሊ ያለማንም ከልካይ እስልምናን አዉጀዉ ሀገሪቱን መጨረሻዉ ለማይታወቅ ዘመን ያህል ይመሩ ነበር ማለት ነዉ፤ ምክንያቱም እስልምናን አዉጀዉ ቢሆን ኖሮ ካሳ

ሀይሉ /ቴድ/ ክርስቲያን ስለሆነ ቤተመንግስት ዉስጥ ቢቀጠርም ያንን ያህል ሹመት የማግኘት እድሉ ጠባብ ነበር፤ እናም አፄ ቴዎድሮስ የሚባል ንጉስ አይከሰትም ነበር ማለት ነዉ ። ስለዚህ የየጁዎች ግዛት ከ74 አመት በላይም ሊቀጥል ይችል ነበር ማለት ነዉ ። እናም ከአገዎች /ከላስታዎች/ና ከሸዋዎች በተጨማሪም ከዚህ ከዘመነ መሳፍንት ጦርነትም በድጋሜ በግልፅ እንደምንረዳው የጁዎች አብዛኞቹ ክርስቲያን በመሆናቸው እንጂ ኢትዮጵያን ሙስሊም ከመሆን ማንም አላዳናትም ነበር ማለት ነው /ትልቁ ራስ አሊ መላዋን ሀገሪቱንና የጎንደር ቤተመንግስትን ሲቆጣጠሩ ሁሉም የክርስትያን ባላባቶች "መደብ" በሚባለዉ ቦታ ላይ ተሰባስበዉ አንድ ላይ ስለተሙቱ በሀገሪቱ ዉስጥ አንድም የክርስቲያን ሀይል አልነበረም/ ። ስለሆነም የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊት ያደረጋት የወሎዎች መቀላቀል ነው ማለት ነው ። ከደርጎ- ኢህዴግ ጦርነት ውጭ ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱ ጦርነቶች በሙሉ የወሎ ህዝቦች ያካሄዷቸው ጦርነቶች ብቻ ናቸው ።

ወደ ርዕሳችን ስንመለስ፣ በረጅሙ/በ12

አሙቱ/ የግሸን አምባ ጦርነት ምክንያት ወደ ግማሽ የሚጠጋዉ የወሎ ህዝብ ሙስሊም መሆኑ ይታወቃል ። የአዓማችን ምቹ እስር ቤት የነበረችው፣ ልዑላን አምባ /ግሸን አምባ/ ለዘመናት የሀገሪቱ የልዑላን እስር ቤትና የመንግስታቱ ግምጃ ቤት በመሆን አገልግላለች ። ከ13ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አፄ ምኒሊክ ግማሽ ዘመን ድረስ የነገስታቱ ሀብት የሚከማቸዉና የስልጣን ተቀናቃኝ ይሆናሉ የሚባሉ ልዑላን ይታሰሩ የነበረዉ ወሎ አምባሰል ግሸን ተራራ ላይ ነበር ። ስለዚህም መግቢያ በሩ በተመረጡ ሻለቆችና በጣም በሰለጠኑ ወታደሮች በብዙ እጥፍ ምሽጎች እጅግ ብርቱ በሆነ ሁኔታ ነበር የሚጠበቀዉ ።

ግራኝ ባጠቃላይ ለ15 አመታት ያህል ሀገሪቱን የመራ ሲሆን ለ12 አመታት ያህል ሲታገል ኖሮ ለመጨረሻዎቹ 3 አመታት ያህል ብቻ ነበር የግሸንን ተራራን መቆጣጠር የቻለዉ ። የግራኝ ቤተመንግስት ጎጃም ጣና ሐይቅ አካባቢ /ደምቢያ/ ላይ ቢሆንም እዚያ አካባቢ ጦርነት ስላልነበር ሰራዊቱ በሙሉ ወሎ ዉስጥ ተከማችቶ ግሸን አምባን ለመያዝ ሲታገል ነበር የኖረዉ ። ስለግሸን ጦርነት ስንደርስበት በግራኝ ስር በዝርዝር እናየዋለን ።

እናም በዚህ ረጅም የግሸን አምባ ጦርነት ምክንያት አሁን ወደ ግማሽ የሚጠጋዉ የወሎ ህዝብ ሙስሊም ነዉ ። ኢትዮጵያ የወሎ ፍጡር ከመሆኗ አንፃር የወሎ ሙስሊሞች የሀገራቸዉን ባህል በግንባር ቀደምትነት መጠበቅ ሲገባቸዉ፣ እነሱ ግን ተቃራኒዉን እየፈፀሙ ይገኛሉ ። እስከ አሁን ድረስ የሀበሻ ነጠላ የተሸፋፈነች ሙስሊም ሴት ታይቶ አይታወቅም ። እስከ አሁን ድረስ የሀበሻ ቀሚስ የለበሰች ሙስሊም ሴትም ታይቶ አይታወቅም ፡ የሀበሻ ልብሶችን ደግሞ በፈለጉት ቀለም

/ጥቁር ራያ/ና ቅርፅ/ዲዛይን/ መስራት ይቻላል ፡ ነገር ግን ሙስሊሞችና ባህላቸዉ አይጥና ድመት ናቸዉ፤ ባህላቸዉን ይፈሩታል፣ ይሸሹታል ። እርግጥ ነዉ የሀበሻ ልብሶች ለአንዳንድ ነገር ላይመቹ ይችላሉ ። ነገር ግን ልክ እንደ ክርስቲያኑ ክብረ በአሎቻቸዉንና አዉዳመቶቻቸዉን በባህላቸዉ መሰረት ማክበር ነበረባቸዉ ። ክርስቲያኖች ወደ ቤተክርስትያን ሲሄዱ ነጠላ የሚለብሱት የዉጮቹ ክርስቲያኖች ነጠላ ስለሚለብሱ ሳይሆን ባህላቸዉ ስለሆነ ነዉ ። ሙስሊሞቹ ግን ወደ አረቦቹ ባህል የመሳብ ችግር አለባቸዉ /አረቦቹ ጀንያ ቢለብሱ እነኝህም ጀንያ ይለብሳሉ/ ።

በአለባበሳቸውም ብቻ ሳይሆን አነጋገራቸውም ላይ አረብኛ ቋንቋን ይመርጣሉ፣ የግለሰቦችን ስም ሳይቀር ወደ አረብኛ ቀይረው መጠቀምን ይወዳሉ፤ ለምሳሌ ያህል አዳም-አደም፣ ኖህ-ኑህ፣ አብረሃምኢብራሂም፣ ዮሴፍ-የሱፍ፣ ሙሴ-ሙሳ፣ ዳዊትዳውድ፣ ሰለሞን-ሱሌይማን፣ ዮናስ-የኑስ …ወዘተ እያሉ ስሞችን ወደ አረብኛ ቅላፄ እየቀየሩ ነው የሚጠሩባቸው ። እናም ከእምነቱ ይልቅ የአረብ ቋንቋና ባህል ነው ልዩነት የፈጠረው ማለት ነው ። እናም ሙስሊሞች የሀገራቸውን ባህልና ቋንቋ እንድጠብቁ እንመክራለን ።

ወሎ የሀገር ግንድ ነዉ፤ ቅርንጫፎች ከግንዱ ጋር እንጂ እርስ በርሳቸዉ አይገናኙም ፡ ፡ /ጎጃምንና ጎንደርን በተደጋጋሚ የምናነሳው ለማሳያ ያህል መሆኑ እንዲታወቅልን እንፈልጋለን/ ። እናም የወሎ ጎረቤት አካባቢዎች የታሪክ ፍርፋሪ የሚያገኙት ከወሎ ነዉ ። ለምሳሌ ያህል ጎጃምና ጎንደርን ብንወስድ ሁለቱም ከወሎ አንድ ታሪክ ነጥቀው ካልተከራከሩ በስተቀር እርስ በርስ የሚከራከሩበት እንኳን አንድ ታሪክ የላቸውም ፡ ሁለቱም ታሪክ ሲፈልጉ ወደ ወሎ ድምበር አቅጣጫ ከሄዱ እንጂ ወደ እርስ በርስ ድምበራቸዉ አቅጣጫ ምንም ነገር የለም ። ጎንደሬዎች ብቸኛዋን የአፄ ቴዎድሮስን ታሪክ

ከየጁ ለመንጠቅ በየጊዜው ሲታገሉ አይተው ጎጃሜዎችም የበላይ ዘለቀን ታሪክ ከቦረና ለመንጠቅ ሲታገሉ ይስተዋላሉ ።

ጎጃም ሰፊ ነዉ፤ ነገር ግን የሚያዜሙላትን ብቸኛዋን ታሪክ ለማግኘት ወሎ ድረስ ሄደዉ ለበላይ ዘለቀ ሲዘፍኑ ይስተዋላሉ ። ስለዚህ ሁለቱንም ጎረቤቶች የታሪክ ፍላጎታቸዉ ከወሎ ጋር የሚያገናኛቸዉ ከሆነና እርስ በርስ የሚያገናኛቸዉ ጉዳይ ከሌለ ወሎ የሀገር ግንድ ነዉ ማለት ነዉ ።

ሆኖም እስከ አሁን ድረስ ስናነባቸው የኖርናቸው መፅሀፎች በሙሉ በሚባል ደረጃ በጎጃምና በጎንደር ሰዎች የተፃፉ ስለሆኑ፣ አሁን እያነበብነው ያለው ነገር ያልተለመደና ግርምትን የሚፈጥር ሆኗል ። እስኪ እንዳዉ ማን ይሙት ኢትዮጵያን የፈጠራት /ያቀናት/ አፄ ሚኒሊክ ነዉ ከምንልና አፄ ቴዎድሮስ ነዉ ከምንል የትኛዉ ይሻላል? ። እስኪ እንዳው በኢትዮጵያ ህዝብ አእምሮ ውስጥ አፄ ምኒሊክና አፄ ቴዎድሮስ ያላቸውን ቦታ እናወዳድረው ። እንግዲህ ነጮችን እንዲናሸንፍ ያደረጉን አፄ ምኒሊክ ናቸው /አድዋ/፣ ኢትዮጵያንም በዚህ መልኩ የፈጠሯት

/ያቀኗት/ አፄ ምኒሊክ ናቸው ። ነገር ግን አፄ ሚኒሊክና አፄ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ህዝብ አእምሮ ውስጥ ያላቸው ቦታ ምድርና ሰማይ ነው ። እስኪ አንድን ህፃን ኢትዮጵያን የፈጠራት /ያቀናት/ ማነው? ብለን እንጠይቅ አፄ ቴዎድሮስ እንጂ አፄ ሚኒሊክ የሚል አይገኝም፤ እስኪ እንዳው ከእንግሊዝ ጀኔራሎች ቅኝ ግዛት ያዳነንን የአፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛን /የዋግሹም ጎበዜን/ ስም የሚያውቅ ሰው ተፈልጎ ይገኛልን? አፄ ቴዎድሮስ እንግሊዞችን ምን አደረጋቸው? መልሱ ምንም ነው ። ስለዚህ የሀገሪቱ ታሪክ እየጠፋ ነው ማለት ነው ። ምክንያቱ ደግሞ ሁሉም የምናነባቸው መፀሀፎችና የምንሰማቸው ዘፈኖች በጎጃምና በጎንደር ሰዎች የተሰሩ ስለሆኑ ነው ። ወሎዎቹ ቁጥራቸው ትንሽ ነው (ሰ/ሸዋ እንጂ የጁና ላስታ ወረዳዎች ናቸው) ፣ እናም ቁጥራቸው ትንሽ ስለሆነ በጎጃምና በጎንደር የኪነጥበብ ስራዎች ይዋጣሉ/dominate ይደረጋሉ/ ። ጎጃምና ጎንደር ደግሞ ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው የሀገሪቱን ታሪክ በማድበስበስ ወደ ጎጥ ታሪክነት እየቀየሩት ነው /ታሪክ ስንፅፍ የኢትዮጵያን ወጥ ታሪክ በግልፅ የማናስቀምጥ ከሆነ፣ የዜማ የቅኔ የቀሳውስት ሀገር ብለን ስናዜም ላሊበላን የማንጠቅስ ከሆነ፣ ታሪክ ስንፅፍ ስለነ አፄ ተክለጊርጊስ 2ኛ የማንፅፍ ከሆነ ... ወዘተ ችግር አለ ማለት ነው/ ። እኛ

ማንንም ለመኮነን አይደለም፣ እኛ እያልን ያለነው ይህ ሁኔታ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ጉዳት አለው ነው፤ ምክንያቱም የሀገሪቱ ታሪኮች የአንድ ብሄር ታሪክ እየመሰሉ መጥተዋል፤ ይህ ደግሞ ሌሎቹ ብሄሮች ስለሀገራቸው ያላቸውን አመለካከት ያዛባዋል /ይሸወዳሉ/ ። ለምሳሌ ያህል በአፄ ምኒሊክ በኢትዮጵያ ፈጠራ ጊዜ ከከሚሴ በተጨማሪ የሸዋ አሮሞዎች ከመነሻው እስከ መጨረሻው ድረስ ተሳትፈዋል፣ ጎጃምና ጎንደር ግን የሉበትም፣ አፄ ሚኒሊክ የትግሬ ዝርያ አላቸው /ሰለሞናዊ፣ ሰለሞን፣ ሳባ/፣ ጎንደር ላይ የምናየው አሮጌው ቤተመንግስት የሸዋዎች እንጂ የጎንደሮች አይደለም ። እናም ብሄሮች ታሪካቸውን የማያውቁ ከሆነ፣ በንግስናም ሆነ በሀገር ማቅናት ላይ ተሳትፎ ባልነበራቸው ሰዎች ኪነጥበብ /አርት/ ተታለው /ተሸውደው/፣ በሀገራቸው ላይ በደል ሊፈፅሙባት ይችላሉ /መገንጠልን ሊያስቡ ይችላሉ/ ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ታሪክ በትክክል መቀመጥ አለበት ማለት ነው፤ በተለይ የኢትዮጵያ አፈጣጠር /የአፄ ሚኒሊክ የዘመቻ ቅደም ተከተሎች/፣ የጎንደር ቤተመንግስት አመሰራረትና የዘመነ መሳፍንት አመሰራረት በትክክል መቀመጥ አለባቸው ። እኛ የአፄ ሚኒሊክን የዘመቻ ቅደም ተከተሎችን፣ ሸዋዎች ቤተመንግስታቸውን ከደብረ ብረሃን ወደ ጎንደር ለምን እንደቀየሩና የዘመነ መሳፍንትን አመሰራረት በትክክል አስቀምጠናል ። እናም አሁንም እያልን ያለነው የኢትዮጵያን ታሪክ የመጠበቁ ስራ የሁሉም ብሄረሰቦች ስራ መሆን አለበት ነው፣ ወሎ የሁሉም ብሄረሰቦች

ድብልቅ /collection/ ነው፣ ነው እያልን ያለነው ። ነገር ግን ይህ የሚሆን አይመስልም፤ ምክንያቱ ደግሞ ሌሎቹ ብሄረሰቦች እንኳን ታሪካቸውን መጠበቅ ቀርቶ አጠቃላይ የሀገሪቱን የታሪክ ሚስጥር አያውቁም /ኢትዮጵያን ማን ፈጠራት፣ጎጃምና ጎንደር ኢትዮጵያን የተቀላቀሉት መቼ ነው፣ ጎጃምንና ጎንደርን ማን ነው በእነ ንጉስ ተከተለሐይማኖት ላይ ዘምቶ ወደ ኢትዮጵያ ያቀላቀላቸው ፣ ኢትዮጵያን የፈጠራት ወሎ ከሆነ ወሎ ምንድን ነው፣ ጎንደር ቤተመንግስት የማን ነው? ወዘተ አያውቁም/ ። እናም ቀስበቀስ የኢትዮጵያ ታሪክ በሙሉ ጠፍቶ የበላይ ዘለቀና የአፄ ቴዎድሮስ መሆኑ አይቀርም ማለት ነው /አይ! ሸዋ፣ላስታ፣ የጁ፣ ወረሂመኖ ። አይ! Mother Ethiopia/

ለመሆኑ ወሎ ይህን ያህል ብቻዉን የኢትዮጵያን እና የአፍሪካን ታሪክ ጠቅልሎ እንዲይዝ ያደረገዉ ነገር ምንድን ነዉ? ሚስጥሩ ምንድን ነዉ?

# የወፋ ዉጊያ

አለቃ ታዬ “የኢትዮጵያ ታሪክ በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ

“የጁ የጥንት ስሟ ገነቴ ነበር ። የጁ የተባለችበት ምክንያት እንዲህ ነዉ፤ ጉባርጃ ማሪያም በገነቴ ምድር የተከበረች ደብር ናት፣ በርሷ ጳጳሳት ይኖሩባት ነበር፣ 7 ጳጳሳትም ተቀብረዉባታል ።

በዚያች ሀገር ጣኦትን የሚያመልኩ፣ በአስማታቸዉ የሚመኩ፣ አስማተኞች ሰዎች

ነበሩ ። በዚያን ዘመን የነበረ ጳጳስ ንስሐ ግቡ፣ በወንጌል እመኑ፣ አስማት ማድረግን ተው፣ ጣኦት ማመንን ተዉ፣ እያለ ቢገስፃቸዉና ቢመክራቸዉ እጅግ አጥብቀዉ ጠሉት ። ቀስበቀስ ግን ቃሉን ያልተቀበሉት አስማተኞች ብቻ ሲቀሩ ሌሎቹ ታላላቆች ወደ ጳጳሱ እየሄዱ የወንጌልን ት/ት እየሰሙ ከዕለት ወደ እለት ብዙዎች ወደ ክርስትና እየተቀየሩ መጡ ።

አስማተኞቹም ክብራቸዉን እንደተገፈፉ ባዩ ጊዜ፣ አንድ ህፃን ሰርቀዉ፣ በስዉር አርደዉ፣ ለጳጳሱ ወጥ ሰሪ ይህንን ወጥ ሰርተህ ጳጳሱ ግብር በሚበሉበት ጊዜ ከጳጳሱ ፊት ይህን አቅርብለነ፣ ይህ ምንድን ነዉ ሲሉህ የወትሮዉ ግብረዎ ነዉ ብለህ በሰዉ ሁሉ ፊት አሳፍርለነ ብለዉ፣ እጅግ ብዙ ገንዘብ ሰጡት ።

ወጥ ሰሪዉም ገንዘቡን ተቀብሎ ያሉትን አደረገ ። የወጡ ሰታቴ ድስት በተከፈተ ጊዜ የዚያ ህፃን ሁለቱ እጆች ከሌላ ስጋዉ ጋር ወጥ ተሰርተው ታዩ ። ጳጳሱና አብሯቸዉ የነበረዉ ሰዉ ሁሉ እጅግ ደነገጡ ። አንተ ዛሬ ያደረከዉ ነገር ምንድን ነዉ? ቢሉት፣ እንደተመከረዉ ጌታዩ እኔ ዛሬ አዲስ ነገር አላመጣሁም ያዉ የወትሮ ግብረዎ ነዉ አላቸዉ፤ ሰዉ ሁሉ ደነገጠ፣ ፈራ ።

ጳጳሱም እጅግ አዘኑና እኔ ከአሁን በፊት የሰዉ ስጋ ስበላ ታዉቀኛለህን? አንተ ከጠላቶቼ ጋር በገንዘብ ተገዝተህ ይህን ታላቅ ድፍረትና ክፋት አድርገህልና ለዘለአለም እርጉም ሁን ብለዉ እረገሙት ። ወጥ ሰሪዉ ያንዉ ጊዜ ልብሱን ጥሎ፣ ሱሪዉን ቀዶ፣ በሰዎች ፊት አብዶ፣ በረረ ገደል ገብቶም ሞተ ፡ ጳጳሱ አገሩንም ረገሙት፤ እንዲህ ብለዉ የዚህ አገር ሰዉ የኔን ስም

ለማከፋት ብሎ ሰዉን ገድሎ፣ እጁን ቆርጦ፣ አናቱን ፈጥፍጦ በሰዉ እንደተጫወተ፤ የእጁን ይስጠዉ፣ ሁል ጊዜ ደም ይፍሰስበት፣ እርስበርሱ ይተላለቅበት ብለዉ ረገሙት ።

ከዚያ ወዲህ አገሩ ገነቴ መባሉ ቀርቶ የጁ ተባለ ። እርስ በርሱም በወፋ ዉጊያ ሁል ጊዜ የሰዉ ደም የሚፈስበት፣ በከንቱ ነፍስ የሚወድቅበት፣ የተረገመ አገር ሆነ ። የየጁ ሰዎች ይህ መርገም ስለፀናባቸዉ አገር ላትገዙበት፣ ስም ላታገኙበት ስለምን? በወፋ ውጊያ እርስ በርሳችሁ በከንቱ ትገዳደላላችሁ ብለዉ ሲለምኗቸዉ፤ ቆሌይቱ ደም ትወዳለችና ወፋ ዉጊያ ሲቀር ከሰማይ ዝናብ ያንስብናል፣ ብናርስም እህሉ ይጠፋብናል፣ በሽታም ይነሳብናል ይላሉ ።

ስለዚህ ሰዉ ሁሉ ጋሻ ጦሩን እየያዘ ይወጣና በያላ ወንዝ፣ በጥቁር ዉሀ፣ በሽሊ፣ በሚሌ እየወረደ ወፋ ይዋጋል ። ባጠገባቸዉና በዙሪያቸዉ ያሉ ወረዳዎችም ይህን ከንቱ ወሬ እየሰሙ ባገራቸዉ ዝናብ፣ በረከት፣ የእህል ብዛት፣ ጤና እንዲሆን አስበዉ ይህን ወፋ ዉጊያ ለመዱ ።

ይህም ወፋ ዉጊያ እስከ ሸዋ ድንበር እስከ ዶባ፣ እስከ መራቤቴ ተለምዶ እስከ አሁን እስከ ዳግማዊ ምኒሊክ ዘመን ድረስ ይዋጉ ነበር ።

አፄ ምኒሊክ ይህን ከንቱ ጥፋት ባዋጅ አስቆሙት ። ብዙ ቀንም በስዉር ተጣቅሶ ወርዶ እርስ በርሱ እየተዋጋ አስቸገረ ። አፄ ምኒሊክም በገዳይና በሟች ቤት እዳ እያስከፈሉ አስተዉት ። ይህም ሆኖ በማመስገን ፋንታ ይህን በከንቱ መሞት አስቀሩብን እያሉ አፄ ምኒሊክን ያሙ ነበር" ይላል ።

ስለ ወፋ ዉጊያ ከሌሎች መፀሀፍት የተሰበሰበዉን መረጃ አንድ ላይ ጨምቀን ስናየዉ ፡ - የወፋ ዉጊያ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ መካሄድ አለበት፤ ይህም የሚሆነዉ ደግሞ የክረምት ጊዜ ከመድረሱ በፊት ነዉ /በቂ የክረምት ዝናብ እንዲገኝ/ ። በቂ ዝናብ ዘንቦ በቂ እህል እንዲገኝ ከክረምት በፊት ቀጠሮ ተይዞ የወፋ ዉጊያ መካሄድ አለበት ። ወጣቶች በቀጠሮዉ ጊዜ እንደ ምርጫቸዉ ጦርና ጋሻ ወይም ጎራደና ጋሻ እየያዙ ወደ ወንዝ ወርደዉ ከባድ የእርስ በርስ ዉጊያ ይካሄዳል ። የዚያን ጊዜ ቆሌይቱ የሰዉ ደምና ሬሳ ትጠግባለች፤ ወጣቶቹም ጀግንነታቸዉን፣ ብቃታቸዉንና ጉልበታቸዉን ያሳዩበታል ።

በዚህ ዉጊያ በሚችና በገዳይ ቤተሰቦች መካከል ፀብ አይኖርም፣ በቀልም አይኖርም፣ ከሞተ ሞተ ነዉ ። ምክንያቱም ለቆሌይቱ የግድ ሰዉ መሞት አለበት፤ የሚሞተዉ ሰዉ የሚወሰነዉ ደግሞ በምርጫ ሳይሆን በራሱ ጀግንነትና ብቃት ነዉ ። እናም የወፋ ዉጊያ ብዙ ደም የሚፈስበት፣ ብዙ ህይወት የሚጠፋበት፣ ብዙዎች አካለ ጎደሎ የሚሆኑበት እጅግ ዘግናኝ ዉጊያ ነበር ።

በጦርነቱ ብዙ ሰዉ ማቁሰልህ፣ ጀግንነትህንና ብቃትህን ማሳየትህ…ወዘተ በቂ አይደሉም፤ የግድ መግደል አለብህ ። ገድለህ የማታውቅ ከሆነ ግን የአንተ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ የቤተሰብህም ስም ይጠፋል ። ወሎ ዉስጥ መግደል እንደነበረብህ የሚያሳዩ በርካታ

የወሎ አረሆዎች አዘውትረው ያዜሟቸው የነበሩ የዘፈንና የሽለላ /ቅረርቶ/ ግጥሞች ነበሩ።

የወቅቱ የወሎ አረሆዎች ያዘወትሯቸው ከነበሩ ግጥሞች መካከል ፡ -

ገዳይ ገዳይ ያልሺዉ አባትሽ አይገድል ወንድምሽ አይገድል፣

አርሰዉ ያብሉሽ እንጂ ሆድሽ እንዳይጎድል ።

ገዳይ በየጎራዉ በየሸንተረሩ፣

የአዳኝ እንኳን ዉሻ ይፈለጋል ዘሩ ።

… ወዘተ ይገኙበታል ።

እንግዴህ ካልገደልክ በዚህ መልኩ ስምህ ይጠፋል ማለት ነዉ ። ቤተሰቡም የገዳይ ቤተሰብ ካልሆነ ዘረ ፈሪ ይባላል፣ ሳይገድሉ ጎፈሬም ያስፎግራል /ያሸማቅቃል/ ። ባጠቃላይ በህብረተሰቡ ዘንድ ተከብረህ የምትኖረዉ ገዳይ ከሆንክ ብቻ ነዉ ። ስለዚህ የግድ አንዱን ያዘዘበት መግደል አለብህ ። ስለሆነም ትግሉ ነፍስን የማትረፍ ሳይሆን የመግደል ትግል ነዉ ፡ ጥያቄዉ ግን ሟቹ ማን ነዉ? ነዉ ። ጦርነቱ እጅግ ዘግናኝ የሚሆንበት ምክንያትም ይህ ነበር ።

የወፋ ጦርነት ጎጅነቱ እንዳለ ሆኖ የጎንዮሽ ጥቅምም ነበረዉ ። ይህ ጦርነት ወጣቶቹን ጨካኝ፣ ደፋርና ጀግና እንዲሆኑ ከማድረጉም በተጨማሪ የመዋጋት ልምድና ዝግጅት እንድኖራቸዉ ያደርጋል ። እናም ወሎ ይችን

ሰፊና ልዩ የጥቁሮች ምድር /land of original black/፣ እስከ አሁን ድረስ ጠብቆ የአለም አንዷ የነፃነት ምልክት/one of the sign of independence countries in the world/ ያደረጋት በዚህ ከየጁ እስከ መራቢቴ ተስፋፍቶ በነበረው የወፋ ባህላዊ ውጊያ ታግዞ ነዉ ተብሎ ይገመታል ።

ስለዚህ ወሎ የኢትዮጵያንና የአፍሪካን ታሪክ ጠቅልሎ እንዲይዝ ያገዘዉ ይህ ከየጁ እስከ መራቤቴ፣ ዶባ ድረስ ተስፋቶ የነበረዉ የወፋ ዉጊያ ባህል ነዉ ማለት ይቻላል ። የጁዎች ብቸኛ ሰለሞናዊ ስረዎ መንግስትን ስልጣን መንጠቅ የቻሉ ህዝቦች ናቸው/ዘመነ መሳፍንት/፤ አገዎች ከሰለሞናዊ ጋር ጋብቻ ነበራቸው /ዛግዌ/ ። የሸዋዎችና የወረሂመኖዎች ጦረኝነትም የመጣው ይኸው የወፋ ባህላዊ ውጊያ እስከ መራቢቴ ዶባ ድረስ በመስፋፋቱ ምክንያት ነው ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ስፋትና የኢትዮጵያ ነፃነት የየጁ ባህል ውጤቶች ናቸው ማለት ይቻላል ።

ከውርስ ሰንጠረዡ እንዳየነው ወሎ ከዛግዌ ስርወ መንግስት የመጀመሪያዉ ንጉስ ከመራ ተክለሃይማኖት 912ዓ.ም ጀምሮ እስከ አፄ ኃይለስላሴ 1967ዓ.ም ድረስ ለ1055 አመት ያህል ኢትዮጵያን ሲመራ፣ ጣልቃ የገቡት አፄ ዮሃንስና ግራኝ አህመድ ብቻ ናቸዉ ። ግራኝ አህመድ 15 አመት፣ አፄ ዮህንስ 17 አመት፣ በአጠቃላይ 32 አመት ጣልቃ ሲገቡ፣ ቀሪዉን 1023 አመት ያህል ኢትዮጵያን የመሩት የወሎ ነገስታት ነበሩ ።

ወሎ ይህን ያህል ዘመን ሀገሪቱን ሲመራ በብሄር ብሂረሰቦች መካከል አንድም ችግርና አድሎ ተፈጥሮ አያዉቅም ። የወሎ አገዛዝ ከብሄር አድሎ እጅግ ነፃ ከመሆኑ የተነሳ ብሄረሰቦች ሊጠቅሱት የሚችሉት በደል ስለሚያጡ፣ አንዳንዶች እንደ ህፃን ልጅ የተተራረቡትንና የተሰዳደቡትን ሲጠቅሱ ይስተዋላሉ ። አንዳንድ ይቃወሙ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችም ህዝብን የሚቀሰቅሱበት በደል ስለሚያጡ፣ እንደ ህፃን በርካታ የትረባ ቃላቶችን እራሳቸዉ አዘጋጅተዉ እያስራጩ፣ ህዝቡን እንደዚህ እየተባልክ እየተሰደብክ ነዉ እያሉ ለመቀስቀስ ይሞክሩነበር ። ይህ እንግዲህ ምን ያህል ሊጠቅሱት የሚችሉት በደል እንዳጡና የወሎ አገዛዝ ምን ያህል ንፁህ እንደ ነበር ያሳያል ። አንዲት ወረዳ ብቻዋን ሀገር ብትሆን እንኳ በቀበሌ መተራረብ አይቀርም ። የሚገርመው ነገር የሁሉም ብሄረሰቦች ትረባ ‘’ኢታውቁም’’ የሚል ነው፤

ሁሉም ትረባዎች ‘’እረ እነሱ እኮ ምንም አያውቁም’’፣ ‘’እረ እነሱ ደግሞ ምን ያውቃሉ’’ ወዘተ የሚሉ ነበሩ፣ ‘’ፈሪ ናቸው’’ ተብለው የተተረቡ የሉም፤ ምንአልባት በጊዜ ብዛት ምክንያት ፈሪ ወደሚለው አቅጣጫ ተቀይረው እንደሆን እንጂ ስድቦች በሙሉ ካለማወቅ ጋር የተያያዙ ነበሩ ። እናም እጅግ የሚገርመው ነገር የማናውቀው ነገር ምንድን ነው? ብሎ እራሱን የሚጠይቅ አለመኖሩ ነው ። ፈሪ የሚል ትረባ አለመኖሩና አያውቁም የሚለው ትረባ በዚህ መጠን

ትኩረት ማግኘቱ በጣም የሚገርም ነገር ነው ። ስለዚህ ተሰዳቢዎቹ የማያውቁት በዚህ መጠን ትኩረት ያገኘ እጅግ ትልቅ ነገር /ሚስጥር/ አለ ማለት ነው ።

አያውቁም የሚለው ነገር የተጀመረው የአፄ ሚኒሊክ መጨረሻ ዘመን አካባቢ ላይ ቢሆንም በጣም ጎልቶ የነበረው ግን በአፄ ኃይለስላሴና በደርግ ዘመን ነበር ። ትረባው በአፄ ሚኒሊክ መጨረሻ ዘመን ላይ ከጀመረና ስድቦች በሙሉ ምንም አታውቁም የሚሉ ከሆኑ በዚያን ዘመን የማናውቀው ነገር ምንድን ነበር? ሳይንሱን ነው የማናውቀው? /በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ ምንሽር ትሰራ ነበር? በልጅግ ትሰራ ነበር? ዳንዴ ትሰራ ነበር? ትምህርት እራሱ የተጀመረው በአፄ ሚኒሊክ ዘመን ነው/ ። ስለዚህ በዚያን ዘመን የሚታወቅ ሳይንስ ካልነበረ ፣ የማናውቀው ሀገራችንን ነው ማለት ነው፣ የኢትዮጵያን የታሪክ ሚስጥር አናውቅም ማለት ነው፣ ሀገሩን የማያውቅ ማለት ደግሞ ወላጆቹን /እናትና አባቱን/ የማያውቅ ማለት ነው ።

ሀገር ማለት ምን ማለት ነው? መልሱ፣ ሀገር ማለት የወለደህ ምድር ማለት ነው /ወላጅ ምድር ማለት ነው/፤ አብዛኞች እናት ሀገራችን ይላሉ፣ ጥቂቶች ደግሞ አባት ሀገራችን ይላሉ፣ ሁለቱም እናትም አባትም ወላጅነትን ያመለክታሉ ። የወለደህን /ያፈራህን/ ምድር የሚቀማህ የለም፤ እራሱ ወልዶሀልና የምድሩ ባለቤት አንተ ነህ፤ ነገር ግን ያልወለደህ ምድር ከሆነ ዜግነት ቢሰጡህም ያንተ አይደለም /ሰጡህ ማለት ባለቤት አይደለህም ማለት ነው፣ ምድሩ አልወለደህም ማለት ነው፣ ምድሩ እራሱ የወለዳቸው የእራሱ ልጆች አሉት ማለት ነው/ ። ስለዚህ የወላጅህን የኢትዮጵያን የታሪክ ሚስጥር የማታውቅ ከሆነ ምንም አታውቅም ተብለህ ብትተረብ የሚገርም ነገር አይደለም ማለት ነው ። ሆኖም ተሰዳቢዎቹ የማናውቀው ሚስጥር ምንድን?

ነው ብለው እራሳቸውን ከመጠየቅ ይልቅ በስድቡ ይናደዱ ነበር /በእርግጥ ጊዜ እየረዘመ ሲመጣ ይህ አያውቁም የሚለው ችግር የሁለትና የሶስት ብሄረሰቦች ችግር ብቻም ሳይሆን የሁሉም ብሄረሰቦች ችግር እየሆነ መጥቷል/ ። ይህ ሁኔታ እንግዲህ ሌላ የሚያናድድ ችግር አለመፈጠሩንና የወሎ አገዛዝ ምን ያህል የብሄር አድሎ የሌለበትና ንፁህ እንደነበር ያሳያል ።

ወፋ በሚለው ርዕስ ስር ያየነው የጳጳሱ እርግማን ግን ወሎዎችን የለቀቃቸው አይመስልም፤ የወሎ የመጨረሻዉ ንጉሰ ነገስት አፄ ኃይለስላሴ አርጅተዉ ስልጣን እየለቀቁ ባለበት አመት፣ የ1966ቱ ድርቅ ተከሰተ፣ ቀጥሎም ከ11 አመት በኋላ የ1977ቱ ድርቅ ተከሰተ፤ አሁን አሁን ደግሞ የወሎና የትግራይ አካባቢ ክረምት እየቀነሰ መጥቶ አንድ ወር ብቻ ሆኗል /የወሎና የትግራይ የክረምት ዝናብ ሐምሌ 17 ቀን አካባቢ ጀምሮ ነሐሴ 20 ቀን አካባቢ ያቆማል/ ። እናም ስልጣን ከወሎዎች እጅ እንደወጣ ወዳውኑ የድርቆቹ መከሰት በጣም የሚገርም ነገር ነዉ ። የወሎ ነገስታት ስልጣን ከመልቀቃቸዉ በፊት ድርቆቹ ተከስተዉ ቢሆን ኖሮ ምናልባት የወሎን የዝናብ ስርጭት ለማስተካከል ይሞክሩ ነበር ።

የዝናብ ስርጭትን ማስተካከል ይቻላል ። የዉሀ አካላት ልክ እንደ ጫካዎች ዝናብ የመሳብ ኃይል አላቸዉ ። አንድ አካባቢ ዉስጥ በርካታ የዉሀ አካላት /ግድቦች/ ካሉ ከእነሱ የሚተነዉ ዉሀ የአካባቢዉን አየር እርጥብ እንዲሆን ያደርገዋል ። አየሩ እርጥብ ከሆነ ደግሞ ወደ አካባቢዉ የሚገባዉ ደመና በቀላሉ ወደ ዝናብ ይቀየራል ። የዉሀ አካላት የሌሉበት አካባቢ ከሆነና አየሩ ደረቅ ከሆነ ግን ወደ አካባቢዉ የሚገባዉ ደመና ወደ ዝናብ ከመቀየር ይልቅ አልፎ ይሄዳል ። ደን መጠበቅ ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም፤ ምክንያቱም አንድ አመት ደን ጥበቃው ሲያቆም ምድሩ ወዳውኑ ተመልሶ ይራቆታል ። እናም በወሎ፣ በትግራይ፣ በአፋርና በሱማሌ አካባቢ ሰፋፊ ዉሀ የሚይዙ

ግድቦችን /water reservoirs/ በመገንባት የአካባቢዉን የዝናብ ስርጭት በዘላቂነት ማስተካከል ይቻል ነበር ። ስልጣን ከወሎዎች እጅ ከመውጣቱ በፊት ድርቆቹ ተከስተው ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባት ውሀ ለገበሬ የመሸጥ ስራም ሊጀመር ይችል ነበር ።

ለገበሬ ውሀ መሸጥ ተጀምሮ ቢሆን ኖሮ ደግሞ እስከ አሁን ድረስ ይህ የውሀ ሽያጭ ስራ በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ተዳርሶ ይህኔ እጅግ

የበለፀገች ሀገር ውስጥ ነበርን ማለት ነው ። እንደ አሜሪካኖቹና አውሮፓዊያኑ ይሄኔ እኛም ገነት ውስጥ ነበርን ማለት ነው ።

## የውሀ ሽያጭ ስራ

ውሀ ለብልፅግና ቁልፍ ጉዳይ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ውሀን ለገበሬዎች ለመሸጥ የሞከረ አፍሪካዊ መንግስት የለም ። ውሀ በአለማችን ላይ በጣም ርካሽ ከሚባሉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው ። ውሀን ለገበሬዎች ለመሸጥ የመነሻውን ካፒታል /initial investment/ እንደ አቅምህና እንደፍላጎትህ ከፍ ዝቅ ልታደርገው ትችላለህ ። ገንዘብ የሌለው መንግስት የውሀ ሽያጩን ስራ በየቦታው በዶዘር በሚቆፈሩ ሰፋፊ ጉድጓዶች መጀመር ይችላል ። ከነዚህ በዶዘር ከሚቆፈሩ ትልልቅ ጉድጓዶች የሚገኘውን ውሀ በኤሌክትሪክ ሞተር እየገፉ ለሽያጭ ማቅረብ ይቻላል /የውሀ ታክስ ነው፣ በውሀው ያመረተው ምርት ተገምግሞ ነው ታክሱ የሚቆረጠው/ ። ግድብ ካስፈለገም ደግሞ በአንድት ግድብ ብቻ የውሀ ሽያጩን ስራ መጀመር ይቻላል /ግድብ ቋሚ ንብረት ስለሆነ ከአንዱ ግድብ የሚገኘው ገንዘብ ሌላ ግድብ እየወለደ እየተባዛ ይሄዳል/ ፡ እናም ከነኝህ በዶዘር ከሚቆፈሩ ሰፋፊ ጉድጓዶች ወይም ከግድቦች የሚገኘውን ውሀ በኤሌክትሪክ ሞተር በመግፋት የውሀ ሽያጭ /ታክስ/ ስራውን መጀመር ይቻላል ። ውሀውን ለገበሬዎቹ በጣም በውድ የውሀ ታክስ ማቅረብ ይቻላል፤ ምክንያቱም የውሀ ታክሱ የሚቆረጠው ገበሬዎቹ ውሀውን ተጠቅመው ካመረቱት ምርት ላይ ብቻ ነው /ውሀውን ቢጠቀሙም ምርቱ ከቀነሰባቸው ታክሱም በዚያው መጠን ይቀንሳል ማለት ነው/ ። ገበሬዎቹ በሁለት ጊዜ ወርዊ የውሀ ታክስ ብቻ አንድ ዙር ያመርቱበታል /በሁለት ወር የክረምት ዝናብ አንድ ዙር እንደሚያመርቱት ሁሉ/ ። አንድ ማሳ ደግሞ በወር 5 ጊዜ፣ በአጠቃላይ በ2 ወር 9 ጊዜ አካባቢ ቢጠጣ ይበቃዋል፤ ቋሚ ተክል /ቡና፣ ሙዝ፣ አቮካዶ ወዘተ/ ከሆነ ደግሞ ስሩ ፅሀይ ስለማያገኘው በወር 2 ጊዜ ብቻ ውሀ ቢጠጣ ይበቃዋል፣ ለከብቶቻቸው የሚሆን ግጦሽም አብሮው ያገኛል ። ስለሆነም በማንኛውም ውድ ታክስ ቢቀርብ ውሀ ለገበሬዎች ርካሽ ነው ማለት ነው /ገበሬዎቹ ውሀውን በቀጥታ ወደ ገንዘብ ይቀይሩታል/ ። ስለዚህ መንግስት እስከሚያዋጣው ድረስ የፈለገውን ያህል የውሀውን ታክስ መጨመር ይችላል ማለት ነው ። ይህን በጉድጓድ ውሀ የመያዝን ስራ

ኢትዮጵያ ጀምራው የነበረ ቢሆንም ጉድጓዶቹ በሰው ጉልበት የሚቆፈሩ ትንንሽ ጉድጓዶች ስለሚሆኑ ውሀውን እራሱ ጉድጓዱ ስለሚመጠው ግልጋሎት ሳይሰጥ ይሰርግ ነበር /በዶዘር የሚቆፈሩ ትልልቅ ጉድጓዶች ከሆኑ ግን ይህ ችግር ሊፈጠር አይችልም/ ።

ውሀን ለገበሬዎች መሸጥ ማለት በቀጥተኛው /በአቋራጩ/ መንገድ ወደ ብልፅግና መሄድ ማለት ነው /ከተፈጥሮ ጥገኝነት መውጣት ማለት ነው/ ። ውሀ በቀጥታ ወደ ገንዘብ የሚቀየር የተፈጥሮ ሀብት ነው /ውሀውን ገበሬዎቹ በቀጥታ ወደ ገንዘብ ይቀይሩታል/ ። ውሀ ለገበሬዎች መሸጥ ማለት በአንድ ድንጋይ 10 ወፍ መምታት ማለት ነው /ከዝናብ ጭንቀት ይገላግላል፣ ሀብታም ገበሬ ይፈጠራል፣ ባለሀብቶች መሬት እየተከራዩ ወደ ምርት ይገባሉ /እንደ ቆቃ ሸንኩርትና እንደ አርባ ምንጭ ሙዝ/፣ የከተማ ስራ አጥ ወጣቶች እየተደራጁ በአቅራቢያቸው ካሉ ገበሬዎች መሬት ለ2ወር እየተከራዩ ማምረት ይችላሉ፣ ውሀ አቅራቢው ሰራተኛ ይቀጠርበታል፣ ገበያ ላይ ምግብና የደለበ ከብት በርካሽ ይቀርባል፣ መንግስት በውድ ዋጋ ከሚሸጠው ውሀ ከሰፊው ገበሬ አስተማማኝ ሀገራዊ የውሀ ታክስ ይሰበስባል፣ ሀገሪቱ በዛፍ ስለምትሸፈን ዝናብ አይቋረጥም ...ወዘተ/ ። ይህን ስራ ለማስፈፀም ደግሞ ጉድጓዶቹ ከተቆፈሩ በኋላ አሁን ካሉት የቀበሌ ግብርና ሰራተኞች ላይ ጥቂት ሰዎችን መጨመር ይበቃል ። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አስተማማኝ የውሀ ሀብት ያላቸው ሀገራት በ3 እና በ4 ኪሎ ሜትር እርቀት በዶዘር የሚቆፈሩ ሰፋፊ ጉድጓዶችን ቢያስቀምጡለት እራሱ ገበሬው ስልት ፈጥሮ የማያቋርጥ ምርት ያመርትባቸው ነበር /ለምሳሌ ያህል እዚያ ምድረበዳ የአፋር መሬት ላይ በ3 እና በ4 ኪሎ ሜትር እርቀት ውስጥ በዶዘር የተቆፈሩ ሰፋፊ ጉድጓዶችን ብናስቀምጥበት እንዴት ገበሬዎቹ ውሀውን እንደሚየጠቀሙበትና እንደት ምድሩን ወደ ገነት እንደሚቀይሩት እናየው ነበር/ ። የቆቃ ገበሬዎች የውሀ መግፊያ ሞተርም /water pumpም/፣ ኢሌክትሪክም አይቀርብላቸውም ነገር ግን መሬቱ ጠቧቸው እንጂ ቆቃ ውስጥ በሽንኩርትና በቲማቲም ያልተሸፈነ መሬት አይገኝም ። እናም ሞተር ባናቀርብላቸውም እንኳን ጉድጓዱን ካስቀመጥንላቸው እራሳቸው ገበሬዎቹ ስልት ፈጥረው ውሀውን የማያቋርጥ ምርት ያመርቱበታል ማለት ነው ። ደን ጥበቃ ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም፤ አንድ

አመት ደን ጥበቃው ሲያቆም ተመልሶ እዚያው ነው /ደን ጥበቃው እንዳቆመ ወዳው መራቆት ነው/ ።

እናም የአፍሪካ መንግስታት ሰፋፊ የውሀ ጉድጓዶችን ብቻ በመጠቀም ሀገራቱን ከአጠቃላይ ችግሮቻቸው መገላገል ይችሉ ነበር ማለት ነው ። ነገር ግን የአፍሪካ መንግስታት ሀገራቸው ውስጥ ሀብት ሞልቶ /ውሀ/ና ገኸ ሞልቶ /ገበሬ/፣ ህዝባቸው ከተፈጥሮ እየጠበቀ ሲማቅቅ ይኖራል፣ መንግስታቸውም ተፈጥሮ ያፈራችውን ከህዝቡ እየተቀራመተ በሚያገኘው ደካማ ሀገራዊ ገቢ ሲልፈሰፈስ ይኖራል ። የአፍሪካ መንግስታት ይህ በእጃቸው ያለው ወርቅ አልታያቸው ብሎ፣ በአረብ ሀገር ነዳጅ ሲቀኑ ይስተዋላሉ፤ ወደ ገንዘብ ከመቀየር አንፃር ከነዳጅ ይልቅ ውሀ ይቀላል /ጃፓንንና አረቦቹን እናወዳድር/፤ አረብ ሀገር ውስጥ ውሀ ስለሌለ ነው፤ ሌሎች አንዳንድ ሀገሮች ግን ከርሰ ምድራቸው ውስጥ ነዳጅ እያለ አይጠቀሙትም አስቀምጠውታል /አሜሪካ/፤ ውሀቸውን ብቻ ተጠቅመው ነው ከተፈጥሮ ጥገኝነት ነፃ የወጡት ።

ከተፈጥሮ ጥገኝነት ነፃ መውጣት የሚቻለው በሦስት መንገዶች ብቻ ነው ። እነሱም አንደኛ ለገበሬ ውሀ በመሸጥ፣ ሁለተኛ በማኑፋክቸሪንግ /ኢንዱስትሪ/ና ሦስተኛ ሰፋፊ እርሻዎችን በማቋቋም ናቸው ። በትንሽ ገንዘብ በፍጥነት ከመበልፀግ አንፃር ውሀ ሽያጭን የሚያክል የለም፣ ማኑፋክቸሪንግ ይከተላል፣ ሁለቱ /ውሀ ሽያጭና ማኑፋክቸሪንግ/ ሊደጋገፉና ሊያያዙ ይችላሉ ። ከነዚህ ከሦስቱ መንገዶች ውጭ ከተፈጥሮ ተፅእኖ ነፃ መውጣት አይቻልም ።

የአፍሪካ መንግስታት ግን ከሦስቱም አማራጮች ውጭ ናቸው ። የአፍሪካ መንግስታት፣ ድንጋዩን ዳቦ ለማድረግ ነው የሚሞክሩት /አድካሚውንና ተስፋ አስቆራጩን ጠመዝማዛውን የብልፅግና መንገድ ነው የሚመርጡት/ ። የአፍሪካ መንግስታት ብዙ ድካምና ገንዘብ የማይጠይቀውን ዳቦ ትተው፣ ድንጋዩን ዳቦ ለማድረግ አሰልችውንና ጊዜ የሚወስደውን የብልፅግና መንገድ ተከትለው ሲዳክሩ ይኖራሉ፣ እንዴት እንደማይታያቸው አይገባንም /በቃ ሀብት ማለት ውሀ ነው አለቀ! ከውሀ ውጭ እፀዋትን የሚያመርት ፋብሪካ የለም፣ የሚበሉት ደግሞ ዕፀዋትና እንስሳት ብቻ ናቸው፣ ሁለቱም የውሀ ውጤት ናቸው፣ ሌላ የሚበላ ነገር የለም አለቀ/ ።

ማኑፋክቸሪንግን በአፄ ኃይለስላሴ ስር በሰፊው እናየዋለን ።

የአፍሪካ መንግስታት ሌላው ቀርቶ የህዝባቸውን ፍላጎት እንኳን ለይተው አያውቁም ። ህዝብ የሚፈልገው ልማትና የልማት ተጠቃሚ መሆንን ብቻ ነው ። ህዝብ ማለት እዉነት ማለት ነዉ፤ አንድ ሰዉ ሁለት ሰዉ ሊሳሳት ይችላል እንጂ ህዝብ ሊሳሳት አይችልም ። ስለዚህ ህዝብ ሊሳሳት ስለማይችል መፍትሄዉ ልማትና የልማት ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ ብቻ ይሆናል ።

ነገር ግን መንግስት እንደተቋሙ ባህል ሊሳሳት ይችላል፤ ህዝቦች መንግስት በመቀየር ሱስ የተጠመዱ ይመስለዋል ። ህዝቦች በተፈጥሯቸዉ መንግስት የመቀየር ሱስ የለባቸዉም፤ አዲስ ጅብ ሳይሆን ልማት ብቻ ነዉ የሚፈልጉት ። እንደ ምሳሌ የቻይናን ህዝብ ማየት እንችላለን ፡ - ከእነ አሜሪካም በበለጠ ሁኔታ በአለም ላይ ኮሽ እንኳን የሚል የፖለቲካ ተቃዎሞ የሌለባት ሀገር ብትኖር ቻይና ነች ። ቻይና እየተመራች ያለችዉ ደግሞ በአንድ ፓርቲ ብቻ ነዉ ። ይህ ፓርቲ ግን ቻይናን ሙሉ በሙሉ ቀይሮ፣ ኢኮኖሚዋን በአለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ እንዲቀመጥ አድርጎታል ። እንደ ግስጋሴቸዉ ከሆነ ቻይና በአስርት አመታት አካባቢ የአለምን የአጠቃላይ ገቢ /የGDP/ የመሪነት ቦታን ትረከባለች ። እናም የቻይና ህዝቦች ይህን ፓርቲ ለመቀየር የሞከሩበት ሰላማዊይም ሆነ ህገወጥ እንቅስቃሴ የለም ። ስለዚህ ህዝብ ልማት እንጂ ፓርቲ የመቀየር ፍላጎት ሊኖረዉ አይችልም ማለት ነዉ ።

የአዉሮፓ መሪዎች ስልጣን በምርጫ የሚለቁት ህዝቡን ፈርተዉ ወይ ለህዝቡ አዝነዉ አይደለም ። ለራሳቸዉ የህግ የበላይነትን ለመጠቀም ሲሉ ነዉ፤ በሚደክሙባት ሀገራቸዉ ዉስጥ ህጋዊ ቋሚ ንብረት እንዲኖራቸዉ ሲሉ ነዉ ህጉን ከላይ የሚያደርጉት ። ለምሳሌ የአሜሪካዉ ፕሬዝደንት ተወልዶ ባደገበትና በሚደክምበት ሀገሩ ዉስጥ የራሱ የሆነ ማንም የማይነካዉ ቤትና ንብረት አለዉ ። የአፍሪካ ፕረዚዳንቶችም ሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ግን ተወልደዉ ባደጉበትና በሚደክሙበት ሀገራቸዉ ዉስጥ የራሴ የሚሉት ህጋዊ ቋሚ ንብረት አይኖራቸዉም ። ስልጣን እስከ ያዙ ድረስ ሁሉም ነገር የእነሱ ነዉ፤ ስልጣን ሲለቁ ግን ምንም ነገር የላቸዉም ። ይህ የሚሆነዉ ደግሞ ስልጣናቸዉን የሚያስለቅቃቸዉ ህግ ሳይሆን ሌላ ጉልበተኛ ስለሚሆን ነዉ ። እናም በሚደክሙባት ሀገራቸዉ ዉስጥ ባዶነት እየተሰማቸዉ ይኖራሉ ።

ጉልበተኛ እስኪፈጠር ድረስ ስልጣን ይዞ መኖርና ጉልበተኛ ሲመጣ ሁሉንም ነገር ጥሎ መጥፋት፣ ህጉን ከጉልበተኞች በታች እንዲሆን ያደርገዋል ። ለዚህ መፍትሄዉ ደግሞ ስልጣን አስለቃቂዉ ጉልበተኛ እንዳይሆን ማድረግ

ነዉ፤ ማለትም ስልጣን የሚያስለቅቅ ጉልበተኛ እስኪ ፈጠር ድረስ ስልጣን ይዞ የመጠበቅ ልምድን ማጥፋት፤ ይህ ማለት ደግሞ የመሪዎቹን የስልጣን ቆይታ በጊዜ መገደብ ማለት ነዉ ። የመሪዎቹ የስልጣን ጊዜ የተገደበ /fixed/ ከሆነ ከህግ በላይ የሆነ ጉልበተኛ ሳያስፈልግ ህጉ ራሱ ስልጣን ያስለቅቃቸዋል ። እናም ከህግ በላይ የሚሆን ሰዉ ሊመጣ አይችልም ማለት ነው፤ ስለዚህ መሪዎችም በሚደክሙባት ሀገራቸዉ ዉስጥ ማንም የማይነካዉ ህጋዊ ቋሚ ንብረት ይኖራቸዋል /ህጉ የሁሉም የበላይ ይሆናል/ ።

እናም የአውሮፓ መሪዎች በምርጫ ስልጣን የሚለቁት፣ የህጉን የበላይነት ለራሳቸዉ ፈልገዉት እንጂ ህዝብ ልማት እስከ ተሰራለት ድረስ መሪ የመቀየር ፍላጎት ኖሮት አያዉቅም ። ስለሆነም የአፍሪካ መሪዎች የሁሉም ነገር መፍትሄ ልማት መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል ማለት ነው፤ የዚያኔ ከላይ የገለፅናቸውን አቋራጭ የብልፅግና መንገዶችን መከተል ይጀምራሉ ።

የአፍሪካ መንግስታት ከዚህ የልማት ጥያቄ ለመገላገል እንደስልት የሚጠቀሙት ሀገራቸውን ጫፍ እስከ ጫፍ አንድ አይነት ማድረግን ነው ። ኢትዮጵያም ዉስጥ ሁሉም ክልሎች አንድ አይነት ናቸው /ከአማራ ትግራይ፣ ከኦሮምያ ደቡብ ቢኬድም ያው ነው/ ። በአንድ ክልል ላይ ጥሩ ስራ ቢሰራ ሁሉም የሀገሪቱ ህዝቦች የዚህ ስራ ተጠቃሚ መሆናቸዉ አይቀርም ። ሰዎች በስደት ወደ አሜሪካና አዉሮፓ የሚጓዙት አሜሪካና አዉሮፓ ዉስጥ የተሰራዉን ልማት ተጠቃሚ ለመሆን ነዉ ። አንደኛዉ ክልል የተሻለ ስራ ሰርቶ ቢቀየር ኖሮ ለሁላችንም ይበቃን ነበር /እስኪ አሜሪካ ውስጥ የሚኖረውን ህዝብ እንይ፣ ከአፍሪካ ከ54ቱም ሀገሮች ከእያንዳንዳቸው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ፣ እንዲሁም ከላቲን፣ ከኢሲያ፣ ከአረብ፣ ከአውሮፓ ወዘተ/ ። ስለዚህ አንዱ ክልል ውስጥ ከተሰራ እንኳን ለእኛ ለአፍሪካም ይበቃል ማለት ነው ። እኛም አረብ ሀገርና አዉሮፓ እንሄዳለን እያልን ባህር እየገባን አናልቅም ነበር፤ እዚሁ አገር ዉስጥ እየተንቀሳቀስን መጠቀም እንችል ነበር፤ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮችም ወደ እዚሁ ክልል ይጎርፉ ነበር /አሁን አሁን በዉጭ ሀገር ሚዲያዎች ላይ የኢትዮጵያዊያን የስደት ዜና ቢቀንስም ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ መሰደድ ቆሟል ማለት ግን አይደለም/ ። እናም ዋናው መሰራቱ ነው ማለት ነው፣ የትም ይሰራ፣ ባህር ማዶ አሻግሮ ከማየት ይልቅ እዚሁ እየተንቀሳቀሱ መጠቀም ይቻል ነበር ። ስልጣኔ ደግሞ በፍጥነት የሚሰራጭ /diffuse የሚያደርግ/ ነገር ነው፤ አንድ ክልል ቢቀየር

/ቢበለፅግ/ ሁሉም ክልሎች ሲቀየሩ ጊዜ አይወስድባቸውም ነበር ። አንዱ ክልል የተሻለ ስራ ሰርቶ ቢቀየር ኖሮ እዛ ክልል ውስጥ መወዳደር ያቃታቸው ባለሀብቶች ሌሎቹን ክልሎች ይቀይሯቸዋል፣ የሌሎች ክልሎች መሪዎችም ዝም ብለው አያዩም፣ የሌሎች ክልል ህዝቦችም ለምን እኛ ወደ ኋላ ቀረን ብለዉ መጠየቃቸዉ ስለማይቀር፣ የሁሉም ክልል መሪዎች አማራጭ መስራት ብቻ ይሆናል ። ልምዱ ደግሞ እዛኛው ክልል ላይ ስለሚኖር ብልፅግናው በአጭር ጊዜ ይዳረሳል ።

በተቃራኒው ሁሉም ክልሎች አንድ አይነት ከሆኑ ግን ባለሀብቶቹ አንድ አይነት ልምድና አቅም ያላቸው ይሆናሉ፣ አንድ አይነት ስለሆኑ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል የሚሸጋገር ልምድ /እውቀት/ና ሀብት አይኖርም፣ ህዝቡ ሀገር ውስጥ እየተንቀሳቀሰ አማራጮችን የመፈለግ ልምድ አይኖረውም፣ በክልሎች መካከል የልማት ፉክክር ስለማይኖር መንግስትን እንዲዘናጋ ያደርገዋል ። ሁሉም ክልሎች አንድ አይነት ሲሆኑ፣ እኛ ለምን ወደ ኋላ ቀረን የሚል መንግስትን ወደ ልማት የሚገፋ የህዝብ ጥያቄ አይፈጠርም፤ ይህ ደግሞ መንግስትን ከነአካቴዉ ልማትን እንዲረሳ ሊያደርገዉ ይችላል ።

በርግጥ አንዳንድ ጥበት /ብሄርተኝነት/ የሚባለው ድንቁርና ያለባቸው ሰዎች ከሀገር ይልቅ የብሄር ጉዳይ ስለሚስጨንቃቸው በብሄር መካከል ያለውን የልማት ልዩነት ላይደግፉት ይችላሉ ። እነዚህ ያልተገለፀላቸው ሰዎች አለም ላይ በተግባር የተከሰተውን ነገር ማስተዋል ያለባቸው ይመስለናል ። ሀገር ውስጥ ያለ አንድ አካባቢ ብቻውን ሊቀየር አይችልም፤ ከተቀየረም እኛም አብረን መቀየራችን አይቀርም ። ስለዚህ ነገሩ ሁሉ አልተገለፀልንም ማለት ነው፤ በብሔር አንድ መሆን መፍትሄ አያመጣም፤ ለምሳሌ ያህል የዉጮቹ ሶማሌዎች አንድ ብሄር ብቻ ናቸው፤ ነገር ግን ይኸው በጎሳ እየገጠሙ እየተገዳደሉ ሊያልቁ ነዉ ። የሩዋንዳ ጎሳዎች እልቂትም በዘግናኝነቱ በአለም የሚቀድመዉ የለም ። ደቡብና ሰሜን ኮሪያም አንድ ብሄር ብቻ ናቸዉ፤ ነገር ግን ይኸዉ ኢትዮጵያ ሳይቀር ሰላም አስከባሪ ልካ የነበረው ኮሪያ ነዉ፣ የአለማችን ከፍተኛ የሰራዊትና የጦር መሳሪያ ክምችት ያለዉም እዚያዉ ኮሪያ ነው ። ስለዚህ ብዙ ብሄር መሆን ይሻላል ማለት ነው፤ አንድ ብሄር ብቻውን ሀገር መሆን አይችልም ማለት ነው ። አንድ ብሄር ብቻውን ሀገር ከሆነ ግን ከላይ ያየናቸው አይነት እልቂቶች አሉ ማለት ነው ። እስከ አሁን ድረስ ብዙ ብሄሮች አብረው በሚኖሩባቸው የአለም ሀገሮች ውስጥ እልቂት ተከስቶ

አያውቅም /ናይጀሪያ/ ። ስለዚህ ከብሄር ይልቅ እጅግ አደገኛው ጎጥ ነው ማለት ነው ። ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር አብረህ እስከ ኖርክ ድረስ የብሔር ዉስጥ /የጎጥ/ ፀብ ሊኖር አይችልም፤ ጎሳን /ጎጥን/ ብሄር ይጫነዋል ። ብዙ ብሄሮች አብረዉ ሲኖሩ አንዱ ብሄር ከሌላዉ ብሄር ጋር እንጂ የጎሳ ዉድድር አይኖርም ። በብሄሮች ደረጃ ያለዉ ዉድድር ደግሞ ወደ ፀብ ሊቀየር አይችልም፤ ምክንያቱም ብሄር በጣም ሰፊ ስለሆነ በቀላሉ ለመዶለትና ለመምራት አይቻልም ። ብሄርን አቀናጅቶ መምራት የሚችል ቡድን ከተፈጠረም እጅግ ትልቅ ቡድን ስለሚሆን ወደ መንግስትነት ይቀየራል ። እናም ሁሉንም ነገር ስለሚቆጣጠረዉ እልቂት ሊከሰት አይችልም ።

ነገር ግን አንድ ብሄር ብቻውን ሀገር ሆኖ ሲኖር ወሬዎች ሁሉ ስለብሔር ሳይሆን ስለጎጥ ይሆናሉ /የዚያኛው ጎጥ ሰዎች ስልጣን እየያዙብን ነው፣ የዚህኛው ጎጥ ሰዎች ስልጣን ይዘው አያውቁም ወዘተ አይነት ወሬዎችና ሎሎችም ቅሬታዎች እጅግ በርካታ በሆኑ ትንንሽ ጎጦች ውስጥ የዘወትር ወሬ ይሆናሉ/ ። በአንድ ብሔር ውስጥ ወይም በጠባብ ቀለበት ውስጥ /በጠባብ ቦታ ውስጥ/ እጅግ በርካታ የሆኑ የጎጥ ቡድኖች /fragments/ ይፋጠጣሉ። ይህ ጠባብ ቀለበት ውስጥ የሚፈጠር ፍጥጫ አይቆይም፣ በየጊዜው ጦርነቶችን ይለኩሳል፣ በየጊዜው የማያቋርጡ እልቂቶችን ያስከትላል ። በአለም ሀገሮች ላይ በተግባር የሚታየው እውነትም ይኸው ነው፣ እስከ አሁን ድረስ ብዙ ብሄሮች አብረው በሚኖሩባቸው የአለም ሀገሮች ውስጥ እልቂት ተከስቶ አያውቅም ። ከላይ በምሳሌ እንደጠቀስነው ሁሉም የአለም እጅግ ዘግናኝ እልቂቶች የተከሰቱት አንድ ብሄር ብቻ በሚኖርባቸው የአለም ሀገሮች ውስጥ ነው ።

ከሌሎች ብሄሮች ተለይተህ ብቻህን ስትሆን ወዳዉኑ ጎሳ /ጎጥ/ የሚባለዉ አደገኛ ነገር ተጭኖት የነበረው ብሄር የሚባል ትልቅ ድንጋይ ስለተነሳለት አፈሩን አራግፎ ይነሳል ። በጠባብ ቀለበት ውስጥ በጎጥ መቀሳሰሩ ይጀመራል፤ ይህ በጠባብ ቀለበት /በጠባብ ቦታ/ ውስጥ በበርካታ ትንንሽ ቡድኖች መካከል የሚፈጠር መቀሳሰር አይቆይም ወዳውኑ ወደ በርካታ ጦርነቶች ይቀየራል /ቀለበቱ ጠባብ ስለሆነ ነው/ ። ነገር ግን ሀገር እስካለች /ሌሎች ብሄሮች አብረዉን እስካሉ/ ድረስ በብሄር የምንዋደድ ስለሚመስለን አደገኛ የሆነው የብሄር ዉስጥ /የጎጥ/ ፀብ አይፈጠርም ። ለምሳሌ ያህል፣ የውጮቹ ሶማሌዎች ከእኛ ጋር ቢሆኑ ኖሮ እርስ በርሳቸው ሊጣሉ በፍፁም አይችሉም ነበር ።

ሆኖም አንዳንድ ያልገባቸዉ ሰዎች የብሄር መዋደዱን በሀገር /በሌሎች ብሄሮች አብሮ መኖር/ ላይ የመጣ መሆኑን ይረሱትና እንደ እዉነተኛ መዋደድ ሊወስዱት ይችላሉ ። እንደዚያ ካሰቡ ደግሞ ብዙ ነገሮችን ሊያበላሹ ይችላሉ ። ይህ ደግሞ ለእያንዳንዱ ብሄር እጅግ ከፍተኛ ጉዳት አለዉ፤ ብቻዉን ሆኖ እንደ ሶማሌዎች መተላለቅን ሊያስከትል ይችላል ። ስለዚህ ዋናዉ ጉዳይ የሀገር /የሌሎች ብሄሮች አብሮ መኖር/ ጉዳይ ነዉ ማለት ነዉ ። ሁሉም ነገር የሚሆነው፣ በብሄር መዋደዱም ቢሆን የሚኖረው ሀገር ስትኖር ብቻ ነው ማለት ነው ። ስለዚህ ብሄርተኝነት ድንቁርና ነው ማለት ነው ። ይህን ሁኔታ በርካቶች ቢያስተውሉትም አንዳንዶች ግን ልብ ላይሉት ይችላሉ ። /በነገራችን ላይ ድንቁርናና መሀይምነት ይለያያሉ ። መሀይምነት ማለት አለመማር ማለት ነው ። ድንቁርና የሚባሉት ደግሞ ጥበት፣ ትምክት፣ እልህ፣ ታዛዥ አለመሆን፣ ራስ ወዳድነት፣ ትዕቢት፣ ንቀት፣ ትሁት አለመሆን፣ ጠማማነት፣ ቅንነት ማጣት ...ወዘተ ናቸው ። እናም መማር መሀይምነትን እንጂ ድንቁርናን አያስወግድም ማለት ነው /መማር ፀባይ አይቀይርም/ ።

እንደ ምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ የህወሀት ኢህአዴግን አመራሮች እንያቸው ፡ - ህወሀት ትግራይን ለመቆጣጠር 15 ዓመት ፈጅቶበታል፤ በ15ኛዉ አመት ግን ደርግ አንድ እጅግ አደገኛ ዉሳኔ ወሰነ፤ የትግራይን ክልል ሙሉ በሙሉ እንልቀቅላቸዉና ይሞክሩት የሚል ዉሳኔ ። ይህ ዉሳኔ ለህወሀት በጣም አደገኛ ነበር፤ ደርጎችም ስራዉን ሰርተዉት ነበር ። ህወሀት ከሰማይ መና የሚያወርድ ይመስል እንገንጠል እንገንጠል እያለ ኖሯል፤ ስለዚህ እንልቀቅላቸዉና እርስ በርሳቸዉ ይፋጠጡ፣ ሲቀሳሰሩና ሲሰለቻቹ እሚዋጋ ስለማይኖር በቀላሉ ተመልሰን እንገባለን የሚል ከደርግ የማይጠበቅ እጅግ በሳል ዉሳኔ ነበር ።

ነገር ግን የህወሀት አመራሮች መቾ ቀላል ሆኑና፤ አሰቡት አሁን ጦርነቱ ሊያልቅ ነዉ፤ ትግራይ ሙሉ በሙሉ ተለቆላቸዋል፤ ከአሁን በኋላ ስለሌላ ብሄር ማውራት የለም፤ በቃ ሌላ ብሔር የለም፤ አሁን መናው ከሰማይም ሆነ ከምድር መምጣት አለበት፤ ካልሆነ ግን እርስ በእርሳቸው በጠባብ ቀለበት ውስጥ መፋጠጣቸው ነው ። ሞኝህን ፈልግ፤ የህወሀት አመራሮች ብሄሩ ውስጡን እስኪመለከት ድረስ ፋታ መስጠት የለባቸውም፣ ይች የብሄር ፍቅር ሳይነቃባትና ሳትጠፋ በፍጥነት አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ አለባቸው ።

እናም የህወሀት አመራሮች ብሄሩ ውስጡን እስኪመለከት ድረስ ሳይዘገዩ ሰራዊታቸዉን ለሌላ ጦርነት ማሳመን ጀመሩ ፡ - ደርግ ዉሸቱን ነዉ ትግራይን የለቀቀልን፣ በኋላ መዋጋቱ አይቀርም፤ ስለዚህ ወደ መሀል ሀገር ማጥቃት አለብን ብለዉ አሳወቁ ። ደርግ ትግራይን የለቀቀላቸው ዉሸቱን መሆኑን ሁሉም የህወሀት ሰራዊት አባላት ያዉቃሉ ። ጥያቄዉ ግን አሁን በክላሽንኮቭ ብቻ የደርግን ታንክና ጀት ከምንታገል በኋላ ታንክ ገዝተን አየር ሀይል /ጀት/ ኖሮን መከላከል በጣም አይቀልም ወይ? በዚያ ላይ ከማጥቃት አንፃር መከላከል እጅግ ቀላል መሆኑ ይታወቃል የሚል ነበር ። የህወሀት አመራሮች ግን አይሞከርም አሉ ። የበኋላዉ መከላከል እጅግ እንደሚቀላቸዉ ለማንም ግልፅ ስለሆነ የህወሀት ሰራዊት አናጠቃም /አንዋጋም/ ብሎ መበተን ጀመረ ። ለህወሀት አመራሮች ደግሞ የማጥቃት ጉዳይ የህልዉናቸዉ ጉዳይ ነዉ ። ብሄሩ ዉስጡን እስኪመለከትና እርስ በርሱ እስኪያያዝ ድረስ ጊዜ መስጠት የለባቸዉም ። ከመነሻዉም የህወሀት አመራር ትግራይን የመገንጠልን ሁኔታ ከልቡ /የእዉነቱን/ አስቦት አያዉቅም /የመለስን ቤተሰብ አመሰራረት ማየት እንችላለን፣ ሚስቱ አዜብ አማራ ነች/ ። ገንጥሎ ምን ሊፈጥር ነዉ፤ እርስ በርስ መግጠም እንጂ ምን ሊፈጠር ይችላል /ሰፊ ሀገር ተይዞም አልሆነም/ ። የጎሳ ግጥሚያ /ስለ ጎሳ ወሬ፣ የዚያ ጎጥ ሰዎች ብዙ ስልጣን ይዘዋል አይነት ወሬ/ መኖሩ እንደማይቀር መቸም ግልፅ ነዉ፤ ምክንያቱም አሁን ስለ ብሄር ወሬ የለም፣ ስለብሄር የማይወራ ከሆነ ደግሞ ስለጎጥ መወራቱ አይቀርም /የዚያ ጎጥ ሰዎች ተጨቋኞች ናቸው፣ የዚህኛው ጎጥ ሰዎች ደህና ናቸው ወዘተ አይነት ወሬዎች ማለት ነው/ ። እናም የህወሀት አመራሮች ሰራዊታቸው እየተበተነ እያዩም ቢሆን ማጥቃት በሚለዉ ዉሳኔቸዉ ቀረጡ ።

ስለዚህ የብሄር መዋደድ የሚባለዉን ውሸት እንደ ህወሀት አመራሮች አይነት በሳል ሰዎች ካልያዙት በስተቀር ችግር ሊያስከትል ይችላል ማለት ነው ። ይህኔ ትግራይ ሶማሌ ሆና ነበር ማለት ነዉ ። ለምሳሌ አማራ ብሄረሰብ ተገንጥሎ ብቻውን አንድ ሀገር ቢሆን የጠባቡ ቀለበት አሰላለፍ /ፍጥጫ/ ወሎ፣ ጎንደር፣ ጎጃም ይሆን ነበር ። እናም ዋናው ጉዳይ የሀገር ጉዳይ ስለሆነ ክልሎች በየራሳቸው ፍጥነት /speed/ ቢሰሩ ያው የሀገሪቱ ንብረት ስለሆነ ህዝቡ አማራጭ ይኖረዋል፣ የክልሎች የልማት ልዩነት መንግስትንም እንዲሰራ ያስገድደዋል ።

ይህን ክልሎችን አንድ አይነት ማድረግን በርካታ የአፍሪካ መንግስታት እንደ ስልት ይጠቀሙታል ። ሀገራቱን ጫፍ እስከ ጫፍ አንድ አይነት አድርገዉ ብቻ ነዉ ተኝተዉ /ልማት ሳይሰሩ/ መኖር የሚችሉት ። መሪዎቹ ከልማት መቆም የሚያገኙት ጥቅም ባይታወቅም፣ የአፍሪካ ሀገሮች በጦርነት እየወደሙ ደቀው የቀሩት ግን በዚሁ በልማት መቆም ምክንያት ነዉ ።

ጦርነት ሰው ሰራሽ አይደለም፤ ጦርነት ተፈጥሮዊ (natural) ነው ። ጦርነት ስላልፈለከው የሚቀርና ስለፈለከው የምታመጣው አይደለም ። ጦርነት ከህዝቡ የችግር አኗኗር የሚወለድ ሌላ የስራ ዘርፍ ነው ። ህዝቡ መኖር ከቻለ /ህይወቱን መምራት ከቻለ) ሞት ያለበትን ስራ አይመርጥም፣ እናም ጦርነት አይኖርም ። ህዝቡ ህይወቱን መምራት ካልቻለና ችግር ውስጥ ከሆነ ግን ጦርነት እንደ አንድ ህይወትን የመምሪያ /የስራ/ አማራጭ ሆኖ ይነሳል ። የሰው ልጅ በዋነኛነት የሚጨነቀው ስለሚመራው ህይወት ስለሆነ ውሳኔዎችንም የሚወስነው ከሚመራው ህይወት ተነስቶ ነው ። ስለዚህ ጦርነት ማለት ልማት በቆመበት ወቅት የልማት ስራን ተክቶ የሚመጣ ሌላ ህይወትን የመምሪያ የመጨረሻ የስራ አማራጭ ነው ማለት ነው ።

አንዳንድ ነገሩ ያልገባቸው ሰዎች በአንዳንድ የመንግስት ህገመንግስቶች ላይ ሲከራከሩ ይስተዋላሉ፤ ለምሳሌ የመናገርና የመፃፍ መብቶች ላይ ይከራከራሉ ። እነኝህም መብቶች ሰው ሰራሽ አይደሉም፤ ፍጡር ናቸው/natural ናቸው/ ። እነዚህ መብቶች መንግስት ስለፈለገ ሳይሆን ልማት ሲኖር የሚመጡና ልማት ሲጠፉ የሚጠፉ ነገሮች ናቸው ። የአፍሪካ መንግስታት የመናገርና የመፃፍ መብቶችን የሚከለክሉት ለምንድን ነው? ነው ጥያቄው ። ጦርነት እንዳይነሳባቸው ነው? ወይስ ህዝቡን ለማሳቀቅ ፈልገው ነው? ይህ ነው ጥያቄው ።

እናም የአፍሪካ መንግስታት ወደው አይደለም እነኝህን መብቶች የሚከለክሉት፣ ህዝቡ ለጦርነት ዝግጁ ነው ማለት ነው፣ ህዝቡ ሰበብ ነው የሚፈልገው ማለት ነው ። ስለዚህ ያንተ መናገር ለውጥ ያመጣል ማለት ነው /ህዝቡ ቤንዚን ነው ማለት ነው፣ እናም የአንተ መናገር ክብሪት ሊሆን ይችላል ማለት ነው/ ። ህዝቡ ለምን ቤንዚን ሆነ ብለን ያልን እንደሆነ፣ ወደዚያው ልማት ወደሚባለው ነገር ይወስደናል ። ልማት ካለ ህዝቡ የተደላደለ ህይወትና ተስፋ ስለሚኖረው ጦርነት ስጋት አይሆንም፣ ጦርነት ስጋት ካልሆነ

ደግሞ መንግስት እነኝህን መብቶች የማፈን ትግል ውስጥ መግባት አያስፈልገውም ማለት ነው ። ስለዚህ ልማት ካለ እነዚህ መብቶች አሉ ማለት ነው ። ዋናው የአፍሪካና የአውሮፓ መሪዎችም ልዩነት ያለውም እዚህ ላይ ነው ። የአፍሪካ መሪዎች ሰላምንና ዲሞክራሲን ለማምጣት በርካታ ትርጉም የሌላቸው ዝባዝንኪ ጥረቶችን እያደረጉ ጊዜቸውን ያጠፋሉ፤ ለምሳሌ ህገመንግስት በማስተካከል፣ ህገመንግስቱ ውስጥ ያሉትን ነገሮች በመቀያየር፣ አዳዲስ ህጎችን በማውጣት …ወዘተ አይነት ትርጉም የለሽና ለውጥ ሊያመጡ በፍፁም የማይችሉ ዝባዝንኪ ነገሮች ላይ ጊዜቸውን ያጠፋሉ ። ለአውሮፓ መሪዎች ደግሞ አለም ላይ ያሉ ጥሩ ነገሮች በሙሉ ከአንድ ዛፍ ብቻ የሚለቀሙ ፍሬዎች ናቸው፣ ዛፉ ልማት ነው፤ ዛፉ ከሌለ ፍሬ ማግኘት አይቻልም ። እናም ሰላምም ሆነ ድሞክራሲ ልማት ከሌለ የሉም ። ስለዚህ መንቀዣቀዥ አያስፈልግም ማለት ነው በቃ ልማት መስራት ብቻ በቂ ነው ። ስለዚህ የሰው ልጆች የሁሉም ችግሮቻቸው መፍትሄ ልማት ብቻ ነው ማለት ነው ። በአፍሪካ መሪዎች ውስጥ ይህ ግንዛቤ ባለመኖሩ ምክንያት የአፍሪካ ምድር ልማት የሚሰራበት ሳይሆን የጦር መሳሪያ ገዥና የተኩስ ምድር ሆኖ ቀጥሏል ። ወደ ዋናው ርዕሳችን እንመለስ፣

# ምዕራፍ ሁለት

## ዛግዌ በላስታ/መስራች ወሎ ላስታ/

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ፣ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች መፀሀፍቶች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋሉ ።

ከ900ዓ.ም ጀምሮ አክሱማዊያኑ በጣም ከመስፋፋታቸዉ የተነሳ የነበራቸዉ የወታደር ቁጥርና ጥብቅ ይዞታ መሳሳት ጀመረ ። የአገዉ ህዝቦች ደግሞ የአክሱምን መዳከም ካስተዋሉበት ጊዜ ጀምሮ ሥልጣን በኃይል ለመዉሰድ እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር ። ከፈላሾች /ከጎንደሮች/ ጋርም እየተዋጉ ሲሸናነፉ ቆይተዋል ። በዚህ መካከል የላስታ ተወላጅና የአፄ ድልነአድ ሴት ልጅ መሶበወርቅ ባል የነበረው መራ ተክለሐይማኖት ላስታ አካባቢ ጦር እያሰባበሰበና እያደራጀ ነበር ። እናም እራሱን እያጠናከረ የመጣዉ መራ

ተክለሐይማኖት የላስታና የአካባቢዉ ህዝብ በአክሱም መንግስት ላይ ማመፁን ሲያስተዉል፣ የህዝቡን አንጻ አንስቶ፣ እየተዳከመ የመጣዉን የአክሱም የንጉሰ ነገስት ስልጣን በኃል በመዉሰድ፣ የመንግስቱንም መቀመጫ ላስታ /ሮሃ/ ላይ አደረገ ። ወዳዉም ከግብፅ ጳጳስ በማስመጣት ተቀብቶ ራሱ መራ ተክለሐይማኖት ንጉሰነገስት ሆኖ የዛጉዌ ስርወ መንግስትን መሠረተ /''ዛግዌ'' የሚለው ስም ''ዘ-አገው'' ከሚለው ስም የመጣ ነው፣ የላስታ አካባቢ ህዝቦች አገዎች ናቸው/ ።

የዛግዌ ስረዎ መንግስት ነገስታት ዝርዝር

ከ333 ዓመት በላይ ስልጣኑን ይዘዉ ኢትዩጵያን ያስተዳደሩት የላስታ ነገስታቶችም ከቀይ ባህር መለስ እስከ አባይ ወንዝ ባለዉ ክልል የሚገኙትን አጎራባች የኩናማ፣ የፈላሻ፣ ጎጃምና አንጎት (ደላንታ) ማህበረሰቦችንና አካባቢዎችን ጠቅልለዉ ይገዙ ነበር ። በስልጣናቸዉ ዘመንም ለኢትዩጵያ መንግስትና ህብረተሰብ ለእድገትና መስፋፋት ጠንካራ መሰረት ጥለዋል ። ከቋጥኝ ድንጋይ አስፈልፍለዉ ያሰሯቸዉ አብያተ ክርስትያናትና ገዳማት እንድሁም መሰል የጥበብ ሥራዎቻቸዉ ከአለም ታላላቅ ባህላዊ ቅርሶች የሚመደቡ የጥቁር አፍሪካ ቁጥር አንድ ሥራዎች የላስታ ነገስታት አስተዋፆ ማስረጃዎች ናቸዉ ።

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ሥም | አውራሽ | የነገሡበት ዘመን ዓ.ም |
|---|---|---|---|
| 1 | መራ ተክለሐይማኖት | በኃይል | 912-925 |
| 2 | ጠጠዉድም | መራ ተክለሐይማኖት | 925-965 |
| 3 | ጃን ስዩም | ጠጠዉድም | 965-1005 |
| 4 | ግርማ ስዩም | ጃን ስዩም | 1005-1045 |
| 5 | መይራራ | ግርማ ስዩም | 1045-1060 |
| 6 | ሐርቤ 1ኛ | መይራራ | 1060-1077 |
| 7 | ይምርሐነ ክርስቶስ | ሐርቤ 1ኛ | 1077-1117 |
| 8 | ቅዱስ ሐርቤ 2ኛ | ይምርሐነ ክርስቶስ/ወንድ ልጅ የለዉም/ | 1117-1157 |
| 9 | ቅዱስ ላሊበላ | ቅዱስ ሐርቤ 2ኛ | 1157-1197 |
| 10 | ቅዱስ ናኩቶለአብ | ቅዱስ ላሊበላ | 1197-1237 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 11 | ይትባረክ | በስምምነቱ ዉል መሰረት | 1237-1245 |

ከነዚህ ዉስጥ ለአገራቸዉ የተሻለ ስራ የሰሩትንና ለየት ያለ ታሪክ ያላቸዉን ብቻ እየመረጥን ለማየት እንሞክራለን ።

## የአፄ ላሊበላ ዘመነ መንግስትስት (ከ1157-1197ዓ.ም)

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች መፀሀፍቶች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋሉ ።

ስለ አፄ ላሊበላ እንደ አንድ ምስክር ሆኖ የሚገኘዉ ገድሉ ነዉ ። ገድሉ ለመድሐኒያለም ቤተክርስትያን በመሰጠቱም ገድለ ላሊበላ ዘቅዱስ መድሐኒያለም ይባላል ። ከዚህም በተጨማሪ በ14ኛዉ መቶ ክ/ዘመን በአፄ ዘርያዕቆብ ጊዜ በደንብ ተደራጅቶ የተፃፈዉ ታሪክ የሚገኝ ሲሆን ይህንን ታሪክነገስቱን መነሻ እያደረጉም በርካታ የዉጭና የሀገር ዉስጥ ፀሀፍት ብዙ ፅፈዉለታል ።

ላሊበላ የተወለደዉ እዚያዉ ላስታ ሮሐ ውስጥ ነዉ ። በተወለደበት እለት ብዙ ንቦች ዙሪያዉን ከበዉ ሲያነበንቡ እናቱ ስላየች፣ ወደፊት ብዙ ሰራዊት የሚከተለዉ ታላቅ ሰዉ የሚሆን ነዉ ብላ በመገመት ስሙን ላሊበላ አለችዉ ። ንብ ፀጋዉን መሪዉን አወቀ ማለት ነዉ ይላሉ፣ "ላሊበላ ብሒል ንህብ አእመረ ፀጋሁ.." የሚለዉን ግዕዝ ተከትለዉ ።

ላሊብላ ተወልዶ ባደገ ጊዜ በዘመኑ የነበረዉ ንጉስ ቅዱስ ሐርቤይ ዙፋን ይቀናቀነኛል በማለት ብዙ ጊዜ ያሣድደዉ ነበር ። ሊያስገድለዉም ይፈልግ ነበር ። አንድ ቀን የላሊበላ እህት ከንጉሱ /ከሌላኛዉ ወንድሟ/ ጋር ተመሣጥራ በመጠጥ ዉስጥ መርዝ ጨምራ ልካለት እነደነበርና የቀመሰዉ ሌላ ሰዉ ሲሞት እሱ ሳይሞት እንደቀረ፣ ከዚያም ሸሽቶ ወደ በረሐ ከገባ በኋላ በወታደር ተይዞ እንደመጣ፣ ቀጥሎም በሐይማኖታዊ ሥረዓት ያገባትን መስቀል ክብራ የተባለችዉን ሚስቱን "ከሰዉ ነጥቆ ነዉ ያገባት" የሚል ከሳሽ አስነስቶ ንጉሱ ብዙ ሰዓት እንዳስገረፈዉና በድጋሜ ከሚስቱ ጋር ሸሽተዉ ወደ በረሀ ሄደዉ

እንደተቀመጡና ከዚያ በኋላ ተመልሰዉ ከንጉሱ ጋር ታርቀዉ መኖር እንደጀመሩ፣ በመጨረሻም አምላክ ለንጉስ ሐርቤይ በራዕይ ተገልጦ “መንግስትህን ለላሊበላ ልቀቅለት” ብሎ እንደነገረዉና ላሊበላ እንደነገሰ ተፅፏል ፡፡

ላሊበላ መንግስቱን ከወንድሙ ተቀብሎ የኢትዩጵያ ንጉሰነገስት ተብሎ በ1157 ዓ.ም ሲነግስ ሥመ መንግስቱ ገብረ መስቀል ተባለ ፡፡

በአፄ ላሊበላ ዘመንም ሆነ ከእርሱ በፊትና በኋላ በነበሩት የዛጉዌ ነገስታት ዘመን የግብፅ ባለስልጣኖች ጣልቃ ገብነታቸዉ እየጎለበተ ሄዶ ነበር ፡፡ ሱልጣን ወይም ከሊፋ የሚባሉትና በየጊዜዉ እየተከታተሉ ግብፅን የሚያስተዳድሩት የግብፅ ሙስሊም ባለስልጣናት በግዛታቸው ስር የሚገኙትን የእስክንድሪያ ሊቃነ ጳጳሳት ግበር ከፈሉ፣ ያለኛ ፈቃድና ምርጫ ጳጳስ ወደ ኢትዩጵያ እንዳትልኩ፣ በመካከላችሁ የሐይማኖትና የሹመት ክርክር ቢነሳ ባለስልጣኖች አብረዉ እየተቀመጡ ሁኔታዉን እንዲመለከቱ ወዘተ በማለት የእስክንድርያ ክርስቲያኖችን ያስቸግሯቸዉ ነበር ፡፡

ሁኔታዉ እየከፋ ሲሄድ የክርስትያኖች ጭቆና በመካከለኛዉ ምስራቅና በግብፅ ሲበረታ ከዚህ ቀደም እንደሆነዉ ሁሉ በላሊበላም ጊዜም በሽሽት አገራቸዉንና ንብረታቸዉን እየጣሉ ወደ ኢትዩጵያ በርካታ ግብፃዊያን ክርስቲያኖች የመጡ ሲሆን ያረፉትም የንጉሰ ነገስቱ መቀመጫ በሆነዉ በላስታና አካባቢዉ ነበር ፡፡ አፄ ላሊበላም ስደተኞችን ተቀብለዉ ልዩልዩ ሥፍራ እየሰጡ አስቀመጧቸዉ ፡፡

በዚያ ዘመን ለሦስተኛ ጊዜ /3ኛዉ/ የመስቀል ጦርነት ተፋፍሞ ቀጥሎ ነበርና የአዉሮፓ ተዋጊዎች የጀርመኑ ንጉስ ፍሬደርክ ባርባሩ፣ የእንግሊዙ ንጉስ ሪቫርኬርደሊዮን፣ የፈረንሳዩ ንጉስ ፍሊፕ አዉግስቲኒ ዋነኛ ተፋላሚዎች ነበሩ ፡፡ የአረቡ አለም ንጉስ ሱልጣን ሣላዲን የሚባለዉ እነዚህን ሁሉ በጀግንነት እየተዋጋ አሸንፎ እየሩስሌም ከተማን መልሶ በእጁ አደረጋት ፡፡ የመስቀል ጦርነት 8ጊዜ የተካሄደ ሲሆን እየሩሳልም ስትያዝ ስትለቀቅ ከ1096-1300 እ.ኤ.አ ዘልቆ እንደ ነበር ይታወሳል ፡፡ ስለዚህ በዚህ እየተበሳጩ በግብፅ ያሉ ባለስልጣናት ጭቆና ሲያበዙ ብቸኛ መጠጊያ ኢትዩጵያ ነበረች ፡፡

አፄ ላሊበላ ግን ወደዚህ ጦርነት ሳይገቡ ከግብፅ ባለስልጣኖችም ጋር ሳይጋጩ ስደተኞችን መቀበልና ማስጠጋቱን ቀጠሉ ፡፡ ስደተኞችን ተቀብለው

ጥገኝነትን በመስጠታቸውም አረቦች “ለምን አስጠጋሀቸዉ? አሳልፈህ ስጠን” የሚል ተቃወሞ አላሰሙም ፡፡

አንዳንድ የዉጭ ሀገርና የሀገር ዉስጥ ፀሀፍት እነዚህን ከግብፅና ከኢየሩሣሌም እየተሰደዱ የመጡትን ስደተኞች፣ የገዳማት ህንፃ ግንባታዉ ላይ ተሳታፊ እንደነበሩ ፅፈዋል ፡፡ ነገር ግን የአገዉ ተወላጆች ጭንጫ እየፈለፈሉ፣ አለትና ድንጋይ እየጠረቡ መኖሪያ ቤት በመስራት የታወቁ ነበሩ ፡፡ በሰቆጣ የብልበላ ጊዮርጊስ ሥራ የላሊበላን አብያተ ክርስትያናት ሥራ ስለሚመስል ከግብፆች መምጣት በፊት በኢትዩጵያዉያን ዘንድ አለቶችን ፈልፍሎና ጠርቦ ገዳማትንና ቤተክርስትያናትን መገንባት የተለመደ እንደነበር ያሳያል ፡፡

በተጨማሪም የላሊበላ አይነት ዉቅር አብያተክርስትያናት በአለም በየትኛዉም አገር ተፈልጎ አይገኝም ፡፡ ከዚህ አንፃር በኢትዩጵያዊያን ብቻ ነዉ የተሰሩት ብለዉ የሚከራከሩ አሉ ፡፡

ምንአልባት አመዛዝኖ ወደ አንድ እዉነታ መድረስ ካስፈለገ ስደተኞቹ በማስዋቡ ስራ ላይ ተሳትፎ እንደነበራቸዉ መገመት ይቻላል ፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል የተሰሩት መሰል ገዳማትና በኖሪያ ቤቶች ግድግዳቸው አባጣ ጎርባጣ የሚበዛዉ ነዉ ፡፡ በአፄ ለሊበላ ጊዜ የተሰሩት ገዳማት ግን ግድግዳቸው ለስላሳ ነው ፡፡ ከዚህ በመነሳት ሁለት መላምቶችን ማስቀመጥ ይቻላል፤ አንደኛው መላምት ኢትዮጵያውያኑ በልምድ አሰራራቸውን እያሻሻሉ ስለመጡ ሊሆን ይችላል ሲሆን ሁለተኛው መላምት ደግሞ ምናልባት በስደት የመጡት የውጭ ዜጎች የግድግዳ ማስዋብ ስራው ላይ እረድተዋቸው ይሆናል ነው ፡፡

አፄ ላሊበላ በዘመናቸው የመንፈሳዊነት ባህሪ የተላበሱ እንደነበሩ ነዉ የሚታወቀዉ ፡፡ አስራ አንዱን ቤተክርስቲያናት ላስታ ውስጥ ከማሰራታቸዉ በፊትም የእግዚአብሔር አብን ቤተክርስትያን በወሎ ግሸን አምባ /አምባሰል ውስጥ/ አስገምብተዋል ፡፡ በተጨማሪም በሸዋ በጎንደር በላስታ ዙሪያ ባጠቃላይ 181 የሚደርሱ መቅደሶችን አሰርተዋል ፡፡

አፄ ላሊበላ ከምፅዋ ጀምሮ እስከ ዘይላ የአዳልን አገር በሙሉ ጦር በመላክ የግዛቱ አካል አድርገዉ ሊያስገብሯቸዉ ችለዋል ፡፡ ነገር ግን እነዚህ አካባቢዎች የአረቦችን ሀይልና ሁኔታ እያዩ አንዳንድ ጊዜ ያስቸግሩ ነበር ፡፡ ስለዚህ በአፄ

ላሊበላም ሆነ በአባቶቹ ዘመን የተጣራዉ ግዛታቸዉ ትግራይ፣ ወሎ፣ ጎንደር፣ ጌምድርና ጎጃም የመሳሰሉት ነበሩ ።

ላሊበላ ከመንፈሳዊነታቸው የተነሳ አምላክን በመፍራትና “ስልጠንህን ወደ ሰለሞናዊ ዘር መመለስ አለብህ” የሚለዉ የካህናቱና የቀሳዉስቱ ጭቅጨቅ ስለበረከተ መንግስቱን ለሰለሞናዊ ዘር ሊመልሱ ያስቡ ነበር ።

በመጨረሻ አፄ ላሊበላ ወደ ፍፃሜ ሲቃረቡ የወንድማቸውን ልጅ ነአኩቶለአብን አስጠርተው ከባረኩት በኋላ መንግስታቸውን ያወረሱት ሲሆን፣ ላሊበላ ኢትዩጵያን ለ40 ዓመታት አስተዳድረው በ1197ዓ.ም ሰኔ 12 ቀን አርፈዋል ። የሞተበትን ቀን ለማሰብ በየአመቱ ሰኔ 12 ቀን የሚነበብላቸው ክፍል ስንክሳር በተባለዉ መፀሀፍ ዉስጥ ይገኛል ። አፅማቸውም ራሳቸው ባሰሩት ቤት ጎለጎታ አርፎ ይገኛል ።

## የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት አመሰራረት

የአፄ ነአኩቶለአብ ዘመነ መንግስት (ከ1197-1237 ዓ.ም)

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች መፀሀፍቶች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋሉ ።

ከላሊበላ ቀጥለዉ የነበሩት የዛጉዌ ስርወ መንግስት ንጉሰነገስትና የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት መስራች አፄ ነአኩቶለአብ ናቸዉ ። ከሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ጋር የስልጣን ሽግግር የተከናወነዉ በእሳቸዉ ዘመን ቢሆንም የላሊበላ ልጅ ይትባረክ በላስታ ዙፋን በንጉሰ ነገስትነት የተቀመጠበት ሁኔታ ነበር ። ነአኩቶለአብ የቅዱስ ሐርቤ ልጅ ናቸዉ ። አርባ አመት በቆየ ግዛታቸዉ ላሊበላ የጀመሯቸዉን ስራዎች ለፍፃሜ ማድረሳቸዉ፣ በልዩ ልዩ የኢትዩጵያ ከተሞች አብያተ ክርስትያናት ማሰራታቸዉ፣ ባልገብርም ባይነት ሲሸፍቱ የኖሩትን ወገኖች ድል እያደረጉ ማስገበራቸዉ ይጠቀስላቸዋል ።

የዛጉዌ ስርወ መንግስት ነገስታቶች በ333 ዓመት የስልጣን ዘመናቸዉ ወደ መሀልና ወደ ደቡብ ኢትዩጵያ እየተስፋፉ የሄዱበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን የሐይማኖት፣ የፖለቲካና የባህል ተወራራሽነት እየተፈጠረ አሐዳዊ መንግስቱን በፅኑ መሰረት ላይ ለመጣል የተጠናከረ እንቅስቃሴ ያደረጉበት ዘመን ነበር ።

በዛግዌ ዘመን ዉስጥ በተደጋጋሚ ከየአቅጣጫዉ የሚሰነዘር ተቃወሞ ነበር ። ይህም መንግስቱን ወደ ቀድሞዉ /ወደ ቀማችኋቸዉ/ ሰለሞናዊ ስርዎ መንግስት ዘር መልሱት የሚል ነበር ።

የዛግዌ ስርወ መንግስት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የመጨረሻዉ የአክሱም ንጉስ የነበረዉ አፄ ድልነአድ ወደ ወሎ ሸሽቶ ሰ/ሸዋ አካባቢ ይኖር ነበር ። ከእርሱ በኋላ የተወለዱ ዘሮቹም በዚያዉ በሸዋ እየተዳቀሉና እየተባዙ ነዉ የኖሩት ።

በዛግዌ ነገስታት ተይዘዉ እንዳይታሰሩ በመስጋትም ዘመናቸዉን ሙሉ በወሎ ዋሻዎች እየተደበቁና እየሸሹ ነበር ያሳለፉት ። ዛግዌች ግን ይህን መሰል ሙከራ አላደረጉም ። እናም የወሎ ህዝቦች ጋር እየተዳቀሉ /እየተዋለዱ/ በዚያዉ ኑሯቸዉን መሰረቱ ። እነሱም ከድልነአድ ጀምሮ ሲዘረዘሩ ድልነአድ፣ አግብዓፅዩን፣ ፅንፈ አርእድ፣ ነጋሽ ዞሬ፣ አስፈሐ፣ ያዕቆብ፣ ባህር አሰግድ፣ አድም አሰግድና ይኩኖ አምላክ ናቸዉ ።

የዛግዌ ንጉስ አፄ ነአኩቶለአብ በላስታ በነገሱ ዘመን ይኩኖ አምላክ በሸዋ ይኖር ነበር ። እንደዚሁም በመላዉ ኢትዩጵያ ይታወቁና በጣም ይከበሩ የነበሩትና የሀገሪቱን አቡን ተክተዉ ይሰሩ የነበሩት አባ ተክለሐይማኖት በዚያዉ በሸዋ ይኖሩ ነበር ።ይኩኖ አምላክ ተወልዶ ባደገ ጊዜ፣

አባቱ እንዳይገደልበት በመስጋት ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም /ከደሴ ወጣ ብሎ ወደ ሚገኘዉ ገዳም/ ወስዶ አደራ ሰጠዉ ። እናም እዚያዉ መንፈሳዊ ትምህርት እየተከታተለ አደገ ። አባ ተከተለሐየማኖትም እዚሁ ገዳም ሲመላለሱ ይኩኖ አምላክን ይጎበኙት ነበር ። አባ ተክለሐይማኖት ይኩኖ አምላክ የንጉስ ዘር እንደነበረና ስላጣናቸዉን ላስታዎች በኃይል እንደቀሟቸዉ ያዉቁ ነበር ። ሆኖም ግን ይህን ጉዳይ እስከ አሁን ድረስ ብዙም ትኩረት አልሰጡትም ነበር ። ይኩኖ አምላክ ጋር ግን በጣም እየተግባቡና እየወደዱት መጡ ። ይኩኖ አምላክም ለአባ ተክለሐይማኖት “የአባቶቼ መንግስት በእርሰዎ ፀሎት ከተመለሰልኝ ለእርሰወም የአባተዎን የአዛርያስን ሊቀ ካህንነት እመልስለወታአለሁ ። ከመንግስቴም ከሦስት እጅ አንዱን እጅ እሰጠዎታለሁ” ብሎ ቃል ገባላቸዉ ።

አባ ተክለሐይማኖትም ለተገባላቸዉ ቃል ሳይሆን ይኩኖ አምላክን ለማንገስ ስለወሰኑ ካህናቱን እየሰበሰቡ ነአኩቶለአብን ስልጣናቸዉን ለይኩኖ

አምላክ እንዲያወርሱ ይጨቀጭቋቸዉ ጀመር ። ቀጥለዉም መምህሩን አስፈቅደዉ ይኩኖ አምላክን ከገዳም አዉጥተዉ ወደ ሸዋ ይዘዉት ሄዱ ። በሸዋም በይፋት፣ በመንዝ፣ በተጉለት፣ በመራቤቴ እያዞሩ ከባላባቶች ጋር አስተዋወቁት ። ከዚህ በኋላ ደግሞ የኩኖ አምላክ አብዘሀኛዉን ጊዜዉን ያሳለፈዉ እራሱን ደብቆ በስዉር ላስታ ሄዶ አሽከርነት ተቀጥሮ የቤተመንግስትን ስርዓትና ህግ እያጠና ሲሆን መካሪዉም አባ ተክለሐየማኖት ነበሩ ይባላል ።

አባ ተክለሐይማኖት በማናቸዉም ረገድ ይኩኖ አምላክን ለማንገስ ስለወሰኑ በየአዉራጃዉ እየተዘዋወሩ "ዛግዌዎች ስልጣኑን ከሰለሞን ዘር ያለአግባብ ነዉ የወሰዱት ስለዚህ ለይኩኖ አምላክ ሊመልሱ ይገባል" እያሉ መስበክ ጀመሩ ። ቀጥለዉም ላስታ ሄደዉ አፄ ነአኩቶለአብን ተገናኝተዉ "የኢትዮጵያን መንግስት የወሰዳችሁት በማይገባ መልክ ነዉና አሁንም ለሚገባዉ ለይኩኖ አምላክ መልሱ" እያሉ ወተወቱ ።

አፄ ነአኩቶለአብም በጣም መንፈሳዊ ሰዉ ስለነበሩ የአባ ተክለሐይማኖትን ቃል እንዳይተላለፉ ፈርተዉ ምክራቸዉን ሰምተዉ "እሺ እለቃለሁ፤ ነገር ግን በዉል ነዉ የምለቀዉ" አሏቸዉ ።

እናም በመጨረሻ በአባ ተክለሃይማኖት አግባቢነት ሠላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዲደረግ ሆነ ። ይህ የስልጣን መወራረስ ሂደት ረዘም ያለ ጊዜ ከወሰደ በኋላ አፄ ነአኩቶለአብ ስልጣናቸዉን በተፃፈ ዉል የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ዘር ለሆነዉ እና በላስታ ቤተመንግስት በአሽከርነት ተቀጥሮ ያገለግል ለነበረዉ ለሸዋው ይኩኖ አምላክ አዉርሰዉታል ።

ጀምስ ብሩስ የተባለ እንግሊዛዊ ፀሀፊ የፃፈዉን ዉል፣ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ አመት ታሪክ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ተርጉመዉ እንደሚከተለዉ አስፍረዉታል ።

1. ይኩኖ አምላክ የአፄ ነአኩቶለአብ ዘመን /40 አመት/ እኪያልቅ ድረስ እዚያዉ የላስታ ቤተመንግስት አገልጋይነቱን እንዲቀጥልና የአፄ ነአኩቶለአብ ዘመን ሲያልቅ ይኩኖ አምላክ በመላዉ ኢትዩጵያ እንዲነግስ፣

2. ይኩኖ አምላክ መንግስቱን ከተቀበለ በኋላ ከዛግዌ ዘር አንድ መስፍን እየተመረጠ በላስታ አልጋ /ዙፋን/ እንድሾም፣የላስታ ግዛትም ከዛግዌ ወገኖች እንዳይወጣ፣
3. ላስታን የሚገዛዉ መስፍን የዛግዌ ዘር ለመሆኑ ምልክት ይሆነዉ ዘንድ ሁለት የብር ነጋሪት እንዲያስጭን፣ የዘበኞቹ ጦር ባለ ብር ሽቦ፣ የሠንደቅ አላማዉ መያዥያ ጫፍ የብር እንድሆን፣
4. ንጉሱ በወርቅ ዙፋን ሲቀመጥ የላስታዉ መስፍን በብር ወንበር እንድቀመጥ፣
5. የላስታዉ መስፍን ከንጉሱ ጋር በተገናኘ ጊዜ ወንድም ከወንድሙ ጋር ሲገናኝ እንደሚደረገዉ እንድሳሳሙ እንጂ የላስታዉ መስፍን እንደሌሎቹ መሳፍንት መሬት እንዳይስም፣
6. እንደ ሌሎች መሳፍንትና መኳንንት ግብር እንዳይገብር፣ መጥን አዉጣ ተብሎ እንዳይታዘዝ የሚሉ ነበሩ ።

አባ ተክለሐይማኖት ይህን ዉል አዋዉለዉ መንግስቱን ከላስታ ወደ ሸዋ፣ ከዛግዌ ወደ ሰለሞናዊ ዘር፣ ከነአኩቶለአብ ወደ ይኩኖ አምላክ እንዲዘዋወር አድርገዋል ። እናም በዚህ በዉሉ መሰረት ይኩኖ አምላክ በመላዉ ኢትዩጵያ ሲነግስ ቁጥር 2 ላይ በተቀመጠዉ ዉል መሰረት በላስታ አልጋ የተቀመጠዉ የአፄ ላሊበላ ልጅ ይትባረክ ነበር ፡ ይኩኖአምላክም የመንግስቱን መቀመጫ ወደ ሸዋ ቀየረ ። ስለዚህ ባየነዉ መልኩ በኢትዩጵያ ታሪክ ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ ስልጣን በሽማግሌ አማካኝነት በሰላማዊ መንገድ ከአንዱ ወደ ሌላዉ የተላለፈበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር ማለት ነዉ ።

እናም ይኩኖ አምላክ በመላዉ ኢትዩጵያ ሲነግስ ከላይ በ2ኛዉ ቁጥር በተገለፀዉ ስምምነት መሰረት በላስታ አልጋ ዙፋን ላይ የተቀመጠዉ የአፄ ላሊበላ ልጅ ይትባረክ ነበር ። ይኩኖ አምላክ ስልጣኑን እስኪያደላድልና ሁኔታዉን እስኪለምደዉ ስምምነቱን በማክበር 8 ዓመት ከቆየ በኋላ፤ በ1253 ዓ.ም ስምምነቱን በመሻር ይትባረክን በኃይል ደመሰሰዉ ።

አፄ ይኩኖ አምላክ ስልጣኑን በአባ ተክለሐይማኖት አማካኝነት ስላገኘ በገባዉ ቃል መሰረት ዉለታዉን ሊፈፅም ችሏል ። ይህም በጠቅላላዉ ቤተክህነት በዝርዝር በየአዉራጃዉ ያሉትን ገዳማትና አብያተ ክርስትያናት፣

መነኮሳትና ቀሳዉስት ካህናቱን የሚያስተዳድሩበት በማለት የመንግስቱን ሲሶ /ከሦስት አንድ እጁን/ በመሀላ ለአባ ተክለሐይማኖት ሰጣቸዉ ፡፡

ስለ አባ ተክለሐየማኖት ታሪክ የሚገልፀዉ ገድለ ተክለሐይማኖት የሚባለዉ ፅሁፍ እንደሚስረዳዉ አባ ተክለሐየማኖት በቡልጋ አዉራጃ ፀጋ ዘአብ ከተባሉ አባታቸዉና እግዚ አርእያ ከተባሉ እናታቸ የተወለዱ ናቸዉ ፡፡ በዘመኑ የሐይማኖት ትምህርት እየተማሩ አድገዉ የድቁና ማዕረግ፣ ከዚየም የምንኩስና ማዕረግ ተቀብለዉ በሸዋ በዳሞትና በአካባቢዉ እየተዘዋወሩ ወንጌልን እየሰበኩ ኖረዋል ፡፡

በዚሁ በ12ኛዉ ክ/ዘመን አጋማሽ በኢትዩጵያ ደቡባዊ ወሎ ያሉ ክርስትያኖችና የአዳል ሙስሊሞች ተጣልተዉ ስለተዋጉና ስላጠቋቸዉ፤ ይህን ጉዳይ የግብፅ መንግስት ሰምቶ ከግብፅ ወደ ኢትዩጵያ ጳጳስ እንዳይመጣ ከለከለ ፡፡ ስለዚህ የጵጵስናዉ ቦታ ለአመታት ባዶ በመሆኑ ቅስናም ድቁናም የሚሰጥ በመጥፋቱ በኢትዩጵያ ቤ/ን ላይ ችግር ተፈጠረ ፡፡ በዚህ ምክንያት ክርስትና ጨርሶ እንዳይጠፋ ተባለና ሊቃዉንቱ በየገዳማቱና በየአድባራቱ ተሰብስበዉ “ከግብፅ ጳጳስ የምናስመጣበት ጊዜ እስኪገኝ ድረስ አንድ ኢትዩጵያዊ ጥሩ ስነምግባር ያለዉና በሐይማኖቱ የፀና፣ ቀና የሆነ ሰዉ እንምረጥ” ብለዉ ወሰኑ ፡፡ በዚህ ጊዜ የአባ ተክለሐይማኖት ምግባርና እየዞሩ ማስተማራቸዉ በሁሉም ዘንድ ስለሚታወቅ መረጧቸዉ ፡፡ ከዚህ በኋላ ከቀድሞ ክብራቸዉ ላይ የጵጵስና ስልጣን ሲጨምሩ መንፈሳዊ ስልጣናቸዉ በመላዉ ኢትዩጵያ ተዘረጋና ተወዳጅ መንፈሳዊ ሰዉ መሆን ቻሉ ፡፡

ከዚያም በጵጵስና አመታትን አሳልፈዉ ይኩኖ አምላክ ከሞተ በኋላ በአፄ ያግብዓ ዘመን በግብፅ ከሊፋ ፈቃድ ጳጳስ ተሹሞ አባ ዮሐንስ የሚባሉት ወደ ኢትዮጵያ ስለመጡ አቡነ ተክለሐይማኖት የጵጵስና ሥራቸዉን ያለምንም ማቅማማት ለአዲሱ ጳጳስ አስረክበዉ ራሳቸዉ ወዳሰሩት ገዳም ወደ ደብረ አስቦ /በአሁኑ አጠራር ወደ ደብረሊባኖስ/ ሄደዉ ሲኖሩ ነሐሴ 24 ቀን 1269 ዓ.ም አረፉና በዚያዉ በራሳቸዉ ገዳም ተቀበሩ፤ የኖሩትም 110 ዓመት ነዉ ፡፡

አባ ተክለሐይማኖት በዘመናቸዉ በፈፀሟቸዉ እጅግ በርካታ መንፈሳዊ ሥራዎች ምክንያት የኢትዩጵያ ተዋህዶ ቤ/ን አንድ ዕለት በበዓል በመስጠት በየወሩ በ24 አስባቸዉ ስትዉል፣ የቆስጠንጥንያ ቤ/ን ሳይቀር ከፃድቆቿ ተርታ

አሰልፋ ታስባቸዋለች ። በስማቸው የተክለሐይማኖት ፅላት/ታቦት/ ተቀርፆላቸዉ በየቦታዉ ቤ/ን እየተገነባ ሲታወሱ የሚኖሩት እጅግ በርካታ መንፈሳዊ ሥራ በመስራታቸዉ ነዉ ።

# ምዕራፍ ሦስት

## ሰለሞናዊ በሸዋ /መስራች ወሎ ሸዋ/

ሰለሞናዊ ስርወ መንግስት እንደት እንደተመሰረተ በአፄ ነአኩቶለአብ ስር አይተናል ።

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ፣ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች ጋር እያመሳከርኩኝ በአጭሩ አስነብባችኋሉ ።

ዋና መቀመጫቸዉን ሸዋ ላይ አድርገዉ የነበሩ የሰለሞናዊ ሥርወ መንግስት ነገስታት ሥም ዝርዝር ።

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስምና ስመ መንግስት | አውራሽ | የገዙበት ዘመን ዓ.ም |
|---|---|---|---|
| 1 | ይኩኖ አምላክ /ተስፋ እየሱስ/ | ነአኩቶለአብ /አሸከር/ | 1253-1268 |
| 2 | አግብአ ፅዮን/ሰለሞን/ | ይኩኖ አምላክ | 1268-1277 |
| 3 | ፅንፈ አርእድ | አግብአፅዮን /5ቱን ልጆቹን ተራ በተራ/ | 1277-1278 |
| 4 | ህዝበ አሰግድ | ፅንፈ አርእድ | 1278-1279 |
| 5 | ቅድመ አሰግድ | ህዝበ አሰግድ | 1279-1280 |
| 6 | ጃን አሰግድ | ቅድመ አሰግድ | 1280-1281 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | ሰብዓ አሰግድ | ጃን አሰግድ | 1281-1282 |
| 8 | ዉድም አርዕድ | ሰብዓ አሰግድ/ልጅ አልነበረዉም/ | 1282-1297 |
| 9 | ዓምደ ፅዮን 1ኛ/ገብረ መስቀል | ዉድም አርዕድ | 1297-1327 |
| 10 | ሰይፈ አርዕድ/ንዋየ ክርስቶስ/ | ዓምደ ፅዮን 1ኛ | 1327-1355 |
| 11 | ዉድም አስፈሬ/ንዋየ ማርያመ | ሰይፈ አርዕድ | 1355-1365 |
| 12 | ዳዊት | ዉድም አስፈሬ | 1365-1395 |
| 13 | ቴዎድሮስ 1ኛ/ዣን ሰበር ራስ/ | ዳዊት | 1395-1399 |
| 14 | ይስሐቅ/ገ/ቀል/ | ቴዎድሮስ 1ኛ | 1399-1414 |
| 15 | እንድርያስ | ይስሐቅ | 1414-1414 |
| 16 | ህዝበናኝ/ተክለ ማርያም/ | እንድርያስ | 1414-1418 |
| 17 | በድልናኝ/ስርዎእየሱስ/ | ህዝበናኝ | 1418-1419 |
| 18 | አምደእያሱ/ዳዊት/ | በድልናኝ | 1419-1426 |
| 19 | ዘርዓ ያዕቆብ/ቆስጠንጢኖስ/ | አምደእያሱ/ዳዊት/ | 1426-1460 |
| 20 | በአደማርያም | ዘርዓ ያዕቆብ | 1460-1470 |
| 21 | እስክንድር | በአደማርያም | 1470-1486 |
| 22 | አምደ ፅዮን 2ኛ | እስክንድር | 1486-1487 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 23 | ናኦድ/አንበሳ በፅር/ | አምደ ፅዮን 2ኛ | 1487-1500 |
| 24 | ልብነ ድንግል/ወናግ ሰገድ/ | ናኦድና ግራኝ በኃይል | 1500-1532 |
| 25 | ገላዉድወስ/አፅናፍ ሰገድ/ | ልብነ ድንግልና ግራኝ በኃይል | 1532-1551 |
| 26 | ሚናስ/አድማስ ሰገድ/ | ገላዉድዎስ | 1551-1555 |

ሰለሞናዊ ስረወ መንግስት መቀመጫዉን ሸዋ ላይ አድርጎ ስራዉን ጀመረ ።

አፄ አግብዓጽዮን /1268-1277 ዓ.ም/ ፡ - በአባ ተክለሐይማኖት አማካኝነት ስልጣን የወረሱት አፄ ይኩኖአምላክ ኢትዩጵያን ለ15 ዓመት ያህል ካስተዳደሩ በኋላ መንግስታቸዉን ለልጃቸዉ ለአግብአጽዮን አወረሱ ። አፄ አግብዓጽዮን አባቱ ይኩኖ አምላክ ከአዳል ሙስሊሞች ጋር በመዋጋቱ ከግብፅ ባለስልጣናት ጋር የነበረዉን ጥሩ ያልሆነ ግንኙነት አዲሶ ሙስሊሞችን በጥሩ አመለካከት ያያቸዉ ጀመር ።

በዚህ አቋሙ በአባቱ ጊዜ የተከለከለዉን ጳጳስ ሊልኩለት ችለዋል ። በዘመኑ ከእርስ በርስ ግጭት ነፃ የሆነ 9 ዓመታትን ገዝቶ ከመሞቱ በፊት በተናዘዘዉ መሰረት 5ቱን ልጆቹን አንድ አንድ አመት ብቻ እንድነግሱ አድርጓል ።

በዚህ መሰረት ጽንፈ አርዕድ አንድ አመት፣ ህዝብ አሰግድ አንድ አመት፣ ቅድመ አሰግድ አንድ አመት፣ ጃን አሰግድ አንድ አመትና ሰብአዓሰግድ አንድ አመት ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል ።

አፄ ዉድም አርዕድ /1282-1297 ዓ.ም/ ፡ ከሰብዓአሰግድ ቀጥሎ የይኩኖ አምላክ ሌላ ልጅ ዉድም አርዕድ ነግሰዉ ኢትዩጵያን ለ15 ዓመታት ያህል ካስተዳደሩ በኋላ መንግስታቸዉን ለልጃቸዉ ለአምደፅዮን አዉርሰዉ ሞቱ ።

አፄ አምደፅዮን (ከ1297-1327 ዓ.ም) ፡ - ይህ ንጉሰ ነገስት የጠፋዉንና የተበታተነዉን የኢትዮጵያ ታሪክ በማፈላለግና በማደራጀት ለትዉልድ እንዲተላለፍ የተቻለዉን ያህል የጣረ ንጉስ ነዉ ። የመጀመሪያ ሥራዉ ያደረገዉ በአረብ ፀሀፊዎችና በሌሎች የዉጭ ሀገር ፀሀፊዎች ስለ ኢትዮጵያ የተፃፉትን መፀሐፍቶች ሁሉ ሰብስቦ ወደ አማርኛ እያስተረጎመና እያደሰ ለትዉልድ እንዲቀመጥ አድርጓል ። በተጨማሪም በተዋጊነቱና በድል አድራጊነቱ እጅግ ስመጥርና ባለታሪክ ንጉስ ነዉ ።

ለ30 አመት ያህል በቆየ ግዛታቸውም እንደ ላስታ /ዛግዌ/ አባቶቻቸው መንፈሳዊ ሥራዎችን ማለትም ቤተክርስትያን ማስገንባትና ሌሎች መሰል ተግባራትን ማከናወናቸው ተፅፎላቸዋል ፡ በሞቱበት ወቅትም መንግስታቸዉን ለልጃቸዉ ለሠይፈ አርዕድ አዉርሰዉ ሞቱ ።

አፄ ሠይፈ አርዕድ (1327-1355 ዓ.ም) ፡ - የዚህ ንጉሰ ነገስት ታሪክ ነገስት እንደሚለዉ በግዛት ዘመኑ ወደ ላእላይ ግብፅ ሄዶ በግብር መክንያት በግብፅ ታስረዉ የነበሩ የግብፅ ጳጳሳትና ክርስትያኖችን እንዳስፈታቸዉ ይገልፃል ። ሙሴ ረኔ ባሴትና አል መቅሪዝ የተባሉ የአረብ ፀሀፊዎች እንደፃፉት የግብፅ ሱልጣኖች በሊቃነ ጳጳሳቱ ምክንያት የሚያገኙት ግብር ከፍተኛ ስለነበረ አሁን በአፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመን ደግሞ በግብፅ ጳጳሶች ላይ ሌላ ተጨማሪ ግብር ሥለተጣለባቸዉ እምቢ ያሉት ለእስር በመዳረጋቸዉ በግብፅ ንጉስና በአፄ ሰይአፈ አርዕድ መካከል መጠነኛ ግጭት ተፈጠረ ።

በዚህም ምክንያት አፄ ሰይፈ አርዕድ ወደ ላዕላይ ግብፅ ሰረሰዊታቸውን አስከትለው እስከ ግብፅ ድንበር ድረስ በመሄድ ዉጊያ እንደተጀመረ ወዳዉኑ በግብፁ ሱልጣን ሞግዚት መካሪነት ጦርነቱ ቆሞ እስረኞቹ እንዲፈቱ ስለተደረገ የኢትዮጵያ ወታደሮችምን ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ አድርገዋል ።

አፄ ሰይአፈ አርዕድ በ1355 ሲሞቱ ልጃቸው ዉድም አስፈሬ ነግሶ ኢትዮጵያን ለ10 ዓመት ያህል አስተዳድሯል ። የአፄ ዉድም አስፈሬ ግዛት ዘመን ምን ይመስል እንደነበር ሰፋ ያለ ታሪክ ባለመገኘቱ" አመተ ጠፍ" ወይም ታሪከ ጠፍ /ታሪክ የሌለዉ/ በማለት ታሪከ ነገስቱ ይገልፃል ። ሌሎች የዉጭ ሀገርና የሀገር ዉስጥ

ፀሀፍትም ለፅሁፍ የሚበቃ ታሪክ እንደሌለዉ ገለፀዋል ።

አፄ ዳዊት (1365-1395 ዓ.ም) ፡ - አፄ ዳዊተ

ስልጣኑን የተረከበዉ ከወንድሙ ከአፄ ዉድም አስፈሬ ነዉ ።

በኢትዮጵያ ለ30 ዓመታት ያህል ስለነገሰዉ ስለአፄ ዳዊት" Historia rerum ISL amitcarumin Abissinia"/ በሐበሻ የእስላም ነገስታት ታሪክ/ በሚለዉ መፀሀፉ አልማቅሪዝ የተባለዉ ግብፃዊ ጸሐፊ፣ እነ እረኔ ባሴት፣ እነ ሞሪዮ ኩልቦና ሌሎችም ከፃፉት የተዉጣጣዉ ታሪኩ ሲገለጽ የሚከተለዉን ይመስላል ።

በአፄ ዳዊት ዘመን በተለያዩ የግብፅና የኢትዩጵያ መልእክተኞች አማካኝነት በተደረጉ ስምምነቶች የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር ። በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል ከቃላት ያለፈ ግንኙነት በመደረጉ የግብፁ ሱልጣን በመደሰቱ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ወደ ግብፅና ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ በየመንገዱ ችግር እንዳይገጥመዉ፣ በኢየሩሳሌምም የሚገኙ መነኮሳትና ምእመናንም ያለችግር እንዲንቀሳቀሱና በሰላም እንዲኖሩ አዘዙ ።

በዚህ ምክንያት የኢየሩሳሌም ፓትሪያርክ ኢትዩጵያ መጥተዉ በተመለሱ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትንና ንግስት ኢለኒ አገኙት የሚባለዉን የእዉነተኛዉን መስቀል እንጨት /የግማደ መስቀሉን/ አንድ ጉማጅ እንዲልኩለት ለእየሩሳሌም ባለስልጣናት ጥያቄ አቀረበ ።

በጥያቄዉ መሰረትም የግማደ መስቀሉ ጉማጅ ጋር ቅዱስ ሉቃስ የሳለዉ የሚባለዉን የእየሱስንና የማርያምን ምስል በአንድነት የያዘዉን ስዕል /ምስለ ፍቁር ወልዳ/ና በተጨማሪም አክሊለ ሶክ እንዳደረገ የሚያሳየዉን ምስል /ኩርዓተ ርዕሱ/ ሰጥተዉ ላኳቸዉ ።

የግማደ መስቀሉ አንድ አካል ኢትዩጵያ የገባዉ በመስከረም 10ቀን 1380ዓ.ም ነዉ ። ግማደ መስቀሉም ወደ ግሸን ደብረ ከርቤ እስከሚሄድ ድረስ እዚያዉ ሸዋ /ተጉለት/ ቤተመንግስት አቀራቢያ ባለ ቤ/ን ተቀመጠ ። በኋላ በዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ ግማደ መስቀሉ አሁን ወደሚገኝበት ወሎ /አምባሰል/ ግሸን ተራራ ላይ ወደሚገኘዉ ደብር /ግሸን ደብረ ከርቤ/ ተዛወረ ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መስቀሉ ኢትዮጵያ ዉስጥ የገባበት መስከረም 10 ቀን የአፄ መስቀል ባዕል ተብሎ እንዲታሰብና መስከረም 17 ዋናዉ የመስቀል ባዕል

ሆኖ በተለይ በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ላይ በታላቅ ስነስረዓት እየተከበረ ይገኛል ።

በአፄ ዳዊት ጊዜ ብዙ የእርስ በርስ ጦርነቶች ቢኖሩም እርሳቸው ግን የሞቱት በፈረስ እርግጫ ነዉ ። አፄ ዳዊት ኢትዮጵያን ለ28 ዓመታት ያህል ካስተዳደሩ በኋላ ጥቅምት 9ቀን 1395 ዓ.ም በፈረስ እርግጫ ግንባራቸዉን ተመተዉ ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል ።

አፄ ቴዎድሮስ 1ኛ (ከ1395-1399 ዓ.ም) ፡ - አፄ ቴዎድሮስ 1ኛ የአፄ ዳዊት ልጅ /የዘርያዓቆብ ወንድም/ ናቸው ። አፄ ቴዎድሮስ 1ኛ ለዬት የሚያደርጋቸው እንደ አባቶቻቸው በርካታ ሚስቶችና እቁባቶች ያልነበሯቸውና በአንድት ሚስት ብቻ የተወሰኑ ነበሩ ። ይህ አይነቱ የትዳር ሂደት ካለመለመዱ የተነሳም ታምረኛና አምላክን የሚፈሩ ንጉሰ ነገስት አስብሏቸዋል ።

ቤተክርስትያኗ ከመጠን በላይ የምትሰበስበዉን ገንዘብ እንድትቀንስ ባደረጉት ሙከራ በደሃዉ ህዝብ ዘንድ እጅግ ይወደዱ የነበሩት ንጉሰ ነገስት አፄ ቴዎድሮስ 1ኛ ከ4 ዓመት የግዛት ዘመን በኋላ ሰኔ 29 ቀን 1399 ዓ.ም በህመም ምክንያት አርፈው እዚያዉ ወሎ አማራ ሣይንት ተቀብረዋል ።

አፄ ይስሐቅ (ከ1399-1414 ዓ.ም) ፡ - አፄ ይስሐቅ የአፄ ዳዊት ልጅ /የአፄ ቴዎድሮስ 1ኛ ወንወድም/ ነዉ ።

አፄ ይስሐቅ 15 ዓመት ገዝቶ በ1414 ዓ.ም ሲሞት አፄ ህዝበናኝ 3 ዓመት ከ6ወር፣ አፄ በድልናኝ 1 ዓመትና አፄ አደም እያሱ 7 ዓመት በንግስና ቆይተዋል ። የነዚህ ነገስቶች የግዛት ዘመን ከማጠሩም በላይ ሁሉም ከአፄ ይስሐቅ ጀምሮ እስከ አፄ ዘርያዕቆብ ድረስ የተፈራረቁት አራት ወንድማማች ነገስታት በእርስ በርስ የዙፋን ሽኩቻ ጊዜያቸዉን እንዳሳለፉ ይገለፃል ።

አፄ ዘርዓያቆብ (ከ1426-1460) ፡ - ዘርዓየቆብ ከመንገሳቸዉ በፊት አፄ ላሊበላ ባስገነቡት የግሸን አምባ ገዳም /ወሎ አምባሰል/ ውስጥ ሲማሩና ሲመራመሩ ነዉ ያደጉት ። ሲኖዶስና ህጉን እጅግ የመረመሩና ያሻሻሉ ናቸዉ ። ቤተ መንግስቱን ከተጉለት ወደ ደብረ ብርሃን ያዛወሩትና የደብረ ብረሃን ቤተ መንግስትን የገነቡት አፄ ዘርያዓቆብ ናቸዉ ። ቁጥር ስፍር የሌላቸዉ /እጂግ በጣም ብዙ/ መፅሐፍትን ፅፈዋል ። ከፃፏቸዉ መጽሀፍት ዉስጥ

ተዓቅቦ ሚስጥር /ስለቁርባን ህግ የሚያትት/፣ መፅሀፈ ሚልድ /ስለ ወርሐዊ ክብረ ባዕላት የሚየትት/፣ መጽሐፈ ባህርይ /ስለ ኑዛዜና ተያያዥ ጉዳዮች የሚያትት/…ወዘተ ይገኙበታል ። እጅግ ሲበዛ የጦር ሜዳ ጀግና ጨካኝ ነበሩ ። ከሚስቶቻቸዉ ከወለዷቸዉ 18 ልጆቻቸዉ ዉስጥ በባዕድ አምልኮ ምክንያት ጥቂቶቹን ገድለዋቸዋል ።

ከእሳቸዉ በፊት ከነበሩት የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ነገስታት አንፃር እሳቸዉ ስመ ጥርና ገናና እንደነበሩ ይነገራል ። የተሻለ የመንግስት አወቃቀርና በርካታ የማዕረግ ስሞች የተፈለሰፉትም /የተፈጠሩትም/ በእርሳቸዉ ጊዜ ነበር ። ፊት አዉራሪ /ቀድሞ የሚጓዝ ና የሚዘምት/፣ ቀኝ አዝማች /በቀኝ በኩል የሚዘምት/፣ ግራ አዝማች /በግራ በኩል የሚዘምት/፣ ደጅ አዝማች /ከኋላ የደጀን ጦር አዝማች/፣ በጅሮንድ /የመንግስትን ሚስጥር በጆሮ ነጋሪ/፣ የግምጃ ቤት /ቁልፍ ያዥ/፣ ባላምባ ራስ /ራስ አምባ ጠባቂ/፣ ነጋአድራስ /የንግድ ወኪል/፣ ባልደራስ፣ ሻለቃ፣ መቶ አለቃ፣ ገበዝ፣ መኮንን ጭቃ ሹም…. ወዘተ የሚሉ ለመዘርዘር በጣም የበዙ የማዓረግ ስሞችን የፈለሰፏቸዉ አፄ ዘርዓያቆብ ናቸዉ ።አፄ ዘርዓያቆብ ኢትዮጵያን ለ34

ዓመታት ካስተዳደሩ በኋላ ጳጉሜ 3 ቀን 1460 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።

አፄ እደ ማርያም (ከ1460-1470 ዓ.ም) ፡ - እደ ማሪየም አባታቸዉ ሲሞት የ20 ዓመት ወጣት የነበሩ ሲሆን በ1460 ዓ.ም ወረኢሉና አማራ ሳይንት ይገኝ በነበረዉ ማረፊያ ቤታቸዉ ንጉሰ ነገስትነታቸዉን ፈፀሙ ።

አማራ ሳይንት የትሮንስ ቤተከክርስትያንን በማስገንባት ከእሳቸዉ በፊት የነበሩ የ18 ነገስታትንና ጳጳሳትን አፅም ከያለበት አስለቅመዉ እዚሁ ቤ/ን ዉስጥ እንዲቀመጥ አድርገዋል ።

አፄ እደ ማርያም ኢትዮጵያን ለ10 ዓመት ካስተዳደሩ በኋላ በወጣትነታቸዉ /በ30 ዓመታቸዉ/ በ1470 ዓ.ም ባልታወቀ ምክንያት ሲሞቱ የተካቸዉ እስክንድር የተባለዉ ልጃቸዉ ነበር ።

አፄ እስክንድር (ከ1470-1486 ዓ.ም) ፡ - አፄ እስክንድር አባታቸዉ በተናዘዘላቸዉ በሰረት በ6 ዓመታቸዉ የንጉሰ ነገስትነት ስልጣኑን ሲይዙ

እናታቸዉ እመቤት ሮማን ወርቅ እንደ ሞግዚት፣ ግራ ብህትወደድ አምደሚካኤል፣ ቀኝ ብህትወደድ በድላርአድ ሆነዉ በእንደራሴነትና በአማካሪነት ተሾሙላቸዉ ።

ፖርቱጋሎች ለመጀመሪያ ጊዜ መልእክተኛ ልከዉ ከክርስትያኗ አገር ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅ ለመሆን መፈለጋቸዉን ያሳወቁት በአፄ እስክንድር ጊዜ ነዉ ።በመጨረሻም ከሀሰብ አንጎት/ደላንታ/ ጨዉ እያመላለሱ ይነግዱ የነበሩ ነጋዴዎች ስላመፁ አፄ እስክንድር ጦራቸዉን አሰባስበዉ ለዉጊያ እየተጓዙ ሳለ በሌሊት ተደብቀዉ ገደሏቸዉ ።

አፄ ናኦድ (ከ1487-1500) ፡ - በዘመኑ ንግስና በውርስ ብቻ ስለሚገኝ የስልጣን ተቀናቃኝ እንዳይሆኑ በመስጋት የነገስታት ወንድሞችና እህቶች በግሸን አምባ በልዩ ጥበቃ ሥር ሆነዉ ትምህርታቸዉን እየተከታተሉ ይቀመጡ ነበር ። ከዚያም የቤተክህነትና የቤተ መንግስቱ ባለስልጣኖች ተመካክረዉ የመረጡትን በአዋጅ ያነግሳሉ ። ይህ የሚሆነዉ የበፊቱ ንጉሰሰገስት ሳይናዘዝ ከሞተ ነዉ ። አፄ እስክንድር ደግሞ ሳይናዘዙ ነበር የሞቱት ።

በዚህ መሰረት የ7 አመቱን ህፃን የአፄ እስክንድር ልጅ የነበረዉን ልዑል እንድሪያስን ከግሸን አምባ አስመጥተዉ "አምደ ጽዮን 2ኛ" በሚል ሥመ መንግስት አነገሱት ። ነገር ግን አምደ ጽዮን 2ኛ ኢትዮጵያን 7ወር እንደገዙ ባልታወቀ ምክንያት ድንገት ሲሞቱ የአፄ እስክንድር ወንድም የነበሩትን ናኦድን ከአምባሰል /ግሸን አምባ/ አስመጥተዉ አነገሷቸዉ ።

አፄ ናኦድ በመጨረሻ ዘመናቸዉ በመንፈሳዊ ሥራ ተጠምደዉ ከ30 የሚበልጡ መንፈሳዊ መፅሐፍትን በእጃቸዉ ፅፈዉ ለእያድባራቱ አበርክተዉ በ35 ዓመታቸዉ ከዚህ አለም በሞት ተለዩ ።

አፄ ልብነ ድንግል (ከ1500-1532 ዓ.ም) ፡ - አፄ ልብነ ድንግል የአፄ ናኦድ ብቸኛ ወንድ ልጅ ናቸዉ ። ሰፊ ጊዜያቸዉን መፀህፍት በመመርመርና ሊቃዉንትን በማከራከር ነዉ ያሳለፉት ።

የአፄ ልብነ ድንግል ዘመን እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ካካሄደቻቸው 7 እጅግ ትልልቅ ጦርነቶች ውስጥ አንዱ የሆነው ጦርነት ከግራኝ አህመድ ጋር የተካሄደበት ዘመን ነበር /ኢትዮጵያ ያካሄደቻቸው 7 እጅግ ትልልቅ ጦርነቶች

የሚባሉት ግራኝ ከወሎ ጋር፣ የጁ ከሸዋ ጋር /ዘመነ መሳፍንት/፣ የአፄ ሚኒሊክ ሀገር የስፋት ዘመቻዎች፣ ወሎ ከኢጣሊያ ጋር /አድዋ/፣ የሰገሌ ጦርነት /በልጅ እያሱ ምክንያት/፣ ኢትዮጵያ ከ ኢጣሊያ ጋር /የኢጣሊያን ዳግም ወረራ/ና ደርግ ከ ኢህአዴግ ጋር ናቸው ።

አፄ ልብነ ድንግል ከሸዋ፣ ከወሎ፣ ከየጁ፣ ከትግራይና ከሌሎች ግዛቶች የተሰበሰበ ሰራዊታቸዉን ይዘዉ፤ ግራኝ ደግሞ ከሐረር እስከ ኤደን ጠረፍ የሚገኘዉን ህዝብ ይዘዉና በአረቦቹ የወቅቱ ዘመናዊ መሳሪያ እየታገዙ እጅግ ከባድ ጦርነት የተካሄደበት ዘመን ነበር ። ግራኝ አህመድ (ከ1519-1534) ፡ - ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋለሁ ።

በነገራችን ላይ ከግራኝ ጋር የተካሄደውን ጦርነት የኢትዮጵያ የእርስ በርስ ጦርነት አድርጎ መውሰድ አይቻልም /ሐረር የዛኔ የኢትዮጵያ አካል አልነበረችም/ ። ስለሆነም ባይሳካላቸውም ለመጀመሪያ ጊዜ ታላቂቷን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ከመሞከር አንፃር ግራኝ የመጀመሪያው ናቸው /ታላቂቷን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ሙከራ ያደረጉት ነገስታት ሁለት ብቻ ናቸው፤ እነሱም አፄ ሚኒሊክና ግራኝ አህመድ ናቸው፤ ግራኝ ታላቂቷን ኢትዮጵያ ለአጭር ጊዜ መፍጠር ቢችሉም ዘላቂ ሊሆን ግን አልቻለም፤ ታላቂቷን ኢትዮጵያ በዘላቂነት መፍጠር የቻሉት አፄ ሚኒሊክ ብቻ ናቸው/ ። ወደ ርዕሳችን ስንመለስ ።

ግራኝ አህመድ የልጅነት ጊዜዉን በዘላይ /ሁባት/ ነዉ ያሳለፈዉ ። በአሚር ማህፉዝ /የሐረርና የአዳል ባላባት/ ቤትም እንደ አገልጋይ ሆኖ ሲኖር በፈረስ ግልቢያ፣ በጦር ዉርወራና በአተኳኮስ ልዩ ብቃት እንዳለዉ ያዩ ሁሉ አድናቆታቸዉን ይቸሩት ነበር ።

አባቱን ገራድ ኢብራሂምን የገደለበት የዘይላዉ ሱልጣን አቡ በከር ነበር ። ከአባቱ ሞት በኋላም የአባቱን ሀብት ወርሶ ተከታዮች አፈራ ። ከዚያም የማህፉዝን ልጅ አገባ ። እሷን ካገባ በኋላ የሐረር ወላስሞችን ቤተመንግስት በይገባኛል አይገባህም ክርክርና ጦርነት አሸንፎ ቤተመንግስቱን ወረሰ ።

ቀደም ብለዉ ሥራቸዉን የጀመሩት ቱረኮች ወዳዉ የዘይላ ሸክ ብለዉ ሾሙት ። ቀጥሎም በሐይለኛነቱና በጋብቻዉ ምክንያት የሐረርና የአዳሎች /አፋሮች/ ሁሉ ዋና መሪ ተባለ ። የማዕረግ ስሙም “ኢማም መሐመድ ”ተሰኘ ። ቱርኮችም አዳዲስ የጦር መሳሪያ ይሰጡት ጀመር ። ሁለት የወቅቱን ዘመናዊ መድፎች ተረከበ ።

የአዳል ሱልጣኖች ወይም የሐረር ወላስሞች ያደርጉት እንደነበረዉ ሁሉ ግራኝ አህመድም በማእከላዊ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ለመነሳት ዝግጅት ማድረግ ጀመረ ። አላማዉንም ለሐረር፣ ለሱማሌና ለአዳል ህዝቦች አሳወቀ ።

ግራኝ በቂ ዝግጅት ካደረገ በኋላ ሠራዊቱን በተሻለ የጦር መሣሪያና የጦር ስልት አደራጅቶ ማጥቃት ጀመረ ። አፄ ልብነ ድንግልም ይህን ሲሰሙ ፋኑኤል የተባለዉን የዋግ /የወሎ ሰቆጣ አካባቢ/ ሀገረ ገዥን ሰራዊቱን አስከትሎ ወደ አዳል እንዲዘምት አዘዙት ። ፋኑኤልም ወደ አዳል ዘምቶ አንድ ክፍል የግራኝን ጦር ድል አድርጎ አካባቢዉን አስመልሶና አስገብሮ ሊመለስ ሲዘጋጅ ግራኝ ሌላ ጦር ይዞ መጥቶ ተዋጋና አሸንፎ ፋኑኤል የሰበሰበዉን ሀብት ሁሉ አስመልሶ በድል አድራጊነት የለቀቃቸዉንም ቦታዎች እንደገና አስመለሰ ።

ግራኝ በድል ላይ ድል እያገኘ መጥቶ በ1520ዓ.ም ይፋት ላይ ሌላ ከባድ ዉጊያ ተካሄደ ። አሁንም ግራኝ ድል ቀናዉ ። የንጉሱ ጦር አዝማች የነበረዉ የሸዋው ወናግ ጃንም ተገደለ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዋናዉ በወሎ፣ በትግራይና በሸዋ ኦሮሞዎች ላይ ታላቅ እልቂት ያስከተለዉና “የሽንብራ ኩሬ ጦርነት” በመባል የሚታወቀዉ እጅግ ዘግናኝ ጦርነት ተካሄደ ።

በድል ላይ ድል እየተቀዳጀ ሲመጣ ንጉሱ ራሳቸዉ ግራኝን ለመደምሰስ ተነሱ ። አዝማች ራሳቸዉ አፄ ልብነ ድንግል ሆነዉ የሽምብራ ኩሬ እጅግ ከባድ ጦርነት ተጀመረ ። የንጉሱ ጦር ኋላ ቀር መሣሪያ ከመታጠቁም በተጨማሪ የአደረጃጀት፣ የአመራርና የዉጊያ ስልት ጉድለት ነበረበት ።

መጋቢት 13 ቀን 1521 ዓ.ም ሙሉ ቀን በተደረገዉ እልህ አስጨራሽ ዉጊያ ምሺት ላይ ሙሉ በሙሉ በግራኝ የበላይነት ተደመደመ ። በንጉሱ በኩል ብቻ ከ20ሺ በላይ ኢትዮጵያዊያን በአንድት ቀን አለቁ ። ከዚህ በኋላ ባሉት ተከታታይ ጊዜየቶችም በየጊዜዉ ጦርነቶች ቢካሄዱም ንጉሱና ሰራዊታቸዉ የሚቋቋሙት አልሆነም ።

እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ከፍተኛ ህዝብ ያለቀበት ጦርነት ከግራኝ ጋር የተካሄደዉ ጦርነት ነዉ ። በአጠቃላ ከግራኝ ጋር በተካሄደዉ ጦርነት ያለቀዉ ህዝብ በደርጎኢህአድግ የእርስ በርስ ጦርነት ካለቀዉ ህዝብ ከ3 እጥፍ በላይ ይበልጣል ። ሌላዎቹን ግንባሮች ሳይጨምር በሽምብራ ኩሬ የአንድ ቀን ጦርነት ብቻ በንጉሱ በኩል ብቻ ከ20ሺህ በላይ ህዝብ አልቋል ።

የዓለማችን ቁጥር አንድ ምቹ እስር ቤት መያዝ

/የግሸን አምባ መያዝ/፣ ወሎ አምባሰል

ልዑላን አምባ /ግሸን አምባ/ ለዘመናት የህገሪቱ የልዑላን እስር ቤትና የመንግስት ግምጃ ቤት በመሆን አገልግላለች ። ከ13ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አፄ ምኒሊክ ግማሽ ዘመን ድረስ የመንግስታቱ ሀብት የሚከማቸዉና የስልጣን ተቀናቃኝ ይሆናሉ የሚባሉ ልዑላን ይታሰሩ የነበረዉ ግሸን ተራራ ላይ ነበር ። በአሁኑ ወቅት ከእስራኤል የመጣዉና ክርስቶስ የተሰቀለበት እዉነተኛ መስቀል ግማሹ /ግማደ መስቀል/ የተቀመጠበትና ‘’ግሸን ደብረ ከርቤ’’ በመባል የሚታወቀዉ ገዳም ነዉ ።

የግሸን ተራራ የሚገኘዉ ወሎ ክ/ሀገር አምባሰል ወረዳ ዉስጥ ነዉ ። ግሸን ደብረ ከርቤ ገዳም፣ ተራራ አናት ላይ ያለ በገደል የተከበበ መስቀለኛ ሜዳ ነዉ ። ወደ ተራራዉ መዉጣት የሚቻለዉ በአንድት ጠባብ መንገድ ብቻ ነዉ ። ተራራዉ ከተወጣ በኋላ የሚገኘዉ መስቀለኛ ሜዳ መሀል ላይ ዉሀ አለ ። ዉሀዉ ከየት እንደሚመጣ አይታወቅም ግን አመቱን ሙሉ አይጠፋም ። በየአመቱ መስከረም 21 ቀን ለሚከበረው የንግስ ባዕል ወደ ግሸን ደብረ ከርቤ የሚገባው በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ሁሉ የሚጠጣው ይህን ሜዳው በሀል ላይ የሚገኘውን ውሀ ነው፤ ነገር ግን አንድም ሰው ታሞ አያውቅም ። በአሁኑ ወቅት አፄ ላሊበላ ሜዳዉ መሀል ላይ ካስገነቡት ቤተክርስትያን በተጨማሪ የሜዳዉ ሁሉም ክንፎች ላይ ሌሎች ቤተክርስቲያናት ተገንብተዉ ይገኛሉ ። ግማደ መስቀሉ የሚቀመጠዉ ግን ሜዳዉ መሀል ላይ ባለዉ የእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን ዉስጥ ነዉ ። ግማደ መስቀሉ ከእየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ የመጣዉ በአፄ ዳዊት ዘመን ነዉ ።

ብዙ የዙፋን ተቀናቃኝ ወንድሞችና እህቶች ያሉባቸዉ ነገስታት፣ “ከፖለቲካ ጣጣ ነፃ ሆነዉ” ይኖሩ ዘንድ ዙፋን ተቀናቃኝ ዘመዶቻቸውን

መዉጫና መዉረጃዉ እጅግ ከባድ በሆነዉ በዚህ ተራራ ላይ እንዲቀመጡ ለማድረግ ወሰኑ ፡፡ ከዚህ ጊዜ አንስቶ ምናልባት በአለም ታሪክ አምሳያ የሌለዉ የልዑላን ቤተሰቦች በድሎትና በምቾት የሚኖሩበት እስር ቤት ተፈጠረ ፡፡ የነገስታት ቤተሰብ አባላት ሁሉ በዚህ መወጣጫ በሌለዉ ጫፈ ጠፍጣፋ አምባ ላይ ሀሳብ የለሽ ኑሮ ይኖሩ ነበር ፡፡

ሁሉም ነገር እየተመረጠ ይቀርባል፤ በየቀኑ የተመረጠ የፊሪዳ /የእርድ/ አቅርቦት በጥንቃቄ ይቀርባል፣ የተመረጡ መጠጦች /የጠጅና የአረቂ መጠጦች/ በእየቀኑ በጥንቃቄ ይቀርባሉ፣ በጌጣጌጥ የተዋቡና ንብረት የተሞሉ መኖሪያ ቤቶች አሏቸዉ፣ የሚጠይቁትን ያህል አገልጋይ /ገረድና አሽከር/ ይመደብላቸዋል፣ ምርጥ የክብር አልባሳቶች በየጊዜው ይቀርባሉ፣ መፀሀፍት የተሞሉ መዝናኛ ቤቶች አሏቸዉ፣ ከመንፈሳዊያን ሊቃዉንት ጋር በስፋት የመከራከርና የመማር እድል አላቸዉ፣ በአስቸጋሪዉ የቅኔ ጥበብ የመሰልጠን እድል አላቸዉ… ወዘተ ፡፡ ከዚህ ቀላል የሀሳብ የለሽ ኑሮአቸዉ ዉስጥ አስከፊ የሆነ አንድ ነገር ቢኖር፣ በጥበቃዉ መጠንከርና በገደሉ ጥርብነት የተነሳ የማምለጥ ተስፋ የተዘጋ መሆኑ ብቻ ነዉ ፡፡

በተጨማሪም ይህ አምባ የሀገሪቱ ዉድ ንብረቶች ማከማቻ ነበር ፡፡ መግቢያ በሩ በተመረጡ ሻለቆችና በጣም በሰለጠኑ ወታደሮች በብዙ እጥፍ ምሽጎች እጅግ ጥብቅ በሆነ ሁኔታ ነበር የሚጠበቀዉ ፡፡ ከ13ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አምባ ግሸን የቤተመንግስትና የኢትዮጵያ ምሽግ ሆኖ እንደመቆጠሩ ገናና ስም የነበረዉ አምባና ለኢትዮጵያ ታላቅነትና ኃይል ምሳሌ ሆኖ የቆየ መሆኑ አይዘነጋም ፡፡ የግሸን አምባ መያዝ ለግራኝ የድል አድራጊነት ፍፃሜ እንደመሆኑ ለክርስቲያን ወገኖች ደግሞ ተስፋ የሚያስቆርጣቸዉና የመጨረሻ ሽንፈት ይሆናል ፡፡

ግራኝ ይህን ተራራ ለመያዝ ለ12 አመታት ያህል የማያቋርጥ ጦርነት አድርጓል ፡፡ ግራኝ በግሸን አምባ ዙሪያ ካደረጋቸዉ እጅግ ብዙ ከባባድ ጦርነቶች መካከል ሦስቱን ብቻ መርጠን እናያለን ፡፡ ግራኝ ከብዙ ከባባድ ግሸንን የመያዝ ጦርነቶች በኋላ ልዩ ዝግጅትና ልምምድ አድርጎ ይህን አምባ ለመያዝ በ1523ዓ.ም የላካቸዉ የጦር አለቆች ኡስማንና ማታን ይባላሉ ፡፡ እነኝህ አለቆች በሁለት አቅጣጫ ከባድ ግሸንን የመያዝ ትንቅንቅ አደረጉ ፡፡ ነገር ግን ግሸን ላይ በመሸገው ምርጥ ጦር ክፉኛ ተመትተው፣ ወታደሮቻቸዉን አስጨርሰዉ ሳይሳካላቸዉ ተመለሱ ፡፡

አሁንም ግራኝ ለ3 አመታት በርካታ ግሸንን የመያዝ ተከታታይ ውጊያዎችን ቢያደርግም የሚቻል አልሆነም ። እናም ለሌላ ልዩ ዘመቻ ተዘጋጀ፤ ልዩ ዝግጅት ካደረገ በኋላ በ1526ዓ.ም እራሱ የጦር መሪ በመሆን አምባዉን ለመያዝ እጅግ ከባድ ግሸንን የመያዝ ትንቅንቅ አካሄደ ። ሆኖም የግሸን ጠባቂው ጦር በርትቶ ተዋጋ፤ በተለይ በግራኝ በኩል ከፍተኛ እልቂት ደረሰ ። ግራኝም ግሸንን የመያዝ ትንቅንቁን አብዛኛው ሰራዊቱ እስኪያልቅ ድረስ ቀጠለ ሆኖም አልሆነም፤ እሱም ወታደሮቹን አስጨርሶ ሳይሳካለት ጥቂት የተረፋ ወታደሮቹን ይዞ ተመለሰ ።

ግራኝ የግድ አምባ ግሸንን መያዝ አለበት፤ ግሸንን መያዝ የፍፃሜ ድል እንደማለትም ብቻ ሳይሆን የመንግስት ንብረት በሙሉ የተቀመጠዉ እዚያዉ አምባ ላይ ነዉ ። እናም ግራኝ አሁንም ሌሎች ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን እያደረገ ትግሉን ቀጠለ፤ የመጨረሻዉን ጦርነት እንይ ።

አምባ ግሸን ላይ የሚወጣባቸዉ መንገዶች ሁለት ናቸዉ ። አንዱ በመንግስትና በህዝብ የሚታወቀዉ ዋናው በር ሲሆን በብርቱ ተመሸጎበታል ። ሁለተኛዋ ግን እንደ ዝንጀሮ እየተንጠላጠሉ በጭንቅ የሚወጡባት፣ በመንግስትና በህዝብ የማትታወቅ የስርቆሽ በር ናት፤ ይች የስርቆሽ በር በመንግስትና በህዝብ ስለማትታወቅ አትጠበቅም ። ግራኝም ከዚህ በፊት ባጠቃባቸዉ ጊዜቶች የዚችን በር መኖር አያዉቅም ነበር ።

ግራኝ አሁንም ለ5 አመት ያህል በርካታ ተከታታይና ከባባድ ግሸንን የመያዝ ጦርነቶችን ቢያደርግም አልተሳካም ። አሁንም ግሸንን የመያዝ ልዩ ዝግጅት ጀመረ፤ ከዚህ ልዩ ዝግጅት በኋላ በ1531ዓ.ም ግሸን አምባን ለመያዝ ግራኝ ያዘዘዉ ቪዚር ምጃሂድን ነበር ። ምጃሂድ በዉጊያ መሞከርን ትቶ አምባዉ ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ማፈላለግ ጀመረ ። በሸሸት አምባ ግሸን ዉስጥ ካሉት መሳፍንቶች አሽከሮች መካከል አንዱ ተገዝቶ በዚች የስርቆሽ በር ወርዶ ከምጃሂድ ጋር ተገናኘ ። ከዚህ በኋላ በዚሁ ሰዉዬ መሪነት ከፊሉ የምጃሂድ ጦር ሌሊቱን በዚችዉ የስርቆሽ በር እየቧጠጠ እየተንጠላጠለ አምባዉ ላይ ወጥቶ አደረ ። ከፊሉ ደግሞ ፊት ለፊት ተጠግቶ አደረ ። ሊነጋጋ ሲል በግሸን ጠባቂው ጦር ጀርባና ፊት ለፊት በያዙት የተሻለ ዘመናዊ መሳሪያ ታግዘዉ እጅግ ከባድ ማጥቃት ሰነዘሩ ። የግሸን ጠባቂው ጦርም ይህን ዙሪያዉን ድንገት የተሰነዘረበትን ያልተጠበቀ ከባድ ማጥቃት ለመቋቋም የሞት ሽረት ትግል አደረገ፤ ከፍተኛ እልቂት ተከሰተ ። ሆኖም በመሳሪያም በቁጥርም

ስለሚያንሱ የግሸን ጠባቂ ወታደሮች በሙሉ ተደመሰሱ ።የግሸን አምባ መያዝ በመላዉ ኢትዮጵያ እንደ ነጎድጓድ ተሰማ ። ለክርስቲያን ህዝቦች እልፈተ አለም እንደ ደረሰ ሆኖ ተሰማቸዉ ። ግሸን አምባ ለንጉሰ ነገስታቱ እንደ ዘዉዳቸዉና እንደ በትረ መንግስታቸዉ ለስልጣናቸዉና ለገናናነታቸዉ እንደ ምስክር ነበረች ። አምባዉ የመንግስታቱ ዋና ግምጃ ቤት ስለነበር እጅግ የታፈረና ጠንካራ ጥበቃና ቁጥጥር ያለበት ነበር ።

ይህ አምባ የመንግስታቱ ሁሉ ግምጃ ቤት ስለነበር እጅግ ዉድ የሆኑና ሊተኩ የማይችሉ የሀገሪቱ ቅርሶች በሙሉ በእዚች እድለ ቢስ ቀን አንድ ላይ ወደሙ ። የኢትዮጵያ የጥንት ስነ ፅሁፎች፣ የታሪክ፣ የእምነትና የባህል ቅርሶች በዚችዉ ተራራ አንድ ላይ ሆነዉ በአንድ ቀን ወደሙ ። የኢትዮጵያን ቅርስንና ታሪክን ከማዉደም አንፃር ይች እለት ተወዳዳሪ የላትም ።

የግራኝ ወታደሮች አሻራ ወሎ ላይ ብቻ የሚታየዉም በዚሁ ረጅም ጊዜ በወሰደዉ የግሸን አምባ ጦርነት ምክንያት ነዉ ። የግራኝ ሰራዊት ይህን አምባ ለመያዝ ለ12 አመት ያህል ወሎ ዉስጥ ተከማችቶ ሲታገል በመኖሩ ምክንያት የህዝቡ ሐይማኖት መቀየር ብቻም ሳይሆን የወሎ የቦታ ስሞችም ሳይቀር ተቀይረዋል ። የወሎ አንዳንድ ቦታ ስሞች /ኮምቦልቻ፣ ቆቦ ወዘተ/ በግራኝ ወታደሮች የተሰየሙ የሐረር የቦታ ስሞች ናቸዉ ።

አፄ ልብነ ድንግልም ከሚስታቸዉ ከሰብለ ወንጌልና ከልጆቻቸዉ ጋር በግሸን አምባ፣ በሣይን ወዘተ ከዋሻ ዋሻ፣ ከተራራ ተራራ እየተደበቁ ኖረዉ በበሽታ ምክንያት በ1532 ዓ.ም አረፉ ።

በግራኝ አህመድ ዘመን ጎጃም ጣና ሐይቅ አካባቢ /ደምቢያ/ የፖለቲካና የሐይማኖት ማዕከል ነበረች ። ግራኝ አህመድ መቀመጫቸዉን ጎጃም ጣና ሐይቅ አካባቢ ደምቢያ ላይ በማድረግ አገሪቱን ማስተዳደራቸዉን ቀጠሉ ።

አፄ ገላዉድዎስ (1532-1551) ፡ - አፄ ልብነ ድንግል ሲሞቱ ልጃቸዉ ተስፋቢስ የሚመስለዉን ዙፋን ወረሰ ። እናም ዋና መቀመጫ ተብሎ የተወሰነ ቤተመንግስት ስላልነበራቸዉ በወሎና በትግራይ አካባቢ ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ ነዉ ትግራይ አገር ዉስጥ ዘዉድ የጫኑት ።

በነገሱ በአንድ ወራቸዉ ከግራኝ አህመድ ጦር ጋር ተጋጥመዉ ቀላል የማይባል ጀብዱ ስለፈፀሙ ወጣቱና መኳንንቱ ደስ ተሰኙ ። በተምቤይንና በሽሬ የነበረዉን የግራኝን ጦር በነበራቸዉ ጦር አሸንፈዉ፣ ለግራኝ

የወገነዉንና የአካባቢዉ የጦር አዝማች የነበረዉን ዮናታንን ከነሰራዊቱ ሙሉ በሙሉ ገድለዉ የሰሜኑን ግዛታቸዉን አደላደሉ ።ይህ ከተፈፀመ ከወራት በኋላ በጉጉት ይጠበቁ የነበሩት 300 የፖርቹጋል ወታደሮች ቅኝ ግዛቷ ከነበረችዉ ከህንድ ተነስተዉ ምፅዋ ደረሱ ። የፖርቹጋል ወታደሮች የወቅቱን ዘመናዊ መሳሪያ ከመታጠቃቸዉም በተጨማሪ 26 መድፎችን ይዘዉ መጥተዋል ። ወዳዉም ግራኝ የቱርኮችን ርዳታ ጠየቀ ።

አፄ ገላዉድዎስ በፖርቹጋሎች እየታገዘ አብዘሀኛዎቹን ሰሜናዊ ግዛቶችን እየተቆጣጠረ ሳለ ግራኝ ይጠብቃቸዉ የነበሩ 900 የቱርክ ወታደሮችና ሌሎች ከየመን ሱልጣን የተላኩ ጋር ባጠቃላይ ወደ 2ሺ የሚሆኑ ወታደሮች ከዘመናዊ መሳሪያ ጋር ደረሱለት ።

እናም ግራኝ በነዚህ 2ሺ የአረብ ወታደሮች እየታገዘ ሰሜናዊ ግዛቶቹን ለማስመለስ በከፍተኛ ሁኔታ ማጥቃት ጀመረ ። በተካሄደዉ ከፍተኛ ጦርነት የፖርቹጋሎች መሪ ክሪስቶፍ ደጋማና ሌሎች 160 የፖርቹጋል ወታደሮች አየቆሰሉ እየወደቁ ተማረኩ ። ይህ ጦርነት በግራኝ የበላይነት ቢጠናቀቅም ንጉሱ ተስፋ ባለመቁረጥ ለሌላ ጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ ።እናም ንጉሱ ከትግራይ፣ ከየጁና ከሌሎችም የወሎ አካባቢዎች የተዉጣጣ አዲስ ሰራዊት አዘጋጅተዉ ከበፊቱ ጦርነት ከተረፉት 140 የፖርቹጋል ወታደሮች ጋር በማቀናጀት ማጥቃት ጀመሩ ። በ1534 ዓ.ም ጎንደር ወገራ በተባለ ቦታ ሲደርሱ ከፍተኛ ጦርነት ተካሂዶ የግራኝ የበታቾች አነሲድ አህመድ፣ እንገራዱ ኡስማንና ሌሎች ታላላቅ የጦር አበጋዞች ተገደሉ ። የተረፉትም የተወሰኑ ሲማረኩ ሌላወቹ ወደ ጎጃም ሸሹ ። ከዚያም እንደገና የ6 ወር ዝግጅት ካደረጉ በኋላ በ1535 ዓ.ም የግራኝ ቤተመንግስት ወደ ነበረበት ወደ ጎጃም ጣና ሐይቅ አቅጣጫ ማጥቃት ጀመሩ ። አፄ ገላዉድዎስ ጦራቸዉን እየመሩ ጎጃም ከደረሱ በኋላ ግራኝ የሰራቸዉን መስጊዶች እያፈረሱ ወደ ቤተመንግስቱ ደንቢያ ተጠጉ ። የካቲት ወር 1535 ዓ.ም ደንቢያ ቤተመንግስቱ አካባቢ ንጉሱ 8ሺ፣ ግራኝ 13ሺ ወታደሮች አሰልፈዉ በተደረገ ከባድ ጦርነት ግራኝ አህመድ በጥይት ተመትቶ ሞተ፣ ባለቤቱና ሌሎች የተረፉ ወታደሮችም አገር እያቆራረጡ ወደ ሐረር ሸሹ ፡ በዚህ መልኩ አፄ ገላውድዎስ መላዋን ሀገሪቱን ከተቆጣጠሩ በኋላ ተመልሰው መቀመጫቸውን ሰ/ሸዋ ላይ አደረጉ ።

በኋላ በ1551 ዓ.ም ኑር አህመድ የተባለዉ የግራኝ አህመድ የእህት ልጅ ተነስቶ የሐረርና አካባቢዉ አለቃ ሆነ ። እሱም የሐረርን ግንብ /ጀንልን/ ስላስገነባ የጎላ ተቀባይነት እንዲኖረዉ አደረገዉ ። ኑር የግራኝን ደም ለመበቀል ዝግጅት ማድረግ ጀመረ ።

ኑር በቂ የሚባል ሰራዊት አስከትሎ ከሐረር ተነስቶ ሸዋ መጥቶ ፈጠጋርን /ቡልጋን/ወረረ ። ይህን የሰሙት አፄ ገላዉድዎስ ሹማምንቶቻቸዉ "ጦርነቱ ከፋሲጋ በኋላ ቢሆን ይሻላል" የሚል ምክር ቢለግሱም እሳቸዉ ግን ፋሲካን በሰማይ ከጌታዬ ከክርስቶስ ጋር አከብራለሁ በማለት የስቅለት ዕለት ጦርነቱን ጀመሩት ። እናም በተጋጋለዉ ጦርነት ውስጥ ከፊት እየመሩ እየተዋጉ ሳለ በጥይት ተመትተዉ ሞቱ ። አፄ ገላዉድዎስ ቢሞቱም ሹማምንቶቻቸዉ በርትተዉ ስለተዋጉ ኑር አህመድ ወደ ሐረር መመለስ ግድ ሆነባቸዉ ። አፄ ሚናስ (ከ1551-1555 ዓ.ም) ፡ - አፄ ሚናስ የአፄ ገላዉድዎስ ወንድም ናቸዉ ። ዙፋኑን ከአፄ ገላውድዎስ ወርሰው ኢትዮጵያን ለ 4 አመት ያህል አስተዳድረዋል ።

በዚህ ዘመን ጎንደር የረጅሙ ከምፅዋ እስከ ሱዳን የተዘረጋዉ የንግድ መስመር ማዕከል /center/ ስለነበረች፤ በተለይ በወቅቱ የባሪያ፣ የወርቅና የቡና ንግድ እያደገ ስለነበር ጎንደር ዉስጥ የሚኖረዉና የሚንቀሳቀሰዉ ህዝብ እየበዛ መጣ ። በተለይ በአፄ ሚናስ ዘመን ጎንደር ውስጥ የሚኖረው ህዝብ በጣም ጨምሮ ነበር ። ስለሆነም ሆሉንም የንግድ እንቅስቃሴ በቅርበት ለመቆጣጠር ሲሉ አፄ ሚናስ መቀመጫቸውን ከደብረ ብረሃን ወደ ጎንደር ለመቀየር ያስቡ ነበር ።

አፄ ሚናስ ኢትዮጵያን ለ4 ዓመት ያህል ካስተዳደሩ በኋላ በ1555 ዓ.ም በወባ ተነድፈዉ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ልጃቸዉ ሰርፀ ድንግል ዙፋኑን ወረሰ ።

# **ምዕራፍ አራት**

## ሰለሞናዊ በጎንደር /መስራች ወሎ ሸዋ/

ይናገር የጎንደር ጃንተከል ዋርካዉ፣

እንደት እንደነበር አፄ ፋሲል የወሎዉ፣
ቤተመንግስቱን ሲያንፀዉ ።
ይናገር ቤተመንግስቱ የጎንደር፣
የወሎዎችን አስተዳደር አመራር፣
የአፄ ፋሲል፣ የራስ ዓሊ፣ የመነን፣
የአሊዎቹን አሻንጉሊት አኗኗር ።
ይናገር የጎንደር ቤተመንግስቱ፣ የ308 አመቱ፣
የትኛዉ ወሎ ይሻላል ለሀገር ለወዳጁ፣
የ234ቱ ሽዋ ወይስ የ74ቱ የጁ ።

ጎንደር ለዋና መቀመጫነት የተመረጠችበት ምክንያት፣ ረጅሙ ከምፅዋ እስከ ሱዳን የተዘረጋዉ የንግድ መስመር ማዕከል /center/ በመሆኗ ነበር /ከሸዋ በታች የነበረው ሀገር የኢትዮፕያ አካል አልነበረም/ ። በተለይ በወቅቱ የባሪያ፣ የወርቅና የቡና ንግድ እያደገ ስለነበር ጎንደር ዉስጥ የሚኖረዉና የሚንቀሳቀሰዉ ህዝብ እየበዛ መጣ ። እናም ነገስታቱ ሁሉንም የንግድ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሲሉ ቤተመንግስታቸዉን ከሸዋ /ከደብረብረሃን/ ወደ ጎንደር መቀየር ግድ ሆነባቸዉ ።

የጎንደር ቤተመንግስት ለ308 ዓመት ያህል መናገሻ ሆኖ ሲያገለግል፣ 308ቱንም አመት የነገሱበት የወሎ ነገስታት ብቻ ናቸዉ /የአፄ ቴዎድሮስ ጉዳይ እንደገና በጥልቀት እንመጣበታለን/፤ ለ234 ዓመት ያህል ጎንደር ቤተመንግስትን የነገሱበት የሸዋ ሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ነገስታት ሲሆኑ ቀሪዉን 74 ዓመት ደግሞ ጎንደር ቤተመንግስት ዉስጥ የነገሱት የየጁ መሳፍንቶች ናቸው ። ስለዚህ ጎንደር ላይ የተፈጠረ ነገር የለም ማለት ነው ። ጎንደር ቤተመንግስትን የተፈራረቁበት ሸዋዎችና የጁዎች ብቻ ናቸው ። እስከ አሁንም ድረስ የኢትዮጵያ ፖለቲካ የሚለወጠዉና የሚንቀሳቀሰዉ በወሎ አካባቢ እስከ ትግራይ ባሉት ሰዎች አማካኝነት ብቻ ነዉ ። ወሎ ካልተንቀሳቀሰ፣ ፖለቲካዉ አይንቀሳቀስም ። በኢትዮጵያ ምንም አይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴና ተሳትፎ ከማያደርጉ አካባቢዎች መካከል ጎጃምና ጎንደር ይገኙበታል ። ቤተመንግስቱ እዚያዉ ጎንደር ድረስ ሄዶላቸዉ እንኳ

የጎንደር ቤተመንግስትን በር መርገጥ ቻለ የጎንደር ሰው ካሳ ሀይሉ /ቴድ/ ብቻ ነዉ፤ ካሳም ቢሆን ወደ ቤተመንግስቱ የገባዉ ለፖለቲካ ሳይሆን ለስራ ቤተመንግስቱ ዉስጥ ለመቀጠር ነበር ። እናም እነዚሁ የወሎ አካባቢ ሰዎች ካልተንቀሳቀሱ በስተቀር በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ለዉጥ አይመጣም ።

ስለሞናዊ ስርዎ መንግስት እንደት እንደተመሰረተ በአፄ ነአኩቶለአብ ስር አይተናል ። አሁን ሰለሞናዊ ስርዎ መንግስት ዋና መቀመጫውን ከሸዋ /ደብረብረሃን/ ወደ ጎንደር ቀየረ ። ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ፣ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች መፀሀፍቶች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋሉ ።

ዋና መቀመጫቸዉን ጎንደር ላይ አድርገዉ

የነበሩ የሰለሞናዊ ሥርወ መንግስት ነገስታት ሥም ዝርዝር ።

| ተ ቁ | የነገስታቱ ሥም | አውራሽ | የስልጣን ቆይታ ዓመት | ያስተዳደሩበ ት ዘመን ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሥርፀ ድንግል | ሚናስ | 34 | 1555-1589 |
| 2 | ያዕቆብ | ሥርፀ ድንግል | 5 | 1589-1594 |
| 3 | ዘድንግል | ያዕቆብ | 2 | 1594-1596 |
| 4 | ሱስኒዮስ | ዘድንግል | 28 | 1596-1624 |
| 5 | ፋሲል | ሱስኒዮስ | 35 | 1624-1659 |
| 6 | ዮሐንስ 1ኛ | ፋሲል | 15 | 1659-1674 |
| 7 | እያሱ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | 24 | 1674-1698 |
| 8 | ተክለሐይማኖት | እያሱ 1ኛ | 2 | 1698-1700 |
| 9 | ቴዎፍሎስ | ተክለሐይማኖት | 3 | 1700-1703 |
| 10 | ዮስጦስ | ቴዎፍሎስ | 5 | 1703-1708 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 11 | ዳዊት 3ኛ | ዮስጦስ | 5 | 1708-1713 |
| 12 | በካፋ | ዳዊት 3ኛ | 10 | 1713-1723 |
| 13 | እያሱ 2ኛ | በካፋ | 25 | 1723-1748 |
| 14 | ኢዮአስ | እያሱ 2ኛ | 14 | 1748-1762 |
| 15 | ዮሐንስ 2ኛ | ኢዮአስ | 1 | 1762-1763 |
| 16 | ተክለሐይማኖት 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | 7 | 1763-1770 |
| 17 | ሠለሞን | ተክለሐይማኖት 2ኛ | 3 | 1770-1773 |
| 18 | ተክለጊዮርጊስ 1ኛ | ሰለሞን | 4 | 1773-1777 |

**አፄ ሠርፀ ድንግል (ከ1555-1589 ዓ.ም)** ፡ - አፄ ሚናስ በ1555 ዓ.ም ሲሞቱ ልጃቸዉ ሠርፀ ድንግል ዙፋናቸዉን ወረሰ ።

በዚያ ዘመን አካባቢ ጎንደር የረጅሙ ከምፅዋ እስከ ሱዳን የተዘረጋዉ የንግድ መስመር ማዕከል /center/ ስለነበረች፤ በተለይ በወቅቱ የባሪያ፣ የወርቅና የቡና ንግድ እያደገ ስለነበር ጎንደር ዉስጥ የሚኖረዉና የሚንቀሳቀሰዉ ህዝብ እየበዛ መጣ ። በዚህ ምክንያት አባታቸው አፄ ሚናስ መቀመጫቸውን ከደብረብረሃን ወደ ጎንደር ለመቀየር እያሰቡ እያለ ነበር የሞቱት ።

እናም አፄ ሠርፀ ድንግል ሁሉንም የንግድ እንቅስቃሴ በቅርበት ለመቆጣጠር ሲሉ ቤተመንግስታቸዉን ከሸዋ ወደ ጎንደር ቀየሩ ።

አፄ ሠርፀ ድንግል ቱርክን በቀይ ባህር በኩል ሁለት ጊዜ ድል አድርገዉ ድንበራቸዉን በማስከበርና በግራኝ ጊዜ የተከፈለዉን ሀገር በአንድ መንግስት

ስር ለማጠቃለል ያለ እረፍት ሲጥሩ ኖረዉ በ1589 ዓ.ም በ47 ዓመታቸዉ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።

**አፄ ያዕቆብ (ከ1589-1594 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ሠርፀ ድንግል እንደሞቱ ከዋናዋ ሚስታቸዉ ወንድ ልጅ ስለሌላቸዉ ከእቁባታቸዉ የወለዱት አቤቶ ያዕቆብ /አቤቶ የነገስታት ልጆች የማእረግ ሥም ነዉ/ በ7 ዓመታቸዉ ዙፋናቸዉን ወረሱ ።

ነገር ግን በሞግዚት ከቆዩ በኋላ በ12 ዓመታቸዉ ሞግዚቶቹን አስወግደዉ ስልጣኑን ጠቅለዉ ከያዙ በኋላ በባላባቶች ላይ እማይሆን ሹም ሺር ስላደረጉ አሳድመዉባቸዉ ከስልጣን ስለወረዱ የሚጠቀስ ታሪክ የላቸዉም ።

**አፄ ዘድንግል (ከ1594-1596 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ዘድንግል የአፄ ሚናስ የልጅ ልጅ ሲሆኑ ከአፄ ያዕቆብ በኋላ ዙፋን ላይ ቢቀመጡም እምነታቸዉን በመቀየራቸዉ ምክንያት በነገሱ በ2 ዓመታቸዉ ከስልጣን እንድወርዱ ተደርገዋል ።

**አፄ ሱስንዮስ (ከ1596-1624 ዓ.ም) ፡ -** ከአፄ ዘድንግል ቀጥለዉ ስልጣን የያዙት የአፄ ልብነ ድንግል የልጅ ልጅ የሆኑት አፄ ሱስንዮስ፣ ወዳዉ ለእስፔንና ለሮማ መንግስታት የወዳጅነት ደብዳቤ፣ የዘመናዊ ጦር መሳሪያና የአጠቃላይ እርዳታ ጥያቄ ጽፈዉ ላኩ ።

ነገር ግን የስፔንና የሮማ መሪዎች ተመካከረዉ "ኢትዮጵያ በቅድሚያ የኦርቶዶክስ ሐይማኖቷን ወደ ካቶሊክ ትቀይር እንጂ የጠየቁት ጥያቄ ሁሉ ይፈፀማል" የሚል መልእክት ላኩላቸዉ ።

በዚሁ ምክንያት ለብዙ ዘመናት ፀንቶ ከነበረዉ የኦርቶዶክስ ቤ/ን ህግ በመዉጣት ለሮማዉ የካቶሊክ ቤ/ን ራሳቸዉን፣ ቤተሰቦቻቸዉንና ህዝባቸዉን አሳልፈዉ ሰጡ ።

ይህንኑ ተከትሎ እጅግ ከፍተኛ ብጥብጥ ተከሰተ ። ንጉሱ በህዝቡ ላይ በወሰዱት የሀይል ርምጃ እጅግ በርካታ ህዝብ፣ ቀሳዉስት፣ ካህናትና መነኮሳት አለቁ ። በዚህ ከንዉን ላይ እያሉ አፄ

ሱስንዮስ ከፉኛ ታመሙ እንደበታቸዉ ተዘጋ፣ ጆሯቸዉ ደነቆረ፣ እግራቸዉም ተልፈስፍሶ መራመድ አልችል አሉ ፡፡ እናም ብዙ እንደማይቆዩ የተረዱት ቤተሰቦቻቸዉ እንዲጠመቁ አድርገዉ ወደ ኦርቶዶክስ ከቀየሯቸዉ በኋላ ሲሞቱ አዘዞ ተክለሐይማኖት ቤ/ን ቀበሯቸዉ ፡፡

**አፄ ፋሲል (ከ1624-1659) ፡ -** አፄ ሱስንዮስ እንዳረፉ ልጃቸዉ አፄ ፋሲል ዙፋኑን ወረሱ ፡፡ ወዳዉም "ተዋህዶ ይመለስ፣ ካቶሊክ ይርከስ" ብለዉ የመንግስት ሐይማኖት ከካቶሊክ ወደ ኦርቶዶክስ መመለሱን ስላሳወቁ ህዝቡ ንግስናቸዉን በደስታ ተቀበለዉ ፡፡

አፄ ፋሲል ከሰሯቸዉ ስራዎች ዉስጥ ትልቁን ቦታ የሚይዘዉ "የፋሲል ግንብ" እየተባለ የሚጠራዉንና በጎንደር ከተማ እስከ አሁን ድረስ በቱሪስቶች እየተጎበኘ የሚገኘዉን የጎንደር ቤተመንግስት ማስገንባታቸዉ ነዉ ፡፡ /ይህ የሸዋ ነገስታት ለኢትዮጵያ ካበረከቷቸዉ ቅርሶች መካከል አንዱ ሲሆን ከላሊበላ ገዳማት ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ በቱሪስቶች እየተጎበኘ ይገኛል፣ ጎንደር ለዋና መቀመጫነት ለምን እንደተመረጠች በዚያኛው ምዕራፍ መጨረሻ ላይ በአፄ ሚናስ ስርና እዚህኛው ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ በአፄ ሰርፀ ድንግል ስር አይተናል /

አፄ ፋሲል ይህን ታላቅ ስራ ከሰሩ በኋላ በነገሱ በ35 ዓመታቸዉ በተወለዱ በ78 ዓመታቸዉ መስከረም 15 ቀን 1659 ዓ.ም አረፉ ፡፡

**አፄ ዮሐንስ 1ኛ (ከ1659-1674 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ፋሲል እንዳረፉ ልጃቸዉ ዮሐንስ 1ኛ ዙፋናቸዉን ወረሰ ፡፡

በዘመናቸዉ ምንም አይነት ከባድ ጦርነት ያላጋጠማቸዉ አፄ ዮሐንስ 1ኛ እጅግ በጣም መንፈሳዊ ስለነበሩ በነገሱ በ15 ዓመታቸዉ አለም በቃኝ ብለዉ ዙፋናቸዉን ለልጃቸዉ ለአቤቶ እያሱ አዉርሰዉ መነኑ ፡፡

**አፄ እያሱ 1ኛ (ከ1674-1698 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ዮሐንስ 1ኛ እንደመነኑ ልጃቸዉ አፄ እያሱ 1ኛ ዙፋኑን ወርሰዉ ኢትዮጵያን ለ24 አመት ያህል ካስተዳደሩ በኋላ፤ ከእለታት አንድ ቀን ታላላቅ ሹማምንትንና ሊቃዉንትን ጠርተዉ በመሰብሰብ በራሳቸዉ ላይ የደፉትን ዘዉድ አዉልቀዉ" ይህ ዘዉድ የህዝብ ስለሆነ ህዝቡ የመረጠዉን ያንግስ" ብለዉ ዙፋናቸዉ ላይ

በማስቀመጥ የዚህን ከንቱ አለም መንግስታቸዉን ትተዉ ጨቅላ ወንዝ ከሚባለዉ ገዳም ሄደዉ ገቡ ።

**አፄ ተክለሐይማኖት (ከ1698-1700 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ተክለሐይማኖት በራሱ ፈቃድ የአባቱን የአፄ እያሱን ዙፋን ያለ ህዝቡ ምርጫ ተቀመጠበት ። አባትዮዉም ካሉበት ገዳም ሆነዉ በመልእክተኛ ያለአግባብ የያዘዉን ዙፋን እንዲለቅ በመላካቸዉ ምክንያት እዚያዉ ባሉበት ገዳም ተደብድበዉ እንዲሞቱ አደረገ ። እናም አፄ ተክለሐይማኖት አባቱን በግፍ ሰለገደለ እርጉሙ ንጉስ በመባል ይታወቃል ። አፄ ተክለሐይማኖት አደን ይወድ ስለነበር የአፄ እያሱ በግፍ መገደል ያበሳጫቸዉ ሹማምንት መክረዉ ላስታ አካባቢ በእንግድነት ሄዶ በአደን እየተዝናና እያለ በጥይት መትተዉ ገደሉት ። በዚህ መልኩ በነገሰ በ2 ዓመቱ አረፈ ።

**አፄ ቴዎፍሎስ (ከ1700-1703 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ተክለሐይማኖት እንደሞተ የአፄ ዮሐንስ 1ኛ ልጅ አፄ ቴወፍሎስ ዙፋኑን የወረሱ ቢሆንም በነገሱ በ3 ኣመታቸዉ በወባ ተነድፈዉ ሞቱ ።

**አፄ ዮስጦስ (ከ1703-1708 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ዮስጦስ የአፄ ቴዎፍሎስ እንደራሴ የነበሩ ሲሆን እሱ ሲሞት ራሳቸዉን አነገሱ ። ነገር ግን ህዝቡ” የነገሴነት ዘር የላቸዉም” እያለ ዉስጥ ዉስጡን እየተነጋገረ እያለ እሳቸዉ በ1708 ዓ.ም ታመዉ ሞቱ ።

**አፄ ዳዊት 3ኛ (ከ1708-1713 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ዮስጦስ ከሞቱ በኋላ ዙፋኑን የአፄ እያሱ ልጅ የነበሩት አፄ ዳዊት 3ኛ ወረሱ ።

አፄ ዳዊት 3ኛ በገና በመደርደር ይታወቃሉ ። ለኪነ ጥበብ ልዩ ፍቅር ነበራቸዉ ። ይህን የተመለከቱት የአገራችን አንጋፋ ጸሀፊ ተዉኔት አያልነህ ሙላቴ ቴያትር ወደ ኢትዮጵያ መቸ እንደገባ ለመግለጽ ሲሞክሩ” ቴያትር /ድራማ/ በዘመነ ዛግዌ ብልጭ ሳይል እንዳልቀረ” ፣ ይጠቅሱና ምክንያቱንም ሲያስቀምጡ የዛግዌ ነገስታት በቤተመንግስታቸዉ አጫዋቾች እንደነበሯቸዉና በተለያዩ ሙዚቃዊ ድራማዎች ይዝናኑ እንደነበር በመጠቆም፣ ነገር ግን አፄ ዳዊት 3ኛ ጊዜ ዘመናዊ ቴያትር /ድራማ/ መሰረቱ እንደተጣለ ለመረዳት የሚያስችል ፍንጭ እንዳለ ይገልፃሉ ።

በመጨረሻም አፄ ዳዊት 3ኛ በጽኑ ህመም ምክንያት ግንቦት 12 ቀን 1713 ዓ.ም አረፉ ።

**አፄ በካፋ (ከ1713-1723 ዓ.ም) ፡ -** አፄ ዳዊት 3ኛ ሲሞቱ ወንድማቸዉ አፄ በካፋ የአባቱን የአፄ እያሱን ዙፋን ወረሰ ።

ከሰሯቸዉ ስራዎች ዉስጥ ጎላ ያለዉ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጣና ሐይቅ የምትሆን መርከብ ማሰራታቸዉ ነዉ ። ኢትዮጵያን ለ10 አመት ያህል ካስተዳደሩ በኋላ አሟሟታቸዉ ሳይታወቅ አስከሬናቸዉ ቀሃ ወንዝ ተፈጥፍጦ ነዉ የተገኘዉ ።

**አፄ እያሱ 2ኛ (1723-1748 ዓ.ም) ፡ -** አፄ በካፋ ከሞቱ በኋላ የ8 አመቱ ልጃቸዉ እያሱ ንጉሰ ነገስት ሆነዉ እስከ ወጣትነታቸዉ ድረስ በሞግዚትና ከወጣትነታቸዉ በኋላ እራሳቸዉ አገሪቱን ለ25 ዓመት ያህል ካስተዳደሩ በኋላ በ1748 ዓ.ም አረፉ ።

**አፄ ኢዮኣስ (ከ1748-1762 ዓ.ም)** ፡ - አፄ እያሱ 2ኛ ሲሞቱ ልጃቸዉ አፄ ኢዮኣስ ዙፋኑን ወርሶ ሀገሪቱን ለ14 አመት ያህል ካስተዳደረ በኋላ እንደራሴያቸዉ ከነበሩት ከራስ ስዑል ሚካኤል ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ተገደለ ።

**አጼ ዮሐንስ 2ኛ (ከ1762-1763) ፡ -** አፄ ኢዮኣስን ከሞቱ በኋላ የ70 ዓመቱ የበካፋን ወንድም አጼ ዮሐንስ 2ኛ ቢነግሱም አንድ አመት ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ተመርዘዉ ተገደሉ።

**አፄ ተክለሐይሞኖት 2ኛ (ከ1763-1770) ፡ -** አፄ ዮሐንስ 2ኛ ከሞቱ በኋላ ልጃቸዉ አፄ ተክለሐይሞኖት ዙፋናቸዉን ወርሰው ሀገሪቱን ለ7 አመት ያህል ከስተዳደሩ በኋላ "ይህን የሚያልፍ መንግስት አልፈልግም" ብለዉ መነኑ።

**አፄ ሰለሞን (ከ1770-1773 ዓ.ም) ፡ -** ከአፄ ተክለሐይሞኖት መመነን በኋላ አርጅተዉ ዙፋን ስለወረሱ ከሦስት አመት በኋላ በእርጅና ምክንያት አረፉ ።

**አፄ ተክለጊዎርጊስ 1ኛ (1773-1777 ዓ.ም) ፡** - አፄ ተክለጊዮርጊስ ከአፄ ሰለሞን ዙፋኑን ቢወርሱም እጅግ በጣም ከባድ እየተባለ የሚነገርለትንና የኢትዮጵያን የውርስ ፖለቲካ የቀየረዉን የየጁዉን የትልቁ እራስ አሊን ጦርነት መቋቋም ስላልቻሉ በሽሽት ቤተመንግስታቸዉን ለቀዉ ጠፉ ።

# ምዕራፍ አምስት

## ዘመነ መሣፍንት (ዘመነ የጁ) በጎንደር፣

### ከትልቁ ራስ አሊ እስከ ትንሹ ራስ አሊ ልጅ እቴጌ ተዋበች (ከ1777-1860)

ዘመነ መሳፍንትን መጥፎ የአገዛዝ ስልት አድርገዉ የሚወስዱት አሉ፤ ይህ እጅግ ስህተት ነዉ ። የዘመነ መሳፍንት የአገዛዝ ስልት ከወቅቱ አንፃር ሲታይ እጅግ ዘመናዊ ያገዛዝ ስልት ነበር ። የነበረዉ አማራጭም ይህው ብቻ ነበር ፡ ይህ ጦርነት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ትልቅ ለዉጥ አምጥቶ ነበር፤ የላስታና የሸዋ ንጉሳዊ ዘር የሌለዉ ሰዉ ሀገር መምራት እንደሚችል አሳይቷል ። ባጠቃላይ የፖለቲካዉን ባህል ቀይሮት ለ74 አመት ያህል ቆይቷል ። የዚህን አገዛዝ ስልት /አሻንጉሊት ንጉስ አስቀምጦ የመግዛት ስልት/ እንግሊዞች እስከ አሁንም ድረስ እንደ ቅርስ ጠብቀዉት ይገኛሉ /ከጠቅላይ ሚኒስቴሩ በተጨማሪ ምንም አይነት ፖለቲካዊ ሚና የሌላት ንግስት ያስቀምጣሉ/ ።

እስከ አሁንም ድረስ የኢትዮጵያ ፖለቲካ የሚለወጠዉና የሚንቀሳቀሰዉ በወሎ አካባቢ እስከ ትግራይ ባሉት ሰዎች አማካኝነት ብቻ ነዉ ። ወሎ ካልተንቀሳቀሰ፣ ፖለቲካዉ አይንቀሳቀስም ። በኢትዮጵያ ምንም አይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴና ተሳትፎ ከማያደርጉ አካባቢዎች መካከል ጎጃምና ጎንደር ይገኙበታል ። ቤተመንግስቱ እዚያዉ ጎንደር ድረስ ሄዶላቸዉ እንኳ የጎንደር ቤተመንግስትን በር መርገጥ የቻለ የጎንደር ሰው ካሳ ሀይሉ/ቴድ/ ብቻ ነዉ ። ካሳም ቢሆን ወደ ቤተመንግስቱ የገባዉ ለፖለቲካ ሳይሆን ለስራ ቤተመንግስቱ ዉስጥ ለመቀጠር ነበር ። እናም እነዚሁ የወሎ አካባቢ ሰዎች ካልተንቀሳቀሱ በስተቀር በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ለዉጥ አይመጣም ።

አሁን እጅግ ለረጅም ጊዜ የቆየዉና ያረጀው የዉርስ ፖለቲካ ሊቀየር ነዉ ። ይህን በራሳቸው በወሎዎች የተፈጠረ ለረጅም ጊዜ የቆየና ያረጀ የውርስ ስርዓትን ለመቀየር ደግሞ ከባድ ዋጋ መክፈልን ይጠይቃል ። ምስጋና ለወፋ ዉጊያ እንጂ ወሎዎች የመግደልና የመሞት ችግር የለባቸዉም ። ወሎዎች ደግሞ ራሳቸዉ ወልደው ባሳደጓት ሀገራቸዉ ጉዳይ ላይ ከዉጭ ሀይሎች ጋር ተነጋግረዉ አያዉቁም ። እስካሁንም ድረስ አይተውታል ብቻቸውን ለውጥ ማምጣት ይችላሉ /በአገውና በሸዋ አባቶቻቸው አይተዉታል ወሎዎች ብቻቸዉን ለዉጥ ማምጣት ይችላሉ/ ።

በእርግጥ መሰዋእትነታቸዉን ለመቀነስና ለማቅለል የተሻ የጦር መሳሪያ ያስፈልጋቸዉ ነበር ። ሆኖም የጁ መሀል አገር ዉስጥ ስለሆነ ከዉጭ ሀገራት ጋር የሚገናኙበት ምንም አይነት ቀዳዳ ወይም ጫላንጭል የለም ። የታጠቁት መሳሪያ እዚያዉ የአካባቢዉ ቀጥቃጮች የሚሰሩት ጦርና ጎራደ ብቻ ነበር ።

በመንግስት በኩል ግን መንግስት ከዉጭ ሀገሮች ጋር መገናኘት ይችላል ። የመንግስት ሰራዊት ከግራኝ ጀምሮ እየተማረከና እየተገዛ የተከማቸዉን መድፍና ምንሽር ታጥቋል ። ከተት ታዉጆ በሀገሪቱ ጫፍ እስከ ጫፍ ያሉት መሳፍንቶች ሰራዊታቸዉን እየያዙ የየጁዉን ጦር ለማቆም ተሰብስበዋል ። ጦርነቱ ከባድ እንደሚሆን ታዉቋል ምክንያቱም በአገሪቱ ዉስጥ የቀረ መሳፍንት የለም ሁሉም ከመንግስት ጎን ተሰልፏል ። የሚጠበቀዉ የወሎዉ ጦር ማጥቃት ነዉ ። ሁሉም ቦታ ቦታዉን ይዞ የየጁዉን ጦር ማጥቃት እየጠበቀ ነዉ ።

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች መፀሀፍቶች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋለሁ ።

"በዚህ ዘመን አካባቢ በመላ ሀገሪቱ እጅግ ግዙፍ ሰራዊት ያላቸዉ መሳፍንቶች የተፈጠሩበት ዘመን ነበር ። በተለይ የየጁዉ ትልቁ ራስ አሊ በሀገሪቱ ሁሉ ስሙ ከንጉሱ በላይ እየገነነ መጣ ። የጎጃም፣ የጎንደርና የሌሎችም አካባቢ ሴቶች በግጥም እየዘፈኑ "አሊና አሊና አሊና በሞቴ፣ የአማራ ማተብ ሰለቸዉ አንገቴ" እያሉ ያዜሙ ነበር ። /ትልቁ ራስ አሊ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለዱ መሆናቸውን አለቃ ታዬ ''የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ'' በሚለው

መፀሀፋቸው ውስጥ አስፍረውታል፤ ወሎ ውስጥ አሊ የሚባል ክርስቲያን እስከ አሁንም ድረስ የተለመደ ነው/

የትልቁ ራስ አሊ ሰራዊት ወሎንና ጎንደርን ሙሉ በሙሉ እየወረረ ወደ ቤተመንግስቱ ተጠጋ ። በዚህ ጊዜ በየግዛቱ ያሉ የንጉሱ መሣፍንቶች ከያሉበት ተሰባስበዉ ራስ አሊን ለመዉጋት ተስማሙ ።

በዚህም የጎጃሙ ራስ ሀይሉ፣ የሰሜኑ ራስ ገብሬ፣ የላስታዉ ዋግ ራስ ስዩም፣ የትግሬዉ ደ/ች ወልደ ገብርኤል፣ የቆማዉ ራስ ደመ ክርስቶስ፣ የአለፋጣቁሳዉ ደ/ች ዘክርስቶስ፣ የቋራዉ መስፍን አዛዥ ልደት…ወዘተ ሁሉም የንጉሱ መሣፍንት ህብረት ፈጠሩና ጦራቸዉን ይዘዉ ወደ በለሳ ተጉዘዉ ‘መደብ’’ ተብላ በምትጠራዉ ቦታ ሰፈሩ ።

በአጠቃላይ በመላ ሀገሪቱ ያሉት የንጉሱ መኳንንት ሁሉ ተጣምረዉ በምድረ ‘‘መደብ’’ ያገራችን ትልቁን ዉጊያ አካሄዱ ። ባገራችን ዉስጥ በርካታ ከባባድ ጦርነቶች ቢካሄዱም ሁሉም የዉጭ ድጋፍ ያለባቸዉና አሸናፊነታቸዉም በዉጩ ድጋፍ መጠንና ጥራት ላይ የተመሰረተ ነዉ ። ባገራችን ዉስጥ የዉጭ ድጋፍ የሌለበት ይህን የሚያህል ከባድ ጦርነት እስከ አሁን ድረስ ተካሂዶ አያዉቅም ። የጁዎች መሀል አገር ዉስጥ ስለሚገኙ ምንም አይነት የዉጭ ድጋፍ ያልነበራቸዉና እጅግ ኋላ ቀር መሣሪያ የታጠቁ ነበሩ ። በአንፃሩ በንጉሱ በኩል ያለዉ ሀይል በርካታ የዘመኑ መድፎችንና ሌሎች የተሻሉ መሣሪያዎችን የታጠቀ ነበር ። ሆኖም የመንግስት ጦር የታጠቀዉን መሳሪያ ለመጠቀም አስቸጋሪ ሆነበት ። ምክንያቱም የጁዎች የሚተኩሱት ነገር ስለሌላቸዉ፣ የጦርነት ስልታቸዉ ፈጥኖ መቀላቀልና የጨበጣ ጦርነት መጀመር ነበር ። ስለሚቀላቀሉባቸዉ ወደ የትም አቅጣጫ መተኮስ አልቻሉም /የወፋ ባህላዊ ውጊያ ውጤት ነው/ ። እናም የወሎዉ ጦር የሞተዉ እየሞተ እጅግ በፍጥነት ስለሚቀላቀል የመንግስት ተኳሾች ጠላትን ከወገን ለይተዉ ለመምታት ይቸገሩ ነበር ።

በአካባቢው ቀጥቃጮች የሚሰራውን ጦርና ጎራደ የታጠቀው በየጁ ልጆች የተዋቀረዉ የራስ አሊ ጦር ከፉኛ አጠቃ ። የተባበረው የንጉሱ ሀይልም የሞት ሽረት መከላከል አደረገ ። ነገር ግን የየጁዉን ሰራዊት እጅግ ፈጣን ማጥቃት የሚቋቋመዉ አልተገኘም ። እናም የንጉሱ ጦር ያለቀዉ አልቆና የተማረከዉ ተማርኮ የተረፈዉ ተበታተነ ። ራስ ደመ ክርስቶስ በዉጊያዉ ላይ

ሲሞት ሌሎቹ መኳንንቶች ወታደሮቻቸዉን አስፈጅተዉ በየቦታዉ ሸሹ ፡፡ ሁሉም የሀገሪቱ መሳፍንቶች ተሰባስበዉ አንድ ቦታ ላይ ስለተሙቱ፤ ትልቁ ራስ አሊ ያለማንም ከልካይ መላዋን አገሪቱንና የጎንደር ቤተመንግስትን ተቆጣጠሩ ፡፡

/በዚያን ጊዜ በወሎ አረሆዎች ይዜሙ ከነበሩ የህዝብ ግጥሞች መካከል የተወሰኑትን መርጬ ላዝናናችሁና እንቀጥላላን ፡፡

ፈሪ ብልጡ ፈሪ ብልጡ፣

ሲሸሽ የሚያይበት አይን አለዉ ከቂጡ ፡፡

ጀግና ይሙት ፈሪ ይኑር ቢሻዉ፣

እሬሳ ለማንሳት ይችላል ትከሻዉ ፡፡

መድፍ ሲንደቀደቅ ምንሽር ሲያጓራ፣

ልብ አይታመንም እንኳን ባልንጀራ ፡፡

የጦረኛውን ሚስት ጦረኛ አይነካትም፣

የመንደር ወሬኛ ካገኘ አይለቃትም ፡፡

አገራችን ወሎ ትዉልድ አገራችን፣

ጓያችን ይሰብራል እንኳን ጥይታችን ፡፡

ባቄላ ምርቱ እንጂ አያምርም ከምሩ፣

ይምጣ የወሎ ልጅ ከነምንሽሩ ፡፡

አገራችን ወሎ ወንዛችን ተከዜ፣

ማን ነዉ የሚነካን እምቢ ባልነ ጊዜ ፡፡

/ተከዜ ትግራይ ዉስጥ ነዉ፣ እንደት እንደሆነ አልገባኝም/ ፡፡

/በነገራችን ላይ ይህን ጦርነት የወሎ የእርስ በርስ ጦርነት አድርጎ መዉሰድ አይቻልም ፡፡ ምክንያቱም በንጉሱ በኩል /በሸዋዎች በኩል/ ሌሎች የሀገሪቱ መሳፍንቶች በሙሉ አብረዉ ተሳትፈዋልና/ ፡፡

እናም በዚህ ወደር በሌለዉ የየጁዎች ጀግንነት ድል ያደረጉት ትልቁ ራስ አሊ መላዋን ሀገሪቱንና የጎንደር ቤተመንግስትን ተቆጣጠሩ ። የኢትዮጵያ መዕከላዊ መንግስት ያለአንዳች የዉጭ እርዳታና ጣልቃገብነት በእርስ በርስ ፍጭት ብቻ አከርካሪዉ ተሰበረ ። ኢትዮጵያዊያን /ወሎዎች/ በራሳቸዉ ሌላ ያገዛዝ ስልት ፈጠሩ /አሻንጉሊት ንጉስ አስቀምጦ የመግዛት ስልት/ ።

እናም ትልቁ ራስ አሊ ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠሩ በኋላ አንድ የሸዋ የነጋሲ ዘር ያለዉ የይስሙላ (አሻንጉሊት) ንጉስ ጎንደር ቤተመንግስት ዉስጥ አስቀምጠዉ ሀገሪቱን እንዳሻቸዉ ማሽከርከር ጀመሩ ።

እዚህ ላይ ቢያንስ አንድ ትልቅ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም ። ትልቁ ራስ አሊ እንደት ክርስቲያን ሆነው ቀጠሉ? /ትልቁ ራስ አሊ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለዱ መሆናቸውን አለቃ ታዬ ‘’የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ’’ በሚለው መፀሀፋቸው ውስጥ አስፍረውታል፣ ወሎ ውስጥ እስከ አሁንም ድረስ አሊ የሚባል ክርስቲያን የተለመደ ነው/ ። እናም አንዳንድ ሰዎች የየጁ ህዝብ አብዛኛዉ ሙስሊም ይመስላቸዋል፤ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ትልቁ ራስ አሊ የአብዛኛውን ሰራዊታቸውን ስሜት ለመጠበቅ ሲሉ እምነታቸውን ወደ እስልምና ቀይረው እስልምናን ማወጃቸው አይቀርም ነበር ። ትልቁ ራስ አሊ መላዋን ሀገሪቱንና የጎንደር ቤተመንግስትን ሲቆጣጠሩ ሁሉም የክርስትያን ባላባቶች “መደብ” በሚባለዉ ቦታ ላይ ተሰባስበዉ አንድ ላይ ስለተመቱ በሀገሪቱ ዉስጥ አንድም የክርስቲያን ሀይል አልነበረም ። ስለሆነም ያለማንም ከልካይ እስልምናን ማወጅ ይችሉ ነበር ማለት ነው ። ስለዚህ ትልቁ ራስ አሊ ክርስቲያን ሆነዉ የቀጠሉበት ምክንያት አብዛኛው የሰራዊታቸው አባላት ክርስትያን ነበሩ ማለት ነው ። ከዚህ በመነሳት ብቻ የጁ ዉስጥ ክርስቲያኑ እንደሚበዛ ማወቅ ይቻላል ።

የጁ አብዛኛዉ ሙስሊም ሆኖ ቢሆን ኖሮ ትልቁ ራስ አሊ ያለማንም ከልካይ እስልምናን አዉጀዉ ሀገሪቱን መጨረሻዉ ለማይታወቅ ዘመን ያህል ይመሩ ነበር ማለት ነዉ፤ ምክንያቱም እስልምናን አዉጀዉ ቢሆን ኖሮ ካሳ ሀይሉ /ቴድ/ ክርስቲያን ስለሆነ ቤተመንግስት ዉስጥ ቢቀጠርም ያንን ያህል ሹመት የማግኘት እድሉ ጠባብ ነበር፤ እናም አፄ ቴዎድሮስ የሚባል ንጉስ አይከሰትም ነበር ማለት ነዉ ። ስለዚህ የየጁዎች ግዛት ከ74 አመት በላይም ሊቀጥል ይችል ነበር ማለት ነዉ ። ስለዚህ የጁ ውስጥ ክርስቲያኑ ባይበዛ ኖሮ

ኢትዮጵያ ክርስቲያን ልትሆን አትችልም ነበር ማለት ነው /ኢትዮጵያ አገውና ሸዋ ያስያዛትን ተፈጥሮዋን እንደገና በየጁ ምክንያት ትቀይር ነበር ማለት ነው/ ። ከሸዋዎችና ከላስታዎች በተጨማሪም ከዚህ ከዘመነ መሳፍንት ጦርነትም በግልፅ እንደምንረዳዉ፣ የጁዎች አብዛኞቹ ክርስቲያን በመሆናቸው እንጂ ኢትዮጵያን ሙስሊም ከመሆን ማንም አላዳናትም ነበር ማለት ነዉ /ትልቁ ራስ አሊ መላዋን ሀገሪቱንና የጎንደር ቤተመንግስትን ሲቆጣጠሩ ሁሉም የክርስትያን ባላባቶች "መደብ" በሚባለዉ ቦታ ላይ ተሰባስበዉ አንድ ላይ ስለተሙቱ በሀገሪቱ ዉስጥ አንድም የክርስቲያን ሀይል አልነበረም/ ። ስለዚህ ኢትዮጵያን ክርስቲያናዊት ያደረጋት የወሎዎች መቀላቀል ነው ማለት ነው /የወሎ ክርስቲያኖች ባይኖሩ ኖሮ ኢትዮጵያ ይህኔ በሙሉ ሙስሊም ነበረች ማለት ነው/ ። በሌላ መንገድ ብናየውም ጎጃምና ጎንደር ወደ ንግስና ወጥተዉ የማያዉቁ ከሆነና አፄ ቴዎድሮስም የነገሰው ወሎን ተጠግቶ /ከራስ አሊ ጋር ተጋብቶ/ ከሆነ፣ ኢትዮጵያን ክርስቲያናዊት ያደረጋት የወሎዎች መቀላቀል ነው ማለት ነው ።

ትልቁ ራስ አሊ አገሪቱን ለ6 አመት ያህል ካስተዳደሩ በኋላ ሲሞቱ ታናሽ ወንድማቸዉ ራስ አሊጋዝ ተተኩ ። ራስ ጉግሳ የሁሉም ታናሽ ነዉ ። ጉግሳን ታላቅየዉ ትልቁ ራስ አሊ ይወደዉ የነበረ ቢሆንም መካከለኛዉ ራስ አሊጋዝ ግን አይወደዉም ነበር ። እናም ጉግሳ፣ ራስ አሊጋዝ ስልጣን ላይ ሲቀመጥ ያስረኛል ብሎ በመፍራት መጀመሪያ ወደ ወረሂመኖ ቀጥሎም ወደ በጌምድር ኮበለለ ።

ጉግሳ የስደት አሽከሮቹን ከ600 ፈረሰኞች ጋር ይዞ በጌምድርን ይገዙ ወደ ነበሩ አጎቶቹ /የእናቱ ወንድሞች/ ራስ አስራትና ራስ ወልደ ገብርኤል ሄደ /አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴል-ኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትና በዓለማየሁ አበበ ከተተረጎመዉ መፀሀፍ ላይ፣ አንፀባራቂዉ የሴሩ ዳንጉል ቤት በሚለዉ ርዕስ ስር፣ ራስ አስራትና ራስ ወልደ ገብርኤል፣ የትልቁ ራስ አሊ አጎቶች የእናቱ ወንድሞች መሆናቸዉን ይገልፃል/ ። እናም ሁለቱ ወንድማማች አጎቶቹ ራስ አስራትና ራስ ወልደ ገብርኤል ተጣልተዉ በጌምድርን ከሁለት ከፍለዉ ይገዙ ነበርና ጉግሳ ወደ ራስ ወልደ ገብርኤል ገባ ። ራስ ወልደ ገብርኤልም በደኅና ተቀብሎ ሮገራ የሚባለዉን አገር ማረፊያ ይሁንህ ብሎ ለጉግሳ ሰጠዉ ።

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ወንድማማቾች ራስ አስራትና ራስ ወልደ ገብርኤል እንደገና ተጣልተዉ ሳሉ የጎጃሙ ራስ መርድ ወደ ራስ አስራት፣ ሰሜነኛዉ ራስ ገብሬ ወደ ራስ ወልደ ገብርኤል ሆነዉ ጦርነት ገጠሙ ። ሁለቱ ወንድማማቾችና የጎጃሙ ራስ መርድ እዚያዉ ጦርነቱ ላይ ሞቱ ። ሰሜነኛዉ ራስ ገብሬ ወደ አገሩ ሸሸ ። በዚህ መልኩ ራስ ጉግሳ አልጋ ላይ /ስልጣን ላይ/ ተቀመጠ ።

ራስ ጉግሳ ከተማዉን ልቦ ከሚባለዉ ቦታ ላይ አደረገ ። ኋላ ግን የበቃ መነኩሴ ከበረሀ መጥቶ ከተማህ እዚህ አይደለም፣ ቦታህን ፈልግ፣ ምልክትም አራስ ነብር ታገኛለህ እዚያ ላይ ከተማ ስራ ብሎ ነገረዉ ።

ያዉ መነኩሴ እንደነገረዉ ቦታዉን ሲፈልግ ያች አራስ ነብር ተገኘች፤ እዚያም ላይ ጫካዉን አስመንጥሮ ደብረ ታቦር የሚባል ከተማ አሰርቶ ተቀመጠ ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ልጆቹም የልጅ ልጆቹም ከተማቸዉን የጎንደሯ ደብደረ ታቦር ላይ አደረጉ ።

ጥንት እየተሾሙ ከወሎ የሄዱት የሰሜን ባላባቶችም የራስ ጉግሳን ልጆች እያገቡ ቤተሰብ ሆኑ ። ከወሎ ወግዲ /ቦረና/ ሄደዉ ስሜንን እያስተዳደሩ ከኖሩት "ከኤሎስ" የዘር ሀረግ የተገኘዉ ሰሜነኛው ደጃች ኃይለማርያም፣ ሂሩት ጉግሳን አገባ ። የደምቢያዉ ገዥ ኩሉዬ ማሩ፣ ወለተተክሌ ጉግሳን አገባ ። የሜጫዉ ኦሮሞ ባላባት ደጃች ወልደሩፋኤል፣ አስቴር ጉግሳን አገባ ። የሰቆጣው ዋግሹም ክንፉ፣ ትርንጉት ጉግሳን አገባ ። በዚህ መልኩ የጎንደሯ ደብረ ታቦር ከተማን አደመቋት ።

ራስ ጉግሳ ሲሞቱ ትልቁ ልጃቸዉ ራስ ይማም ተተክቶ 3 አመት ገዛ ። ከዚያ ተከታዩ ልጁ ራስ ማርዬ 3 አመት ገዛ ። ቀጥሎም ትንሹ ልጁ ራስ ዱሪ 3 ወር ገዝቶ ሞተ ። ከዚህ ቀጥሎ የራስ ጉግሳ የልጅ ልጅ ትንሹ ራስ አሊ በተወለደ በ12 አመቱ አልጋ ላይ /ስልጣን ላይ/ ተቀመጠ ። ትንሹ ራስ አሊም ካሳ ኃይሉ /አፄ ቴዎድሮስ/ እስከ ከዳቸዉ ድረስ ሀገሪቱን ለ22 አመት ያህል መርተዋል ።

በዘመነ መሣፍንት (በዘመነ የጁ) ጊዜ በየጊዜዉ ስልጣን ይይዙ የነበሩ የትልቁ ራስ ዓሊ ቤተሰቦች የሸዋና የላስታ የነጋሲ ዘሮችን እያመጡ በጎንደር ቤተመንግስት ያነግሷቸዉ ነበር ባይባልም ግንብ ያስጠብቋቸዉ ነበር ። በዚህ ረጅም ዘመን ዉስጥም 14 ያህል ግንብ ጠባቂ (አሻንጉሊት) ነገስታት

ተቀያይረዋል ። ከዚህ ቀጥለዉ የተዘረዘሩት ነገስታት በየዘመናቸዉ እንደ ግንብ ጠባቂ /አሻንጉሊት/ ነገስታት የተደረጉ ናቸዉ ።

1. አጽቁ እያሱ 3 አመት
2. ህዝቅያስ 7 አመት
3. ዮናስ 1 አመት
4. በእደ ማሪያም8 ወር
5. ሰለሞን2 ወር
6. ድሜጥሮስ3 አመት
7. ዕጓለ ጽዮን2 አመት
8. ኢዮአስ4 አመት
9. ጊጋር 9 አመት
10. ገብረክርስቶስ 10 አመት
11. በእደ ማሪያም1 አመት
12. አያሱ 4 አመት
13. ዮሐንስ 3ኛ1 አመት
14. ሳህለ ድንግል 22 አመት 15. ካሳ /ቴዎድሮስ/ 5 ዓመት

የነገስታቱ ስምና በግንብ ጥበቃ የቆዩበት ጊዜ ያየነዉን ሲመስል፣ የተፈራረቁት የየጁ መሣፍንት /የትልቁ ራስ አሊ ቤተሰቦች/ ደግሞ የበላይነቱን ይዘዉ ያሻቸዉን እየፈፀሙ የኖሩበት ዘመን በሚከተለዉ መልኩ ይዘረዘራል ።

1. ትልቁ ራስ አሊ ከ1777-1882---የየጁ መኳንንት ለ6 አመት
2. የትልቁ ራስ አሊ ወንድም ራስ አሊጋዝ ከ1782-1786 ---የየጁ መኳንንት ለ4 አመት
3. የራስ አሊ የእናቱ ወንድሞች ራስ አስራትና ራስ ወ/ገብርኤል ከ1786-
4. 1792---የየጁ መኳንንት ለ6 አመት
5. የራስ አሊ ሌላ ወንድም ራስ ጉግሳ /የደብረታቦር ከተማ መስራች/
6. ከ1792-1818 ---የየጁ መኳንንት ለ26 አመት
7. የራስ ጉግሳ ልጅ ራስ ይማም ከ1818-
8. 1820 ---የየጁ መኳንንት ለ 2 አመት

9. የራስ ጉግሳ ሌሎች ልጆች ራስ ማርዬና ራስ ዱሪ ከ1820-1823--የየጁ መኳንንት ለ3 አመት
10. የራስ መርዬና የእቴጌ መነን ልጅ ትንሹ ራስ አሊ ከ1823-1845---የየጁ መኳንንት ለ22 አመት
11. እቴጌ ተዋበች /የአጼ ቴዎድሮስ ሚስትና የትንሹ ራስ አሊ ልጅ
12. ከ1847-1852---የየጁ መኳንንት ለ5 አመት

የትንሹ ራስ አሊ ልጅ እቴጌ ተዋበች የአፄ ቴዎድሮስ ሚስት ናት፤ መሳፍንቱ ይገብሩ የነበረዉ ለተዋበች ስለነበር ነዉ፣ እሷ ስትሞት ግን መገበር አቁመው ቴድን ቤተመንግስቱንና መላውን ግዛቱን አስለቅቀውት መቅደላ ላይ መሽጎ ነበር የሚኖረው ። ስለዚህ ዋናዋ እሷ ነበረች ማለት ነዉ፤ መሳፍንቶቹ ቴድን እንደ አጋዥ /እሷ ስላስጠጋችው እንደ አሻንጉሊቶቹ ንጉሶች/ ነበር የቆጠሩት ማለት ነዉ፤ ከዘመኑ አንፃር ቴድ በጣም የተማረ ሰው ስለነበር እንደ እረዳት ነበር የቆጠሩት ማለት ነው /ገዳም ውስጥ እየተማረ ነው ያደገው/ ። የአጼ ቴዎድሮስ ጉዳይ በጣም አወዛጋቢ ስለሆነ ለብቻዉ በጥልቀት ማየት ይኖርብናል ።

## እቴጌ ተዋበችና ካሳ ሀይሉ /አጼ ቴዎድሮስ 2ኛ/

**አፄ ቴዎድሮስ ፡ -** ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ፣ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፍሩት **ቃል በቃል ሲቀመጥ ፡ -**

"ልጅ ካሳ /በኋላ አጼ ቴዎድሮስ/ ጥር 6 ቀን 1811 ዓ.ም ከቋራዉ ተወላጅ ከሀይሉ ወልደጊዮርጊስና ከእንፍራዧ እመቤት ከወ/ሮ አትጠገብ ነበር የተወለዱት ።

በተወለዱ በ1 ዓመታቸዉ አባታቸዉ ስለሞቱ እናታቸዉ ወ/ሮ አትጠገብ ተምረዉ ለወግ ለማዕረግ ይበቁ ዘንድ ወደ አንድ ገዳም ወስደዉ ለመነኮሳቱ አደራ ሰጧቸዉ ። በመጀመሪያ በማህበረ ስላሴ ገዳም፣ ቀጥለዉ በቾንክር ተክለሐይማኖት ገዳም መንፈሳዊ ትምህርትና ዓለማዊ ትምህርታቸዉን ሲከታተሉ አደጉ ።

ወደ ወጣትነት ሲሸጋገሩም ከደንቢያዉ ባላባት ከናታቸዉ ወንድም ከደጃች ክንፉ ጋር ሆነዉ እየኖሩ ሳለ ገሰሰች እንግዳ የተባለች ልጃገረድ ጋር ተጋብተዉ መሸሻንና አልጣሽን ወለዱ ፡፡ ትዳራቸዉ ግን ብዙ አልቆየም ፡፡ ትዳራቸዉ ስኬታማ ስላልነበረ ከአጎታቸዉ ጋር ወደ ጎንደር ቤተመንግስት መጡ ፡፡ ቤተመንግስቱ ዉስጥም ማገልገል ጀመሩ ይልና፣

በአጭር ጊዜ ዉስጥም በሚፈፅሟቸዉ የድፍረትና የጀግንነት ሥራዎች በእቴጌ መነን ዘንድ ተወዳጅ እየሆኑ ሄዱ ፡፡ በልዩ ልዩ ግዛቶች ለዘመቻ ሲሄዱም በታላቅ ጀብድ ድል እያደረጉ ምርኮም እያመጡ ለትንሹ ራስ አሊና ለእናቱ ለእቴጌ መነን በማስረከብ ታማኝ አገልጋይ ሆኑ ይልና፣

በ1840 አካባቢ የግብፅ ጦር በሱዳን በኩል ኢትዮጵያን ለማጥቃትና ለመዉረር ከመቸዉም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ የመጣበት ወቅት ነበር ፡፡ ካሳም ጦሩን በከፍተኛ ጀግንነት በመምራት ስናር ድረስ ዘልቀዉ ገብተዉ የግብፅን ወራሪ ሀይል ድምጥማጡን አጥፍተዉ ተመለሱ ፡፡ እጅግ ጀግና መሆናቸዉ በሁሉም የቤተመንግስት ሰዎች ዘንድ ታየላቸዉ ፡፡ ራስ አሊና እቴጌ መነንም ከሁሉም መኳንንቶቻቸዉ የበለጠ ካሳን ወደዷቸዉ ፡፡

ነገር ግን የካሳ ጀግንነት ለራሳቸዉም ስጋት ሆናቸዉ ፡፡ ስለዚህ በዘዴ መያዙን መረጡና በጋብቻ ገመድ ጠፍረዉ ለማሰር ሲሉ የራስ አሊን ልጅ፣ የእቴጌ መነንን የልጅ ልጅ ተዋበችን በሚስትነት ሰጥተዉ አጋቧቸዉና 40 ቀን የቆዬ ድግስና ግብዣ ተካሄደ ፡፡ የደጃዝማችነት ማዕረጉንም ያገኙት በዚሁ በሰርጉ ጊዜ ነበር'' ይላል ፡፡

/እዚህ ላይ ማለትም ''በዘዴ መያዙን መረጡና በጋብቻ ገመድ ጠፍረዉ ለማሰር ሲሉ'' የሚለዉ ሀረግ ታሪኩ ተቀጥቅጦ የተጣመመበት ቦታ ነዉ ፡፡ ካሳ ቤተመንግስት የገባዉ ባዶ እጁን መሆኑን አይተናል ፡፡ አንዳንዶች ካሳ ባዶ እጁን አልነበረም፣ ሰራዊት ነበረው እያሉ ይከራከራሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ ሽፍታ ያደርጉታል ፡፡ ሁለቱም እጅግ ስህተት ናቸው፤ ምክንያቱም ካሳ የራስ አሊ ሎሌ እንደነበር፣ በዚያው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን በህይወት የነበሩት እነ ጸሐፊ ትዛዝ ፅፈዋል (ጸሐፌ ትእዛዝ በአፄ ቴዎድሮስም በአፄ ሚኒልክም ጊዜ በህይወት ነበሩ፣ አፄ ሚኒሊክ በአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ ታስረው ነበር) ፡፡ ካሳ ሎሌ ከሆነ በኋላ ሽፍቶ ቢሆን ኖሮ ደግሞ እንደገና ተመልሶ ታዛዥ ሆኖ ቀጥለን እንደምናየው አንድ እግር ወርች ስጋ አይላክለትም ነበር ፡፡ እናም የእቴጌይቱ

ውለታ ገደል የገባበትና የየጁ ወታደሮች ታሪክ ተጣሞ ለቴድ የተሰጠበት ቦታ ይህ ነዉ /በጋብቻ ገመድ ጠፍረው ለማሰር የሚለው ሀረግ/ ። እስኪ እንደዉ ማን ይሙት? ሴት ልጅ እንጂ ወንድ ልጅ እንደት ተገዶ ሊያገባ ይችላል ። በዚያ ላይ ማስገደድ ከተቻለና ሰውየው ስጋት ከሆነ አስገድዶ ከማጋባት ይልቅ መግደል ይቀላል ። ቀጥለን እንደምናየው ቴድ ተዋበችን ከሞት መንጋጋ /ከግብፆች እስር ቤት/ አውጥቶ ነው ያገባት ። እናም የኢትዮጵያን /የወሎን/ ታሪክ አጣሞና አድበስብሶ ለመውሰድ ሲባል የወሎን ውለታ መካድና የአባቶቻችንን መዋደድ ማበላሸት ተገቢ አይመስለንም ። ጎጃሜዎች የበላይ ዘለቀን ታሪክ በዘፈን አማካኝነት ብቻ ከወሎ መውሰዳቸው ይታወቃል ። ይህ ለሀገራችንም ጥሩ አይሆንም፣ ታሪክ ሰሪዉ ሌላ ተሸላሚዉ ሌላ ከሆነ ታሪክ ሰሪ አይገኝም ። የወሎ ታሪክ የሁላችንም ታሪክ ሆኖ እያለ ታሪክ ሰሪዎቹን ማበረታታት ሲገባን ታሪካቸዉን ለመዝረፍ ስንል የኢትዮጵያን /የወሎን/ ታሪክ በማጣመም ለሌላ ሰዉ እየሸለምን ሀገሪቱ ጀግና እንዳይኖራት ማድረግ ጥሩ አይመስለንም/ ። ታሪኩ ተስተካክሎ ሲፃፍ እንዲህ ይሆናል ።

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴልኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትና በዓለማየሁ አበበ ከተተረጎመዉ መፀሀፍ ውስጥ የሰፈረዉ ፅሁፍ ቃል በቃል ሲቀመጥ "ከግብፅ ጋር በተካሄደዉ ጦርነት የመነን ሰራዊት ጠንክሮ እንዲዋጋ እንዲታደፋፍር ተብሎ፣ የልጅ ልጇ ልዕልት ተዋበች ሰራዊቱን እንዲታጅብ ተደርጎ ነበር ። ነገር ግን ግብፆች ያሏቸዉ መድፎች ለድል አበቋቸዉ፣ ኢትዮጵያዊያኑ ተሸነፉ፣ ልዕልት ተዋበችም ተማረከች ይልና፣

በዚህ ጊዜ ካሳ ከእቅዶቹ ዉስጥ ብዙዉን ክፍል እዉን የሚያደርግበት ጊዜ እንደ ደረሰ ተገነዘበ ። ይኸዉም በመጀመሪያ ደረጃ በኢትዮጵያ ዉስጥ ለማዕከላዊዉ ስልጣን ለሚደረገዉ ትግል አመች መቆናጠጫ ማግኘት፤ ቀጥሎም የራስን አቋም ማሻሻል ነዉ ፡ እነዚህንም በሁለት መንገዶች ለማከናወን ወሰነ ፡ - አንደኛ ግብፆችን ድል ማድረግና በጠላት ኃይል ላይ በተገኘዉ ድል አማካኝነት የራሱን ወታደራዊ ተደማጭነት ማጠናከር ። ሁለተኛ ከቤተመንግስቱ ጋር መጋባትና በባላባታዊዉ የደረጃ ርብራብ ዉስጥ ተቀባይነት የሚያስገኝ የጎላ ስፍራ መያዝ ። ምናልባትም ይህን ታላቅ ምኞትና የመሪነት ተሰጥኦ የታደለዉ ካሳ፣ ይህን ሁለተኛዉን ሀሳብ መተግበሩ ወደ ፊት

ለንጉሳዊዉ ዙፋን ለሚደረገዉ ትግል ጥሩ መቆናጠጫ እንደሚሆንለት ሳይገነዘብ አልቀረም ይልና፣

ካሳ ሰራዊቱን እየመራ የግብፅን ጦር ወግቶ በመበታተን፤ ከተማረከች በኋላ፣ ለሙላ ፓሻ ሐሬም የመዝናኛ ጫጉላ ታጭታ የነበረችዉን ልዕልት ተዋበችን፣ ከግብፆች እስር ቤት መንጥቆ አወጣት ። ያን ጊዜ ገና የ15 ዓመት ጉብል የነበረችዉ ተዋበች እጅግ የምታምር ቆንጆ ነበረች ። ከጎንደሩ ቤተመንግስት ጋር በጋብቻ የመተሳሰሩ የካሳ ምኞት እዉን ወደ መሆኑ የተቃረበበት ዋናዉ ምክንያት ይህ ነዉ ፡ ለጊዜዉ ግን ተዋበች ወደ ወላጆቿ ቤተመንግስት ጎንደር እንድትሄድ አደረገ'' ይላል ።

/በነገራችን ላይ ይህ ተርጓሚ አፄ ቴዎድሮስ ላይ ሲደርስ በርካታ የአደባባይ ሚስጥሮችን ዘሎቸዋል፤ ለምሳሌ ያህል ካሳ የራስ አሊ ሎሌ እንደነበር፣ በዚያው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን በህይወት የነበሩት እነ ጸሐፊ ትእዛዝ ፅፈዋል፣ እንዲሁም ተርጓሚው ካሳና እቴጌ መነን የተከዳዱበትን የወይፈንና የአንድ እግር ወርች ስጋ ጉዳይንም ዘሎታ፤ እነኝህን የመሳሰሉ የአደባባይ ሚስጥሮችን ቆርጦ መጣል ተገቢ አይመስለንም ። ሆኖም ግን እስከ አሁን ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፃፉ የታሪክ መፀሀፎች ውስጥ ይህ መፀሀፍ እጅግ የተሟላና እጅግ የተሻለ ሚዛናዊነት ስለሚታይበት እኛም ልንጠቀምበት በአንደኛ ደረጃ መርጠነዋል ። የፀሐፊ ትእዛዝ መፀሀፍ ደግሞ አፄ ሚኒሊክ በጆት በጅተው ከራሳቸው ከአፄ ሚኒሊክ አፍና ከእቴጌ ጣይቱ አፍ ላይ እየተወሰደ የተፃፈ ትክክለኛ (original) መፀሀፍ ስለሆነ ስለ አፄ ሚኒሊክ ዘመን ይህንን መፀሀፍ ልንጠቀምበት በአንደኛ ደረጃ መርጠነዋል ። የጋዜጠኛ ፍሰሐ መፀሀፍ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ እጅግ በተሟላ ሁኔታ የያዘና እጅግ የተሻለ ሚዛናዊነት ስለሚታይበት ይህንንም መፀሀፍ ልክ እንደላይኞቹ በፅሀፎች በአንደኛ ደረጃ ልንጠቀምበት መርጠነዋል/ ።

እናም ከላይ ካየነው የትርጉም መፅሀፍ እንደተረዳነው ካሳ ተዋበችን ከሞት መንጋጋ /ከግብፆች እስር ቤት/ ነበር ያወጣት ማለት ነዉ ፡ ስለዚህ ለተዋበች ከካሳ የበለጠ ሰዉ አይኖርም ማለት ነዉ ።

ወደ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ፅሁፍ ስንመለስ “በዚህ ድርጊታቸዉ /ታዘው ልጅቱን ከግብፆች እስር ቤት በማውጣታቸው/ ካሳ እጅግ ጀግና መሆናቸዉ በሁሉም

የቤተመንግስት ሰዎች ዘንድ ታየላቸዉ ።ራስ አሊና እቴጌ መነንም ከሁሉም መኳንንቶቻቸዉ የበለጠ ካሳን ወደዷቸዉ ። ነገር ግን የካሳ ጀግንነት ለራሳቸዉም ስጋት ሆናቸዉ ። ስለዚህ በዘዴ መያዙን መረጡና በጋብቻ ገመድ ጠፍረዉ ለማሰር ሲሉ የራስ አሊን ልጅ፣ የቴጌ መነንን የልጅ ልጅ፣ ተዋበችን በሚስትነት ሰጥተዉ አጋቧቸዉና 40 ቀን የቆዬ ድግስና ግብዣ ተካሄደ ። የደጃዝማችነት ማዕረጉንም ያገኘዉ በዚሁ በሰርጉ ጊዜ ነበር ይልና፣

በመሐመድ አሊ በተመራዉ የግብፅ ጦርና በእቴጌ መነን ጦር መካከል በተካሄደዉ ከባድ ዉጊያ በርካታ ሰራዊት ከማለቁም በላይ እራሳቸዉ የጦር መሪዎቹም ቆስለዉ ነበር ። በዚህ ጦርነት ደጃዝማች ካሳ ሀይሉና አብሯቸዉ ዘምቶ የነበረዉ የባለቤታቸዉ የተዋበች ወንድም፣ ቆስለዉ ነበርና ሁለቱም እንዲያገግሙ በማሰብ እቴጌ መነን ለልጅ ልጃቸዉ /ለተዋበች ወንድም/ ጥሩ ወይፈን ሲልኩ ለደጃዝማች ካሳ ግን አንድ እግር ወርች ሥጋ ብቻ ላኩላቸዉ ይልና፣

እቴጌዋ ደጃዝማች ካሳን ዝቅ አድርገዉ በማየታቸዉ ያዘኑት ጀግናም ባለቤታቸዉን ተዋበችን "ተመልከች የእናትሽን ግፍ" አሏት በምሬት ። ተዋበችም በእናቷ እጅግ አዘነች ። በተለይም በበርካቶች ዘንድ "ከደሐ ጋር የተጋባች" እየተባለች ትወቀስ ነበርና በንዴት ተዉጣ ዝም ባለች ጊዜ "ምን ትያለሽ ተዋበች" ብለዉ ሲጠይቋት "ተነሳ ነዋ የምልህ! ታጠቅ ነዉ የምልህ" የሚል መልስ ሰጠች" ይላል ።/እንግዲህ ካሳ ወይፈን እንኳ ማረድ አይችልም ነበር ማለት ነው ። ካሳ ቤተመንግስት ባዶ እጁን ሄዶ የተቀጠረ መሆኑንም አይተናል ። አንዳንዶች ካሳ ባዶ እጁን አልነበረም፣ ሰራዊት ነበረው እያሉ ይከራከራሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ ሽፍታ ያደርጉታል ። ሁለቱም እጅግ ስህተት ናቸው፤ ምክንያቱም ካሳ የራስ አሊ ሎሌ እንደነበር፣ በዚያው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን በህይወት የነበሩት እነ ጸሐፌ ትዛዝ ፅፈዋል፤ ካሳ ሎሌ ከሆነ በኋላ ሸፍቶ ቢሆን ኖሮ ደግሞ እንደገና ተመልሶ ታዛዥ ሆኖ አንድ እግር ወርች ስጋ አይላክለትም ነበር ።

እናም ካሳ በራስ አሊ ቤተመንግስት ውስጥ ከሎሌነት ጀምሮ እየተሾመ፣ እየተሾ መጥቶ የእቴጌ መነን ጦር ዋና አዛዥ እስከመሆንና ደጃዝማች እስከመባል ደረሰ ። ካሳና ተዋበች በተጋቡበት የስርግ ስነስረዓት ላይም ካሳ የደጃዝማች ማዕረግ ተሰጥቶት የመንግስት ጦር አዛዥ ተደርጎ ተሾመ ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ካሳ የሚያዘውን የመንግስትን ሰራዊት ይዞ ለመክዳት ተዋበችን

የሚያሳምንበት ነገር ብቻ ነበር የሚፈልገዉ ። ተዋበች ደግሞ ከሞት መንጋጋ ያወጣትን ካሳን ትወደው ስለነበርና በዘመኑ የነገስታት ልጆች የእናት-የአባትን ስልጣን ቀድመው ለመውረስ ይሽቀዳደሙ ስለነበር የአባቷን ስልጣን ቀድማ ለመውረስ ፈልጋለች ። ተዋበች ካሳ ሸፈተም አልሸፈተም ከእቴጌ መነን እጅ እንደማይወጣ እርግጠኛ ነበረች ። ምክንያቱም የያዘዉ ሰራዊት የሱ ሰራዊት አይደለም፤ የየጁዉ የእቴጌ መነን ሰራዊት ነዉ ። በዚያ ላይ ቴድ ባላባት አይደለም /ተዋበች ከሌለች መንገስ አይችልም፣ አይቻልም፣ እዚያ ዘመን ላይ ሆነን ማሰብ አለብን ጭሰኛ መንገስ አይችልም፣ ስለዚህ እሷ ነች የምትነግሰው ማለት ነው፣ ቴድ ከተዋበች እጅ ሊወጣ አይችልም ማለት ነው፤ መጨረሻ ላይ ተዋበች ስትሞትም የታየዉ ይኸዉ ነዉ ።

እናም ተዋበች ለወንድሟ ወይፈን ተልኮ ለእሷ አንድ እግር ወርች ሥጋ ብቻ መላኩ አስቆጥቷታል፤ ካሳን ሳይሆን እሷን ነው ማየት ያለባቸው፤ ካሳን ከናቁት አለማጋባት ነበር፣ ከሞት መንጋጋ ካወጣት ከካሳ የበለጠ ሰዉ ደግሞ የላትም ። እናም ምን ትያለሽ ተዋበች ሲላት፣ በሁኔታው ተናዳ ስለነበርና በዘመኑም

የነገስታት ልጆች የእናት-የአባትን ስልጣን ቀድመው ለመውረስ ይሽቀዳደሙ ስለነበር ፈቀደችለት፣ ተነስ ታጠቅ አለችዉ ።

እናም ካሳ ተዋበች ሀሳቧን ትቀይራለች ብሎ የፈራ ይመስላል፤ ወዳው በፈቀደችለት ሌሊት ተዋበችንና የሚመራውን ሰራዊት ሁሉ ጠራርጎ ይዞ ወደ ቋራ ሲጓዝ አድሮ በአካባቢው በረሀ ሰፈረ ። ከሸፈቱም በኋላ ተዋበች ብዙም ፖለቲካዊ ብቃት ስላልነበራት፤ ሁሉንም የፖለቲካ ስራዎች የሚያስፈፅመዉ ወትሮዉንም የተሻለ ፖሊቲካዊ ተሰጦ የነበረዉ ካሳ ሀይሉ ነበር ። እቴጌ ተዋበችም ልክ እንደ እናቷ ካሳ በሚሰራቸዉ ስራዎች እምነት እያደረባት ስለመጣ የፖለቲካዉን ስራ ሙሉ በሙሉ ለቀቀችለት ። ከዚህ በኋላ ካሳ ያለማንም ከልካይ በየጁዉ የእቴጌ መነን ሰራዊትና መሣሪያ መሣፍንቱን ሁሉ ያጭደዉ ጀመር ። በሸፈተ በአመቱ በደረስጌ ማሪያም ቤ/ን በጳጳሱ ተቀብቶ ነገሰ ።

ወደ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ስንመለስ “ምን ትያለሽ ተዋበች” ብለዉ ሲጠይቋት “ተነሳ ነዋ የምልህ! ታጠቅ ነዉ የምልህ” የሚል መልስ ሰጠች ። ይህ አጋጣሚ በዉስጣቸዉ የተጸነሰዉን ሀገር አንድ የማድረግ ፍላጎትና አላማ የማሳኪያ

የመጀመሪያዉ መንገድ ስለሆነላቸዉ እየተደሰቱ የዚያኑ ዕለት ሌሊት የሚመሩትን ጦር አስከትለዉ ተዋበችንም ይዘዉ ሸፈቱ፤ ወደ ቋራ አቅንተዉም በአካባቢዉ ባለዉ በረሀ ሰፈሩ ይልና፣

ወዳዉም ከእቴጌ መነን ጋር ተጣልቶ የሸፈተዉን ይልማ ወሰንን አገኙትና በከፍተኛ ደስታ ተቀብሎ ከጎኑ አደረጋቸዉ ። የመሪነቱን ቦታም ለደጃዝማች ካሳ ሀይሉ ለቀቀላቸዉ ። ህብረት ፈጥረዉም የአካባቢዉን ግዛት ሹማምንት ድል እያደረጉ በርካታ ቦታዎችን ተቆጣጠሩ" ይላል ።

እንግዴህ በርካታ ፀሀፍት የካሳን ታሪክ መፃፍ የሚጀምሩት ከዚህ በኋላ ያለውን ነው፣ እስካሁን ድረስ ያየነው የካሳ ታሪክ ይዘለላል /ተቆርጦ ይጣላል/ ወይ ተድበስብሶ ይታለፋል ፡ እናም በወቅቱ በኢትዮጵያ ተወዳዳሪ የሌለዉንና የግብፅን ጦር እንዴ እሳት የበላዉን የቴጌ መነንን ጦር ይዞ የሸፈተዉ ደጃዝማች ካሳ ሀይሉ መሳፍንቱን ሁሉ ይጠራርገዉ ጀመር ። ሁሉም መሳፍንቶች የቴጌ መነን ገባር ስለነበሩ ጦራቸዉም በትጥቅም ሆነ በብዛት ከእቴጌ መነን ጦር እንደሚያንስ ግልፅ ነዉ ። እናም የበርካታ መድፎችና የተሻለ ትጥቅ ባለቤት የሆነዉን የቴጌ መነንን ጦር ይዞ የሸፈተዉን ደጃዝማች ካሳ ሀይሉን የሚቋቋመዉ መሳፍንት አልተገኘም ።

በቤተመንግስቱ ውስጥ ከፍተኛ ሽብር ተፈጠረ፣ እቴጌይቱ ብዙ በእጃቸዉ የቀረ ጦር የላቸዉም ። አባዛኛውን ጦራቸዉን በደጃማች ካሳ ስር አድርገዉት ስለነበር ካሰም ከድቶ ሁሉንም ሰራዊታቸዉን ይዞባቸዉ ሄዷል ።

እቴጌ መነንም እጅግ ጀግና ሴት ስለነበሩ በንደት የነበሯቸዉን ጥቂት ወታደሮች ሰብስበዉ ደጃዝማች ካሳን ለመያዝ መሞከራቸዉ አልቀረም ። ትንሹ ራስ አሊም ካሳን ለመያዝ ሌላ ሙከራ አደረጉ ። ሆኖም ደጃዝማች ካሳን መያዝ የሚቻል አልሆነም ። የተለያዩ ሙከራዎች ቢደረጉም አልተሳካም ። እቴጌይቱና የቤተመንግስቱ ሰዎች በጣም ተፀፁ፣ ጥፋቱ ሁሉ የእራሳቸዉ መስሎ ታያቸው፣ ካሳ ታማኝና ጨዋ መስሎ አታሏቸዋል፣ ደሐ ሰዎች ሁሉ ጋጠወጥ መሰሏቸዉ፣ ደግ አድርጎሻል ጥፋቱ የአንችው ነው፣ ዱሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ አምነሽ አስጠግተሽ ወዘተ የሚሉ ቃላቶች በረከቱ ። አማራጮችን ሁሉ ፈተሹ፣ ምንም ማድረግ አይቻልም፣ ያመኑት እንድህ ድንገት ሲከዳ ቅስም ይሰብራልና ከህደትን ረገሙ ። እናም እቴጌይቱ ጎንደር ቤተመንግስትን ለቀዉ ወደ ዋድላ ደላንታ ሄዱ ።

ጸሓፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ "ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒሊክ በሚለዉ መጸሀፋቸዉ "ደጃች ካሳ የራስ አሊ ሎሌ ነበር /ራስ አሊ የእቴጌ መነን ልጅ ነዉ/ ። ጌታ አክዓብን በተጣላዉ ጊዜ መንግስቱን ለሎሌዉ ለኢዩ አሳልፎ እንደሰጠዉ ሁሉ የነዚህንም ትዕቢታቸዉንና ጥጋባቸዉን እግዚአብሔር አይቶባቸዉ መንግስታቸዉን አሳልፎ ለሎሌቸዉ ለደጃች ካሳ ሰጠባቸዉ ይሉና፣

ደጃች ካሳም ደግሞ በአመቱ ደጃች ዉቤን ድል አድርጎ፤ ደጃች ዉቤ እነግሳለሁ ብሎ ባሰራዉ ምንጣፍ፣ ባሰራዉ ዘዉድ፣ ባሰራዉ ቤተክርስቲያን ደረስጌ ማሪያም ላይ ስሜም ቴዎድሮስ ነዉ ብሎ ነገሰ" ይላል ። /ስለዚህ በዓለም ላይ በሽፈተ በአመቱ የነገሰ ሽፍታ ካሳ ሀይሉ ይሆናል ማለት ነው፤ አንዳንድ ፀሀፍት አንድ አመት ተኩል ያደርጉታል፣ ጋዜጠኛ ፍሰሀ መፀሀፍ ላይም ስናቀናንሰው እንዲሁ አንድ አመት ተኩል አካባቢ ነው/ ።

ወደ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ስንመለስ፣ ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ካሳ ሀይሉ በኢትዮጵያ ግዛቶች ያለእረፍት እየተዘዋወሩ፣ መኳንንቱን ሁሉ ነጣጥለዉ ድል እያደረጉ ለ1 አመት አካባቢ ያህል ቆዩ ። ከዚያም በሽፈቱ በአመታቸዉ በእለተ እሁድ የካቲት 5 ቀን 1847 ዓ.ም በደረስጌ ማሪያም ቤ/ያን በታላቅ ስነ-ስረአት የንጉሰ ነገስት ዘዉዱን ተቀዳጁ ። ስመ መንግስታቸዉም በራሳቸዉ ምርጫ የዚህ ቀደሙን ትንበያ መሰረት አድርገዉ "ዳግማዊ ቴዎድሮስ" አሰኙ ይልና፣

ቀጥሎም የሚከተሉትን ህጎች በአዋጅ አስነገሩ ። /እዚህ ላይ ለካህናቱ የወጣዉን ህግ፣ ቁጥር 3ን፣ ልብ እንበል፤ ተዋበች ከሞተች በኋላ ይቀየራል/ ።

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ቃል በቃል አስነብባችኋለሁ ።

1. ''ክርስትያን በክርስትያንነቱ፣እስላም በእስላምነቱ ጸንቶ ይቀጥል ።ነገር ግን እምነቱን ከአንዱ ወደ ሌላ የቀየረ እንደሆነ ሰባኪዉም ተሰባኪዉም አንገቱ በሰይፍ ይቆረጣል ። ደረቱ በጦር ይወጋል ።
2. ክርስትያን የሆነ ሆሉ ከአንድት ሴት ዉጭ ሌላ አግብቶ ቢገኝ ሀብቱን ሁሉ እንዳለ ለመጀመሪያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣና

እርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠዉ/ተዋበችንና የየጁን ሰራዊት ለማስደሰት የታሰበ ይመስላል/ ።

3. ከጥንት ጀምሮ የነበረዉ የቄስና የደብተራ የመሬት ግብር እንደነበረ ሆኖ ይቀጥል /ይህን ህግ ተዋበች ከሞተች በኋላ መሳፍንቱ ሁሉ ስላመፁበት፣ ካህናቱ አመፁን
4. ማስቆም አለባቸዉ በሚል ቀይሮታል/ ።
5. የቤተመንግስቱ ባለስልጣኖች በእለት ተግባራቸዉ በደመወዝ እንዲሰሩ እንጂ ባሪያ መግዛትና መሸጥ እንዳይፈጽሙ ።
6. የቤት ሰራተኞች ገረድና አሽከሮች በደመወዝ እንዲያገለግሉና ከአሰሪያቸዉ ጋር ተጣልተዉ ቢወጡ በዉላቸዉ መሰረት ነገሩ የጸናል ።
7. ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በሙያዉ እንድሰለፍ፣ገበሬዉም በግብርናዉ ነጋደዉም በንግዱ እንድተዳደር ።
8. ገበሬዉ ከጥንድ በሬ በላይ የሚያርስ ከሆነና ነጋደዉ ከአጋሰስ ጭነት በላይ የሚነግድ ከሆነ ግብር እንዲከፍል’’ ይላል ።

አሁን ሁሉም በሰላም እየገበረ ነዉ ። ያጋጠማቸዉ ችግር የለም መኳንንቱና መሳፍንቱም በሰላም እየገበሩ ያለምንም ችግር እየተገዙላቸዉ ነዉ ። ቴድም ያለምንም ተቃዉሞ ንጉሰነገስት ሆኖ ጎንደር ቤተመንግስት ዉስጥ ተቀምጦ ነበር ።

ነገር ግን በ1852ዓ.ም ተወዳጇ ባለቤታቸዉ እቴጌ ተዋበች ድንገት አረፉ ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ሁሉም ነገር ተቀያየረ ። ተዋበች በሞተች ማግስት ጀምሮ ሰራዊቱ እየሟሸሸ /እየተመናመነ/ መጣ ። እቴጌ ተዋበች ከመሞታቸዉ በፊት ከ150ሺ በላይ የነበረዉ የቴድ ጦር እቴጌ ተዋበች ከሞቱ በኋላ በጥቂት ጊዜት ዉስጥ በማይታመን ፍጥነት ተመናምኖ ወደ 58ሺ ወረደ ። በ1854ዓ.ም ቴድ 10ሺ የማይሞላ ሰራዊት ብቻ ነበር የነበረዉ ።

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴልኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች “የኢትዮጵያ ታሪክ” በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ካሳፈሩትና በዓለማየሁ አበበ ከተተረጎመዉ በፅሀፍ ዉስጥ ያለው ፅሁፍ ባጭሩ ሲቀመጥ “ቴዎድሮስ ከተዋበች ጋርና እሷም ከሞተች በኋላ ከጥሩወርቅ ጋር የፈፀማቸዉ ጋብቻዎች ፖለቲካዊ ፀባይ ያላቸዉ ነበሩ ። ተዋበች ከሞተች በኋላ ባላባታዊ ተቃወሞ

ተቀሰቀሰ ፡፡ ሰራዊቱም /የየጁዉ ሰራዊት/ ከ150ሺ ወደ 10ሺ አሽቆለቆለ ፡፡ በዚህ ምክንያት አፄ ቴዎድሮስ ከሚሰነዝርበት የግድያ ሙከራ የተነሳ ጭንቀት ዉስጥ ወድቆ ነበር ፡፡ የተወዳጇ ሚስቱ የተዋበች በ1852 ዓ.ም መሞት ለዚህ የግድያ ሙከራና ጭንቀቱ ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል ፡ ወዳዉም የወሎዉ መስፍን ዋግሹም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ተዋበች ከሞተች በኋላ አፄ ቴዎድሮስ ባላባት አይደለም በሚል የአፄ ቴዎድሮስን መሪነት አልቀበልም ብሎ ግዛቱን ዙሪያዉን አጥሮ በመቆጣጠር ቴድን በመቅደላ ብቻ እንዲወሰን አደረገዉ /መቅደላ ደቡብ ወሎ ውስጥ የሚገኝ ወረዳ ነው/ ፡፡ በ1856 ዓ.ም የአፄ ቴዎድሮስ ግዛት ከሁለቱ ማለትም ከበጌምድርና ከዋድላ ደላንታ አዉራጃዎች የሚያልፍ አልነበረም" ይላል ፡፡ /ስለዚህ የቴድ ንግስና የቆየው ተዋበች እስከ ሞተችበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር ማለት ነው/ ፡፡

ተዋበች ከሞተች በኋላ ቴድ ባላባት

ስላልሆነና የየጁ ሰራዊትን በፍጥነት እየሟሸሸ መምጣትን ተከትሎ በየቦታዉ ያሉ መሳፍንቶች አመፁ፣ አንገብርም አሉ ፡፡ መሳፍንቶቹ ቴድን እየተዉ ግዙፍ ሰራዊት ለነበረዉ ለወሎዉ ለሰቆጣዉ መስፍን ለዋግሹም ስዩም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ መግባት ጀመሩ፡፡

መሣፍንቶቹ በቴድ ሰራዊት መመናመን ብቻ አይደለም ያመፁት ፡፡ የህልውና ጉዳይ ስለሆነባቸው ነው፤ ምክንያቱም መሳንቶቹ በዉስጣቸዉ ያለዉን ጭሰኛ የሚያስገብሩት "እኛ ባላባት ነን፣ እንበልጥሀለን፣ የተሻልን ዘሮች ነን ወዘተ" እያሉ ነዉ ፡፡ ጭሰኛዉም በዚሁ የባላባትነት ስርዓት አምኖ ነዉ የሚገብረዉ ፡፡ ተዋበች እስካለች ድረስ መሳፍንቶቹ ችግር አልነበረባቸዉም ፡፡ ምክንያቱም እየገበሩ ያሉት ለራስ ዓሊ ልጅ፣ ለእቴጌ መነን የልጅ ልጅ፣ ለእቴጌ ተዋበች ነዉ ፡ እቴጌ ተዋበች ደግሞ በባላባትነት ሁሉንም ሀገሪቱ ዉስጥ ያሉትን መሳፍንቶች ትበልጣቸዋለች፣ የምትኖርበት ጎንደር ቤተመንግስትም የአባቷ የራስ አሊና የአያቷ የእቴጌ መነን ቤተመንግስት ነዉ፤ ይህን ደግሞ የሀገሪቱ ጭሰኛ ሁሉ አሳምሮ ያዉቀዋል ፡፡ ስለዚህ ተዋበች እስካለች ድረስ የባላባትነት ስረዓት አልፈረሰም ማለት ነው ፡፡ እናም መሳፍንቶቹ በሰላም ለእቴጌ ተዋበች ሲገብሩ ኖሩ ፡፡ ቴድም ያለምንም ተቃዉሞ ንጉሰነገስት ሆኖ ጎንደር ቤተመንግስት ውስጥ ተቀምጦ ነበር ፡፡

አሁን ግን እቴጌ ተዋበች ሞተዋል ፡፡ እቴጌ መነንና ራስ አሊም የሉም ፡፡ ቴድን ደግሞ በባላባትነት ሀገሪቱ ዉስጥ ያሉት ሁሉም መሳፍንቶች ይበልጡታል ፡፡ ስለዚህ ከአሁን በኋላ መሣፍንቶቹ ለቴድ ገበሩ ማለት አንገታቸዉ ላይ ገመድ አስገቡ ማለት ነዉ፤ በዉስጣቸዉ ያለዉ ጭሰኛ "የባላባትነት ስረዓት ፈረሰ" እያለ እየጨፈረ ወጣ ማለት ነዉ /የህልዉና ጉዳይ ነዉ ማለት ነው/ ፡፡ መሳፍንቶቹ እንደለመዱት እኛ ባላባት ነን፣ እንበልጥሀለን፣ አርፈህ ተቀመጥ ብለዉ ጭሰኛዉን መናገር አይችሉም ማለት ነዉ ፡፡ ስለዚህ ወይ ቴድ ወይ መሳፍንቶቹ መጥፋት ነበረባቸዉ ፡፡

ቴድም አማራጭ አልነበረዉም ፡፡ እንደ ትልቁ ራስ አሊ አሻንጉሊት ንጉስ እንዳያስቀምጥ ቸኩሎ እራሱ ንጉስ ሆኗል ፡፡ እናም አማራጭ ስላልነበረው እየተመናመነ ላለዉ ጦሩ የእቴጌ መነንን መሳሪያ እያስታጠቀ ወደ አንድ ቦታ ዘምቶ ለመቀጣጫ እያለ እጃቸዉን ቆርጦ ሲመጣ ሌላ ቦታ ያምጻሉ ፡፡ ሰራዊቱም እጅጉን እየተመናመነ መጣ ፡፡

ቴድ የመሣፍንቶቹ አመፅ ከአቅሙ በላይ ሲሆን ከካህናቱ ጋር ተጋጠመ ፡፡ ካህናቱ አመፁን ማረጋጋት አለባቸዉ፣ አመፁን ለማቆም እየሞከሩ አይደለም በሚል ግምት የሚከተለዉን ህግ አወጣ ፡፡

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ቃል በቃል አስነብባችኋለሁ ፡፡

1. ''በመጀመሪያ ከጥንት ጀምሮ ከ24 እስከ 500 የሚደርሱ ካህናት ለየአድባራቱ አገልግሎት ይመደቡ የነበረዉን በመሻር ለአንድ ቤተክርስትያን 2 ቄስና 3 ድያቆን ብቻ እንዲያገለግል ሲያደርጉ፤ የቀረዉ አገልጋይ በምርት ተግባር ላይ ተሰማርቶ እራሱ ሰርቶ እንዲተዳደር አደረጉ ፡፡
2. ለየአድባራቱ በርስትነት የተሰጠዉ መሬት ተነጥቆ ለወታደሩ እንዲከፋፈል አደረጉ'' ይላል ፡፡

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ቀጥለውም፣ ''በተለይ የቤተክህነት ሰዎች እብድ ሆኑ ፡፡ ከጳጳሱ ከአቡነ ሰላማ ጋርም ሀይለኛ ግጭት ዉስጥ ገቡ ፡፡ የቃላት ምልልሱ ከጳጳሱ ጋር እየተካረረ በመሄዱም ተሰዳደቡ ፡፡ አፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተቆጥተዉ "ጳጳሱን ከሴቶች ጋር በስዉር ሲወሰልት አይቸዋለሁ" በማለት ራሳቸዉን

ምስክር አድርገዉ አቀረቡ ። በዚህ ጊዜ ጳጳሱ እጅግ ተበሳጭተዉ ‘’ልዑል እግዚያብሄር በሚያመጣዉ መቅሰፍት ይቅሰፍህ፣ ከከዳተኛዉ ይሁዳ ጋር እድል ፋንታህ ይሁን’’ ብለዉ ተራገሙ ። አፄ ቴዎድሮስ በእርግማኑ /በተለይ ከከዳተኛዉ ጋር በምትለዉ ቃል/ እጅግ ተናደዉ አቡነ ሰላማን አሰሩና አድባራቱንና ገዳማቱን ማፍረስ ጀመሩ’’ይላል ።

ቴድ አመፁን አስቁሙልኝ ብሎ ለካህናቱ አልነገራቸውም ። ቴድ አመፁን አስቁሙልኝ ብሎ ለካህናቱ ግልፅ መሆንን እንደ ሽንፈት ነበር የቆጠረዉ ። እናም ካህናቱን ሳሰቃያቸዉ አመፁን ያስቆሙታል በሚል፤ ግልጽነት የሌለዉና እልህ የሚያጋባ አካሄድን ተከተለ ። ካህናቱን ግልጽ ሆኖ አመፁን አረጋጉልኝ ቢላቸዉ ኖሮ፣ እንደማይሳካ ቢያዉቁትም መሞከራቸዉ አይቀርም ነበር ።

ቴድ ጳጳሱን ካሰሯቸዉ በኋላ ካህናቱም አመጹን ያቀጣጥሉት ጀመር ። በየግዛቱ አምጸዉ ላሉ የወሎ መሳፍንቶች በተለይ ለዋግሹም ስዩም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ምቹ አጋጣሚ ተፈጠረላቸዉ፤ በቴድ ቅዠትም መሳቅ ጀመሩ /ካህናቱ ምንም አላደረጉትም ነበር/ ። ወደ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ስንመለስ ‘’ቴድም ነገሩ ሁሉ ከቁጥጥራቸው ዉጭ እየሆነ ሲመጣ ቁጣቸዉ ገንፍሎ አሁንም ካህናቱን እጣን ጠባሽ፣ ሬሳ መሪ፣ ራሱን ታጣቂ፣ ወገቡን ሰባቂ… እያሉ ይዘልፏቸዉ ጀመር ። በርካቶችን ወደ ገደል አስወረወሯቸዉ ። ብዙዎችንም እሳት አንዲደዉ ወደ እሳት ጨመሯቸዉ ። የቀሩትንም በጦር አስወጓቸዉ ይልና፣

ይህን ሁሉ ግፍ በካህናቱ ላይ ቢፈፅሙም የመሳፍንቱ አመፅ እንኳን ሊቆም እየባሰበት ሄደ ። አፄ ቴዎድሮስም አመፁን መቋቋም ተሳናቸዉና የጎንደር ቤተመንግስትን ለመልቀቅ ተገደዱ ። እቃቸዉን ጠቅልለዉ ይዘዉ ሄደዉ መቀመጫቸዉን ደብረ ታቦር አደረጉ’ ይላል ።

ከዚህ በኋላ የሀገሪቱ የፖለቲካ ቁልፍ የሰቆጣዉ ዋግሹም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ እጅ ዉስጥ ገባ ። ቴድ ወደ ደብረ ታቦር ሲያፈገፍግ ሁሉንም የጦር መሳሪያና እስረኞቹን ይዞ ነበር ። ዋግሹም ጎበዜም /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛም/ ቴድን ዙሪያውን ከቦ እየተከታተለ ግዛቶቹን ሁሉ ነጥቆ በደቡብ ወሎዋ መቅደላ ብቻ እንዲወሰን አደረገው /ዋግሹም የሰቆጣ አካባቢ የማዕረግ ስም ነው/ ።

ለዚህም ነዉ እንግዴህ እቴጌ ተዋበችን እንደ ዋና ቴድን እንደ ተጨማሪ /ኢጋዥ/ ለማድረግ የምንገደደው ፡፡ በእርግጥ የፖለቲካውን ስራ ሙሉ በሙሉ ለቴድ ለቃለት ስለነበር እሱ ነበር አድራጊ ፈጣሪው ፡፡ ነገር ግን ተዋበች ባልኖረች ጊዜ ቴድ ንጉስ ሆኖ መቀጠል አልቻለም፤ መጀመሪያም ዝም ያሉት እሷ ስላስጠጋችው ነበር ማለት ነው ፡፡ ምክንያቱም እሷ ከሞተች በኋላ ወዳውኑ በሚሰነዘሩበት የግድያ ሙከራዎች ምክንያት ጭንቀት ውስጥ ገባ፣ ቤተመንግስቱንና መላውን ግዛቱንም አስለቀቁት ፡፡ ስለዚህ ቴድን ያነገሰችው እሷ ነበረች ማለት ነው ፡፡ እናም የቴድ መንግስት የቆመዉ እሷ እስካለችበት ጊዜ ድረስ ብቻ ከሆነ ዋናዋ እሷ ነበረች ማለት ነዉ ፡፡ ልክ በዘመነ መሳፍሰት ጊዜ መንግስቱ የሚቆመዉ በተቀባው በአሻንጉሊቱ ንጉሱ ላይ ሳይሆን ባነገሰው መስፍን ላይ ነበር ፡፡ አሻንጉሊት ንጉሱ ኖረም አልኖረም ችግር የለዉም ነበር ፤ ካስፈለገ አሻንጉሊት ንጉሱ ሊቀየር ይችላል ፡፡ አሻንጉሊት ንጉሱ እንደተቀባ ነግሶ የሚኖረው ደግሞ ያነገሰው መስፍን እስካለ ድረስ ብቻ ነበር ፡፡

የእነ ቴድንም ጉዳይ ስናየዉ ከተዋበች ይልቅ ቴድ ባይኖር ይሻል ነበር ፡፡ ቴድ ባይኖርም ሰራዊቱ አይበተንም ነበር ፡፡ መሳፍንቶቹም ለእቴጌ ተዋበች መገበራቸዉን ይቀጥሉ ነበር ፡፡ ስለዚህ ምን ይሻላል? አሻንጉሊቱ ማን ይሁን? እርግጥ ነዉ ቴድ አሻንጉሊት መሆንም አይችልም /የነጋሲ ዘር የለዉም/ ፡፡ ተዋበች ከሞት ስላዳናትና በዘመኑ የነገስታት ልጆች የእናትየአባትን ስልጣን ለመውረስ ይሽቀዳደሙ ስለነበር ነው ቴድን እዚህ ደረጃ ላይ ያደረሰችው ፡፡ እናም ቴድ እቴጌ ተዋበችን ተጠግቶ ነበር ነግሶ የኖረዉ ማለት ነው /ልክ አሻንጉሊቱ ንጉስ ወራሹን መስፍን ተጠግቶ ነግሶ እንደሚኖረዉ/ ፡፡ አሻንጉሊቱ ንጉስ ነግሶ /ተቀብቶ/ የሚቆየዉ ደግሞ ያነገሰዉ መስፍን እስካለ ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር ፡፡ ቴድም ነግሶ /ተቀብቶ/ የኖረዉ ተዋበች እስካለች ጊዜ ድረስ ብቻ ነዉ ፡፡ ስለዚህ ከመስፈርቱ አንፃር መሳፍንቱን /ገባሩን/ መከተል ስላለብን፣ የግድ ቴድን ሙሉ በሙሉ አሻንጉሊት ንጉስ ለማለት ባይቻልም የእቴጌዋ ረዳት /ኢጋዥ/ ለማድረግ እንገደዳለን ፡፡ ለዚህም ነዉ ቴድ ከእቴጌ መነን እጅ ወጥቶ አያዉቅም የሚባለዉ ፡፡

እንግዲህ ከላይ እዳየነው ተዋበች ከሞተች በኋላ የየጁዉ ጦር እየሟሸሸ መጥቶ ከ150ሺ ወደ 10ሺ በመዉረዱና ቴድ ባላባት ስላልሆነ ሁሉም መሳፍንቶች መገበር አቁመዉ ቴድን ቤተመንግስቱን አስለቅቀዉ ለዋግሹም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ መገዛት ጀመሩ ፡፡ ቴድም የእንግሊዞች

መምጣት ድረስ ወሎ መቅደላ ላይ መሽጎ ነበር የሚኖረዉ ፡፡ ግዛቱም ከሁለት አዉራጃዎች ማለትም ከበጌምድርና ከዋድላ ደላንታ አይበልጥም ነበር ፡፡

ቴድ ቀደም ብለዉ /ቤተመንግስቱን ከመልቀቃቸዉ በፊት/ የእንግሊዝ ንግስት ለነበሩት ለንግስት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ፅፈዉ የወቅቱ ቆንሲል ዳንካ ከሜሩንን መርጠዉ "…የጦር መሳሪያ እርዳታ፣ የጦር መሳሪያ የሚያመርቱ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች …ወዘተ…" በማለት በድፕሎማሲያዊ ቃላት የታጀበ ደብዳቤ አስይዘዉ ልከዉ ነበር ፡፡ ነገር ግን የላኩት ሰዉ የዉሀ ሽታ ሆነባቸዉ ፡፡ ምላሽ ሲጠፋ በአካባቢያቸዉ ያገኙትን ምድረ ቆንሲል ለቃቅመዉ 30 የሚደርሱ የዉጭ ዜጎችን ወሎ መቅደላ አምባ ከሚገኘዉ እስር ቤታቸዉ አስረው የጦር መሳሪያ ለማሰራት ሞከሩ ፡፡ እንግሊዛዊያኖቹ በርከት ይሉ ነበር ፡፡

ከተዋበች ሞት በኋላ ምንም ዓይነት ሰላምና ስልጣን ኖሮት የማያዉቀዉና ቤተመንግስቱንና መላውን ግዛቱን እስከ መልቀቅ የደረሰዉ ቴድ፤ የተሻለ የጦር መሳሪያ አስመጥቶ፤ ካልተቻለ ደግሞ አሰርቶ ፣ መሳፍንቱን ሁሉ በማንበርከክ ወደ ጎንደር ቤተመንግስት ለመመለስ በጁ ያሉትን አማራጮች በሙሉ መሞከሩን ቀጠለ ፡፡ በዲፕሎማሲ ማግኘት ያልቻሉትን የዘመናዊ መሳሪያ ጥማት፤ ሙያዉ በሌላቸዉ ሰዎች በግድ ለማግኘት" እንደምንም መድፍ ስሩ "ብለዉ እስረኞችን አስገደዱ ፡፡

እንግሊዞች ደግሞ ሁሉም መረጃ /information/ ነበራቸው ፡፡ ቴድ አሁን መንግስት አይደለም፤ ቤተመንግስቱንና መላውን ግዛቱን ለቆ ወሎ መቅደላ አምባ ላይ መሽጎ ነዉ የሚኖረዉ ፡፡ በፊት መንግስት በነበረበት ሰዓት ባለሙያ ጠይቋቸው ቢሆን ኖሮ ምናልባት ሊልኩለት ይችሉ ነበር፤ እሱ ግን በፊት ሰላም በነበረበት ሰዓት ይህን መሳሪያ የማሰራት ጉዳይ አስቦት አያውቅም፤ አሁን ግን መንግስት ላልሆነና ገና እንግሊዞችን የጦር መሳሪያ አሰርቼ ወደ ቤተመንግስቴ እመለሳለሁ ብሎ ተስፋ ላደረገ ቡድን ባለሙያ ሊልኩ አይችሉም ማለት ነው ፡፡ አሁን ሀገሪቱን እያሽከረከረ ያለዉ ዋግሹም ጎበዜ የሚባል ነዉ ፡፡ ንጉሰ ነገስቱ /ቴድ/ ትግሉን እስካላቆመ ድረስ ሁለተኛ ሰዉ ተቀብቶ ንጉሰ ነገስት መባል ስለማይቻል ነዉ እንጂ ሀገሪቱን በበላይነት እያስተዳደረ ያለዉ ዋግሹም ስዩም ጎበዜ ነዉ /ዋግሹሙ ተከቦ መቅደላ ላይ የሚኖረውን ቴድን በትንሽ መሰዋእትነት ለመያዝ የጦር መሳሪያውን

እስኪጨርስ ድረስ ነበር የተወው፤ ለዚያም ነበር ቴድ መሳሪያ የማሰራት ትንቅንቅ ውስጥ የገባው/ ። እናም እንግሊዞች፣ ይህን ያውቁ ስለነበር ለአንድ መንግስት ላልሆነና ገና እንግሊዞችን የጦር መሳሪያ አሰርቼ ወደ ቤተመንግስቴ እመለሳለሁ ብሎ ተስፋ ላደረገ ቡድን ባለሙያ ሊልኩ ስለማይችሉ ነበር፣ ዜጎቻቸዉን በማታለል ለማስፈታት ሲሞክሩ የነበረው ።

ቴድም ቆንሲሎቹን የግድ የጦር መሳሪያ ለማሰራት ወሰነ ። ቆንሲሎቹ የጦር መሳሪያ ለመስራት ቢሞክሩም አልቻሉም ። ቴዎድሮስም መረር ያለ እርምጃ መዉሰድ ጀመረ ። በጅራፍ ያስገርፋቸዉ ጀመር ። በተለይ በእንግሊዞቹ ላይ በጣም የከፋ ነበር እርምጃዉ ። ሄንሪ ስተርን የተባለዉ እንግሊዛዊም በጅራፍ ግርፋት ምክንያት ስቃይ በዝቶበት ለሞት መቃረቡን እንግሊዛዉያኑ ሲሰሙ በጣም አዘኑ ። እንግሊዞችም ለማታለል ሲሉ እደ ጥበብ ባለሞያዎችን ላኩ ። ከለንደን የመጡት ባለሞያዎች ግን የምፅዋ ወደብ ከደረሱ በኋላ "የታሰሩት ካልተፈቱ በስተቀር ወደ መሀል ሀገር አንገባም" ብለዉ ላኩ ። ነገር ግን አላማቸዉ አታለዉ ለማስፈታት እንጂ የተላኩት ሰዎች ሙያተኞች አልነበሩም ። ቴዎድሮስ ግን "እስረኞችን የምለቀዉ ባለሞያዎቹ ደብረ ታቦር ሲደርሱ ብቻ ነዉ" በማለት ዉሳኔቸዉን አሳወቁ ። በዚህ መካከል ሴባስቶፖል የተባለዉ መድፍ በእስረኞች ተሰራ ። ሁሉም በደስታ ከመፈንደቃቸዉ ባሻገር ቴዎድሮስ በግድ ያሰሩትን መድፍ አቅፈዉ ሳሙት ።

እንግሊዞችም ዜጎቻቸውን ለማስፈታት ብዙ ድርድሮች ተካሄዱ፣ በማባበያ ቃላትና በገጸ በረከት ዜጎቻችዉን ለማስለቀቅ እንግሊዞች ብዙ ጣሩ ። በዋግሹም ጎበዜ፣ ቤተመንግስቱንና መላውን ግዛቱን ለቆ መቅደላ የሚኖረዉ ቴዎድሮስ ደግሞ፤ ማባበያና ገጸ በረከት ሳይሆን የግድ የጦር መሣሪያ አግኝቶ ዋግሹም ጎበዜን አምበርክኮ ወደ ቤተመንግስቱ መመለስ ይኖርበታል ። ስለሆነም የጦር መሳሪያ ካላመጣችሁ ወይ ካልተሰራ በቀር በቃላት አልሸነገልም አለ ።

እንግሊዞች ትዕግስታቸዉ ተሟጠጠ ። የለንደን ምክር ቤት አስቸኳይ ጉባኤ ጠርቶ "ጦር ተልኮ እስረኞቹ በሀይል እንዲፈቱ" የሚል ዉሳኔ አሳለፈ ። ለዘመቻዉም 4,330,285 ፓዉንድ ተመደበ ።

እንግሊዞችም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ተቃወሞ እንዳይገጥማቸዉ "እስረኛ ለማስፈታት እንጂ ሀገር ለመዉረር አልመጣንም" እያሉ ህዝቡን

በፈገግታ ያሳምኑ ነበር ። በዚህ ጊዜ የአድዋዉ ደጃች ካሳ ምርጫ /በኋላ አፄ ዮሃንስ/ የእንግሊዝ ጦር ወደ ሰፈረበት ቦታ ሄደዉ “እንኳን ደህና መጣችሁ” በማለት አቀባበል አደረጉላቸዉ ። ለዋናዉ መሪ ለጀኔራል ናፒየርም ታላቅ ግብዣ በማድረግ የአንበሳ ጎፈር በራሱ ላይ በመጫን የተሸለሙች በቅሎዋቸዉን ሰጥተዉ መልካም ምኞት ተመኝተዉ ጎራደና ጦር ሰጥተዉ ነበር የሸኙት ፡ ፡ /የአድዋው ካሳ ምርጫ ይህ ሁሉ ጥረት ከእንግሊዞች የጦር መሳሪያ ሰብስቦ የወሎውን ዋግሹም ስዩም ጎበዜን ለመምታት ነዉ/ ። እንግሊዞችም ከወደብ፣ ወደ ሰንአፌ፣ ከሰንአፌ ወደ አሸንጌ፣ ከአሸንጌ ወደ ደቡብ ወሎዋ መቅደላ ተጠግተው ሰፈሩ ።

ከአሽከርነት አንስተው እየሾሙ የጦራቸዉ ዋና አዛዥ ባደረጉት በእቴጌ መነን ላይ በፈፀመዉ ክህደት ምክንያት ከባድ ዋጋ ሲከፍልና ሲሰቃይ የኖረዉ ቴድ፣ የተሻለ የጦር መሳሪያ አስመጥቶ፤ ካልተቻለ ደግሞ አሰርቶ ዋግሹም ጎበዜን ለማንበርከክና ወደ ቤተመንግስቱ ለመመለስ ያደረገዉ ጥረት አልተሳካም ። በዚህ ቡድን የታሰሩበትን ዜጎቹን ለማስፈታት የመጣዉ የእንግሊዝ ጦር እየተጠጋ ነዉ ።

ቴዎድሮስ ከወቅቱ አንፃር በጣም የተማረ ሰው ስለነበር /ገዳም ውስጥ መንፈሳዊና አለማዊ ትምህርት እየተማረ ነው ያደገው/ በእቴጌ መነን ስር ሆኖ መስራቱን ቢቀጥል ኖሮ አገሪቱንም መጥቀም ይችል ነበር ። ሁሉም ነገር ተመቻችቶለት ነበር ። እናም ከወቅቱ አንፃር ቴድ በጣም የተማረ ሰው ስለነበር በእቴጌ መነን ስር ሆኖ ቢቀጥል ኖሮ ለኢትዮጵያም ብዙ ስራዎችን መስራት ይችል ነበር፤ እሱም ከዚህ ሁሉ ስቃይ ይድን ነበር ።

ትልቁ ራስ አሊ አሻንጉሊት ንጉስ ያስቀመጠዉ ወዶ አይደለም ። የህዝቡን ኋላ ቀር አመለካከት በስልት ለመያዝ ስለፈለገ ነበር ። ከላይ የባላባትነትን ስርዓት አፍርሶ ከታች ህዝቡን በባላባት ስርዓት መቆጣጠር ፈፅሞ አይቻልም ። አማራጮቹ 3 ብቻ ነበሩ ። 1ኛ የባላባትነት ስረዓትን ከነአካቴዉ ከላይ እስከ ታች አጥፍቶ ህዝቡን በሹመኞች መምራት፣ 2ኛ የዘር መበላለጥን ከላይ እስከ ታች ጠበቆ የባላባትነት ስርዓትን ማስቀጠልና 3ኛ እንደ ትልቁ ራስ ዓሊ የነጋሲ ዘር ያለዉ መጋረጃ /ኮፍያ/ ማስቀመጥ ነበሩ ። 3ኛዉ ምርጫ ለቴድ አይሆንም፤ እራሱ ሮጦ ንጉስ ስለሆነ አሻንጉሊት ንጉስ ማስቀመጥ አይችልም ። 2ኛዉ ምርጫ ደግሞ እራሱ ስልጣን ካለቀቀ በስተቀር

አይሆንም ። 1ኛዉ ምርጫ ይቻላል፤ ነገር ግን 1ኛዉን ምርጫ ለማስፈፀም መጀመሪያ የባላባቶችን አመፅ መቆጣጠር ያስፈልጋል፤ ይህ ነበር ችግሩ ።

እናም ቴዎድሮስ አልቻሉም ። ተዋበች እስከምትሞት ድረስ በሰላም ገዝተዋል፣ ምንም አይነት ጦርነትና አመፅ አልነበረም ። አሁን ግን እቴጌ ተዋበች ሞተዋል ። ክህደት ባይፈፅም ኖሮ ተዋበች ብትሞትም ለ22 ዓመታት ያህል አገሪቱን ያስተዳደሯት እቴጌ መነንና ትንሹ ራስ አሊ ከላይ ስለሚኖሩ ማንም አይነካዉም ነበር ፡ ክህደቱ ካልቀረ ደግሞ የባላባት ስርዓቱን ከነአካቴዉ /ከላይ እስከ ታች/ መቀየር ነበረበት፤ ሁሉም አልሆነም ። እናም ሳያስበዉ የወጣለትን ትልቅ ሎተሪ ሳይጠቀምበት አበላሸዉ ።

ሚያዝያ 7 ቀን 1860 ዓ.ም በቴድ የሚመራዉ ቡድን መሸጎባት የነበረችዉ የደቡብ ወሎዋ መቅደላ ተራራ በእንግሊዞች ጦር ተከበበች ። ቴድም ጦራቸዉን ሰብስበዉ ወደ እዚያዉ አመሩ ። ሰራዊታቸዉንም በርትቶ እንዲዋጋ አዘዙ ። ነገር ግን የእንግሊዝ ጦር በታጠቀዉ ዘመናዊ መሳሪያ የዚህን ቡድን ጦር በቅፅበት አራገፈዉ ። በዚህ ጊዜ ቴድ በጥልቅ ሀዘን አለቀሰ፤ ወዳዉም እስረኞቹን ፈቶ ለቀቃቸዉ ። እስረኞቹ ቢፈቱም ጦርነቱ አልቆመም፤ እንግሊዞች እስረኞቹን ከተቀበሉ በኋላ እንደገና ጦርነቱን ጀምረው ቴድን እጅ እንዲሰጡ ቢጠይቋቸዉም ቴድ ግን በያዙት ሽጉጥ እራሳቸዉን በማጥፋት አረፉ /የቴድ አሟሟት አከራካሪ ቢሆንም እኛ ግን ጥቅሙ ስላልታየን ለማረጋገጥ አልሞከርን/ ።

የእንግሊዝን ጦር እየመሩ የመጡት ጀኔራሎች እዚሁ መንግስት ሆነው የመቀጠል ፍላጎት ነበራቸው ። ነገር ግን ሀገሪቱ ከገመቱት በላይ ጠንካራና ከአቅማቸው በላይ ሆና ነው ያገኟት ። ሁሉም መሳፍንቶች በዋግሹም ጎበዜ /በኋላ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ዙሪያ እንደተሰለፉና ሀገሪቱ ጠንካራ መንግስት እንዳላት ተረዱ ።

እንግሊዞች ቡድኑን በመምታት ቴድ ከሞተ በኋላ ለተወሰኑ ቀናት የአካባቢውን ሁኔታ ማስተዋል ጀመሩ፤ የቴድ መሞት ምንም ለዉጥ አላመጣም ። መጀመሪያ የነበራቸዉ መረጃ /information/ ትክክል እንደነበር አረጋገጡ ። ደቡብ ወሎ መቅደላ አምባ መሽገዉ ይኖሩ የነበሩት ቴድ ምንም አይነት ሀገራዊ ሚና እንዳልነበራቸዉና ስልጣናቸዉም ከሚመሩት

ቡድን ዉጭ እንዳልነበር በአይናቸዉ አረጋገጡ ። በተቃራኒው ዋግሹም ጎበዜ የሚባል ከአቅማቸው በላይ የሆነ ጠንካራ መንግስት እንዳለ አረጋገጡ ።

የእንግሊዝ ጀኔራሎች ቀጥለውም የአፄ ቴዎድሮስ የነበረውን ግዛት ስፋት ማጥናት ጀመሩ፤ ነገር ግን የአጼ ቴዎድሮስ ግዛት እጅግ ጠባብ ሆነባቸው /እዚሁ መንግስት ሆነው የሚቀጥሉ ከሆነ ዋግሹም ጎበዜን መዋጋትና ግዛታቸውን ማስፋት የግድ ሆነባቸው/ ። እንግሊዞች ቀጥለውም የራሳቸዉንና የዋግሹም ጎበዜን ሁኔታ ማመዛዘን ጀመሩ ። በስንቅ ስለሆነ የመጡት በማያዉቁት አገር ዉስጥ ተከበዉ ከ60ሺ በላይ በሚሆነዉ የዋግሹም ጎበዜ ጦር መሀል ላይ ነበር የሚገኙት ። እናም ምንም ሌላ ነገር ሳይፈልጉ በፍጥነት ሀገሪቱን ለቀዉ ወጡ /የቴድ ግዛት እጅግ ጠባብ ስለሆነባቸው ትተውት ወጡ እንጂ በቴድ እጅ ያገኟቸውን ቅርሶች ግን ጠራርገው ወስደዋል/ ። በዚህ ምክንያት እንግሊዞች ዋግሹም ጎበዜን በጣም ስለጠሉት አንድት እንኳን የጦር መሳሪያ አልሰጡትም፤ እንግሊዞች ከጎበዜ ጋር በቃላትም ሆነ በአካል ተገናኝተው አያውቁም ።

ስለዚህ ዋግሹም ጎበዜ ሀገሪቱን ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አውጥቷታል ማለት ነው ። ነገር ግን ስሙ ተነስቶ አያውቅም፤ ምክንያቱ ደግሞ ጎበዜ ከተነሳ ቴድ ትርጉም አይኖረውም፤ ስለዚህ ጎበዜ መረሳት አለበት ነው ። ምክንያቱም ዋግሹም ጎበዜ /አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ካልተረሳ፣ ቴድን ከስልጣኑ ያወረደው /ቤተመንግስቱንና መላዋን ሀገሪቱን ያስለቀቀው/ ዋግሹም ጎበዜ እንጂ እንግሊዞች እንዳልሆኑ ይታወቃል ማለት ነው ። እናም የእንግሊዝ ጀኔራሎች አዝነውልን እንደወጡ ይቆጠር እንጂ ቴድ በጎበዜ ተሸንፎ እንደነበርና እንግሊዞችም ጎበዜን ፈርተው እንደወጡ መታወቅ የለበትም ነው /የእንግሊዝ ጀኔራሎች ሌሎች የአፍሪካ አገሮችን አሳራቸውን እያበሉ እኛን ሊያዝኑልን አይችሉም፣ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ሁኔታ ስለነበር ነው/ ። በእርግጥ እስከ አሁን ድረስ የእንግሊዝ ጀኔራሎች አዝነውልን ነው የወጡት ተብሎ የተፃፈ የለም /አዝነውልን እንደማይወጡ ይታወቃል/ ። ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ እንግሊዞች በፍጥነት የወጡበት ምክንያት ተፅፎ አያውቅም ። የኢትዮጵያ ህዝብም እስከ አሁን ድረስ እንግሊዞች ለምን በፍጥነት እንደወጡ አያውቅም፣ ምክንያቱ ደግሞ ዋግሹም ጎበዜ /አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ ካልተረሳ፣ ቴድን ቀድሞ ከስልጣኑ ያወረደው /ቤተመንግስቱንና መላዋን ሀገሪቱን ያስለቀቀው/ ዋግሹም ጎበዜ እንጂ እንግሊዞች እንዳልነበሩ ይታወቃል ማለት ነው ። እናም

የአፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ ታሪክ፣ እንዲጠፋ ከተደረጉ የሀገራችን ታሪኮች መካከል አንዱ ነው ማለት ነው /ከጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ታሪክ በሙሉ ጠፍቶ የበላይ ዘለቀና የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ብቻ መሆኑ አይቀርም/ ፡፡

በጀኔራል ሮቤርቶ ናፒየር የተመራዉ የእንግሊዝ ጦር ሰራዊት ይህ ቡድን በመሸገባት የመቅደላ ተራራ ተከማችተዉ ያገኟቸዉን የየጁና የሸዋ ነገስታት የወርቅ ዘዉድ፣ የወርቅ ፅዋ፣ የእቴጌ መነንን የወርቅ አክሊል፣ በሳጥን የተሞሉ ወርቆችን፣በወርቅ የተለበጡ ጋሻዎችን፣ በወርቅ የተለበጡ ጻናጽሎችንና የበርካታ አድባራትን ዉድ ቅርሶች በደላንታ ሜዳ ለእንግሊዝ ዜጎች ጨረታ አቅርበዉ ከተቀራመቷቸዉ በኋላ በፍጥንት ኢትዮጵያን ለቀዉ ወጡ ፡፡

## <u>አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ/ዋግሹም</u> <u>ጎበዜ/</u> ከ1860-1863 ዓ.ም

እንግሊዞች እስረኞቻቸዉን ካስፈቱ በኋላ ዉልቅ ብለዉ የሄዱት ከ60ሺ በላይ በሚሆነው የዋግሹም ጎበዜ ሰራዊት በመከበባቸው ነበር ፡፡ በዚህ ምክንያት እንግሊዞች ዋግሹም ጎበዜን በጣም ስለጠሉት አንድት እንኳን የጦር መሳሪያ አልሰጡትም፤ እንግሊዞች ከጎበዜ ጋር በቃላትም ሆነ በአካል ተገናኝተው አያውቁም ፡፡ እናም ዋግሹም ጎበዜ ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ ጀኔራሎች ቅኝ ግዛት አድነዋታል ማለት ነው ፡፡ ነገር ግን ስማቸው ተነስቶ አያውቅም፤ እስከ አሁን ድረስ እንግሊዞች ለምን ፈጥነው እንደወጡ ተፅፎ አያውቅም፣ አዝነውልን ነው የወጡት ተብሎ የተፃፈም የለም /አዝነውልን እንደማይወጡ ይታወቃል/ ፡፡ እናም የኢትዮጵያም ህዝብ እስከ አሁን ድረስ እንግሊዞች እንደት በፍጥነት እንደወጡ አያውቅም ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛመረሳት አለበት ነው፤ ካልተረሳ ግን ቴድን ከስልጣን ያወረደው /ቤተመንግስቱንና መላዋን ሀገሪቱን ያስለቀቀው/ ጎበዜ እንጂ እንግሊዞች እንዳልሆኑ ይታወቃል ማለት ነው ፡፡ እናም የአፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ ታሪክ እንዲጠፋ ከተደረጉ የሀገራችን ታሪኮች መካከል አንዱ ነው ማለት ነው /ከጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ታሪክ የበላይ ዘለቀና የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ብቻ መሆኑ አይቀርም /ወሎ ገራገሩ// ፡፡

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ “የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ” በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች ጋር እያመሳከርኩንና እያሳጠርኩኝ አስነብባችኋሉ ።

እንግሊዞች ጉዳያቸዉን ፈፅመዉ “ተስማምታችሁ ኑሩ” ብለዉ ሄዱ ። በወቅቱ ከ60ሺ በላይ ሠራዊት የነበራቸዉ የላስታዉ ተወላጅ ከአፄ ላሊበላ የዘር ሀረግ የወረዱት ዋግሹም ጎበዜ በፍጥነት ተነሱና ለመንገስ ሲሉ ጳጳስ የለም /ሁለተኛ ተቀብቶ ንጉሰ ነገስት መባል ስለማይቻል እንጂ ንጉሰ ነገስትነታቸውን የተቃወመ አልነበረም፣ ቀድሞ ያለቀ ነገር ነበር ማለት ነው፤ በትንሸ መሰዋእትነት ለመያዝ ቴድ መሳሪያውን እስኪጨርስ ድረስ ብቻ ነበር የሚጠበቀው፤ ለዚያም ነበር ቴድ መሳሪያ የማሰራት ትንቅንቅ ውስጥ የገባው/ ። እናም አቡነ ሰላማ በቴዎድሮስ ጊዜ ስለሞቱና የጳጳስ ማስመጫዉ ወደብም በግብፆች ስለተያዘ ዋግሹም ጎበዜ በኢትዮጵያዊዉ እጨጌ ገብረ እየሱስ እጅ ተቀብተዉ በሚያዝያ ወር 1860 ዓ.ም ንጉሰ ነገስት ተብለዉ የመንግስት ስማቸዉንም አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ አሰኙ ። /ቴድ ሚያዝያ 7 ቀን 1860ዓ.ም ነዉ የሞተዉ፤ ዋግሹም ጎበዜ አንድ ወር እንኳን ሳይቆዩ ነዉ ንጉሰ ነገስት የተባሉት ማለት ነው፣ ቀድሞ ያለቀ ጉዳይ ነበር ማለት ነው፣ በጳጳስ መቀባቱ ብቻ ነበር የቀረው ማለት ነው/ ።አፄ ተክለጊዮርጊስ 2ኛ ከሰሯቸዉ ስራዎች ዉስጥ ሊጠቀስላቸዉ የሚችለዉ የጎንደር ቤተመንግስትን ማሳደሳቸዉ ነዉ ።

እንግሊዞች ከመጡ ጀምሮ የትግሬዉ ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ከእንግሊዞች መሳሪያ እየሰበሰበ መሆኑን ስላወቁ በኋላ ላይ እሳቸዉም በእንግሊዞች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት በርካታ ደብዳቤዎችን ይፅፉ ነበር ። ሆኖም የደጃዝማች ካሳ ምርጫን ያህል ተቀባይነት ማግኘት አልቻሉም ።

ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ድምፃቸዉን አጥፍተዉ ለ3 ዓመት ያህል የንግስና መንገዳቸዉን እዚያዉ አድዋ ሆነዉ እያመቻቹ ቆዩ ። ወታደሮቻቸዉ በእንግሊዛዊያኖቹ በእነ ኪርክሀምና በእነ ሉዊ በቂ ስልጠና እየወሰዱ ቆዩ ። በቂ ዘመናዊ የጦር መሳሪያም ከእንግሊዛዊያኑ መሰብሰብ ቻሉ ።

ካሳ ምርጫ ድምፃቸዉን አጥፍተዉ ዝግጅታቸዉን ከጨረሱ በኋላ አንዳንድ የአመፅ እንቅስቃሴዎችን ከማድረግም በተጨማሪ ለንጉሰ ነገስቱ መገበር አቆሙ ። አፄ ተክለጊዮርጊስም በመልዕክተኛ ዛቻ ቢያዥጎደጉዱም ዉጤት አልባ ሆነ ።

በመጨረሻ በ1863 ዓ.ም 60ሺ ወታደር አስከትለዉ ያረጀ መሳሪያና ጋሻ፣ ጦር፣ ጎራዴ አስታጥቀዉ ወደ አድዋ ተጓዙ ። ደጃዝማች ካሳ ምርጫም 12ሺ ሰራዊታቸዉን ስድስትና አምስት ኢንች ዉፍረት ያለዉን ሞርታር፣ 12 መድፎችና ሌሎቹን ቀላል ዘመናዊ መሳሪያዎችን አስታጥቀዉ በእንግሊዛዊያኑ በነ ኪርክሀምና በነ ሉዊ ስልጠና የወሰዱ ወታደሮቻቸዉን ጥሩ ምሽግ አስይዘዉ ጠበቋቸዉ ።

አሳም ላይ ዉጊያዉ ተካሄደ ። አፄ ተክለጊዮርጊስ ፈረሳቸዉ ላይ ሆነዉ ሲያዋጉ እያለ በመድፍ ጥይት ከፈረሳቸዉ ጋር ተመተዉ ወደቁ፤ ቆስለዉ ከወደቁበት ላይ ተያዙ ። በዚህ ጊዜ ያሁሉ ወታደራቸዉ የንጉሱን መማረክ ሲያይ ተደናግጦ ዉጊያዉን አቆመና ድል የደጃዝማች ካሳ ምርጫ ሆነ ። 60ሺ ጦር ብዙም ሳይዋጋና ብዙ እልቂት ሳይፈጠር 1ሺ የሚሆን ጦር ቆስሎ ጦርነቱ ተጠናቀቀ ።

አፄ ዮሃንስ 4ኛ (ከ1864-1881 ዓ.ም) ፡ - ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች መፀሀፍት ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋሉ ።

ደጃዝማች ካሳ ምርጫ የተወለዱት በትግራይ ግዛት አድዋ አካባቢ /ተምቤይን/ በ1825 ዓ.ም ሲሆን በትግራይ መኳንንት እግር ተተክተዉ የአካባቢዉ ገዥ ሆነዉ ቆይተዋል ። ከአፄ ተክለጊዮርጊስ ድል በኋላም ጥር 13 ቀን 1864 ዓ.ም በእለተ እሁድ በአክሱም ፅዮን ቤተክርስትያን በጳጳሱ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተዉ "ዮሃንስ 4ኛ" ተብለዉ ነገሱ ።

አፄ ዮሃንስ 4ኛ በየወደቡ አሰፍስፈዉ ያሉ ኢትዮጵያን የመዉረር እቅድ ያላቸዉ አገሮች መበርከታቸዉን ባዩ ጊዜ፣ ከተለያዩ የአዉሮፓ ነገስታት ጋር ወዳጅነታቸዉን ለማጠናከር እንደ ተጉ ነበሩ ።

ግብጽ በመሪዋ በከዲቭ ኢስማኤል አማካኝነት ከምፅዋ አልፋ ኢትዮጵያን ለመዉረርና ለመያዝ ተነሳች ። አፄ ዮሃንስ 4ኛ የግብፅን የወረራ ሀሳብና እንቅስቃሴ እንዳዩ ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ቢጥሩም የአዉሮፓ አገሮች ፊታቸዉን ወደ ግብፅ አዞረዉ ማድላት ጀመሩ ።

ግብፆች ከምጽዋ ተነስተዉ የቦጎስ ከረንን ክልል ተቆጣጠሩ ። በሰሜን የዘመተዉም የግብፅ ወራሪ ጦር ከምፅዋ በመንቀሳቀስ ዶጋሊን፣ከዚያም ሐማሴንን ወረረ ።

አፄ ዮሃንስ 70ሺ የሚደርስ የጦር ሰራዊታቸዉን ባልተጠበቀ ፍጥነት በማሰባሰብ ወደ ወራሪዉ በመገስገስ ጉንደት ላይ ገጠሙት ፡ ሰራዊታቸዉ በእነ ራስ አሉላ እየተመራ በማጥቃት ጥላትን ብትንትናቸዉን አዉጥቶ ድል አደረጋቸው ። አዝማቹ አሬንድረፕም ተገደለ ። በአዉሳ ግንባር ያለዉም ወራሪ ጦር በኢትዩጵያ የደፈጣ ተዋጊዎች ደንከል በረሀ ዉስጥ አለቀ ።

በዚህ ሽንፈት ዉርደት የተሰማቸዉ ግብፆች 20ሺ የሚደርስ ወራሪ ጦር በመሐመድ ራቲብ ፓሻና በከዲቭ ኢስማኤል ልጅ ልዑል ሃሰን እየተመራ በ1868 ዓ.ም ኢትዮጵያን በድጋሜ ወረረ ። የግብጽ ጦርም ከምጽዋ ወደ አስመራ፣ ከዚያም ጉራእን ተቆጣጥረዉ ጠንካራ ምሽግ ገነቡ ።

አፄ ዮሃንስ 4ኛ "ምታ ነጋሪት፣ ከተት ሰራዊት" ብለው ከአስሩ አንዱ ብቻ መሳሪያ የታጠቀ 70ሺ ጦር ሰራዊታቸዉን አስከትለዉ ከዋና መቀመጫቸዉ ከአድዋ ተነስተዉ ዘመቱ ፡ የኢትዮጵያ ጦር በጉንደትና በአዲኳላ አድርጎ ወደ ጉራእ አመራ ። ጉራእ ላይ የመሸገዉ የግብፅ ጦር 40 መድፍና 10 ሮኬት ደግኖ ኢትዮጵያዊያኑን መጠበቅ ጀመረ ። የሁለቱ ሰራዊት ምሽጋቸዉን ተገን አድርገዉ ለሳምንታት መቆየታቸዉ የጦርነቱን ጊዜ አራዘመዉ ።

ልዑል ሃሰን የኢትዮጵያን ሰራዊት ቀስቅሶ ለመፍጀት አስቦ የግብፅ ጦር እንዲያጠቃ አዘዘ ፡ የኢትዮጵያ ጦር እንደንብ ከምሽጉ ወጥቶ ወደነሱ ሲወረወር ልዑል ሃሰን ወዲያዉ ሰራዊታቸዉ ምሽግ ዉስጥ እንዲገባ አዘዙ ። ከቀሰቀሳቸዉ በኋላ የግብፅ ጦር ምሽግ ዉስጥ ሆኖ ኢትዮጵያዉያኑን ማርገፍ ጀመረ ። እንደገመቱትም ኢትዮጵያዊያኑ ከዚያ በኋላ አልተመለሱም ጠላት ከገባበት ምሽግ ዉስጥ ተከታትለዉ እየገቡ መዋጋታቸዉን ቀጠሉ፤ ብዙ ጀግና አለቀ ። ጦርነቱ በማግስቱም ቀጠለና ኢትዮጵያዉያኑ ምሽጉን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠሩት ። አብዛኛዎቹ ግብፆች ከዘመናዊ መሳሪያዎቻቸዉ ጋር ተማረኩ፣ ጥቂቶቹ አመለጡ ። በዚህ ድል 20 መድፍና በርካታ ዘመናዊ መሳሪያዎች ተማረኩ ።

ከድሉ በኋላ ግብፅ የእርቅ ጥያቄ አቀረበች ። በጉዳዩም እንግሊዝ አስታራቂ ሆነችና ማግባባት ጀመረች ። የግብፅ ጥያቄ ወደቡን እንደያዘች

ልትቀጥል፣ ነገር ግን ሌላ የኢትዮጵያን ግዛት ላትነካ የሚል የነበረ ሲሆን፣ አፄ ዮሃንስ ግን ሁሉም ካልተመለሰልኝ አልታረቅም አሉ ። በዚህ መሀል በማህዲ የሚመራዉ የሱዳን አርበኞች ጦር /ማህዲስት/፣ ግብፅ በኢትዮጵያ መሸነፏን ሲሰማ ቀዝቅዞ የነበረዉን ትግሉን እንደገና ጀመረ ። የማህዲስቶች ጦር የበላይነቱን እየያዘ ሲመጣ ግብፅ እንኳን ሱዳን ዉስጥ ለመቆየት አካባቢዉን ለቆ ለመዉጣትም ተሳናት ። የማህዲ ጦር ሱዳን ውስጥ የነበረውን የግብፅን፣ የቱርክንና የእንግሊዝን ጦር እያባረረ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር አስጠጋቸዉ ። አልፈዉ እንዳይሄዱና እዚያዉ እንዲያልቁ ስለፈለገም ኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ከሰላ ላይ አስከበባቸዉ ።

እንግሊዝ ይህን የኢትዮጵያ ድምበር ከሰላ ላይ በማህዲስቶች ተከቦ እየተጨነቀ ያለዉን ጦሯን በሰላም ለማስወጣት ስትል ተቋርጦ የነበረዉን የግብፅና ኢትዮጵያን ስምምነት እንደገና አንስታ አጼ ዮሃንስን ማግባባቷን ቀጠለች ። ግብፅና ኢትዮጵያ በእንግሊዝ ሽምጋይነት ተስማሙ ። ግብፅ ወደቡን ለቃ እንዲትወጣ፣ አፄ ዮሃንስ ደግሞ በማህዲስቶች ተከቦ የሚገኘዉን የግብፅ ጦር ተዋግተዉ ከበባዉን ሰብረዉ በሰላም አስወጥተዉ ወደ ግብፅ እንዲያሻግሩ የሚል ያለበት ስምምነት ሰኔ 3 ቀን 1876 ዓ.ም ተፈራረሙ /የሔዊት ዉል/ ። እናም በማህዲስቶች የተከበበዉን ጦር አፄ ዮሃንስ ከጀግናዉ አሉላ አባነጋ ጋር ሆነዉ ተዋግተዉ ነፃ አዉጥተዉ በሰላም እንዲሻገሩ አደረጉ ። በዚህ ምክንያት ማህዲስቶች በኢትዮጵያ ላይ አደገኛ ቂም ያዙ ።

እንግሊዝ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መታች ። ግብጽ ከሁለቱም አገሮች ከወጣች በኋላ ሱዳንን ራሷ ስትቆጣጠር፣ የምፅዋ ወደብን የኢጣሊያ ወኪሎቿን አስይዛ ወደቡ ላይ ያሻትን ለማድረግ አመቻቸች ። ይህን ተከትሎ ኤርትራ የምትባል ሀገር ተፀነሰች ። ግብፅ ከሱዳን እንደወጣች እንግሊዝ ሌሎች ሱዳናዉያንን በማስታጠቅ የማህዲን ጦር እንዲወጉ አደረገችና የማህድስቶች መሪ ማህዲ ተገደለ ።

ነገር ግን የማህዲ ጦር በኢትዮጵያ ላይ ቂም ይዞ ስለነበር በኡስማን ዲግና እየተመራ በኢትዮጵያ ላይ ተነሳ ። በዚህ መሀል ከምፅዋ ተነስቶ ለመስፋፋት ሞክሮ በጀግናው አሉላ አባነጋ የተመታዉ የኢጣሊያ ጦር፣ በስልት አሉላን ከአፄ ዮሃንስ ጋር አጣልቶ፣ አሉላን ካሳሰረ በኋላ በመስፋፋት ኤርትራ የምትባል ሀገርን ፈጠረ ። የሱዳን ማህዲስቶች /ድርቡሾች/ በቂ ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ቂማቸዉን ለመወጣት፣ በ1881 ዓ.ም 85ሺ የሱዳን ጦር

በመተማ አድርጎ ጎንደር ድረስ በመዝለቅ ህዝቡን በጭካኔ በመጨፍጨፍ፣ ቤተክርስቲያንንና ገዳማትን በማቃጠል ከፍተኛ ጥፋት ካደረሰ በኋላ ተመልሶ መተማ ላይ መሽጎ መጠባበቅ ጀመረ ። አፄ ዮሃንስም ጦራቸዉን ይዘዉ ተጉዘዉ በዚሁ ቦታ ዉጊያዉ ተጀመረ ። ቀኑን ሙሉ በተካሄደ ከባድ ጦርነት የኢትዮጵያ ጦር ምሽጉን እየጣሰ መግባት ጀመረ፣ ሱዳኖችም በርትትዉ መዋጋታቸውን ቀጠሉ፣ አፄ ዮሃንስም አብረዉ እየተዋጉ ሲያዋጉ ዉለዉ አመሻሽ ላይ ድል ለኢትዮጵያ ሊሆን በተቃረበበት ሰአት ድንገት አንድት ተባራሪ ጥይት የአፄ ዮሃንስ ደረት ዉስጥ ገባችና ፍፃሜቸዉ ሆነ ።

# ምዕራፍ ስድስት

## አፄ ምኒሊክ 2ኛ (ከ1882-1906)

ልጅ ምኒሊክ ከሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ነገስታት ዉስጥ አንዱ ከሆኑት ከአፄ ያዕቆብ ትዉልድ 13ኛ የዘር ሀረግ ላይ ይቀመጣሉ ። አያታቸዉ ሳህለስላሴ የሸዋዉን ንጉስ ሐይለመለኮትን ወለዱ ። ሐይለመለኮት ከወ/ሮ እጅጋየሁ ልጅ ሚኒሊክን ወለዱ ።

ነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም የተወለዱት ልጅ ምኒሊክ በ11 አመታቸዉ አካባቢ አባታቸው ሞቶ ስለነበር አፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ ይዘዋቸዉ ወደ ጎንደር ሄደዉ ነበር ። ከወሰዷቸውም በኋላ በእስር እንዲቀመጡ አደረጓቸው ። በ1857 ዓ.ም ከወሎ ባላባቶች ጋር ዉስጥ ዉስጡን ሲላላኩ ቆይተዉ ከመቅደላ እስር ቤት አምልጠዉ ወሎ ገቡ ።

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮና ማንቴል ኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች “የኢትዮጵያ ታሪክ” በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ካሳፈሩትና በዓለማየሁ አበበ ከተተረጎመዉ መጸሀፍ ዉስጥ የሰፈረዉ ቃል በቃል ሲቀመጥ “በዝግጅቱም ላይ /ሚኒሊክ ከእስር ለማምለጥ ሲዘጋጅ/ የወሎ ገዥ የነበረችው ልዕልት ወርቂት፣ ለአፄ ቴዎድሮስ ፍቅር አልነበራትምና ሚኒሊክን እረድታዋለች ። ሚኒሊክም በሰኔ 22 ቀን 1857 ዓ.ም ሌሊቱን ተደብቆ ከመቅደላ እስር ቤት አመለጠ ይልና፣

ቴዎድሮስም ሚኒሊክ ማምለጡንና ወርቂት ያደረገችለትን እርዳታ ሲሰማ በመያዣነት መቅደላ ታስራ የነበረችዉን የልዕልት ወርቂትን ልጅ እጅና እግሯን አስቆርጦ ገደል አስወረወራት ። ይህ አድራጎት መስፍኑን /ሚኒሊክን/ ጠቅሞታል፤ የበቀል ስሜት ያዘለችዉ ወርቂት አንድ የታጠቀ ጓድ /ሰራዊት/ ስለመደበችለት የማይናቅ ኃይል አስከትሎ ነዉ ሸዋ የገባዉ" ይላል ።

ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ "ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒሊክ በሚለዉ መጸሀፋቸዉ" ያሰፈሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ "ሰኔ 21 ቀን 1857 ዓ.ም ዳግማዊ ሚኒሊክ ከመቅደላ ከአጼ ቴዎድሮስ እስር ካምፕ ወጥተዉ እናታቸዉንና መኳንንቶቻቸዉን ይዘዉ ወደ ወሎ ወረሂመኖ ተጓዙ ። አጼ ቴዎድሮስም የዳግማዊ ሚኒሊክን ማምለጥ በሰሙ ጊዜ ተበሳጭተዉ የወሎ የወረሂመኖን ይማሙንም መኳንንቱንም ሁሉ እጃቸዉንና እግራቸዉን እየቆረጡ ገደል አስወረወሯቸዉ ። ሚኒሊክም ከመቅደላ ከወጣ በኋላ የአባቱ ወዳጅ ወደነበሩት ወ/ሮ ወርቂት እየመጣሁ ስለሆነ ተቀባይ ሰዉ ላኪልኝ ብሎ ላከ ። እሷም ተቀባይ ሰዉ ላከችለት ። በዚህ ጊዜ አቶ በዛብህ ነገስኩ ብሎ በሸዋ ዙፋን ተቀምጦ ነበርና ይህን በሰማ ጊዜ ለወ/ሮ ወርቂት ሚኒሊክን እሰሪልኝ ብሎ ሁለት ሺ ብር፣ በርካታ ፈረስና በቅሎ ላከላት ። ወ/ሮ ወርቂት ግን በዛብህን ተቃዉማ፤ ሚኒሊክ ከመቅደላ ተነስቶ ቦሩ ሜዳ በደረሰ ጊዜ ተቀብላ፣ የሸዋ ሰዉ አዉራህ መጥቶልሀልና ደስ ይበልህ ተቀበል ብላ አዋጅ አስነግራ፣ በዘብ እያስጠበቀች፣ ሶስት የጭፍራ አለቃ ሰራዊት፣ መለከትና እምቢልታ ጨምራ ወደ ግሼ ድምበር ወደ ዓሊ ቡኮ ላከችዉ ። ይህን ተከትሎ አጼ ቴዎድሮስ በመያዣነት መቅደላ ታስራ የነበረችዉን የወ/ሮ ወርቂትን ልጅ አስደብድበዉ ገደል ወረወሯት" ይላል ።

እዚህ ላይ አንዳንድ ፀሀፍት ይህንንም የፀሓፌ ትእዛዝ መጸሀፍ ጨምሮ ወ/ሮ ወርቂት ልጇን ለማስለቀቅ እንደገና ሚኒሊክን ለቴዎድሮስ አሳልፋ ልትሰጠዉ ሽማግሌ ልካ እንደ ነበርና፤ ነገር ግን ሽማግሌዎቹ ገና መንገድ ላይ እያሉ ልጇ ተደብድባ መሞቷን ስለሰሙ እንደተመለሱ አስፍረዋል ። ትክክል ነው፤ ነገር ግን እናት መሆኗን መርሳት የለብንም፤ ማንኛዋም እናት ልጇን ማስቀደሟ አይቀርም ።

እናም ሚኒሊክ የወረሂመኖ ሰዎችና የልዕልት ወርቂት ልጅ በከፈሉት የህይወት /የነፍስ/ ዋጋ ከእስር ካመለጡ በኋላ ከልዕልት ወርቂት በቂ የመነሻ ሰራዊት አግኝተዋል ማለት ነው /የሦስት አለቃ ጭፍራ ሰራዊት አግኝተዋል/ ።

ራስ ሚካኤል /መሐመድ ዓሊ/ና አፄ ሚኒሊክም ተጣምረዉ የቀሩት በዚህ ምክንያት ነዉ፤ ራስ ሚካኤልም የወረሂመኖ ሰው ናቸዉ ፡ የአፄ ሚኒሊክ ህይወት የተረፈዉ ደግሞ ወረሂመኖዎችና የወ/ሮ ወርቂት ልጅ በከፈሉት የነፍስ ዋጋ ነዉ ። እናም አፄ ሚኒሊክ እድሜ ልካቸዉን የወረሂመኖን ዉለታ ለመመለስ ቦዝነዉ አያዉቁም ። በሀገሪቱ ዉስጥ ከአፄ ሚኒሊክ ቀጥለዉ እጅግ ግዙፍ ሰራዊት የነበራቸዉ ንጉስ ሚካኤል ነበሩ ። አብዛኛዉን የሀገሪቱን ክፍል ያቀናዉም /ያሰፋውም/ የዚሁ የንጉስ ሚካኤል ሰራዊት ነው ።

ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ቀጥለዉም "ሚኒሊክ፣ ወ/ሮ ወርቂት የሰጧቸዉን ሶስት የጭፍራ አለቃ ሰራዊትና የስደት አሽከሮቻቸውን ይዘዉ ነሐሴ 16 1857 የወቅቱን የሸዋ ገዥ የነበረዉን በዛብህን ድል አድርገዉ የአባታቸዉን መንግስት ከጨበጡ በኋላ መራቢቴ ወርደዉ አምባዉን ሰብረዉ አካባቢዉን ተቆጣጠሩ ። በዚህም ወቅት ወ/ሮ ወርቂት ሸዋ መጥታ ነበርና ክረምቱ ካለፈ በኋላ በመስከረም አብረው ወደ ወረሂመኖ ሄደዉ የወሎ ዘመቻቸዉን ቀጠሉ ። ይማም አባዋጠዉን ግባ /ገብር/ ብለዉ ቢልኩበት እምቢ አለ ። መስቀላ ከበሩ ላይ በተካሄደ ዉጊያ ድል አደረጉት ። ከዚህ በኋላ ይማሙ አባዋጠዉ ይማሩኝ ብሎ ከፊት እናቱ ወ/ሮ መስታወት ከኋላ እሱ ሆነዉ ገቡ ። ንጉስ ሚኒሊክም ሁለቱንም ሸልመዉ ልጁን ባባቱ አገር ሹመዉ ደስ አሰኝተዉ ሸኟቸዉ ።

ነገር ግን አባዋጠዉ ንጉሱ ራቅ ማለታቸዉን አይቶ እንደገና አመፀ ። ንጉሱም ተናደዉ ወርቅ ለሰጠ ጠጠር እህል ለሰጠ አፈር ይሰጡታልን? እንግዲህ እዚሁ መቀመጫየን አደርጋለሁ ብለዉ የወረኢሉ ከተማ ተጀመረ፤ እፁብ ድንቅ ሆኖም ተሰራ ። ከዚህም በኋላ ወረኢሉ ተቀምጠዉ ሌሊት እየገሰገሱ ቀን እየወረሩ ቤተክርስቲያን እየተከሉ ወሎን ለ6 አመት ያህል አቀኑት ። ከዚያም ወዲህ ሸዋንና ወሎን እንደ እልፍኝና እንደ አዳራሽ አድርገዉ እስከ አሁን ድረስ ይገዙታል ይሉና፣

ከዚህ በኋላ በ1868 ዓ.ም ንጉስ ሚኒሊክ ያልገበረዉን ለማስገበር ወደ ደቡብ ሊዘምቱ ልቼ (ደ/ብረሃን) ከተማ መጥተዉ ነበር ። በዚያን ጊዜ ይማሙ አባዋጠዉ እንግዲህ ክረምት ነዉ አይመለሱብኝም ብሎ አሽከሮቹን አስከተተ የሚል ወሬ ሲሰሙ ንጉስ ሚኒሊክ ተመልሰዉ ገስግሰዉ ወረኢሉ ገቡ ። በዚህ ጊዜ አባዋጠዉ ጠቅሎ ወደ የጁ ወርዶ ነበር ። ንጉስ ምኒሊክ በሰኔ 22 ቀን ከወረኢሉ ገስግሰዉ በደላንታ ወጥተዉ፣ በእዜት ወርደዉ፣ በሰኔ 29 የጁ ላይ ሲደርሱ፣ ይማሙ አባዋጠዉ ደጃዝማች ዘገየን ተዋግቶ ድል አድርጎ የማረከዉን ነፍጥ እያስቆጠረ ሲፎክር ደረሱበት ። የንጉሱ ፈረሰኛ በተለቀቀ ጊዜ የአባዋጠዉ አንድ እንኳን ሰዉ ሳያመልጥ ከነ ሙሉ አሽከሮቹ ተያዘ ። ከዚህ በኋላ አባዋጠዉን አስረዉ ነፍጡን ሁሉ ሰብስበዉ በየጁ ደጃች ወሌን የአባቱን አገር ሾመዉ ተመልሰዉ ወረኢሉ ከተማቸዉ ከረሙ ይልና፣

አንድ ዘዴ ካልፈለጉ በስተቀር አባዋጠዉ አላንቀሳቀሳቸዉም ። በዚህ ጊዜ ለመሐመድ ዓሊ /በኋላ ራስ ሚካኤል/ ሹመት አንድ ትልቅ ድግስ እንዲዘጋጅ አዘዉ ነበር ወረኢሊ የከረሙት ። ደጃዝማቹን፣ ፊታዉራሪዉን፣ ቀኛዝማቹን ወዘተ ሁሉንም ደግስ አሉት ። መኳንንቱም እንደታዘዙት በጣም ትልቅ ድግስ አዘጋጁ ።

በስነ ስረዓቱ ቀንም ንጉስ ምኒሊክ ለመኳንንቶቹ እንዲህ አሉ ። የወሎ ሙስሊሞች ዛሬ እስላም ቢሆኑም፣ እስከ አንድ አመት ካልሆነ ደግሞ እስከ ሁለት አመት አብዛኛዎቹ በጥምቀት ቁርባን ወደ ዱሮዉ እምነታቸዉ ተመልሰዉ እምናያቸዉ ናቸዉ ። እግዚአብሔር አሁን የሰጠንን አለም አብረዉን የሚገዙ ኋላም በእሱ ቸርነት አብረዉን መንግስተ ሰማያት የሚገቡ ናቸዉና አትጥሉብኝ ። እናንተ ሰንጋዉን ፊሪዳዉን እያቀረባችሁ ስጧቸዉ፣ እነሱ እያረዱ ይብሉ /በእምነታቸዉ እየባረኩ ይረዱ ለማለት ነዉ/ ። የወሎን ሰዉ በትህትና በፍቅር እየሳብኩ አሁን ለዚህ አለም ግዛት ኋላም በክርስቶስ ቸርነት ለመንግስተ ሰማያት ለሙብቃት ነዉ እንጂ ለመዝረፍና ለማጥፋት አልተነሳሁም ። አሁንም ልጆቼ ወዳጆቼ ከቤታችን እስላም ገባብን ብላችሁ ቅር አይበላችሁ ። ሳሳድጋችሁ ስሾማችሁ አታሳፍሩኝም ። አሁንም ከዋያት እስከ በሽሎ ከአባይ እስከ አዘሎ ያለዉን ግዛት ለልጅ ለወዳጄ ለመሐመድ ዓሊ ሰጥቻለሁ ብለዉ አዋጅ አስነግሩ'' ይላል ።

በዚህ መልኩ አባዋጠውን ተገላገሉ ። ከዚህ በኋላ ከየጁ እስከ መራቢቴ ያሉ ወጣቶችን በመሐመድ አሊ፣ በየጁዉ ወሌ፣ በደጃች ዳርጌ፣ በራስ ጉበና፣

በራስ ወልደ ወዘተ ዙሪያ ግዙፍ ሰራዊት በመገንባት ወሎን በአስተማማኝ ሁኔታ በመያዝ መሰረታቸዉን ማንም ሊነቀንቀዉ በማይችል በልኩ ገነቡ ። አሁን ከማንም የተሻ አስተማማኝ መሰረት ስለያዙ ከወሎ እየወጡ ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ አቅጣጫዎች ለመዝመት ወሰኑ ። /ጎጃምና ጎንደር ግን በአፄ ዮሃንስ ስር ስለነበሩ ሀገር የማስፋት ስራዉ ዉስጥ አልተሳተፉም ። አሮምያ ዉስጥ ግን አንዳንድ ባላባቶች ሀገር የመፍጠር ስራዉ ላይ ተሳትፈዋል፣ በተለይ አባጅፋር ብዙ ሀገር የማስፋት ጦርነቶች ላይ ተሳትፈዋል/ ።

# የኢትዮጵያ አፈጣጠር

(የወሎ የመስፋፋት ሂደት)

## የሸዋና የደቡብ ዘመቻ፡ -

ጸሓፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ቀጥለዉም “ንጉስ ሚኒሊክ የወሎዉን መሰረታቸዉን ካፀኑ በኋላ የመጀመሪያ ዘመቻቸዉን ወደ ደቡብ አደረጉ ። በሸዋ አካባቢ ያሉ የኦሮሞ ባላባቶችን ካስገቡ /ካስገበሩ/ በኋላ በ1867 ዓ.ም የደቡብ ዘመቻቸውን ከሸዋ ኦሮሞዎች ቀጥለዉ በሚገኙት በጉራጌዎች ጀመሩ ። ንጉስ ሚኒሊክ ራስ ጎበናን /የወሎ ባላባት/ በመላክ አንዳንድ የደቡብ ባላባቶች ጋር እየተዋጉ ከጊቤ ወንዝ በስተ ምስራቅ ያለዉን አገር አስገበሩ” ይላል ።

## የኦሮሚያ ዘመቻ፡ -

ጸሓፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ቀጥለዉም “ከአባ ጅፋር ጋር ተላልከዉ አባጅፋርም እንደሚገብሩ ከገለፁ በኋላ፣ ንጉስ ሚኒሊክ ጥቅምት 5ቀን 1869 ዓ.ም አዋጅ ነግረዉ ወደ ኦሮሞ ዘመቱ ። ጥቅምት 20 ቀን ጉመር ሰፈሩ ። ሚኒልክ እነ ራስ ሚካኤልን /የወሎ ባላባት ወረሂመኖ/፣ እነ ራስ መርሶን /የወሎ ባላባት /፣ እነ ራስ ዳርጌን /የወሎ ባላባት ሸዋ/፣ ራስ ጎበናን /የወሎ ባላባት ሸዋ/፣ ራስ ወሌን /የወሎ ባላባት የጁ/፣ ራስ ወልደጊዮርጊስን /የወሎ ባላባት/፣እነ ባሻህ አቡየን /የወሎ ባላባት/ ከነጦራቸዉ እየላኩ ጅማን አልፈዉ

ጌራን፣ከፋን፣ በጊቤ ወንዝና በአዋሽ መካከል ያለዉን አገር ሁሉ ከየግዛቱ ባላባት ጋር እየተዋጉ አስገበሩ ። ወሊሶን፣ አመያን፣ ኖኖን፣ ነቀምትንና የወለጋ አገርን በሙሉ በራስ ጎበና አማካኝነት አቀኑት ። ራስ መርሶ ከፋ ሊሙንና ጃንጃሮን ማስገበር ቻሉ ። አሩሲ ግን ገና ነዉ" ይላል ።

በዚህ ላይ እያሉ ሌላ ችግር አጋጠመ፤ ዋናዉ ንጉሰ ነገስቱ አፄ ዮሃንስ ዝም ብለዉ ማየት አልፈለጉም ። እሳቸዉም እንደ ሚኒሊክ ሹመኞቻቸዉን እየላኩ ለመስፋፋት ፈለጉ ። ነገር ግን ዙሪያቸዉን ሚኒሊክ ስለዘጋባቸዉ ያለቻቸዉ ቀዳዳ አንድት ብቻ ነች ። እሷም በጎጃም በኩል አድርጎ ወደ ከፋ መስፋፋት ። ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ቀጥለዉም "የአፄ ዮሃንስ ሹመኛ የጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖት ያስቸግር ጀመር ። እናም ንጉስ ሚኒሊክ ወደ ጎጃም ለመዝመት ወሰኑ ። የካቲት 2ቀን ተነስተዉ ሲጓዙ ከርመዉ መጋቢት 24ቀን ደጃዝማች መንገሻ /የወሎ ባላባት ሳይንት/፣ ራስ ሚካኤል /የወሎ ባላባት ወረሂመኖ/፣ ደጃች ዳርጌ /የወሎ ባላባት ሸዋ/፣ ደጃች ወልዴ /የወሎ ባላባት/ እነዚህ አራቱ ከነጓዛቸዉ አባይን በእግር በር በኩል ተሻግረዉ ሰፈሩ ። ንጉሱ ግን የቀረዉን ሰራዊት ይዘዉ ወዲህ ማዶ አደሩ ። ጎጃሞች የወሎን ፈረስ እንኳን የአሁኑ አባይ የክረምቱም አባይ አያግደዉም፣ አንችልም ብለዉ መከረዉ፣ የሰፈሩበትን ለቀዉ ሄዱ፤ ይሉና፣

በዚህ ጊዜ የጎጃም አድባራት ይህንን ሲሰሙ በየደብራቸዉ ወረባቸዉን እያዘጋጁ የወሎን ሰራዊት ለመቀበል ተዘጋጅተዉ ነበር ። በነጋዉም ወጥተዉ ፡ -

አዴት መድኃኒአለሞች "አርአየ ስልጣኖ ላዕለ ምድረ ወሎ ወበጌምድር አፄ ሚኒሊክ" አሉ

የመርጡለ ማሪያም ካህናት "በጽፋትም ከመእንተ ሙብረቅ ዘይወፅዕ እምጽባህ ወያስተርኢ እስከ አርብ ከማሁ ምጽአቱ ለሳህለ ማሪያም በንጥረ መባርቅት ምስለ አእላፍ ሠራዊት ወሎ ወበጌምድር" አሉ ።

ደብረ ወርቆች "ፃኡ ተቀበሉ ካህናተ ደብረ ወርቅ መርዓዊ አፄ ሚኒሊክ ዘመጽእ አምሀገረ በእደ ማሪያም ወተወልደ እምቅድስት ሀገረ በእደ ማሪያም" አሉ ... ወዘተ ይሉና፣

የጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖትም ወደ ዳሞት ሸሸ ተብሎ ዳሞት ሲኬድ ደግሞ ወደ ደጋዉ ዘለቀ ተባለ እዚያም ቢኬድ አልተገኘም ፡ እናም የካህናቱ ፀሎት ተሳክቶ አንድም ጥፋት ሳይከሰት የወሎዉ ሰራዊት ወደ ወረኢሉ ተመለሰ ።

ወደ ጎጃም በመዝመታቸዉ ምክንያት በንጉስ ሚኒሊክና በአፄ ዮሃንስ መካከል ያለዉ ፀብ ፀንቶ ነበርና አባ ገብረ ፃድቅና አባ እኑን የሚባሉ መነኮሳት ከአፄ ዮሃንስ ጋር ታረቁልን ብለዉ ወደ ንጉስ ሚኒሊክ መጡ ። ንጉስ ሚኒሊክም እርቅ እምቢ ብየ የሰዉ ልጅ ደም በከንቱ አላፈስም ። አጼ ዮሃንስ ግን እርቅ እምቢ ያሉ እንደሆነ እግዚአብሔር ለተገፋ ይርዳ ብለዉ ሸኟቸዉ ። እነዚያ መልእክተኞችም ህዳር 27ቀን ከአፄ ዮሃንስ ሰፈር ቀበሮ ሜዳ ገብተዉ መልእክታቸዉን ተናገሩ ። አፄ ዮሃንስም እሺ አስታርቁኝ ብለዉ በጅሮንድ ንጉሴን ከነዚያ መልዕክተኞች ጋር ወደ ንጉስ ሚኒሊክ ላኩት ።

ንጉስ ሚኒሊክም ለአፄ ዮሃንስ ደስ የሚል የፍቅር ደብዳቤ ላኩላቸዉ ። ከዚያም በኋላ የአፄ ዮሃንስ ወደ ወሎ መምጣት ተሰማ ። አጼ ዮሃንስም አምባሰል መጥተዉ እንደሰፈሩ ለንጉስ ሚኒልክ፣ እኔ እዚህ መጥቸ የሰፈርኩት ለፍቅር እንጂ ለሌላ አይደለም ። እኔ ለወንድሜ እንኳንስ ይህንን ወሎን አገረዎን ሌላም ብሰጠዎት እወዳለሁ የሚሉ ቃላቶችን የያዘ ደብዳቤ ላኩላቸው ። ንጉስ ሚኒሊክም አሁንም ደስ የሚል የፍቅር ደብዳቤ ፅፈዉ ለአጼ ዮሃንስ ላኩላቸዉ ። ነገር ግን አጼ ዮሃንስ ደብዳቤዉን ሊሰጧቸዉ ሲሉ ተቆጥተዉ መልክተኞቹን ካባረሯቸዉ በኋላ ትንሽ ቆይተዉ፣ ሰዉ ስለበዛብኝ ነዉ የተቆጣሁት ብለዉ ደብዳቤዉን ተቀበሉ ። ከዚህ በኋላ አጼ ዮሃንስ ተጠግተዉ አጤ ዉሀ ላይ ሰፈሩ የሚል ወሬ ለንጉስ ሚኒሊክ ደረሳቸዉ ።

በዚህ ጊዜ ንጉስ ሚኒሊክ ለጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ ። የአጼ ዮሃንስ ጉዳይ አላማራቸዉም ። ወደ ጎጃም መዝመታቸዉ ያበሳጫቸዉ ይመስላል ። ቀጥለዉም አጼ ዮሃንስ ወደራ ላይ ሰፈሩ ። ንጉስ ሚኒሊክም ለጦርነት ተዘጋጅተዉ ወደ አጼ ዮሃንስ ተጠግተዉ ስሪቲ ላይ ሰፈሩ ። ለእርቅ የሚመላለሱት ሰዎች እስኪመጡ ሰራዊቱ ፈንድቶ ወጥቶ ጦርነት እንዳይገጥም እያስከለከሉ ቆዩ ። አጼ ዮሃንስ መጥተዉ ድንባሮ ሜዳ ላይ ሲሰፍሩ የአጼ ዬሃንስ ጦር በሬሳ ወንዝን ተሻግሮ ዘለቀ፤ በዚህን ጊዜ የንጉስ የሚኒሊክ ጦር ጋር አይን ለአይን ሲተያዩ የወሎ ፈረሰኛን የሚያቆም መታገኛ ጠፋ ። ጥቂት ፈረስኛ ወጥቶ ገጠመዉ፣ ብዙ ሰዉ ካለቀ በኋላ የአጼ ዮሃንስ ጦር ተመልሶ

ወደ ሰፈሩ ገባ ። በዚች ቅጽበት ባሻ አቦዬም ገድለዉ ሲናድር ማርከዉ ለንጉስ ሚኒሊክ አስገቡ ። የቀኝ አዝማች ዉቤ አሽከር ማናዬም የደጃች ገብረ ስላሴን ልጅ አምኃን ማርኮ አመጣዉ ። ሌሎች የንጉስ ሚኒሊክ አሽከሮችም ብዙ ግዳይ ጣሉ ። ከዚህ በኋላ የአጼ ዮሃንስ ሰፈር ተደናገጠ ። የወሎዉ ጦር ግዳይ እንጂ ምርኮ አያዉቅም የሚል ወሬ /ወፋ ዉጊያ/ ይወራ ስለነበር የደጃዝማቹ ልጅ አመኃ በመማረኩ ይገድሉታል ብለዉ ተጨነቁ ።

ከዚህ በኋላ እርቅ ተጀመረ ። እርቁም ንጉስ ሚኒሊክ ከአጼ ዮሃንስ ግዛት እንዳይገቡ/ ጎጃም ገብተዉ ስለነበር ነዉ/ ። አጼ ዮሃንስ ጠላት በተነሳባቸዉ ጊዜም ጦር በአበጋዝ ልከዉ እንዲረዱ በሚል እርቁ ተጨርሶ መሀላና ግዝት ተፈጽሞ ተጠናቀቀ” ይላል ።

የአፍሪካ ትልቁ የሐይማኖት ጉባኤ /ወሎ ቦሩ ሜዳ/

ጸሓፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ቀጥለዉም “ከላይ የተገለጸዉ እርቅ በተካሄደ በ3ኛዉ ቀን ሁለቱም ነገስታት ተማክረዉ የሀይማኖት ጉዳይ ተነሳ ። 3 ልደት ክርስቶስን የጺጋ ልጅ የሚሉ የደብረ ሊባኖስ ሰባኪዎች ተገኝተዉ ታሰሩ ። ቀጥሎም ከአንድ አባት ከቅዱስ ማርቆስ ከአንዲት እናት ከእስክንድሪያ ሐይማኖት አልሆንም የምትሉ ሰዎች ከክርስቲያኑ ተለዩና መጻሀፍ አለኝ ልከራከር የምትሉ ከሆነም ጉባኤ እንሰጣችኋለን ብለዉ አዋጅ አስነገሩ ። ጉባኤዉም በግንቦት 18 ቀን እንዲሆን ቀጠሮ ተያዘ ።

ንጉስ ሚኒሊክም በምገዛዉ አገር የምትኖር ካህን ሁሉ ወሎ አፄ ዮሃንስ ካሉበት አደባባይ ለርክበ ካህናት ያልተገኘህ እንደሆነ፣ ሹመት ያለህ በሹመትህ፣ ሹመት የሌለህ በመሬትህ እቀጣሀለሁ ብለዉ አዋጅ አስነገሩ ። ከዚያም በተባለዉ ቀን ሰራዊቱና ህዝቡ ጠቅሎ ሲገባ ሁለቱም ነገስታት በየዙፋናቸዉ ተቀመጡ ። መኳንንቱም ሊቃዉንቱም በየማዕረጋቸዉ ሆነዉ ሰራዊቱ ተሰልፎ በቀኝ በግራ ቆመ ። በዚህ ጊዜ ግርማ መንግስት ሆነ ።

ከዚህ በኋላ አጼ ዮሃንስ እንዲህ አሉ ። ዘእንበለ ስጋ ይትቀዉም ነፍስ ይላልና እስከ አሁን በሁለታችን ፍቅር የመንግስታችን ነገር ይቅደም ብለን ሰነበትን ። ከእንግዲህ ግን የምንፈልገዉ የምንይዘዉ የሐይማኖትን ነገር ነዉ ። አሚንሰ መሰረት ይእቲ እንዳለዉ የቀረዉ ነገር ሀላፊ ጠፊ ነዉ ብለዉ ከተናገሩ በኋላ “ክርስቶስ የጺጋ ልጅ ነዉ” ወደ ሚሉት ፊታቸዉን መልሰዉ እንግዲህ ተከራከሩ አሏቸዉ ። የጺጋ ልጆችም ወንድሞቻችን ይምጡልን

ይጨመሩልን አሉ ። አጼ ዮሃንስም ብቻችን ብለዉ ሰበብ እንዳያደርጉ ይምጡላቸዉ ብለዉ ስለፈረዱ የታሰሩት እነዋልድቤ እንግዳ፣ ዙር አምቤ እንግዳ፣ ተክለ አልፋና ተከታዮቻቸዉ ተፈተዉ መጡ ። ከመጡም በኋላ የጸጋ ልጆች በግራ ሲቆሙ፤ ሁለት ልደት ክርስቶስ የባህሪ ልጅ በሰዉነቱ አምላክ የሚሉ እነ ሊቀ ካህን ኪዳነ ወልድ፣ መምህር ግርማ ስላሴ፣ መምህር አካለወልድና ሌሎችም ሊቃዉንትና ደቀመዛሙርት ሆነው በቀኝ ቆሙ ።

ይህን ጊዜ አጼ ዮሃንስ የጸጋ ልጆችን ሀገራችሁ ወዴት ነዉ? አስተማሪያችሁስ ማን ነዉ? አሏቸዉ ። እነዚያም ከላይ አባታችን ክርስቶስ ከታች አባታችን ማርቆስ እናታችን እስክንድሪያ ናት አሉ ። አጼ ዮሃንስም በእስክንድሪያ በመንበረ ማርቆስ የተቀመጠዉ ሊቀ ጳጳስ የሚያስተምረዉን ባለ መሀተም ደብዳቤ ልኮልናል ትቀበሉታላችሁን? አሏቸዉ ፡ እነዚያም መከረዉ እንቀበለዋለን አሉ ።

በዚያም ጊዜ የሐይማኖት ደብዳቤዉን አስመጥተዉ፣ የመጣልን በአረቢ ተጽፎ ነዉ፤ እኔ ግን በአማርኛ አስገልብጬ አኑሬለሁ ። አሁን ግን እናንተ ደስ እንዲላችሁ የአረብ ቋንቋ ከእናንተ የሚያዉቅ ካለ አምጡና ይነብብላችሁ አሏቸዉ ። እነዚያም የአማርኛዉን እንስማዉ አሉ ። በዚህ ጊዜ በአማርኛ የተፃፈዉን ደብዳቤ መምህር ግርማ ስላሴ አነበቡላቸዉ፤ ቃሉም ይህ ነዉ ፡ -

የተላከ ከአባ ቄርሎስ ዘነበረ በመንበረ ምርቆስ ይድረስ ለልጅ ለወዳጄ ለስዩመ እግዚአብሔር ዮሃንስ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያ ላሉ ምዕመናን ሁሉ ። ልጆቼ ወዳጆቼ ከእኔ በፊት በነበሩት አባቶቻችን ሐይማኖትና ምግባር፣ ለጸና ሰዉ ሁሉ ፀጋ እግዚአብሔር ይደርበት፣አምላከ ማርቆስ ይጠብቀዉ ።

ቀዳማዊ ልደት ከአብ፣ ደህራዊ ልደት ከድንግል ማሪያም፣ ስለኛ ሲል እንበለ አባት እንደ ተወለደ የማያምን፣ በሁለት ልደት በተዋህዶ ከበረ፣ ወልድ በተለየ አካሉ ቅብዕ ነዉ፣ በሰዉነቱ የባህሪ አምላክ በሰዉነቱ እንደ አብ እንደ መንፈስ ቅዱስ ያዉቃል፣ማወቂያም ነዉ፣ የማይልና ሶስት ልደት የጸጋ ልጅ በቅብአት የባህሪ ልጅ የሚል ሁሉ የአርዮስ የንስጥሮስ የይሁዳ መርገም ይድረስበት፣ ከምእመናን የተለየ ይሁን ተብሎ ግዝት ያለበት ቃል ነበር ። የጸጋ ልጆችም እንዲህ አሉ፤ ትግሮች ጳጳስ ሲያመጡ ከመንገድ አቆይተዉ የሰዉነት ባህሪ አምላክ ያሰኟቸዋል እንጂ ጳጳሳቱ እንዲህ አይሉም አሉ ።

በዚህን ጊዜ ንጉሱ ጋር ክርክር ሲጀመር እጨጌ ቴዎፍሎስ ወንበራቸዉን አስወርደዉ ሊቀ ካህናት ኪዳነ ወልድ አጠገብ ከቆሙት ከሊቃዉንት ወገን ተቀምጠዉ፣ ባላጋራችሁ እኔ ነኝ እኔ ጋር ተከራከሩ አሏቸዉ ። ሁለቱ ነገስታት ዳኞች ሆነዉ እጨጌው ጥያቄ ጀመሩ ። ከእጨጌዉም በኋላ አለቃ ኪዳነ ወልድና አለቃ ተክለ ስላሴ ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቁ ። ጥያቄቸዉ ስልቱ ልዩ ልዩ ነዉ ሚስጥሩም ብዙ ስለሆነ ሊፃፍ አይችልም ።

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ነገስታት መኳንንቱም የጸጋ ልጆችን ከአራቱ ጉባያተ መጻህፍት በፊደል አህዝ ሶስት ልደት የሚል ታገኙ እንደሆነ አምጡ አሏቸዉ ። በዚህ ጊዜ የጸጋ ልጆች እኛ ፈንታችንን /ተራችንን/ እንጠይቅ ቢሉ መልአከ ብርሃን በዚሁ በአመንከዉ ቃል ተረታ እንጂ እንግዲህ ምን ጥያቄ አለህ ሲሉ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ተነስተዉ ባገራችን አንዱ ጠይቆ ሌላዉ ሳይጠይቅ አንፈርድም ጃንሆይ ግን እንዳወቁ ብለው ተቀመጡ ። ነገስታቱም ፈንታችሁን ጠይቁ ብለዉ ፈቀዱላቸዉ ።

ከዚህ በኋላ ከጸጋ ልጆች አንዱ ደብተራ፣ እግዚአብሔር አዳምን በነፍስ ህያዉ አድርጎ ሲፈጥረዉ መንፈስ ቅዱስ አክብሮት የጸጋ ልጅ አድርጎ አኖረዉ ብሎ ሲጠይቅ መልአከ ብርሃን አዎ ብሎ መለሰ ። ቀጥሎም ስርዓቱን ቢያፈርስ ነዉ ልጅነቱ የሄደበት ቢለዉ አዎን ብሎ መለሰ ፡ ቀጥሎም ስርአቱን ጠብቆ ቢኖር በኩራችን ይሆን ነበር ቢለዉ ይሆን ነበር ብሎ መለሰ ። የሚሉት ጥያቆዎች በሁለቱ ነገስታት ፊት አልተጠየቁምን አለዉ ።

በዚህ ጊዜ በጸጋ ልጆች የአደባባዩ ሰዉ ሁሉ ሳቀባቸዉ ። የጸጋ ልጆችም በ2 ልደት ሐይማኖት እንገባለን አሉ ። ከዚህ በኋላ 2ልደት ተዋህዶ ከበረች ።

ይህ ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ የጸጋ ልጆች ተነስተዉ እንግዲህ በሐይማኖት አንድ ከሆን የልባችን እንናገር አሉ ። አጼ ዮሃንስም ነገራችሁ ምንድን ነዉ አሏቸዉ ። አድባራቱን ወለወልዳ እንበል ወይስ ዘምሰል ወልዳ አሉ ። ሁለቱም ነገስታት አንድነት ወለወልዳ ይባል እንጂ ዘምሰል ወልዳ ከተባለማ መልሶ የጸጋ ልጆች ሆነ አይደለምን አሉ ።

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ነገስታት እስላሙን ሰብስበዉ እንዲህ አሉ ። እግዚአብሔር በቸርነቱ ሁለታችንን በፍቅር አንድ ካደረገን ህዋርያህ እኛ ነን ። ቀድሞ በግራኝ ጊዜ በጭንቅ ሐይማኖት ጠፋ እንጂ የክርስቲያን ሀገር መሆኑን ታዉቃላችሁ ። አሁንም እስላምም ኦሮሞም በክርስቶስ ስም እመን ተጠመቅ፤

ክርስቲያን ሆነህ ምግባር ብትሰራ ይህን አለም ትገዛለህ፣ ኋላም መንግስተ ሰማያትን ትወርሳለህ ብለዉ አዋጅ ነገሩ ።

በመነጋዉ አጼ ዮሃንስ ይማሙ መሐመድ ዓሊን ክርስትና አንስተዉ ስማቸዉም ሚካኤል ተባለ ። ንጉስ ሚኒሊክ ደግሞ ይማሙ አባዋጠዉን ክርስትና አንስተዉ ስማቸዉም ኃይለማሪያም ተባለ ። ንጉስ ሚኒሊክም እንዲህ አሉ ። በጥምቀት ቁርባን እኔ ጋር አንድ የምትሆኑ ሁሉ ለዚህ አለም ግዛት ኋላም ለመንግስተ ሰማያት በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ ቸርነት እንበቃለን ብለዉ ክርስቲያን ለመሆን እንዲጥሩ ብዙ መንፈሳዊ ቃላትን ከተናገሩ በኋላ ህዝቡን አሰናበቱ" ይላል ።

ይህ የሐይማኖት ጉባኤ ከህዝብ ብዛት አንፃር በአፍሪካ ትልቁ የሐይማኖት ጉባኤ ነዉ /የሁለቱም ነገስታት ሙሉ ሰራዊትና የወሎ ህዝብ ታድሞበታል/ ። ይህ ጉባኤ ቅብአቶችን ሙሉ በሙሉ ወደ ኦርቶዶክስ ከመቀየሩም በተጨማሪ በርካታ ሙስሊሞችን ወደ ክርስትና እንዲቀየሩ አድርጓ ።

## <u>የአሩሲ ዘመቻ፡-</u>

ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ቀጥለዉም "ከዚህ በኋላ ንጉስ ሚኒሊክ ከተማ ጠባቂ አጎታቸዉን ራስ ዳርጌን /የወሎ ባላባት ሸዋ/ ትተዉ፤ የራስ ሚካኤልን /የወሎ ባላባት ወረሂመኖ/ ጦር ይዘዉ ከቤት አሽከሮቻቸዉ ጋር ደምበል ዘምተዉ የዟይን ባህሩን ዳር ሁሉ መቱት ። ቀጥለዉም ወደ አሩሲ ዘመቱ ።

በአሩሲዉ ጦርነት ብዙ ሰዉ ያለቀ ሲሆን ከንጉሱም አሽከሮች የአቶ አንዳርጋቸዉ ልጅ ከምሲ፣ የግራዝማች ባቡ ልጅ ጠንፋ፣ ጋሻ ጃግሬዉ ወንድማገኘሁ ሞቱ ። ንጉሱም ድል አድርጌለሁ ብለዉ ቀዲዳ ላይ ሰፍረዉ ወደ ሸዋ ለመመለስ እየተዘጋጁ እያለ፣ የአሩሲ ዲና እንደገና አስከትቶ እጅግ ብዙ ሆኖ በ3 ወገን መጣ ። ንጉሱም ጥቂት ሆነዉ ዘምተዉ ነበርና ያለዉን ጦር አሰልፈዉ ተቀመጡ ። በግምባርና በግራ የመጣዉ የአሩሲ ጦር ነገ ነዉ የምንዋጋዉ ብሎ ተመለሰ ። በቀኝ በኩል የመጣዉ ግን እየጨፈረ እልል እያለ ሲጠጋ ንጉሱም ፈረሰኛዉን ከፊት እግረኛዉን ከኋላ አድርገዉ በለዉ ብለዉ በለቀቁት ጊዜ የአሩሲዉ ጦር ተበተነ ። ጭላሎ እጨቆዉ ድረስ ተከታትለዉ

አባረሯቸው ። ነገር ግን የአሩሲ ዲና እንደገና ተጠናክሮ ገፍቶ መጣ ። በግራም በቀኝም መጥቶ እየተዋጋ እያለ መሪያቸዉ ፈረስ ላይ እያለ በጥይት ተመትቶ በወደቀ ጊዜ ሌላዉም ጠቅሎ ሸሸ ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሌላ ችግር ተፈጠረ አፄ ዮሃንስ እንደገና ጎጃሜዎችን ተጠቅመዉ ለመስፋፋት ሞከሩ ። ንጉስ ሚኒሊክ እዚህ ጦርነት ላይ እያሉ ከከፋዉ ገዥ ራስ ጎበና ደብዳቤ መጣላቸዉ ። ደብዳቤዉም እንዲህ ይላል ፡ - ራስ ደርሶ የጎጃምን ጦር እየመራ አባይን ተሻግሮ ጉማ ላይ ተገናኘን ። ጦርነት ገጥመን የዘረፉትንና ያስገበሩትን ገንዘብ ሁሉ ተቀበልናቸዉ ። ከእንግዲህ ንጉስ ሚኒሊክ ከፈቀዱላችሁ አገር እንዳታልፉ ብለን አምለን አስገዝተን ተራርቀን ወደ ሀገራቸዉ ተመለሱ” ይላል ።

ይህ በወሎዉ አዝማች ራስ ጎበናና በጎጃሙ አዝማች ራስ ደርሶ መካከል የተካሄደዉ ጦርነት ቀላል ጦርነት አልነበረም ። ባህሩ ዘዉዴ “የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1983” በሚለዉ መፅሀፋቸዉ ዉስጥ “የወሎ ጦረኞች አዝማች ራስ ጎበናና የጎጃሙ ጦር አዝማች ራስ ደርሶ በጥር 1874 ዓ.ም ሊሙ በተባለዉ ቦታ ላይ ጉልበት ተፈታተሹ ። ሆኖም የጎጃሙ የራስ ደርሶ ጦር በግብርም በዘረፋም የሰበሰበዉን የዝሆን ጥርስ ጥሎ ለመሸሽ ተገደደ ። በዚህም ምክንያት እንዲህ ሲባል ተተረተ፤

እንግዲህ ጎጃሞች በምን ይስቃሉ፣

ጥርሳቸዉን ሊሙ ትተዉት ሄዱ አሉ”

ይላል ።

ይቺ የህዝብ ግጥም፣ ጦርነቱ ከባድ እንደነበረና ጦርነቱ በጥይት እንዳልነበር ታመለክታለች /የወፋ ዉጊያ ዓይነት እንደ ነበር ታመለክታለች/ ። ይህ የአጼ ዮሃንስ የመስፋፋት ሙከራ በዚህ መልኩ ከከሸፈ በኋላ ሌላ እጅግ ዘግናኝ ጦርነት ተከትሏል ።

ወደ ጸሓፊ ትእዛዝ ፅሁፍ እንመለስ “ከዚህ በኋላ ጎጃሞች በሀላቸዉንና ግዝታቸዉን /ሊሙ ላይ ደጃች ጎበና ያስማላቸዉን/ አፍርሰዉ ዋናዉን አለቃቸዉን ንጉስ ተክለሐይማኖትን ይምጡልን ብለዉ ልከዉ ራስ ጎበናን ለመዉጋት እንደገና ወደ ከፋ ጉዞ ጀመሩ ። ራስ ጎበናም ጎጃሞች እንደገና ከዋናዉ አለቃቸዉ ጋር እየመጡ መሆኑን ለንጉስ ሚኒሊክ ላከ” ይሉና፣

‘‘ንጉስ ሚኒሊክም ይህ መልዕክት በደረሳቸው ጊዜ ክተት ሰራዊት ምታ ነጋሪት ብለዉ ከእንጦጦ ከተማቸዉ ተነስተዉ ጉዞ ጀመሩ ። ንጉስ ሚኒሊክ ከራስ ጎበና ጋር ኖኖ ላይ ተገናኝተዉ ሰፈሩ ። በዚህ ጊዜ የወረኢሉዉ ጦር እነ ወ/ሮ መስታወት /ያባዋጠዉ እናት/ ወደ ኋላ ቀርተዉ ነበርና ከንጉሱ ሰፈር ደረሱ ። ቀጥለውም ደጋዉን ተጉዘዉ ደዴሳን ተሻግረዉ የንጉስ ሚኒሊክን ድኳን ሴሴ ወንዝ ዳር ተክለዉ መንገድ ማስጠረግ ጀመሩ ። ጎጃሞች የንጉሱን ድኳንና የመንገዱን መጠረግ ባዩ ጊዜ በጎጃሞች ሰፈር ብርቱ ፍርሃትና ጭንቅ ተፈጠረ ።

በዚህን ጊዜ ፊታዉራሪ ይመር የሚባል ከጎጃሞች ተልኮ ወደ ንጉሱ ድኳን ገባ ። ንጉስ ሚኒሊክም ፊታዉራሪ ይመርን እንዲህ አሉት ። ከአባይ ወዲህ ምን ግዛት አላችሁ እኔ በፍቅር ስለወዳጅነት ብየ አሞሩን፣ ሆሮን፣ ጉድሩን፣ ግንደበረትን፣ የቀዲዳን ሀገር ለንጉስ ተክለሐይማኖት ብሰጠዉ እያለፋችሁ ሌላዉን ሀገር ትወጉ ጀመር ። ተጠማኝ ሲሰነብት ባለርስት ይሆናል የሚሉት በእናንተ ደረሰ ። አሁንም የሰጠሁትን ሀገሬን ወስጃለሁ፤ እናንተም አባይን ተሻግራችሁ ወደ ጌታችሁ ሂዱ ። ጌታችሁ ግን አገሩን ከወሰዱብኝ እዋጋለሁ ብሎ የመጣ እንደሆነ እናንተም አብራችሁ ትመጣላችሁ ብለዉ ሸኒ ሰጧቸዉ ። ወዳዉም አባይን ተሻግረዉ ሄዱ ።

ከዚህም ቀጥለዉ ንጉስ ሚኒሊክ ሹምሽር ለማድረግ ወደ ሆሮ ተጓዙ /አሞሩን፣ ሆሮን፣ ጉድሩን፣ ግንደበረትን፣ የቀዲዳን ሀገር ለንጉስ ተክለሐይማኖት ፍቅር በነበሩበት ጊዜ ሰጥተውት ነበርና አሁን ግን ስለቀሙት ሹም ሽር ለማድረግ ወደዚያው ተጓዙ/ ። ንጉስ ሚኒሊክ የሆሮ አካባቢን ሹም ሽር ጨርሰዉ ወደ እንጦጦ ለመመለስ ሆሮ ጃሬ ላይ ሰፍረዉ እያለ የጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖት መልእክተኞች መጡ ። ወደ ንጉሱ በቀረቡም ጊዜ ደብዳቤዉን ስጡኝ ቢሏቸዉ ደብዳቤስ አልያዝንም በቃል ነዉ የተላክነዉ አሉ ። የቃል መልእክቱን ንገሩኝ ቢሏቸዉ መኳንንቱ

ካልተሰበሰቡ አንነግርም አሉ ። በዚህ ጊዜ መጋቢያ አድርገዉ መኳንንቱም ሊቃዉንቱም ተሰበሰቡ ። ከዚህ በኋላ መልእክታቸዉን እንዲህ ብለዉ ተናገሩ ።

የንጉስ ተክለሐይማኖት ቃል ይህ ነዉ ፡ - ምነዉ እኔን እርስዎ ሁልጊዜ ያዋርዱኛል ። ከዚህ ቀደም አገሬን ጎጃምን አጠፉት ። እንግዲህስ አይሂዱ መጣሁ ። የጠራ ሜዳ ይዘዉ ይቆዩኝ ። ደብዳቤ አለመላኬ ብቻዎን አይተዉ

ቀደዉ ጥለዉ እንዳልሰማ ሆነዉ ይሸሻሉ፤ በቃል የሆነ እንደሆነ ግን መኳንንትዎ፣ ሰራዊተዎ፣ አሽከሮቸዎ ሰምተዉ ቢሸሹ ይንቁዎታል አሉ ብለዉ ተናገሩ ።

ንጉስ ሚኒሊክም ሐሰተኞች ናችሁ ንጉስ ተክለሐይማኖት ይህን አይልም ። መኅተም ያለዉ ደብዳቤ ይልክ ነበር አሏቸዉ ። መልእክተኞቹ ግን የጌታችንን ቃል ነዉ የተናገርነዉ አሉ ። ንጉስ ሚኒሊክም እንደዚህስ ከሆነ ከእናንተ አንዱ ከእኔ ጋር ይቆይ፣ ሌላው አንዱ ይሂድና እዉነት መሆኑን የሚያስረዳ ማህተም ያለዉ ደብዳቤ ይዞ እስከ 5ቀን ድረስ ይምጣ፣ ሳይመጣ የቀረ እንደሆነ ግን እኔ ዘንድ ያለዉን እቀጣዋለሁ አሏቸዉ ። መልክተኞቹም እሺ አሉ ። የዚህ ጊዜ ንጉስ ሚኒሊክ ምላሹን እንዲህ ሲሉ ላኩ ። ያንተንስ ጦርነት ሰግቼ አልሄድም ። ነገር ግን ለመዋጋት ከአጼ ዮሃንስ ፈቃድ አግኝተህልን፣ ተዋጋ ብለዉህ እንደሆነ ባለማኅተም ደብዳቤህን ላክብኝ፤ ለጦርነቱስ አንተንም መንገድ አላስመታ እዚያዉ እደጅህ እንመጣልሀለን ብለህ ንገረዉ ብለዉ አንዱን መልከተኛ ላኩት ። አንዱ በዘበኞች እጅ ተቀመጠ ።

ይህ ከተፈፀመ በኋላ ንጉስ ሚኒሊክ ተነስተዉ ወደ ጉድሩ ተጓዙ ። በቀጣዩም ቀን ተነስተዉ ተጉዘዉ ወምበር እምባቦ ሜዳ ላይ ሲደርሱ የጎጃሞች ሰልፍ ፊት ለፊት ታየ ። እዚያዉ የንጉሱ ድኳን ተተክሎ ለጦርነት ዝግጅት አደረጉ ።

ከቀኑ 5አዓት ላይ የጎጃሞች መድፍ መተኮስ ጀመረ ። የወሎ ጦረኞች ሄደዉ ጦርነት ገጠሙት ። ንጉስ ሚኒሊክም አሽከሮቻቸዉን ይዘዉ መሀል ለመሀል ገቡ ። በዚህ ጊዜ የጎጃሙም ንጉስ ተክለሐይማኖት መድፍ መተኮስ ጀመረ ። ሁለት ጊዜ ተኮሰ በሶስተኛዉ መንኮራኩሩ ተመትቶ ተሰብሮ ወደቀ ። ጎጃሞችም የጦርነቱን ሁኔታ ባዩ ጊዜ ደነገጡ ። የወሎዉ ጦር ተጠግቶ ከቦ አስጨንቆ 2ሰዓት ሳይሞላ ንጉስ ተክለሐይማኖትን አቁስለዉ ማርከዉ ይዘዋቸዉ መጡ ። ጦርነቱ ግን እስከ 3ሰዓት ድረስ ቆየ ። የወሎው ጦር ከቦታልና የጎጃሙ ጦር ለመሸሽም ለመማረክም የማይቻለዉ ሆነ ። እጅግ ብዙ ሰዉ ካለቀ በኋላ ጎጃሞች ሙሉ በሙሉ እጅ ሰጥተዉ ጦርነቱ ተጠናቀቀ /የወሎን ስም የማጥፋት ዘመቻ መነሻው ይህ ጦርነት ነው/ ።

በዚህን ጊዜ ንጉስ ሚኒሊክ ኢትማዖ ለእኩይ በእኩይ ግሙራ የሚለዉን ቃል አስበዉ የተዋጉበት ስፍራ ድረስ ሄደዉ የጎጃሞችን ነፍሱ ያልወጣችውን

ቁስለኛ /ሬሳ ነው እየተባለ የተተወ ነፍሱ ያልወጣችውን ቁስለኛ/ እየመረጡ ብዙ ቁስለኛ አስነሱ ይልና፣

ቁስለኞችን ካስነሱ በኋላ ወደ ምርኮኛዉ ሄደዉ፣ እኔ አልመጣሁባችሁ እናንተ ፈልጋችሁ መጣችሁ እንጂ እግዚአብሔር ደግሞ በትቢዕታችሁ ጣላችሁ ። በሉ አሁን ወደ አገራችሁ ግቡ ብለዉ አሰናብተዉ አስለቀቋቸዉ ። ንጉስ ሚኒሊክ የሞተዉን እያስቀበሩ፣ ለቁስለኛዉም መድኃኒት እያስደረጉ እረፍት አድርገዉ ዋሉ ።

በነጋዉ ራስ ጎበና በንጉሱ ትእዛዝ የጎጃሙን ምርኮኛ አባይ ድረስ ሸኝቶ ተመለሰ ። የሚወስደዉ ዘመድ ያጣዉን የጎጃሞችን ቁስለኛ ሁሉ በዘበኛ ላይ ተመርቶ አድሮ ነበርና ጅማ ለፊታዉራሪ ቀዲዳ አገር አድን ብለዉ ሰጡት ።

ከዚህ በኋላ የተማረከዉን ነፍጡን ሰብስበዉ በአይነት በአይነቱ ለዩት ። መድፉን ባንድ ወገን፣ መርቡጡን ባንድ ወገን፣ ሲናዲሩን ባንድ ወገን፣ ባለከምሱሩን ባንድ ወገን፣ ባለቋዱን ባንድ ወገን፣ ባደረጉት ጊዜ መጠን የሌለዉ ሆነ /አፄ ዮሃንስ ዋግሹም ጎበዜን ለመምታት ብለዉ ከእንግሊዞች የሰበሰቡት መሳሪያ ነዉ/ ። መድፉንና መርቡጡን ፊታዉራሪ ቀዲዳን /የጅማ ባላባት/ ውሰድ ብለዉ ሰጡት ። ሌላዉን መሳሪያ አስጭነዉ ምርኮኛውን ንጉስ ተክለሐይማኖትንም በአልጋ አስይዘዉ ወደ እንጦጦ ጉዞ ጀመሩ ። ሰኔ 19 ቀንም እንጦጦ ከተማ ገቡ’’ ይላል ።

ይህን ጦርነት የአጼ ዮሃንስና የንጉስ ሚኒሊክ ጦርነት አድርጎ መዉሰድ ይቻላል ። ይህ ጦርነት ንጉስ ሚኒሊክ የዘመናዊ የጦር መሳሪያ አቅማቸዉን በእጅጉ ያሳደጉበት ነበር ። ከማጓጓዝ አቅማቸዉም በላይ የሆነ መጠን የሌለዉ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ በምርኮ መገኘቱ፣ የንጉስ ሚኒሊክን አይደፈሬነትም በብዙ እጥፍ አሳደገው ። በባዶ እጃቸዉ ድል ሆነዉ የማያዉቁ ሰዉዬ ይህን መሳሪያ አግኝተዉ በኢትዮጵያ ምድር ማንም ደፍሮ ሊሞክራቸዉ አይችልም ። እናም አጼ ዮሃንስም እጅ ሰጡ የመስፋፋቱን ጉዳይ እርግፍ አድርገው ተውት /ወፋ/ ።

ጸሓፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ቀጥለዉም “ከዚህ በኋላ ንጉስ ሚኒሊክ ለአጼ ዮሃንስ መሸሻ ወርቄንና ሻፕዉ ተፈሪን ላኩ ። አፄ ዮሃንስ ግን የጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖት ድል ሆነዉ መማረካቸዉን ሲሰሙ፣ ይህ ሰዉዬ ዘዉድ መግፈፍ ለመደ፣ እንግዲህስ እኔንም ይደግመኛል፣ ቁስለኛዉ ንጉስ

ተክለሐይማኖት ሳይድን ልሂድበት ብለዉ፤ በሐምሌ ከጎንደር ደብረ ታቦር ተነስተዉ ሰራዊታቸዉ በበረዶና በዉሀ ሙላት እያለቀ ወደ ወሎ መጡ ።

ንጉስ ሚኒሊክም የአጼ ዮሃንስን መምጣት በሰሙ ጊዜ በጣም ተደንቀዉ በብዙ ትእግስት የመልክተኞቹን ምላሽ ሲጠባበቁ፣ መልክተኞቹ ከአጼ ዮሃንስ ደብዳቤ ይዘዉ መጡ ። ቃሉም ይህ ነዉ ፡ - በጌምድር ላይ ሳለሁ ሁለቱ ነገስታት ተዋግተዉ ድል ለንጉስ ሚኒሊክ ሆነ ንጉስ ተክለሐይማኖትን ይዘዉ ወደ ሸዋ ተጓዙ ሲሉ ብሰማ እግዚአብሔር የፈቀደዉን ሰርቷል ብየ የናንተን ደብዳቤ ስጠብቅ ደብረታቦር ላይ ወር ሙሉ ተቀመጥኩ ። ኋላ ግን ወሬችሁ ቢጠፋብኝ ይህስ ነገር አለበት ብየ ተነስቼ ስመጣ ሳይንትን ሳልፍ የእርስዎ ወረቀት ደረሰኝ ። ደብዳቤዉንም አይቸ መዘግየቱ በመንገዱ እርዝመት ሆኖ ተንኮል አለመኖሩን ባዉቅ ወደ በጌምድር ለመመለስ አሰብሁ ። ነገር ግን ክረምቱ ተጭኗልና ሰራዊቴ የሚጎዳብኝ ሆነ ። በወሎ እንድከርም ፈቃድ ይደረግልኝ እኔም አገር አልበድልም ። በዚያዉም ተገናኝተን ሁሉንም ተማክረን ወደ በጌምድር መመለስ ይሻለኛል ብየ ነዉ እንጂ ሌላ ነገር አስቤ አይደለም ። ደግሞ ይህ የሚያሳዝን ነገር ከሆነ ተመልሼ ሰራዊቱ በዉሀ ሙላትና በጭቃ ያለቀዉ አልቆ የተረፈዉን ይዤ መመለስ ይሻለኛል ብለዉ ላኩ" ይላል ።

/አጼ ዮሃንስ በጣም ጀግና ሰዉ ናቸዉ፤ እድሜ ልካቸዉን ከዉጭ ሀይሎች ጋር እንደተፋለሙ ነዉ የኖሩት፤ የሞቱትም ከዉጮች ጋር እየታገሉ ነዉ ። ከዉጮች ጋር በጦርነት ጉዳይ አይደራደሩም ። ለሀገር ዉስጥ ጦርነት ግን አይቸኩሉም ። ከዚህ አንጻር ንጉስ ሚኒሊክም እጅግ ያከብሯቸዋል ይወዷቸዋል ።

ሆኖም ግን አጼ ዮሃንስ ሁለት ንጉስ በአንድ ቤተመንግስት መሆኑ የተመቻቸዉ አይመስልም ። የሚኒሊክ ሀይል ከእሳቸዉ ሀይል በመብለጡና ሹመኞቻቸዉ ወዴየትም እንዳይስፋፉ አድርጎ የእሳቸዉ ግዛት በትግራይ፣ በጎጃምና በጎንደር ብቻ እንዲወሰን ስላደረጋቸዉ፣ ንጉስ ተክለሐይማኖትን በማፈርጠም የንጉስ ሚኒሊክ ጥሩ ባላንጣ እንዲሆንላቸዉ ጥረት አድርገዉ ነበር ። ነገር ግን ጥረታቸዉ ሁሉ ከሽፎ አሁን ጭራሽ ንጉስ ሚኒሊክ ንጉስ ተክለሐይማኖትን በመደምሰስ በምርኮ የዘመናዊ የጦር መሳሪያ ጥማታቸዉን ቆርጠዉ/ ረክተዉ/፤ በቂ የዘመናዊ መሳሪያ ባለቤት ለመሆን በቅተዋል/ ።

ጸሓፊ ትእዛዝ ቀጥለዉም “ንጉስ ሚኒሊክ ደብዳቤዉን አይተዉ እንዲህ ብለዉ ፃፉ ። እዚህ ከቀረቡ ሳንገናኝ አንከርምም፤ እኔም መጣሁ ። ከድኳን ቤት ይሻላልና ወረኢሉ ከእኔ ቤት ይግቡ ። ብለዉ ልከዉ ሐምሌ 12 ቀን ከእንጦጦ ተነስተዉ ምርኮኛዉን የጎጃሙን ንጉስ ተክለሐይማኖትን ይዘዉ ተጉዘዉ ነሀሴ 7ቀን ወረኢሉ ከአጼ ዮሃንስ ጋር ተገናኙ ።

ከዚህ በኋላ በፍቅር ሰንብተዉ፤ ከእለታት አንድ ቀን ራስ አሉላ፣ ራስ ገብረ ኪዳን፣ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ከአጼ ዮሃንስ ተልከዉ ወደ ንጉስ ሚኒሊክ ድኳን ገቡ ። ቀድሞዉን መሀላና ግዝት አፍርሰዉ ወደ ወሎ ስለመጡ በነገሩ አዝነዉበት ነበርና ስለዚህ ልጅዎን ወ/ሮ ዘዉዲቱን ለልጄ ለራስ አርአያ ይስጡልኝ ብለዉ ላኩ ።

ንጉስ ሚኒሊክም ልጅቱ የ6 አመት ህፃን ናት ። አልደረሰችም እንጂ ምን ከፋኝ ግቢዉ ግን ያማረ ነዉ ብለዉ መለሱ ። አጼ ዮሃንስም የንጉስ ልጅ በማደጎ በአንቀልባ ይሄዳል ግዴለም አሉ ። ከዚህ ወዲህ የሰርጉ ቀን ተቆርጦ መሰናዶ ተጀመረ ። ንጉስ ሚኒሊክም ለራስ አርእያ ስላሴ ግማሽ ወሎን ሾመዉ አዋጅ አስነገሩለት ። የሁለቱ ነገስታት ወዳጅነትም በጣም እየተጠናከረ መጣ ። አጼ ዮሃንስም ምርኮኛዉን የጎጃሙን ንጉስ ተክለሐይማኖትን እዚያዉ ጎጃም መልሰዉ ሾመዉ የሰርጉንም ቀን ወስነዉ ተሰነባበቱ” ይላል ።

የዓለማችን ትልቁ ሰርግ /የወረኢሉዉ ሰርግ/፣ ወሎ ወረኢሉ

ያ ወሎ እሚባል ገደል ውስጥ፣ ያ ወሎ የሚባል ልዩ የጥቁሮች ምድር ውስጥ ያልተፈፀመ ነገር የለም ። የሰርግ መለኪያ መስፈርቶች ላይ እርግጠኛ መሆን ባይቻልም፤ ከሰዉ ብዛት፣ ከወጣበት ወጭና ከዲምቀቱ አንፃር ሲታይ ይህ የወረኢሉዉ ሰርግ የዓለማችን ትልቁ ሰርግ ይሆናል ።

ጸሓፊ ትእዛዝ ቀጥለዉም “የሰርጉ መሰናዶ እየተጠናቀቀ ነዉ ። ዳሱን የማስዋብ ስራም እያለቀ ነዉ ። ዳሱ በላይ በታች በሸማ እየተለበጠ ነዉ ። ከእኩሌታዉ በላይ ደግሞ በቀይ በለዲ፣ በሌታ፣ የቀኙ ግምጃ በደማስ እየተሸለመ ነዉ ። መሬቱ እኩሌታዉ ሰርፍ ምንጣፍ እየለበሰ ነዉ ። ዳሱን የሚሸከመዉ ባላ ሁሉ የመጀመሪያዉ በአምሳለ ሰኒ የዚያ ተከታይ በቀይ ምስዕ፣ ቀጥሎ አረንጓደ ግምጃ ሶስተኛዉ እረድፍ አይነቱ ልዩ ልዩ የሆነ ሱቲ ። የመጨረሻዉ ወደ መግቢያ በኩል ያለዉ በሸማ እየተለበጠ ነዉ ። የንጉሱም ዙፋን በተነጠፈዉ በዳሱ ሲሶ /አንድ ሶስተኛ/ ቦታ ላይ ተዘርግቶ ዙሪያዉንም

በወርቀ ዘቦ መጋረጃ ተጋረደ ።የድግሱም ነገር በወገን በወገኑ ተዘጋጅቷል ። በድግሱም 1,350 ድልብ ሰንጋዎች ታርደዋል /ከበጉና ከፍየሉ ውጭ ነው/ ። የሌላዉን ድግስ የቂቤውን፣ የማሩን፣ የጠጁን፣ የአረቂዉን፣ የድለሁን፣ የእንጀራዉን …ወዘተ መጠን ሰዉ ደክቶ /ለክቶ/ ሊናገረዉ አይችልም ።

ከዶባ፣ መራቢቲ እስከ የጁ ያሉ የወሎ ባላባቶች ከነሰራዊታቸዉ ከተዉ ገብተዋል ። መኳንንቱና ሹማምንቱ ሁሉ ቋሬ የተሸለመ ወርቀ ዘቦ ቀሚስ ለብሷል ። ሰራዊቱም ሁሉ እንደ አቅሙ አጊጧል ።

ራስ አርአያ ከእድምተኞቻቸዉ ጋር መጥተዉ ነደዱ ከሜዳዉ ላይ ሰፈሩ ። በነጋዉ እሑድ ማለዳ ወደ ሰርጉ ገቡ ። በዚህም ጊዜ መላዉ ሰራዊቱ አጊጦ አምሮ ተሰልፎ ተቀበላቸዉ ። ሲበሉ ሲጠጡ ሲዘፍኑ ዋሉ ። ፀሀይ ሲገባ ወደ ሰፈራቸዉ ጉዞ ሲጀምሩ ዘበኛ ታዞ በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ሆኖና ሙሉ ግብር /ድልብ ሰንጋ ጠጅ አረቄ/ ይዞ አደረሳቸዉ ። በነጋዉ ሰኞ ጧት እንደገና ተጠርተዉ ገቡ ። ሲበሉ ሲጠጡ ሲጨፍሩ መኳንንቱም ሲሸልሙ ዉለዉ አመሻሽ ላይ ወደ ሰፈራቸዉ ወረዱ ።

የራስ አርአያ ስላሴ ሽልማት ይህ ነዉ ። አንድ መድፍ፣ 500 ነፍጥ፣ 500ፈረስና በቅሎ፣ 500 አገልጋይ፤ 100 ሰርፍና ስጋጃ ምንጣፍ ከዚህ አንዱ ባለወርቅ ነዉ፣ ግራ ቀኝ የወርቅ ማከዳ፣ የብር ዳታን ሰንና ብርት፣ 200ሊና ብርጭቆ፣ 5000 ላምና በሬ፣ 5000 በግና ፍየል፣ ባለወርቅ መጣምር ፈረስ፣ ባለወርቅ መጣምር በቅሎ፣ የወርቅ ጋሻ፣ የወርቅ ጎራደ፣ የወርቅ ቢተዋ፣ ልዩ ልዩ አይነት ቀሚሶች፣ ሁለት ማለፊያ ለምዶች፣ ግምጃ ሱሪ፣ ግምጃ መታጠቂያ፣ ድርብ ግምጃ፣ ጥላ፣ ግምጃ ድኳን፣ 2 ባለመደረቢያ ድኳን፣ 30 ለምድ፣ 100 ቀጭን ሸማ፣ 600 ኩታና 5000 ብር ነበር ። /ሴቲቱ

ሙሽራ የምትሸለመዉ እዚያኛዉ ስትሄድ ስለሆነ አልተፃፈም/ ።

የመኳንንቱ ሽልማት ደግሞ ለራስ ቢትወደድ ገብረ ኪዳን ባለብር መጣምር ፈረስ፣ ባለመርገፍ በቅሎ፣ 8ሌጣ ፈረስ፣ የወርቅ ጋሻ፣ ጥንድ የወርቅ ጦር፣ የወርቅ ቢተዋ፣ ወርቀ ዘቦ ቀሚስ፣ ማለፊያ ለምድና ድርብ ሲሆን ለደጃች ሐጎስም፣ ለደጃች ተሰማም፣ ለደጃች ገብረ እግዚአብሔርም፣ ለብላታ ሐጎስም ለሁሉም እንደዚሁ ሸልመዋቸዋል ።

በሶስተኛዉ ቀንም ሲበሉ ሲጠጡ ሲዘፍኑ ሲሸልሙ አርፍደዉ እኩለ ቀን ሲሆን ሙሽራይቱ ወ/ሮ ዘዉዲቱ ተነሳች፤ 12 ጊዜ መድፉም ነፍጡም ሙሉ ግባት ጫፍ እስከ ጫፍ ተተኮሰ ። ያሁሉ ሰራዊት ሲተኩስ ወረኢሉ ከተማ በጭስ ተሰወረች ። የተኩሱ ወሰን ሰፊ ስለሆነ ተኩሱ በመላዉ ሀገሪቱ ይመስል ነበር ። የተኩሱን ወሰን በጆሮ መድረስ አይቻልም፤ ወታደሩ ጠግቦ በየቦታው ስለነበረ ጋራው፣ ወንዙ፣ ሳር ቅጠሉ ሁሉ ይተኩስ ነበር ፡ መኳንንቱም ሰራዊቱም ይደልቃል፣ ይዘፍናል፣ ካህናቱም በማህሌት እግዚአብሔርን ያመሰግናል፣ በአጠቃላይ ዳር እስከ ዳር ወረኢሉና አካባቢው በሰው ተሞልቷል ። ቃላቶች የራሳቸው የአቅም ውስንነት ስላላቸው የዚህን ሰርግ ሁኔታ በቃላት መግለፅ አይቻልም ። ለሙሽራይቱም በ4 ማዕዘን ሁለት የወርቅ ድባብ ሁለት የብር ድባብ ተደብቦላታል ። ደንገጡሮቹም እጅግ ብዙ ሆነው በፊት በኋላ በብርና በወርቅ አጊጠዉ ተሸልመዉ አምረዉ ጥላ ይዘዉ እጅግ ብዙ ሆነዉ ከበዋት ይጓዙ ነበር ። ከጌጡም ማማር የተነሳ ሙሽራይቱን ለይቶ ማወቅ አይቻልም ነበር ። የስንድድ መሶብም የስንድድ ቀሚስ ለብሶ ከፊት ከፊታቸዉ ብዙ ሆኖ ይጓዝ ነበር ።

ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን አጠገብ ሲደርሱ እንደገና ሙሉ ግባት ጫፍ እስከጫፍ ተተኮሰ ። የሚተኩሰዉ ሰራዊት ድካ /ስፋት/ በጆሮ ግምትም በአይንም መገመት ስለማይቻል፣ ሳር ቅጠሉ፣ ተራራዉና ኮረብታዉ ሁሉ ተኩስ ነበር ። ነጋሪቱ እየተጎሸመ፣ እምቢልታዉ እየተነፋ፣ ሰራዊቱ እየደለቀ እየጨፈረ እሰፈራቸዉ አድርሶ ተመለሰ ።

እራትም እንደ በቀደሙ ሙሉ ግብር ሄደላቸዉ ። ገምቦኛዉ ጠጁን፣ ወረገኑን፤ ስጋ መልከኛዉ የሰንጋዉን፣ የሙክቱን፣ የበጉን፤ አዛዡ ቅቤዉን፣ ማሩን፣ ድልሁን፣ ዱቄቱን፤ ቋሚዉ መሶቡን ተሸክሞ ተከተለ ። ለሚዜዎቹም ለ10ሩ ለእያንዳንዳቸዉ አስር አስር ፈረስና አስር አስር በቅሎ ከነ ሙሉ እቃቸዉ ሸለሟቸው ።

እንግዶች ከተሸኙ በኋላ ሙሉ ግብር አግብተዉ 450 ድልብ ሰንጋዎች ታርደዉ ከማለዳ ጀምሮ እስከ ዶሮ ጩህት ድረስ ግብር ሆነ ። ከአንድ ቀን በኋላም ወደ ሸዋ /ወደ እንጦጦ/ ጉዞ ተጀመረ” ይላል ።

# የንጉስ ሚኒሊክ እና የእቴጌ ጣይቱ መገናኘት

ጸሓፊ ትእዛዝ በዚሁ መፀሐፋቸው "ነገሩ የተጀመረዉ በአጼ ቴዎድሮስ ጊዜ ነዉ ። የንጉስ ሚኒሊክ ሞግዚት አቶ ናደዉ ይባል ነበር ። ወሌና አሉላ የሚባሉ ሁለት የየጁ ባላባት ወንድማማቾች ነበሩ ። ሁለቱም ወንድማማቾች በጣም ያምራሉ ። እናም የሚኒሊክ ሞግዚት እነዚህን ሁለት የሚያማምሩ ወንድማማቾች ሲያዩ እነዚህ ልጆች እህት የላቸዉምን ብሎ ጠየቀ ። እህት እንዳላቸዉም በተነገረዉ ጊዜ በቅሎዉን ጭኖ፣ ወደ ዘመዶቿ ሄዶ፣ ዘራችሁ መልካም አባታችሁ ትልቅ መሆኑን ሰምቻለሁና ለሸዋዉ ንጉስ ልጅ ለሚኒሊክ ልጃችሁን እንድትሰጡልኝ እማልዳችኋለሁ አለ ።

እነሱም ጋብቻዉ እጅግ የተስማማ ነበር፣ እኛም የምንሻዉ ነበር ። ነገር ግን አጼ ቴዎድሮስ ለምን አባታችሁ ገዛ ብለዉ ጠልተዉናል ። አልጋዉን /ንግስናውን/ ከእኛ ነዉና የወሰዱት በጣም ፈርተውናል ። እናም እኛ የየጁ አገር ሰዎች ሆነን ሚኒሊክ የሸዋ ንጉስ ልጅ ሆኖ ስንጋባ ሁላችንንም በአንድ ቀን ያስሩናል ብለዉ ተዉት፤ ነገሩም ተረሳ" ይላል ።

የእቴጌ ጣይቱ የዘር ሀረግ ደግሞ ፡ - ስለአንደኛዉ የእቴጌ ጣይቱ የዘር ሀረግ አለቃ ታዬ "የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ" በሚለዉ መፅሀፋቸዉ ያሰፈሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ "የወረሴሆች ነገርና ትዉልድ እንዲህ ነዉ፤ ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን ባጠፋ ጊዜ ከባህር ማዶ ከአረብ አገር ሼህ ዑመር የሚባል የብር ዘንግ የብር ርከት አሲዞ መጥቶ በወሎ የጁ ተቀመጠ ። ሸህ ዑመር ብዙ ሴቶች አግብቶ ብዙ ልጆችን ወለደ ። መንደሩ ቢበዛ ወረ ሺህ ተባለ ። አሁን ወረሴህ የሚባሉት የእሱ ዘሮች ናቸዉ ።

ከሼህ ዑመር ልጆች የበህሩ /የመጀመሪያዉ/ ወሌ ይባል ነበር ። ወሌ አብዬን ወለደ ። አብዬ ሲወልድ ልጁን ባባቱ ስም ወሌ አለው ። ወሌ አባ ገትዬን ወለደ ። አባ ገትዬ አባ ሴሩ ጓንጉልን ወለደ ። አባ ሴሩ ጓንጉል ክርስትና ተነስቶ የላስታና የሰለሞን ባላባት የራስ ፍሬስን እህት ወ/ሮ ገለቡን አግብቶ ራስ ዓሊን፣ ወ/ሮ ከፈይን፣ ራስ አሊጋዝን ወለደ ። ወ/ሮ ከፈይ የኢልማ ፆርማን ባላባት መርሶ በሬንቶን አግብተዉ ራስ ጉግሳን፣ ደጃች አሉላን ወለዱ ። ራስ ጉግሳ ወ/ሮ ሎሚታን አግብተዉ ራስ ማርዬን፣ ራስ ይማምን፣ ራስ ዶሪን፣ ወ/ሮ ሂሩትን ወለዱ ። /በዘመነ መሳፍንት ርዕስ ስር እንዳስቀመጥነው/ ወ/ሮ ሂሩት

አባቷ ራስ ጉግሳ ነግሶ የደብረታቦር ከተማን በመሰረተበት ወቅት ቀደም ብለው በአፄ ሱስንዮስ ተሹመው ከወሎ ወግዲ /ቦረና/ ሄደው ሰሜንን እያስተዳደሩ ከኖሩት ከኤሎስ የዘር ሐረግ የተወለደውን የሰሜኑን ባላባት የራስ ገብሬን ልጅ ደጃች ኃይለ ማሪያምን አግብታ ደጃች ብጡልን፣ ደጃች መርሶን፣ ወ/ሮ የዉብ ዳርን ወለደች ። ደጃች ብጡል የሜጫይቱን አሮሞ ወ/ሮ የዉብ ዳርን አግብተዉ እቴጌ ጣይቱን፣ ፊታዉራሪ አሉላን፣ ራስ ወሌን፣ ወ/ሮ ደስታን ወለዱ ። እቴጌ ጣይቱ የዳግማዊ ምኒሊክ ሚስት መካን ናቸዉ ። ፊታዉራሪ አሉላ ወ/ሮ የተመኘን ወለዱ ። ራስ ወሌ ራስ ጉግሳ፣ ወ/ሮ ከፈይን፣ ደጃች አመዴን፣ ደጃች ኃይሉን ወለዱ ። ወ/ሮ ደስታ ደጃች ወልደ ሀናን አግብተዉ ደጃች ገሰሰን፣ ወ/ሮ አሰለፈችን ወለዱ ። ደጃች መርሶ ደጃች ትኩን፣ ወ/ሮ ላቀችን ወለዱ ። ራስ አሊጋዝ ደጃች ጎጅን፣ ደጃች ብሩን ወለዱ ። ደጃች ጎጅ ልጅ ዘለቀን ወለዱ ። ልጅ ዘለቀ አባ ግርሻን ወለዱ ። ደጃች ብሩ ደጃች ዘገየን ወለዱ ። ደጃች ዘገየ ደጃች ጓንጉልን፣ ደጃች አሊን፣ ደጃች አሊጋዝን፣ ወ/ሮ ሂሩትን፣ ደጃች ኃይሉን ወለዱ ። ደጃች ጓንጉል ደጃች ይማምን፣ ደጃች አሊን ወለዱ" ይላል ።

ስለ እቴጌ ጣይቱ ሁለተኛ የዘር ሀረግ ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ "ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ሚኒሊክ በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ያሰፈሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ "ኤሎስ የተባለ ሰዉ ከወሎ ወግዲ /ቦረና/ ሄዶ ሰሜንን ከባምብሎ በመለስ ተከዜ በፈሰስ በአፄ ሱስንዮስ ተሹሞ ይገዛ ነበር ። ኤሎስ ቁርሎስን ወለደ ። ቁርሎስ ኤራቅሊስን ወለደ ። ኤራቅሊስ የንጉሱን ልጅ ወ/ሮ ሰማዕታን አግብቶ ተስፋን ወለደ ። ተስፋ ማሪቱን ወለደ ። ማሪቱ ያበርገሌዉን ደጃች ወ/ ፋኤልን አግብታ ራስ ገብሬን ወለደች ። ራስ ገብሬ ከበየዳ የክፍለ እየሱስን ልጅ ወ/ሮ ሳህሊቱን አግብቶ ደጃች ኃይለማሪያምን ወለደ ፡ ደጃች ኃይለማሪያም ደብረታቦር ከተማ በተመሰረተችበት ጊዜ የየጁዉን የራስ ጉግሳን ልጅ ወ/ሮ ሂሩትን አግብቶ ደጃች ብጡልን፣ ደጃች መርሶን፣ ወ/ሮ የዉብዳርን ወለደ ። ደጃች ብጡል የሜጫይቱን አሮሞ ወ/ሮ የዉብ ዳርን አግብተዉ እቴጌ ጣይቱን፣ ፊታዉራሪ አሉላን፣ ራስ ወሌን፣ ወ/ሮ ደስታን ወለዱ" ይላል ።

እናም ንጉስ ሚኒሊክ ሌላ ሚስት አግብተዉ ኖረዉ ኖረዉ በ1875 ዓ.ም ስጋ አምላክ ለመቀበል አሰቡ ። ነገር ግን ባልታወቀ ምክንያት በሚስታቸዉ በወ/ሮ ባፋና ስጋ አምላክ ለመቀበል አልፈለጉም ። የየጁዉን ባላባት ራስ ወሌ

ብጡልን ጠርተዉ፣ ወሌ እኔ በአንተ እህት ነዉ ስጋ አምላክ የምቀበለዉ ብለዉ በብዙ ሰዎች ፊት ተናገሩ ። እንደተናገሩም አልቀሩም በዚሁ በ1875 ዓ.ም ከወ/ሮ ጣይቱ ጋራ ተገናኝተዉ ስጋ አምላክ ተቀበሉ’’ ይላል ።

## የአዲስ አበባ ከተማ መቆርቆር

ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ቀጥለዉም “ንጉስ ሚኒሊክ ንጉሰ ነገስት ከመሆናቸዉ በፊት በ1878 ዓ.ም በእቴጌ ጠይቱ መካሪነት መቀመጫቸዉን ወደ እንጦጦ /አዲስ አበባ/ ቀይረዉ ነበር ። ሹማምንቱም ሁሉ በዚያዉ በአካባቢዉ ሰፍረዉ ይኖሩ ነበር ። ከለታት አንድ ቀን ንጉስ ሚኒሊክና ወ/ሮ ጣይቱ ከእንጦጦ በታች ወደ ሚገኘዉ ፍል ዉሀ ለመታጠብ ወርደዉ ነበር ። በዚያን ጊዜ ወ/ሮ ጣይቱ ከድኳኑ ደጃፍ /በር/ ሆነዉ ከእንጦጦ አንፃር ሲታይ ሙቀቱ የሚመችና አካባቢዉም የሚያምር መሆኑን ተመለከቱ ። በዚች ሀገር ቦታ ይስጡኝና ቤት ልስራ ብለዉ ጠየቁ ። ንጉሱም መጀመሪያ ቤቱን ስሪና በኋላ አገሩን እሰጥሻለሁ አሏቸዉ ። ወ/ሮ ጣይቱም የት ልስራ ብለዉ ጠየቁ ። ንጉሱም አባቴ ንጉስ ሳህለ ስላሴ አጥር ያሳጠሩት ቦታ ይህ ነበር፤ ከዚህ ላይ ይሁን ብለዉ ቦታዉን አሳዮአቸዉ ። ወ/ሮ ጣይቱም አዛዣቸዉን አስጠርተዉ ከዚህ ላይ ቤት ቶሎ አሰራ ብለዉ አዘዙት ። ቤቷም እጅግ ቆንጆ ሆና በጥቂት ቀን ተጨረሰች ። ነገር ግን በተለያዩ ዘመቻወች ምክንያት ቤቷን አልገቡባትም ነበር ። በዚሁ ወቅት ሌላ ያልተጠበቀ ክስተት ተከሰተ’’ ይልና፣

## የሐረር ዘመቻ ፡ -

ጸሓፌ ትእዛዝ ቀጥለዉም “ንጉስ ሚኒሊክ፣ የአሩሲ ገዥ የነበሩት ደጃች ዳርጌና ደጃች ወልደ ገብርኤል የአሩሲ ዲና እንደገና አምፆባቸዉ ሲዋጉ መክረማቸዉ አሳዝኗቸዉ በ1879 ወደዚያዉ ወደ አሩሲ ለመሄድ ተነሱ ። ንጉሱ ወደ ደጃች ወልደ ገብርኤል እየሄዱ መንገድ ላይ እያሉ፤ የደጃች ወልደ ገብርኤል ሰራዊት ተጣልቶ በሌላ አቅጣጫ ወደ ሸዋ መጣ ። ንጉስ ሚኒሊክ ጋር መንገድ ላይ ተላለፉ ። ንጉስ ሚኒሊክ ወደ እነሱ እየሄደ መንገድ ላይ መሆኑን አልሰሙም ። የተጣሉበት ምክንያትም ደጃች ወልደ ገብርኤል ሐረርን እወጋለሁ ብሎ ዝግጅት በመጀመሩ ነበር ። ሰራዊቱ ደግሞ ሐረር ላይ ብዙ

ፈረንጅ አለ፣ ብዙ መድፍና ነፍጥ አለ እየተባለ ይወራ ስለነበር፤ ይህ ሰዉ ብቻችንን ወስዶ ሊያስፈጀን ነዉ ብሎ ጠቅሎ ወደ እንጦጦ መጣ ። ደጃች ወልደ ገብርኤልም ብቻዉን ሰራዊቱን ከኋላ ከኋላ እየተከተለ እንጦጦ ገባ ።

በዚህ ጊዜ ወ/ሮ ጣይቱ እንጦጦ ከተማቸዉ ነበሩ ። የደጃች ወልደ ገብርኤል ሰራዊት ጌታዉን ትቶ እየመጣ አዋሽ መድረሱ ተሰማ ። ወ/ሮ ጣይቱም የደጃች ወልደ ገብርኤል ሰራዊት ጌታዉን ትቶ የመጣበት ምክንያት ምንድን ነዉ ብለዉ ወደ ምንጃሩ ምስለኔ ላኩ ። ምስለኔዉም ሰራዊቱ ከደጃች ወልደ ገብርኤል ጋር ተጣልቶ መጥቶ ነበር፤ አሁን ግን የንጉሱን መዝመት ሲሰማ ጨንቆታል ብሎ ላከ ። ወ/ሮ ጣይቱም ደጃች ወልደ ገብርኤልን ትቶ የመጣዉ ሰራዊት ጠቅሎ ወደ እንጦጦ እንዲገባና እኔን እንዲጠብቅ አድርግ፣ ወዳ ወዲህ ያለ እንደሆነ ግን እጁን ለኔ ከብቱን ንብረቱን ላንተ መርቄልሃለሁ /ሰጥቸሀለሁ/ ብለዉ ለምንጃሩ ምስለኔ መልሰው ላኩ ። ሰራዊቱም ይህን በሰማ ጊዜ ጠቅልሎ ወደ እንጦጦ ገባ ።

ወደ እንጦጦ የገባዉ ወታደር ቀለባችን አለቀብን የምንበላዉ አጣን እራበን እያለ አቤት አቤት አለ ። ወ/ሮ ጣይቱም በዚህ ነገር ተናደዉ እያሉ ለጊዜዉ መልካም ነገር ተናገሩ ። ወደ እኔ መምጣታችሁ ደግ አደረጋችሁ፣ ቀለባችሁም እንዲዘጋጅ አደርጋለሁ ። ከዚህ ላይ ሰፍራችሁ ቆዩ ብለዉ አዘዙ ። ወታደሩም እየመጣ ተከማቸ ። ወ/ሮ ጣይቱም ሹማምንቶቻቸዉን ጠርተዉ ይህን ሰራዊት ደኅና ቦታ ላይ ወስዳችሁ እሰሩ ብለዉ አዘዙ ። ከአዋሽ አንስቶ እስከ ጎልማሴ ቀብር ያለዉ ወታደር ሁሉ በአንድ ዕለት ተይዞ ታስሮ አደረ ። ሰዉ ሁሉ ወ/ሮ ጣይቱ ባደረጉት ነገር በጣም ተደነቀ ።

በዚህ ጊዜ ራስ ጎበና /የወሎ ባላባት/ ከበቅሎ ወድቀዉ ታመዉ ነበር ። ህዝቡ የንጉሱን ወሬ መጥፋት፣ የራስ ጎበናን መታመም ባየ ጊዜ አገሩ ተናወጠ ። ህዝቡ ሚኒሊክ ሞተዋል የሚል ግምት በመያዙ አስፈሪ ሁኔታ ተፈጠረ ። የህዝቡን አለመረጋጋትና መጨነቅ የሰሙት ወ/ሮ ጣይቱ፣ እንጦጦን ትተዉ ወደዚያች ፍል ዉሀዉ አጠገብ ወዳሰሯት ቤት ወርደዉ ገቡ ። ወዳዉም ከተማ መስራት ተጀመረ ። መኳንንቱም ቦታ እየተመራ ቤቱን ይሰራ ጀመር ። ህዝቡም ወ/ሮ ጣይቱ አዲስ ከተማ ማሰራታቸዉን ባየ ጊዜ ንጉስ ሚኒሊክ ደህና መሆናቸውን ስለተረዳ ዳር እስከ ዳር ረጋ ። ከተማዉም በጣም ያማረ ሆነ ሹማምንቱም ወደዱት ። ወ/ሮ ጣይቱም ይህን ከተማ ስሙን ‘’አዲስ

አበባ'' በሉ ብለዉ አዘዙ ፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ንጉስ ሚኒሊክ አይሰሙም ሐረር ናቸዉ ።

ንጉስ ሚኒሊክ በታህሳስ 10ቀን ገለምሶ ደጃች ወልደ ገብርኤል ከተማ ቢሰፍሩም ቀደም ብለን እንደገለጽነዉ ደጃች ወልደ ገብርኤል ወደ እንጦጦ ስለመጡ አላገኟቸዉም ። ከገለምሶም ተነስተዉ ወደ ሐረርጌ ተጓዙ ። በ18 ሂርና ሰፈሩ፣ በ21 በወራ መገናኛ ቡርቃ ወንዝ ሰፍረዉ መንገድ አስጠረጉ ። በ24 ቀን ገበያ ወንዝ ላይ ሰፈሩ፣ በታህሳስ 25 ቀን ጨለንቆ ላይ ሰፈሩ ። የሐረርጌ ገዥ አሚር አብዱላሂም ሰፈር ወራቢሌ ላይ ታየ ። ንጉስ ሚኒሊክም ግባ /ገብር/ እኔ ለአንተ ነዉ እንጂ የመጣሁት አገር ላጠፋ አይደለም ። ከገባህ ከተገዛህ ገዥነትህን /ሹመትህን/ አልነሳህም፣ ጦርነት ከፈለክ ግን ኋላ ይፀፅትሀል ብለዉ ላኩ ። አሚር አብዱላሂ ግን ይህን ሲልኩበት የፈሩት መስሎት መልእክተኞቹን አሰራቸዉ ።

ታህሳስ 29 የገና እለት አሚር አብዱላሂ ዛሬ ክርስቲያኖች በዓል ስለሆነ ይዘናጋሉ ብሎ መክሮ ጦሩን ጠቅሎ ሲናድሩን ከፊት፣ መድፎችን ከመካከል፣ ቀስተኛዉን ከኋላ፣ ቀጥሎ ፈረሰኛዉን፣ ቀጥሎ ጋሻኛዉን አሰልፎ በ5 አዓት ወደ ንጉሱ ሰፈር ጉዞ ጀመረ ።

የንጉሱም ሰራዊት መብሉን መጠጡን እንጂ የጦርነት ነገር አላሰበም ነበር ። ንጉስ ሚኒሊክ ከዙፋናቸዉ ፊት ለፊት ቆመዉ በመነፅር አካባቢዉን ሲመለከቱ ከሰፈር ማዶ ያለዉን ቁልቁለት የአሚር አብዱላሂ ሰራዊት አጥለቅልቆት ሲመጣ አዩት ። በዚህን ጊዜ ፈጥነዉ ሹማምንቶቻቸዉን ጠርተዉ ሰራዊታቸዉን አሰልፈዉ ትንሽ ከጠበቁ በኋላ ሲጠጋ ሄደህ በለዉ ብለዉ ለቀቁት ።

አሚር አብዱላሂ መድፍ ማስተኮስ ጀመረ ። በዚህ ጊዜ ፅኑ ዉጊያ ሆነ፤ አያሌ /እጅግ ብዙ/ ህዝብ አለቀ ። የንጉሱ ሰራዊት የአሚር አብዱላሂን መድፎች እጅ አድርጎ /ማርኮ/ አዞሮ ተጠቀመባቸዉ ። የአሚር አብዱላሂ ሰራዊት ድል ሆነ ። ባላገሩም /ነዋሪዉ/ ለዉጊያ ሰብስቦት ነበርና አንማረክም እያለ ጠንክሮ ተዋግቶ ነበር፤ ነገር ግን በመጨረሻ ድል ሆነ ። አሚር አብዱላሂ መድፉን ነፍጡን ሰራዊቱን ለንጉስ ሚኒሊክ አበርክቶ /አስማርኮ/ በፈረስ አመለጠ ። ንጉስ ሚኒሊክም አሚር አብዱላሂን ሊሾሙት ፈልገው ና ብለው ቢልኩበትም አብዱላሂ ግን ያስሩኛል ብሎ ስለፈራ በዚያው ጠፋ ። ንጉሱም

ጥር 5 ቀን ሐረርጌን ለደጃች መኮንን ሰጥተዉ፤ የካቲት 28 ቀን አዲስ አበባ ከአዲሱ ከተማ ገቡ ። ንጉስ ሚኒሊክ በአዲሱ ከተማ በጣም ተደነቁ፤ ወዳዉም የአሁኑ የአራት ኪሎ ቤተመንግስት ግንባታ ተጀመረ’’ ይሉና ።

ፀሐፌ ትእዛዝ ቀጥለውም ‘’ንጉስ ሚኒሊክ ጥቂት ቀን አዲስ አበባ ከቆዩ በኋላ የወሎን ሁኔታ ለማየት ወደ ወረኢሉ ጉዞ ጀመሩ ። መጋቢት 6ቀን ደብረ ብረሃን ገቡ ። መጋቢት 11 ቀን ከደብረ ብረሃን ተነስተዉ መጋቢት 17 ቀን ቀወት ሲደርሱ አፄ ዮሃንስ ማረፋቸዉ ተሰማ ። ንጉስ ሚኒሊክም የአፄ ዮሃንስን ሞት እንደሰሙ ለደቂቃዎች በሐዘን አቀርቅረው /አንገታቸውን ደፍተው/ ዝም ብለዉ ከቆዩ በኋላ አሟሟታቸዉስ እንደት ነዉ ብለዉ ጠየቁ ። ደርቡሽ ጋር እየተካሄደ በነበረ ዉጊያ እንደሞቱ ተነገራቸዉ ።

ግሸን አምባ የሁሉም ነገስታት ግምጃ ቤት ስለነበረች፣ ንጉስ ሚኒሊክ ሰገራት ሲደርሱ፣ ግሸን አምባን ይጠብቁ የነበሩ የአፄ ዮሃንስ ሹማምንትና መኳንንቶች፣ የንጉስ ዕቃ ለንጉስ ነዉና ግሸን አምባ የተከማቸዉን ዕቃ ይረከቡን ብለዉ ገቡ ። ንጉሱም የአምባሰልን ባላባት ጃንጠራ አስፋዉን ሹመዉ፣ እቃዉን የሚቀበል ደጃች ወልደን ልከዉ፣ ግሸንን ጠባቂ አቶ ወልደ ተክሌን አድርገዉ ሚያዝያ 10ቀን ወደ የጁ ጉዞ ጀመሩ ። ሐይቅ ሲደርሱ ደጃች ወሌን /የእቴጌዋ ወንድም/ ራስ አሰኝተዉ ከጨጨሆ በላይ ያባቱን ሀገር ሹመዉ ላኩት’’ ይሉና፣

## የጎንደር፣ የጎጃምና የትግራይ ዘመቻ ፡ -

ጻሓፌ ትእዛዝ ቀጥለዉም “አሁን አፄ ዮሃንስ ስለሞቱ የአፄ ዮሃንስን ግዛቶችንና ባላባቶችን ለማስገባት /ለማስገበር/ ወደ ጎንደርና ጎጃም ዘሙቱ ። ንጉስ ሚኒሊክ ባሻቻፌ ሰፍረዉ ሳለ ራስ ሚካኤልን /የወሎ ባላባት ወረሂመኖ/ ሰዉህን ጠቅለህ ዋድላ እንገናኝ ብለዉ ላኩት ። ንጉሱም በሳንቃ በር ወጥተዉ በጥላ አስፈሬ ተጉዘዉ ቀጭን አምባ ሰፈሩ ። ጓዙን ሁሉ እዚያዉ ትተዉ፣ ላሊበላ ሄደዉ ቤተክርስቲያን ስመዉ፣ ንጉሱም እመቤቲቱም ለነዳያን ብዙ ምጽዋት ሰጥተዉ ተመለሱ ። ንጉስ ሚካኤልም ጋር እዚያዉ ተገናኙ ።

እዚያዉ እያሉ የአገዉ ባላባት ዋግሹም ብሩ ገባ /እገዛለሁ አለ/ ። የአባቱን ሀገር ዋግን ሹመዉ ሸልመዉ ላኩት ። ከዚያም ተነስተዉ በድብኮ አልፈዉ

በገረገራ በኩል አድርገዉ ግንቦት 27 ቀን ቋራ ሰፈሩ ። ከዚያም ላይ ሳሉ የጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖት ገባ /እገዛለሁ አለ/ ። ንጉስ ሚኒሊክም የቀድሞ በደሉን ሳያስቡ ከቀድሞ መዓረጉ ሳያዋርዱ አፄ ዮሃንስ ሰጥተዉት ከነበረዉ ጎጃም ላይ ከፋን ጨምረዉ ሾሙት ።

ሰሜነኞች አባትና ልጁ ራስ ወልደ ስላሴና ደጃች ነጋሽ ገቡ /እንገዛለን አሉ/ ። የበጌምድርም፣ የበለሳም፣ የደምቢያም፣ የቋራም፣ የበለሳም መኳንንት አንድም ሳይቀር ጠቅሎ ገባ /እገዛለሁ አለ/ ። ንጉሱም ሁሉንም የያዙትን አገር ሾመዉ ሸልመዉ ላኳቸዉ ። አንድም ጦር ሳይወረወር አንድም አመፀኛ ሳይታይ የጎንደርና የጎጃም ዘመቻ በሰላም ተጠናቀቀ ።

ከዚህ በኋላ ንጉሱ ወደ ሸዋ ጉዞ ጀመሩ ። ንጉሱም በአንበሳ ማሰሪያ /ደላንታ/ አድርገዉ ዉጫሌ ሰፈሩ፣ ከኢጣሊያ ጋር የውጫሌን ውል ፈርመው ሰኔ 21ቀን ደሴ ሰፈሩ፤ ሐምሌ 9 ቀን 1881 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ ። ቀጥለዉም ለትግራይ ዘመቻ ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ ።

አዲስ አበባ እረፍት እያደረጉ ባለበት ወቅት በንጉሱም በወ/ሮ ጣይቱም ቤት ልክ የሌለዉ ድግስ ተደግሶ አዲስ አበባ በደረሱ በ4ኛው ወር በጥቅምት በ1882 ዓ.ም ስርዓተ መንግስት ተደርገ ። ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም በጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ተቀብተዉ "ዳግማዊ ሚኒሊክ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ" ተብለዉ በእንጦጦ ማሪያም ቤ/ን ነገሱ ። ዳግማዊ ሚኒሊክ /ሚኒሊክ 2ኛ/ የተባሉበት ምክንያት ሚኒሊክ የተባለ የንግስተ ሣባና የሰለሞን ልጅ በዚህ ሥም ቀድሞ ነግሶ ስለነበር ነዉ ።

በሦስተኛዉም ቀን ወ/ሮ ጣይቱ ብጡል በጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ዘዉድ ደፍተዉ እቴጌ ተባሉ ። ከዚያም ቀን ጀምሮ "ጣይቱ ብርሐን ዘኢትዮጵያ" እየተባሉ መጠራት ጀመሩ ።

አፄ ሚኒሊክ በ46 አመታቸዉ የመላዉ ኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ይሁኑ እንጂ ከ22 አመታቸዉ ጀምሮ ለሁለት አስርት አመታት ያህል አገር ሲያቀኑና ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርን ሲገነቡ /ሲፈጥሩ/ የቆዩ ናቸዉ ። ስለዚህም የሩቁም የቅርቡም መሣፍንት ያለማንገራገር ተገዛላቸዉ" ይላል ።

## የትግራይ ዘመቻ ፡ -

ጸሓፊ ትእዛዝ ቀጥለዉም “አፄ ሚኒሊክ በታህሳስ 9ቀን ለትግራይ ዘመቻ ተነሱ ። ታህሳስ 27 ቀን ደሴ ከተማ ገቡ ። ራስ ሚካኤልን /የወሎ ባላባት/፣ ራስ ወሌን /የወሎ ባላባት የእቴጌዋ ወንድም/፣ ባሻ ታምሬን /የወሎ ባላባት/፣ ደጃች ኃይለማሪያምን /አባዋጠዉ የወሎ ባላባት/፣ ፊታዉራሪ ተክለ ማሪያምን /የወሎ ባላባት/፣ ደጃች ደስታን /የወሎ ባላባት/ና ሌሎችም መኳንንቶች ተጨምረዉ ቀድመዉ ወደ ትግራይ እንዲጓዙ ታዘዙ ።

አፄ ሚኒሊክ ግን የካቲት መባቻ ከጎሊማ ተነስተዉ የካቲት 16 መቀሌ ላይ ሰፈሩ ። ያጋሜዉ ባላባት ደጃች ብሩ እዚህ ገባ /እገዛለሁ አለ/ ። ከመቀሌ ተነስተዉ የካቲት 20ቀን መከደን ሰፈሩ፣ በ21ቀን አጉላ ሰፈሩ፣ በ22ቀን ገንፈል ሰፈሩ፣ በ23ቀን ዛና ማርቆስ ሰፈሩ ስንቅ ስላለቀ ሰራዊቱ ለወረራ ተለቀቀ ። የካቲት 25ቀን አብርሀ አፅብሀ ሰፈሩ ። እዚህ አካባቢ የሚዘረፍ ጠፍቶ ሰራዊቱ ተርቦ ነበርና ወደ ኋላ ተመልሰዉ በ27ቀን ገንፈል ሰፈሩ፣ በ28 ሐይቅ መስሐል ሰፈሩ፣ በ29 አጽቢ ዕዳ ስላሴ ሰፈሩ፣ መጋቢት 3ቀን አጽቢዳራ ሰፈሩ፣ በ4 ፀዐዳ አምባ ሰፈሩ እዚህ አካባቢ ቀላል ዉጊ አጋጥሞ ነበር ። በ7 ሐረማት መሬት አጉዲ ላይ ሰፈሩ ።

እዚህ እያሉ የአጼ ዮሃንስ ልጅ ራስ መንገሻ ገቡ /እገዛለሁ አሉ/ ። አፄ ሚኒሊክም ከመረብ ወዲህ ራስ መንገሻን ከመረብ ወዲያ ከጣሊያን የተረፈዉን አከባቢ ራስ መሸሻን ሹመዉ መጋቢት 11ቀን ወደ ሸዋ የመልስ ጉዞ ጀመሩ ። የትግራይ ዘመቻም በሰላም በዚህ መልኩ ተጠናቀቀ” ይሉና፣

## የወላይታ ዘመቻ ፡ -

ጸሓፊ ትእዛዝ ቀጥለዉም “አፄ ሚኒሊክ በ1887 ዓ.ም ወደ ወላይታ ለመዝመት ተነሱ ። ህዳር 7ቀን ገጃ ሰፈሩ፣ በ22 ቆርጋ ሾኔ ሰፈሩ ።

እዚያም ሆነዉ ለወላይታዉ ገዥ ካዎ ጦና እንዲህ ብለዉ ላኩበት ። ሰዉህን አታስፈጅ፣ አገርህን አታስጠፋ፣ ግብርህን ይዘህ ግባ አሉት ፡ እሱ ግን

አልገባም እዋጋለሁ አለ ። ኬላዉን ፈረስና ሰዉ እንዳያስገባ አድርጎ አጥሮት ነበር ።

አፄ ሚኒሊክም ይህን እንደሰሙ፤ ራስ ሚካኤልን /የወሎ ባላባት/፣ ራስ ኃይለማሪያምን /አባዋጠዉ የወሎ ባላባት/፣ ፊታዉራሪ ገበየሁ ገቦን /ሰራዊቱ የወሎ/፣ ሊቀ መኳስ አባተን /የወሎ ባላባት ሰቆጣ/ እነዚህን ሄዳችሁ አጥሩን አፍርሳችሁ መንገዱን ደልድሉ ብለዉ አዘዟቸዉ ።

መንገዱም ከተደለደለ በኋላ የወላይታን ኬላ አልፈዉ በ23 ቆንጦላ ሰፈሩ ። እዚህ አካባቢ ከባድ ጦርነት ተካሂዶ በሁለቱም ወገን በዙ ሰዉ አለቀ በንጉስ ሚኒሊክ በኩልም 75 ሰው ሞተ ። ከዚህ በኋላ በ27ቀን አስጎላ ሜዳ ሰፈሩ፣ በ29 ዳሞት ከወላይታዉ ገዥ ከካዎ ጦና ከተማ ደልቦ ላይ ሰፈሩ ። አፄ ሚኒሊክ የሀገሩን ልምላሜና ማማር አይተዉ እንዳይወድም አዝነዉ፣ አሁንም ሌላ መልእክት እንዲህ ብለዉ ላኩ ። አገር ከጠፋ በኋላ ሲያለሙት ያስቸግራል ። ገንዘብም በግድ ካልሆነ በስተቀር በፈቃድ የሰጡት አይጎዳም ። ስለዚህ አገርህን አታስጠፋ ። ግብርህን ይዘህ ግባ ብለዉ ላኩበት ። እሱ ግን አልገባም ብሎ ቀረ ።

ከዚህ በኋላ አፄ ሚኒሊክ ሰራዊታቸዉ ለጦርነት እንዲሰለፍ ካዘዙ በኋላ፣ የቀኙን በቀኝ፣ የግራዉን በግራ፣ ግዙፉን የራስ ሚካኤልን ጦር በግምባር አድረገዉ በለዉ ብለዉ ለቀቁት ። አንድ ቀን ሙሉ የዋለ ከባድ ጦርነት ተካሄደ፤ እጅግ አሰቃቂ እልቂት ተከሰተ፤ እጅግ ብዙ ህዝብ አለቀ ። የአፄ ሚኒሊክ ጦር አንድ ቀን ሙሉ በዋለ ከባድ ጦርነት የወላይታን ድንበር አልፎ ቦረዳ የሚባለዉን አገር ሁሉ አስገበረዉ ። የወላይታው ገዥ ካዎ ጦናም ቦረዳ ላይ ቆስሎ ወድቆ ተያዘ'' ይላል ።

ካዎ ጦና የመጣበትን ሰራዊት ሁኔታ አለማገናዘቡ ስህተት እንዲሰራ አድርጎታል ። የሰሜኖቹ ባላባቶች በሰላም የገቡት/የገበሩት/ ወደዉ አይደለም ። የመጣበት ሰራዊት እጅግ የጦር ልምድ ያለዉ፣ እድሜ ልኩን በተለያዩ የሀገሪቱ አቅጣጫዎች ሲዋጋ የኖረ ከመሆኑም በተጨማሪ የራስ ሚካኤል ጦር በቀኝም በግራም አጋዦች ነበሩት፤ የጦና ጦር ግን ብቻዉን ነበር ። ስለሆነም በምንም አይነት ሁኔታ ጦና የራስ ሚካኤልን ጦር መደምሰስ አይችልም ነበር ማለት ነው ። እናም ልክ እንደሰሜኖቹ ባላባቶች መጀመሪያ ሁኔታውን አጥንቶ በሰላም መገበር ነበረበት ማለት ነው ።

ጦርነቱ በዚህ መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ አፄ ሚኒሊክ ቆስሎ የተማረከዉን ካዎ ጦናን እንደገና የወላይታ ገዥ አድርገዉ ሹመዉ ወደ ሸዋ ጉዞ ጀመሩ ። ጥር 11ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

## የአድዋ ዘመቻ

/ወሎ ከ ኢጣሊያ/

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ካሰፈሩት ውስጥ "ንጉስ ሚኒሊክ የግዛት ማስፋፋቱንሥራ እየሰሩ፣ ጎንለጎን ከአዉሮፓ መንግንታት ጋር ወዳጅነታቸዉን ያጠናክሩ ነበር ። በርካታ ሚሲዮናዊያንና ቆንሲሎችም ወደ ሸዋ ይመጡ ነበር ። አባ ማስያስ የተባሉ ኢጣሊያዊ ሚሲዮን ወደ ሸዋ መጥተዉ፣ ንጉስ ሚኒሊክ ከኢጣሊያ መንግስት ጋር ጥብቅ ወዳጅነት እንዲመሰርቱ ይገፋፏቸዉ ነበር ። በእርሳቸዉ አማካኝነት ከኢጣሊያ ጋር ቶሎ ቶሎ ይፃፃፉ ነበርና በርከት ያሉ የኢጣሊያ ዜጎች ከአገራቸዉ መንግስት ተልከዉ በቆንሲልነት ወደ ሸዋ መጥተዉ ነበር ። ንጉስ ሚኒሊክም የቆንሲሎቹ መብዛት ስላልተዋጠላቸዉ፣ አባ ማስያስን "ወደ አገራቸዉ እንዲመለሱ ያድርጉ" ሲሏቸዉ አባ ማስያስ ግን አዉሮፓዉያን ደግ እንደሆኑ፣ ክፋት እንደሌለባቸዉ፣ የጥንቱን የፖርቹጋልን ወዳጅነት …ወዘተ እየጠቀሱ "እነዚህም ለግርማዊነትዎ ጥሩ ጥሩ መሳሪያ የሚሰጡ ናቸዉ እነጂ ተንኮል የለባቸዉም፤ እኔ ዋስ እሆናለሁ" ብለዉ አሳመኗቸዉ ።

የኢጣሊያ እንግዶች በአባ ማስያስ አስተርጓሚነት ወደ ንጉስ ሚኒሊክ ቀርበዉ እጅ ነስተዉ በአንኮበር ቦታ ተሰቷቸዉ በሰላም መኖር ጀመሩ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ዋናዉ ንጉሰ ነገስት አፄ ዮሃንስ ነበሩ ። እሳቸዉ በመቀሌ መናገሻቸዉ ተቀምጠዉ የዉጭ መንግስታት ትኩረታቸዉ ወደ ሸዋዉ ንጉስ ሚኒሊክ ነበር ።

አፄ ዮሃንስ እንደሞቱ ንጉስ ሚኒሊክ የጎጃምና የጎንደር ባላባቶችን ለማስገባት ወደ ሰሜን ዘምተዉ በነበረበት ወቅት ሲመለሱ፣ አምባሰል ዉጫሌ በተባለዉ ቦታ ላይ ሰፍረዉ ሳለ ከኢጣሊያ መንግስት ጋር የሚቀጥለዉን ዉል

ተዋዋሉ ፡፡ “የዉጫሌ ዉል” እየተባለ የሚጠራዉ በግራዝማች ዮሴፍ አስተርጓሚነት የተዋዋሉት ዉል የሚከተለዉን ይመስላል ፡፡

“…የኢጣሊያ ንጉስ ነገስት ኡምቤርቶና … የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ዳግማዊ ሚኒሊክ ለኢትዮጵያ መንግስትና ለልጅ ልጅ የሚኖር ሰላምና እርቅ ለማድረግ የፍቅርና የንግድ ዉል ተዋዋሉ ፡፡ በኢጣሊያ ንጉስ ኮንት አንቶሎኒ ወደ ንጉሰ ነገስት ሚኒሊክ የኢትዮጵያን አልጋ የወረሱ እርሰዎ ስለሆኑ ይህን ከዚህ ቀጥሎ የተፃፈዉን ዉል ከኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሚኒሊክ ጋር ተዋዋልን ፡፡ ገና ሳይነግሱ በዘመቻ ተወጥረዉ ባሉበት ወቅት ነበር ያስፈረሟቸዉ ፡ የተፈረመው ውልም ፡ -

1. በኢትዮጵያና በኢጣሊያ ንጉሰ ነገስት መካከል በወራሾቻቸዉም በህዝባቸዉም እነዚህንም በተጠጉ ህዝቦች መካከል ሰላምና ፍቅር ሳይጓደል ለዘወትር ለልጅ ልጅ ይኖራል ፡፡
2. እነዚህ ሁለቱ አሁን የተዋዋሉት ነገስታት በየአገራቸዉ በየምስለኔቸዉ ይነጋገራሉ ፡፡ አንዱ ከአንዱ አገር ቆንስልም፣ የቆንስልም ወኪል መሾም ይቻላቸዋል ፡፡ እነዚህም ሾሞች እንደአዉሮፓ ነገስታት ስርዓት መታፈርና መከበር አይጓደልባቸዉም ፡፡
3. በነዚህ በሁለቱ ነገስታት ወሰን ፀብና ክርክር እንዳይነሳ በእዉቅ የተመረጡ ከሁለቱ ወገኖች ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ልከዉ በማይጠፋ ምልክት የግዛቱን ድንበር ይወስናሉ ፡፡ ከድንበሩ ወዲህ የሚጨመሩት አገሮች እነዚህ ናቸዉ ፡፡ የደጋዉ አፈር ከኢትዮጵያና ከኢጣሊያ መሐል ወሰን ይሆናል ፡፡ ከራፋሊ ጀምሮ ሂላይ፣ ሰገነይቲና አስመራ እነዚህ ሦስቱ የኢጣሊያ መንደሮች ይሆናሉ ፡፡ በቦጎስ በኩልም አዲነፋስ፣ አዲሞገስ በኢጣሊያ ድንበር ዉስጥ ይሆናሉ ፡፡ ከአዲሞገስ ጀምሮ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ባቀና ይከፈላል፡፡
4. የደብረ ቢዘን ገዳም ከእነ ጉልቱ፣ ከነርስቱ የኢትዮጵያ መንግስት እንደሆነ ይቀራለ ፡፡ የጦር አምባ መሆን ግን አይቻለዉም ፡፡
5. ከምፅዋ የሚመጣ የንግድ እቃ ከመቶ ስምንት በገቢ እቃ እየተገመገመ በገቢ አንድ ጊዜ ይከፍላሉ ፡፡

6. የጦር መሳሪያ ንግድ በኢትዮጵያና በምፅዋ መካከል የሚመላለሰዉ ለንጉሰ ነገስቱ ብቻ ይፈቀድለዎታል ። ሲያስመጡም ባለመሐተም ደብዳቤዎን ለኢጣሊያ ሹማምንት እየላኩ ያስመጣሉ ። ነፍጡንም የያዘዉን ጭነት ከምፅዋ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድንበር ድረስ የኢጣሊያ መንግስት ወታደሮች ዘበኛ ሆነዉ ይሸኛሉ ።
7. የነዚህ የሁለቱ ዉል ያደረጉ ነገስታት ዜጎች የንግድ እቃዉ ይዘዉ ከአንዱ ወደ አንዱ አገር መሄድ መምጣት ይቻላቸዋል ። በየመንግስቱና በየወረዳዉ ባለዉ ሹም ጥግነት/ድንበር/ ያሉት ደስ ባሏቸዉ ይመላለሳሉ ። ነገር ግን ከሁለቱም ወገኖች የጦር መሳሪያ የያዘ ብዙ ሆኖ ከአንዱ ድንበር ወደ አንዱ ድንበር መተላለፍ ተከልክሏል ። እንድህም ማለት አንዱ ያንዱን ከብት እንዳይዘርፍ በሁሉም ነገር እንዳይነካካ ተከልክሏል ።
8. የኢጣሊያ ሰዎች በኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያ በኢጣሊያና የኢጣሊያ መንግስት በሚገዛዉ ሀገር ቢሆን እንደየአገሩ ልማድ መግዛት መሸጥ መከራየት ይቻላቸዋል ።
9. የነዚህ የሁለቱ ነገስታት ዜጎች አንዱ ከአንዱ አገር ቢሄድ በሐይማኖታቸዉ ይኖራሉ ።
10. የኢጣሊያ ሰዉና የኢጣሊያ ሰዉ የተካሰሱ እንደሆነ እራሳቸዉ በመረጡት ዳኛ ያለዚያም ተያይዘዉ ምፅዋ ወርደዉ ይዳኛሉ ። የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ሰዉ የተጣሉ እንደሆነ ግን የኢትዮጵያ መንግስት ወኪልና የኢጣሊያ የምፅዋ ሹም በአንድነት ሆነዉ ይዳኛሉ ።
11. የኢጣሊያ ሰዉ በኢትዮጵያ የሞተ እንደሆነ፤ የኢትዮጵያም ሰዉ በኢጣሊያ አገር፣ የኢጣሊያ መንግስት በሚገዛዉ አገር የሞተ እንደሆነ፣ ከሟቹ መንግስት ወገን ገንዘቡን የሚቀበል ሰዉ እስኪመጣ ድረስ የሁለቱ ነገስታት ሹማምንት ገንዘቡን ጠብቀዉ ያስቀምጣሉ ።
12. በማናቻዉም ሀጢያት ተከሶ የተያዘዉ የኢጣሊያ ሰዉ በኢጣሊያ ሹማምንት ይዳኛል ። የኢትዮጵያ መንግስት ግዛት ዉስጥ ታላቅ ሀጢያት ሰርቶ የተገኘ የኢጣሊያን ሰዉ ፈጥነዉ ይዘዉ ለምፅዋ ሹማምንት መስጠት ነዉ ። ደግሞ በኢጣሊያ መንግስት ግዛት

የኢትዮጵያ ሰዉ ታላቅ ሀጢያት ሰርቶ የተገኘ እንደሆነ በኢትዮጵያ ዳኛ ይዳኛል ።

13. በኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስትም ውስጥ በኢጣሊያ ንጉስም ውስጥ ብርቱ ሀጢያት የሰራ ሰዉ ከአንዱ ግዛት ወደ አንዱ ግዛት ሸሽቶ የሄደ እንደሆነ ሁለቱም እያሰሩ ይልካሉ ።
14. የባሪያ ንግድ በክርስቲያን ሐየማኖት የተከለከለ ስለሆነ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት በተቻላቸዉ ነገር ሁሉ ባገራቸዉ ባሪያ እንዳይነገድ ይከለክላሉ ።
15. ይህ አሁን የተፃፈዉ ዉል ለኢትዮጵያ መንግስት ሁሉ ዉል ነዉ ።
16. ይህ ዉል ከተደረገ ከ5 አመት በኋላ ከሁለቱ መንግስታት አንዳቸዉ ዉል ለመጨመር ወይም ለመለወጥ ያስፈለጋቸዉ እንደሆነ ከአመት በፊት አስቀድሞ መናገር ይገባቸዋል ። ነገር ግን የንግድ ዉል ብቻ ማረም ማስጠንቀቅ ይገባቸዋል እንጂ ዛሬ የተለየዉን የድንበር ወሰን ማፍረስ አይቻላቸዉም ።
17. የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከአዉሮፓ ነገስታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግስት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል ።
18. የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከሌላ መንግስት ሰዎች ጋር የጥበብና የንግድ ነገር ለመለዋወጥ የፈለጉ እንደሆነ ከሁለቱ አማርጠዉ ሲያበቁ የሁለቱም ዉል አንድ የሆነ እንደሆነ ለኢጣሊያ ሰዉ ይሰጡታል ።
19. ይህ አሁን የተደረገዉ ዉል በአማርኛና በኢጣሊያ ቋንቋ ትክክል ሆኖ ተገልብጦ ሲያበቃ የታመነ ምስክር ይሆናል ።
20. ይህ አሁን የተፃፈዉ ዉል በሮማ ከተማ ፈጥኖ ይጠናቀቃል /ተግባራዊ ይሆናል/ ነገር ግን ይህን ዉል ኮንት ፒየትሮ አንቶሎኒ በኢጣሊያ ንጉሰ ነገስት ስም ከንጉሰ ነገስት ሚኒሊክ ጋር ተዋዉለዉ አትመዉ ጨርሰዋል ይላል ።

ሌሎቹ አንቀፆች ሁሉም የማንኛዉም አገራት ገዥዎች ሁሉ የሚዋዋሏቸዉ አይነት ዉሎች ይመስላሉ ። ነገር ግን አንቀጽ 17 ላይ በአማርኛ ትርጉሙ “የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከዉጭ አገር መንግስታት ጋር የሚያደርገዉን ግንኙነት ፈቃዱ ከሆነ በኢጣሊያ መንግስት በኩል ሊያደርግ

ይቻለዋል፣ የሚል ትርጉም የሚሰጠዉ አረፍተ ነገር በኢጣሊኛ ግን "የኢትዮጵያ መንግስት ከዉጭ አገር መንግስታት ጋር የሚያደርገዉን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት አማካኝነት ማድረግ ይገባዋል" የሚል ጭብጥ ያለዉ አረፍተ ነገር ነበር ።

ንጉስ ሚኒሊክ ዘዉድ መጫናቸዉን ለዉጭ አገር መንግስታት በቀጥታ ባስተላለፉ ጊዜ የፈቃዱን እንደ ግደታ ቆጥሮ የኢጣሊያ መንግስት ለውጭ ሀገር መንግስታት በእኔ በኩል እንጂ በቀጥታ ማስተላለፍ አይችሉም ብሎ ክርክር ስላነሣ፤ ለ5 አመት እንዲቆይ ተፈራርመውት የነበረዉ ዉል ጭራሽ ፈርሶ ነገሩም የአደዋን ጦርነት አስከተለ ።

የኢጣሊያ መንግስት ወረራዉን በይፋ ላለመፈጸምና ኢትዮጵያን ቀስ በቀስ ቅኝ ግዛቱ ለማድረግ ነበር አንቀጽ 17ን አምታች ጭብጥ እንዲኖረዉ አድርጎ ያስፈረሚቸዉ ። እናም አፄ ሚኒሊክ አንቀጽ 17 ላይ የጭብጥ ልዩነት መኖሩን ያወቁት ንጉሰ ነገስት ሆነዉ ሲቀቡ የደስታቸዉን መልእክት ለአዉሮፓ መንግስታት በቀጥታ ሲያሳዉቁ፣ ጣሊያኖች "አይቻልም መልእክትንም ቢሆን እኛ ነን መንገር ያለብን" የሚል አቋም በመያዛቸዉ ነበር ። ከዚህም ጊዜ በኋላ ጣሊያን አንቀጽ 17ን መሰረት አድርጋ ሞግዚት መሆን ፈለገች ። ይህ ሁኔታ እቴጌ ጣይቱንም ንጉሰ ነገስቱንም እጅግ በጣም አበሳጨ ። እናም እቴጌይቱም ንጉሱም ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን ግልጽ አደረጉ ። አንቀጽ 17 እጅግ በጣም ያስቆጣቸዉ እቴጌይቱን ነበር፤ ዉሳኔያቸዉንም ቀድመዉ ያሳወቁት እቴጌይቱ ነበሩ ። "እኔ ሴት ነኝ፣ ጦርነት አልወድም፣ ግን እንዲህ መሣዩን ዉል ከምቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ፤ እኛ ለራሳችን እንበቃለን፣ የናንተን የበላይ ጠባቂነት አንፈልግም፣ ለአገሩ ደረቱን ለጥይት እግሩን ለጠጠር የማይሰጥ ያለ እንዳይመስልህ፣ አንፈራም ጦርነቱን ከፈለግከዉ ነገ አድርገዉ፣ ሂድ አይምሽብህ" ብለዉ ለድርድር የመጣዉንና የጦርነት ዛቻ እየዛተ ያስቸገረዉን የኢጣሊያን መንግስት ተወካይ አባረሩት ።

ከዚህ በኋላ የኢጣሊያ መንግስት ቀስ በቀስ በአፄ ዮሃንስ ጊዜ ይዞት ከነበረዉ ኤርትራ አልፎ ብዙ ግዛቶችን መያዝ ጀመረ ። ራስ አሉላና ራስ መንገሻ በሜጀር ቶዞሊ ከሚመራዉ የጠላት ጦር ጋር ተዋግተዉ ድል አድርገዉ ኩዓቲትን አስለቀቁ ። ነገር ግን በጀኔራል አርሞንዲ የሚመራዉ የጣሊያን ጦር ተተክቶ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ ሰንአፌን ተቆጣጠረ ። ቀጥሎም በርካታ

ባሽባዙቆችን /ከኤርትራ የቀጠራቸዉን ወታደሮች/ ከፊት እያደረገ የወረራዉን መጠን እያሰፋ አድዋ አደረሰዉ ።

አፄ ሚኒሊክም “ወዳጅነትህን አፍርሰህ የያዘከዉን አገር በሰላም ለቀህ ዉጣ” ብለዉ ልከዉበት ነበር ። ሆኖም ጀኔራል ባራቴሪ እንኳን ለቆ ሊወጣ ከአድዋ እስከ መቀሌ፣ ከመቀሌ እስከ አምባላጌ ደረሰ ።

ጥቁሮች አስደናቂ ታሪክ የሚሥሩበትና የአለም ታሪክ ፀሀፊዎችም የጥቁሮችን እጅግ አስገራሚ ጀግንነትና ጀብዱ የሚፅፉበት ጊዜ እየተቃረበ ነዉ ። አፄ ሚኒሊክም ተከታዩን የክተት አዋጅ ለህዝቡ አስተላለፉ ።

“አገር የሚያጠፋ፣ ሐየማኖት የሚለዉጥ ጠላት ልዑል እግዚአብሔር የወሰነልንን ባህር አልፎ መጥቷል ። እኔም ያገሬን ከብት ማለቅና የሰዉን መድከም አይቼ፣ እስካሁን ዝም ብለዉ ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር ።

አሁን ግን በልዑል እግዚአብሄር እረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠዉም ። ያገሬ ሰዉ፣ ከአሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም፣ አንተም እስከ አሁን አላስቀየምከኝም ። አሁንም ጉልበት ካለህ በጉልበትህ እርዳኝ፤ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለሚስትህ፣ ለሐየማኖትህ ስትል በፀሎት እርዳኝ ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ አልተዉህም ። እግዝዕትነ ማሪያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም ። ዘመቻየም በጥቅምት ነዉና የሸዋ ሰዉ እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረኢሉ ከተህ ላግኝህ ። የአፄ ምኒሊክ የክተት አዋጅ መስከረም 7 ቀን 1888 ዓ.ም” ይላል ።

ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ “ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ሚኒሊክ በሚለዉ መጻህፋቸዉ” ያሰፈሩትን አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋለሁ ።

“ጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ሲነሱ እቴጌ ጣይቱም አብረዉ ተነሱ ። ጥቅምት 18 ወረኢሉ ከተማቸዉ ሰፈሩ ። እዚያዉ ወረኢሉ እያሉ፣ ራስ ሚካኤልን /የወሎ ባላባት/፣ እራስ ወሌን /የወሎ ባላባት የእቴጌዋ ወንድም የጁ/ ፣ ራስ መንገሻ /የወሎዉ ነዉ ሳይንት፣ ትግራይም በዚህ ስም አለ/፣ ራስ መኮነን /የወሎ ባላባት ሸዋ/፣ ራስ አሉላ /የወሎዉ ነዉ የጁ የእቴጌዋ ወንድም፣ ትግራይም በዚህ ስም አለ/፣ ዋግሹም ጓንጉል /የወሎ ባላባት ሰቆጣ/፣

ደጃች ወልደ /የወሎ ባላባት/፣ ፊታዉራሪ ገበየሁ ገቦ /ሰራዊቱ የወሎ/፣ ፊታዉራሪ ተክሌ /የወሎ ባላባት/፣ ሊቀ መኳስ አድንቀዉ /የወሎ ባላባት/፣ ቀኛዝማች ታፈሰ /የወሎ ባላባት/ እነዚህን አምባላጌ ላይ የመሸገዉን የኢጣሊያ ጦር የምትችሉ ከሆነ ዉጉት የሚከብዳችሁ ከሆነ ግን ወደ እኔ ላኩብኝ ብለዉ አስቀድመዉ ላኳቸዉ ። የትግሬዉ ገዥ ራስ መንገሻ ለመንገዱም ለምክሩም /ለመረጃ/ ስለሚሆናችሁ ተገናኙት ብለዉ አዘዙ ።

አፄ ሚኒሊክ ግን ሌላዉ ሰራዊት ከቶ እስኪገባ ድረስ እዚያዉ ወረኢሉ ሰነበቱ ። ሰራዊቱ ከቶ /ተጠቃሎ/ ከገባ በኋላ፣ አባ ጅፋርን /የጅማ ባላባት/፣ ደጃች ጆቴን /የሌቃ ባላባት/፣ ካዎ ጦናን /የወላይታ ባላባት/ እነዚህን የውስጡን ሀገር ጠብቁ ብለዉ መለሷቸዉ ።

አፄ ሚኒሊክ የቀረዉን ጦር ይዘዉ ህዳር 2ቀን ከወረኢሉ ተነስተዉ ወደ አድዋ ጉዞ ጀመሩ ። ታህሳስ 4ቀን አለማጣ ሰፈሩ ። በዚህን ጊዜ በራስ ሚካኤል የተመራዉ የአምባላጌዉ ጦርነት ተወራ ። ከአምባላጌዉ ጦርነት የነበረ የራስ መንገሻ መልእክተኛ ደብዳቤ ይዞ መጣ ።

“ደብዳቤዉ እንዲህ ይላል፤ የጣሊያን ጦር የመሸገበት ስፍራ እንኳን መድፍና ነፍጥ የታጠቀን ወታደር ድንጋይ የያዘ ሰዉንም ለማጥቃት አስቸጋሪ ነበር፤ ፈረሰኛ አያስገባም ፡ ሆኖም ግን የእኛ ሰራዊት /የወሎ ሰራዊት/ የኢጣሊያን ሰራዊት የመድፍና የነፍጥ ተኩስ ከቁብ ሳይቆጥር እጅ ለእጅ እየተያያዘ፣ እጀን ያዘኝ፣ ነፍጤን ተቀበለኝ እየተባባለ ገደሉን ወጥቶ እፁብ ድንቅ ዉጊያ አድርጎ ድል አደረገዉ፤ ፈጀዉ ። የኢጣሊያ ጦር መሪ ማጆር ቶዞሊም እዚያዉ ሞተ ። ፊታዉራሪ ገበየሁ ገቦም ከፊት ሆኖ በከፍተኛ ጀግንነት በለዉ እያለ ሲያዋጋ ዋለ ። ገበየሁ ገቦ ድንቅ ጀግንነት ፈፀመ” ይላል ። /ገበየሁ ገቦ የቤተመንግስት አሽከሮች አለቃ ነዉ/ ።

ጳሓፌ ትእዛዝ ቀጥለውም ‘’በዚህ የአምባላጌ ጦርነት የኢጣሊያን ጦር ለመርዳት እየመጣ የነበረዉ 5ሺ የኢጣሊያ ጦር፣ የአምባላጌዉን የኢጣሊያ ጦር መሸነፍ ሲሰማ እዚያዉ ካለበት አዲራቅ ላይ መድፉንና ነፍጡን ደግኖ የንጉሰ ነገስቱን ጦር /የወሎን ጦር/ መምጣት መጠባበቅ ጀመረ ። ወዳዉም የወሎ ጦር ሲያባርር የኢጣሊያ ጦር ሲሸሽ አባራሪና ተባራሪ ሆነዉ አዲራቅ ሲደርሱ አዲራቅ ላይ መሽጎ ሲጠብቃቸው ከነበረው የኢጣሊያ ሰራዊት ጋር

ሌላ አዲስ ከባድ ጦርነት ተጀመረ ፡ በዚህ ከባድ ጦርነትም የጦር መሪዉ የማጆር ጋሊያኖ ፈረስ ተመትቶ ወደቀ ። የዚያን ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ሸሸ ። ማጆር ጋሊያኖም በሌላ ፈረስ ተዛዉሮ ሸሸ ። የወሎም ጦር መከተሉን ቀጠለ፤ የኢጣሊያ ጦርም እየሸሸ መቀሌ ደረሰ’’ ይላል ። /ከላይ ከተዘረዘሩት ባላባቶች እንደምናየው፣ እዚህ የአምባላጌና የአዲራቅ ጦርነት ላይ የተሰለፉት በሙሉ አፄ ሚኒሊክ ወረኢሉ ሳሉ የተላኩት የወሎ ባላባቶች ብቻ ነበሩ/ ።

ጸሓፊ ትእዛዝ ቀጥለውም ‘’ኢጣሊያኖች መቀሌ ላይ ብዙ እቃ ስለነበራቸዉ ዋናው ጀኔራላቸው መቀሌ ያለዉን እቃ ጥሎ ሸሸ ይሉኛል ብሎ፣ ማጆር አሞሊዮንን፣ ማጆር ካስቴንንና ማጆር ጋልያኖን መቀሌን ለመጠበቅ እጣ ተጣጣሉ አላቸዉ ። እጣዉም ለማጆር ጋሊያኖ ወጣበት ። ከዚያም ማጆር ጋሊያኖን መቀሌ ትተዉ፣ ጀኔራል አርሞንዲ፣ ማጆር ካስቴና ማጆር አሞሊዮ ሆነዉ ሲሸሹ ባላገሩ /ነዋሪው/ እየተታኮሰ አላስኬድ ሲላቸዉ እቃቸዉን፣ መጠጣቸዉንና ልብሳቸዉን እየጣሉ የ3ቱን ቀን ጎዳና በአንድ ሌሊት ጨርሰዉ አዲግራት ገቡ ። /ይህ ሁሉ ሲሆን አፄ ሚኒሊክ ገና አልደረሱም/ ።

አፄ ሚኒሊክ ታህሳስ 26ቀን ጨለቆ ሲደርሱ ፊት ቀድመዉ ከነበሩት መኳንንቶች ከእነ ራስ ሚካኤል ጋር ተገናኙ ። እነ ራስ ሚካኤልም አምባላጌና አዲራቅ የተማረከዉን መድፍና ነፍጥ ለአፄ ሚኒሊክ አስረከቡ ። አፄ ሚኒሊክም የተማረከዉን መድፍ ወደ አዲስ አበባ ላኩት ። በ29 ተጠቃለው መቀሌ ሰፈሩ ።

በዚያም ቀን የኢጣሊያ ሰራዊት ያለበትን ምሽጉን ካቡን መኳንንቶች በመነፅር፣ ሰራዊቱም

በአይኑ የቻለዉን ያህል አሻግሮ ባየ ጊዜ እንደ እሸት የሚቅመዉ እንደ ጥህሎ የሚዉጠዉ መሰለዉ ። ነገር ግን አፄ ሚኒሊክ በመነፅር የምሽጉን ብርታት አይተዉታልና ሰራዊቱ ወደ ምሽጉ እንዳይሄድ ከለከሉ ።

ለአራት ወር ያህል መቀሌ ላይ የተገነባዉ የኢጣሊያ ምሽግ በመነፀር /በአቅርቦ ማሳያ/ ሲታይ 3በ3 ድንጋይ እየተጠረበ በጥንቃቄ የተሰራ ነዉ ። በእያንዳንዷ ቀዳዳ መድፍ ተደግኖባታል ። የወሎ ፈረሰኛና እግረኛ ወታደር ወደ ምሽጋቸው እንዳይጠጋ ከድንጋዩ ምሽጋቸው በ20 ክንድ /በ10ሜትር/

እርቀት ላይ ባላ ባላ እየተተከለ ዙሪያዉ በሸቦ ታጥሯል /የወሎው ሰራዊት ሽቦ አጥሩን ለመሹለክ እስኪታገል ድረስ ለመምታት ነዉ/ ፡፡

ይህን ከስተዋሉ በኋላ የንጉስ ነገስቱ ድኳን ከምሽጉ ትይዩ ተተከለ ፡፡ ሰራዊቱም በየሰፈሩ ድኳኑን ተከለ ፡፡ ምሽት በሆነ ጊዜ ሊቀ መኳስ አባተ /የወሎ ባላባት/ና በጅሮንድ ባልቻ /የቤተመንግስት አሽከሮች አለቃና ሚስጥር ጠባቂ/ ተጠሩ ፡፡ እንግዲህ ከዚህ ጉድጓድ ዉስጥ ያሉትን ጣሊያኖች ሳላስወጣ ወዳ ወዲህ አልልም ብለዉ አዘዟቸዉ ፡፡ ሊቀ መኳስ አባተም ከአሽከሮቹ ጋር ሆኖ በስተግራ በኩል የኢጣሊያን ዘበኛ አባሮ ተጠግቶ እንደነሱ የድንጋይ ካቡን ክቦ መድፍና ነፍጥ ደግኖ ተቀመጠ ፡፡ በስተቀኝ በኩል ደግሞ በጅሮንድ ባልቻ እንዲሁ ከአሽከሮቹ ጋር ተጠግቶ ሌሊቱን የድንጋይ ምሽግ ሲክብ አድሮ መድፍና ነፍጥ ደግኖ ተቀመጠ ፡፡ ኢጣሊያኖችም የወሎው ጦር ጨለማን ተገን አድርጎ እንደቀረባቸዉ ባዩ ጊዜ መድፋቸዉንም ነፍጣቸዉንም አጠንክረዉ ይተኩሱ ጀመር ፡፡

ሊቀ መኳስ አባተም ብልህ አይነ ጥሩ ነፍጠኛ ነበርና ከድንጋይ ምሽጉ ውስጥ ሆኖ ኢጣሊያኖች የሚኖሩበትን ቤተክርስቲያን እያነጣጠረ መስኮቱን በመድፍ ይመታዉ ጀመር ፡፡ የመድፋቸዉንም መንኮራኩር በመድፍ ይሰብረዉ ጀመር ፡፡ የኢጣሊያ መድፈኛም የሊቀ መኳስ አባተን የተኩሱ ድምፅ አቅጣጫና ርችት እየተከተለ ጥይቱን እንደ በረዶ ያዘንበው ጀመር ፡፡ ነገር ግን በወሎ በኩል አንድም ሰዉ አልቆሰለም ፡፡ ከወደ ኢጣሊያ በኩል ግን ብዙ ሰዉ ሞተባቸዉ /አነጣጥሮ ከመምታት አንፃር ከኢጣሊያዎቹ ይልቅ ወሎዎቹ በጣም ይሻሉ ነበር/ ፡፡

በዚህ ጊዜ ንግስቲቱ እቴጌ ጣይቱ ከድኳናቸዉ ብቅ ብለዉ የግምጃቸዉን አጥር አስገልጠዉ ሲመለከቱ አዛዥ ዘአማኑኤል አጠገባቸዉ ቆሞ ነበርና ወደ እሱ አይናቸዉን ዘወር አድርገዉ ተናገሩ ፡፡ ‘’አንተ ሂድና ዉሀዉን ለመያዝ ይመች እንደሆነ ስፍራዉን ሰልለዉ፣ ለሊቀ መኳስ አባተም አማክረዉ’’ ብለዉ አዘዙት ፡፡ ሊቀ መኳስ አባተም ‘’ስፍራዉ ጎድጓዳ ነዉ፣ ለኢጣሊያኖች በጣም ቅርባቸዉ ነዉ፣ የዉሀዉና የምሽጉ እርቀት በግምት 150ክንድ /75ሜ/ይሆናል፣ ነገር ግን እኔ የዉሀዉን መግቢያ በር በመድፍ መጠበቅ እችላለሁ፣ ለአይን ሲነሳ /ሲጨልም/ ዘበኛ ከወንዙ ገብቶ እንዲተኛ

አደርጋለሁ’’ ብሎ ላከ ፡ ይህም ነገር በእቴጌ ዘንድ የተወደደ ሆነ፤ ለንጉሰ ነገስቱም አማከሯቸዉ፤ ንጉሰ ነገስቱም ‘’እሺ እንዳልሽ’’ አሉ ።

እቴጌዋም የአሽከሮቻቸዉን አዛዦች ጠርተዉ እንዲህ ብለዉ አዘዙ ። ‘’እናንተ ከጉድጓድ ገብተን ካልተዋጋን እያላችሁ ስትመኙ ነበር ። ነገር ግን ለብዙ ሰራዊት ጥቂት ስፍራ አይበቃዉምና አንድ ላይ ከሄዳችሁ ከኢጣሊያዉ ነፍጥ ይልቅ እርስ በርሳችሁ ትተላለቃላችሁ ። ስለዚህ የተወሰነ ሰዉ ብቻ ቀንሳችሁ ልካችሁ ከዉሀዉ ተኝታችሁ ኢጣሊያዎች ዉሀ እንዳይቀዱ ጠብቁ፤ አይዟችሁ በህይወት የተረፈን እሸልማለሁ፣ የሞተን ልጁን አሳድጋለሁ፣ ቁርባኑንም አወጣለሁ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን’’ ብለዉ አሰናበቷቸዉ ። ዘመቻዉ ከተጀመረ ጀምሮ እቴጌዋ ሌሊቱን ሙሉ ሲፀልዩ ነዉ የሚያድሩት ።

ከሌሊቱ 11 ሰዓት በሆነ ጊዜ የእቴጌዋ የእልፍኝ አሽከሮች ተነሱ ። ስማቸዉም ገብረ ጊዮርጊስ፣ ድልነሴና ሸዋዬ ይባላሉ ። እነዚህ አሽከሮች ሁሉም የ300 የ300 ነፍጥ ሹመኞች ናቸዉ /የሦስቱ ባጠቃላይ 900 ወታደር/ ። ሶስቱም ከነሰራዊታቸዉ ተሰልፈዉ ወደ ወንዙ ወረዱ ። መታኮሻቸዉን /ምሽጋቸውን/ አደራጁ፣ ዉሀዉንም በአፈርና በድንጋይ ደፈኑት ። እንደ አዳራሽ እንደ እልፍኝ አመቻችተዉ ወንዙን ተቀመጡበት ።

ኢጣሊያኑም ዉሀዉና ምሽጋቸዉ ቅርብ ስለነበር ዉሀዉ ይያዝብናል ብለዉ አላሰቡትም ነበር ። የዉሀዉን መያዝ ቁርጡን ባወቁ ጊዜ መድፉንና ነፍጡን አቀናጅተዉ ሀሙስ ማታ ከምሽቱ 3 ሰዓት ላይ ዉሀዉን ለማስለቀቅ ከምሽጋቸዉ ወጥተዉ ከፍተኛ ማጥቃት አደረጉ ። ነገር ግን ወሎዎቹ በርትተዉ ተዋግተዉ ወደ ምሽጋቸው መለሷቸው ። እንደገና ከሌሊቱ በ6 ሰዓት ተቀናጅተዉና እጅግ ብዙ ሆነዉ ዉሀውን የማስለቀቅ ትንቅንቅ አደረጉ ። በከፍተኛ ተኩስ ሽፋን ብዙ ሆነዉ ወደ ውሀው ይመጡና ሲመቷቸዉ ተመልሰው ወደ ምሽጋቸዉ ለመግባት በር ይጠባቸዉ ነበር ። በዚህ ሁኔታ በኢጣሊያኑ በኩል አያሌ ሰዉ ሞተ ።

በነጋም ጊዜ ሊቀመኳስ አባተና በጅሮንድ ባልቻ የጣሊያኖች እቃ ያለበትን፣ ምሳቸዉን የሚበሉበትን፣ መድፋቸዉ የተደገነበትን በመነፅር እያዩ ይመቷቸዉ ጀመር ። ኢጣሊያኑም ተኩሱ በጠነከረባቸዉ ጊዜ እቃቸዉን ለመድፍ ወደ ማይመች ስፍራ ማሸሽ ጀመሩ ። ሊቀመኳስ አባተም ኢጣሊያዉ

ከጉድጓዱ እስኪ ወጣ ድረስ እንቅፍ አልተኛም፣ ወገቡን አልፈታም፣ እንዳይንቀሳቀሱ አስጨንቆ አስጠብቦ በመድፍ ይጠብቃቸዉ ነበር ፡፡

እቴጌ ጣይቱም ዉሀዉን ለሚጠብቁ 900 አሽከሮቻቸዉ ፍሪዳዉ እየታረደ ስጋዉ በእንቅብ እየሆነ፣ እንጀራዉ በማለፊያ /በምርጥ/ ወጥ እየተፈተፈተ በመሶብ እየሆነ፣ ጠጁ በገምቦ እየሆነ ከሌሊቱ ከ9 እስከ 10 ሰዓት ይወስዱላቸዉ ነበር ፡፡ አሽከሮቹም የጎደለባቸዉ ነገር የለምና ለአንድ ቀን የሚያስመርረዉን ጦርነት 15 ቀን ሙሉ ሌትና ቀን እየተዋጉ ዉሀዉን ከልክለዉ በጭንቅ ኢጣሊያኑን ከምሽጉ ዉስጥ እንዲወጣ አደረጉት ፡፡

የኢጣሊያ ጦር በጭንቅ ብዛት እጅ ከመስጠቱ በፊት አንድ ሙሴ ፌልተር የሚባል የኢጣሊያ ሰዉ አዲግራት ካሉት የኢጣሊያ ጀኔራሎች ተልኮ መጥቶ ነበር ፡፡ ወደ አፄ ሚኒሊክ ድኳንም ካስገቡት በኋላ እንዲህ ብሎ ተናገረ ፡፡

የናንተስ ሰዉ ወደ ምሽግ ዳር እየሄደ እየተታኮሰ ለምን ያልቃል ፡፡ እነዚያስ ከምሽጉ ዉስጥ ያሉት ኢጣሊያኖችስ በዉሀ ጥም ለምን ያልቃሉ ፡፡ እኛም የምንፈልገዉ ፍቅርና እርቅ ብቻ ነዉ ፡፡ በፍቅር እንኳን የመቀሌን ምሽግ የአዲግራትንም ለቀን እንሄዳለን ብሎ ተናገረ ፡፡ አፄዉም እሺ ይሁን አሁንም እርቅ ከፈለጋችሁ ሄደህ ከዋናዎቹ አለቃዎችህ የዚህን ነገር ጨርሰህ ምላሹን አምጣ ብለዉ ወደ አዲግራት ላኩት ፡፡

መልእክተኛዉም መቀሌ ያሉት በዉሀ ጥም እየተጨነቁና በዉሀ ጥም ነፍስ እየጠፉ መሆኑን ስለሚያዉቅ የ3ቱን ቀን መንገድ በአንድ ቀን ጨርሶ አዲግራት ገባ ፡፡ ወዳዉኑም ወደ ሮማ ስልክ ደዉለዉ ከኢጣሊያ መንግስት ልቀቁ የሚል ምላሽ ስለመጣላቸው ጀነራሎቹን ባለማህተም ደብዳቤ አፅፎና ባለማህተም ደብዳቤውን ይዞ ወደ አፄ ሚኒሊክ ተመለሰ፡፡

አሁንም መንገዱን በአንድ ቀን ጨርሶ በ3ኛዉ ቀን ከአፄ ሚኒሊክ ሰፈር ገባ ፡፡ አፄዉም ባለማህተም ደብዳቤዉን ካዩ በኋላ፣ ምሽግ ያሉት ኢጣሊያኖች መዉጣት እንዲችሉ የሚፈቅድ ደብዳቤ ፅፈዉ፣ መሀተም አድርገዉ፣ ከዚያም ያመጣዉን ደብዳቤ ጨምረዉ መቀሌ ለተከበቡት ጣሊያኖች ላኩላቸዉ ፡፡ እነዚያም ምሽጉን ለቃችሁ ዉጡ የሚለዉን ባለመሀተም ደብዳቤ ባዩ ጊዜ ተድላ፣ ደስታ፣ የሙዚቃ ዘፈን፣ ጭፈራ ጀመሩ፡፡

ከዚያም በጅሮንድ ባለቻ የኢጣሊያኑ ሰዉም ከብቱም ዉሀ ይጠጣ ብሎ፣ ዘበኞቻቸዉን ላኩ ። ጣሊያኖችም ይህን በሰሙ ጊዜ ወደ ዉሀዉ በሩጫና በእሽቅድም ወጡ ። ከጠጡ በኋላም ግን ብዙ ሰዉ ሞተ ። አንድቷ ሴት በሩን እንደከፈቱላት ሩጣ ወጥታ ከዉሀዉ ደርሳ ሶስት ብርጭቆ ዉሀ ከጠጣች በኋላ ሁለት መንታ ሙት ወልዳ እሷም እዚያዉ ላይ ሞተች ።

ከዚህ በኋላ በጅሮንድ ባልቻ ወደ ምሽጉ ሄዶ የኢትዮጵያን ባንድራ ተከለበት ። ኢጣሊያኖችም ከምሽጉ እቃቸዉን ይዘዉ ወጥተዉ ሜዳ ላይ ሰፈሩ ። ነገር ግን ሁሉም ፈረሶቻቸውና በቅሎዎቻቸው በ15 ቀኑ ዉሀ ጥምና በመድፍ ስላለቁባቸዉ እቃቸዉን የሚጭኑበት አጥተዉ ነበርና አፄ ሚኒሊክ ከነጋዴዉና ከባላገሬዉ 500 ግመልና በቅሎ በየዋጋቸዉ እየገዙ ጭነዉ እንዲጓዙ አዘዙላቸዉ ። ከዚህ በኋላ ኢጣሊያኖች ከመቀሌ እቃቸዉን አንስተዉ በራስ መኮነን እጅ ወደ አዲግራት ከወሎው ሰራዊት ጋር ጉዞ ጀመሩ ።

አፄዉም በጥር 16 ቀን ከመቀሌ ተነስተው ተጉዘዉ ፈለገ ዕዳሮ ሰፈሩ፣ በ17 አጉላ ሰፈሩ፣ በ19 ገንፈላ ሰፈሩ ። ይህ የአዲግራት አካባቢ ስለሆነ ጣሊያን ተደብቆ አደጋ እንዳያደርስ ጥንቃቄ ተጀመረ ። በ20 አብርሀ ወአጽብሀ ሰፈሩ፣ በ21 ሐዉዜን ሰፈሩ ።

ከዚህ እያሉ ፊልተር የተባለዉ ኢጣሊያዊ መጥቶ ከአፄ ሚኒሊክ ድኳን ገብቶ እንዲህ ብሎ ተናገረ ። በእናንተ እጅ ያሉት /መቀሌ ከምሽጉ የወጡት/ ወታደሮቻችንን ወደ እኛ ካለቀቃችሁልን እርቅ ለመጀመር አንችልም አሉ ብሎ ተናገረ ።

አፄ ሚኒሊክም እነዚህን አልነካቸዉም፣ ምን ያደርጉልኛል፣ እንደታጠቁ ይዘሀቸዉ ትሄዳለህ ፡ ነገር ግን ከነ መድፋቸዉና ከነነፍጣቸዉ የምለቅልህ ሞኝ ሆኘ አይደለም፣ መንግስቴን ለማክበር ነዉ፣ የነዚህ ጥቂት መድፍ በእኛ ላይ ለዉጥ አያመጣም ብየ ነዉ ። አሁንም ብትታረቁም ድንቅ፣ ጦርነትም ከከጀላችሁ /ከፈለጋችሁ/ እነዚህን ጨምራችሁ ጠቅላችሁ ኑ ብለዉ ከነመድፋቸዉና ከነነፍጣቸዉ ሰጥተዉ ሰደዱት /አሰናበቱት/ ።

ከዚህ በኋላ አፄዉ በ22ቀን ሀራህር ሰፈሩ፣ በ23 ወርዕ ሰፈሩ፣ በ24 ጸዲያ ሰፈሩ ። በዚህን ጊዜ አዲግራት የነበረዉ ኢጣሊያ እቃዉን ጠቅሎ ወደ እንኪጨዉ እየተጓዘ መሆኑን ሰሙ ። አፄዉም የአዲግራትን ምሽግ እንለቃለን

ያለዉን ቃሉን አክብሯል ጥሩ ነዉ፤ እንደዚሁ በፍቅር ሁሉንም ግዛቴን መልቀቅ አለባቸዉ አሉ ። በ25 ቀን ፈረስ ማይ ሰፈሩ ። በ26 ባላገሩን /ነዋሪዉን/ መንገድ ሲያስጠርጉ ዋሉ ። በ27 ዛታ ሰፈሩ፣ በዚህም ጊዜ የኢጣሊያ ጦር አዲግራትን ለቆ ተጉዞ የሰፈረበትን ስፍራ እንኪጨዉን ለዉጊያ ይመች እንደሆነ በመነፅር ለማየት አፄ ሚኒሊክ እንኪጨዉ አፋፍ ዘለቁ ። እዚህ ላይ እንዳሉ የኢጣሊያዉ ሹም ጄኔራል ባራቴሪ እርቅ እፈልጋለሁ ብሎ ላከ ። አፄዉም እርቅ ከፈለክ ወረቀት ነገር አይፈፅምምና እርቁን የሚጨርስ ደህና ሽማግሌ ላክ ። እኔ ለከብት /ለፈረስና ለበቅሎ/ ከሚመች ሳር ካለበት ቦታ ሰፍሬ እጠብቅሀለሁ ብለዉ ላኩ ። ጣሊያኖች መልእክተኛ የላኩት ለስለላም ጭምር እንደነበር ንጉሰ ነገስቱ ስላወቁ ለጦርነትም ለእርቅም ተጠንቅቀዉ ነበር የሚጠብቁት ።

በ30 ሳር ካለበት ይኃ ላይ ሰፈሩ ። በዚህ ጊዜ ማጆር ሳልሳ የሚባል ኢጣሊያዊ፣ አንድ የኢጣሊያ ወታደርና ብዙ ባሽባዙቆች /ኤርትራዊያን ወታደሮች/ አስከትሎ መጣ ። እቴጌዋም ይህ ሰዉ ለመሰለል እንጂ ለማስታረቅ የመጣ አይመስለኝም ብለዉ ባለሟሎቻቸዉን አስጠነቀቁ ። በዚሁ መስረት ሽማግሌዉ ኢጣሊያዊ ወደ አፄ ሚኒሊክ ከመሄዱ በፊት ራስ መንገሻ /የወሎ ባላባት ሳይንት/፣ ራስ መኮንን /የወሎ ባላባት ሸዋ/፣ ፊታዉራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ /የወሎ ባላባት/ እነዚህ አብረዉ ወደ ተቀመጡበት ተወስዶ የመጣህበትን ጉዳይ ንገረን ብለዉ ጠየቁት ። እሱም ያልተጠበቀ ነገር ተናገረ፤ ባንዲራችን ተተክሎበት የነበረዉን ከአምባላጌ ጀምሮ ያለዉን ቦታ ይተዉልን ሌላ አንነካም ብሎ ተናገረ ።

ይህን ይዘዉ ወደ አፄዉ ሄዱ ። አፄዉም የመጣሁት የተተከለዉን ባንዲራ ላስነሳ ነዉ እንጂ ላጸና አይደለም ። የምትታረቁ ከሆነ ቀድሞ ለነጋዴዎቻችሁ ማረፊያ በአፄ ዮሃንስ ከያዛችሁትና እኔም ካፀናሁላችሁ ቦታ ላይ ሁኑና እርቁ ይጨረስ ። በተረፈ ግን አምላክን ጨምሬ በመጣችሁበት መንገድ እቀበላችኋለሁ ብለዉ መለሱት ።

ማጆርም ሳልሳ እንደ ሄደ ራስ መንገሻ ንግስቲቱ እቴጌ ጣይቱ ወደ አሉበት እልፍኝ ገባ ። ማጆር ሳልሳ የተናገረዉንም ነገር ሁሉ ለእቴጌ ነገራቸዉ ። እቴጌም እየተደነቁ አይናቸዉን ወደ ሰማይ አነሱ ። አምላከ እስራኤል ይህን ግፍ ተመልከት ። መድፋቸዉንና ነፍጣቸዉን ተማምነዉ እንደልባቸዉ

ተናገሩ ። ኃይሉ የመድፍ ሳይሆን የእግዚአብሔር መሆኑን አላወቁም ። እኛ ክርስቶስን ይዘን የእነሱን መድፍ አንፈራዉም አሉ ።

ማጆር ሳልሳም እንደ ደረሰ እንኪጨዉ ላይ የሮማን ባንዲራ ተከለ ። ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስ የሚባሉ የአጋሜ ባላባቶች ከወንድማቸዉ ከራስ መንገሻ /የአድዋ ባላባት የአፄ ዮሃንስ ልጅ/ ከድተዉ ለኢጣሊያ ገብተዉ ነበር ። በዚህ ወቅት ግን ኢጣሊያን ከድተዉ ከነታጠቁት ነፍጥና ከነሰዋቸዉ ሌሊቱን ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ። እነዚህ የመጡት ሰዎች ስለጣሊያኖች ምሽግ አስረዱ ። ኢጣሊያኑ ጉድጓድ ቆፍረዉና ድንጋይ ክበዉ ዉስጥ ተቀብረዉ የወሎን ሰራዊት ማጥቃት እየተጠባበቁ ነዉ ። እነሱን ከጉድጓድ ለማስወጣት የተዋጋን እንደሆነ ጀግኖቻችን ያልቃሉ ብለዉ ተናገሩ ።

አፄ ሚኒሊክም እኔ ጉድጓድ ዉስጥ ተቀብሮ ቢኖር ምንቸገረኝ /ምናገባኝ/ ወደ ዋናዉ ቦታቸዉ እንሂድ ብለዉ፣ ወደ አድዋ ጉዞ ተጀመረ ። የካቲት 2ቀን ገንደብታ ላይ ሰፈሩ፣ በቀጣዩ ቀንም ተጉዘዉ አሳይ ሰፈሩ፣ ጉዟቸዉን ቀጥለዉ በ14 አድዋ ሰፈሩ ። አፄ ሚኒሊክም እዚህ በደረሱ ጊዜ ምናልባት ጣሊያኑ ከምሽጉ ወጥቶ ጦርነት ያሰበ እንደሆነ ብለዉ ራስ ሚካኤልን /የወሎ ባላባት ወረሂመኖ/፣ ራስ ወሌን /የወሎ ባላባት የእቴጌዋ ወንድም የጁ/፣ ራስ መንገሻን /የወሎ ባላባት ሳይንት/፣ ራስ መኮንን /የወሎ ባላባት ሸዋ/፣ ራስ መንገሻ /የአድዋ ባላባት የአፄ ዮሃንስ ልጅ/ እነዚህን በግምባር አሰልፈዉ፣ ግራና ቀኝ ሰፋሪዎቻቸዉንም በግራና በቀኝ አሰልፈዉ መጠበቅ ጀመሩ" ይላል ።

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴል-ኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለዉ መጻህፋቸዉ ካሳፈሩትና በዓለማየሁ አበበ ከተተረጎመዉ መጻህፍ ዉስጥ ፡ -

"በዚህ በአድዋ ጦርነት የኢትዮጵያ ጦር አሰላለፍ የሚከተለውን ይመስላል ።

1. እራሳቸዉ አፄ ምኒሊክ ከ30ሺ ሰራዊት ጋር (ወሎ ሸዋ)
2. እቴጌ ጣይቱ ከ3ሺ ሰራዊት ጋር (ወሎ የጁ)
3. ንጉስ ሚካኤል ከ8ሺ ሰራዊት ጋር (ወሎ ወረሂመኖ አማች)
4. ራስ መኮንን ከ8ሺ ሰራዊትጋር (ወሎ ሸዋ የአፄዉ አክስት የልጅ ልጅ)

5. ፊትአዉራሪ ገበየሁ ገቦ ከ6ሺ ሰራዊት ጋር (ሰራዊቱ ወሎ)
6. ዋግሹም ስዩም ጓንጉል ከ6ሺ ሰራዊት ጋር (ወሎ ሰቆጣ)
7. ራስ ወሌ ከ3ሺ ሰራዊት ጋር (ወሎ የጁ የእቴጌ ወንድም)
8. ራስ መንገሻ ከ3ሺ ሰራዊት ጋር (ወሎ ሳይንት) ።
9. ንጉስ ተክለሐማኖት ከ3ሺ ሰራዊት ጋር (የጎጃም ባላባት፣ በጥርጣሬ) ።
10. ራስ መንገሻ ከራስ አሉላና ከራስ ሀጎስ ጋር ከ3ሺ ሰራዊት ጋር (ትግራይ)

በድምሩ 73ሺ የጦር ሰራዊት ይሆናል ። /ከላይ እንደምናየው 67ሺ የሚሆነዉ ሰራዊት ከወሎ የተሰበሰበ ነዉ፣ 9ኛና 10ኛ ላይ ከተጠቀሱት ባላባቶች በድምሩ 6ሺ ሰራዊት ብቻ ነው ከሌላ ቦታ የመጣው/ ።

ጣሊያኖች የአምባላጌዉንና የመቀሌዉን ሽንፈታቸዉን ገምግመዉ የወሎ ጦር /የንጉሰ ነገስቱ ጦር/ እንደ ገመቱት ቀላል እንዳልሆነ በማመን ለአድዋዉ ጦርነት ከፍተኛ ዝግጅት አደረጉ ። እናም የወቅቱን የመጨረሻዉን ዘመናዊ የጦር መሳሪያ አይነት የታጠቀውንና በ60 መድፎች የታጀበውን ከ20ሺ በላይ ጦራቸውን በሚከተለዉ መልኩ አሰለፉት ። የጦር ካርታ ካዘጋጁ በኋላ በካርታዉ መሰረት ሰራዊታቸዉን ለ4 ከፍለዉ በአንደኛዉ ግንባር ጄ/ል አርሞንዲን፣ በ2ኛዉ ጄ/ል ዳቦርሚዳንን፣ በ3ኛዉ ጄ/ል አልበርቶኒን፣ በ4ኛዉ ጄ/ል ኤሌናን አድርገዉ በአራቱም አቅጣጫ አሰለፏቸዉ” ይላል ።

ወደ ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ስንመለስ “ነገር ግን ይህ ከላይ የተገለፀዉ የንጉሰ ነገስቱ የሰራዊት ቁጥር አጠቃላይ እንጂ ጦርነት ላይ የተሳተፈዉ አንድ እጁ (1/3ኛዉ) ብቻ ነዉ ። አብዛኛዉ (2/3ኛዉ) አክሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን ለመሳም ሄዶ ስለነበር ለጦርነቱ አልደረሰም ።

ኢጣሊያዎች የወሎን /የንጉሰ ነገስቱን/ ወታደሮች እያታለሉ ለመፍጀት አሰቡ ። ከምሽጋቸዉ ወጥተዉ ጦርነት ይጀምሩና የወሎ ወታደር ወደ እነሱ ሲሄድ ፈጥነዉ ተመልሰዉ ወደ ምሽጋቸዉ ገብተዉ ይታኮሳሉ ። የወሎ ሰራዊትም ስንጠጋዉ ምሽግ ዉስጥ ይገባል ስንመለስ ይወጣል እንዲህ እያደረገ እየተጫወተብን ነዉ ብሎ ተናደደ ። መኳንንቱም ተሰብስበዉ ማለዳ እዚያዉ

ካለበት ምሽግ ድረስ ሄደን እንዋጋለን ብለዉ መከሩ፤ ንጉሰ ነገስቱም ተስማሙ ።

ይህ ምክር እንዳለቀ የትግሬዉ ገዥ ራስ መንገሻ መጥቶ አንድ ነገር ልናገር ይፍቀዱልኝ ብሎ ወደ ንጉሰ ነገስቱ ቀርቦ እንዲህ አለ፤ ምሽግ በር ድረስ ሄደን ይህን ሁሉ ጀግና ልናስፈጀዉ ነዉን? አፄ ዮሃንስ መተማ ሄደዉ እንጨት ምሽግ ስር ሄደዉ ያን ሁሉ ህዝብ አስፈጁ፣ እኛም አሁን ከካብ ስር ሄደን ይህን ሁሉ ሰዉ እናስፈጅ! ብለው ተናገሩ ። ይህ ምክር የተሰማ ምክር ሆነ፤ ሁሉም ተስማሙ ። አፄ ሚኒሊክም እንግዲህ ከጉድጓዱ ወጥቶ ባይኔ ካላየሁት በቀር ተሰልፌ አልሄድም ብለዉ ተናገሩ ። ትንሽ ቀን አይተነዉ ወጥቶ የማይዋጋ ከሆነ አልፈን ወደ ሐማሴን /ኤርትራ/ እንሄዳለን ብለዉ ተስማሙ ።

ኢጣሊያኑም ቢጠበቁ ቢጠበቁ ከምሽጋቸው አልወጣ በማለታቸው ወደ ሐማሴን ለመሻገር የካቲት 21 ቀን መኳንንቱ ተሰብስቦ መክሮ ቁርጥ ዉሳኔ ተወሰነ ። በበነጋዉ ወደ ሐማሴን ለመሻገርም ቀኝ አዝማች ታፈሰ /የወሎ ባላባት/ ታዞ ምንገድ ጠረጋ ተጀመረ ።

ነገር ግን በዚያን ቀን ሌሊት ያልተጠበቀ ክስተት ተከሰተ ። በዚያን ቀን ሌሊት የዘቡ ተራ የትግሬው ራስ መንገሻ ነበር ። 500 ነፍጥ የያዙ የራስ መንገሻ ሰዎች ዘብ ሲጠብቁ የካቲት 22 ቀን ሌሊት በ11 ሰዓት የኢጣሊያ ጦር ተሰልፎ መጥቶ ድንገተኛ አደጋ ካደረሰ በኋላ ዘበኞቹ ጋር ተኩስ ጀመረ ። ሆኖም እንደ እስከዛሬዉ ተመልሶ ወደ ምሽጉ መግባቱ አይቀርም ተብሎ ብዙም ትኩረት አልተሰጠዉም ነበር ።

ነገር ግን መንገድ ለመጥረግ ሄዶ የነበረዉ ቀኝ አዝማች ታፈሰ፣ በፈረስ እየሮጠ ንጉሰ ነገስቱ ዘንድ ደረሰ ። ከደረሰም በኋላ እንዲህ ብሎ ተናገረ፤ የኢጣሊያ ሰራዊት በ4 ጀኔራሎች ጠቅሎ እየመጣ ነዉ ። በግምባር አንድ ጀኔራል፣ በአባ ገሪማ በኩል አንድ ጀኔራል፣ በማሪያም በኩል አንድ ጀኔራል፣ በሸዊቶ በኩል አንድ ጀኔራል ሆነዉ እየተጠጉ ነዉ ብሎ ተናገረ ። አፄ ሚኒሊክም እንደዱሮዉ አሰልፎን ሊመለስ ነዉ እንጂ እዉነት ይዋጋል ብለህ ነዉ ብለዉ መለሱለት ። ቀኛዝማች ታፈሰ ግን ዛሬስ እርግጥ ነዉ አለ ። በዚህን ጊዜ አፄው በጅሮንድ ተሰማንና የፈረስ ዘበኛዉን ሂዱ ሰልሉ ብለዉ ላኳቸዉ ። ጦሩንም ታጠቅ /ተዘጋጅ/ ብለዉ አዘዙ ። እሳቸዉም የጦር ልብሳቸዉን ለብሰዉ ወደ አዳራሹ ድኳን ሄደዉ ተቀመጡ፤ በዚህ ጊዜ ነጋ ። የወሎ

አብዛኛዉ /2 እጅ የሚሆነዉ/ ሰራዊት አክሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን ለመሳም ሄዶ ስለነበር ለጦርነቱ አልደረሰም ። ዘበኞቹም ከ11ሰዓት ጀምረዉ እስኪ ነጋ ድረስ ይታኮሱ ነበር ።

የኢጣሊያ ዋናዉ ጦር ስለተጠጋ ግምባር ሰፋሪዉና ግዙፉ የራስ ሚካኤል ጦር ቀድሞ ዘበኞቹን ተቀላቅሎ በግምባር ተሰለፈ፤ የኢጣሊያ ዋናዉ ጦርም ደረሰ /አንባቢያን ፀሐፊ ትእዛዝ መፅሐፍ ውስጥ ከራስ ሚካኤል ጦር ውጭ ሌላ የተጠቀሰ ጦር የለም/ ። አፄ ሚኒሊክም በቅሎ ላይ ሆነዉ ወደ ራስ ሚካኤል ሄዱ ። የራስ ሚካኤል ሰራዊትም ክምር እንዳየ ዝንጀሮ ወደ ጠላት መድፍ ይሮጥ ጀመር ። ከየአቅጣጫዉ የመጣዉ የኢጣሊያ ጦር በነጎድጓድ የታጀበ የጥይት በረዶዉን ያወርደዉ ጀመር ። ወሎዎቹም የጥይት በረዶዉን የዝናብ ያህል እንኳ አይፈሩትም ነበር፤ ጦርነቱን ልክ ደስ እንደሚያሰኝ የጨዋታ ዓይነት ነው የቆጠሩት ። ቆስሎ የወደቀዉም ሰዉ ኋላ ስትመለስ ታነሳኛለህ ወደፊት ሂድ በመሀይም አንደበቱ ገዝቸሀለሁ ይል ነበር ። የኢጣሊያ 4ቱም ጀኔራሎች በፍጥነት ወደ ተከላካይነት ተቀየሩ ። ዉጊያዉ በፍጥነት ወደ ጨበጣ /ወደ ጎራደና ጦር/ በመቀየሩ፣ ጣሊያኖቹ በቦታቸዉ ተኘተዉ መተኮስ ስላልቻሉ ከተኙበት እየተነሱ ወደ ኋላ እያፈገፈጉ መታኮስ ጀመሩ ። የኢትዮጵያም ጦር የኢጣሊያን ጦር እየተከተለ በጎራደ ይፈልጠው ጀመር ። ሰዉም ከመንገዱ እርዝመት የተነሳ እየደከመዉ እየተቀመጠ እንደገና እየተነሳ ወደ ፊት ይሮጥ ነበር ።የሰራዊቱ እሩጫ በጣም ፈጣን ስለነበር አፄ ሚኒሊክ ወደ ኋላ ቀርተዉ ነበር ። እቴጌዋ ደግሞ ትንሽ መፍጠን ችለዉ ነበር ። አፄ ሚኒሊክም ጦሩ ጋር በደረሱ ጊዜ አቡነ ማቴዎስ ካህናቱንና ታቦተ ማሪያምን አሲዘዉ በታቦቷ በኋላዋ በኩል ቁመዉ፣ እቴጌ ጣይቱም ከአቡነ ማቴዎስና ከታቦተ ማሪያም አጠገብ ከዘበኞቻቸዉ ጋር ቆመዉ አገኞቸዉ ።

በዚህ ጊዜ ከቀኑ 4ሰዓት ነበር ። ተኩሱ አያባራም፤ በኖጎ ሰማዩ ተቀዶ መሬትን አጠፋ እንደሚባለዉ ይመስል ነበር እንጂ በሰዉ እጅ እየተተኮሰ አይመስልም ነበር ። ቀድመው የገቡት የእነ ራስ ሚካኤል ጦር ያሉበት አካባቢ ጫፍ እስከ ጫፍ በጭስ ተሸፍኗል፤ አይታይም ፡ ጭሱ በፈጠረዉ የጭስ ደመና ምክንያት እነ እቴጌ በቆሙበት አካባቢ ፀሀይ አልነበረም ። ሁሉም ሰው ጭሱ ውስጥ ገብቷል የሚታይ ነገር የለም ። እሳትና ጭስ የሚፈነጥቅ የነጎድጓድ ድምፅ ጫፍ እስከ ጫፍ ይንተገተጋል /የዚህን ጦርነት ሁኔታ በቃላት መግለፅ አይቻልም/ ። እቴጌዋም በዚያን ጊዜ ጫማቸዉን አዉልቀዉ በባዶ እግራቸዉ

ሆነዉ፣ በግምባራቸዉ ተደፍተዉ፣ በጉልበታቸዉ ተምበርክከዉ፣ ድንጋይ ተሸክመዉ ወደ እግዚያብሔር እያመለከቱ ያለቅሱ ነበር፤ ፀሀይ የመሰለዉ ፊታቸዉ በለቅሶ ብዛት ፅልመት ለበሰ ። በዚህ ሰዓት ሌላ ድንገተኛ ክስተት ተከሰተ ።

ንጉሰ ነገስቱ ከቆሙበት ከቢ ላይ የመድፍና የነፍጥ በረዶ ወረደ፤ ተኩሱ የኢጣሊያ የደጀን /የተጠባባቂው/ ጦር ተኩስ ነበር ። ግምባር ላይ የነበረዉ የኢጣሊያ ጦር በሩጫ እየሸሸ በመሆኑ የደጀን ጦሩን አልፎት ሄዷል ። በዚህ ምክንያት የኢጣሊያው የደጀን ጦር ከኋላ ካሉት ከእነ አፄ ሚኒሊክ ጋር ተገናኘ /አንዳንዶች ይህ ተንኮል አለበት ይላሉ፤ እዚህ ላይ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ ጣሊያን አስቦበት ላይሆን ይችላል /by difault ሊሆን ይችላል/፤ ምክንያቱም የኢጣሊያ ጀኔራሎች ጦርነቱ ከቁጥጥራቸዉ ዉጭ ሆኖ ስለነበር አፄዉን ለመግደል የሚያስቡበት ፋታ አልነበራቸዉም፤ ሆኖም ግን ይህን ጉዳይ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም/ ።

እናም የደጀን ጦሩ የጥይት ዶፉን ከእነ አፄ ሚኒሊክ ላይ ያወርደዉ ጀመር ። ይህ ከባድ ጦርነት በተሰማ ጊዜ እየሸሸ የነበረዉ የኢጣሊያ ጦርም አቅጣጫዉን እየቀየረ እንደ ሳር እንደ ቅጠል እልፍ /እጅግ ብዙ/ ሆኖ ተመልሶ መጣ ። የተኩሱም መጠን እየባሰ መጣ ። የወሎ ወታደር አብዛኛዉ ጥይት ጨርሶ በጎራደ ነዉ የሚዋጋዉ ። ኢጣሊያዉያኑ ኃይላቸዉን አሰባስበዉ የመጨረሻዉንና ከፍተኛዉን አቅማቸዉን የወሎ ሰራዊት የኋለኛዉ ሰልፍ ላይ ተጠቀሙ ። የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጀ/ል አልበርቶኒ በፍጥነት በርካታ መድፎቹ እየተማረኩበት ስለሆነ “ሻርፐኔል” የተባለዉን የዘመኑን ሀይለኛ ቦምብ እንዲተኮስ አዘዘ ። በዚህ ሀይለኛ ቦምብ ምክንያት የወሎ ሰራዊት የኋላ ሰልፍ መወዝወዝ ጀመረ ። የዚህ ጊዜ እቴጌዋ ድምፃቸዉን ከፍ አድርገዉ አይዞህ እንጂ አንተ ምን ሆነህል፣ ድሉ የእኛ ነዉ፣ በለዉ እንጂ እያሉ ሲጮሁ ሰራዊቱም የእቴጌዋን ሁኔታ ባየ ጊዜ ሴት ልጅ በወኒ እንደዚህ እየሆነ ወንድ መሸሽ አይሆንለትምና አዲሱ ቦምብ ፍፁም ቢበረታበትም መተናነቁን ቀጠለ ። በርካታ የወሎ ልጆች የሚወዷትን ህይወታቸዉን እጅግ ለሚወዷት ሀገራቸዉ ሰጡ ። ለሀገራቸዉ ያለቻቸዉን እጅግ ዉድና የመጨረሻ ስጦታቸዉን እየሰጡ መዉደቃቸዉን ቀጠሉ ።

እቴጌም ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ ተቀየሩ፣ የሴቶችን ባህሪ ትተዉ እንደተመረጠ የጦር አርበኛ ሆኑ ። እቴጌዋ ነፍጠኞቻቸዉን በግራና በቀኝ

ካሰለፉ በኋላ መድፈኛ አሽከሮቻቸዉን በግምባር አሰልፈዉ “ስድስት ሐኪስ” የተባሉትን መድፎች እያስተኮሱ በፍፁም ጀግንነት ገብተዉ በመካከል በጣም ተጠናክሮ አስቸግሮ የነበረዉን የኢጣሊያ ጦር በተኑት ። በዚህ ጊዜ ኢጣሊያዊያኑ እንደገና በየአቅጣጫዉ ሸሸት ጀመሩ ። አያሌ የኢጣሊያ አርበኞች ከፉኛ ወደቁ /አለቁ/ ።

ህየ ይወድቁ ኩሎሙ ገበርተ አመፃ፤ ይሰደዱ ወኢይክሉ ቀዊመ እንዳለ፤ የወሎ ወታደር እየተከተለ የራቀዉን በፋዚግራ፣ የቀረበዉን በጎራደ ራስ ራሳቸዉን እየፈለጠ፣ በጦር እየወጋ አብዛኛዎቹን ጣሊያኖች አስቀራቸዉ ። አብዛኛዎቹ ኢጣሊያዊያንና ባሽባዙቆች /ኤርትራዊያን/ አለቁ ። ሸሽቱም ጠናባቸዉ /ባሰባቸዉ/፤ ከዚህ በኋላ ኢጣሊያዉ አልቆመም፤ ተበታትኖ በተናጠል ነፍሴ አዉጭኝ አለ ። የወሎ ወታደርም እየተከታተለ መረብን አሻገረዉ” ይላል ።

የእቴጌ ጣይቱ የጀግንነት ሚስጥር ምንድን ነዉ? እቴጌ ጣይቱ ከየት መጡ?

ስለእቴጌ መነን 1ኛ ንቁ ፖለቲካዊ ተሳትፎና ጀግንነት ቀደም ሲል በአፄ ቴዎድሮስ ስር አይተናል ። እቴጌ ጣይቱና እቴጌ መነን 1ኛ የአንድ ወረዳ ሰዎች ናቸዉ ። ሁለቱም በወሎ ክ/ሀገር የየጁ ወረዳ ሰዎች ናቸዉ ። የእቴጌ መነን ጀግንነት ደግሞ እንኳን የጁ በመላዉ ኢትዮጵያ ሲወራ የኖረ ነዉ ። እናም እቴጌ ጣይቱ ጀግና የሆኑት የወረዳቸውን ልጅ እቴጌ መነንን እንደ አርአያ /ሞዴል/ በመዉሰድ ነዉ ተብሎ ይገመታል ። እቴጌ መነን በጣም ሰዉ አማኝና የዋህ ሲሆኑ እቴጌ ጣይቱ ደግሞ በጣም ተጠራጣሪ ናቸዉ ። ይህም የሆነበት ምክንያት እቴጌ መነን ካሳ ሀይሉን /ቴድን/ አምነዉ መንግስታቸዉን ተነጥቀው የደረሰባቸውን እንግልትና ስቃይ ስለሚያውቁ ነዉ ። እናም የእቴጌ ጣይቱ ጀግንነትና ንቁ ፖለቲካዊ ተሳትፎ የመጣዉ ከእቴጌ መነን ነዉ ማለት ይቻላል ።

ስለ እቴጌ ጣይቱ ወደ ምድር አመጣጥ ቀደም ሲል እንዳስቀመጥነዉ፣ ስለአንደኛዉ የእቴጌ ጣይቱ የዘር ሀረግ አለቃ ታዬ “የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ” በሚለዉ መፅሀፋቸዉ ያሰፈሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ “የወረሴሆች ነገርና ትዉልድ እንዲህ ነዉ፤ ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን ባጠፋ ጊዜ ከባህር ማዶ

ከአረብ አገር ሼህ ዑመር የሚባል የብር ዘንግ የብር ርከት አሲዞ መጥቶ በወሎ የጁ ተቀመጠ ። ሸህ ዑመር ብዙ ሴቶች አግብቶ ብዙ ልጆችን ወለደ ። መንደሩ ቢበዛ ወረ ሺህ ተባለ ። አሁን ወረሴህ የሚባሉት የእሱ ዘሮች ናቸዉ ።

ከሼህ ዑመር ልጆች የበህሩ /የመጀመሪያዉ/ ወሌ ይባል ነበር ። ወሌ አብዬን ወለደ ። አብዬ ሲወልድ ልጁን ባባቱ ስም ወሌ አለው ። ወሌ አባ ገትዬን ወለደ ። አባገትዬ አባ ሴሩ ጓንጉልን ወለደ ። አባ ሴሩ ጓንጉል ክርስትና ተነስቶ የላስታና የሰለሞን ባላባት የራስ ፍሬስን እህት ወ/ሮ ገለቡን አግብቶ ራስ ዓሊን፣ ወ/ሮ ከፈይን፣ ራስ አሊ ጋዝን ወለደ ። ወ/ሮ ከፈይ የኢልማ ፆርማን ባላባት መርሶ በሬንቶን አግብተዉ ራስ ጉግሳን፣ ደጃች አሉላን ወለዱ ። ራስ ጉግሳ ወ/ሮ ሎሚ ታን አግብተዉ ራስ ማርዬን፣ ራስ ይማምን፣ ራስ ዶሪን፣ ወ/ሮ ሂሩትን ወለዱ ። /በዘመነ መሳፍንት ርዕስ ስር እንዳስቀመጥነው/ ወ/ሮ ሂሩት አባቷ ራስ ጉግሳ ነግሶ የደብረታቦር ከተማን በመሰረተበት ወቅት ቀደም ብለው በአፄ ሱስንዮስ ተሹመው ከወሎ ወግዲ /ቦረና/ ሄደው ሰሜንን ሲያስተዳድሩ ከኖሩት ከኤሎስ የዘር ሐረግ የተወለደውን የሰሜኑን ባላባት የራስ ገብሬን ልጅ ደጃች ኃይለ ማሪያምን አግብታ ደጃች ብጡልን፣ ደጃች መርሶን፣ ወ/ሮ የዉብ ዳርን ወለደች ። ደጃች ብጡል የሜጫይቱን አሮሞ ወ/ሮ የዉብ ዳርን አግብተዉ እቴጌ ጣይቱን፣ ፊታዉራሪ አሉላን፣ ራስ ወሌን፣ ወ/ሮ ደስታን ወለዱ ። እቴጌ ጣይቱ የዳግማዊ ምኒሊክ ሚስት መካን ናቸዉ ። ፊታዉራሪ አሉላ ወ/ሮ የተመኘን ወለዱ ። ራስ ወሌ ራስ ጉግሳ፣ ወ/ሮ ከፈይን፣ ደጃች አመዴን፣ ደጃች ኃይሉን ወለዱ ። ወ/ሮ ደስታ ደጃች ወልደ ሀናን አግብተዉ ደጃች ገሰሰን፣ ወ/ሮ አሰለፈችን ወለዱ ። ደጃች መርሶ ደጃች ትኩን፣ ወ/ሮ ላቀችን ወለዱ ። ራስ አሊ ጋዝ ደጃች ጎጅን፣ ደጃች ብሩን ወለዱ ። ደጃች ጎጅ ልጅ ዘለቀን ወለዱ ። ልጅ ዘለቀ አባ ግርሻን ወለዱ ። ደጃች ብሩ ደጃች ዘገየን ወለዱ ። ደጃች ዘገየ ደጃች ጓንጉልን፣ ደጃች አሊን፣ ደጃች አሊ ጋዝን፣ ወ/ሮ ሂሩትን፣ ደጃች ኃይሉን ወለዱ ። ደጃች ጓንጉል ደጃች ይማምን፣ ደጃች አሊን ወለዱ" ይላል ።

ስለ እቴጌ ጣይቱ ሁለተኛ የዘር ሀረግ ጸሓፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴ "ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ሚኒሊክ በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ያሰፈሩት ቃል በቃል ሲቀመጥ "ኤሎስ የተባለ ሰዉ ከወሎ ወግዲ /ቦረና/ ሄዶ ሰሜንን ከባምብሎ በመለስ ተከዜ በፈሰስ በአፄ ሱስንዮስ ተሹሞ ይገዛ ነበር ። ኤሎስ ቁርሎስን ወለደ ።

ቁርሎስ ኤራቅሊስን ወለደ ። ኤራቅሊስ የንጉሱን ልጅ ወ/ሮ ሰማዕታን አግብቶ ተስፋን ወለደ ። ተስፋ ማሪቱን ወለደ ። ማሪቱ ያበርገሌዉን ደጃች ወ/ ፋኤልን አግብታ ራስ ገብሬን ወለደች ። ራስ ገብሬ ከበየዳ የክፍለ እየሱስን ልጅ ወ/ሮ ሳህሊቱን አግብቶ ደጃች ኃይለማሪያምን ወለደ ፡ ደጃች ኃይለማሪያም ደብረታቦር ከተማ በተመሰረተችበት ጊዜ የየጁዉን የራስ ጉግሳን ልጅ ወ/ሮ ሂሩትን አግብቶ ደጃች ብጡልን፣ ደጃች መርሶን፣ ወ/ሮ የዉብዳርን ወለደ ። ደጃች ብጡል የሜጫይቱን ኦሮሞ ወ/ሮ የዉብ ዳርን አግብተዉ እቴጌ ጣይቱን፣ ፊታዉራሪ አሉላን፣ ራስ ወሌን፣ ወ/ሮ ደስታን ወለዱ" ይላል ።

በዚህ የአድዋ ጦርነት 5ሺ ጣሊያናዊ ነጭ ወታደሮች፣ 2ሺ ባሽባዙቆች /ከኤርትራ የተመለመሉ ወታደሮች/ የሞቱ ሲሆን፣ 2500 ቆስለዉና 2400 የሚሆኑት ከ60 መድፍና ከብዙ ዘመናዊ መሳሪያወቻቸዉ ጋር ተማርከዉ ጦርነቱ ተጠናቀቀ ። ጄ/ል ዳቦር ሚዳና ጄ/ል አርሞንዲ ሲገደሉ፣ ጄ/ል አልበርቶኒ ቆስሎ ተማረከ ። ጄ/ል ኤሌና ብቻ በሽሽት ማምለጥ ቻለ ።

የወሎዉ ወታደርም ''ተኝቶ መተኮስ የፈሪ ነዉ'' እያለ ቆሞ ይዋጋ ስለነበር ብዙ ጀግኖች እንደ ቅጠል ረግፈዋል ። አጠቃላይ የሟች ቁጥርም 10ሺ እንደነበርም የብዙዎች ግምት ነዉ ። በዚህ ጦርነት ዉስጥ እቴጌ ጣይቱ፣ ፊታዉራሪ ገበየሁና ሰላዩ አዉአሎም ጎላ ያለ ዉጤት አስገኝተዋል ። ፊታዉራሪ ገበየሁ ገቦ ጦርነቱ ላይ ቢሰዋም፣ ሰላዩ አዉአሎም ከመሰዋእትነት ተርፎ ለፈፀመዉ ጀብዱ ከአፄ ሚኒሊክ ተገቢዉን ወረታ አግኝቶ የእንትጮ ወረዳ አስተዳዳሪነትን አግኝቶ እድሜዉን በደስታ ጨርሶ በ78 አመቱ ከዚህ አለም በሞት ተለየ ።

እናም በዚህ በወሎ ወጣቶች ከፍተኛ መሰዋዕትነት በተገኘዉ ድል፣ ኢጣሊያ አንገቷን ደፋች ። ይህ በታላቅ ተጋድሎና መሰዋዕትነት የተገኘዉ የአድዋ ድል የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ስለነበር፤ ይህ እለት THE BLACK HISTORY MONTH እየተባለ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚከበር እለት ሆኗል ።

ከሞትና ከምርኮ የተረፉት የኢጣሊያ ወታደሮችም ከአድዋ ተበታትነዉ እየሸሹ ወደ አዲ ሐይቅ ሲጓዙ የወሎ ወታደሮች ተከታትለዉ እያሳደዱ ከመረብ ወዲያ አሻግረዋቸዉ ተመለሱ" ይላል ።

እዚህ ላይ አንድ ትልቅ ጥያቄ አለ ። የወሎ ወታደሮች መረብን ያልተሻገሩበት ምክንያት ምንድን ነዉ? የአቅም ማነስ ነዉ ሊባል አይችልም ። ምክንያቱም የኢጣሊያ ሰራዊት ተበታትኖ ነፍሱን ለማዉጣት ነበር የሚሮጠዉ ፡ በእርግጥ እንደገና ተደራጅተዉ የተወሰነ መከላከል ማድረጋቸዉ አይቀርም ነበር ። ሆኖም ግን እስካሁን ከተከፈለዉ መሰዋእትነት አንፃር ሲታይ በትንሽ ተጨማሪ መሰዋእትነት ኤርትራን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ይቻል ነበር ።

የኤርተራዊያንም ጥያቄ ይኸዉ ነዉ ። ለመቀሌና ለአድዋ ስትሉ ከአዲስ አበባ 4ወር ተጉዛችሁ ያን ሁሉ መሰዋእትነት ስትከፍሉ፣ ለእኛ ግን ከተበታተነ ሰራዊት ልታጋጥማችሁ የምትችለዉን ትንሽ ተጨማሪ መሰዋእትነት እንኳ መክፈል አልፈለጋችሁም ። ያን ሁሉ ከተጓዛችሁና ያን ሁሉ መሰዋእትነት ከከፈላችሁ በኋላ እኛ ጋር ስትደርሱ ድርቁና የከብቱ ማለቅ ትዝ አላችሁ ። የኢጣሊያ ሰራዊት ተበታትኖ ነፍሴ አዉጭኝ እያለ ባለበት ሰዓት ትንሽ ተጨማሪ መሰዋእትነት ብትከፍሉ ኖሮ ነፃ ታወጡን ነበር ። ይህ ባለመሆኑ ምክንያት እናንተ ቅኝ ግዛትን ለ40 አመት /ጣሊያን ተመልሶ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ/ ያህል ስታሸንፉ እኛ ግን ከ50 አመት በላይ ተገዛን ወዘተ ይላሉ ።

ምክንያቱ ግን ኤርትራዊያን እናንተ ለኛ አንድም መታደር መሰዋት አትፈልጉም እንደሚሉት ሳይሆን ከአድዋ ድል በኋላ የታየዉ ሁኔታ ነበር ። የአድዋ ድል በአለም ከተሰማ በኋላ፣ አንገታቸዉን ደፍተዉ ቅኝ እየተገዙ የነበሩ የአፍሪካ አገሮች ዉስጥ የተለየ ሁኔታ መታየት ጀምሮ ነበር ። በጥቁሮች ዘንድ በኢትዮጵያ የመመካት አይነት እንደ ኢትዮጵያ የሚሉ ቃላቶች እየበዙ ነበር ። የኢትዮጵያ ዝና ግዛቷን ከማስመለስ አልፎ ቢሄድ ኖሮ፣ ጣሊያኖች በአየርና በባህር ወደ ሀገራቸው ሸሽተው ቢሆን ኖሮ፣ የጥቁሮች እንቅስቃሴ ጨምሮ፣ እንደ ፈረንሳይ ያሉ አብዛኛዉ ቅኝ ግዛታቸዉ አፍሪካ ዉስጥ የሆነ አገሮች ችግር ዉስጥ ይገቡ ነበር ። ይህ ከሆነ ደግሞ እነ ፈረንሳይ፣ ጥቁሮች እንደገና አንገታቸዉን ደፊተዉ እንዲገዙ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርን መምታታቸዉ አይቀርም ነበር ። ይህ ደግሞ ለማንም ግልፅ ነዉ ። በዚህ ምክንያት ነዉ አፄ ሚኒሊክ ገበሬዉ ከብቶቹ በድርቅ ስላለቁበት ከዚህ በኋላ ሊዋጋ /ሌላ ጠላት ቢነሳ ለማለት ነዉ/ ስለማይችል ዉጊያዉ መቆም አለበት ያሉት ።

ጂ.ኤፍ. ኤ ባርክሌይ የተባለ እንግሊዛዊ ጸሀፊ ስለ አድዋ ድል የተሰማዉን ስሜት ሲገልጽ “ድሉ በአፍሪካ ዉስጥ አዲስ ሀይል የመነሳቱ ምልክት ነዉ ።

የዚያ ክፍለ አለም ሰዎች ልናስታዉሰዉ የሚገባን የወታደር ሀይል እንዳላቸው አሳዉቆናል" ብሏል ። ስለዚህ የአፄ ሚኒሊክ ዉሳኔ ትክክል ነበር ማለት ነዉ ።

ሆኖም ለትግሬዎች ከሁለት ተከፍሎ መቅረት ተጠያቂዎቹ ራሳቸዉ የትግራይ ህዘቦች ናቸዉ ። ምክንያቱም ሁለት ጊዜ ሁሉ የተከፈሉት የእራሳቸዉ ሰዎች በነገሱበት ወቅት ነዉ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ትግሬዎች የተከፈሉትና ኤርትራ የሚል ስም የወጣዉ በአፄ ዮሃንስ ዘመን ነዉ ። ለሁለተኛና ለመጨረሻ ጊዜ የከፈላቸዉ ደግሞ የእራሳቸዉ በኢሳያስ አፈወርቂ የሚመራዉ ሻዕቢያ /ቃሉ አረብኛ ነዉ/ የሚባል ቡድን ነዉ ። ሻቢያ የጀብሐ አንድ ክፋይ ነው ። ጀብሐ ግብፅ ካይሮ ዉስጥ በይፋ የተመሰረተዉ አፄ ኃይለስላሴ አባይን ለመገደብ ጥናት እያደረጉ ባለበት ወቅት ነበር ። አሁን አባይ እየተገደበ ያለበት ቦታ በኃይለስላሴ በተደረገዉ ጥናትም የተመረጠዉ ይህዉ ቦታ ነበር ። እናም በዚሁ ወቅት ግብፅ ጀብሐን መሰረተች ። ጀብሐም የኢትዮጵያ መንግስትን መታገል ጀመረ ። በኋላ ላይ በመካከላቸዉ በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት ጀብሐ ለሁለት ተከፍሎ አንድኛዉ ክፋይ /ጀብሐ/ ቀስ በቀስ እየሟሸሸ ሲጠፋ ሌላኛዉ ክፋይ /ሻዕቢያ/ ጀብሐን አጥፍቶ ብቸኛ የኤርትራ ተወካይ ሆኖ፤ ትግሬዎችንም ለሁለተኛና ለመጨረሻ ጊዜ ከፈላቸዉ ።

ትግሬዎች እንደገና ይገናኙ ይሆን ወይ? ብለን ያልን እንደሆነ፣ እንደ ትግሬዎቹ ሁኔታ ከሆነ ሊገናኙ አይችሉም ። ምክንያቱም የተከፈለባቸዉን ብሄራቸዉን አንድ የማድረግ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ቀርቶ ሀሳቡም ያለዉ ትግሬ አይገኝም ። ስለዚህ ትግሬዎች እስከ መጨረሻዉ ተለያይተዋል ።

ወደ ርዕሳችን ስንመለስ፣ ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ "አፄ ሚኒሊክ ግዛታቸዉን ካስመለሱ በኋላ ምርኮኛዎቻቸዉን ይዘዉ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመሩ ። ሚየዝያ 8 ቀን አዲስ አበባ ሲገቡ ህዝቡ በታላቅ ደስታና እልልታ ተቀበላቸዉ ።

ከአድዋ ድል በኋላ ኢተዮጵያ በፍጥነት ወደ ዘመናዊ አገርነት መራመድ ጀመረች ። ሌተናል ጄ/ል ጂ.ላ. ሀሪንግተን ከእንግሊዝ፣ ሌዎንስ ላጋርድ ከፈረንሳይ፣ ጄ/ል ከላሶዉን ከሞስኮ፣ ካፒቴን ቺኮዲካላን ከኢጣሊያ ተልከዉ

መጥተዉ የሹመት ደብዳቤቸዉን ለአፄ ሚኒሊክ አቅርበዉ ሌጋሲዮናቸዉን እየከፈቱ ተቀመጡ ፡፡

አፄ ሚኒሊክ ከሁሉም መንግስታት ጋር ግንኙነት ያድርጉ እንጂ ትኩረታቸዉ ግን ከፈረንሳይ ጋር ነበር ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ብለዉ ከጂቡቲ እስከ ሐረር፣ ከሐረር እስከ እንጦጦ፣ ከእንጦጦ እስከ ከፋ፣ ከዚያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ የባቡር ሀዲድ ለማስገንባት ከፈረንሳይ የምድር ባቡር ኩባንያ ጋር ተፈራርመዉ ስለነበር የሀዲድ ግንባታዉም ከጦርነቱ በፊት በ1884 ዓ.ም ተጀምሮ እየተሰራ ስለነበር ነዉ ፡፡ ሆኖም ኩባንያዉ የገንዘብ እጥረት ስላጋጠመዉ ከጂቡቲ አዲስ አበባ ድረስ ያለዉን ብቻ በሰኔ ወር 1909 ዓ.ም አጠናቆ አስመረቀ ፡፡ ኩባንያዉ በእራሱ የገንዘብ እጥረት ምክንያት ከእንጦጦ ከፋና ነጭ አባይ ድረስ ያለዉን የሀዲድ ግንባታ ግን መቀጠል አልቻለም ፡፡

አፄ ሚኒሊክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆኑ በርካታ ተግባራቶችን በዘመናቸዉ አከናዉነዋል ፡፡ እነዚህም ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ናቸዉ ፡ - የመጀመሪያዉ የመንግስት ት/ቤት የአራት ኪሎው ዳግማዊ ሚኒሊክ ት/ቤት በ1901 ዓ.ም ተመሰረተ ፡፡ በዚየዉ ዘመን በደሴ፣ በሐረርና በአንኮበር ተመሳሳይ ት/ቤቶች ተከፈቱ ፡፡ የመጀመሪያዉ ጋዜጣ “አእምሮ ጋዜጣ” ጥር 17 1901 ዓ.ም ጀምሮ መታተም ጀመረ ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በስማቸዉና በመልካቸዉ የተቀረጹ የመገበያያ ገንዘቦች ያሰሩ ሲሆን የብሮቹ ስሞችም “አላድ፣ ሩብ፣ ትሙንና ግርሻ” ይባሉ ነበር ፡፡ ገንዘቡን ያሳተሙት ፓሪስ ሲሆን ወዲያዉ የገንዘቡን መቅረጫ አዲስ አበባ አቋቁመዉ በ1901 ዓ.ም ገንዘቡ በመላዉ ኢትዮጵያ መገበያያ እንዲሆን አወጁ ፡፡ ቀጥለዉ “ሐበሻ ባንክ” እየተባለ ይጠራ የነበረዉንና የመጀመሪያዉን ባንክ አቋቋሙ ፡፡ ዳምጠዉ የሚባለዉን ማሽን አስመጥተዉ አዲስ አበባ አካባቢንና እስከ አዲስ አለም ያለዉን 45 ኪ.ሜ መንገዶችንና ድልድዮችን አሰርተዉ፣ በ1901 ዓ.ም አዉቶሞቢል አስገብተዉ መንሽራሽር ጀመሩ ፡፡ እስከአሁን ድረስ በአገልግሎት ላይ ያሉት የራስ መኮነንና የቀበና ድልድዮችም በዚሁ ጊዜ የተሰሩ ናቸዉ ፡፡ የቴሌግራምና የቴሌፎን አገልግሎቶችም እንዲስሩ አድርገዋል ፡ የመጀመሪያዉ ሐኪም ቤት የአሁኑ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል በ1901 ዓ.ም ተቋቋመ ፡፡ በ1894 ዓ.ም የመጀመሪያዉ የቧንቧ ዉሀ ቤተመንግስት ገባ ፡፡ ጣይቱ ሆቴል

እየተባለ የሚጠራዉን የመጀመሪያ ዘመናዊ ሆቴል ፒያሳ ላይ አሰርተዋል ። ዘመናዊ የኤሌክትሪክ መብራትን አስከትለዉ የስፌት መኪና፣ የእንጨት መሰንጠቂያ ማሽን፣ የእህል ወፍጮ፣ የሣሙና ፋብሪካ…. ወዘተ እያመጡ ኢትዮጵያን መስመር ያስያዟት እሳቸዉ ናቸዉ ። አዲስ አበባ የማገዶ እንጨት ችግር አጋጥሞ ስለነበር ባህርዛፍ ከአዉስትራሊያ ያመጡትም እርሳቸዉ ናቸው ።

አፄ ሚኒሊክ በ1902 ዓ.ም በፅኑ ታመሙ ። ባለቤታቸዉ እቴጌ ጣይቱም ከማስታመሙ ጎን ለጎን መንግስትን በመምራት ጅምራቸዉን ለማስቀጠል ይጥሩ ነበር ። አፄ ሚኒሊክም ህመማቸዉ ቀስበቀስ እየበረታባቸዉ ሲሄድ የሚከተለዉን የኑዛዜ ቃል ይፋ አደረጉ ።

“…በአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ የአንዱን አገር አንዱ እደርባለሁ፣ አንዱን ገድየ እኔ ጌታ እሆናለሁ እያለ ሁሉም ላይረባ ተላልቆ ቀረ ። ባገር በሽታ ሳይገባበት ሌላ የባዕድ ጦር ሳይነሳበት በምቀኝነት እርስ በርሱ እንደተላለቀ አይታችኋል ። አሁንም ልጆች ወዳጆች አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር ። ያንዱን አገር አንዱ እኔ እደርባለሁ እንዳትሉ ። እኔ እስከ አሁን በፍቅር እንዳኖርሁዋችሁ እናንተም ተስማምታችሁ በፍቅር እንድትኖሩ እለምናችኋለሁ ። እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ኢትዮጵያን ለሌላ ለባእድ አትሰጧትም ። ክፉም ነገር አገራችንን አያገኛትም ። ይህንን ምክር ለእናንተ መስጠቴ እኔማ በእግዚአብሔር ቸርነት ይህንን ያህል ዘመን ገዝቸ የለምን ። ነገር ግን ሰዉ ነኝና እንግዲህ ለስንት ያህል ዘመን እቆያለሁ ስል ነዉ ።

አሁንም እኔ እንደተመኘሁት እግዚአብሔር ከተጨመረበትና ፈቃዱ ሆኖ ልጃን /የልጅ ልጃቸዉን መለታቸዉ ነዉ/ ቢያቆምላችሁ ከልጄ ጋራ ሆናችሁ አገራችሁን ጠብቁ አደራ ብያችኋለሁ” ይህ የኑዛዜ ቃል በማህተም እየታተመ በየግዛቱ ተሰራጨ፣ በጃን ሜዳም ተነበበ ።

አፄ ሚኒሊክ ከ4 አመት ፅኑ ህመም በኋላ በ70 አመታቸዉ በ1906 ዓ.ም አረፉ ። እቴጌ ጣይቱም ወደ አገራቸዉ ወደ የጁ ለመሄድ ቢፈልጉም ከወንድሞቻቸዉ ከየጁ ባላባቶች ከራስ ወሌና ከራስ አሉላ ጋር ሆነዉ አመፅ ሊያስነሱ ይችላሉ በሚል ስጋት እንዳይሄዱ በልጅ እያሱ መግዚት ተከለከሉ ። ከዚህ በኋላ እቴጌ ጣይቱ ቤተመንግስቱን ለቀዉ ወደ እንጦጦ ማሪያም

ቤተክርስትያን ሄደዉ እስከ እለተ ሞታቸዉ እስከ 1910 ዓ.ም ድረስ በዚያዉ አሳልፈዉ አረፉ ። አፄ ሚኒሊክና እቴጌ ጣይቱ በ4 ኪሎዋ ባእታ ማሪያም ቤተክርስቲያን ነዉ የተቀበሩት ።

እንግዲህ ባየነው መሰረት አፄ ሚኒሊክና እቴጌ ጣይቱ የውጭና ውስጥ የሀገሪቱን ጠላቶች እየወቁ /እየደበደቡ/ ይችን የምታክል እጅግ ሰፊ ሀገር አቅንተው /ፈጥረው/፣ አንድነቷንና ነፃነቷን ጠብቀው ለዚህ ትውልድ ማውረስ ችለዋል ። ከአፄ ሚኒሊክ በፊት በኢትዮጵያ ስር የነበሩት ሁለት ብሔረሰቦች ብቻ ነበሩ፤ እነሱም አማራና ትግሬ ብቻ ነበሩ ። አፄ ሚኒሊክ በአቀኗት /በፈጠሯት/ ሰፊዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከ70 በላይ ብሔረሰቦች ይኖራሉ /አፄ ሚኒሊክ ከ70 በላይ ብሄረሰቦችን አንድ ማድረግ ችለዋል/ ። ከዚህ ቀጥለን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩትን ዋና ዋና ነገዶች እንደት ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ እናያለን ።

## የኢትዮጵያ ነገዶች አመጣጥ

የኢትየጵያ ህዝብ ነገድ በአራት ይከፈላል ። እነሱም ነገደ ኦሪት፣ ነገደ ካም /ኩሽ/፣ ነገደ ሴም /አጋዚያን/ና ነገደ እስራኤል ናቸው /እዚህ ላይ ነገደ እስራኤል የካምና የሴም ቅልቅል መሆኑን ልብ ልንል ይገባል፤ ካምና ሴም ወንድማማቾች ናቸው፤ ሁለቱም የኖህ ልጆች ናቸው/ ።

### 1. ነገደ ኦሪት

ከኖህ በፊት /ከጥፋት ውሀው በፊት/ በኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ህዝቦች ነገደ ኦሪት ይባላሉ ። ከኖህ በፊት /ከጥፋት ውሀው በፊት/ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰው ይኖር እንደነበር አፋር ውስጥ የተገኙት እነ ሉሲና እነ ያርዲ ማስረጃዎቻችን ናቸው ። ነገር ግን እነኝህ ነገደ ኦሪቶች በኖህ ዘመን ጊዜ በውሀ ስለጠፉ ከዚህ ወዲህ እስከ ባቢሎን ግንብ መፍረስ ድረስ ኢትዮጵያ ሰው የሌለባት ባዶ ነበረች ። ከባቢሎን ግንብ በኋላ ግን ነገደ ካም መጥተው ወረሷት ።

## 2. ነገደ ካም /ኩሽ/

ነገደ ካም ከእስያ ተነስቶ በባብእልማንደብ /የመን/ አድርጎ ቀይ ባህርን ተሻግሮ መጥቶ ወደ ኢትዮጵያ ገባ ። ካሞች ኢትዮጵያን ቀድመው የወረሱና በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን መንግስት የመሰረቱ ነገዶች ናቸው ። ቀጥለንም የነገደ ካምን ዘመነ መንግስት የነገስታት ዝርዝርን እናያለን ። ሰንጠረዡ ውስጥ ትውልዱ አጭር ሲሆንብን ግር ሊለን አይገባም፤ ምክንያቱም በዚያን ዘመን አካባቢ አንድ ሰው እስከ 600 አመት ድረስ ይኖር ነበር /በደርግ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 30 ሚሊዮን እንደነበርና አሁን ደርግ ስንት አመቱ እንደሆነ አስቡ/ ።

| ተ. ቁ | የነገስታት ስም | የነገሱበት ዘመን ከክ.ል.በፊት |
|---|---|---|
| 1 | ኖህ /ኢትዮጵያ ሳይመጡ/ | 3844 – 3500 |
| 2 | ካም /ኢትዮጵያ ሳይመጡ/ | 3500 – 2910 |
| 3 | ኩሽ /ኢትዮጵያ ሳይመጡ/ | 2910 – 2545 |
| 4 | ሰብታህ /ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ፤ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ንጉስ/ | 2545 – 2515 የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ንጉስ ዘመን |
| 5 | ኤሌክትሮን | 2515 – 2485 |
| 6 | ነቢር | 2485 – 2455 |
| 7 | አሜን 1ኛ | 2455 – 2434 |
| 8 | ነህሴ /አቢስ/ | 2434 – 2404 |
| 9 | ታርኬም | 2404 – 2375 |
| 10 | ሳባ 1ኛ /ሳባኖባ/ | 2375 – 2345 |
| 11 | ሳፎሪድ | 2345 – 2315 |

| | | |
|---|---|---|
| 12 | እስክንዲ | 2315 – 2290 |
| 13 | ሆይህ ስጥአ | 2290 – 2255 |
| 14 | ኣህያጥ | 2255 – 2235 |
| 15 | አድጋስ | 2235 – 2205 |
| 16 | ባኬንደን መሊስ | 2205 - 2180 |
| 17 | ማንቶራይ ሐቃቤ | 2180 – 2145 |
| 18 | ራክሁ ድድሜ | 2145 – 2115 |
| 19 | ሶቢ | 2115 -2085 |
| 20 | አዜጋን ፈርአን | 2085 – 2055 |
| 21 | ሱስሀል አቶሳኔዝ | 2055 – 2035 |
| 22 | አሜን ዳዊዛ 2ኛ | 2035 - 2020 |
| 23 | አሜን ፀሀቲ መስልኔ | 2020 – 2000 |
| 24 | ዋኔና 3 ቀን የነገሰ | 2000 - 2000 |
| 25 | ጺኦሪ 1ኛ | 2000 – 1985 |

በዚህም ዘመን ውስጥ ሌሎች ነገዳቸው በውል የማይታወቅ 4 አይነት ህዝቦች ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል ። እነሱም ሻንቅላ፣ ቅማንት፣ ወይጦና ሽናሻ ናቸው፤ የገቡትም በኑቢያ /በሱዳን/ በኩል የአባይን ወንዝ ተከትለው ነው ።

**ሻንቅላ ፡** - እነዚህ ህዝቦች ጎንደር ውስጥ ከጭልጋ አፋፍ እስከ በሽሎ ሰፍረው ይኖሩ ነበር ። በኋላ ግን የካም አገዛዝ ስለከበደባቸው ለካም ነገዶች ግብር አንገብርም በማለታቸው ምክንያት የካም ነገዶች ሻንቅሎችን ወደ ታችኛው ኢትዮጵያ አሳደዷቸው ።

**ቅማንት ፡ -** ከእስያ ከከነዓን /ፓልስታይን/ አገር ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ አሁን በሚኖሩበት ጎንደር ጭልጋ አካባቢ ሰፈሩ ።

**ወይጦ ፡ -** ከእስያ ተነስተው በሱዳን አድርገው የአባይ ወንዝን ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ግማሾቹ ጎጃም ጣና ሐይቅ አካባቢ ተቀመጡ፤ ግማሾቹ ግን ተከፍለው ወደ ከፋ ሄደው በኦሮሞ ሀገር ተቀመጡ ። በኦሮሞ ሀገር /በከፋ/ ያሉት እስከ ዛሬ ድረስ ባባታቸው ስም ዋቶ ይባላሉ ። በጎጃም ያሉት ግን በጊዜ ብዛት ዋቶ ተቀይሮ ወይጦ ይባላሉ ።

**ሽናሻ ፡ -** ከእስያ ከከነዓን ሀገር ተነስተው መጥተው ግብፅ መኖር ቢጀምሩም ለከብቶቻቸው መሰማሪያ የሚሆን መሬት ስላጡ በረሃብ ምክንያት ከግብፅ ተሰደው ብዙ ሰራዊት ሆነው የአባይን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ በጎጃም በዳሞትና በኩታይ፣ በአሞሩ መካከል በአባይ ወዲህ ማዶና ወዲያ ማዶ ተቀመጡ ።

## 3. ነገደ ሴም /አጋዚያን/

የሴም ነገዶች ስፍራ በእስያ ከሜሻ እስከ ሳፋር ድረስ ነበር ። እናም ሴሞች እየበዙ ሲመጡ ለከብቶቻቸው ማሰማሪያ ስፍራ በጠበባቸው ቁጥር ሲፈልሱ ሲፈልሱ ሲጓዙ ሲጓዙ መጥተው የመን ደረሱ ። እነዚህ የሴም ነገዶች የመን ከገቡ ጀምሮ ለካም ንጉስ ይገብሩ ነበር ። በኋላ ግን የየመንን ካም ደካማነት አይተው በተንኮል ካሞችን እርስ በርስ አጋጭተው የራሳቸውን ሰው አንግሰው የየመን ሁሉ ባለቤት ሆኑ ። ነገር ግን በኋላ የህንድ መንግስት እስከ የመን ሲስፋፋና ሲባርራቸው የሴም ነገዶች በየአቅጣጫው ተበተኑ ። ከእነዚህም የሴም ነገዶች ውስጥ 3ቱ የዮቅጣን ልጆች ማለትም ሳባ፣ አባልና ኦፊር የሚባሉ ወንድማማቾች ከተከታዮቻቸው ጋር ሆነው በባብአልማንደብ በኩል ተሻግረው ብዙ ህዝብ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ፤ የኢትዮጵያው የጲኦሪ 1ኛ ንጉስም አልተቃወማቸውም ። ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላም ሳባ በትግሬ፣ አባል በአዳል /አፋር/፣ ኦፊር በኦጋዴን ተቀመጡ ። በዚህ መልኩ ከሰፈሩ በኋላም የመጀመሪያዎቹን 5ቱን አመታት ለካሙ ንጉስ ለጲኦሪ 1ኛ ሲገብሩ ኖሩ ፡ በዚህ መካከል የህንዱ ንጉስ ራማ /ብርሃማ/ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ጲኦሪ 1ኛን ወግቶ አሸንፎ መንግስቱን በመቀማት ህዝቡን እንደባሪያ መግዛት ጀመረ ። በዚህ ጊዜ እነዚህ የዮቅጣን ልጆች ተላልከው ካያሉበት ተሰባስበው ራማን

ወግተው ሰራዊቱን አሸንፈው እርሱን ገደሉና ህዝቡን ሁሉ ነፃ አወጡት ። በዚህም ምክንያት ካሞች ሴሞችን አጋዚያን አሏቸው /አጋዚ ማለት በግዕዝ ነፃ አውጭ አጋዥ ማለት ነው/ ። ከዚህ በኋላም የሴምና የካም ህዝቦች በአንድ ላይ ተመካክረው ከሳባ ወገን የሆነውን የሴሙን ሰው አክናሁስን አነገሱት ። ቀጥለን የሴምን /የአጋዚያንን/ ነገስታት ዝርዝር እናያለን ።

| ተ.ቁ | የነገስታት ዝርዝር | የገዙበት ዘመን ከከ.ል.በፊት |
|---|---|---|
| 1 | አክናሁስ ሳባ | 1985-1930 |
| 2 | ነክህቲ ካሊስ | 1930-1890 |
| 3 | ካስዮጲ | 1890-1871 |
| 4 | ሳባ 2ኛ /ሳባ ሻባ/ | 1871-1856 |
| 5 | ኢትዮጲስ 1ኛ | 1856-1800 |
| 6 | ላክንዱን ኒዎር ኦሪ | 1800-1770 |
| 7 | ቱት ኢምሐብ | 1770-1750 |
| 8 | ሐርሂቶር ሽኒ | 1750-1730 |
| 9 | ኢትዮጲስ 2ኛ | 1730-1700 |
| 10 | በኑካ | 1700-1683 |
| 11 | ቦኑ 1ኛ | 1683-1675 |
| 12 | ሙማዚስ | 1675-1671 |
| 13 | አሩአስ 7 ወር | 1671-1671 |
| 14 | አሚን አሳሮ | 1671-1641 |
| 15 | ኦሪ (2ኛ) | 1641-1611 |

| | | |
|---|---|---|
| 16 | ጲኦሪ 2ኛ | 1611-1596 |
| 17 | አሚን አምሐት 1ኛ | 1596-1556 |
| 18 | ፃውዕ | 1556-1541 |
| 19 | አክቲሳኒስ | 1541-1531 |
| 20 | ሚንዲስ | 1531-1514 |
| 21 | ፕሮተውስ | 1514-1481 |
| 22 | አሞይ | 1481-1460 |
| 23 | አንኪ | 1460-1455 |
| 24 | ቦኑ 2ኛ | 1455-1453 |
| 25 | ሳቢ 3ኛ | 1453-1438 |
| 26 | ጀጎንስ | 1438-1418 |
| 27 | ስኑካ | 1418-1408 |
| 28 | አንጋቦስ 1ኛ | 1408-1358 |
| 29 | ሚአሙር2 ቀን | 1358-1358 |
| 30 | ከሊና/ንግስት ሳዶኒ/ | 1358-1347 |
| 31 | ዘግዱር 1ኛ | 1347-1307 |
| 32 | ሔርሀቶር 2ኛ | 1307-1277 |
| 33 | ሔርቶር 3ኛ | 1277-1276 |
| 34 | ኔክቲ | 1276-1256 |
| 35 | ቲቶን ስትዩ | 1256-1246 |
| 36 | ሔርመንተ 1ኛ1 ወር | 1246-1246 |

| | | |
|---|---|---|
| 37 | አሚን አምሐት 2ኛ | 1246-1241 |
| 38 | ኮንሳብ 1ኛ | 1241-1236 |
| 39 | ኮንሳብ 2ኛ | 1236-1231 |
| 40 | ሰኑካ 2ኛ | 1231-1226 |
| 41 | አንጋቦ /ህዝባይ/ | 1226-1186 |
| 42 | አሜን ህስተት | 1186-1156 |
| 43 | ሔርሀር | 1156-1140 |
| 44 | ፒያንኪያ 1ኛ | 1140-1131 |
| 45 | ጥኖት ሴም 1ኛ | 1131-1114 |
| 46 | ጥኖት ሴም 2ኛ | 1114-1073 |
| 47 | ማስሔርታ | 1073-1057 |
| 48 | ራሜን ኮበርም | 1057-1043 |
| 49 | ጥኖት ሴም 3ኛ | 1043-1036 |
| 50 | ሣቢ 4ኛ | 1036-1026 |
| 51 | ተዋስያ ዴውስ /አጋቦስ/ | 1026-1013 |
| 52 | ንግስት ሳባ /ማክዳ/ | 1013-982 |
| 53 | ሚኒሊክ 1ኛ /የመጀመሪያው ሰለሞናዊ ንጉስ/ | 982-957 |
| 54 | ሐንድዮን | 957-956 |
| 55 | ሲራህ 1ኛ | 956-930 |

| | | |
|---|---|---|
| 56 | አሜን ሆቴቭ /ዘግዱር/ | 930-889 |
| 57 | አክሱማይ ራሚሱ | 889-869 |
| 58 | ሲራህ 2ኛ | 869-831 |
| 59 | ተዋስያ 2ኛ | 831-810 |
| 60 | ፒያንኪ 2ኛ /አብራሊዮስ/ | 810-778 |
| 61 | አክሱማይ ወረደ ፀሀይ | 778-755 |
| 62 | ካስታህ ሐንዲዮን | 755-742 |
| 63 | ሻባካ | 742-730 |
| 64 | ኒካንታ ህንዳኬ | 730-720 |
| 65 | ቲሃርቃ /ወረደ ነጋሽ/ | 720-671 |
| 66 | አርድአሜን አውስያ | 671-665 |
| 67 | ገስዮ 1 ቀን | 665-665 |
| 68 | ታንታሙን | 665-661 |
| 69 | ቶማድዮን ፒያንኪያ 3ኛ | 661-649 |
| 70 | አሚን አሳሮ 2ኛ | 649-633 |
| 71 | ፒያንኪያ አውጥዮ 4ኛ | 633-599 |
| 72 | ዝዋሬንብረት አስፑርታ | 599-558 |
| 73 | ሰይፋይ ሐርሲአተው | 558-546 |
| 74 | ራምሐይ ናስቶስኔን | 546-532 |
| 75 | ሐንዲዮ አብራ | 532-521 |
| 76 | ሰፎሊያ ኒኮቦን | 521-490 |

| | | |
|---|---|---|
| 77 | አግልቡል ስዌኮስ | 490-469 |
| 78 | ጵፅመረት /ወረደ ነጋሽ/ | 469-448 |
| 79 | አውስያ ብራክስ | 448-436 |
| 80 | ቀኒዝ ጵስሜዝ | 436-423 |
| 81 | አጵራስ | 423-413 |
| 82 | ካስታህ ወልደ እሁህ | 413-393 |
| 83 | ኤላልዮን ቲአንኪ | 393-383 |
| 84 | አርቲስክ አሚን 3ኛ | 383-373 |
| 85 | አርቲስክ አሚን 4ኛ | 373-363 |
| 86 | ሐዲና | 363-353 |
| 87 | አርቲስክ አሚን 5ኛ | 353-343 |
| 88 | አርቲስክ አሚን 6ኛ | 343-333 |
| 89 | ኒካውላ ህንዳኬ 3ኛ | 333-323 |
| 90 | ባስኡ | 323-316 |
| 91 | ኒካውላ ህንዳኬ 4ኛ | 316-306 |
| 92 | አውጥጥ አራውራ | 306-296 |
| 93 | አርካሚን 2ኛ | 296-286 |
| 94 | ከልአስ 2ኛ | 286-276 |
| 95 | ዙዋሬ ንብረት | 276-260 |
| 96 | ስትዮ | 260-246 |
| 97 | ሰይፋይ | 246-233 |

| | | |
|---|---|---|
| 98 | ኒኮሲስ ህንዳኬ 5ኛ | 233-223 |
| 99 | ራምሐይ አርሚን 4ኛ | 223-213 |
| 100 | ፊልያ ሁርኔክሀት | 213-198 |
| 101 | ሃንዲ አውኪራራ | 198-178 |
| 102 | አግሐቡ ብሴህራን | 178-168 |
| 103 | ሉላይ ከዋውማኑን | 168-148 |
| 104 | መሰልኒ ቁራርሜር | 148-140 |
| 105 | ነክሳይ ብስንቲ | 140-130 |
| 106 | ኤትቢኑ ካውር | 130-120 |
| 107 | ስፈልያስ አብራሚን | 120-100 |
| 108 | ሥናይ | 100-90 |
| 109 | ንግስት አውሲና | 90-79 |
| 110 | ዳዊት | 79-69 |
| 111 | አግልቡስ | 69-61 |
| 112 | በዋውል | 61-51 |
| 113 | ባረዋስ | 51-41 |
| 114 | ዳኒዳድ | 41-31 |
| 115 | ኣሞይ መሐሲ | 31-26 |
| 116 | ኒክትራስ ህንዳኬ 6ኛ | 26-16 |
| 117 | ኖልኪ | 16-14 |
| 118 | ሉዛይ | 14-6 |

| | | |
|---|---|---|
| 119 | ባዚን | 6-9 ዓ.ም |
| 120 | ሰርጡ ዕንፈ አሰግድ | 9-30 |
| 121 | አካጥታህ ፅንፈ አሰግድ | 30-32 |
| 122 | ሆርኤምትኩ 2ኛ | 32-34 |
| 123 | ንግስት ህንዳኬ 7ኛ | 34-46 |
| 124 | ሀታዝ ባህር አሰግድ | 46-70 |
| 125 | ምንሴህ ግርማ ሰር | 70-77 |
| 126 | ሰጥዋ ግርማ አስፋር | 77-86 |
| 127 | አድገለ | 86-96 |
| 128 | አግባ | 96-97 |
| 129 | ሠርአዳ | 97-113 |
| 130 | መሊስ አላሚዳ | 113-117 |
| 131 | ሀቃቤ ከሎፅዮን | 117-123 |
| 132 | ሐቅሌ ሠርጓይ | 123-135 |
| 133 | ድድሜ ዘርዓይ | 135-145 |
| 134 | አውጥፓ | 145-147 |
| 135 | አልአዶ በጋማይ | 147-154 |
| 136 | አውዶ ዣን አሰግድ | 154-184 |
| 137 | ዛግን ፅዮን ሕግዛ | 184-189 |
| 138 | ሬፅዮን ሕግዛ | 189-192 |
| 139 | አዚጋን መዓልባጋድ | 192-199 |
| 140 | ገፈሌ ሰብዓ አሰግድ | 199-200 |

| | | |
|---|---|---|
| 141 | ፅጋዮን ብእሴ ወርቅ | 200-204 |
| 142 | ጋዛ አግድ | 204-213 |
| 143 | አግዱር አስጓጓ | 213-221 |
| 144 | ደዊዛ | 221-222 |
| 145 | ንግስት ዋከና 1 ወር | 222-222 |
| 146 | ሀውዶስ 4 ወር | 222-222 |
| 147 | አዕላል ሰገሠገል | 222-225 |
| 148 | አስፍሐ | 225-239 |
| 149 | አድገቦ ሰይፈ አርእድ | 239-245 |
| 150 | አይባ /አይላ/ | 245-262 |
| 151 | ፀሐመ ለክዱን | 262-271 |
| 152 | ድጋብ | 271-281 |
| 153 | ታዜር /ታዜና/ | 281-291 |
| 154 | ንግስት አህየዋሶፍያ | 291-298 |
| 155 | ኢዛናና ሲዛና በአንድነት /አብርሃና አፅባሃ ባንድነት/ | 298-324 |
| 156 | አፅባሃ ብቻውን | 324-336 |
| 157 | አስፋሐ ደለዝ | 336-343 |
| 158 | ሳህል /ስሁል 1ኛ/ | 343-357 |
| 159 | አርፍድ ገ/ቀል | 357-361 |
| 160 | ንግስት አፅሃን | 361-366 |

| | | |
|---|---|---|
| 161 | ርትዕ | 366-367 |
| 162 | አስፍሐ 2ኛ | 367-368 |
| 163 | አፅብሐ 2ኛ | 368-373 |
| 164 | አሜድ | 373-388 |
| 165 | አብርሐ 2ኛ7 ወር | 388-389 |
| 166 | እለ ሳህል2 ወር | 388-389 |
| 167 | እለ ገበዝ | 389-391 |
| 168 | ሳህል /ስሁል 2ኛ/ | 391-395 |
| 169 | አብረሐ 3ኛ | 395-405 |
| 170 | ንግስት አድሐን 2ኛ | 405-411 |
| 171 | ኢዮአብ | 411-421 |
| 172 | ፀሀም 2ኛ | 421-423 |
| 173 | አሜድ 2ኛ | 423-424 |
| 174 | ሳህል /ሳህለ ህዝብ/ | 424-426 |
| 175 | ፅባህ ማህረነ ክርስቶስ | 426-429 |
| 176 | ፀሃም 3ኛ | 429-431 |
| 177 | እለገበዝ 2ኛ | 431-437 |
| 178 | አጋሊ አጋቢ | 437-438 |
| 179 | ሊዊ | 438-440 |
| 180 | አሜደ 3ኛ/ያዕቆብ/ | 440-443 |
| 181 | እርማህ /ዳዊት 1ኛ/ | 443-457 |

| | | |
|---|---|---|
| 182 | አምሲ | 457-462 |
| 183 | ሰልአዮባ | 462-471 |
| 184 | እልአሜዳ | 471-479 |
| 185 | ታዚና /ዋዜና/ | 479-485 |
| 186 | ካሌብ | 485-515 |
| 187 | ዘእስራኤል1 ወር | 515-515 |
| 189 | ገብሩ1ወር | 515-515 |
| 190 | ገብረ መስቀል | 515-529 |
| 191 | ቆስጠንጢኖስ ሳህል | 529-557 |
| 192 | ወሰን ሰገድ መሐረነ ክርስቶስ | 557-572 |
| 193 | ፍሬ ሥናይ | 572-595 |
| 194 | አድርአዝ | 595-615 |
| 195 | አካለወድም | 615-623 |
| 196 | ግርማ አስፈር 2ኛ | 623-638 |
| 197 | ዝርጋዝ | 638-648 |
| 198 | ድግና ሚካኤል | 648-674 |
| 199 | ባህር ኤክላ | 674-693 |
| 200 | ጉም /አፄ ገርስም/ | 693-717 |
| 201 | አስጎምጉም /አፄ ባካሳ/ | 717-722 |
| 202 | ለትም እዮኤል | 722-738 |

| | | |
|---|---|---|
| 203 | ተላትም /አፄ እንደቢስ/ | 738-758 |
| 204 | አደጉሽ /አፄ ማህየዊ/ | 759-772 |
| 205 | አይዙር1 ቀን | 772-772 |
| 206 | ድድም /አፄ አስፈሪ/ | 772-777 |
| 207 | ውድድም/አፄ ዳንኤል/ | 777-787 |
| 208 | ውድም አስፈሬ | 787-817 |
| 209 | አርማህ 3ኛ /አፄ እለቆስጠንጢኖስ/ | 817-822 |
| 210 | ደግናዥን | 822-741 |
| 211 | ግዳዥን /አፄ ህዝብናኝ/ | 841-842 |
| 212 | ዮዲት ጉዲት | 842-882 |
| 213 | አንበሳ ውድም /አፄ አንበሳ ሰገድ/ | 882-902 |
| 214 | ድልነአድ | 902-912 |
| የአገው፣ የዛግዌ ስርዎ መንግስት ይቀጥላል/ዘአገው/ | | |

## 4. ነገደ እስራኤል/ቤተ እስራኤል/

በእስራኤሉ ንጉስ በሰለሞን ዘመን ጊዜ ሳባ የተባለች የአክሱም ንግስት የንጉስ ሰለሞንን ጥበብ ለማየት ከብዙ ጓዝ ጋር ወደ እስራኤል ሄደች ። ከንጉስ ሰለሞንም ጋር በፈፀመችው ግንኙነት ልጅ አርግዛ ተመለሰች ። ንግስት ሳባም ከአጃቢዎቿ ጋር ወደ ሀገሯ ስትመለስ የኤርትራን ባህር ተሻግራ ሐማሴን አውራጃ ማይበላ በተባለው ቦታ ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሚኒሊክ አለችው ።

ሚኒሊክም ከእናቱ ጋር አክሱም አድጎ 22 አመት ሲሆነው አባቱን ንጉስ ሰለሞንን ለማየት ወደ እስራኤል ሄደ፤ ለ3 አመት ያህልም እዚያው እየሩሳሌም አባቱ ጋር ሆኖ የኦሪት ህግን፣ የመንግስት አስተዳደርንና የእብራይስጥን ቋንቋ ተምሮ ጨረሰ ። ከዚህ በኋላ ንጉስ ሰለሞን ልጃቸውን ሚኒሊክን የኢትዮጵያ ንጉስ ይሆን ዘንድ በካህናት እጅ ቅብአ መንግስትን አስቀብተው /ቅብአ ሜሮንን አስቀብተው/፣ የመንግስት ልብስ አልብሰውና የህገ ኦሪትን ስርዓተ መንግስት ሰጥተው ከ12 ሺህ እስራኤላዊ ሰራዊት ጋር ወደ ኢትዮጵያ ላኩት ።

ንግስት ሳባም ልጇ ሚኒሊክ ከእየሩሳሌም ሲመለስ በታላቅ ክብር ሰልፍ አድርጋ ተቀበለችው ። ሚኒሊክና ሰዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አዛርያስ በተባለው ሊቀ ካህን አማካኝነት በልዑል እግዚአብሔር ጣቶች ተቀርፆ ለሙሴ የተሰጠው እውነተኛው ፅላት ወደ ኢትዮጵያ አብሮ መጣ፤ በእስራኤሎቹ አስተማሪነትም ብዙ ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ከጣኦት አምልኮ ወጣ፤ ፅላቱ አሁን በአክሱም ፅዮን ገዳም ውስጥ ይገኛል ።

ከዚያም ንግስት ሳባ በህይወቷ እያለች ልጇን ሚኒሊክን በኢትዮጵያ አነገሰችው ። ከሚኒሊክ ጋር የመጣው 12 ሺህ የእስራኤል ሰራዊትም አብዛኛው ጎንደር ውስጥ ከቋራ እስከ መተማ ቦታ ተሰጥቶት ሰፈረ፤ ከተማቸውንም ቋራ ላይ አደረጉ፤ እስከ ዛግዌ ስረወ መንግስት ድረስም ይግባቡበት የነበረው የአካባቢው የጥንት ቋንቋ ኳረኛ የሚባል ነበር፤ አሁን ግን ቋንቋቸውን አጥፍተው ባማርኛ ቋንቋ ብቻ ይናገራሉ ።

እነኝህም የእስራኤል ነገዶች ጎንደር ውስጥ ከጋፋትና ከቅማንት ህዝቦች ጋር አብረው ይኖራሉ ። ሆኖም የእስራኤሎቹ ነገዶች በየጊዜው ወደ እስራኤል እየፈለሱ /እየተወሰዱ/ ይገኛሉ ።

***ጋፋት* ፡ -** ጋፋት ከእስያ ከመጣው ከካም /ከኩሽ/ ወገን ይመደባል ። ጋፋቶች መጀመሪያ በሸዋ ይኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ቀማኛ፣ ሌቦችና ግፈኞች ስለነበሩ ነገስታት በየዘመናቸው ያሳድዷቸው ነበር ። በዚህም ምክንያት ጋፋቶች ከሸዋ ፈልሰው የአባይን ወንዝ ተከትለው በጎጃም ዳሞት አካባቢና በጎንደር ደብረ ታቦር አካባቢ ሰፈሩ ። ጎንደር ደብረ ታቦር አጠገብ ያለው አገርም በስማቸው ጋፋት ይባላል፣ እዚያው ጎንደር እስቴይ መካነ እየሱስ አጠገብ ያለው ቦታም በስማቸው ጋፋት ይባላል ። በአሁኑ ወቅት የጎንደርም

የጎጃምም ጋፋቶች የጥንት ቋንቋቸውን ጋፋትኛን አጥፍተው ባማርኛ ብቻ ይናገራሉ፤ በአሁኑ ወቅት አንዳንዶች ያረሱት ብቻ በጥንት ጋፋትኛ ቋንቋቸው እርስ በርሳቸው ለሚስጥር ይነጋገሩበታል እንጅ ዋና ቋንቋቸው ግን አማርኛ ሆኗል ።

## ብሔረ ትግሬ

በነገደ ካም በጺአሪ 1ኛ ዘመን ጊዜ የህንድ ነገስታት በርትተው ወደ የመን እየመጡ በጦርም በዘረፋም ባስቸገሯቸው ጊዜ በየመን ከነበሩ የሴም ነገዶች ውስጥ 3ቱ የዮቅጣን ልጆች ማለትም ሳባ፣ አባልና ኦፌር ከተከታዮቻቸው ጋር ብዙ ሰራዊት ሆነው ከየመን ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ። ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላም ሳባ በትግሬ፣ አባል በአዳል፣ ኦፌር በኦጋደን ተቀመጡ ። ሳባዎችም ነጋዴ ሆነው ለካም ንጉስ ለጺአሪ 1ኛ ቀረጥና ግብር እየከፈሉ ጥቂት ዘመን /ለ5 አመት ያህል/ ስለተቀመጡ የዚያን ሀገር ስም ትግሬ አሉት፤ ትግሬ ማለት በአረብኛ ነጋዴ ማለት ነው ።

## ብሔረ ኦሮሞ

የኦሮሞ ህዝብ ከካም ነገድ የሚመደብ ሲሆን ብዙ ልዩነት አላቸው ባይባሉም ስለኦሮሞ ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ የሚገልፁ 2 አይነት ፅሁፎች አሉ ። አንደኛው ፅሁፍ ፡ - የኦሮሞ ህዝብ ከእስያ ተነስቶ ለከብቶቹ የሚሆን ማሰማሪያና ግጦሽ እየተከተለ ወደ ማዳጋስካር ተሻገረ፤ ከዚያም ከማዳጋስካር ተነስቶ ቦባሳ ባህር ወደብ አጠገብ ሰፈረ /ቦባሳ ማለት በኦሮምኛ ለሰውም ለከብትም መሰማሪያ ማለት ነው/ ። ከዚያም ከቦባሳ ወደብ ተነስተው ገናሌ ወንዝ ውስጥ ገቡ፤ ከዚያም የገናሌን ወንዝ ተከትለው ኢትዮጵያ ገብተው ባሌ አካባቢ ሰፈሩ ። ባሌ ውስጥም ‘’ሆር ወላቡ’’ በተባለ ቦታ ሰፈሩ /ሆር ወላቡ ዋነተኛ በዋና የሚሻገራት ትንሽ ባህር ናት/ ። በዚህም ምክንያት ኦሮሞዎች መሰረታችን /መነሻችን/ ባህር ነው በሚል ለባህር ልዩ ክብር ነበራቸው ፡ አንደኛው ፅሁፍ ይሄ ሲሆን ሁለተኛውና በርካቶች የሚያሰፍሩት ደግሞ ፡ -

የኦሮሞ ህዝብ ከእስያ ተነስቶ ወደ ማዳጋስካር ተሻገረ፤ ከዚያም ከማዳጋስካር ተነስቶ ቦባሳ ባህር ወደብ አጠገብ ሰፈረ ። ከዚያም ከቦባሳ ወደብ

ተነስቶ ገናሌ ወንዝ ውስጥ ገባ ። ከዚያም የገናሌ ወንዝን ተከትሎ መጥቶ ኢትዮጵያ ውስጥ ገባ፤ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላም በባሌ ዳርቻ ገላና በሚባለው ወንዝ አጠገብ ተቀጠ /ገላና ማለት በኦሮምኛ ባህር ማለት ነው፣ ፀሀፊዎቹ ግን ወንዝ ነው የሚሏት/ ።

የሁለቱ ፅሁፎች ልዩነት ያለው ኦሮሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰፈረበት /መኖር የጀመረበት/ ቦታ ላይ ነው፤ ይህን ቦታ የመጀመሪያው ፅሁፍ ''ሆር ወላቡ'' ሲለው ሁለተኛው ፅሁፍ ግን ''ገላና ወንዝ'' ይለዋል ።

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ከኦሮሞ ውጭ ያሉ ሁሉም ነገዶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በስተ ሰሜን አቅጣጫ ነው ። ባልተለመደ አቅጣጫ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ብቸኛ ህዝብ የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ነው ። ከኦሮሞ ውጭ አሁን በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሁሉም ነገዶች የመጡት ከዚሁ ከቅርቡ ከየመን እየተነሱ ነው፤ ከየመን እየተነሱ ጥጆቻቸውንና ጨቅላዎቻቸውን በጀልባ ላይ እያደረጉና እየቀዘፉ አጭሯን የኤርትራን ባህር አቋርጠው መጥተው ይሰፍሩና እንደገና እየተመላለሱ ቦታውን እየተለማመዱ፣ የአባይን ወንዝ እየተከተሉ ነው የገቡት ። ኦሮሞ ግን ባልተለመደ አቅጣጫ ከመግባቱም በተጨማሪ በሁለት አለቆች ስር ሆኖ /በበርቱማና በቦረን ስር ሆኖ/ እጅግ ብዙ ሆኖ ነበር የገባው /ኦሮሞ እጅግ ብዙ ሆኖ መግባቱን መገመት ይቻላል፤ ኦሮሞ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዛግዌ የመጀመሪያ ንጉስ በመራተክለሐይማኖት ዘመን ነው፤ ነገር ግን በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያን ጫፍ እስከ ጫፍ በሚባል ደረጃ መውረር ችሏል/ ። እናም እጅግ ብዙ ሆነው ይጓዙ ስለነበር ለዚያ ሁሉ ህዝብ ከብቶች መጠጥ የሚሆን ትልቅ ባህር /ገላና/ ቀድመው በሰላዮች /በአሰሳ/ ካገኙ በኋላ ነበር ሄደው በባህሩ /በገላናው/ አጠገብ የሚሰፍሩት ። ኢትዮጵያም ውስጥ መጥተው ለመጀመሪያ ጊዜ መኖር የጀመሩት /የሰፈሩት/ ገላና ባህር አጠገብ ነው ። በዚህም ምክንያት ኦሮሞዎች መነሻችን /መሰረታችን/ ባህር /ገላና/ ነው ብለው ያምኑ ስለነበር ለባህር ልዩ ክብር ነበራቸው፤ አሁንም ድረስ ኦሮሞዎች ለባህር /ለገላና/ የነበራቸውን ክብር የሚጠቁሙ ምልክቶች አሉ፤ ለምሳሌ ያህል ደብረ ዘይት ውስጥ በየአመቱ የሚከበረውን የኢሬቻ ባህላዊ የኦሮሞ ባህል እንደ ምልክት መውሰድ ይቻላል ፡ እናም ኦሮሞዎች ለገላና ባላቸው ልዩ ክብር ምክንያት ይች ኦሮሞዎች ባልተለመደ አቅጣጫ መጥተው ለመጀመሪ ጊዜ መኖር የጀመሩባት /የታወቁባት/ የገላና ባህር ትኩረት አግኝታ ነበር፤

ገላናዎች ናቸው ይባሉ ነበር ። እናም ኦሮሞዎች ገላና አጠገብ ስለተገኙ ገላናዎች ናቸው ይባሉ ነበር ። ይህ ‘’ገላና’’ የሚለው ቃል በፅሁፍ እንጅ በቃል ኦሮምኛ ተናጋሪ ያልሆኑ ሰዎች ቃሉን በትክክል አይናገሩትም ነበር፤ አንዳናዶች ‘’ጋላና’’ ሲሉት ሌሎች ደግሞ ‘’ገላ’’ ወዘተ ይሉት ነበር ። ልክ እንደ ጀማሪ አማርኛ ተናጋሪ ሰው ማለት ነው፤ ለምሳሌ ያህል አንድ ጀማሪ አማርኛ ተናጋሪን ሰው ‘’ሚጥሚጣ’’ በል ብትለው ‘’ምጥምጣ’’ ነው የሚለው፤ ልክ እንደዚያ ማለት ነው ። እናም ኦሮምኛ ተናጋሪ ያልሆኑ ሰዎች ይህን ገላና የሚለውን ቃል ጋላና፣ ገላ ወዘተ እያሉ በዘፈቀደ ስለሚናገሩት በጊዜ ብዛት ምክንያት ገላና የሚለው ቃል መልኩን ተቀይሮ ብዙ ኦሮሞዎች የማይፈልጉት ቃል ሆኗል /እንደ ስድብ ተቆጥሯል/ ። እኛም የዚህን እንደስድብ የተቆጠረውን ቃል ትርጉም ለማወቅ ያልቆፈርነው ጉድጓድ የለም፤ ሆኖም መላ ምት እንጂ ማንም ስለዚህ ቃል የሚያውቅ ሰውም ሆነ ፅሁፍ አልተገኘም ። እንዲሁ ቃሉን እንደስድብ ሲቆጥሩት ሲያይ ሰው በግምት ‘’እንደዚህ ማለት ይሆናል’’ እያለ ከአንዳንድ ነገሮች ጋር እያያያዘ ይገምታል እንጂ በትክክል የቃሉን ትርጉም የሚያውቅ ሰው አይገኝም ። ስለቃሉ ትርጉም የሚያውቅ ሰውና ፅሁፍ ጠፋ ማለት ደግም ቃሉ ስድብ አልነበረም ማለት ነው /በግድ ነው እንደስድብ የተቆጠረው ማለት ነው/ ። እኛም ስለቃሉ ለማወቅ ባደረግነው ጥረት ይህን ካላይ ያሰፈርነውን ብቻ ነው ያገኘነው ። እናም ከዚህ የምንረዳው፣ ቃሉን በግምት ስድብ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ስድብ አድርገነዋል እንጂ ቃሉ ስድብ አልነበረም ማለት ነው /ካለማንበብና ታሪክን ካለማወቅ የመጣ ችግር ነው ማለት ነው/ ።ኦሮሞዎች 2 ዘር ናቸው፤ እነሱም በርቱማና ቦረን ይባላሉ፤ በርቱማና ቦረን ወንድማማች ናቸው ። በርቱማ 6 ለጆችንና ቦረን 11 ልጆችን ወለዱ ።

የበርቱማ ልጆች እነዚህ ናቸው መረዋ፣ ከረዮ፣ ኢቱ፣ አክቹ፣ ወርነሻና ሁበና ናቸው ። ከረዩ 8 ልጆችን ወለደ፤ እነሱም ሊበን፣ ሜጫ /ጎጃም/፣ ትሎማ፣ ጅሌ፣ ወሎ፣ አባ፣ ሉባና በላእ ናቸው ። የመለዋ ልጆች 4ናቸው፤ እነሱም ወርዲያ፣ አሩሲ፣ ኢቱና ጥሙጋ ናቸው ። ሁበናም 3 ልጆችን ወለደ፤ እነሱም ራያ፣ አዘቦና ሐሸንጌ ናቸው ።

**የሜጫ ልጆች ፡ -** የሜጫ ኦሮሞዎች ወደ ጎጃም ሄደው በሜጫ፣ በጣና ሐይቅና በዳሞት የሰፈሩት በአፄ አምደፅዮን ዘመን ነው፤ አገሩንም በአባታቸው

ስም ሜጫ አሉት፤ ሌላኛውንም አገር በሌላ ኦሮሞ ሰው ስም ዳሞት አሉት፤ በአሁኑ ወቅት ኦሮሞኛን አጥፍተው ባማርኛ ብቻ ይናገራሉ ። በአሁኑ ወቅት ጎጃም ውስጥ ሜጫና ዳሞት የሚባሉ ወረዳዎች አሉ ።

**የወሎ ልጆች ፡ -** የወሎ ልጆችም በዚሁ ዘመን አካባቢ ነው ወደ ላኮመልዛ የገቡት ። የአገሩም ስም ጥንት ላኮመልዛ ይባል የነበረ ሲሆን በኋላ ላኮመልዛን ቀይረው ባባታቸው ስም ወሎ አሉት ።

**የራያ፣ የአዘቦና የሐሸንጌ ልጆች ፡ -** የራያ፣ የአዘቦና የሐሸንጌ ልጆችም ወደ ትግራይ የገቡት በዚሁ ዘመን አካባቢ ነው፤ በአሁኑ ወቅት ኦሮሞኛን አጥፍተው በትግርኛ ይናገራሉ /የትግራይ ህዝብ ተቀላቅሏቸዋል/ ።

ከላይ ያየናቸው የበርቱማ ልጆች ሲሆኑ የቦረን ልጆች ደግሞ ፡ - ደጬ፣ ጅሌ፣ ኮኖ እነዚህ ቱለማ ይባላሉ ። ጭሌ፣ ሊበን፣ጉድሩ፣ሆኮ እነኝህ ሆኮ ይባላሉ ። አካኮ፣ ወቦ፣ ሉባ እነኝህ ደግሞ ሰደቻ ይባላሉ ። በድምሩ 11 ናቸው ።

የጅሌ ልጆች ወለጋና ጉማ ናቸው ። የኮና ልጆች ሊሙ፣ ጅማና ጌራ ናቸው ። የደጬ ልጆች ሌቃና ጨለባ ናቸው ። የጭሌ ልጆች ጉለሌና ሰላሌ ናቸው ። የሆኮ ልጅ ቦረና ብቻ ነው ።

## ብሔረ ወላይታ /እናሪያ/

የእናሪያ ዘር ከካም ነገድ ይመደባል ። የሴም ነገዶች /ኢጋዚያን/ በኋላ መጥተው የነገደ ካምን መንግስት በወረሱ ጊዜ መሬት ስለጠበባቸው ህዝቡንም መጨፍጨፍና ማሳደድ ጀመሩ ። በዚህን ጊዜ የእናሪያ ዘር ከሰሜን ፈልሶ ባዶ ወደ ነበረው ምድር ወደ ደቡብ መጥቶ አሁን ወላይታ፣ ሲዳሞ፣ ኩሎ፣ ኮንታ፣ አማሮ፣ ዝንጀሮ እየተባሉ በሚጠሩት አካባቢዎች ሰፈረ ፡ በኋላ ላይ ኦሮሞዎች ያዙት እንጂ በፊት ከፋ፣ ሉቅማ፣ ጅማ፣ ሌቃ፣ ትቤ ሁሉ የእናሪያ ህዝብ አገር ነበር ። እነዚህ እናሪያዎች በመጀመሪያ አካባቢ አጎራባቻቸው ከነበረው ከኦሮሞ ህዝብ ጋር በኦሮምኛ ይግባቡ የነበረ ቢሆንም በጊዜ ብዛት ግን የራሳቸውን ቋንቋ ፈጥረው በአሁኑ ሰዓት የየራሳቸው ቋንቋ አላቸው ።

## ብሔረ ጉራጌ

በአፄ አምደፅዮን ዘመን ከትግሬ ጉርዓ ከሚባል አገር ከኩሎ ግዛይ ክፍል /ግዛት/ የወጣ ሰራዊት ከአዝማች ስብሐት ጋር መጥቶ በአይመለል ሰፈረ ። በጊዜ ብዛትም ጉርዓ የሚለው ቃል ወደ ጉራጌ ተቀየረ ።

## ብሔረ አማራ

አማራ ከወዴየትም አልመጣም፤ አማራ ከወዴየትም አልገባም ። አማራ ማለት ጥሩ የላስታ ወታደር፣ ከየአይነቱ /ከየነገዱ/ የተውጣጣ፣ ሀይለኛ፣ ግፈኛ፣ ጨካኛና አድመኛ የወታደር ክፍል ነበር ። በንጉስ ላሊበላ ዘመን አማራ የተባለ ወታደር በዋድላ ደላንታ፣ በበጌምድርና በሣይንት ተመስርቶ ነበር ። አማራ ማለት የንጉስ ላሊበላ የአንድ ክፍለ ጦር መጠሪያ ሥም ነበር /ልክ ባሩድ ክፍለ ጦር እንደሚባለው ማለት ነው፣ አማርኛ፣ ባሩድኛ/ ፡ ፡ እናም አማርኛ ቋንቋ እዚሁ አማራ ክፍለ ጦር ውስጥ በነበሩ ‘’አራዳ ነን’’ በሚሉ ወታደሮች የተፈጠረ የአራዳ ቋንቋ ነበር፤ ይህ የአንዳንድ ወታደሮች መነጋገሪያ የነበረው የአራዳ ቋንቋ /አማርኛ/፣ ቀስበቀስ የመላው የአማራ ክ/ጦር አባላት መግባቢያ ቋንቋ እየሆነ መጣ ። በአጭር ጊዜ ውስጥም ‘’አራዳ ነን’’ የሚሉ የአካባቢው ማህበረሰብ ሰዎች ሁሉ የወታደሮቹን ቋንቋ መጠቀም ጀመሩ ። በዚህ መልኩ አማርኛ በዘመኑ ‘’አራዳ ነን’’ የሚሉ ሰዎች ሁሉ ቋንቋ እየሆነ መጣ፤ በአጭርም ጊዜ ውስጥ ተስፋፋ ። በዘመኑ ከወታደሮች የበለጠ ‘’አራዳ ነኝ’’ የሚል ሰው ስላልነበር ይህ የዘመኑ የአራዳ ቋንቋ የነበረው አማርኛ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰራጨ ። ይህ ‘’አራዳ ነኝ’’ የሚለው ማህበረሰብ ሁሉ መነጋገሪያ የሆነው አማርኛ ቋንቋ በአጭር ጊዜ ውስጥ በዛግዌ ግዛቶች ውስጥ ይነገሩ የነበሩ በርካታ ትንንሽ ቋንቋዎችን እያጠፋ መጥቶ ብቸኛ የአካባቢው ቋንቋ ሆነ ። የጎንደርና የጎጃም ህዝብ ቋንቋዎች ሙሉ በሙሉ ሲጠፉ ትግርኛ ብቻ በሰፊው ህዝብ ይነገር ስለነበር ሙሉ በሙሉ ከመጥፋት ዳነ ። በመጀመሪያ ይህ አማርኛ ቋንቋ በፍጥነት ከላስታ እስከ መራቢቴ ዶባ ድረስ ተስፋፋ፤ ሆኖም ወሎ ውስጥ እስከ አሁንም ድረስ አማርኛ ቋንቋን ኦሮሞኛ ቋንቋ እየታገለው ነው ። ከወሎ ቀጥሎም አማርኛ ቋንቋ ወደ ጎንደር በመስፋፋቱ ምክንያት የጎንደር ህዝብ ቋንቋ የነበሩትን ጋፋትኛንና ኳርኛን አጥፍቶ ብቸኛ የአካባቢው ቋንቋ ሆነ ። ቀጥሎም አማርኛ ቋንቋ ወደ ሌላኛው

የዛግዌ ግዛት ወደነበረው ወደ ጎጃም በፍጥነት ተስፋፍቶ የጎጃም ህዝብ ቋንቋ የነበሩትን አሮምኛን፣ ሽናሽኛን፣ ወይጦኛንና ጋፋትኛን ወዘተ ሙሉ በሙሉ አጥፍቶ ብቸኛ የአካባቢው ቋንቋ ሆነ /ጎጃምን የአባይ ወንዝ ከኦሮሚያ ስለሚለየው ጎጃም ውስጥ የነበረው ኦሮምኛ ሙሉ በሙሉ እንደጠፋ ቀረ/ ። እናም አማርኛ በዚህ መልኩ በፍጥነት ተስፋቶ ሰፊ የአማርኛ ቋንቋ ብቻ ተናጋሪ ክልል ምፍጠር ቻለ ። ስለዚህ አማራ ብሔርን የፈጠረው ቋንቋ ነው ማለት ነው፤ ስለሆነም አማራ ማለት የአማርኛ ቋንቋን ቀድሞ የተቀበለ የሁሉም ነገዶች ስብስብ ነው ማለት ነው ።

አማርኛ ቋንቋ ከየትኛው የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል? ለሚለው ጥያቄ ፡ - አማርኛ ከአረብኛ፣ ከግዕዝና ከትግርኛ የመጣ እንደሆነ ይታወቃል ። ግዕዝ /አማርኛ/ ከአረብኛ የመጣ መሆኑን ለማሳየት ያህል ፡ - ሀምሲ-ሀምሳ፣ አርባ-አርባ፣ አሽራ ዋህድ-አስራ አንድ፣ ዋህድአንድ፣ ሱልጣን- ስልጣን፣ ጀነት- ገነት፣ ተወከል- ወኪል፣ መዲና-መዲና …ወዘተ ። እናም የግዕዝ አባት አረብኛ መሆኑ የሚያጠራጥር ጉዳይ ስላልሆነ በሁሉም የታሪክ መፅሀፎች ላይ ተፅፎ ይገኛል ።

የሸዋው ሚኒሊክ በፈጠሯት በዚች በሰፊዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ70 በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ /ኢትዮጵያ የሚለው መጠሪያ ስም የመጣው ጥንት ኢትዮጵያ የኩሽ ሀገር ተብላ ትታወቅ ስለነበር በኦሪት ላይ ‘’ኩሽ’’ ተብላ ሰፍራለች ። እናም በኋላ ላይ 70 ሊቃውንት በጋራ ሆነው ብሉይን ከእብራይጥ ወደ ፅርዕ /ግሪክ/ ሲተረጉሙ ‘’ኩሽ’’ የሚለውን ቃል ‘’አይቶ ፒያ’’ ብለው ተረጎሙት፤ የህንኑ መፅሀፍ ወደ ግዕዝ ሲተረጉሙ ቃሉን ብቻ እንደወረደ ‘’ኢትዮጵያ’’ ብለው አስቀመጡት ። አንዳንድ የሀገር ውስጥ ፀሀፊዎች ኢትዮጵያ የሚለው ስም በንጉስ ኢትዮጲስ 1ኛ ስም የተሰየመ ነው ብለው ፅፈዋል፤ ይህ ስህተት ነው፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከንጉስ ኢትዮጲስ 1ኛ በፊት ይታወቅ ነበር ። አቢሲኒያ የሚለው ደግሞ የኩሽ የልጅ ልጅ በነበረው /በናምሩድ ልጅ/ በአቢስ ስም የተሰየመ ነው ። ሐበሻ ‘’ሐበሽ’’ ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ነው፤ ሐበሽ በአረብኛ ድብልቅ ማለት ነው/ ። እናም እነዚህን በአሁኒቷ በሰፊዋ ኢትዮጵያ የሚነገሩትን ከ70 በላይ ቋንቋዎች ምሁራኑ በ3 ከፍለዋቸዋል ። እነሱም ፡ -

1. **የኩሽ ቋንቋዎች ፡ -** አገውኛ፣ ኦሮምኛ፣ ሱማሊኛ፣ አፋርኛ፣ ሲዳምኛ፣ ሳሆኛ፣ ሀድይኛ፣ ከምባትኛ፣ ኮንሶኛ፣ ቤጂኛ፣ ብሌን፣ ደራሲኛ …ወዘተ የሚገኙበት ሲሆን በጠቅላላው 23 ያህል የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው ።
2. **የሴም ቋንቋዎች ፡ -** አማርኛ፣ ትግረ፣ ትግርኛ፣ ጋፋትኛ፣ ጉራግኛ፣ አርጎብኛ፣ ሐረርኛ …ወዘተ የሚገኙበት ሲሆን በጠቅላላው 17 ያህል የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የሴም ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው ።
3. **የኦሞ ቋንቋዎች ፡ -** ወላይትኛ፣ ሸናሸኛ፣ ዶርዚኛ፣ ማጂኛ፣ ኮሉኛ /ኮንታ/፣ ጃንጃሮኛ፣ ጊሚርኛ …ወዘተ የሚገኙበት ሲሆን በጠቅላላው 16 ያህል የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የኦሞቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው ።

ከነዚህ ከ56ቱ /23 + 17 + 16/ ውጭ ያሉት ቋንቋዎች ገና በርግጠኝነት ተለይተው ያልተመደቡ ናቸው ።

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ነገዶች ሁሉ እስከ አፄ ሚኒሊክ ዘመን ድረስ ለየብቻ ተከፋፍለው ይኖሩ ነበር ። ከአፄ ሚኒሊክ በፊት አማራና ትግሬ ብቻ ነበሩ አንድላይ የነበሩት ። የሸዋው ሚኒሊክ ግን በየአቅጣጫው እየዘመቱ እነኝህን ነገዶች ሁሉ አንድ ማድረግ ችለዋል /ምስጋና ይገባቸዋል/ ።

## ያኮረፉ ምድሮች /ወሊጋና ጎጃም/

አንድትን እጅግ ሰፊ የሆነች ሀገር መፍጠርና አንድነቷን ጠብቆ ለትውልድ ለማስረከብ እጅግ በርካታ መሰዋዕትነቶችን መክፈልን ይጠይቃል ፡ በአለም ላይ ጥቂት ሰፋፊ ሀገሮች ቢኖሩም ምርት ሊመረትበት የሚችለው የሀገራቸው ክፍል /productive land/ በጣም ጠባብ ነው ፡ ለምሳሌ ያህል ጎረቤታችን ሱዳን ሰፊ ሀገር ነች፤ ነገር ግን አብዛኛው አካሏ በረሀ ስለሆነ ምርት ሊመረትበት አይችልም፣ በአለም በቆዳ ስፋቷ አንደኛ የሆነችው ሩሲያም ብዙው አካባቢዋ እጅግ ቀዝቃዛና በረዶ ስለሆነ ምርት ሊመረትበት አይችልም ። ሰፊዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ምርት የማይመረትበት አካባቢ የለም፤

የሱማሌና የአፋር ምድሮችም ቢሆኑ የክረምት ዝናባቸውን በግድብ እየያዝን ብንጠቀምባቸው የፈለግነውን ያህል ምርት መስጠት ይችላሉ ።

ኢትዮጵያ እጅግ ሰፊ ሀገር በመሆኗ ምክንያት እጅግ በርካታ በተፈጥሮ የከበሩ /ሀብታም/ ምድሮች ባለቤት ሆናለች /ኢትዮጵያ ያለምንም የቴክኖሎጂ እገዛ በተፈጥሮ ብቻ በቂ ምርት ሊሰጡ የሚችሉ እጅግ ብዙ ሰፋፊ የከበሩ ምድሮች ባለቤት ነች/ ። ለምሳሌ ያህል ''የኢትዮጵያ ካናዳ'' እየተባሉ የሚጠሩት የአሩሲና የባሌ ምድሮች ኢትዮጵያን በየአመቱ የምትፈልገውን ያህል የስንደና የገብስ ምርት ይሰጧታል ። በመስከረምና በጥቅምት አንድ አሩሲና ባሌን ለጎበኘ ሰው፣ ከአሰላ ጀምረህ መኪናህን ወደ ባሌ አቅጣጫ ቀኑን ሙሉ ስታሽከረክር ስትውል ያ በተፈጥሮ የከበረ የአሩሲና የባሌ ሜዳ አይንህ እስከደረሰበት ድረስ በስንደና በገብስ ተሞልቶ ስታይ ስትውል ካናዳ እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለህ አይመስልህም ። ''የኢትዮጵያ ካናዳ'' አሩሲና ባሌ ባይኖሩ ኖሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ስንደ በወርቅ ዋጋ /እጅግ በውድ ዋጋ/ ይሸጥ ነበር ። እንዲሁም በተፈጥሮ የከበሩት የጎጃም፣ የጎንደርና የሸዋ ምድሮች ኢትዮጵያን በየአመቱ የምትፈልገውን ያህል የጤፍ ምርት ይሰጧታል ፡ በመስከረምና በጥቅምት በተፈጥሮ ብቻ የከበረው የጎጃም ምድር ጫፍ እስከ ጫፍ በጤፍ ሰብል ተሞልቶ ይታያል፤ እንዲሁም ሸዋን በመስከረምና በጥቅምት ከአዲስ አበባ ተነስተን በአምቦ መስመርም ሆነ በደብረዘይት መስመር ብንጓዝ ሀብታሙ የሸዋ ምድር በጤፍ ተሞልቶ ይታያል /በእርግጥ ሸዋ ውስጥ የሚመረተው ጤፍ ከጎጃም ጋር አይወዳደርም፤ ምክንያቱም በደብረዘይት መስመርም ሞጆ ሳይደርስ ያቆማል፣ በደብረብረሃን መስመርም ለገጣፎ ላይ ያቆማል፣ በታችኛው መስመርም የለውም፣ በአምቦ መስመር ይሻላል፤ ሆኖም ግን ሸዋ ውስጥ የሚመረተው ጤፍ ጎጃምና ጎንደር ውስጥ የሚመረተውን እጅግ ሰፊ የጤፍ ምርት ከማገዝ አንፃር የማይናቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል/ ። ያው ሁላችንም እንደምናውቀው ኢትዮጵያ ውስጥ ወጡ ይለያያል እንጂ ሁሉም ሰው የሚበላው የጤፍ እንጀራ ነው፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ታዲያ በተፈጥሮ የከበሩት የጎጃም፣ የጎንደርና የሸዋ ምድሮች ስላሉን ነው፤ የጎጃም፣ የጎንደርና የሸዋ ምድሮች ባይኖሩን ኖሮ ልክ እንደ ኤርትራ ኢትዮጵያም ውስጥ የጤፍ

እንጀራ ለብርቅ ነበር የሚበላው ። እንዲሁም የአርባ ምንጭ ምንጮች ባይኖሩ ኖሮ አዲስ አበባ ውስጥ ሙዝ በፍለጋ አይገኝም ነበር ። የወሎና

የትግራይ ገደሎችም ቢሆኑ በቂ ዝናብ አያገኙም እንጂ በቂ ዝናብ /ውሀ/ ካገኙ በቂ ምርት መስጠት ይችላሉ /የወሎና የትግራይ ክረምት አንድ ወር ነው፣ የወሎና የትግራይ የክረምት ዝናብ ሐምሌ 17 ቀን አካባቢ ጀምሮ ነሐሴ 20 ቀን አካባቢ ያቆማል/ ፡፡

እናም አባቶቻችን /ሸዋና የጁ/ በስልጣኔ ወደ ኋላ ቢያስቀሩንም ይችን ጫፍ እስከ ጫፍ ሊመረትባት የምትችልና የበርካታ በተፈጥሮ የከበሩ ምድሮች ባለቤት የሆነችን እጅግ ሰፊ ሀገር አንድነቷን ጠብቀው ስላስረከቡን ሊመሰገኑ ይገባቸዋል ማለት ነው ፡፡ አንዳንዶች በዚች እጅግ ሰፊ ሀገር ውስጥ ለመጠቀም ይሞክራሉ፤ ጀግኖች ባይኖሩ ኖሮ ይች ሰፊ ሀገር ትገኝ ነበር ወይ? ነው ጥያቄው ፡፡

ዋናው ጥያቄ ታዲያ ሸዋና የጁ ይችን የምታክል እጅግ ሰፊና በተፈጥሮ የከበረች ሀገር እንደት መፍጠር /ማቅናት/ ቻሉ? እንደትስ እስከ አሁን ድረስ አንድነቷን ሊጠብቁት ቻሉ? ከውጭ ወራሪስ /አድዋ/ እንደት ሊያድኗት ቻሉ? ነው ፡፡

ቀደም ሲል የወፋን ባህላዊ ውጊያ አይተናል፤ እናም የኢትዮጵያ ስፋት፣ አንድነትና ነፃነት የወፋ ባህላዊ ውጊያ ውጤቶች መሆናቸውን አስተውለናል ፡፡ ሸዋና የጁ ኢትዮጵያን ያቀኗት /ያሰፏት/፣ አንድነቷንና ነፃነቷን ጠብቀው እዚህ ያደረሷት የውስጥና የውጭ የሀገሪቱን ጠላቶች እየወቁ /እየደበደቡ/ ነው፤ ሸዋና የጁ ያልወቁት የለም ፡፡ ሸዋና የጁ ኢትዮጵያን ያቀኗት /ያሰፏት/ በየቦታው የነበሩ መሳፍንቶችንና ባላባቶችን እየተዋጉ እያሸነፉ ነው፤ በአፄ ሚኒሊክ ስር እንዳየነው ሸዋ፣ የጁና ወረሂመኖ ሀገር በሚያሰፉበት ጊዜ እንቅፋት በመሆናቸው ምክንያት ከተደበደቡት አካባቢዎች ውስጥ

ጎጃም /3 ጊዜ/፣ ሐረር /1 ጊዜ/፣ ወላይታ /1 ጊዜ/፣ አሩሲ /1 ጊዜ/፣ ደቡብ፣ ጊቤ አካባቢ፣ ከፋ አካባቢ …ወዘተ ይገኙበታል /ቅደም ተከተሉ በድብደባው ክብደት ነው/ ፡፡ እነኝህ ሁሉ የተወቁት /የተደበደቡት/ ግን በቅድሚያ በሰላም አንድ እንሁን እየተባለ እየተላከባቸው እምቢ እንዋጋለን በማለታቸው ነው ፡፡ በአፄ ሚኒሊክ ስር እንዳየነው ጎጃሜዎች ላይ የተፈፀመው ድብደባ ከሌሎቹ ይልቅ እጅግ መረር ያለ ነበር፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ጎጃሜዎች ከወሎ ጋር ሁለት ጊዜ ተዋግተው ተሸንፈው ምህረት

ከተደረገላቸው በኋላ እንደገና ለ 3ኛ ጊዜ በመጋጠማቸው ነው ፡፡ እናም 2 ጊዜ ምህረት ከተደረገላቸው በኋላ ለ 3ኛ ጊዜ በመጋጠማቸው ምክንያት ጎጃሜዎች ላይ እጅግ ጠንከር ያለ እርምጃ በመወሰዱ እጅግ ዘግናኝ እልቂት ተከስቷል ፡፡ በጎጃሜዎች በኩል የሞተውን ሬሳውንና ነፍሱ ያልወጣችውን ቁስለኛ መለየት እስከሚያቅት ድረስ እጅግ ብዙ ጎጃሜዎች አልቀዋል ፡፡ በመሆኑም በሐረር ጦርነት፣ በወላይታ ጦርነት፣ በአሩሲ ጦርነት፣ በደቡብ ጦርነት፣ በጊቤ አካባቢ ጦርነት፣ በከፋ አካባቢ ጦርነት ወዘተ የሞተው ህዝብ ሁሉ ቢደመር እንኳ የጎጃም በ3ኛው ጦርነት ጊዜ ብቻ የሞተውን ህዝብ አያክልም ፡፡ ይህ ሁኔታ ነው እንግዲህ ጎጃሜዎች በወሎ ላይ በተለይ በየጁ ላይ እስከ አሁን ድረስ አልጠፋ ብሎ ያስቸገረውን ቅሬታ እንዲይዙ ያደረጋቸው /በሁለተኛው የጎጃም ጦርነት ጊዜ አፄ ሚኒሊክ ያዘዙት ባብዛኛው የጁዎችን የነበረ ሲሆን በ3ኛውም ጦርነት ጊዜ የጁዎች ይበዙ ነበር፣ የጁ የአፄ ሚኒሊክ ሚስት የእቴጌ ጣይቱ ሀገር ነው፣ የጁዎች ብቸኛ ሰለሞናዊ ስረወ መንግስትን ስልጣን መንጠቅ የቻሉ ስለሆኑ አፄ ሚኒሊክም ሁልጊዜ በየጁ ያምኑ ነበር፣ እቴጌ ጣይቱ መካን ቢሆኑም አፄ ሚኒሊክ በየጁ ስለሚያምኑ እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ እቴጌ ጣይቱን በቁርባን አግብተው ነው የኖሩት/ ፡፡ እናም ቀደም ሲል እንዳየነው በዚህ ጦርነት ምክንያት ጎጃሜዎች በወሎ ላይ እጅግ ከባድ ቅሬታ በመያዛቸው ምክንያት ''ባንዳ'' ሆነው በማገልገል ሀገሪቱን በውጭ ጠላት እንዲትደፈር እስከማድረግ ድረስ ሄደዋል /የኢጣሊያ ዳግም ወረራ/ ፡፡

እርዕሳችን ላይ ወለጋን አስቀድመን ''ወለጋና ጎጃም'' ያልንበት ምክንያት ወለጋ ሲባል ትኩረት እንደሚስብ ስለምናውቅ ነው እንጂ ካላቸው የቅሬታ መጠን አንፃር ሲታይ ግን ቅደም ተከተሉ መሆን ያለበት ''ጎጃምና ወለጋ'' ነው ፡፡ በወለጋ በኩል ያለው ቅሬታ እንዲሁ በህዝቡ ዘንድ ጎልቶ ይታያል እንጂ በሀገሪቱ በኢትዮጵያ ላይ እስከ አሁን ድረስ ያደረሰው ጉዳት የለም፤ እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ ላይ በደረሱ የውጭ ጥቃቶች ላይ በወለጋ በኩል ምንም አይነት የሀገር ክህደት አልተመዘገበም /ተፅፎ አይገኝም/ ፡፡ በጎጃም በኩል ያለው ቅሬታ ግን ማንም ልብ የማይለውና ሀገሪቱን እስከማስደፈር የደረሰና አሁንም በሀገሪቱ ታሪኮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ያለ እጅግ ከባድ ቅሬታ ነው ፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነውና በአፄ ኃይለስላሴም ስር እንደምናየው በኢጣሊያ ዳግም ወረራ ጊዜ የጎጃም ባላባቶች ከነሙሉ ሰራዊታቸው የፈፀሙት ክህደት ለኢጣሊያ አሸናፊነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ

አድርጓል /ከህደቱ የኢትዮጵያ ሰራዊትን የአንድነት ስሜትንና መተማመንን አፍረሶታል/ ።

እናም ውጮቹ የሰለጠኑት ሀገሮች እንደሚያደርጉት እንደነኘህ አይነት መጥፎ ታሪኮቻችንን በግልፅ አውጥቶ ትውልድ እንዲማርባቸውና የዚህ መጥፎ የታሪክ ባለቤቶችም በድርጊታቸው እንዲያፍሩና ዳግም ወደ መሰል ድርጊት እንዳይመለሱ ማድረግ ወደ ፊት ለሀገሪቱ ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል ። ለምሳሌ ያህል የአሁኑ የአሜሪካ ብሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ በእሩሲያ ጣልቃ ገብነት እንደተመረጠ ይጠረጠራል ። በዚህም ምክንያት እስከ አሁንም ድረስ የአሜሪካ ሚዲያዎች ትራምፕን ከእሩሲያ ጋር በማያያዝ እየነነተሉት እረፍት ነስተውት ቀጥለዋል፤ እንዳንዶቻችን መጀመሪያ አካባቢ በትራምፕ ላይ ጉንተላው /ዝርጠጣው/ ለረጅም ጊዜ ሲቆይበት አይተን ''እረ አሁንስ በተውት'' እንል ነበር፤ የአሜሪካ ሚዲያዎች ግን ጉንተላቸውን እስከ አሁንም ድረስ ቀጠሉበት እኛም ''እረ አሁንስ በተውት'' ማለቱን ትተን ''ይኸ ሰውዬ ቢቀርበት ይሻለው ነበር'' ማለት ጀመርን፣ ይህ ማለት እንግዲህ ሁሉም የአሜሪካ ዜጋ ''ይህ ሰውዬ ቢቀርበት ይሻለው ነበር'' አለ ማለት ነው፤ ይህ ማለት ደግሞ ከዚህ በኋላ ያለ ህዝብ ምርጫ በትራምፕ መንገድ ወደ ስልጣን የሚመጣ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት አይኖርም ማለት ነው /የሚድያዎቹም የማያቋርጥ ጉንተላ ይህን ውጤት ለማምጣት ነበር ማለት ነው/ ። ነገር ግን የትራምፕ ጉንተላ ለአንድ ሰሞን ብቻ ሆኖ ቢቀር ኖሮ ትራምፕ ወደ ስልጣን የመጡበት መንገድ እንደ አንድ የስልጣን መያዣያ አማራጭ ሆኖ ይቀጥል ነበር ማለት ነው /በሀገራቸው ላይ የውጭ ጣልቃ ገብነት ይቀጥል ነበር ማለት ነው/ ።

እናም በእኛም ዘንድ ፡ -

እምዬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፣

የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ ።

አይነት ዘፈኖችን መዝፈን ብቻ በቂ አይደለም፤ ምክንያቱም ጎጃሜዎች አሁንም ከመጥፎ ድርጊታቸው ሊቆጠቡ አልቻሉም ። ከአንድ የጎጃም ሰው አፍ ውስጥ አፄ ሚኒሊክ፣ እቴጌ ጣይቱ፣ አፄ ኃይለስላሴ፣ ላሊበላ፣ ግሸን … ወዘተ የመሳሰሉ የወሎ ስሞች ከአፋቸው አይወጡም ከወጡም በግድ ነው፤

ልብ አንለውም እንጂ ''ኢትዮጵያ'' የሚለው ቃልም ከጎጃምና ከጎንደር ሰዎች አፍ ላይ የተለመደ አይደለም፤ ''ጎንደር፣ ጎጃም'' ስለሚሉ ብቻ ኢትዮጵያ ያሉ ይመስለናል እንጂ ''ኢትዮጵያ'' የሚለው ቃል በግድ ነው ከአፋቸው የሚወጣው፤ ይህ እየሆነ ያለው ታዳ በኢትዮጵያን ፈጠራው ላይ /በሀገር ማቅናቱ ላይ/ እንደሌሉበት ስለሚዌውቁ ነው ። ይህን ተከትሎ ጎንደርና ጎጃም ውስጥ ባህል እየሆነ የመጣ አደገኝ ነገር አለ፤ በአካባቢያቸው ማህበረሰብ ዘንድ እንደእነኝህ አይነት ነገሮችን ማሳየትን እንደ ስልጣኔና ጀግንነት የመቁጠር ባህል አለ፤ ይህ ባህል ለሀገሪቱ እጅግ ጎጅ ነው እናም ግልፅ መውጣት አለበት ነው እያልን ያለነው ። ለምሳሌ ያህል፣ ጎጃም ውስጥ ከንዋይ ደበበ የበለጠ ጀግና የለም፤ ምክንያቱ ደግሞ ደስ በሚልና በግድ ጆሮ ውስጥ በሚገባ ዜማ

''ጋምዬ ነይ ጋምዬ''፣

''እንግዴህ ጎጃም ላይ ምን ተሰራ አትበሉ፣

ታሪክ ጠይቃችሁ በላይ በላይ በሉ''

በሚለው ዘፈኑ የበላይ ዘለቀን ታሪክ ከወሎ በመንጠቁ ነው ። ቀደም ሲልም እንደምሳሌ ''የዜማ የቅኔ የቀሳውስት ሀገር'' የሚለውን የንዋይን ዘፈን አይተናል፣ እዚህ ዘፈን ውስጥ የአፍሪካ ትልቁ ቅርስ ላሊበላ አልተጠቀሰም፤ በሚገርም ሁኔታ ''ፋሲለደስ አክሱም የታሪክ ምስክር'' ሲል ፋሲለደስም የሸዋ ሰዎች ቅርስ እንደሆነ ዘፋኙ አሳምሮ ያውቃል /ህዝቡ ታሪኩን እንደማያውቅና እንደተደነባበረ ስለሚያውቅ ነው ፋሲለደስን የጎንደር ቅርስ ለማስመሰል ''አክሱም ላሊበላ'' በማለት ፋንታ ''ፋሲለደስ አክሱም'' ያለው/ ። ይህ እንግድህ ምን ያህል የወሎ /የኢትዮጵያ/ ታሪኮች ከአፋቸው እንደማይወጡና የኢትዮጵያ ታሪኮችንም በምን አይነት ስልት ወደ እነሱ እየቀየሯቸው እንደሆነ ያሳያል ።

ይህ በአጠቃላይ የጎንደርና የጎጃም ባህል ነው፤ ጎንደርና ጎጃም ውስጥ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ጀግና የምትባለውና የምትሞገሰው አንድ የወሎን ታሪክ ደስ በሚል ኪነጥበብ የጎንደር ወይ የጎጃም አስመስለህ ስርተህ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተደራሽ ያደረክ እንደሆነ ነው ። ለምሳሌ ያህል ስለ አፄ ቴዎድሮስ ሚስት፣ ስለትንሹ ራስ አሊ ልጅ ስለ እቴጌ ተዋበች ሞት የፃፈ አንድ የጎንደር ፀሐፊ ፡ - ''እስኪ ጠይቁልኝ እርቃ ሳትሄድ፣እቴጌ ተዋበች

ሚስት ናት ገረድ’’ ብሎ በመፃፉና ግጥሙ በተለያዩ ስልቶች ለህዝብ በመድረሱ ምክንያት ፀሀፊው በጎንደር ሰዎች ዘንድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ ጀግና ተብሎበታል /በሚገርም ሁኔታ አፄ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ነገስታት ታሪክ ውስጥ ከሚስቱ ከእቴጌ ተዋበች ውጭ ሌላ ሴት አያውቅም፤ ምክንያቱ ደግሞ የአፄ ቴዎድሮስ አነጋገስ ላይ ያየነው ነው/ ።

እናም በጎንደርና በጎጃም ማህበረሰብ ዘንድ እንደ ጀግና የምትቆጠረው እንደዚህ የወሎን ስም አጥፍተህ ታሪኩን ያንተ አስመስለህ ለህዝብ ያደረስክ እንደሆነ ነው ። ይህ ሁኔታ በየጊዜው የኢትዮጵያን ታሪክ እያጠፋና የአፄ ቴዎድሮስና የበላይ ዘለቀ ታሪክ ብቻ እያስመሰለው ቀጥሏል ።

ሌላውና ዋናው ጎንደርና ጎጃም የኢትዮጵያን ታሪክ ለመቀየር የሚከተሉት ስልት የወሎን ተፈጥሮ እንዳልወደዱት በማስመሰል የወሎን ስም ማደብዘዝን ነው፤ ነገር ግን እውነታው ሌላ ነው /ወሎን ጠልተው አይደለም/፤ ምክንያቱም ለምሳሌ ያህል፣ የጎጃሙ ጀግና ንዋይ ለሐረር ዘፍኗል፤ የሐረርና የወሎ ህዝብ ተፈጥሮ ደግሞ አንድ አይነት ነው፣ የወሎና የጉራጌ ህዝብ ተፈጥሮም አንድ አይነት ነው ። ስለዚህ ወሎን ጠልተውት ሳይሆን ታሪኩ ግልፅ እንዳይወጣ ስለሚፈሩ ነው ማለት ነው ። ከሆነም ደግሞ ይህ እነሱ የፈጠሩት ስልት እነሱን ብቻ የኢትዮጵያ የታሪክ ባለቤት ሊያደርጋቸው አይገባም፤ ሌሎች ከእነሱ እጅግ የተሻለ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ብሔረሰቦችም የኢትዩጵያ ታሪክ ባለቤት መሆን አለባቸው /ወሎ የሁሉም ብሄረሰቦች ድብልቅ ነው/ ። ይህ የሚሆነው ታዳ በታሪክ ስነፅሁፍና በታሪክ የዘፈን ስራ ውስጥ ሌሎቹ ብሔረሰቦችም ተሳታፊ ከሆኑና የኢትዮጵያን ትክክለኛ ታሪክ በየጊዜው ለህዝብ ማድረስ ከቻሉ ብቻ ነው ። ይህ ግን እየሆነ አይደለም፤ ይህ የማይሆንበት ዋናው ምክንያት ደግሞ አንዳንድ ብሔረሰቦች የሚያዩት የሚነገረው ቋንቋ አማርኛ መሆኑን ነው፤ ይህ እጅግ ስህተት ነው፤ ቀደም ሲል እንዳየነው አማርኛ ቋንቋ ከመምጣቱ በፊት የጎንደሬዎችም ቋንቋ ጋፋትኛ፣ ኳረኛና ቅማንትኛ ነበር ። ግዕዝ /አረብኛ/ መናገራችን ደግሞ በዙሪያችን ያሉት ሀገሮች አረብ በመሆናቸው ነው /አረብ ocean ውስጥ ስለምንገኝ ነው/ ። ቀደም ሲል እንዳየነው አማርኛ ቋንቋ የማንም ያልሆነ የወታደሮች ቋንቋ ነው፤ አረብኛው ከየመን መጥቶ ትግራይ ውስጥ ወደ ግዕዝነት ተቀየረ ከዚያም ላስታ /አገው/ ውስጥ በወታደሮቹ አማካኝነት ወደ አማርኛ ተቀየረ ። አረብኛ ቋንቋ ደግሞ በአሁኑም ወቅት ቢሆን አለምን እየወረረ ያለ ቋንቋ ነው፤ የኢትዮጵያ

ህዝብ አብዛኛው ሙስሊም ቢሆን ኖሮ ምን ልንሆን ነበር፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ሙስሊም ሆኖ ቢሆን ኖሮ ይህኔ ይህ ሁሉ የኢትዮጵያ ቋንቋ ጠፍቶ የኢትዮጵያ ብቸኛ ቋንቋ አረብኛ ብቻ ይሆን ነበር /ሱዳንና ግብፅ በርካታ የራሳቸው ቋንቋዎች ነበሯቸው፤ አሁን ግን ሁሉንም ቋንቋዎቻቸውን አረብኛ አጥፍቷቸው፣ ተረስተው ተረት ሆነው፣ አረብኛ ብቸኛ የሀገሮቹ ቋንቋ ሆኗል/ ። ስለዚህ አረብኛ መናገራችንን ሳይሆን ታሪካችንን ነው ማየት ያለብን ማለት ነው ። አብዛኞች ጎንደር ላይ ያለውን አሮጌውን ቤተመንግስት የሸዋዎች መሆኑን እንኳ ስለማያውቁ የጎንደርን ቤተመንግስት በቴሌቭዥ ሲያዩ የኢትዮጵያ ታሪክ የማይመለከታቸው ስለሚመስላቸው ወደ የታሪክ ዘፈን ስራና የታሪክ መፅሀፎች ድርሽ /ዝር/ አይሉም ። ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው ነው የኢትዮጵያን ታሪክ እያበላሹት የቀጠሉት ።

እናም ሌሎቹ ብሄረሰቦች በጋራ ይህን የጎጃምንና የጎንደርን ማህበረሰብ የመሞገሻ ባህል በመከላከል፣ በስነፅሁፍና በዜማ የኢትዮጵያን ትክክለኛ ታሪክ በየጊዜው ለህዝብ ማድረስ አለባቸው ማለት ነው ። ለቀጣዩም ትውልድ ትክክለኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ አስቀምጦ ማለፍ ከሁሉም ብሄረሰቦች ይጠበቃል ማለት ነው ።

ወደ ርዕሳችን ስንመለስ ፡ - በኢጣሊያ ዳግም ወረራ ጊዜ እንዳየነው እነዚህ በግንዛቤ ችግር የተፈጠሩ ቅሬታዎች ግልፅ ካልወጡ በስተቀር ውስጥ ውስጡን የሀገሪቱን ታሪክ ማጥፋት ብቻም ሳይሆን የሀገሪቱንም አንድነት ችግር ውስጥ ሊከቱት ይችላሉ ። ሸዋና የጁ በጎጃም ላይና በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የፈፀሙት ድብደባ የሀገር ማቅናቱ /ማስፋቱ/ አካል እንጂ ቅሬታ ሚያስከትል ነገር አይደለም ። ሸዋና የጁ እየወቁ አንድ ባያደርጉን ኖሮ ይህኔ ይችን የምታክል እጅግ ሰፊና በተፈጥሮ የከበረች ሀገር አትኖረንም ነበር ማለት ነው ። ስለሆነም ከዚህ ያረጀ አስተሳሰብ ከፈጠረው ኋላቀር አመለካከታችንና ጭፍንነታችን መውጣት ይኖርብናል ማለት ነው

በአረጀ አስተሳሰብና ጭፍንነት ምክንያት የተፈጠረው የጎጃሞች ቅሬታና እያስከተለው ያለው ጥፋት ያየነውን ሲመስል የወለጋዎች ቅሬታ ግን በወቅቱ የሀገሪቱ አጠቃላይ ችግር ከነበረው ከባሪያ ንግድ ጋር የተያያዘና በተጨባጭ ተፅፎ የማይገኝ የመንደር ወሬ ነው ። ወሬዎች ደግሞ ሁል ጊዜ መነሻቸውና አላማቸው ይለያያል፤ ለምሳሌ ያህል አፄ ኃይለስላሴንና አፄ ሚኒሊክን ይቃወሙ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች እራሳቸው እየፈበረኩ /እየፈጠሩ/

የለቀቋቸው ወሬዎች ቢሆኑስ ማንያውቃል? ስለሆነም በተጨባጭ ተፅፈው በማይገኙ የመንደር ወሬዎች ላይ ተመስርቶ መፃፍም ሆነ ዘፈን መስራት አይቻልም ማለት ነው /ወሬዎች አላማቸው ይለያያል/ ፡፡ እናም የወቅቱ የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴ መጠኑ ይለያያል እንጅ ወለጋ ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተከሰተ ችግር ነበር፤ ስለሆነም ችግሩ የወለጋዎች ችግር ብቻ አልነበረም ማለት ነው ፡፡ ኢንፎርሜሽን በሰበሰብንበትና ሰዎችን ባነጋገርንበት ወቅትም ወለጋ ላይ ከሌሎቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተለዬ ሊፃፍ የሚችል ተጨባጭ ነገር አላገኘንም ፡፡ ስለሆነም የወለጋ ቅሬታ ተፅፎ የማይገኝና የወቅቱን ሁኔታ እንኳን ካለማወቅ የመጣ እጅግ ያረጀ አስተሳሰብና ኋለቀር አመለካከት የወለደው ቅሬታ ነው ማለት ነው /conservativeness የወለደው ቅሬታ ነው ማለት ነው/ ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያች ቀደም ሲል ያየናት ከገላና ወንዝ ጋር የተያያዘችው ቃልም በወለጋዎች ዘንድ ቅሬታ ሳታሳድር አትቀርም ፡፡ እናም ኢትዮጵያ ውስጥ ካለማንበብና ታሪክን ካለማወቅም ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮች አሉ ማለት ነው ፡፡ ወደ ዋናው ርዕሳችን ስንመለስ ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## ልጅ እያሱ (ከ1906-1909)

ጋዜጠኛ ፍሰሐ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፅሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋለሁ ፡፡

የልጅ እያሱ እናት ወ/ሮ ሸዋረጋ ከእናታቸዉ ከወ/ሮ ደስታና ከአባታቸዉ ከአፄ ሚኒሊክ በድብቅ የተወለዱ ነበሩ ፡፡ ወ/ሮ ደስታ በቤተመንግስት ዉስጥ በጠጅ ክፍል ሲሰሩ የኖሩ ናቸዉ ፡፡ በወ/ሮ ደስታ ዉበት የተማረኩት አፄ ሚኒሊክ በድብቅ ተገናኟቸዉና ፀነሱ ፡፡ ወዘሮዋ መፀነሳቸዉን እንዳወቁ ሸሽተዉ ወደ አገራቸው ወደ ወሎ በማቅናት ኑሯቸዉን እዚያዉ መሰረቱ ፡፡ ወዳዉም ሸዋረጋ ተወለደች ፡፡

ሸዋረጋ ለአቅመ አዳም እንደደረሰች አግብታ ከወታደር ባለቤቷ ጋር ወደ ሐረርጌ ሄዳ መኖር ጀመረች ። የሸዋረጋ ባለቤት ምንም ቢሆን ልታወልወቀዉ የማትደፍረዉን የአንገት ክታቧን ተጠራጥሮ አዉልቆ ከፍቶ ሲያነበዉ፤ የአፄ ሚኒሊክ ልጅ መሆኗን ተረዳ ። ሁኔታዉ ቢያስደነግጠዉም ይህን ሚስጥር ገልጦ ለእቴጌ ጣይቱ ቢናገር ሊያሾመዉና ሊያሸልመዉ እንደሚችል በመገንዘብ ሚስቱን ይዞ ወደ እቴጌ ጣይቱ ሄዶ ለእቴጌ ጣይቱ ጉዳዩን ገልጦ አስረዳ ።

እቴጌ ጣይቱም መካን ስለሆኑ ሸዋረጋን በደስታ ተቀብለዉ ቤተመንግስት ዉስጥ እንድትቀር አድርገዉ ሚስጥሩን ለነገራቸዉ ወታደርም ተገቢዉን ወረታ ከፍለዉ አሰናበቱት ።

እቴጌዋ ከቀናት በኋላ ሸዋረጋን አለባብሰዉ፣ ኳኩለዉና ከሌሎች ወዛዝርት ጋር ቀላቅለዉ ንጉስ ሚኒሊክን እጅ እንዲነሱ ሲያደርጉ፣ አፄ ሚኒሊክ ሸዋረጋ ላይ አፍጥጠዉ “ይች የማናት ልጅ” ብለዉ ሲጠይቁ፣ የወ/ሮ ደስታ ልጅ መሆኗ ተነገራቸዉ ። ሸዋረጋም ኑሮዋን በዚያዉ በቤተመንግስት ዉስጥ ቀጠለች ። ዉበቷ የመኳንንቱን አይን መሳብ ጀመረ ። ብዙም ሳትቆይ የአፄ ሚኒሊክ አብሮ አደግ ለነበሩት ለራስ ጉበና ዳጪ ልጅ ለወዳጆ ጎበና ተዳረች ፡ ይህ ትዳር ግን ሳይቆይ ወዳዉ ፈረሰና ራስ ሚካኤልን /መሐመድ ዓሊን/ አገባች ። ከወዳጆ ጋር ያለዉን ትዳር ለምን በፍጥነት እንዳፈረሱት አልታወቀም ።

አንዳንዶች እንደሚሉት ከሆነ ግን የወዳጆ ጎበናና የሸዋረጋ ሚኒሊክ ትዳር እንዲፈርስ የተደረገበት ምክንያት በሚከተለዉ ትንቢት ነዉ ይላሉ ፡ -

- ጌታዉ መሐመድ ዓሊ በአዳራሹ ገብተህ በእልፍኝ ብትወጣ፣
- ወቀሳ ቢያገኝህ እኔ በጉድ ልዉጣ፣
- በዳግመኛዉ እግርህ ሸዋረጋን አምጣ፣
- ከእመት ሸዋረጋ የሚገኘዉ ልጅ፣
- እምብዛም አይከፋ እምብዛም አይበጅ ።

በዚህ ትንቢት ምክንያት ይመስላል ራስ ሚካኤል ሸዋረጋን ለማግባት ለአፄ ሚኒሊክ ጥያቄ አቀረቡ ። አፄ ሚኒሊክም ራስ ሚካኤል ከአላቸዉ ኃይልና ከተፅኖ ፈጣሪነታቸዉ አንፃር ስለሚስፈልጓቸዉ ወዳዉ ሸዋረጋን

ለራስ ሚካኤል ዳሯት /አፄ ሚኒሊክ ከዚህ የደረሱት በልዕልት ወርቂትና በወረሂመኖ ህዝብ ላይ መሆኑ ይታወሳል፣ ራስ ሚካኤል ደግሞ የወረሂመኖ ሰው ናቸው/ ። እናም ልጅ እያሱ ከእናታቸዉ ከወ/ሮ ሸዋረጋ ሚኒሊክና ከአባታቸዉ ከራስ ሚካኤል ዓሊ ጥር 25 ቀን 1888 ዓ.ም በወረሂመኖ ተንታ ዉስጥ ተወለዱ ፡ የክርስትና ስማቸዉም ክፍለ ያዕቆብ ተባለ ።

አፄ ሚኒሊክ ግንቦት 10 ቀን 1902 ዓ.ም አልጋ ወራሻቸዉ ልዑል እያሱ መሆኑን ባሳወቁበት ወቅት ልጅ እያሱ ገና የ13 አመት ልጅ ስለነበር ራስ ተሰማ ናደዉን የራስ ቢትወደድነት ማእረግ ሰጥተዉ የልጅ እያሱ ሞግዚት አድርገዉ ሾሟቸዉ ። ሆኖም ራስ ቢትወደድ ተሰማ በነበረባቸዉ የደም ብዛትና በእድሜ መግፋት ምክንያት 1 አመት እንኳን ሳይሞላቸዉ በ1903 ዓ.ም አረፉ ።

ይህን ተከትሎ በርካታ ራሶች የሞግዚትነት ስልጣኑን ለመያዝ ሲሻኮቱ ወደ አላስፈላጊ ዉዝግብ ሲያመሩ በማየቱ ብቻ ልጅ እያሱ “በቃ ሞግዚት አልፈልግም” አለ ። በዚህም ምክንያት አቤቶ እያሱ በዚህ እድሜቸዉ ያለሞግዚት ሀገር ለማስተዳደር ወሰኑ ። ይህ ለልጅ እያሱም ሆነ ለሀገሪቱ እንደማይበጅ በጣም ግልፅ ነዉ ። /እንግዲህ የ13 አመት ልጆች በየቤታችሁ የሚያደርጉትን እዩ/ ።

የልጅ እያሱ የስልጣን ዘመን ተብሎ የሚመደበዉ ከ1906-1909 ዓ.ም ይሁን እንጂ ልጅ እያሱ ራሱን ችሎ ማስተዳደር የጀመረዉ ግን ከ1903 ዓ.ም ጀምሮ ነዉ ። አፄ ሚኒሊክ እስከ 1906 ዓ.ም ድረስ እስትንፋሳቸዉ ስለነበረ እስከ ሞቱበት ድረስ ያለዉን ጊዜ የእሳቸዉ ዘመን አድርጎ መዉሰድ የግድ ስለሆነ ነዉ ።

ልጅ እያሱ አፄ ሚኒሊክ ከመሞታቸዉ በፊት ወራሽነታቸውን ካረጋገጡበት ጊዜ ጀምሮ “አገር ለመጎብኘትና ያልቀናዉን አገር ለማቅናት” በሚል ራቅ ወዳሉ ግዛቶች ወጣ እያሉ ለሳምንታትና ለወራት እዚያዉ መሰንበት ልማዳቸዉ አድርገዉ ቀጠሉበት ። በዚህም ላይ ሚስት ለማግባት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ሐይማኖት፣ ብሔረሰብና የዘር ግንድን እንደ መመዘኛ አይጠቀሙም ነበር ። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ሹማምንት ነቀፋና ቁጣ ማሳየት ጀመሩ ። ልጅ እያሱም በንደት፣ ተከብረዉ የኖሩትንና ታላላቅ ማዕረግ ያላቸዉን ሁሉ “የአባቴ ሙክቶች” እያሉ በንቀት ማጣጣል ጀመሩ ። እንደ

ዱሮዉ ንጉሳቸዉን ተከትለዉ አገር የመዞር ልማድን አስቀረባቸዉ ፡፡ ልጅ እያሱ "እኔ ወጣቶችን አስከትየ አገር ለመጎብኘትና ያልቀናዉን አገር ለማቅናት በምነሳ ጊዜ ያለፈቃዴ መከተል የለባችሁም ፡፡ ወፍራችኋል፣ አርጂታችኋል፣ በጊዜችሁ አባቴን ተከትላችሁ አገር አቅንታችኋል፤ አሁን ግን አባራችሁ አትጨብጡም፣ ሽሽታችሁ አታመልጡምና ተመልሳችሁ በየስራችሁ ጠንክሩ" ማለታቸዉን መርስሔህዘን ወልደ ቂርቆስ ፅፈዋል ፡፡ /ይህ ሁኔታ ለእያሱ የስልጣን እድሜ ማጠር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሳያደርግ አይቀርም/ ፡፡

ልጅ እያሱ ህፃንነት ያጠቃቸዉ እንደነበር ብዙዎች ይስማማሉ ፡፡ የሚያከናዉኗቸዉ ተግባራት ከፊሎቹ ያለፈዉን ስረዓትና ወግ የሚፃረሩ የነበሩ ናቸዉ ፡፡ የቀሩት ስራዎቹ ግን በዚያን ዘመን ሰዎች ሲታሰቡ እንጂ በዘመናዊ አስተሳሰብ እይታ ተራማጅነታቸዉን የሚያጎሉ ናቸዉ ፡፡

ልጅ እያሱ "የግል ንብረትን የማስከበርና አስራትን በወቅቱ የመሰብሰብ ደንብን አዉጥተዋል ፡፡ ከሳሽና ተከሳሽ አብረዉ እንድማቅቁ ያደርግ የነበረዉን የቁራኛ ስረዓት ለመሻር እርምጃ ወስደዋል ፡፡ እንዲሁም ከፍትህ ይልቅ ለቂም መወጫና ደካማዉን ለማጥቂያነት የሚያገለግለዉን የሌባ ሻይ ስረዓትን መልክ ለማስያዝ ሞክረዋል ፡፡ የመንግስትን ሂሳብ ኦዲት በማስደረግና አላግባብ የመንግስትን ገንዘብ ባባከኑት ላይ እርምጃ መዉሰዱ ልጅ እያሱን የመጀመሪያዉ ኢትዮጵያዊ መሪ ያደርጋቸዋል ፡፡ በዚሁ በገንዘብ ምክንያት በርካታ ሰዎች እንዲታሰሩ አድርገዋል /ይህ ሁኔታ ለእያሱ የስልጣን እድሜ ማጠር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሳያደርግ አይቀርም/ ፡፡

ህፃን ከመሆናቸዉ ጋር ተያይዞ ለስልጣናቸው ጥንቃቄ ካለማድረጋቸውም በተጨማሪ አንዳንድ የሚፈፅሟቸዉ ነገሮችም ይቃረኑ ነበር ፡፡ ባንድ ወገን የተጠቃ እንባ አድራቂ ሆነዉ የጅሌ ኦሮሞ ህዝብን የዘረፉት አፋሮች ላይ ሲዘምቱ በሌላ በኩል ደግሞ በስማቸዉ ላይ ጥቁር ነጥብ የጣለዉን የጊሚራ ዘመቻ ሲመሩና በርካታ ዜጎችን ለባርነትና ሞት ሲዳርጉ እናየዋለን ፡፡ አሁንም "ጥርንቡሌ" የተባለዉን የከተማ ዘበኛ ካቋቋሙ በኋላ ራሳቸዉ ሰዓት እላፊ እየጣሱ ከእነሱዉ ጋር ሲታኮሱ ያመሻሉ ፡፡ እራሳቸዉ የሰዓት እላፊ አዋጅ ደንግገዉ፣ ነገር ግን አዋጁን እራሳቸዉ ጥሰዉ ከአራዳ ዘበኞች ጋር ሌሊት ሌሊት ሲታኮሱ ያድሩ ነበር ፡፡

በ1905 ዓ.ም አጋማሽ ላይ አፄ ሚኒሊክ ከመሞታቸዉ በፊት ልጅ እያሱ ወደ አንኮበር እንዲሄዱ አስበዋል የሚል ወሬ በመሰማቱ፣ የግቢ ዘበኞች ልጅ እያሱን አናስገባም ብለዉ በሩን ዘጉ ። እያሱ ከዉጭ ሆነዉ በማስከበብ ስንቅ እንዳያገኙ በማድረጋቸው ሁከት ተፈጠረ ፡ ለ5 ሰዓታት በተደረገ የተኩስ ልዉዉጥ 17 ሰዎች ከሞቱ በኋላ በጳጳሱ ሽምጋይነት ዘበኞቹ እጅ እንዲሰጡ ተደርጎ ሰላም ወረደ ። ከዚህ በኋላ ሌላ የግቢ ዘበኛ ተሹሞ የቀድሞዎቹ ወደ ጎጃም ሄደዉ እንዲታሰሩ አደረጉ ።

ይህን የሰሙት አባቱ ንጉስ ሚካኤል ደግሞ የ4 ኪሎ ቤተመንግስትንና አካባቢዉን የሚጠብቅና ታምኝ የተባለ ወደ 35,000 የሚጠጋ ጦር ከወሎ ተነስቶ ከቀናቶች በኋላ አዲስ አበባ ገባ ። ወዳዉም አራት ኪሎ ቤተመንግስትና ዙሪያዉ እጅግ ጥብቅ በሆነ ጥበቃ ዉስጥ ገባ ። ቤተመንግስቱ ይህን ያህል እጅግ በጣም ጠንካራ ጥበቃ ቢደረግለትም ልዑል እያሱ ግን አብዛኛዉን ግዜቸዉን የሚያሳልፉት ከቤተመንግስት ዉጭ በክፍለ ሀገር ስለነበር ጠባቂዎቹ ባዶ ግንብ ነበር የሚጠብቁት ።

በልጅ እያሱ የሚታዘዝ ወደ 300,000 የሚሆን የአፄ ሚኒሊክ ጦር እያለ ንጉስ ሚካኤል 35,000 ጦር አስገብተዉ ቤተመንግስቱን መዉረራቸዉን አንዳንድ ፀሀፍት “ልጁ እፃን ስለሆነ ታማኝ መምረጥ ስለማይችል በእኔ ታማኞች ይጠበቅ” ብለዉ ነዉ በሚል አስቀምጠዉታል ።

ልጅ እያሱ ገና ዘዉድ ሳይጭን በ1906 ዓ.ም ባደረገዉ ሹም ሽር ራስ ወልደጊዮርጊስን ከደቡብ ግዛታቸዉ ሽረዉ የበጌምድር አስተዳዳሪ አድርገዉ ሲሾሙ ደጃዝማች ተፈሪ መኮነንን ከሐረርጌ ግዛታቸዉ ሽረዉ ወደ ከፋ እንድሄዱ አደረጉ ። የጦር ሚኒስተሩ ፊታዉራሪ ሐብተጊዮርጊስም ደርበዉ ይዘዉት የነበረዉን የሚንስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበርነትን እንዲለቁ አድርገዉ በጦር ሚኒስተርነታቸዉ ብቻ እንድወሰኑ አደረጉ/ እዚህም ላይ ትልቅ ስህተት ሰሩ፣ ከተቀያየሙ በኋላ በጦር መሪነታቸዉ እንዲቀጥሉ ማድረግ አልነበረባቸዉም/ ።

በዚህ ምክንያት ፊታዉራሪ ሐብተጊዮርጊስና ደጃዝማች ተፈሪ እጅግ ተበሳጭተዉ ቅሬታቸዉን ቢያሳዩም የሚሰማቸዉ አልተገኘም ።

ልጅ እያሱ ለክርስቲያኖች ቤ/ን ሲያሰሩ ለሙስሊሞችም መስጊድ አሰሩ ። ይህ ተግባር ብዙ ሹማምንትን አሳዘነ ። ከበፊቶቹ ቂሞች ጋር ተያይዞ ለሙስሊሞች ያሰሩት መስጊድ እንጂ ስላሰሩት ቤተክርስቲያን አይወራም ነበር ። ሆኖም የአዲስ አበባዉን ቀጨኔ መድኃኔለምንና የሐረር መድሐኔለም ቤተክርስቲያናትን ያሰሯቸዉ ልጅ እያሱ ናቸዉ ። ቀጨኔ መድሐኔለም የእህቱ የወ/ሮ ስህን ሚካኤል፣ የልዕልት እጅጋየሁ አስፋወሰን፤ የእመቤት ሆይ አለም ፀሀይ እያሱ፣ የወ/ሮ እስከዳር ገ/ህይወት ሚካኤልና የሌሎችም አፅም ይገኝበታል ። አፄ ኃይለስላሴም በዘመናቸዉ ሄደዉበት የሚዉቁት ብቸኛ ቤ/ን ይህዉ ቀጨኔ መድሐኒዓለም ብቻ ነዉ ።

ቀጥሎም ልጅ እያሱ የአፋሩን ባላባት አቡበከርን ልጅ አፍቅረዉ አገቧት ። ከዚህም በተጨማሪ እንደ ቀድሞዎቹ ነገስታት ልጅ እያሱም ብዙ እቁባቶችን በየቦታዉ ያስቀምጡ ነበር ። ከእቁባቶቻቸዉ ዉስጥም ፡ - ከጎጃም ባላባት የተወለደችዉ ሰብለወንጌል፣ የአፄ ዮሃንስ የልጅ ልጅ፣ የጅማዉ አባጅፋር ልጅ፣ የአባጅፋር የእህት ልጅ፣ የሐረሩ አሚር አብዱላሂ ልጅ፣ የነጋድራስ መሐመድ ልጅ፣ የአዳሉ ባላባት ልጅ ይገኙበታል ። ይህን ጋብቻ አንዳንድ ፀሀፍት "ከሁሉም ጎሳ በመዉለድ አንድነትን ለማጠንከር ሲሉ የፈፀሙት ነዉ" ይላሉ ። ብዙ ቅምጥ ማስቀመጡን ሌሎችም ነገስታት ሲያደርጉት የኖሩት ነዉ /ከአፄ ቴዎድሮስ ዉጭ፣ እሱም ከተዋበች ዉጭ ሌላ ሴት ያልነካዉ ስራዊቱ የሚስትየዋ ስለሆነ ነዉ/፤ ሌሎቹ ነገስታቶች ግን እንዳዉም ከልጅ እያሱ በላይ በርካታ እቁባቶችን ያስቀምጡ ነበር፤ ለምሳሌ ያህል የእስራኤሉ ንጉስ ሰለሞን ሰባት መቶ /700/ ሚስቶችና ሶስት መቶ /300/ እቁባቶች ነበሩት ። ልጅ እያሱን ለዬት የሚያደርጋቸዉ ሚስት በሚያገቡበት ሰዓት ሐይማኖትንና ብሔርን እንደመስፈርት አለመጠቀማቸው ብቻ ነው ።

አቤቶ እያሱ ወደ ምስራቅ በመሄድ የሱማሌ ጎሳ መሪ የነበረዉን አብደላ ሰዬቅን የኦጋደን ገዥ አድርገዉ ሾሙ ። ይባስ ብለዉ፣ ቅኝ ገዥዎቹ እንግሊዞችና ጣሊያኖች የተካፈሏትን ሶማሌን ነፃ ለማዉጣት ከእንግሊዝና ከጣሊያን ጋር ለ15 አመታት ያህል ሲዋጋ ለነበረዉ ለሰይድ ሙሐመድ አብደላ ሀሰን የገንዘብ፣ የመሳሪያና የስንቅ ድጋፍ ማድረግ ጀመሩ ። በእርግጥ ይህን ሲያደርጉ ልጅ እያሱ አላማ ነበራቸዉ ። "ኤርትራን፣ ጅቡቲን፣ የሞቃድሾ ሶማሌንና በርበራን ሳልጠቀልል ዘዉድ አልጭንም" የሚል መፈክር ነበራቸዉ ። እነዚህ የተጠቀሱት ቦታዎች ደግሞ የእንግሊዝና የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች

ናቸው ። የአዉሮፓዉያኑም ትልቅ የቤት ሥራ ልጅ እያሱን ከስልጣን ማዉረድ የሚለዉ ሆነ ።

ልጅ እያሱ በሹማምንቱ ዘንድ ያልተወደደላቸዉ ችኩልነታቸዉ እንጂ በጀግንነታቸዉና በአላማቸዉ ሁሉም ተቃዎሞ የላቸዉም ። ልዑል እያሱ ሁሉንም የኢትዮጵያ ጎሳዎች በማስተባበር ኤርትራን፣ ጅቡቲን፣ የሞቃድሾ ሶማሌንና በርበራን የማስመለስ እቅዳቸዉን ለሹማምንቱ ሁሉ አሳወቁ ። ከዚህም የተነሳ አቤቶ እያሱ 380ሺ ጦር ለማሰናዳትና ለየደጃዝማቹ በየግላቸዉ የሚያዘጋጁትን የጦር ሰራዊት ብዛት በመንገር፣ የራሳቸዉን ወስነዉ “ፈረሴ ከቀይ ባህር ዉሀ ሳይጠጣ ዘዉድ አልጭንም” እያሉ ይፎክሩ ነበር ። ልጅ እያሱ አፄ ሚኒሊክ እንደሞቱ ዘዉድ ደፍተዉ ንጉሰ ነገስት ተብለዉ በአፄነት ማዕረጋቸዉ መጠራት ነበረባቸዉ ። እናም ይህንኑ ለማድረግ ሲሞከር “ኤርትራን፣ ሶማሌን /ሞቃድሾ/፣ ጂቡቲን፣ በርበራን ሳልጠቀልል ዘዉድ አልጭንም” በማለት እምቢ አሉ ።

ልጅ እያሱ ኤርትራን ለማስመለስና ሞቃድሾን ለመጠቅለል ከቅኝ ገዥዎቹ ከእንግሊዝና ከጣሊያን ጋር መዋጋት ይኖርባቸዋል ። ለዚህ ደግሞ መሣሪያ ያስፈልጋቸዋል ። ስለዚህ የእንግሊዝና የኢጣሊያ ባላንጣ ከሆኑት ከጀርመንና ከቱርክ ጋር ወዳጅነት ጀመሩ ። ይህን ያስተዋሉት እንግሊዝና ጣሊያን በቆንሴሎቻቸዉ በኩል የተቻላቸዉን ያህል እያሱን የመጣል ሴራ መሸረብና ዉድቀቱን የማፍጠን እቅድ ያዙ ። ወዳዉም ልጅ እያሱ ከጀርመናዊቷ ኦስትሪያ ጋር የጦር መሣሪያ ለመግዛት ተዋዋሉ ። አንደኛዉ የአለም ጦርነት ተነስቶ ስለነበርም ጀርመንን ለማገዝ ወደ ቀድሞዋ ታንጋኒካ የአሁኗ ታንዛኒያ ወታደር ላኩ ። ከ700 በላይ የሚሆኑት እነዚህ ወታደሮች ከጦርነቱ በኋላ ‘’አሩሻ’’ በተባለዉ ግዛት ስለቀሩ ከአካባቢዉ ህዝብ ጋር በጋብቻ ተሳስረዉ በአሁኑ ወቅት እዚያዉ ገበሬ ሆነዉ እየተባዙ ይገኛሉ ።

እንግሊዝ ወዲያዉ ልጅ እያሱን ከስልጣን የማዉረዱን ስራ ጀመረች ። ሐረር የነበረዉን የቆንሲል ባለስልጣናቸዉን ከስልጣን አዉርደዉ በምትኩ ህዝቦችን በማሳመፅ የሚታወቀዉን ሰላይ ሻለቃ ቲ.ኢ ሎዉሬንስን የሐረር ቆንሲል አድርገዉ አስገቡ ። ይህ ሰዉ አረቦችን በቱርኮች ላይ እንዲያምፁ አድርጎ ቱርኮች በርካታ ይዞታቸዉን እንዲለቁ ያደረገ አደገኛ መኮንን ነዉ ።

እናም መኮንኑ ሐረር እንደደረሰ ሥራዉን የጀመረዉ ከልጅ እያሱ ጋር ጥልና ቂም ያለባቸዉን ሹማምንት በማጥናትና በማገዝ ነበር ። ይህን የእንግሊዞች አላማ ያላወቁት ደጃዝማች ተፈሪና ፊታዉራሪ ሐብተጊዮርጊስ ቀድመዉ ከእንግሊዛዊዉ ጋር ህብረት ፈጥረዉ ልጅ እያሱን የመጣል ሥራቸዉን ጀመሩ ። ወዳዉኑ ሎዉሬስ እያሱን ከስልጣን የማዉረድ ሥራ መጀመር ብቻም ሳይሆን ተተኪዉን ገዥም እስከመምረጥ ደረሰ ።

ከዚህም ቀጥሎ የእያሱን የአገር ዉስጥ ተቃዋሚ መኳንንቶች በደጃዝማች ተፈሪና በፊታዉራሪ ሐብተጊዮርጊስ ዙሪያ ካሰለፋቸው በኋላ አጠቃላይ የኢትዮጵያን ሁኔታ ሐይማኖት፣ ባህል፣ ወግ፣ አስተሳሰብ ሳይቀር በሚሲዮኖችና ኢትዮጵያ ዉስጥ ባሉ የዉጭ ሀገር ዜጎች አስጠንቶና በዙሪያዉ ካሉ መሰሎቹ ጋር መክሮ የሚከተለዉን የሥራ እቅድ አዘጋጀ።

1. በደጃዝማች ተፈሪ ዙሪያ ያሉ መኳንንቶች ልጅ እያሱ መስለሙን እንዲያስተጋቡ፣
2. ለዚህ ተግባር ሙሴ ሊዮን የተባለዉን አርመናዊ ታዋቂ ፎቶ ግራፍ አንሺ፣ የልጅ እያሱን መልክ በፎቶ ግራፍ ጥበብ የሙስሊም ልብስ የለበሰ አስመስሎ፣ 20ሺ ኮፒ በግብፅ ሀገር አሳትሞ በማስመጣት፣ በገ/ህይወት ባይከዳኝ አማካኝነት እንዲበተን አደረገ ። ከዚህም ባለፈ በአማርኛና በፈረንሳይኛ ፅሁፎች በድሬዳዋ ማተሚያ ቤት እያሳተሙ በማሰራጨት ሹማምንቱንም፣ ካህናቱንም፣ ተራዉንም ህዝብ አሳመኑት ። የአደገኛዉ ቲ. ኢ. ሎዎሬንስ እቅድም በትክክል ሰራ ።
3. ቀጥሎም ባለ 13 አንቀፅ የክስ ዝርዝሮች እንዲዘጋጁ አደረገ /የክሶቹ አንቀፆች በጣም ረጅም ስለሆኑ አልፌቻዋለሁ/ ።

ይህን ከላይ ያለውን የስራ እቅድ ካጠናቀቀ በኋላ ልጅ እያሱ ለስራ ወደ ኦጋዴን ሲሄዱ ጠብቆ በፍጥነት ወደ ተግባር ለወጠዉ /ልጅ እያሱ እዚያዉ ኦጋዴን ለ9 ወራት ያህል ቆይተዉ ነበር/ ።

በዚህ መሰረት መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ጳጳሱና ሁሉም ያገሪቱ ሹማምንት ባሉበት የተዘጋጁት 13ቱ የእያሱ ክሶች ተነበቡ ። በልጅ እያሱ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች መካከል ከፍተኛ ክርክር ከተካሄደ በኋላ በተበተነዉ ፎቶ ምክንያት የመንግስትን እምነትን ወደ እስልምና ለመቀየር ማሰቡ

ታምኖበት “ሙስሊምና ክርስትያኑን ያጫርስብናል” በሚል ከስልጣን መዉረድ አለበት በሚለዉ ተስማሙ ። በምትኩ የአፄ ሚኒሊክ ልጅ ዘዉዲቱ ‘’ንግስተ ነገስታት’’ ተብለዉ ሲመረጡ ደጃዝማች ተፈሪ ‘’ራስ’’ በሚል ማዕረግ ‘’አልጋ ወራሽ’’ ተብለዉ ተመረጡ ።

ልጅ እያሱ ከተሻሩ በኋላ ከአባቱ ከንጉስ ሚካኤል ዉጭ ሁሉም መሳፍንቶች ከዷቸዉ ። የእህቱ የወ/ሮ ስህን ሚካኤል ባል ቢትወደድ ሃይለጊዮርጊስም ሳይቀር ከዷቸዉ ። ፍፃሜቸዉ የሆነዉ ግን ምክትል ጦር አዛዡ ሲከዷቸዉ ነዉ ። 300,000 የሚሆነዉ የአፄ ምኒሊክ ጦር ዋና አዛዥ እራሳቸው ልጅ እያሱ ቢሆኑም በእያሱ ደጋፊነቱ የሚታወቀዉ ምክትል አዛዡ፣ በተበተነው ፎቶና እያሱ ወደ ሐረር ሄደዉ በነበረበት ወቅት ክርስቲያኖችን ሽረው ሙስሊሞችን በመሾማቸው ምክንያት እኔም አይቀርልኝም በሚል ከተቃዋሚዎቻቸዉ ጋር በማበር፣ የእያሱ ፖለቲካዊ ስልጣን ማብቃቱን ለህዝብ አበሰረ ። የልጅ እያሱ ጉዳይ እዚህ ላይ አበቃ ። የጦሩ የእዝ ሰንሰለት ምክትል አዛዡ ላይ ተቋረጠ ።

ልጅ እያሱ ይህን እንደሰሙ በዚያዉ ባሉበት በኦጋዴን አካባቢ ጦር ሰብስበዉ እየዛቱ ወደ ሸዋ ለመዝመት ከሐረር ተነስተዉ እየተጓዙ ሳለ ሚኤሶ ላይ ከአዲስ አበባ ቀድሞ የተላከ 15000 ጦር አድፍጦ ጠብቆ ዉጊያ ገጠማቸዉና ብዙ ሰዎች ካለቁ በኋላ የእያሱ ጦር ተሸነፈ ። እያሱም የተረፉትን ወታደሮች ይዘዉ ወደ አፋር በረሀ ሄዱ ።

ይህን የሰሙት ንጉስ ሚካኤል “ልጄን ቢያጠፋ እንኳን እኔ እመክርና አርመዉ የነበረዉን እንደት ሳያማክሩኝ” በሚል፣ ሸዋ አንኮበርና ደብረ ብረሃን ላይ መሽጎ የነበረዉን ሰራዊታቸዉን አንቀሳቀሱ ። ደብረ ብረሐን ብቻ 56ሺ የሚሆን የንጉስ ሚካኤል ጦር መሽጎ ይኖር ነበር ። ንጉስ ሚካኤል የደብረ ብረሐኑን ጦር ወደ አንኮበር አንቀሳቅሰዉ ባጠቃላይ 80ሺ ጦር አንኮበር ላይ አከማቹ ። የንጉስ ሚካኤልን ጦር ለመመከት ከአዲስ አበባ በኩል 120,000 ጦር ተዘጋጅቶ በራስ ሉልሰገድ አጥናፍሰገድና በደጃች ተሰማ ገዝሙ እየተመራ ወደ አንኮበር ተጠጋ ። የመጀመሪያዉ ጦርነት ጥቅምት 7 ቀን 1909 ዓ.ም ከአንኮበር በስተ ሰሜን በቶራ መስክ ላይ ተካሂዶ በማይታመን ፍጥነት የወሎው ጦር የመንግስትን ጦር በታተነዉ ። በዚህ ጦርነት ላይ የመንግስት ሰራዊት መሪ የነበሩት ራስ ሉልሰገድ አጥናፍሰገድንና ደጃች ተሰማ ገዝሙን

ጨምሮ በርካታ የጦር መሪዎች አለቁ ። ከዚህ ድል በኋላ የወሎዉ ሰራዊት ሁለቱም መሪዎቹ ሞተውበት የተበታተነዉን የመንግስትን ሰራዊት እያባረረ ወደ አዲስ አበባ በገስገሱን ቀጠለ ። በዚህ መልኩ የወሎው ጦር ወደ አዲስ አበባ በመጠጋት ላይ እያለ፣ የጦር ሚኒስትሩ ፊታዉራሪ ሐብተጊዮርጊስ ለንጉስ ሚካኤል ገፀበረከትና ሽማግሌዎችን በመላክ ሁሉም ነገር ይስተካከላል በሚል ተዘናግተዉ እንድቆዮ አደረጉ ። እራስ ሚካኤልም "ሁሉም ነገር ይስተካከላል" የሚለዉን የጦር ሚኒስተሩን ቃል አምነዉ ተረጋግተዉ ሰገሌ ሜዳ ላይ ሰፍረዉ ቆዩ ።

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ማንቴል ኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ያሰፈሩትና በዓለማየሁ አበበ የተተረጎመዉ መጸሀፍ ዉስጥ የሰፈረዉ ቃል በቃል ሲቀመጥ "አድመኞቹ የግልበጣዉን ወቅት በጥንቃቄ አጥንተዉ ነበር የመረጡት ። ልጅ እያሱ በኦጋዴንና በሐረር ጉብኝት ላይ ነበሩ ። አባታቸዉ ንጉስ ሚካኤልም ወሎ ደሴ ነበሩ ። ንጉስ ሚካኤልም የልጃቸዉን ከስልጣን መዉረድ እንደሰሙ ለጦርነት ዝግጅት ጀመሩ ። የአዲስ አበባ ህዝብ ስጋት ላይ ወደቀ ። በዋና ዋና የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶችም ከሞሐመዳዊ ግዛቶች በተለይ ከሸዋ፣ ከምስራቅና ከሰሜን ምስራቅ በኩል ታላቅ ጦርነት ሊነሳ ይችላል የሚል ጭንቀት ዉስጥ ገቡ ።

የራስ ሚካኤል ሰራዊት ከአንኮበር በስተ ሰሜን ቶራ መስክ ላይ የመጀመሪያዉን የመንግስት ተከላካይ ጦር ጥቂት ሺህ ወታደር ይዞ ገጠመዉ ። የዚህ የቶራ መስክ ጦርነት በመንግስት ክፍለ ጦር መሸነፍ ተፈፀመ ። ራስ ሉልሰገድና ደጃዝማች ተሰማ ከጦር አዉድማዉ ላይ ወደቁ ። ከድሉ በኋላ ንጉስ ሚካኤል ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግሱ የመንግስት ወታደሮች መንገድ ለመዝጋት ሙከራ አደረጉ ። የጦር ሚኒስትሩ ሀብተጊዮርጊስ የጠላት ቁጥር ብልጫ ሳይሆን በጀግንነቱና በዉጊያ ስልቱ ዝና ያተረፈዉ የወሎ ፈረሰኛ ጦር ይበልጥ አስፈርቷቸዉ ነበር ። ሀብተጊዮርጊስ ገና ቀደም ብለዉ ከጅቡቲ አንድ ጭነት መትረየስ አዝዘዉ ነበርና ይህ በጦርነቱ ላይ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል የሚል እምነት ያዙ /በእንግሊዛዊዉ የመጣ መሳሪያ ነዉ/ ። ስለሆነም ይህ መሳሪያ ከመድረሱ በፊት ወሳኙን ግጥሚያ ማድረግ ስላልፈለጉ ንጉስ ሚካኤልን በሰላም ድርድር ሰበብ ጠምደዋቸዉ ሰነበቱ ። ሁለት ነባር የሚኒሊክ ጦር አበጋዞች ተዋጉ ቢባል ለሰሚዉ ግራ ነዉ ሲሉ ደብዳቤ ፃፉላቸዉ ። ንጉስ ሚካኤል በበኩላቸዉ ሀብተጊዮርጊስና ተፈሪ መቃቃር

መጀመራቸዉን ያዉቁ ነበርና አንደኛቸዉን ወደ ልጅ እያሱ ጎን ላመጣቸዉ እችላለሁ በሚል ተስፋ ለድርድር ዝግጁ ነኝ የሚል መልስ ሰጡ ። የሀብተጊዮርጊስ የተንኮል እቅድ ተሳክቶ ወሳኙን ጦርነት ለጥቂት ቀናት ማዘግየት ቻለ ። በመካከል የወሎን ፈረሰኛ ጥቃት ዋጋ የሚያሳጣዉ መሳሪያ ከጅቡቲ ገባ ። ይህ ስያሜዉ ለዘለቄታዉ በኢትዮጵያ ታሪክ ካርታ ላይ ተቀርፆ እንዲኖር ያደርገዉ የሰገሌ ጦርነት ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም ተካሄደ" ይላል ። /በነገራችን ላይ ንጉስ ሚካኤል፣ ዘዉዲቱን ተቃዉመዉ እንጂ ተፈሪ እንደሚነግስ አውቀው ቢሆን ኖሮ አይዋጉም ነበር ። የተፈሪ ሚስት ወ/ሮ መነን 2ኛ የንጉስ ሚካኤል የልጅ ልጅ ነች ። ይህንን ጦርነት የወሎ የእርስ በርስ ጦርነት ወይም የንጉስ ሚካኤል ቤተሰቦች የእርስ በርስ ጦርነት አድርጎ መዉሰድ ግን አይቻልም ። ምክንያቱም በነተፈሪ በኩል የሁሉም ብሄረሰቦች ጦር አብሮ ተሳትፏልና/ ።

በእንግሊዛዊው ምክር መሰረት፣ የመንግስት ሰራዊት መሪዎች ከጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም በፊት በስዉር ለቀናት ያህል በጥንቃቄ የወሎዉን ጦር ከበቡት ። ይህን ጦርነት እንግሊዛዊዉ መኮንን፣ ቲ. ኢ. ሎውሬንስ ከጀርባ ሆኖ፣ ጦሩን እየመሩ ያሉትን የጦር ሚንስትሩንና ራስ ተፈሪን፣ ከበባዉን እንዲያጠቡ ካደረገ በኋላ፣ ተዘናግቶ ትጥቁን እንኳን በአግባቡ ካልታጠቀዉ የወሎ ሰራዊት ላይ ድንገተኛና ከባድ ማጥቃት ሰነዘሩ ። የወሎዉም ጦር በድንጋጤ እየተተራመሰ ትጥቁን ከጣለበት እየፈለገ እያነሳና ከፊሉም ባዶ እጁን የጠላትን በሳሪያ ለመቀማት እየታገለ እጅግ አሰቃቂ እልቂት ተፈጠረ ። ከወሎዉ ጦር እጥፍ የሚበልጠዉ፣ የተሻለ መሳሪያ የያዘዉና የተዘጋጀዉ፣ የአዲስ አበባ ጦር እንደ ጎርፍ ሳያቋርጥ እየገባ ያልተዘጋጀዉን የወሎ ጦር ደበደበዉ ። የወሎዉ ጦርም 1ለ2 እና 1ለ3 እየታገለ ቁጥሩ እጅጉን ስለተመናመነ ሙሉ በሙሉ ተደመሰሰ ።

በርካታ ፀሀፍት ይህንንም የእንግሊዛዊያኖችን የትርጉም መፅሀፍ ጨምሮ፣ ይህ የሰገሌ ጦርነት የአድዋ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ ብዙ ደም የፈሰሰበት ከባድ ዉጊያ መሆኑን ዘግበዋል /ከኢጣሊያ ዳግም ወረራ ጦርነት ይበልጣል ማለት ነው/ ። ይህ የሰገሌ ጦርነት ኢትዮጵያን 10 አመት ወደ ኋላ ጎትቷታል ይባላል ። ይህን ጦርነት ተከትሎም በአዲስ አበባና አካባቢዉ ከፍተኛ ረሐብ ተከስቶ እንደነበር ይታወቃል ።

/እንግዲህ እስከ አሁን ድረስ እንዳየነው ከደርጎ- ኢህዴግ ጦነቶች ውጭ ያሉት ሁሉም ኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የተካሄዱት ጦርነቶች የወሎ ህዝብ ያካሄዳቸው ጦርነቶች ብቻ ናቸው ማለት ነው ። እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የተካሄዱት ሁሉም ጦርነቶች የወሎ ህዝቦች እርስ በእርሳቸው በስልጣን ሽኩቻ ያደረጓቸው ጦርነቶችና የወሎ ህዝቦች ከውጭ ጠላት ጋር ያደረጓቸው ጦርነቶች ብቻ ናቸው ማለት ነው ። /ኢትዮጵያ ያካሄደቻቸው 7 እጅግ ትልልቅ ጦርነቶች የሚባሉት ግራኝ ከወሎ ጋር፣ የጁ ከሸዋ ጋር /ዘመነ መሳፍንት/፣ የአፄ ሚኒሊክ ሀገር የስፋት ዘመቻዎች፣ ወሎ ከኢጣሊያ ጋር /አድዋ/፣ የሰገሌ ጦርነት /በልጅ እያሱ ምክንያት/፣ ኢትዮጵያ ከ ኢጣሊያ ጋር /የኢጣሊያን ዳግም ወረራ/ና ደርግ ከ ኢህአዴግ ጋር ናቸው ።

## ንግስት ዘዉዲቱ (ከ1909-1922 ዓ.ም)

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋለሁ ።

ዘዉዲቱ ከአባታቸዉ ከአፄ ሚኒሊክና ከወሎ የወረኢሉ ባላባት ከተገኙ እናታቸዉ ወ/ሮ አብችዉ በያን ሚያዝያ 22 ቀን 1968 ዓ.ም ተወለዱ ። ንግስት ዘዉዲቱ የተመረጡት የአፄ ሚኒሊክ ቀጥተኛ ልጅ ስለሆኑ ሲሆን ራስ ተፈሪ የተመረጡት ደግሞ ሰለሞናዊ ስርወ መንግስት የንጉስ ሳህለሥላሴ ዝርያ ስላላቸዉና በፖለቲካ ብስለታቸው ነው ።

ንግስት ዘዉዲቱ በ1893 ዓ.ም የወሎ የየጁ ባላባትና የእቴጌ ጣይቱ ወንድም የራስ ወሌ ብጡል ልጅ የሆነዉን ራስ ጉግሳ ወሌን አግብተዉ በኡራኤል ቤተክርስትያን አጠገብ የአሁኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ጥበቃ ቢሮ ያለበት ላይ ይኖሩ ነበር ። (ለዚህም ነዉ ሰፈሩ የንግስት ሰፈር እየተባለ የሚጠራዉ) ።

አፄ ሚኒሊክ ራስ ጉግሳ ወሌን የጎንደር ገዥ አድርገዉ ስለሾሙት ዘዉዲቱና ጉግሣ አዲስ አበባም ጎንደርም ነበር የሚኖሩት ።

የካቲት 4 ቀን 1909 ዓ.ም በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤ/ን ስርዓተ ንግስ ተደርጎላቸዉ "ንግስተ ነገስታት ዘዉዲቱ ወለተ ለዳግማዊ ሚኒሊክ ስይምተ እግዚአብሔር" ተብለዉ በሊቀ ጳጳሱ እጅ ቅብዓ መንግስት ተቀብተዉ ዘዉድ ሲጭኑ ራስ ተፈሪ ደግሞ ታላቁን የሰለሞን ኒሻን ተሸልመዉ ለአልጋ ወራሽነት የሚገባዉ ፀሎት ተደርጎ "ልዑል አልጋ ወራሽ" ተብለዉ ተሰየሙ ። በዚህ እለት ከቤተመንግስት አልፎ የማያዉቀዉ የኤሌክትሪክ መብራት በአዉሮፓዉያኑ ድጋፍ እስከ አራዳ ጊዮርጊስ ድረስ ተዘርግቶ የአዲስ አበባ ህዝብ አዲስ ነገር አየ ። በንግስት ዘዉዲቱ የቤተመንግስቱ መኳንንት ደስ ሲሰኙ፣ በራስ ተፈሪ አልጋ ወራሽነት ደግሞ አዉሮፓዊያን ቆንስሎች ተደሰቱ ። የንግስ ባዕሉም በደማቅ ሁኔታ አለፈ ።

ንግስት ዘዉዲቱ ሐይማኖታቸዉን አጥባቂ፣ በፆም በፀሎት የተጉና የህይወታቸዉ ሚዛን ወደ መንፈሳዊነቱ ያዘነበለ ነበር ። ማንም ሹም ያለስልጣኑ ያሻዉን ሲፈፅም "ለአገር ከጠቀመ ይሁን ብያለሁ" ከማለት ዉጭ እንደት ያለስልጣኑና ያለ እኔ ፈቃድ" ማለትን አያዉቁም ነበር ። ይህን ያህል ፈላጭ ቆርጭ ስልጣን ይዘዉ ሌላዉ ቀርቶ ፊት ለፊት የመጣባቸዉን ጠላት እንኳ በአግባቡ ተጋፍጠዉ አያዉቁም ። በዚህም ነዉ ጥቂት ፀሀፍት "ምስኪኗ ዘዉዲቱ" እያሉ የሚጠሯቸዉ ። "እርሰዎ በፆለተዎ ይርዱኝ፣ እኔ እፈፅማለሁ" ይሉ ነበር አልጋ ወራሹ ። የዘዉዲቱ መልስ "እሺ" የሚል ነበር ። ይህን ማድረጉ ከሐይማኖት ሰዉ የሚጠበቅ ቢሆንም፣ ገደብ ያለፈ የዋህነታቸዉ ግን በስተመጨረሻ ሳይጎዳቸዉ አልቀረም ።

በንግስት ዘዉዲቱ ከተሰሩ ዋና ዋና ስራዎች ዉስጥ ኢትዮጵያ የመንግስታቱ ማህበር አባል መሆን (1916) ፣ የኢትዮጵያ የመጀመሪያዉ አዉሮፕላን መግባት (1921) ፣ የመጀመሪያዎቹ 4 ኢትዮጵያዊያን ጳጳሳት መሾም (1919) ፣ ጊዮርጊስ የሚገኘዉ የአፄ ሚኒሊክ የነሀስ ሐዉልት መሰራት (1923 የተመረቀበት ነዉ) ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት (1914) ፣ መጀመሪያ ለሴቶች ማዋለጃ ታስቦ የተሰራዉ የአሁኑ ንግስት ዘዉዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ይገኙበታል ።

አልጋወራሽ ተፈሪ ቀስ በቀስ የንግስት ዘዉዲቱን ስልጣን እየገዘገዙ ቆይተዉ በመጨረሻ ዘዉዲቱን ማማከሩንም ትተዉ ታችኛዉ ቤተመንግስት ዉስጥ ሆነዉ ስልጣኑን ሁሉ ጠቅልለዉ ያዙ ። በዚህ ሁኔታ እያሉ ግርማዊት

ንግስተ ነገስት ዘዉዲቱ ባልታወቀ ምክንያት መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም አረፉ ።

# ምዕራፍ ስምንት

## አፄ ኃይለስላሴ (ከ1923-1966)

ጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ" በሚለዉ መፀሀፋቸዉ ያሰፈሩትን ከሌሎች ጋር እያመሳከርኩኝና አጠር አጠር እያደረኩኝ አስነብባችኋለሁ ።

አፄ ኃይለስላሴ የአፄ ሚኒሊክ አክስት ልጅ ከሆኑት አባታቸዉ ከራስ መኮነን ወልደሚካኤልና ከወሎ ባላባት ከተወለዱት እናታቸዉ ከወ/ሮ የሺመቤት አሊ ከሐረር ከተማ በ30 ኪ.ሜ እርቀት ላይ በምትገኘዉ ኤጀርሳ ጎሮ በተባለች ቦታ ተወለዱ ።

እናታቸዉ ወ/ሮ የሺመቤት ዓሊ ከተፈሪ በፊት 6 ልጆች ቢወልዱም ሁሉም እንደተወለዱ ሙተዉባቸዋል ። አሁንም ተፈሪ ያለጊዜዉ በተረገዘ በ7ኛ ወሩ ተወለደ ። ተፈሪ እንደተወለዱ ቤተዘመድ "እናቱ ካዩት እንደተለመደዉ ይሞታል" ብለዉ ህፃኑን ለእናቱ ሳያሳዩ ወስደዉ ዘመድ ቤት ማደግ ጀመረ /በባህል ሾተላይ ይባላል/ ። እናቱ የልጁን ሁኔታ በመልእክት ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ እንደገና አርግዘዉ ስለነበር ከ20 ወራት በኋላ መጋቢት 6 ቀን 1886 ዓ.ም በዚሁ በወሊድ ምክንያት አረፉ ። እናም ተፈሪ የእናትን ጣእም ሳያዉቅ ነዉ ያደገዉ ።

ደጃዝማች ተፈሪ በ19 አመታቸዉ የንጉስ ሚካኤል /የመሐመድ ዓሊ/ የልጅ ልጅ የሆኑትን ወ/ሮ መነንን አግብተዉ፣ የመጀመሪያ ልጃቸዉን ልዕልት ተናኘወርቅን በ1905ዓ.ም ወለዱ ። ከዚያም በተከታታይ ልዑል አስፋወሰንን፣ ልዕልት ዘነብወርቅን፣ ልዕልት ፀሐይን፣ ልዑል መኮነንንና አቤቶ ሣህለስላሴን ወልደዋል ።

(ንጉስ ሚካኤል፣ ልጅ እያሱ ቢሻርባቸዉም በወ/ሮ መነን በኩል እንደገና ቤተመንግስት መግባታቸዉ አልቀረም ። አለቃ ታዬም ወሎ ተረግሟል ብለው

የፃፉትም እውነት ይመስላል፤ አፄ ኃይለስላሴ አርጅተዉ ስልጣን እየለቀቁ ባለበት አመት ለመጀመሪያ ጊዜ የ1966ቱ ድርቅ ተከሰተ፣ ቀጥሎም ከ11 አመት በኋላ የ1977ቱ ድርቅ ተከሰተ፣ ኃይለስላሴ የመጨረሻው የወሎ ንጉስ ከመሆኑ አኻፃር ስልጣን ከወሎዎች እጅ እንደወጣ የድርቆቹ መከሰት የሚገርም ነገር ነው) ፡፡

ወደ ርዕሳችን ስንመለስ፣ ንግስት ዘዉዲቱ በሞቱ በ7ኛዉ ወር ጥቅምት 23 ቀን 1923ዓ.ም ነበር የጃንሆይ የስርዓተ ንግስ በዓላቸዉ በደማቅ ሁኔታ የተከናወነዉ ፡፡ እነዚያ 7 ወራት በኢትዮጵያ ምድር እስከ አሁን ታይቶ የማይታወቅ የባዕል ማሽብረቂያ የተካሄደባቸዉ ናቸዉ ፡፡ ንጉሰ ነገስቱና እቴጌዋ የሚጓዙበት ሰረገላ ከጀርመን አገር መጣ ፡፡ ልብሱ ሁሉ በወርቅና በሐር የተሸቆጠቆጠ ነበር ፡፡ የአዲስ አበባ ክርንክስ ቤቶች ሁሉ እንዲወገዱ ተደረገ ፡፡ የአዲስ አበባ መንገድ ሁሉ አስፓልት ሆነ ፡፡ የከተማ ፖሊሶች ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ አይነት ልብስ /ዩኒፎርም/ ለበሱ ፡፡ አብዛኛዉ የአዲስ አበባ አካባቢ በኤሌክትሪክ መብራት አሸበረቀ ፡፡ ዘዉዲቱ ያሰሩት የአፄ ሚኒሊክ ሐዉልትም ለከተማዋ ዉበት ተብሎ በበዓሉ ዋዜማ ነበር የተተከለዉ ፡፡

በበዓሉም እንግሊዝን ወክሎ የግሎስተር መስፍን፣ ፈረንሳይን በመወከል ማርሻል ፍራንስ ዴስፔሪ፣ ኢጣሊያን ወክሎ የሶቮይ ልዑል፣ ልዩ አምባሳደር ያኮብ መሬይ አሜሪካን በመወከል፣ ጄ. ጂዱስስኪ ፖላንድን በመወከል፣ ማክሲም ማክሲም ጄራርድ ቤልጀምን በመወከል፣ ባሮን ቢልት ስዊድንን በመወከል፣ ባሮን ፎን ቫልትሀዉዘን ጀርመንን በመወከል፣ ዩንክሄር ሄንድሪክ ሆላንድን በመወከል፣ ኢሳቡሮ ዮድሻ ጃፓንን በመወከል፣ መሐመድ ቶፊቅ ናሲብ ፓሻ ግብጽን በመወከል፣ መስፍን ፓ. ሜታክሳስ ግሪክን በመወከል … ወዘተ የተገኙ ሲሆን በዓሉ 15 ቀን ሲቀረዉ ጀምሮ አዲስ አበባ መግባት ጀመሩ ፡፡ ስፍር ቁጥር የሌላቸዉ ጋዜጠኞች አዲስ አበባን አጥለቅልቀዋት ስለነበር የበዓሉን ድምቀት የአለም ህዝብ ተከታትሎታል ፡፡ ባጭሩ በሀገሪቱ ብቻም ሳይሆን በአህጉሪቱም ታይቶ የማይታወቅ ደማቅ የንግስ በዓል ነበርና ሁሉንም አስደንቆ አልፏል ፡፡

በእለቱ ተፈሪ “ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ስዩመ እግዚአብሔር ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ” ተብለዉ ቅብዓ መንግስቱን ተቀብተዉ የወርቅ ዘዉዳቸዉን የጫኑት በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤ/ን ነበር

። ከዚያም የእቴጌይቱ የዘዉድ መጫን ስነስረዓት ቀጠለ ። በእለቱም ወ/ሮ መነን የእቴጌነቱን ዘዉድ ሲጭኑ ልጃቸዉ ልዑል አስፋወሰንም አልጋወራሽ ተብሎ የወርቅ አክሊል ደፋ ። ስርዓቱ ተፈፅሞ ወደ ታላቁ ቤተመንግስት ተመልሰዉ ዙፋናቸዉ ላይ ሲቀመጡ 101 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ ። አዲስ አበባ ከተማም በንጉሰ ነገስቱና በእቴጌይቱ ፎቶግራፎችና በሰንደቅ አላማ አጊጣ፣ የደመቀዉ የኤሌክትሪክ መብራት ሳይቋረጥ ለአንድ ሳምንት ያህል እንዳሸበረቀች ቆየች ።

አፄ ኃይለስላሴ ከንግስናቸዉ በኋላ ቀደም ሲል ጀምረዉት የነበረዉን አገራቸዉን የማዘመን ስራ አጠናክረዉ ቀጠሉ ። አፄ ኃይለስላሴ የሰሯቸዉን ስራዎች መቁጠር /መዘርዘር/ አይቻልም ። አሁን አገሪቱ ላይ የምናያቸዉ ከሞላ ጎደል ሁሉም ነገሮች በአፄ ኃይለስላሴ የተሰሩ ናቸዉ ። ጃንሆይ ከዜሮ ተነስተዉ ነዉ ይችን አገር አዘምነዉና አሰልጥነዉ እዚህ ደረጃ ላይ ያደረሷት ። አገሪቱ ጃንሆይ እንዳስቀመጧት ነች ማለት ይቻላል ።

ከአፄ ኃይለስላሴ ወዲህ የተሰሩ ስራዎችን መቁጠር ይቻላል ። ሰይጣኖች ተሰባስበዉበት የነበረዉ ደርግ የተባለዉ ቡድን /ግሩፕ/ ደብረዘይት አካባቢ የሚገኙትን የጦር መሳሪያ መጠገኛና ማምረቻ ተቋማትን ሲገነባ ከ1997ዓ.ም ወዲህ ያለዉ ኢህአዴግ ደግሞ በርከት ያሉ መንገዶችን፣ በርከት ያሉ ከት/ት ጋር የተያያዙ ስራዎችን፣ በርከት ያሉ የኃይል ማመንጫዎችን፣ በቴሌኮም በኩል የተወሰኑ ስራዎችን ሰርቷል ። በስኳርና በባቡርም የጀማመራቸዉ ስራዎች አሉ ። አንድ የባቡር መስመር አዲሶ ሌሎች የጀመራቸዉም አሉ ። ከ1997ዓ.ም በፊት የነበረዉ ኢህአዴግ ስራ ሰርቷል ማለት አይቻልም፣ ት/ት አካባቢ የተወሰኑ ቀላል እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ነበር ጊዜዉን ያሳለፈዉ ። የደርግንና የኢህአዴግን እድሜ ብንደምረዉ ከአፄ ኃይለስላሴ እድሜ ይበልጣል ። አፄ ኃይለስላሴ የሰሩትን ስራ፣ ደርግና ኢህአዴግ ባንድ ላይ ከሰሯቸዉ ስራዎች ጋር ማወዳደር ማለት ግን አባይና ቀበናን ማወዳደር ማለት ነዉ ።

ስለ ኢትዮጵያ በርካታ መፅሐፍትን የፃፉት አሜሪካዊ ሐሮልድ ማርክስ ጃንሆይን “የዘመናዊት ኢትዮጵያ አርክቴክት” ይሏቸዉና፣ ኢትዮጵያን በስልጣኔ ለማራመድ ስለሚጠቀሙበት ዘዴም፣ ጥንቁቅ ነበሩ ብለዉ ይገልፁዋቸውና ስልጣኔ አይቶ የማያዉቀዉ ህዝባቸዉ ፈጣንና ድንገተኛ

ማህበራዊ ለዉጥ ሲፈጠር በህዝባቸዉ ላይ የጎንዮሽ ጉዳት እንዳያመጣ ይጠነቀቁ እንደነበር ይጠቁማሉ ፡፡

እናም ጃንሆይ በዚህ መልኩ ሀገራቸዉን በከፍተኛ ፍጥነት እያዘመኑና እያሳደጉ ባለበት ወቅት ከ40 አመት በፊት የደረሰበትን ሀፍረትና ዉርደት ለማስመለስ በድብቅ ለ40 አመት ያህል ሲዘጋጅ የቆየዉ የኢጣሊያ መንግስት፣ ሳይታሰብ ድንገተኛ ወረራ ጀመረ ፡፡ የኢጣሊያ መንግስት በ1928ዓ.ም ከኤርትራ በመነሳት ድንገተኛና ይፋዊ ወረራዉን ጀመረ ፡፡

የአድዋ ሽንፈት እንዳይደገም በሚል 500,000 ነጭና 100,000 ባሽባዙቆች /ኤርትራዊያን ወታደሮች/ ባጠቃላይ 600ሺ ሰራዊት፣ 400 የጦር ጀቶች፣ እጅግ በርካታ ታንክና መትረይስ፣ ጦርነቱን የሚመሩ 100 ምርጥ የተባሉ ጀኔራሎችን …ወዘተ ይዘዉ ወረራዉን በሁለት አቅጣጫ ማለትም ሰሜንና በምስራቅ በፈጣን ሁኔታ ቀጠሉበት፡፡

በኢትዮጵያ በኩል ምንም አይነት ዝግጅት ስላልነበረና ስላልታሰበበት ይህን ድንገተኛ ወረራ በደመነፍስ ለመከላከል ተሞከረ ፡፡ የኢትዮጵያ ጀግኖችም እንደ ለመዱት ለሚወዷት ሀገራቸዉ የሚወዷትን ህይወታቸዉን መስጠት ጀመሩ ፡፡ ሆኖም ኢጣሊያ ባደረገችዉ ከፍተኛ ዝግጅት ምክንያት ይዛዉ የተሰለፈችዉን ዘመናዊ የጦር መሳሪያና ጋዝ መቋቋም አልተቻለም ፡፡ በርግጥ እዚህ ላይ በነጭ ፀሀፊዎችና በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሀፊዎች መካከል ልዩነት አለ ፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን፣ በዚህ ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያ የተሸነፈችዉ በጦር በሳሪያ ብልጫ ነዉ እንላለን ፡፡ እንደ ነጭ ፀሀፊዎች ግን ኢትዮጵያ የጦር መሳሪያ ብልጫዉን መቋቋም ትችል ነበር /አትሸነፍም ነበር/ ፡፡ ኢትዮጵያን እንዲትሸነፍ ያደረጋት የጎጃሞች ክህደት ነዉ፣ ጎጃሞች የኢጣሊያንን መምጣት ከሸዋ አገዛዝ ለመገላገል የተፈጠረ ልዩ አጋጣሚ አድርገዉ ነበር የወሰዱት ፡፡ የጎጃሞች አመፅ አጠቃላ የሰራዊቱን የአንድነት ስሜት ገድሎታል፣ የወታደሩን ኢትዮጵያዊነት ስሜቱንና የእርስ በርስ መተማመኑን አዳክሞታል፣ የወታደሩን አቋም /ሀገራዊ አቋም/ ሰብሮታል…ወዘተ ይላሉ ፡፡

አንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴልኒየችኮ የተባሉ እንግሊዛዊያን ፀሀፊዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለዉ መጸሀፋቸዉ ያሰፈሩትና በዓለማየሁ አበበ የተተረጎመዉ መጸሀፍ ዉስጥ የሰፈረዉ ፅሁፍ **ቃል በቃል ሲቀመጥ ፡ -**

“ከረጅም ጊዜ አንስቶ ሲብላላ የቆየዉ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ላይ የተቃጣዉ የጎጃሞች አመፅ፣ በጦርነቱ ዋዜማ ላይ የንጉሰ ነገስቱን ሰራዊት አቋም አዳክሞታል ። ጎጃሞች፣ ጦርነቱ ከአፄ ኃይለስላሴ አገዛዝ ለመላቀቅ ጥሩ አጋጣሚ ነዉ የሚል እምነት ነበራቸዉ ። ጎጃሞች፣ ይህ “የሸዋ ንጉስ” ይላሉ እንጂ “ንጉሰ ነገስት” የሚለዉ ቃል ከአፋቸዉ አይወጣም ነበር ይልና፣

ጦርነቱ እንደተጀመረ የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ዉስጥ አንዳንድ የጎጃም መኳንንት ንጉሰ ነገስቱን እየተዉ ከየዕርስታቸዉ እየሄዱ ይቀመጡ ጀመር ። በራስ ኃይሉ ተከተለሐይማኖት ቀስቃሽነት ግልፅ አመፅ ጀመሩ ። በዚህም ምክንያት ታህሳስ 8 ቀን 1928 ዓ.ም ንጉሰ ነገስቱ ለጎጃም ህዝብ አዋጅ አስነገሩ ። በዚህ አዋጅ ዉስጥ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ከብዙዉ በጥቂቱ እንዲህ ብለዋል ፡ - የጎጃም ህዝብ ሆይ፣ ጠላት ሲመጣ ያለርህራሄ በጭካኔ ሐይማኖትህን ያስለዉጥሀል፣ ሚስትህንና ሴት ልጆችህን ይነጥቅሀል፣ ከአባቶችህ የወረስከዉን መሬት ይቀማሀል ። ለሀገርህ ለኢትዮጵያ ነፃነት፣ ለኦርቶዶክስ እምነትህ ደምህን ታፈሳለህ እንጂ ትከዳኛለህ የሚል እምነት አልነበረኝም ። ደጃች ገሠሠ፣ ፊታዉራሪ ታምራት፣ ፊታዉራሪ ገሠሠ ንጉሴ፣ ፊታዉራሪ ዘለቀ ካሳ፣ ፊታዉራሪ ዘለቀ ወሌ፣ ቀኛዝማች አየለ ኃይሉ፣ ቀኛዝማች መርዕድ ዋሴ፣ ቀኛዝማች ዘለቀ አሰጌ ወዘተ የተባሉት ባላባቶች አገራቸዉን ኢትዮጵያንና እኔን ንጉሰ ነገስቷን ከድተዋል” ብለዉ አዋጅ አስነገሩ ይልና፣

ሆኖም ግን የታህሳሱ፣ የንጉሰ ነገስቱ አዋጅ ምንም አድማጭ አላገኘም ። ጎጃም ዉስጥ ንጉሰ ነገስቱ፣ በአዋጁ፣ በሥም በጠቀሷቸዉ መኳንንት መሪነት ግልፅ ጦርነት ተቀጣጠለ ። ከዚህ በኋላ አንድ ታማኝ ጦር ከግምባር ቀንሶ ወደ ጎጃም ማዝመት ግድ ሆነ ። ይህ ጎጃሞች ያቀጣጠሉት የክህደት ጦርነት የኢትዮጵያን ሰራዊት አቋም /የአንድነት አቋም/ አዳክሞታል ፡ ይህ በጎጃም የተቀሰቀሰዉ ሁከት በተለይ በሰሜኑ ግምባር ወሳኝ በነበረዉ የማይጨዉ ጦርነት ላይ የኢትዮጵያን ጦር ኃይል አቋም አዳክሞታል” ይላል ።

ጎጃምና ጎንደር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ታማኝ ተቆጥረው ጦርነት ላይ የተሰለፉት በዚህ ጦርነትና ደርግ ከኢህአዴግ ጋር ባደረገው ጦርነት ላይ ብቻ ነው ። ይህ የሆነበትም ምክንያት ጎጃሞች የበፊቱን የአፄ ሚኒሊክን ቂም ይረሱታል ተብሎ ስለተገመተ ነበር ጥርጣሬው የቀረላቸው ። ነገር ግን ጎጃሜዎች የበፊቱን በአፄ ሚኒሊክ የደረሰባቸውን ቂም

አረሱትም ነበርና በአፄ ኃይለስለሴ ጊዜ የጣሊያንን መምጣት እንደ ልዩ አጋጣሚ ተጠቅመው በሸዋና በየጁ ላይ ቂማቸውን ለመወጣት ሞከሩ ። በአድዋ ጦርነት ጊዜ ግን እራሳቸው አፄ ሚኒሊክ ስለነበሩና የቂማቸውንም መጠን ስለሚያውቁት በጥርጣሬ ጎጃሜዎችን ለብቻቸው ነበር ያሰለፏቸው፤ ስለሆነም ጦርነቱን ጥሩ በሆነ ሀገራዊ አቋም ማሸነፍ ተቻለ /ጦርነቱ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ነደመደመ/ ። ነገር ግን ጎጃሞች ለመጀመሪያ ጊዜ ታማኝ ተደርገው በተሰለፉበት በዚህ የጣሊያን ዳግሞ ወረራ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሀገራዊ አቋም ባየነው መልኩ ስለተበላሸ ጦርነቱ በኢትዮጵያ ተሸናፊነት ተጠናቀቀ /የውስጥ ባንዳ ካለ የውጭ ጠላትን በርትቶ መዋጋት አይቻልም/ ። እናም ጎጃሜዎች ወሎን /ሸዋና የጁን/ የተበቀሉ መስሏቸው ለውጭ ጠላት በባንዳነት በማገልገልና የውስጥ ውጋት በመሆን ሀገራቸውን እንድትደፈር አደረጉ ።

እናም የኢጣሊያ ሰራዊት የጦር መሳሪያ ብልጫዉንና ይህን የጎጃሞችን ባንዳነት ተጠቅሞ፣ ልክ ጀርመን በድንገት የፈረንሳይን ወታደሮች ጠርምሳ ፓሪስ እንደገባችዉ ሁሉ ጣሊያንም በድንገት የኢትዮጵያን ወታደሮች ጠርምሳ አዲስ አበባ ገባች ።

አፄ ኃይለስላሴ የተዘናጉት ኢትዮጵያ በ1916ዓ.ም የመንግስታቱ ማህበር /ሊግ ኦፍ ኔሽን/ አባል መሆን ስለቻለችና ከተፈራረሚቸዉ ዉሎች ዉስጥ አንዱ ማንም ሀገር የመንግስታቱ ማህበር አባል የሆነን አገር መዉረር አይችልም ስለሚል ነበር ። እናም ጃንሆይ ይህንን ህግ አምነዉ የጦርነትንና የመከላከያን ጉዳይ እረስተዉት ነበር ።

ጃንሆይ ሰኔ 23 ቀን 1929ዓ.ም ለመንግስታቱ ድርጅት አቤቱታ ለማቅረብ ይኖሩበት ከነበረዉ ለንደን ተነስተው ወደ ጀኔቭ በማቅናት፣ የዓለምን ህዝብ ህሊና ሰርስሮ የገባ ንግግራቸዉን ለጉባኤዉ አቀረቡ ። “ህግ ኃይልን ያሸንፋል ወይስ ኃይል ህግን ያሸንፋል? በአንድ ዉል ግርጌ የተፈረመ ፊርማ የሚረጋዉ ፈራሚዎቹ መንግስታት የሚጠቅማቸዉ ከሆነ ብቻ ነዉን? እግዚአብሔርና ታሪክ ፍርዳችሁን ሲያስታዉሱት ይኖራሉ” የሚሉ አረፍተ ነገሮች የተካተቱበት ሰፊ ንግግር ቢያደርጉም አንዳችም ፍሬ ሊያስገኝ አልቻለም ።

ፈረንሳይና እንግሊዝ፣ ኢጣሊያን አለመቃወማቸዉ፣ የተፈረመዉ ሊግ ኦፍ ኔሽን ዉል የይስሙላ መሆኑን ከማሳየትም አልፎ፣ ጃማይካዊያን እንደሚሉት ንጉሱን ነብይ ሊያስብላቸዉ በቃ ።

ፈረንሳይንና እንግሊዝን እግዚአብሔርና ታሪክ ሳይዘገዩ ፈረዱባቸዉ ። ወዳዉ ጀርመንና ኢጣሊያ የጦር ጓደኛ ሆኑ ። መስከረም 1931ዓ.ም ጀርመን ከኢጣሊያ ጋር ተመሳጥራ ቼኮዝላቫኪያን በመዉረር 2ኛዉን የዓለም ጦርነት ጀመረች ።

በዚህ ምክንያት እንግሊዝ የኢትዮጵያን አርበኞች ለማገዝና ኢጣሊያን ከአፍሪካ ለማስወጣት ወሰነች ። እናም ከሱዳንና ከኬንያ የተነሳዉ የእንግሊዝ ጦር በመጀመሪያ ጃንሆይን የጦሩ ሁሉ ጠቅላይ አዛዥ እንድሆኑ አደርጎ መረጠ ። ንጉሱም የአገራቸዉን ጀግኖች ከእንግሊዝ ወታደሮች ጋር እያስተባበሩና በእንግሊዝ የጦር አዉሮፕላኖች እየታገዙ ኢጣሊያን ከኢትዮጵያ ጠራርገዉ በማስወጣት ሚያዝያ 27 ቀን 1933ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ ። እናም ይህ ከ800ሺ በላይ ኢትዮጵያዊያን ያለቁበት የኢጣሊያ ዳግም ወረራ የተቋጨበት ሚያዝያ 27 ቀን ብሔራዊ ባዕል ሆኖ ይታሰባል ።

ኢጣሊያ በ5 ዓመት ቆይታዋ የተወሰኑ መንገዶችን ከመስራት ዉጭ ሌላ የሰራችዉ ቋሚ ነገር አልነበረም ። እናም ንጉሱ ሀገሪቱን የመቀየር እንቅስቃሴቼዉን እንደገና ካቆሙበት ጀመሩ ። ፍፁም በሆነ የሀገር ፍቅርና ቀናነት አገሪቱን በሁሉም ዘርፍ በማይታመን ፍጥነት ቀየሯት ። በዚህ መልኩ በተለይ እስከ 1953ዓ.ም ድረስ አገራቸዉን በሰላም ሲገነቡ ኖሩ የኮሌጆች፣ ዮኒቨርስቲዎና የምሁራኑም ቁጥር ከዘመኑ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ ።

ነገር ግን ከ1953ዓ.ም ጀምሮ የኮሌጆችና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ አንዳንድ የአመፅ እንቅስቃሴዎችን ጀመሩ ። ይህ የተማሪዎች የአመጽ እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ እየጨመረና በሌላዉ የማህበረሰብ ክፍልና ወታደሩ ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ መጣ ። ሰራዊቱ ተማሪዎቹን በመደገፍ ስረዓቱን ከማሻሻል ጀምሮ እስከ መገርሰስ የቻሉ እንቅስቃሴዎችን አደረገ ።

ንጉሱም እድሜቸዉ በጣም ስለገፉ ለተቃዋሚዎቹ በቂና ፈጣን መልስ መስጠት አልቻሉም ነበር ። አልጋ ወራሻቸዉ አስፋወሰንም ስለታመመባቸዉ ተተኪዉን ለህዝቡ ማሳወቅ አልቻሉም ።

እናም ሰራዊቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን እያቋቋመ አንዳንድ የህዝብ ጥያቄዎች እንዲመለሱና ስረዓቱም እንዲሻሻል የማድረግ ሙከራዉን ቀጠለ ። ሰራዊቱ አቋቁሟቸዉ ከነበሩት 3 ኮሚቴዎች ዉስጥ የመጨረሻዉ እነ ሻ/ቃ መንግስቱ ኃይለማሪያም ያሉበት "ደርግ" የተባለዉ ኮሚቴ ነበር ።

2ኛዉ ኮሚቴ ከተበተነ በኋላ እነ ሻለቃ አጥናፉ አባተ ዉስጥ ዉስጡን በድብቅ እየተገናኙ ይዶልቱ ነበር ። ወደ 80 የሚሆኑ የኮንጎ ዘማቾች ከተባበሩት መንግስታት የተሰጠን ገንዘብ አልተከፈለንም በሚል አንዳንድ የአመጽ እንቅስቃሴዎችን ጀምረዉ ስላልተሳካላቸዉ፣ የ4ኛ ክፍለ ጦርን እርዳታ ጠየቁ ። እናም እነ ሻ/ቃ አጥናፉ ይህን አጋጣሚ ሊጠቀሙበት ፈለጉ ። ሽ/ቃ አጥናፉ አባተ፣ ሻ/ል እንዳለ ተሰማ፣ ሃ/ቃ አሊ ሙሳ፣ ሻ/ል ወንዶሰን ብርሃኑ የተባሉ መኮንኖች ወደ ኮንጎ ዘማቾቹ ስብሰባ ተቀላቀሉ ። የኮንጎ ዘማቾችም ለዉጥ የማምጣትን ሀሳብ ካነሱ በኋላ ስብሰባዉ መልክ ይኖረዉ ዘንድ ሻ/ቃ አጥናፉን ሊቀመንበር አድርገዉ መርጠዉ ወደ 4ኛ ክ/ጦር የስብሰባ አዳራሽ ገቡ ።

ከዚህም በኋላ ስብሰባዉ ዉስጥ ብዙ የ4ኛ ክ/ጦር አባላት ስለተቀላቀሉና ስለበዙ የተወሰኑት እንዲቀነሱ ተደረገ ። በዚህ ስብሰባ የሚከተሉትን ዉሳኔዎች ወሰኑ ።

1. የምድር ጦር ልዩልዩ ክፍሎች፣ የአየር ኃይል፣ የባህር ኃይልና የፖሊስ ሰራዊት የየራሳቸዉን ወኪል መርጠዉ እንዲልኩ ።
2. ኣዲስ አበባ ያሉት የሬድዮና የቴሌቭዥን ጣቢያዎች፣ እንዲሁም ልዩልዩ ቁልፍ ቦታዎችን በጦሩ እንዲጠበቁ ማድረግ ።
3. የስጋት ምንጭ ይሆናሉ ተብለዉ የሚገመቱ የሲቭልና የጦር ባለስልጣናትን በቁጥጥር ስር ማዋል ።
4. መለዮ ለባሹ /ወታደሩ/ ሁሉ ለተጀመረዉ እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲሰጥ ጥሪ ማቅረብ ።
5. ለንጉሰ ነገስቱ ታማኝነትን መግለፅ ናቸዉ ።

በዚያኑ እለት ምሽት 2 ሰዓት ላይ እነኝህን መንግስትን በአንድ ጊዜ ከስልጣን ዉጭ የሚያደርጉ ቁልፍ ዉሳኔዎችን በፍጥነት በተግባር እንዲተረጎሙ ያደረጉት ሻ/ቃ አጥናፉ አባተ ናቸዉ ። ባንድ ጊዜ ሁሉም ነገር

በወታደሩ ቁጥጥር ዉስጥ ስለገባና ሊያስቸግሩ ይችላሉ ተብለዉ የተገመቱ ቁልፍ ባለስልጣናት በቁጥጥር ስር ስለሆኑ፣ መንግስት ዝም ብሎ ከማየት ዉጭ ምንም ነገር ማድረግ አልቻለም ፡ መንግስት እንቀሳቀሳለሁ ሲል እንቅስቃሴ ያሳዩ ባለስልጣናት ተለቅመዉ ስለሚታሰሩ ሁሉም ባለስልጣን አርፎ ተቀመጠ ።

በደረሳቸዉ መልእክት መሰረት አንዳንዶቹ ቢዘገዩም በአገሪቱ ካሉ 40 ያህል ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች አብዛኞቹ 3 አባላትን እየመረጡና እየወከሉ ወደ አዲስ አበባ 4ኛ ክ/ጦር ጊቢ ላኩ ። ገሚሱ "ሂድ እስኪ የሚባለዉን ሰምተህ ና" ተብሎ የመጣ እንጂ ለጉዳዩ ብዙዎች ትኩረት አልሰጡትም ነበር ። ባጠቃላይ ከሁሉም ክፍሎች የተዉጣጣ ወደ 120 አባላት ያሉት ኮሚቴ ስራዉን ጀመረ ።

በሻ/ቃ አጥናፉ የሚመራዉ ይህ ኮሚቴ ሰኔ 21 ቀን 1966ዓ.ም በ4ኛ ክ/ጦር ግቢ ዉስጥ መቋቋሙን በሬድዮ ይፋ ካደረገ በኋላ ለ4 ቀናት ያህል ጥቂት የቀድሞ ባለስልጣናትን እየመረጠ በ4ኛ ክ/ጦር ግቢ ዉስጥ ሲያስር ቆየ ። ሰኔ 26 ቀን ከምስራቅ ከአንበሳዉ ክ/ጦር ልዩ ልዩ ክፍሎች የተዉጣጡ 10 የ3ኛዉ ክፍለ ጦር አባላት ደረሱ ። ከነዚህ ዉስጥ አንዱ መንግስቱ ኃይለማሪያም ነበር ።

ሻ/ቃ መንግስቱ በመጡ በማግስቱ በተካሄደ ስብሰባ፣ መንግስቱ እጃቸዉን በማዉጣት "…ለመሆኑ ወደዚህ እንዲንመጣና ድጋፍ እንዲንሰጥ የጠየቃችሁን ምን አላማ ይዛችሁ ነዉ? ምን ለመስራት ነዉ አላማችሁ?" የሚሉ ጥያቄዎችን አቀረቡ ። ሻ/ቃ አጥናፉም "ተወክላችሁ የመጣችሁት መለዩ ለባሾች ምን እናድርግ? እንደት እናድርግ? አላማችንስ ምን ይሁን? የሚሉትን ጥያቄዎች በጋራ እየተወያየንና እየወሰንን ለህዝቡ ለዉጥ እንዲናመጣ ነዉ" ብለዉ መለሱ ። ሻ/ቃ መንግስቱም "ከምስራቅ እየመራሁ ያመጣኋቸዉ መለዩ ለባሾችና እኔ ስብሰባዉን የምንቀበለዉ ለህዝብ መሰረታዊ ለዉጥ የሚያመጣ አንድ እቅድ ካለን ብቻ ነዉ ። መለዩ ለባሹ ጥቃቅን ጥያቄዎችን እያነሳ ዘላቂነት የሌላቸዉ መልሶችን እየተቸረ ወደ ጦር ሰፈሩ መመለስ የለበትም ። እንደዚህ አይነቱን ተግባር ለመፈፀም ከሆነ ከቡድኔ ጋር ወደ መጣሁበት እመለሳለሁ ። በጎ ምኞት ብቻ አይበቃም፣ መርህ ያስፈልጋል፣

ወደ ተግባር የሚለወጥ እቅድ ያስፈልጋል” በማለት የተናገሩት ንግግር በሁሉም ተሰብሳቢዎች ዘንድ ትኩረትን አስገኘላቸዉ ።

ከ15 ደቂቃ የሻይ እረፍት በኋላ ዉይይቱ ቀጥሎ ከአባላቱ “አዲስ እቅድና ፕሮግራም የምናወጣ ከሆነ ለምን አዲስ ሊቀመንበር አንመርጥም” የሚል ሀሳብ ተነሳ ። አናም እንደገና ምርጫ ተካሂዶ ሻ/ቃ መንግስቱ ሊቀመንበር፣ ሻ/ቃ አጥናፉ ም/ሊቀመንበር፣ ገብረየስ ወ/ሃና ፀሀፊ ሆነዉ ተመረጡ ። ም/ሊቀመንበሩንና ፀሀፊዉን የመረጧቸዉ ተሰብሳቢዉን አስፈቅደዉ እራሳቸዉ ሻ/ቃ መንግስቱ ናቸዉ ።

ቀጥለዉም ሻ/ቃ መንግስቱ ንዑስ ኮሚቴዎችን በማቋቋም ስራቸዉን ሲጀምሩ፣ የፖለቲካና የዉጭ ጉዳይ ኮሚቴ፣ የኢኮኖሚ ኮሚቴ፣ የመከላከያ ኮሚቴ፣ የሶሻል ጉዳይ ኮሚቴ፣ የህዝብ ደህንነት ኮሚቴ፣ የአስተዳደርና ህግ ኮሚቴ፣ የእስረኞች አስተዳደር ጉዳይ ኮሚቴ፣ የስራ መቆታጠሪያ ኮሚቴና የጽህፈት አገልግሎት ኮሚቴ የተባሉትን ኮሚቴዎች በማቋቋም ነበር ።

ቀጥሎም “መፈክራችን ምን ይሁን?” የሚል ጥያቄ ተነሳ ። መንጌም ፈጥነዉ “ኢትዮጵያ ትቅደም” አሉ ። በእርግጥ ይች መፈክር የአዶልፍ ሂትለር “ጀርመን ትቅደም” ናት ። በኢትዮጵያ ምድር ግን መንጌ የመጀመሪያዉ ናቸዉ ። የኮሚቴዉንም ስም አንድ ግለሰብ የግእዙን ቃል አጣቅሰዉ “ደርግ” አሉት ። የአማርኛ ትርጉሙ ያዉ ኮሚቴ ማለት ነዉ ።

ደርግ የመንግስትን ስልጣንን መቦርቦርን ነበር ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት የጀመረዉ ። ይህንንም ሲያደርግ ለንጉሰ ነገስቱ ያለዉን ታማኝነት በተደጋጋሚ እየገለፀ የነበረ ሲሆን ጃንሆይም እዉቅና አልነፈጉትም ። ደርግም ከተለያዩ ወገኖች ትኩረት አገኘ ። በተለይ የስልጣን ጥም ያለባቸዉና ለለዉጥ ስንታገል ቆይተናል የሚሉት ምሁራን ያችን ያበቃላት ወንበር ለመቅለብ ከደርግ ተጣበቁ ። እናም ደርግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስር ሰደደ ።ከዚህ በኋላ ለንጉሱ ተከታታይ ጥያቄወችን ማቅረብ ጀመሩ ። ጃኖሆይም ከሌላ አመፀኛ እነዚህ ትንንሾቹ ሳይሻሉኝ አይቀሩም፤ ጀኔራሎች ቢሆኑ እንጂ እነኝህ ዞሩን አይመኙም ብለዉ ያሰቡ ይመስላል የጠቋቸዉን ጥያቄዎች ሁሉ እምቢ ያሉበት ጊዜ አልነበረም ።

ደርግ መጀመሪያ ለንጉሱ ያቀረባቸዉ ጥያቄዎች “…ለፖለቲካ እስረኞችና ስደተኞች አጠቃላይ ምህረት እንዲታወጅ” የሚል ሲሆን ጃንሆይም እምቢ

አላሉም ። ቀጥሎም ሙሰኛና የለዉጥ እንቅፋት የሆኑ ታላላቅ ባለስልጣናትና የጦር ጀነራሎች በቁጥጥር ስር እንዲዉሉ ተጠይቆ፣ ሳይዉል ሳያድር ባለስልጣናት በየቦታዉ እየተለቀሙ ይታጎሩ ጀመር ። በዚህ ስልት የዚያ ግዙፍ ግንድ ቅርንጫፎች ተመልምለዉ አለቁ ። ደርግ /መንግስቱ/ ምንጠራዉን በማጧጧፍ፣ ጦር አዝምተዉ ጉዳት ያደርሱብናል ብሎ የገመታቸዉን ታላላቅ ባለስልጣናት አጉሮ በመጨረሱ፣ ከዚህ በኋላ የጃንሆይ መንግስት ለደርግ ስጋት እንደማይሆን አረጋገጠ ።

ይህንንም ተከትሎ አንዳንድ የደርግ አባላት እየባነኑና እየነቁ መጡ ። ሊቀመንበር መንግስቱ እያዘናጋ ሳያስቡት በስልት እንቅፋቶቹን እየጠረገና ደጋፊዎቹን /ቲፎዞዎቹን/ በዙሪዉ እየሰበሰበ መንግስት እየሆነ ነዉ ። ፈጣኑ መንጌ ደግሞ አንዳንድ የኮሚቴዉ አባላት እየነቁ ሲመጡ የስልጣን ሽኩቻ ከመፈጠሩ በፊት መጋረጃ /ኮፍያ/ የሚሆን ሰዉ ከላዩ ላይ /ከፊት ለፊት/ ማስቀመጥ እንዳለበት ወሰነ ።

እናም በጦሩ ዉስጥ እጅግ ታዋቂና ተወዳጅ የሆኑትን ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን “የኮሚቴዉ መሪ እንዲሆኑ ይሹሙልን” የሚል ጥያቄ ከሌሎች ጥያቄዎች ጋር አጣምሮ የያዘ፣ በሻ/ቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን የሚመራ የደርግ ሉክ ወደ ጃንሆይ ተላከ ። የተላከዉንም ፅሁፍ ሻለቃ ናደዉ ዘካርያስ በንጉሱ ፊት አነበበ ። ንጉሱም በጣም ተቆጥተዉ “ሹዋሚና ሻሪ እናንተ መሆናችሁ ነዉ” በሚሉና በሌሎችም ጥያቄዎች አፋጠጧቸዉ ። የሉዕካን ቡድኑ አባላትም ጥያቄዉ የእነሱ ሳይሆን የሰራዊቱ መሆኑን አስረድተዉ ጀኔራል አማንን አሹመዉ ተመለሱ /በኋላ ደርግ ጀኔራል አማንን ገድሏቸዋል ። ጀኔራል አማን ሁኔታውን እንዳዩ ስልጣን እንደማይሰጧቸው ሲያውቁ ሌሎች ጀኔራሎችን ይቀሰቅሱባቸው ጀመር፤ በዚህ ምክንያት ደርግ ይዞ ሊያስሯቸው እጅ እንዲሰጡ ሲጠየቁ ተኩስ በመክፈታቸው፣ በተኩስ ልውውጡ ተገደሉ ። ጀኔራል አማን በሰራዊቱ ዘንድ እጅግ ይወደዱ ስለነበር ደርግ፣ የጀኔራል አማን ሞት ትኩረት እንዳይሰጠው ለማድረግ፣ ወዳው ማታ ታስረው የነበሩ ሌሎች 60 አዛውንቶችን ገደለ፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መግደል የደርግ ባህል ሆኖ ቀረ ። እናም የ60ቹ ሰዎች ሞት ምክንያት ጀኔራል አማን ናቸው ማለት ነው፤ መግደል የደርግ ባህል ሆኖ የቀረውም በጀኔራል አማን ምክንያት ነው/ ። ወደ ርዕሳችን ስንመለስ፣ ደርግ ቀጥሎም ጠቅላይ ሚኒስተር

እንዳልካቸዉ መኮነንን ሽሮ እንዲታሰሩ በማዲረግ በምትካቸዉ በሲቭሉ ማህበረሰብ ዘንድ ታዋቂና ተወዳጅ የነበሩትን ልጅ ሚካኤል እምሩን ሾመ ።

በመጨረሻም ጥቂት የደርግ አባላት ወደ ቤተመንግስት ሄደዉ እልፍኝ አስከልካያቸዉን ጀኔራል አሰፋን ለማሰር ሲሞክሩ ንጉሱ እርጅና በተጫነዉ ከባድ ቁጣ "እሱ ደግሞ ምን አደረገ ነዉ የምትሉት? የፈለጋችሁትን ዉሰዱ! እሱን ግን አትነኩትም! አለዚያ እኛንም እሰሩን!" ብለዉ አንባረቁባቸዉ ። ደርግም ለጊዜዉ ቢተዉላቸዉም ጄኔራሉ ማታ ወደ ቤታቸዉ ሲሄዱ ተይዘዉ ታሰሩ ።

አሁን ደርግ የቀረዉ እንቅፋት የለም ። በጃንሆይ ዙሪያ የነበሩ ወፋፍራም ባለስልጣናት ሁሉ ተለቅመዉ አልቀዋል ። የቀሩት ራሳቸዉ ጃንሆይ ከጥቂት አሽከሮቻቸዉ ጋር ብቻ ነዉ ። መስከረም 2 ቀን 1967ዓ.ም ሌሊቱን በጀኔራል አማን ትእዛዝ ቤተመንግስቱን በታንክና በወታደር አስከብበዉ አደሩ ። ማለዳ ላይ 13 አባላት ያሉት የደርግ ልዑክ ቤተመንግስት ገባ ፡ ሻ/ል ደበላ ዲንሳ በጃንሆይ ፊት የኮሚቴዉን የዉሳኔ ቃል አነበበ፤ "…ለሀገርና ለህዝብ ደህንነት ሲባል በዛሬዉ እለት ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ ከስልጣን ወርደዋል፣ ለደህንነተዎ ሲባልም አስተባባሪዉ ኮሚቴ ወዳዘጋጀለዎት ቦታ እንዲሄዱ ተወስኗል…." የሚል ጭብጥ ያለዉ ሀተታ ተነበበላቸዉ ።በመጨረሻ ንጉሰ ነገስቱ መናገር ጀመሩ "…ያነበባችሁትን ሰምተናል፣ በየጊዜዉ የሚለዋወጠዉ ነገር ለአገር የሚጠቅም ነገር እስካለበት ችግር የለዉም ። የኢትዮጵያን ታሪክ ጠብቃችሁ ማልማት ከቻላችሁ የእኛ ታሪክ እዚህ ላይ ያበቃል፤ ካልቻላችሁ የእናንተ ታሪክ እዚያ ላይ ያቆምና የእኛ ይቀጥላል ። አገራችንና ህዝባችንን በምንችለዉ አገልግለናል ። የኢትዮጵያ ህዝብ እድል የእኛን መወገድ የሚጠይቅ ከሆነ ግን ስራችንን አቁመን ማንኛዉንም ነገር ለመቀበል ዝግጁ ነን ። አሁን ተራዉ የእኛ ነዉ ካላችሁ ኢትዮጵያን ጠብቁ" ብለዉ አበቁ ። ደርግም ባዘጋጀላቸዉ ቮልስዋገን መኪና ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር ግቢ ይዟቸዉ በረረ ። የደርግ አብዮት ተሳካ ። ጃንሆይም በተወለዱ በ83 አመታቸዉ መስከረም 2 ቀን 1967ዓ.ም ስልጣናቸዉን ለቀቁ ።

ጃንሆይ ከቤተመንግስት ተወስደዉ በ4ኛ ክ/ጦር ግቢ ዉስጥ በቁም እስር ቆይተዉ፣ እንደገና ደግሞ ወደ ቤተመንግስቱ ግቢ ተመልሰዉ በአንድ መካከለኛ ቤት ገብተዉ እንዲኖሩ /እንድታሰሩ/ ተደረገ ። ከጊዜ በኋላ

ፊኛቸዉን መታመማቸዉ ተገለፀ ። ፕ/ር አስራት "ዉጭ አገር ሂደዉ መታከም አለባቸዉ" በማለት ደርግን ጠየቁ ። ደርግ ግን እዚሁ ይታከሙ እንጂ ዉጭ የማይሞከር እንደሆነ ወስኖ፣ እዚሁ እንዲታከሙ ተደረገ ። ንጉሱም እንደ ታከሙ ማገገም ቢጀምሩም፣ ደርግ /መንግስቱ/ ያች ዉጭ አገር ሄደዉ ይታከሙ የምትለዉ ጥያቄ ትከነክነዉ ጀመር ። እናም ደርግ ይችን የህመም አጋጣሚ ተጠቅሞ አፋጣኝ እርምጃ ለመዉሰድ ወሰነ ።

የመንግስቱ ኃይለማሪያም ልዩ ጠባቂ ጦር አዛዥ የነበሩት ሻ/ል ተስፋዬ ርስቴ ከ12 አመት እስር ከወጡ በኋላ ባሳተሙት መፀሀፍ፣ ነሐሴ 20 ቀን 1967ዓ.ም ተረኛ አብሮ የሚያድር አልባሻቸዉ ከንጉሱ መኖሪያ ለማደር ሲሄድ፣ በኮ/ል ዳንኤል አስፋዉ አማካኝነት "ለዛሬ ማደር አያስፈልግህም" ተብሎ እንዲመለስ እንደተደረገና ሌሊቱንም አፍኖ እንዲገድል የተላከዉ ወታደር ህሊናዉ እምቢ ብሎት እየተርበተበተ በመቸገሩ ራሱ ዳንኤል አስፋዉ አፈናዉን እንደፈፀመዉ አስፍረዋል ።

ደርግ በዚህ መልኩ ከገደለ በኋላ ቀብራቸዉ ላይ ችግር ሊፈጠር ይችላል በሚል ፍራቻ የሚከተለዉን ፈፀመ ። ስለ አቀባበራቸዉ ምስክርነት የሰጡት የቤተመንግስቱ የጥገና ክፍል ኃላፊ የነበሩት መሐንዲስ ጥላሁን ኪዳኔ "ነሐሴ 21 ቀን ከጧቱ 2 ፡ 30 ሰዓት ላይ በመርዕድ ንጉሴ ተጠርቸ፣ የከፈን ጨርቅና የሬሳ ሳጥን እንዳቀርብ ተጠይቄ…ሰጥቻለሁ ። ከቀኑ 7 ሰአት ላይ ሦስት 3በ3 የሆኑ ጉድጓዶች አስቆፈርኩ ። አራተኛ ጉድጓድም በሌሎች ሰዎች ተቆፈረ ። ጉድጓዶቹ 4 የሆኑት እኛ እንዳናዉቅ መሰለኝ ። ጉድጓዶቹን በዳንኤል አስፋዉ ትእዛዝ በኮንክሪት ዘጋኋቸዉ፣ በአጭር ጊዜም በጉድጓዶቹ ላይ የፕሬዝዳንቱ ቢሮ ተሰራ" ብለዋል ። ኢህአዴግ ሲገባ ኮ/ል ስለሺ መኩሪያ ቦታዉን ካሳዩ በኋላ 8 ሜትር ተቆፍሮ 3በ3 ሜትር ቱቦ ተገኘ፣ በኮ/ሉ መሪነት እንደገና ወደ ዉስጥ 3 ሜትር ሲቆፈር የንጉሱ አፅም ተገኘና በሙሉ ወጥቶ ስላሴ ቤተክርስቲያን እንዲያርፍ ተደረገ ።

እንግዲህ ወሎ ከዛግዌ ስርወ መንግስት የመጀመሪያዉ ንጉስ መራ ተክለሃይማኖት 912ዓ.ም ጀምሮ እስከ አፄ ኃይለስላሴ 1967ዓ.ም ድረስ ለ1055 አመት ያህል ኢትዮጵያን ሲመራ፣ ጣልቃ የገቡት አፄ ዮሃንስና ግራኝ አህመድ ብቻ ናቸዉ ። ግራኝ አህመድ 15 አመት፣ አፄ ዮህንስ 17 አመት፣

በአጠቃላይ 32 አመት ጣልቃ ሲገቡ፣ ቀሪዉን 1023 አመት ያህል ኢትዮጵያን የመሩት የወሎ ነገስታት ነበሩ ፡፡

ወሎ ይህን ያህል ዘመን ሀገሪቱን ሲመራ በብሄር ብሂረሰቦች መካከል አንድም ችግርና አድሎ ተፈጥሮ አያዉቅም ፡፡ የወሎ አገዛዝ ከብሄር አድሎ እጅግ ነፃ ከመሆኑ የተነሳ ብሄረሰቦች ሊጠቅሱት የሚችሉት በደል ስለሚያጡ፣ አንዳንዶች እንደ ህፃን ልጅ የተተራረቡትንና የተሰዳደቡትን ሲጠቅሱ ይስተዋላሉ ፡፡ አንዳንድ ይቃወሙ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችም ህዝብ የሚቀሰቅሱበት በደል ስለሚያጡ፣ እንደ ህፃን በርካታ የትረባ ቃላቶችን እራሳቸዉ አዘጋጅተዉ እያሰራጩ፣ ህዝቡን እንደዚህ እየተባልክ እየተሰደብክ ነዉ እያሉ ለመቀስቀስ ይሞክሩነበር ፡፡ ይህ እንግዲህ ምን ያህል ሊጠቅሱት የሚችሉት በደል እንዳጡና የወሎ አገዛዝ ምን ያህል ንፁህ እንደ ነበር ያሳያል ፡፡ አንዲት ወረዳ ብቻዋን ሀገር ብትሆን እንኳ በቀበሌ መተራረብ አይቀርም ፡፡ የሚገርመው ነገር የሁሉም ብሄረሰቦች ስድብ አታውቁም የሚል ነው፤ ሁሉም ትረባዎች ‘’እረ እነሱ እኮ ምንም አያውቁም’’፣ ‘’እረ እነሱ ደግሞ ምን ያውቃሉ’’ ወዘተ የሚሉ ነበሩ፣ ‘’ፈሪ ናቸው’’ ተብለው የተተረቡ የሉም፤ ምንአልባት በጊዜ ብዛት ምክንያት ፈሪ ወደሚለው አቅጣጫ ተቀይረው እንደሆን እንጂ ስድቦች በሙሉ ካለማወቅ ጋር የተያያዙ ነበሩ ፡፡ እናም እጅግ የሚገርመው ነገር የማናውቀው ነገር ምንድን ነው? ብሎ እራሱን የሚጠይቅ አለመኖሩ ነው ፡፡ ፈሪ የሚል ትረባ አለመኖሩና አያውቁም የሚለው ትረባ በዚህ መጠን ትኩረት ማግኘቱ በጣም የሚገርም ነገር ነው ፡፡ ስለዚህ ተሰዳቢዎቹ የማያውቁት በዚህ መጠን ትኩረት ያገኘ እጅግ ትልቅ ነገር /ሚስጥር/ አለ ማለት ነው ፡፡

አያውቁም የሚለው ነገር የተጀመረው የአፄ ሚኒሊክ መጨረሻ ዘመን አካባቢ ላይ ቢሆንም በጣም ጎልቶ የነበረው ግን በአፄ ኃይለስላሴና በደርግ ዘመን ነበር ፡፡ ትረባው በአፄ ሚኒሊክ መጨረሻ ዘመን ላይ ከጀመረና ስድቦች በሙሉ ምንም አታውቁም የሚሉ ከሆኑ በዚያን ዘመን የማናውቀው ነገር ምንድን ነበር? ፣ ሳይንሱን ነው የማናውቀው? /በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ ምንሽር ትሰራ ነበር? በልጅግ ትሰራ ነበር? ፣ ጓንዴ ትሰራ ነበር? ትምህርት እራሱ የተጀመረው በአፄ ሚኒሊክ ዘመን ነው/ ፡፡ ስለዚህ በዚያን ዘመን የሚታወቅ ሳይንስ ካልነበረ ፣ የማናውቀው ሀገራችንን ነው ማለት ነው፣

የኢትዮጵያን የታሪክ ሚስጥር አናውቅም ማለት ነው፣ ሀገሩን የማያውቅ ማለት ደግሞ ወላጆቹን /እናትና አባቱን/ የማያውቅ ማለት ነው ፡፡

ሀገር ማለት ምን ማለት ነው? ሀገር ማለት የወለደህ ምድር ማለት ነው /ሀገር ማለት ወላጅ ምድር ማለት ነው/፤ አብዛኞች እናት ሀገራችን ይላሉ፣ ጥቂቶች ደግሞ አባት ሀገራችን ይልሉ፣ ሁለቱም እናትም አባትም ወላጅነትን ያመለክታሉ ፡፡ የወለደህን /ያበቀለህን/ ምድር የሚቀማህ የለም፤ እራሱ ወልዶሀልና የምድሩ ባለቤት አንተ ነህ፤ ነገር ግን ያልወለደህ ምድር ከሆነ ዜግነት ቢሰጡህም ያንተ አይደለም /ሰጡህ ማለት ባለቤት አልነበርክም ማለት ነው፣ ምድሩ አልወለደህም ማለት ነው፣ ምድሩ እራሱ የወለዳቸው የእራሱ ልጆች አሉት ማለት ነው/ ፡፡ ስለዚህ የወላጅህን የኢትዮጵያን የታሪክ ሚስጥር የማታውቅ ከሆነ ምንም አታውቅም ተብለህ ብትሰደብ የሚገርም ነገር አይደለም ማለት ነው ፡፡ ሆኖም ተሰዳቢዎቹ የማናውቀው ሚስጥር ምንድን ነው ብለው እራሳቸውን ከመጠየቅ ይልቅ በስድቡ ይናደዱ ነበር፤ ይህ እንግዲህ ሌላ የሚያናድድ ነገር እንዳልተፈጠረና የወሎ አገዛዝ ምን ያህል የብሄር አድሎ የሌለበትና ንፁህ እንደነበር ያሳያል ፡፡

ሆኖም የወሎ ነገስታት ሀገሪቱን ለ1023 ዓመት ያህል ሲመሩ ለሀገሪቱ መጥፎ ባይሆኑም ለወሎ ህዝብ ግን ካለበት ተፈጥሯዊ ችግር አንፃር ያደረጉለት የተለየ ነገር የለም ፡፡ የገዥ መደቦቹ ለራሳቸዉ እንጂ ለህዝቡ ዴንታ አልነበራቸዉም ፡፡ ሌላዉ ቀርቶ የወሎን የዝናብ ስርጭት ለማስተካከል እንኳ አልሞከሩም ፡፡

ቀደም ሲል እንዳስቀመጥነው የዝናብ ስርጭትን ማስተካከል ይቻላል ፡፡ የዉሀ አካላት ልክ እንደ ጫካዎች ዝናብ የመሳብ ኃይል አላቸዉ ፡፡ አንድ አካባቢ ዉስጥ በርካታ የዉሀ አካላት ካሉ ከእነሱ የሚተነዉ ዉሀ

የአካባቢዉን አየር እርጥብ እንዲሆን ያደርገዋል ፡፡ አየሩ እርጥብ ከሆነ ደግሞ ወደ አካባቢዉ የሚገባዉ ደመና በቀላሉ ወደ ዝናብ ይቀየራል ፡፡ የዉሀ አካላት የሌሉበት አካባቢ ከሆነና አየሩ ደረቅ ከሆነ ግን ወደ አካባቢዉ የሚገባዉ ደመና ወደ ዝናብ ከመቀየር ይልቅ አልፎ ይሄዳል ፡፡ እናም በወሎ፣ በትግራይ፣ በአፋርና በሱማሌ አካባቢ ሰፋፊ ዉሀ የሚይዙ ግድቦችን/water reservoirs/ በመገንባት የአካባቢዉን የዝናብ ስርጭትን ማስተካከል ይቻል ነበር ፡፡

ኢህአዴግ የተንዳሆንና የተከዜን ግድቦች መስራቱ ለወሎና ለትግራይ ህዝብ ከፍተኛ ጥቅም አለዉ ። በ2007 ዓ.ም የተከሰተዉ የኢሊኖ ድርቅ ወሎንና ትግራይን በቀላሉ ያለፋቸዉ እነዚህ ግድቦች ባደረጉት አስተዋፆ ነዉ ብሎ መገመት ይቻላል ። ቀደም ሲል ጀምሮ በወሎ፣ ትግራይ፣ አፋርና በሱማሌ አካባቢ በርከት ያሉ ግድቦች ቢገነቡ ኖሮ ወሎ፣ ትግራይ፣ አፋርና ሱማሌ ያለምንም ስጋት የተስተካከለ የክረምት ዝናብ ማግኘት ይችሉ ነበር ። እናም የወሎ ነገስታት አገሪቱን እጅግ በጣም ረጅም ለሆነ ጊዜ ያህል ሲመሩ የዝናቡን ሁኔታ ለማስተካከል አልሞከሩም ነበር ።

የወሎ ነገስታት ለወሎ ህዝብ የተለዬ ጥቅም ባይኖራቸዉም፣ ለሀገሪቱ ግን ከሌሎች ነገስታት አንፃር ሲታይ እጅግ የተሻለ ስራ ሰርተዋል ። ከአፄ ኃይለስላሴ ስልጣን የነጠቀዉ ደርግ የራሱን ፀባይ ማስተካከል አቅቶት የራሱ ፀባይ ከሚያመነጫቸዉ ታጋዮቹ ጋር እየታገለ አንድም ቀን የተረጋጋ ስልጣን ሳይዝና ለሀገሪቱም አንድ ነገር ሳይሰራ ሞተ ።

የደርግ ተፈጥሯዊ ጥላት በመባል የሚታወቀዉ ኢህፓ ደርግን ገድሎ እሱም ሞተ ። ደርግን የጣሉት ሦስት ድርጅቶች ናቸዉ፤ እነሱም ኢህፓ፣ ህወሀትና ሻዕቢያ ናቸዉ ። ደርግን ሰይጣን እንዲሆን በማድረግ ከህዝብ የነጠለዉና ህወሀትንም ሻዕቢያንም ያፈረጠማቸዉ ኢህፓ ነዉ ። ህወሀትና ሻዕቢያ በቂ ወታደር ያገኙት በቀይና በነጭ ሽብሮች ጊዜ ነበር ። የህወሀትና የሻዕቢያ አብዛኛዉ ወታደር ወይ ዘመድ ተገድሎበት ነዉ ካልሆነ ደግሞ እራሱ ሊገደል አምልጦ ነዉ ። ስለዚህ ለሁለቱ ድርጅቶች ዋናዉን ስራ የሰራላቸዉ ኢህፓ ነዉ ማለት ነው ።የሦስቱንም ድርጅቶች ታሪክ አመዛዝነን ስናስቀምጠዉ ኢህፓ 45%፣ ህወሀት 35%፣ ሻዕቢያ 20% ደርግን የመጣል አስተዋፆ አድርገዋል ። ህወሀት ባትኖር ኖሮ ሻዕቢያ ደርግን አይጥለዉም ነበር፤ ሲጀመር በቀይ ኮከብ ዘመቻ ይደመሰስ ነበር ።

ሻዕቢያ ባይኖርም ህወሀት ደርግን ትጥለዉ ነበር፤ ሻዕቢያ እዚያዉ አፋቤት እያለ ህወሀት ሸዋ ደርሳ ነበር ። ሁለቱም ድርጅቶች ባይኖሩ ኢህፓ ደርግን ይጥለዉ ነበር፤ ህዝቡ ሲጨፈጨፍ ጫካ ዉስጥ ወደ ነበሩ ሌሎች ድርጅቶች መሄዱ አይቀርም ነበር /ደርግ አማራና ኦሮሞን አይንከባከብም ነበር/ ። ስለዚህ ኢህአዴግ ደርግ የወደቀዉ በሁሉም ብሄረሰቦች የጋራ ትግል ነዉ የሚለዉ እዉነቱን ነዉ ማለት ነው ።

እናም ደርግ ከራሱ ፀባይና ተፈጥሮ ጋር ታግሎ ከሞተ በኋላ ስልጣን የያዘዉ ኢህአዴግ፣ እስከ 1997ዓ.ም ድረስ ት/ት አካባቢ አንዳንድ ቀላል እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ተኝቶ ቆየ ፡፡ በ1997ዓ.ም ኢህአዴግ በህዝብ ተቀስቅሶ ከእንቅፉ ነቅቶ ተነሳ ፡፡ ከተኛበት የተነሳዉ ኢህአዴግ እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ በመንገድ፣ በኃይል ማመንጫዎች፣ በት/ት፣ በስኳር በኩል በርከት ያሉ እንቅስቃሴዎችን አደረገ፤ በባቡርም በኩል አንድ መስመር አድሶ የጀመራቸዉም አሉ ፡፡ ድርቅን በራስ አቅም ከመቋቋም አንፃር ኢህአዴግ በጣም ጥሩ ስራ ሰርቷል ፡፡ ባጠቃላይ ኢህአዴግ ከ1997-2007 ድረስ በጣም ጥሩ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል ማለት ይቻላል ፡፡

ነገር ግን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከሞቱ ወዲህ ኢህአዴግ ቀስበቀስ ወደ መቀነስ አዝማሚያ እየሄደ ይመስላል ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከመሞታቸዉ በፊት ጀምረዉት የነበረዉ የማኑፋክቸሪነግ /ኢንዱስትሪ/ ጉዳይም ከበፊቱ አንፃር ሲታይ እንቅስቃሴውን እየቀነሰ ይመስላል ፡፡ በእርግጥ ተከስቶ የነበረዉ ሰፊ ድርቅ በልማት እንቅስቃሴዉ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እንደሚያሳድር ይታወቃል፤ ሆኖም መንግስት እንደገና በፍጥነት በአዲስ ሞራል ወደ ልማት መመለስ ይኖርበታል ፡፡

## ማኑፋክቸሪንግ

/Manufacturing/

ለገበሬ ውሀ ከመሸጥ ቀጥሎ ማኑፋክቸሪንግ ለአንድት ዘመናዊት ሀገር የጀርባ አጥንት ነዉ ፡፡ ያደጉት ሀገሮች አብዛኛዉ ህዝብ ተቀጥሮ ህይወቱን የሚመራዉ እዚሁ ዘርፍ ዉስጥ ነዉ፣ ለምሳሌ ያህል የጀርመን ከተሞች ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝባቸው ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ነው ፡፡ ያደጉት ሀገሮች የኋላ ቀር ሀገሮችን ገንዘብ የሚበዘብዙትና ሀብት የሚያጋብሱትም በዚሁ ዘርፍ ነዉ ፡፡ ኢትዮጵያም በቡናም ይሁን በሌጦ የምታገኛትን ዶላር መልሳ የምታስረክበዉ እነዚህኑ የኢንዳስትሪ ዉጤቶችን ለማስገባት ነዉ ፡፡

ነጮቹ የአፍሪካ ዜጎች ስራ አግኝተዉ በመቀጠራቸዉ ይደነቃሉ ፡፡ አሁን ከተቀመጥንበት ቦታ ሆነን ዙሪያችን የምናያቸዉ ነገሮች፣ በእጃችን የያዝናቸዉ

ነገሮች.... ወዘተ በሙሉ የዚሁ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዉጤቶች ናቸዉ ። ለምሳሌ ያህል፣ የምናሽከረክራቸዉ ተሽከርካሪዎች፣ እቤታችን ያሉት ማቀዝቀዣ፣ ቴሌቭዥን፣ ኮምቲዉተር፣ ሞባይል፣ እስኪርቢቶ፣ የምንበላባቸው፣ የምንጠጣባቸው፣ የለበስናቸው ...ወዘተ የዚሁ ዘርፍ ዉጤቶች ናቸዉ ። ስለዚህ እነኝህ ነገሮች ሁሉ ሀገር ውስጥ የማይሰሩ ከሆነ ህዝቡ ስራ እየሰራ አይደለም ማለት ነው /ስራ የለም ማለት ነው/ ። እናም ነጮቹ አፍሪካዊያን ወደ እነሱ በስደት በመኮረፋቸው ሳይሆን የሚደነቁት ሀገር ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች እነኝህን በዶላር የሚገቡ እቃዎች በሙሉ በሁለት ወር የክረምት ዝናብ ብቻ በሚያገኟት ገቢ እየገዙ መኖር በመቻላቸው ነው ።

የአፍሪካ አገሮች የማኑፋክቸሪንግ ዉጤቶችን ለማስገባት ወደ ዉጭ የሚጋዘዉን ገንዘብ አስቁመዉ እዚሁ የማምረት ጥረት ቢያደርጉ ኖሮ በ5ና 10 አመት ዉስጥ ሁሉንም የሀገሮቹን ችግሮች /ስራ አጥነት፣ የመንግስትን የበጀት እጥረት፣ የዶላር ወጭን...ወዘተ/ ማጥፋት ይችሉ ነበር ። አሁን ሀገራቱ /በተለይ ኢትዮጵያ/ ውስጥ እነዚህን ነገሮች የሚያመርት የተማረ የሰዉ ኃይል ችግር የለባቸዉም ። የሀገራቱ ችግር አልቀየር ብሎ ያስቸገረዉ የመንግስት አመለካከት ነዉ ። ከላይ ሆነዉ የኢንዳስትሪዉን ዘርፍ የሚመሩት ሰዎች፣ የማህበረሰብ ሳይንስ /social science/ የተማሩ ሰዎች ናቸዉ ። ለነዚህ ሰዎች ደግሞ መኪና ወይ ፍሪጅ መስራት ማለት ፡ - ከሰማዬ ሰማያት ለነጮች የተሰጠ፣ በጥቁሮች የማይሞከር፣ እጅግ ዉስብስብና አስቸጋሪ መስሎ ስለሚታያቸዉ፣ ሀገራቱን ገዥ ሆነዉ እንዲቀጥሉ አድርገዋቸዋል ።

እንደ እዉነቱ ከሆነ ግን መኪና መስራት ፡ - የሸክላ ጀበናና ጋን ከመስራት ወይም የሞፈርና የቀምበር እቃዎችን አምርቶ ከመገጣጠም አይበልጥም ። ጀበና፣ ጋን፣ ሸማ፣ ሞፈር፣ እንስራ፣ ማረሻ፣ ወገል፣ብራና፣ የብራና ቀለም፣ ማሲንቆ፣ ጡሩምባ፣ አረቂ ...ወዘተ መስራት ከአባቶቻችን የወረደ ስለሆነ አቅለን ስለምናየዉ ለመስራት እንሞክራለን፤ ከብዙ ሙከራና ማበላሸት በኋላም ትክክለኛዉን ጀበናና ጋን መስራት እንለምዳለን ። ስለመኪና ያለን አመለካከት ግን መኪና ለመስራት እንዳንሞክር ያደርገናል፤ ካልሞከርን ደግሞ መኪና መስራት ለእኛ ዉስብስብ እንደሆነ ይቀራል ማለት ነው ፡ አንድን ጋን ሰርቶ የማያዉቅን ሰዉ ጋን ስራ ብንለዉ ገበሬዎቹ ስለሰሩት እሱም እሰራዋለሁ የሚለዉ አመለካከት /ሞራል/ ስለሚኖረዉ መሞከሩ አይቀርም፤ ከሞከረ ደግሞ ከሙከራዎች በኋላ አንድ ቀን ትክክለኛዉን ጋን መስራቱ አይቀርም

/ዋናው አመለካከቱ፣ ሞራሉ ነው ማለት ነው/ ። ስለዚህ ገበሬዎቹ ያልሞከሩትን ነገር ለመሞከር እንፈራለን ማለት ነው /ችግራችን ይኸ ነው ማለት ነው/፤ ገበሬዎቹ ያልሞከሩትን ነገር የማንሞክር ከሆነ ደግሞ ኢኮኖሚያችንም ገበሬ መራሽ እንደሆነ ይቀጥላል ማለት ነዉ /GDPው በገበሬዎቹ ላይ ብቻ የተመሰረተ ይሆናል፣ እኛ የምንፈጥረው ሀብት የለም ማለት ነው፣ ሀገር ውስጥ የምንጠቀመውም ወደ ውጭ የምንልከውም ገበሬው የሚያመርተውን ብቻ ነው ማለት ነው፣ የምንበላውም ገበሬውን እያታለልን ነው ማለት ነው/ ። ገበሬው ደግሞ ተፈጥሮን /የሁለት ወሯን የክረምት ዝናብ/ ተጠግቶ ነው ያለው፣ ውሀ በማቅረብ እንኳን ልናግዘው ይገባ ነበር ። የሁለት ወሯን የክረምት ዝናብ ብቻ መሰረት አድርገን ገበሬውን ለማገዝ የምናደርገው መፍጨርጨር የትም አያደርሰንም /በሁለት ወሯ ዝናብ ብልፅግናን ማስብ ህልም ነው፣ ቅዠት ነው፣ በእውን ሊጨበጥ የማይችል የሌሊት ህልም ነው፣ ከተፈጥሮ ጥገኝነት አልወጣንም ማለት ነው/ ።

አሁን አፍሪካ በመኪናዎችና በመሽነሪዎች እየተሞላች ነው፤ የሚገርመው ነገር ግን ሁሉም ከውጭ የተገዙ ናቸው፤ ገበሬዎቹ ያመረቱትን ሸጠን የተገዙ ናቸው/ቡና/ ። እናም ሀብት በማመንጨት ገበሬዎቹን ልናግዛቸው ይገባል ። ለምሳሌ ያህል ኢትዮጵያ ውስጥ ፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስተር ስር ቢያንስ 9 ተጨማሪ ኮርፖሬሽኖች መቋቋም አለባቸው ብለን እናምናለን፤ እነሱም የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች አምራች ኮርፖሬሽን /ሞባይልን፣ ኮምፒውተርን፣ ቴሌቭዥንን ወዘተ ያጠቃልላል/፣ የኢንጂን አምራች ኮርፖሬሽን /የመኪናን፣ የጀነሬተርን፣ የwater pumpን ወዘተ ያጠቃልላል/፣ የመለዋወጫ እቃዎች /spare part/ አምራች ኮርፖሬሽን /የመኪናን፣ የጀነሬተርን፣ የwater pumpን ወዘተ ያጠቃልላል/፣ የማቀዝቀዣ እቃዎች አምራች ኮርፖሬሽን /ፍሪጅን፣ air conditioningን ወዘተ ያጠቃልላል/፣ አልባሳት አምራች ኮርፖሬሽን /አልባሳትን፣ ጫማን ወዘተ ያጠቃልላል/፣ የህክምና መድኃኒቶችና እቃዎች አምራች ኮርፖሬሽን፣ የፅህፈት መሳሪያዎች አምራች ኮርፖሬሽን፣ የቤት እቃዎች አምራች ኮርፖሬሽን፣ ምግብ አምራች ኮርፖሬሽን /ዘይትን፣ ለስላሳን፣ ብስኩትን ቢራን ወዘተ ያጠቃልላል/ ።

ይህ ሲሆን ከውጭ የምናስገባበትን ዶላር አስቀረነው፣ ዶላሩን ተጠቀምንበት፣ ሰራተኛ ቀጠርንበት ወዘተ ማለት ነው ። በዚህ መልኩ

ገበሬዎቹን ስናግዛቸው ተጨማሪ የሀብት ምንጭ ሆን ማለት ነው /ከገበሬና ከተፈጥሮ ብቻ መጠበቅን አቆምን ማለት ነው/ ። በአሁኑ ሁኔታ ግን የምንበላው ገበሬዎቹ የሚበሉትን ብቻ ነው፣ የምንጠጣውም ገበሬዎቹ የሚጠጡትን ብቻ ነው …ወዘተ ። ለምሳሌ ያህል ወጥ ውስጥ የሚገቡት ቅመሞች እነዚያው ገበሬው ያገኛቸው ቅመሞች ብቻ ናቸው፤ ዝንጅብልና ኮረሪማን ገበሬው ባይጠቀምባቸው ኖሮ እኛ ደፍረን አንሞክራቸውም ነበር /ከማይበሉ ነገሮች መድበናቸው ይቀጥሉ ነበር፣ እንደ ገዳይ ነገር እንቆጥራቸው ነበር/ ። ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያ ውስጥ በፋብሪካ የሚመረቱትን ብስኩቶች እንኳን እስከ አሁን ድረስ አልቀየርናቸውም፣ እስከ አሁንም ድረስ ሁሉም ብስኩቶች ከስንደ ብቻ ነው የሚሰሩት /ሁሉም በአፄ ኃይለስላሴ ጊዜ ከስንደ ብቻ እንደየሚመረቱት ናቸው/ ። እንደነ ጅግራ፣ ቆቅ፣ ሶረኔ …ወዘተ የመሳሰሉ የዱር እንስሳዎችም ብዙ ሀገር ውስጥ የቤት እንስሳ ናቸው /በተለይ አረብ ሀገር ውስጥ/፤ እኛ ጋር ግን ገበሬዎቹ ስላላመዷቸው ተረስተው እየጠፉ ነው /ከዱር የተወለዱት የዱር እንስሳት እድሜ ልካቸውን ቢታሰሩም አይለምዱም፣ ወዳደጉበት ወደ ዱሩ መሄዳቸው አይቀርም ። ነገር ግን እነሱን አስሮ እንዲወልዱ በማድረግ ጫጩቶቹ ከታሰረችው እናታቸው ጋር አብረው ከሰው መሀል ካደጉ የትም አይሄዱም/ ። እናም ገበሬዎቹን ከኋላ ከኋላ መከተልን ማቆም አለብን፤ ከፊት ሆነን ልንመራቸው ይገባል እንላለን /በገበሬ መመራትን ማቆም አለብን እንላለን/ ።

ወደ ርዕሳችን ስንመለስ መኪናን እንደምሳሌ አነሳን እንጂ ዱሮ አገር ዉስጥ ይሰሩ የነበሩትን እጅግ ቀላል እቃዎችን ሳይቀር ከዉጭ እናስገባለን ። ለምሳሌ የብረት ድስት /ግብፅ/፣ የተለያዩ ሰሀኖች /ግብፅ/፣ የተለያዩ መጠጫዎችን /ግብፅ/፣ እስኪርቢቶ /ግብፅ/…ወዘተ ።

የማኑፋክቸሪንጉ ዘርፍ በመንግስት ትኩረት አግኝቶ ብቃቱ ባላቸው ባለሙያዎች /መካኒካል መሐንዲሶች/ ቢመራ ኖሮ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ሁሉንም የሀገሪቱን ችግሮች በማጥፋት ህዝቡ የተሻለ ህይወት እንዲኖረዉ ማድረግ ይቻል ነበር፣ ሲያዛጋ የሚዉል ስራ አጥም አይኖርም ነበር፣ ሀገሪቱ ዉስጥም ከፍተኛ ሀብት ይመነጭ ነበር ። ነጮቹ እንደ ሚያደርጉት የገበያ ተወዳዳሪነቱ እስኪዳብር ድረስ ህዝቡ የሀገር ዉስጥ እቃዎችን እንዲገዛ የሚያስገዲዱ ጫናዎችን ማድረግ፣ የአለም ገበያ ተወዳዳሪነትን ማፍጠን

ካስፈለገም 20 መኪና በማያስገባ ገንዘብ የዉጭ የታዋቂ ኢንዱስትሪ ሰራተኞችን ለአጭር ጊዜ /በእረፍት ጊዜቸዉ/ በማስመጣት አንዳንድ ምክሮችን በመዉሰድ የሀገሪቱን ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት ይቻል ነበር ፡፡

እናም የአፍሪካ መንግስታት ይህን መስራት አቅቷቸዉ፣ በየቦታዉ እያዛጋ የሚዉል ስራ አጥ ሞልቶ፣ በዶላራቸዉ የዉጭ ሀገር ሰራተኞች ተቀጥረውበት ይኖራሉ ፡፡ እቃዎችን ከዉጭ እያስገባህ ነዉ ማለት በአንተ ገንዘብ የዉጭ ሀገር ዜጎች ተቀጥረዉበታል ማለት ነዉ ፡፡ ከዉጭ የሚገቡ እቃዎችን ቀስ በቀስ በመቀነስ ወደ ዜሮ ማምጣት ማለት በአንድ ስኬት አራት እጥፍ ማደግ ማለት ነዉ ፡ አንድ ከዉጭ የሚገባን እቃ እዚሁ አመረትከዉ ማለት ፡ - ወደ ዉጭ ሊወጣ የነበረን ገንዘብ አድነህል፣ ሰራተኛ ቀጥረህል፣ ሞክረህበታል /ልምድ አግኝተህበታል/፣ ምርት ለገበያ አቅርበህል /ሻጭ ሆነህል/ ማለት ነዉ ፡፡

ይህን የውሀ ሽያጭና የማኑፋክቸሪንግ ጉዳይ /በጥቁሮችና በነጮች መካከል ያለዉ ልዩነት ጉዳይ/ የገባዉ አፍሪካዊ መሪ የለም ፡፡ አንዳንድ የአፍሪካ አገር ዜጎች ጀግኖች እያሉ የሚጠቃቅሷቸዉ ግለሰቦች አሉ ፡፡ ለምሳሌ ያህል ማንደላ፣ ሙጋቤ… ወዘተ ፡፡ ከምክንያቶቻቸዉ ዉስጥ ደግሞ ከቅኝ ግዛት ነፃ አዉጥተዉናል የሚል ይገኝበታል፤ እጅግ ስህተት ነው ፡፡ እርግጥ ነዉ ለነፃነታቸዉ ለዬት ባለ ሁኔታ መታገላቸዉ ሊያስከብራቸዉ ይገባል፤ ነገር ግን አፍሪካንና ሌሎች ቅኝ ተገዥዎችን ከቅኝ ግዛት ነፃ ያወጣቸዉ የጀርመኑ የናዚ ፓርቲ መሪ የነበረዉ አዶልፍ ሂትለር ነዉ ፡፡ እንደምናውቀው የሁለተኛዉ የአለም ጦርነት ዋናዉ መነሻዉ የቅኝ ግዛት ሺሚያ ነበር፤ የሁለተኛው የአለም ጦርነት ቀስቃሺ ደግሞ የጀርመኑ አዶልፍ ሂትለር ነው ፡ በዚህ ጦርነት ምክንያት ከ80 ሚሊዮን በላይ የአለም ህዝብ አልቋል ፡፡ በዚህ የአለም ህዝብ እልቂት ምክንያት ሀያላኑ ሀገሮች፣ ቁጭ ብለው አሰቡት ፡፡ ይህ የቅኝ ግዛት ሽሚያ ካልቆመ በስተቀር እርስ በርሳቸዉ ሊተላለቁ ነው ፡፡ ስለዚህ በአፋጣኝ ሌላ የቅኝ ግዛት ስልት /ዘዴ/ መፈለግ ነበረባቸዉ፤ አሰቡት፣ ቅኝ ግዛቶቻችንን እየለቀቅን ብንወጣ ምን የሚቀር ነገር አለ? እዚህስ ሆነን ምን እንሰራለን? እንደዉም እነሱን ማሰልጠንና ስራ እንዲለምዱ ማድረግ ይሆናል /ምሳሌ ደቡብ አፍሪካ/ ፡፡ ስለዚህ ‘’ምርቱን እዚያዉ እያመረትን ወደ ቅኝ ግዛቶቻችን መላክ’’ የሚለዉን ስልት ፈጠሩ ፡፡

አሁን የቻይና ዉድድር አስቸገራቸዉ እንጂ ለምሳሌ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የነበሩት ሀገሮች ዉስጥ የሚሸጠዉ እቃ በሙሉ ፈረንሳይ ሀገር ዉስጥ የተመረተና ፈረንሳይኛ የተፃፈበት ነዉ ። የፈረንሳይ ቅኝ ግዛቶች እስከ አሁንም ድረስ የፈረንሳይ ወታደራዊ ከለላ አላቸው፣ የእንግሊዝም እንደዚያው ።

እናም አፍሪካ ዉስጥ ጀግና የለም፤ ሀገሩን አምራች ያደረገ የለም፤ እስከ አሁንም ድረስ ሁሉም የአፍሪካ ሀገሮች ገዥዎች ናቸው፣ የአለም ደካማ ሀገሮች ሁሉ ማምረት የሚለማመዱት ለአፍሪካ በመሸጥ ነው ። አሁን ከአፍሪካ ውጭ ያሉ የአለም ሀገሮች በሙሉ በብዛት የሚፈልጓቸውን እቃዎች የሚያመርቱት እራሳቸው ናቸው /ዜጎቻቸውንም በብዛት ይቀጥርላቸዋል/፣ አሁን ከአፍሪካ ውጭ ያሉ ሁሉም የአለም ሀገሮች ከውጭ የሚያስገቡት በብዛት የማይፈልጓቸውን እቃዎች ብቻ ነው /ፋብሪካ ቢከፈትም ብዙ ደምበኛ አይኖራቸውም ብለው የገመቷቸውን እቃዎች ብቻ ነው ከውጭ የሚያስገቡት/ ። እናም አፍሪካ ውስጥ እስከ አሁን ድረስ ጀግና አልተወለደም ማለት ነው ። ሙጋቤ የነጮችን መሬት እየቀማ ለጥቁሮች ሲያድል የአለም አቀፉን ሁኔታ በመተማመን እንጂ እንግሊዝ ተመልሳ ብትመጣ ዚምባቡዌ ዉስጥ የተሰራ የሚተኮስ ሚሳይል /ሮኬት/ ወይም ጀት ቀርቶ ዚምባቡዌ ዉስጥ የተሰራ ክላሽንኮቭ እንኳን አይገኝም ። ጀግና ማለት ሀገሩን ከገዥነት ወደ አምራችነት ቀይሮ ማንኛዉንም ጥቃት በራሷ መመከት የምትችልበት ደረጃ ላይ ያደረሰ እንደሆነ ነዉ ። አሁንም ነጮቹ ሀሳባቸውን ቀይረው እንደገና ወረራ ቢጀምሩ ወይ እኛን ማጥፋት ቢፈልጉ ትንሽ እንኳን መከላከል የሚያደርግ አፍሪካዊ ሀገር የለም ።

አንዳንዶች ዱሮ አፄ ሚኒሊክ ከኢጣሊያ ጋር ሲዋጉ በነበረዉ የጦር መሳሪያና የስልጣኔ ልዩነት ይስቃሉ፤ ትክክል አይደለም ። የበፊቱ የስልጣኔ ልዩነት ይሻል ነበር /ልዩነቱ ጠባብ ነበር/ ። አሁን እንግሊዝ ወይ ኢጣሊያ አንድትን የአፍሪካ ሀገር ለመዉረር ቢፈልጉ፣ ህዝብና ወታደሩን እየመረጡ ለመምታት ካልተጠነቀቁ በስተቀር ጦርነቱን በርቀት፣ እዚያዉ ሀገራቸው ሆነው ይጨርሱታል፣ በግምባር ተገናኝቶ መዋጋት እንኳን አይቻልም፣ አይደለም ልንገድላቸው ይቅርና እነሱን በአይናችን እንኳን ማየት ሳንችል በእርቀት ያጠፉናል ። አሁን ዘመኑ የሮኬት ዘመን ነዉ፤ ዉድድሮች ሁሉ የሮኬት ዉድድር እየሆኑ መጥተዋል ። የሮኬት ቴክኖሎጂ፣ የበላይነትና የስልጣኔ መለኪያ እየሆነ መጥቷል ። ሮኬቶች ደግሞ የማይሄዱት እርቀት

የለም፤ እንኳን እዝች አለም ዉስጥ ቀርቶ ቤት እየተሸከሙ ጁፒተር ድረስ እየሄዱ ነዉ /ካሜራና ቪዲዮ መቅረጫ የሚይዝ ቤት/ ። ስለዚህ ሮኬቶችን ፈንጂ አሸክሞ የተፈለገዉን ያህል እርቀት መላክ ይቻላል ማለት ነው /ፈንጂ ተሸክመዉ የሚጓዙ ሮኬቶች ሚሳይል ይባላሉ/ ። እናም ጅምላ ጦርነቶችን በርቀት መጨረስ ተችሏል፤ ይህ ሁሉ ሲሆን አፍሪካ ዉስጥ ታንክና ክላሽንኮቭ እንኳን በትክክል የሚያመርት ሀገር የለም ። እናም የስልጣኔ ክፍተቱ የዱሮው ይሻል ነበር ። ስለዚህ አፍሪካ ዉስጥ እስከ አሁን ድረስ ገና ጀግና አልተወለደም ማለት ነዉ ።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመለስ፣ በርካታ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ለመስራት በእቅድ ይዘዋቸዉ የነበሩ ስራዎች ሳይጀመሩ ተረስተዋል ። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከመሞታቸዉ በፊት ሊጀመሩ በእቅድ ተይዘዉ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሞቱ በኋላ ከተረሱት እቅዶች መካከል ፡ - እያንዳንዱን የሀገሪቱን ቀበሌ በመንገድ ማገናኘት፣ እያንዳንዱ የሀገሪቱን ቀበሌ ቢያንስ በማእከል ደረጃ የኤሌክትሪክ መብራት እንዲያገኝ ማድረግና መሬት የሌላቸዉ የገጠር ወጣቶች የሙያ ስራዎችን /እደ ጥበብ ሥራዎችን/ የሚሰሩባቸዉ ማእከላትን በእያንዳንዱ ቀበሌ ማዘጋጀት የሚሉት ይገኙበታል ።

እነዚህ እቅዶች ለአንድት ሀገር መለወጥ እጅግ ቁልፍ እቅዶች ናቸዉ ። ይህን የሜክል ኋላ ቀር የገጠር ህዝብ ተሸክሞ ማደግ አይቻልም ። ሽግግር/transformation/ ማለትም ይኸዉ ነዉ ። በአጠቃላይ ስልጣኔ ማለት መሰረተ ልማት ማለት ነዉ፣ መሰረተ ልማት ሀብት ነው /ገንዘብ ነው/ ። የኢትዮጵያን ከተሞች ብናያቸው፣ ሁሉም መንገዶችን ተከትለው የተደረደሩ ናቸው፤ በአንፃሩ የሰለጠኑና የተሻለ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችም ያሉት በእነዚሁ መንገዶች ዳርቻ ነው ። የሀገሪቱም የታክስ ገቢ ከሞላ ጎደል በሙሉ የሚሰበሰበው እነዚህን መንገዶች ተከትለው ከሰፈሩት ህዝቦች ነው ። ስለዚህ መሰረተ ልማት ሀብት ነው ማለት ነው ። አንዲት መሰረተ ልማትን ለሁሉም አካባቢዎቿ /ህዝቦቿ/ ያላዳረሰች ሀገር በቂ የታክስ ገቢ ከሰፊው ህዝብ ልትሰበስብ አትችልም ማለት ነው ። በሀብታም ሀገሮችና በደሐ ሀገሮች መካከል ያለው የአጠቃላይ ገቢ /GDP/ ልዩነትም ይኸው ነው ። እነሱ ሁሉም የሀገራቸው ህዝብ መሰረተ ልማት የተሟለለትና የተሻለ ገቢ ያለው ስለሆነ ከመላው የሀገራቸው ህዝብ ጥሩ የታክስ ገቢ ስለሚሰበስቡ ነው ። እናም እኛ በነዚህ መንገዶች ዳርቻ የምንሰበስባት ታክስ ከነሱ ከመላው ሀገሪቱ

ከሚሰበሰበው ታክስ ጋር ሲወዳደር ምድርና ሰማይ ይሆናል ። ስለዚህ መበልፀግ ማለት መንገድ ማለት ነው፣ መበልፀግ ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ማለት ነው፣ መበልፀግ ማለት ማኑፋክቸሪንግ ማለት ነው፣ መበልፀግ ማለት ትምህርት ማለት ነው፣ መበልፀግ ማለት የህክምና አቅርቦት ማለት ነው፣ መበልፀግ ማለት ሰፋፊ እርሻዎች ማለት ነው …ወዘተ ። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም ሀገሪቱን ሙሉ በሙሉ ለመለወጥ ቆርጠዉ ተነስተዉ ስለነበር ነዉ እነዚህን እጅግ ቁልፍ እቅዶች አቅደዉ የነበረዉ ። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህን እጅግ ቁልፍ እቅዶች እንደገና ማስታወስ ይኖርበታል ማለት ነው ።

ከዚህም በተጨማሪ መንግስት ቀጥተኛውን /አቋራጩን/ የብልፅግና መንገድ መምረጥ አለበት፣ ይህ አጠቃላይ የአህጉሪቱ ችግር ነው፤ አጠቃላይ የአፍሪካ መሪዎች ድንጋይን ወደ ዳቦ ለመቀየር ነው የሚሞክሩት /እጅግ ጠመዝማዛውንና አሰልችውን የብልፅግና መንገድ ነው የሚከተሉት/ ። በቃ ውሀ ሀብት ነው /ውሀ ገንዘብ ነው/! ቀደም ሲል እንዳስቀመጥነው፣ ውሀ ለብልፅግናና ከተፈጥሮ ጥገኝነት ለመውጣት ቀጥተኛው መንገድ ነው /ከውሀ ውጭ እፀዋት የሚያመርት ፋብሪካ የለም፣ የሚበሉት ደግሞ ዕፀዋትና እንስሳት ብቻ ናቸው፣ ሁለቱም የውሀ ውጤት ናቸው፣ ሌላ የሚበላ ነገር የለም/ ። ነገር ግን እስከ አሁንም ድረስ ውሀን ለገበሬ ለመሸጥ የሞከረ አፍሪካዊ መንግስት የለም ። ውሀ በአለማችን ላይ በጣም ርካሽ ከሚባሉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው ። ውሀን ለገበሬዎች ለመሸጥ የመነሻውን ካፒታል /initial investment/ እንደ አቅምህና እንደ ፍላጎትህ ከፍ ዝቅ ልታደርገው ትችላለህ ። ገንዘብ የሌለው መንግስት የውሀ ሽያጩን /የውሀ ታክሱን/ ስራ በየቦታው በዶዘር በሚቆፈሩ ሰፋፊ ጉድጓዶች መጀመር ይችላል ። ከነዚህ በዶዘር ከሚቆፈሩ ትልልቅ ጉድጓዶች የሚገኘውን ውሀ በኤሌክትሪክ ሞተር እየገፉ ለሽያጭ ማቅረብ ይቻላል ። ግድብ ካስፈለገም ደግሞ በአንድት ግድብ ብቻ የውሀ ሽያጩን ስራ መጀመር ይቻላል /ግድብ ቋሚ ንብረት ስለሆነ ከአንዱ ግድብ የሚገኘው ገንዘብ ሌላ ግድብ እየወለደ እየተባዛ ይሄዳል/ ። እናም ከነኝህ በዶዘር ከሚቆፈሩ ትልልቅ ጉድጓዶች ወይም ከግድቦች የሚገኘውን ውሀ በኤሌክትሪክ ሞተር በመግፋት የውሀ ሽያጭ /ታክስ/ ስራውን መጀመር ይቻላል ። ውሀውን ለገበሬዎች በጣም በውድ ዋጋ ማቅረብ ይቻላል፤ ምክንያቱም የውሀ ታክሱ የሚቆረጠው ገበሬዎቹ ውሀውን ተጠቅመው

ያመረቱት ምርት ብቻ ተገምግሞ ነው፤ ውህውን ቢጠቀሙም ምርት ከቀነሰባቸው የውሀ ታክሱም በዚያው መጠን ይቀንስላቸዋል ማለት ነው/ ፡፡ ገበሬዎቹ በሁለት ጊዜ ወርዊ የውሀ ታክስ ክፍያ ብቻ አንድ ዙር ያመርቱበታል፣ /በሁለት ወር የክረምት ዝናብ አንድ ዙር እንደሚያመርቱት ሁሉ፣ በሁለት ወር ወርሀዊ የውሀ ክፍያ ብቻ አንድ ዙር ያመርታሉ ማለት ነው/፣ አንድ ማሳ ደግሞ በወር 5 ጊዜ፣ በአጠቃላይ በ2 ወር 9 ጊዜ አካባቢ ውሀ ቢጠጣ ይበቃዋል፣ ቋሚ ተክል /ቡና፣ ሙዝ፣ አቮካዶ ወዘተ/ ደግሞ ከሆነ ስሩን ፅሀይ ስለማያገኘው በወር 2 ጊዜ ብቻ ውሀ ቢጠጣ ይበቃዋል ፡፡ መንግስት እስከሚያዋጣው ድረስ የፈለገውን ያህል የውሀውን የታክስ ዋጋ መጨመር ይችላል፤ ምክንያቱም ገበሬዎቹ ውሀውን በቀጥታ ወደ ገንዘብ ስለሚቀይሩትና ታክሱም የሚቆረጠው ካመረቱት ምርት ላይ ብቻ ስለሆነ በማንኛውም ውድ ዋጋ ቢቀርብ ውሀ ለገበሬዎች ሁልጊዜ ርካሽ ነው ማለት ነው ፡፡

ይህን በጉድጓዶች ውሀ የመያዝ ስራ የኢትዮጵያ መንግስት ጀምሮት የነበረ ቢሆንም ጉድጓዶቹ በሰው ጉልበት የሚቆፈሩ ትንንሽ ጉድጓዶች ስለነበሩ ውሀውን እራሱ ጉድጓዱ ስለሚመጠው ግልጋሎት ሳይሰጥ ይሰርግ ነበር /በዶዘር የሚቆፈሩ ሰፋፊ ጉድጓዶች ከሆኑ ግን ይህ ችግር ሊፈጠር አይችልም/ ፡፡

ውሀን ለገበሬዎች መሸጥ ማለት በቀጥተኛው /በአቋራጩ/ መንገድ ወደ ብልፅግና መሄድ ማለት ነው ፡፡ ውሀ በቀጥታ ወደ ገንዘብ የሚቀየር የተፈጥሮ ሀብት ነው

/ውሀውን ገበሬዎቹ በቀጥታ ወደ ገንዘብ ይቀይሩታል/ ፡፡ ውሀ ለገበሬዎች መሸጥ ማለት በአንድ ድንጋይ 10 ወፍ መምታት ማለት ነው /ከዝናብ ጭንቀት ይገላግላል፣ የበለፀገ ገበሬ ይፈጠራል፣ ባለሀብቶች መሬት ከገበሬው እየተከራዩ ወደ ምርት ይገባሉ /እንደ ቆቃ ሸንኩርት/፣ የከተማ ስራ አጥ ወጣቶች እየተደራጁ በአቅራቢያቸው ካሉ ገበሬዎች መሬት ለ2ወር እየተከራዩ ማምረት ይችላሉ፣ ውሀ አቅራቢው ህዝብ ይቀጠርበታል፣ መንግስት አስተማማኝ የውሀ ታክስ ከሰፊው ገበሬ ይሰበስባል፣ ገበያ ላይ ምግብና የደለበ ከብት በርካሽ ይቀርባል፣ ሀገሪቱ በዛፍ ስለምትሸፈን ዝናብ አይቋረጥም …ወዘተ ፡፡ ይህንን የውሀ ሽያጭ/ታክስ/ ስራ ለማስፈፀም ጉድጓዶቹ ከተቆፈሩ በኋላ አሁን ካሉት የቀበሌ ግብርና ሰራተኞች ላይ ጥቂት ሰዎችን ብቻ መጨመር በቂ ነው ፡፡

በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አስተማማኝ የውሀ ሀብት ያላቸው ሀገራት በ2 እና በ3 ኪሎ ሜትር እርቀት በዶዘር የሚቆፈሩ ሰፋፊ ጉድጓዶችን ቢያስቀምጡለት እራሱ ገበሬው ስልት ፈጥሮ የማያቋርጥ ምርት ያመርትባቸው ነበር /ለምሳሌ ያህል እዚያ ምድረበዳ የአፋር መሬት ላይ በ2 እና በ3 ኪሎ ሜትር እርቀት ውስጥ በዶዘር የተቆፈሩ ሰፋፊ ጉድጓዶችን ብናስቀምጥበት እንዴት ገበሬዎቹ ውሀውን እንደሚየጠቀሙበትና እንደት ምድሩን ወደ ገነት እንደሚቀይሩት እናየው ነበር/ ። የቆቃ ገበሬዎች የውሀ መግፊያ ሞትም /water pumpም/ ኢሌክትሪክም አይቀርብላቸውም ነገር ግን መሬቱ ጠቧቸው እንጂ ቆቃ ውስጥ በሸንኩርትና በቲማቲም ያልተሸፈነ መሬት አይገኝም ። እናም ሞተር ባናቀርብላቸውም ጉድጓዱን ካስቀመጥንላቸው እራሳቸው ገበሬዎቹ ስልት ፈጥረው ውሀውን የማያቋርጥ ምርት ያመርቱበታል ማለት ነው ። እናም የአፍሪካም መንግስታት ውሀን ብቻ በመጠቀም ሀገራቱን ከአጠቃላይ ችግሮቻቸው መገላገል ይችሉ ነበር ።ነገር ግን የአፍሪካ መንግስታት፣ አድካሚውንና ተስፋ አስቆራጩን ዘወርዋራውን የብልፅግና መንገድ ነው የሚመርጡት ። የአፍሪካ መንግስታት ይህ በእጃቸው ያለው ወርቅ አልታያቸው ብሎ፣ በአረብ ሀገር ነዳጅ ሲቀኑ ይስተዋላሉ ። ወደ ገንዘብ ከመቀየር አንፃር ከነዳጅ ይልቅ ውሀ ይቀላል /ጃፓንን ና አረቦቹን እናወዳድር/ ። አረብ ሀገር ውስጥ ውሀ ስለሌለ ነው፣ ሌሎች አንዳንድ ሀገሮች ግን ከርሰ ምድራቸው ውስጥ ነዳጅ እያለ አይጠቀሙትም አስቀምጠውታል /አሜሪካ/፣ ውሀቸውን ብቻ ተጠቅመው ነው ከተፈጥሮ ጥገኝነት ነፃ የወጡት ።

እናም የአፍሪካ መንግስታት ሀገራቸው ውስጥ ሀብት ሞልቶ /ውሀ/ና ገኸ ሞልቶ /ገበሬ/፣ ህዝባቸው ከተፈጥሮ እየጠበቀ ሲማቅቅ ይኖራል፣ መንግስታቸውም ተፈጥሮ ያፈራችውን ከህዝቡ እየተቀራመተ በሚያገኘው ደካማ ሀገራዊ ገቢ ሲልፈሰፈስ ይኖራል ። ከተፈጥሮ ጥገኝነት ነፃ መውጣት የሚቻለው በሦስት መንገዶች ብቻ ነው ። እነሱም አንደኛ ለገበሬ ውሀ በመሸጥ፣ ሁለተኛ በማኑፋክቸሪንግ /ኢንዱስትሪ/ና ሦስተኛ ሰፋፊ እርሻዎችን በማቋቋም ናቸው ። ሁለቱ /ውሀ ሽያጭና ማኑፋክቸሪንግ/ ሊደጋገፉና ሊያያዙ ይችላሉ ። ከነዚህ ከሦስቱ መንገዶች ውጭ ግን ከተፈጥሮ ተፅእኖ ነፃ መውጣት አይቻልም ። የአፍሪካ መንግስታት ግን ከሦስቱም አማራጮች ውጭ ናቸው ።

ሌላ አፍሪካ ዉስጥ የሚስተዋለዉ ችግር፣ የሀገራቱ አካባቢዎች ጫፍ እስከ ጫፍ አንድ አይነት መሆን ነዉ ። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ክልሎች አንድ አይነት ናቸው ። በአንድ ክልል ውስጥ ጥሩ ስራ ቢሰራ ሁሉም የሀገሪቱ ህዝቦች የዚህ ስራ ተጠቃሚ መሆናቸዉ አይቀርም ። ሰዎች በስደት ወደ አሜሪካና አዉሮፓ የሚጓዙት አሜሪካና አዉሮፓ ዉስጥ የተሰራዉን ልማት ተጠቃሚ ለመሆን ነዉ ። አንደኛዉ ክልል የተሻለ ስራ ሰርቶ ቢቀየር ኖሮ ለሁላችንም ይበቃን ነበር /አሜሪካ የቻለችውን ጉድ እንይ እስኪ፣ ከ54ቱም የአፍሪካ ሀገሮች ከእያንዳንዳቸው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ፣ ካላቲን፣ ከእሲያ፣ ከአረብ፣ ከአውሮፓ ወዘተ/ ። ስለዚህ አንድ ክልል ውስጥ ከተሰራ እንኳን ለእኛ ለአፍሪካም ይበቃል ማለት ነው ። እኛም አረብ ሀገርና አዉሮፓ እንሄዳለን እያልን ባህር እየገባን አናልቅም ነበር ማለት ነው፣ እዚሁ አገር ዉስጥ እየተንቀሳቀስን መጠቀም እንችል ነበር፣ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮችም ወደ እዚሁ ክልል ይጎርፉ ነበር /አሁን አሁን በዉጭ ሀገር ሚዲያዎች ላይ የኢትዮጵያዊያን የስደት ዜና ቢቀንስም ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ መሰደድ ቆሟል ማለት ግን አይደለም/ ። እናም ዋናው መሰራቱ ነው ማለት ነው፣ የትም ይሰራ፣ ባህር ማዶ አሻግሮ ከማየት ይልቅ እዚሁ እየተንቀሳቀሱ መጠቀም ይቻል ነበር ። ስልጣኔ ደግሞ በፍጥነት የሚሰራጭ /diffuse/ የሚያደርግ ነገር ነው፤ አንድ ክልል ቢቀየር /ቢበለፅግ/ ሁሉም ክልሎች ሲቀየሩ ጊዜ አይወስድባቸውም ነበር ። አንዱ ክልል የተሻለ ስራ ሰርቶ ቢቀየር ኖሮ እዛ ክልል ውስጥ መወዳደር ያቃታቸው ባለሀብቶች ሌሎቹን ክልሎች ይቀይሯቸዋል፣ የሌሎች ክልሎች መሪዎችም ዝም ብለው አያዩም፣ የሌሎች ክልል ህዝቦችም ለምን እኛ ወደ ኋላ ቀረን ብለዉ መጠየቃቸዉ ስለማይቀር፣ የሁሉም ክልል መሪዎች አማራጭ መስራት ብቻ ይሆናል ። ልምዱ ደግሞ እዛኛው ክልል ላይ ስላለ ብልፅግናው በአጭር ጊዜ ይዳረስ ነበር ። በተቃራኒው ሁሉም ክልሎች አንድ አይነት ከሆኑ ግን ባለሀብቶቹ አንድ አይነት ልምድና አቅም ያላቸው ይሆናሉ፣ አንድ አይነት ስለሆኑ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል የሚሸጋገር ልምድ /እውቀት/ና ሀብት አይኖርም፣ ህዝቡ ሀገር ውስጥ እየተንቀሳቀሰ አማራጮችን የመፈለግ ልምድ አይኖረውም፣ በክልሎች መካከል የልማት ፉክክር ስለማይኖር መንግስትን እንዲዘናጋ ያደርገዋል ።ሁሉም ክልሎች አንድ አይነት ከሆኑ፣ እኛ ለምን ወደ ኋላ ቀረን የሚል መንግስትን ወደ ልማት የሚገፋ ጥያቄ አይፈጠርም፤ ይህ ደግሞ መንግስትን ከነአካቴዉ ልማትን እንዲረሳ ሊያደርገዉ ይችላል ።

ይህን በርካታ የአፍሪካ መንግስታት እንደ ስልት ይጠቀሙታል ። ሀገራቸውን ጫፍ እስከ ጫፍ አንድ አይነት አድርገዉ ብቻ ነዉ ተኝተዉ /ልማት ሳይሰሩ/ መኖር የሚችሉት ። መሪዎቹ ከመተኛት /ከልማት መቆም/ የሚያገኙት ጥቅም ባይታወቅም፣ የአፍሪካ ሀገሮች በጦርነት እየወደሙ ደቀው የቀሩት ግን በዚሁ በልማት መቆም ምክንያት ነዉ ።

ጦርነት ሰው ሰራሽ አይደለም፤ ጦርነት ተፈጥሮዊ (natural) ነው ። ጦርነት ስላልፈለከው የሚቀርና ስለፈለከው የምታመጣው አይደለም ። ጦርነት ከህዝቡ የችግር አኗኗር የሚወለድ ሌላ የስራ ዘርፍ ነው ። ህዝቡ መኖር ከቻለ /ህይወቱን መምራት ከቻለ) ሞት ያለበትን ስራ አይመርጥም፣ እናም ጦርነት አይኖርም ። ህዝቡ ህይወቱን መምራት ካልቻለና ችግር ውስጥ ከሆነ ግን ጦርነት እንደ አንድ ህይወት የመምሪያ /የስራ/ አማራጭ ሆኖ ይነሳል ። ስለዚህ ጦርነት ማለት ልማት በቆመበት ወቅት የልማት ስራን ተክቶ የሚመጣ ሌላ ህይወትን የመምሪያ የመጨረሻ የስራ አማራጭ ነው ማለት ነው ።

አንዳንድ ነገሩ ያልገባቸው ሰዎች በአንዳንድ የመንግስት ህገመንግስቶች ላይ ሲከራከሩ ይስተዋላሉ፤ ለምሳሌ የመናገርና የመፃፍ መብቶች ላይ ይከራከራሉ ። እነኝህም መብቶች ሰው ሰራሽ አይደሉም፣ ፍጡር ናቸው/natural ናቸው/ ። እነዚህ መብቶች መንግስት ስለፈለገ ሳይሆን ልማት ሲኖር የሚመጡና ልማት ሲጠፉ የሚጠፉ ነገሮች ናቸው ። የአፍሪካ መንግስታት የመናገርና የመፃፍ መብቶችን የሚከለክሉት ለምንድን ነው? ነው ጥያቄው ። ጦርነት እንዳይነሳባቸው ነው? ወይስ ህዝቡን ለማሳቀቅ ፈልገው ነው? ይህ ነው ጥያቄው ። እናም የአፍሪካ መንግስታት ወደው አይደለም እነኝህን መብቶች የሚከለክሉት፣ ህዝቡ ለጦርነት ዝግጁ ነው ማለት ነው፣ ህዝቡ ሰበብ ነው የሚፈልገው ማለት ነው ። ስለዚህ ያንተ መናገር ለውጥ ያመጣል ማለት ነው /ህዝቡ ቤንዚን ነው ማለት ነው፣ እናም የአንተ መናገር ክብሪት ሊሆን ይችላል ማለት ነው/ ። ህዝቡ ለምን ቤንዚን ሆነ ብለን ያልን እንደሆነ፣ ወደዚያው ልማት ወደሚባለው ነገር ይወስደናል ። ልማት ካለ ህዝቡ የተደላደለ ህይወትና ተስፋ ስለሚኖረው ጦርነት ስጋት አይሆንም፣ ጦርነት ስጋት ካልሆነ ደግሞ መንግስት እነኝህን መብቶች የማፈን ትግል ውስጥ መግባት አያስፈልገውም ማለት ነው ። ስለዚህ ልማት ካለ እነዚህ መብቶች አሉ ማለት ነው ። ዋናው የአፍሪካና የአውሮፓ መሪዎችም ልዩነት ያለውም እዚህ ላይ ነው ። የአፍሪካ መሪዎች ሰላምንና ዲሞክራሲን ለማምጣት በርካታ

ትርጉም የሌላቸው ዝባዝንኪ ጥረቶችን እያደረጉ ጊዜቸውን ያጠፋሉ፤ ለምሳሌ ህገመንግስት በማስተካከል፣ ህገመንግስቱ ውስጥ ያሉትን ነገሮች በመቀያየር፣ አዳዲስ ህጎችን በማውጣት ወዘተ አይነት ትርጉም የለሽና ለውጥ ሊያመጡ በፍፁም የማይችሉ ዝባዝንኪ ነገሮች ላይ ጊዜቸውን ያጠፋሉ ። ለአውሮፓ መሪዎች ደግሞ አለም ላይ ያሉ ሁሉም ጥሩ ነገሮች ከአንድ ዛፍ ብቻ የሚለቀሙ ፍሬዎች ናቸው፣ ዛፉ ልማት ነው፤ ዛፉ ከሌለ ፍሬ ማግኘት አይቻልም ። እናም ሰላምም ሆነ ድሞክራሲ፣ ልማት ከሌለ የሉም ። ስለዚህ መንቀዣቀዥ አያስፈልግም በቃ ልማት መስራት ብቻ በቂ ነው ።

ስለዚህ የሰው ልጆች የሁሉም ችግሮቻቸው መፍትሄ ልማት ብቻ ነው ማለት ነው ። በአፍሪካ መሪዎች ውስጥ ይህ ግንዛቤ ባለመኖሩ ምክንያት የአፍሪካ ምድር ልማት የሚሰራበት ሳይሆን የጦር መሳሪያ ገዥና የተኩስ ምድር ሆኖ ቀጥሏል ።

አፍሪካ ዉስጥ ሌሎች የልማት መቆም የሚወልዳቸዉ እጅግ ከባባድና ውስብስብ ችግሮች አሉ ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ የዉጭ ሀይሎች ለመንግስት በሚኖራቸዉ የንቀት አመለካከትና በቀላሉ የህዝቡን ልብ ስለሚያገኙት በድፍረት እጃቸዉን በረጅሙ እያስገቡ ሀገራቱን እየበጠበጡ አንዳንድ ጥቅሞቻቸዉን ያስጠብቃሉ ።

የተሻለ ልማት ያላቸዉ ሀገራት ከሌሎች ደሐ ሀገሮች ያላቸዉን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲሉ የወቅቱን ዘመናዊ /ስዉር/ ጦርነትን ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ ማለትም ዘመቻና መሰዋዕትነት ሳያስፈልጋቸዉ የደሐ ሀገር ህዝቦችን እርስ በርስ እያጋጩ፣ ሀገራቱን እንደ ደኸዩ /እንደደከሙ/ እንዲቀጥሉ ያደርጓቸዋል ። በዚህ በስውሩ የዉጊያ ስልት ሀገራቱን ሁል ጊዜ ከእነሱ በታች ሆነዉ እንዲቀጥሉ ማድረግ ይችላሉ ።

ይህ ጦርነት ከቀጥተኛዉ ጦርነት አንፃር ሲታይ ብዙ ገንዘብ የማይፈልግ፣ በአመራር ብቃትና በጭንቅላት መበላለጥ ብቻ የሚካሄድ ጦርነት ነዉ ። በቀጥተኛ ጦርነት ጊዜ፣ በአንድ ቀን /በአንድ ሰዓት/ ጦርነት ብቻ የሚረጨዉ የከባድ መሳሪያ ጥይት መግዣ ገንዘብ፣ ለዚህኛዉ/ለስዉሩ/ ጦርነት አመታትን ያዋጋል ፡ የአንድ ጀት መግዣ ገንዘብ ለዚህኛዉ ጦርነት በርካታ ወራትን ያዋጋል ። እናም ማንም በትንሽ በጀት ሊዋጋው ይችላል ማለት ነው ። ስለዚህ ለደሐ ሀገራትም ከቻሉበት /ብስለቱ ካላቸዉ/ ስዉሩ ጦርነት ይሻላቸዋል

/advantage ነዉ/ ማለት ነው ። እንዳዉም ደሐ መንግስታት ይህን የጦርነት ስልት ሊጠቀሙበት ይገባ ነበር ። የትኛዋንም ስጋት የሆነች ሀገር በዚህ ስልት ቀድሞ በማዳከም፣ አሽቆልቁላ ከስር እንዲትሆን ማድረግ ይቻላል ። ችግሩ ግን የደሐ ሀገር መንግስታት ብስለቱ አይኖራቸዉም፣ ልዩነቱም ይኸው የብስለት ጉዳይ ነው ።

ባስተሳሰብ የተሻልን ነን የሚሉት ሀገራት ይህ ጦርነት ለነሱም አደገኛ መሆኑንና ማንም በትንሽ በጀት ሊዋጋዉ እንደሚችል እያወቁ በድፍረት ጦርነቱን የሚጀምሩበት ምክንያት ለመንግስት በሚኖራቸዉ ንቀት ነዉ ። ይህኛዉ መንግስት የእነሱን ሀገር አጠቃላይ የእርስ በርስ ፖለቲካዊ ችግር አጥንቶና እጁን የእርስ በርስ ችግሮቻቸዉ ዉስጥ አስገብቶ የደከመዉን ቡድን አገዝ /ደገፍ/ እያደረገ እነሱንም እርስ በርሳቸዉ የማውደምና የማድከም አስተሳሰቡ /ብስለቱ/ እንደማይኖረዉ እርግጠኛ ስለሚሆኑ ነዉ ። የደሀ ሀገር መንግስታት ተከላካይ ብቻ እንደሚሆኑ ያውቁታል ። የደሐ ሀገር መንግስታት ተከላካይ ብቻ ስለሚሆኑ እነዚያኞቹ እንደተረጋጉ ይቀጥላሉ ። እንደተረጋጉ ቀጠሉ ማለት ደግሞ እነሱ እየፈረጠሙ እነዚህ እየደከሙ ሄዱ ማለት ነው፤ ስለዚህ የግድ የጦርነቱ አሸናፊ እነሱ ይሆናሉ ማለት ነው ።

ስዉሩን ጦርነት ያሸነፈ ቀጥተኛዉን ጦርነትም ማሸነፉ አይቀርም ። ምክንያቱም ስዉሩ ጦርነት ሀገርንም ሆነ መንግስትን ፍፁም የሚያዳክም፣ የሚያሽመደምድና ሽባ የሚያደርግ ስለሆነ ቀጥተኛዉን ጦርነት በርትቶ መዋጋት አይቻልም ። በዚያ ላይ የቀጥተኛዉ ጦርነት አሸናፊነት በገንዘብ ላይ የተመሰረተ ነዉ ። ገንዘቡ ደግሞ ከስዉሩ ጦርነት መሸናነፍ ጋር ይያያዛል ። እርስ በርስ ካወደምካቸዉና ካደከምካቸዉ ገንዘብ አይኖራቸዉም ። ስለዚህ የመሸናነፉ ቁልፍ ስዉሩ ጦርነት ነዉ ማለት ነዉ ። የደሐ ሀገር መንግስታት ተከላካይ ብቻ ስለሚሆኑ እነዚያኞቹ ተረጋግተው ስስ ብልታቸውን እየፈለጉ ይመቷቸዋል ። እነዚያኞቹ እንደተረጋጉ እየለሙና እየጠጠሩ ሲሄዱ እነዚህ ወደ ተቃራኒው /ወደ ታች/ ሲጓዙ ክፍተቱ /ልዩነቱ/ ከመሸናነፍም የከፋ ይሆናል ። ስለዚህ ዋናዉ ነገር መከላከሉ ብቻ ሳይሆን እጅን እነዚያኞቹ ውስጥ በማስገባት በዚሁ ስልት እነሱንም ማዳከምና የሀገር ዉስጥ ልማትን ማፋጠን ነዉ ማለት ነው ።

የሀገር ውስጥ ልማት ሲፋጠን፣ ገንዘብ ይንሸራሸራል፣ ፕሮጀክቶች በፍጥነት ያልቃሉ፣ ፕሮጀክቶች በፍጥነት ሲያልቁ ከመዘዛቸውም በፍጥነት

መውጣት ይቻላል ።ፕሮጀክቶች በፍጥነት ሲያልቁ ተጨማሪ ጉልበት /ሀብትና ልምድ/ ይሆናሉ፤ ልማት ሲፋጠን መሰረተ ልማቱም ስለሚጨምር ሀገሪቱ ውስጥ የሚመነጨው ገንዘብ /ገባር/ ይጨምራል ። ልማት ሲፋጠን ሀገሪቱ የሚያስፈልጓትን እቃዎች ራሷ ማምረት ስለምትጀምር ወጭዎቿ ይቀንሳሉ ። የሀገር ውስጥ ልማት ሲፋጠን ህዝቡ ይንቀሳቀሳል፣ ሀብት ይንሸራሸራል፣ በርካታ ባለሀብቶች ይፈጠራሉ /ይቀጥራሉ/ ። የሀገር ውስጥ ልማት ሲፋጠን ልምድ ያላቸው በርካታ ግዙፍ ባለሀብቶች ስለሚፈጠሩ ወደ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች እየሄዱ ስራዎችን /ለምሳሌ መንገድ/ መስራት ይጀምራሉ፣ በሁሉም መስክ አፍሪካ ውስጥ ያለውን ስራ እየተቆጣጠሩት ይመጣሉ ። በዚህ መልኩ የበለፀገችና የምትፈራ ጥቁር ሀገር መፍጠር ይቻላል ።

ሁለቱም ስልቶች ማለትም እነዚያኞቹ እንዳይረጋጉ ማድረግና የሀገር ዉስጥ ልማትን ማፍጠን አንድ ላይ ከሄዱ፣ እነዚያኞቹ ወደ ታች ሲጓዙና እነዚህኛዎቹ ወደ ላይ ሲጓዙ አጠቃላይ ክፍተቱ /ልዩነቱ/ የሁለቱም ጉዞዎች ድምር ስለሚሆን ጦርነቱን በሰፊ ክፍተት/ልዩነት/ ማሸነፍ ይቻላል ።

እናም የአፍሪካ መንግስታት ባጠቃላይ ስለህዝባቸዉ ፍላጎት ያላቸዉን ግንዛቤ ማስተካከል ይኖርባቸዋል ማለት ነው ። ህዝብ ማለት እዉነት ማለት ነዉ፤ አንድ ሰዉ ሁለት ሰዉ ሊሳሳት ይችላል እንጂ ህዝብ ሊሳሳት አይችልም ። ስለዚህ መፍትሄዉ ልማትና የልማት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ብቻ ነው ማለት ነው ።

ነገር ግን መንግስት እንደተቋሙ ልምድ ሊሳሳት ይችላል፤ ህዝቦች መንግስት በመቀየር ሱስ የተጠመዱ ይመስለዋል ። ህዝቦች በተፈጥሯቸዉ መንግስት የመቀየር ሱስ የለባቸዉም ። አዲስ ጅብ ሳይሆን ልማት ብቻ ነዉ የሚፈልጉት ። እንደ ምሳሌ የቻይናን ህዝብ ማየት እንችላለን ፡ - ከእነ አሜሪካም በበለጠ ሁኔታ በአለም ላይ ኮሽ እንኳን የሚል የፖለቲካ ተቃዎሞ የሌለባት ሀገር ብትኖር ቻይና ነች ። ቻይና እየተመራች ያለችዉ ደግሞ በአንድ ፓርቲ ብቻ ነዉ ። ይህ ፓርቲ ግን ቻይናን ሙሉ በሙሉ ቀይሮ፣ ኢኮኖሚዋን በአለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ እንዲቀመጥ አድርጎታል ። እንደ ግስጋሴቸዉ ከሆነ ቻይና በአስርት አመታት አካባቢ የአለምን የአጠቃላይ ገቢ /GDP/ የመሪነት ቦታ ትረከባለች ። እናም የቻይና ህዝቦች ይህን ፓርቲ ለመቀየር የሞከሩበት

ሰላማዊይም ሆነ ህገወጥ እንቅስቃሴ የለም ። ስለዚህ ህዝብ ልማት እንጂ ፓርቲ የመቀየር ፍላጎት ሊኖረዉ አይችልም ማለት ነዉ ።

የአዉሮፓ መሪዎች ስልጣን በምርጫ የሚለቁት ህዝቡን ፈርተዉ ወይ ለህዝቡ አዝነዉ አይደለም ። ለራሳቸዉ የህግን የበላይነትን ለመጠቀም ሲሉ ነዉ ። በሚደክሙባት ሀገራቸዉ ዉስጥ ቋሚ ንብረት እንዲኖራቸዉ ሲሉ ነዉ ህጉን ከላይ የሚያደርጉት ። ለምሳሌ የአሜሪካዉ ፕሬዝደንት ተወልዶ ባደገበትና በሚመራዉ ሀገሩ ዉስጥ የራሱ የሆነ ማንም የማይነካዉ ቤትና ንብረት አለዉ ። የአፍሪካ ፕረዚዳንቶችም ሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ግን ተወልደዉ ባደጉበትና በሚመሩት ሀገራቸዉ ዉስጥ የራሴ የሚሉት ቋሚ ንብረት አይኖራቸዉም ። ስልጣን እስከ ያዙ ድረስ ሁሉም ነገር የእነሱ ነዉ፤ ስልጣን ሲለቁ ግን ምንም ነገር የላቸዉም ። ይህ የሚሆነዉ ደግሞ ስልጣናቸዉን የሚያስለቅቃቸዉ ህግ ሳይሆን ሌላ ጉልበተኛ ስለሚሆን ነዉ ። እናም በሚደክሙባት ሀገራቸዉ ዉስጥ ባዶነት እየተሰማቸዉ ይኖራሉ ።

ጉልበተኛ እስኪፈጠር ድረስ ስልጣን ይዞ መኖርና ጉልበተኛ ሲመጣ ሁሉንም ነገር ለቆ መጥፋት፣ ህጉን ከጉልበተኞች በታች እንዲሆን ያደርገዋል ። ለዚህ መፍትሄዉ ደግሞ ስልጣን አስለቃቂዉ ጉልበተኛ እንዳይሆን ማድረግ ነዉ፤ ማለትም ስልጣን የሚያስለቅቅ ጉልበተኛ እስኪ ፈጠር ድረስ ስልጣን ይዞ የመጠበቅ ልምድን ማጥፋት፤ ይህ ማለት ደግሞ የመሪዎቹን የስልጣን ቆይታ በጊዜ መገደብ ማለት ነዉ ። የአመራሮቹ የስልጣን ጊዜ የተገደበ/fixed/ ከሆነ ከህግ በላይ የሆነ ጉልበተኛ ሳያስፈልግ ህጉ ራሱ ስልጣን ያስለቅቃቸዋል ። እናም ከህግ በላይ የሚሆን ሰዉ ሊመጣ አይችልም ማለት ነው፤ ስለዚህ መሪዎችም በሚደክሙባት ሀገራቸዉ ዉስጥ ማንም የማይነካዉ ህጋዊ ቋሚ ንብረት ይኖራቸዋል ።

ስለዚህ መሪዎች በምርጫ ስልጣን የሚለቁት ለራሳቸዉ ፈልገዉት እንጂ ህዝብ ልማት እስከ ተሰራለት ድረስ መሪ የመቀየር ፍላጎት ኖሮት አያዉቅም ። እናም የአፍሪካ መሪዎች የሁሉም ነገር መፍትሄ ልማት መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል ። ጥቁር ኢትዮጵያም የጀመረችዉን ልማት አጠናክራ መቀጠል ይኖርባታል ።

እንግዲህ የወሎ ነገስታት እንዳስቀመጧት የነበረችዉን ኢትዮጵያን ማንቀሳቀስ የጀመረዉ ኢህአዴግ ልማቱን ይበልጥ አጠናክሮ በመቀጠል፣ ከወሎ መሪዎች የተሻለ ለዉጥ ማምጣት ይኖርበታል ። የወሎ ነገስታት

ከአፍሪካ መሪዎች የማይጠበቅ የተሻለ ስራ ሰርተው ኢትዮጵያን አሁን ከደረሰችበት ደረጃ ላይ አድርሰዋታል ። ያ የዋህና ገር የወሎ ህዝብ ወልዶ ባሳደጋት ኢትዮጵያ ውስጥ ስንኖር በሀብት በቴክኖሎጂና በስልጣኔ ብንበለጥም፣ ነፃነታችና ክብራች ግን እንደነ እንግሊዝና ሩሲያ ህዝቦች እኩል በአለም በአንደኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ። እጅግ ከባባድ መሰዋዕትነቶችን እየከፈሉ ኢትዮጵያ አንዷ የአለም የነፃነት ተምሳሌት፣ የአፍሪካ የታሪክ፣ የድልና የቅርሶች ማእከል እንዲትሆን አድርገዋታል ።

የወሎ መሪነት "ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል መፈክር በመቋረጡ ምክንያት እጅግ ረጅም የነበረዉ የወሎ አገዛዝ፣ አፄ ኃይለስላሴ ላይ ሊቆም ችሏል ። የዚች መፀሀፍ ትኩረትም የወሎ ነገስታት ላይ ስለሆነና የወሎ ነገስታት መሪነት ደግሞ አፄ ኃይለስላሴ ላይ "ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚለው መፈክር ስላበቃ፣ እኔም ፅሁፌን ለማጠናቀቅ እገደዳለሁ ። በሌላ መፀሀፍ እንደምንገናኝ ተስፋ እያደረኩኝ፣ ይህኛዉ መፅሀፌ ግን በዚሁ ተፈፀመ ።

ልማት

ልማት

ልማት

ልማት

ልማት ልማት ልማት ልማት ልማት ልማት

ልማት

ልማት

ልማት

ልማት

ልማት

ልማት

ልማት

ለአፍሪካ

ተፈፀመ

ዋናው እግዚአብሔር እራሱ ወደ ምድር ወርዶ በሰጠን ብቸኛ ነገር በታቦቱ አምናለሁ /የሰው ልጆች እስከ አሁን ድረስ ከዋናው እግዚአብሔር /ከአብ/ እጅ ላይ የወሰዱት ብቸኛ ነገር ታቦቱን ነው/ ። ስለታቦቱ ማስቀመጫ አሰራርም ዋናው እግዚአብሔር /አብ/ እራሱ አስተምሮናል ። ቀናተኛው አምላክ በሌላ በምንም ነገር እንዳናመልክ ከልክሎ ታቦቱን ግን ፈቅዶልናል /እራሱ በእጁ ሰጥቶናል/ ። ስለዚህ በመፅሀፍ ቅዱስና በቁራን የምናምን ከሆነ የሙሴን /የሙሳን/ ታቦት በከተል የግድ ነው!!! ህግ የሻረ የለም ።

## ስብሐት ለእግዚአብሔር

# ዋና ዋና ዋቢ መጻህፍት

1. ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ፣ ንጉሰ ነገስት ዘ ኢትዮጵያ፤ በጸሓፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ
2. የኢትዮጵያ የ5ሺ አመት ታሪክ፣ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ፤ በጋዜጠኛ ፍሰሐ ያዜ
3. የኢትጵያ ታሪክ፣ ከመጀመሪያ እስከ አሁኑ ዘመን፤ በአንድርዜይ ባርትኒስኪና ዮዓና ማንቴል-ኒየችኮ፤ ትርጉም በአለማየሁ አበበ
4. የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ፤ በአለቃ ታዬ
5. አባ ኮስትር በላይ ዘለቀ፤ በአበራ ጀምበሬ

አስተያየትዎን ፡ -

tesfayed@gmail.com

only text 0913-117766

0906-477004

0904-783232